# ጨለማም አላሸነፈውም

## የዮሐንስ ወንጌል ማብራሪያ



መልሳቸው መስፍን (ዶ/ር)

# «ጨለማም አላሸነፈውም»

## የዮሐንስ ወንጌል ማብራሪያ

መልሳቸው መስፍን (ዶ/ር)

የቅጂ መብት - © መልሳቸው መስፍን - 1998
© Mellsachew Mesfin - 2006

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::
ይህን መጽሐፍ ለንግድ ወይም ትርፍ ለሚያስገኝ ሥራ በሙሉም ሆነ በከፊል አባዝቶ መጠቀም አይፈቀድም:: ሆኖም በደራሲው ፈቃድ ለማስተማር አገልግሎት በጥቂትም ሆነ በብዙ አባዝቶ በነጻ ማሰራጨትና መጠቀም ይበረታታል::


በክፍሉ ካልተጠቀሰ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1962 ከታተመው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው::


የመጀመሪያ እትም - 1998 ዓ.ም.
First printing - 2006



አስተያየት ቢኖርዎት፡-
ፖ. ሣ. ቁ. 31716
አዲስ አበባ

Email: onebmtm@yahoo.com




# አበርክቶ

**ይህ መጽሐፍ**

በራሱ ሕይወት ላለው፤
መንፈስ ለሆነው፤
በመንፈስና በእውነት ለሚመለከው፤
ዓለሙን ሁሉ እንዲሁ ለወደደው፤
በኃጢአታችን እንዳንጠፋ አንድያ ልጁን ለላከው፤
ከሰማይ የሆነውን እውነተኛ እንጀራ ለሰጠን፤
ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ላስነሣው፤
በልጁ ለሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ለሚሰጠው፤
አጽናኙን የእውነት መንፈስ፤ መንፈስ ቅዱስን ለላከልን፤
የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፤ የእኛም አባት ለሆነው፤
ክብር ሁሉ ለሚገባው፤
በሰማይ ለሚኖረው ቅዱስ፤ ጻድቅና ዘላለማዊ እምላክ፤

# ለእግዚአብሔር አብ

ክብር ይሁን::

# ማውጫ


መግቢያ ........................................ 7

ስለ ዮሐንስ ወንጌል አጠቃላይ መግቢያ ........................ 9

ምዕራፍ 1 ........................................ 19
ምዕራፍ 2 ........................................ 41
ምዕራፍ 3 ........................................ 52
ምዕራፍ 4 ........................................ 64
ምዕራፍ 5 ........................................ 80

ምዕራፍ 6 ........................................ 96
ምዕራፍ 7 ........................................ 111
ምዕራፍ 8 ........................................ 121
ምዕራፍ 9 ........................................ 132
ምዕራፍ 10 ........................................ 140

ምዕራፍ 11 ........................................ 150
ምዕራፍ 12 ........................................ 166
ምዕራፍ 13 ........................................ 184
ምዕራፍ 14 ........................................ 198
ምዕራፍ 15 ........................................ 214

ምዕራፍ 16 ........................................ 228
ምዕራፍ 17 ........................................ 238
ምዕራፍ 18 ........................................ 251
ምዕራፍ 19 ........................................ 263
ምዕራፍ 20 ........................................ 274
ምዕራፍ 21 ........................................ 284

# መግቢያ

እግዚአብሔር መታወቅ የሚፈልግና ራሱን የገለጠ አምላክ ነው። ራሱን በልዩ ልዩ መንገድ ባይገልጥ ኖሮ ሰው ሊያውቀው ባልቻለም ነበር፤ በምርምር ሊታወቅ አይችልምና። እግዚአብሔር ግን ከጥንት ጀምሮ ራሱን በልዩ ልዩ መንገድ ገልጧል።

እግዚአብሔር ራሱን የገለጸበት አንዱ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የሚመሰክረው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በጉልህ ከሚናገሩ መጻሕፍት አንዱ የዮሐንስ ወንጌል ነው። የዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና የዘላለም ሕይወት የሚገኘውም በእርሱ በማመን መሆኑን በግልጽና በሥርዓት የሚገልጽ መጽሐፍ ነው።

የዚህ የዮሐንስ ወንጌል ማብራሪያ አቀራረብ በየምዕራፉ በተቻለ መጠን ቁጥር በቁጥር በመሄድና ቁጥሩን ወይም ሐረጐችን አንዳንዴም ቃላትን በመውሰድ ከሌላው የመጽሐፉ ክፍሎች እንዲሁም ከጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ጋር በማዛመድ ፍቺአቸውን (ትርጉማቸውን) ማሳየትና ማብራራት ነው።

እንደ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች ሁሉ ይህን የዮሐንስ ወንጌል ማብራሪያም ለመረዳት የተሻለ ጥቅም የሚሰጠው አንባቢው መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ፤ በጐን ማብራሪያውን አብሮ ሲያገናዝብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ጽሑፎች በምንም መልኩ ያን መጽሐፍ (ወይም መጽሐፍ ቅዱስን) አይተኩልንም። የማብራሪያዎች ዋና ዓላማ በዚያ ጸሐፊ መረዳት መጠን ያ ቃል/ሐረግ ወይም ቁጥር ምን ማለት እንደሆነ ብርሃን ለመፈንጠቅና የተሻለ መረዳት ለማግኘት ማገዝ ነው። ስለሆነም ሁልጊዜም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎችና አስተማሪዎች እራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስን ደጋግመው በማንበብ ራሳቸው ከዚያው ከመጽሐፍ ቅዱስ በማጥናት ለመረዳት መሞከር በምንም ሊተካ የማይችል መሆኑን መገንዘቡ ይጠቅማል።

ይህ ማብራሪያ የተመሠረተው «ላይፍ አፕሊኬሽን ባይብል ኮሜንታሪ»[1] ከሚለው የዮሐንስ ወንጌል ማብራሪያ ላይ ሆኖ ይህ ጸሐፊ በራሱ መረዳት አገናዝቦ ለማቅረብ ሞክሮአል።

ማብራሪያን በረቂቅ ደረጃ በማየት ጠቃሚ አስተያየታቸውን የሰጡኝንና በኮምፒዩተር በመጻፍ የተባበሩትን ወገኖች ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፤ እግዚአብሔር ይባርካቸው።

የዮሐንስ ወንጌል ስለ ሕያው የእግዚአብሔር ልጅ በስፋትና በጥልቀት የሚገልጥና የሚያስረዳ በመሆኑ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ሙሉ የሆነ ነገር ለማቅረብ በሰው ዘንድ ቀላል አለመሆኑ ግልጽ ነው። ስለሆነም በበቂ ሁኔታ የተዘጋጀ ነው ለማለት ቢያዳግተኝም እግዚአብሔር በረዳኝ መጠን ይህን አጭር ማብራሪያ ለጊዜው አቅርቤአለሁ።

እግዚአብሔር ይህን ሥራ ለእርሱ ክብር፤ ለሕዝቡም መንፈሳዊ እድገትና መታነጽ ምክንያት እንዲያደርገው ከልብ እመኛለሁ።

[1] Life Education Bible Commentary (LEBC) (1993). Tyndale House Publishers,Inc. Wheaton.



# ስለ ዮሐንስ ወንጌል አጠቃላይ መግቢያ

## *ጸሐፊው*

የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ ሐዋርያው ዮሐንስ ነው። ስለ ራሱም ሲገልጽ በምዕራፍ 20፡20 እና 24 ላይ *«ኢየሱስ የሚወደው ደቀ መዝሙር»* ይላል። እንዲሁም 13፡23፣ 19፡26፣ 22፡21፣7፤20)።

ዮሐንስና ወንድሙ ያዕቆብ የዘብዴዎስ ልጆች ናቸው (ማር. 10፡35)። ዮሐንስ የያዕቆብ ታናሽ ወንድም ነው። እናታቸው ሰሎሜ ነበረች (ማቴ 27፡56-61፤ ማር 15፡40፣47)። ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስ በጠራው ጊዜ እንደ እባቱ ዘብዴዎስ አሳ አጥማጅ ነበረ (ማቴ 4፡21፤ ማር. 1፡19-20)።

ያዕቆብና ዮሐንስ የነጐድጓድ ልጆች ተብለዋል (ማር 3፡17፤ ሉቃ 9፡54)። ነጐድጓድ ጆሮን ጭው የሚያደርግ ኃይለኛ ድምጽ ነው። እንዲህ ብሎ የሰየማቸው ጌታ ኢየሱስ ነው (ማር 3፡17)። ይህም የመጮህ፣ የመባረቅ ወይም አስደንጋጭ የሆነ ባሕርያቸውን የሚገልጥ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ እነዚህ ወንድማማቾች በሉቃ 9፡52-56 እንደምናየው በሳምራውያን መንደር ባለፉ ጊዜ ሳምራውያን ስላልተቀበሉአቸው ከሰማይ እሳት ወርዶ እንዲበላቸው ጌታን ጠየቁት። እነዚህ እሳት ለመጥራት የፈለጉ ሁለቱ ወንድማማቾች በሌላ ሁኔታ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ በመንግሥቱ የክብሩ ሥፍራ እንዲሰጣቸው የጠየቁት ነበሩ (ማር 10፡35-44)።

እነዚህ የነጎድጓድ ልጆች የተባሉ አስደንጋጭ ባሕርይ የነበራቸውን ወንድማማቾች ጌታ ባሕሪያቸውን ለውጦ የእርሱን ሀሳብ የሚያገለግሉ አድርጓቸዋል። ይልቁንም ከእርሱ ጋር ቀረብ ብለው በአገልግሎት ከተባበሩት ከሦስቱ (ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ) መካከል ሁለቱ እነርሱ ነበሩ (ማር. 5፡37፣ 9፡2፣ 14፡33)።

የነጐድጓድ ልጅ የተባለው ዮሐንስ ለራሱ ከፍ ያለ ሥልጣን የሚፈልግ ሰው ነበር። ነገር ግን በኋላ «የፍቅር ሰው» በመባል ይታወቃል።

ታላቅ የሕይወት ለውጥ በዘመኑ የታየበት ደቀ መዝሙር ነው። የነጐድጓድ ልጅ ይባል የነበረው፤ የፍቅር ሐዋርያ በመባል ተጠራ።

የጌታ ኢየሱስን ደቀ መዝሙር የማድረግ መንገዱን፤ ጥበቡንና የመለወጥ ኃይሉን በዚህ ሰው ሕይወት ከሆነው እንመለከታለን። ነጐድጓድ (አስቸጋሪ) የሚባሉትን ስፍራ (ሥልጣን) ፈላጊዎችን ሳይቀር ወደ እርሱ ጠርቶ ከእርሱ ጋር ሲያኖራቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ ባሕርያቸው ተቀይሮ አገልጋዮች፣ የፍቅር ሰዎች፣ አደራ ተቀባዮች ይሆናሉ።

ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እናቱን ይኸውልሽ ልጅሽ (ዮሐ 19:26-27) ብሎ አደራ የሰጠው ለዚሁ ለዮሐንስ ነበር። ከአሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት መካከል በመጨረሻዋ ሰዓት ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በዋለበት ጊዜ በዚያ ቦታ የተገኘው ይህ ዮሐንስ ነበር።

በወጣትነት እድሜው ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር ለደቀ መዝሙርነት የተጠራው ዮሐንስ ከሐዋርያት ሁሉ በመጨረሻ እንደ ሞተ በታሪክ የሚነገርለት ሰው ነው። ያዕቆብ ከሐዋርያት መካከል መጀመሪያ ሰማዕት የሆነ ሰው ነው (የሐዋ 12÷2)። ዮሐንስ በእድሜ ዘመኑ ሁሉ ታማኝ የጌታ ደቀ መዝሙር ሆኖ የኖረ ሰው ነው። ከጅማሬው ይልቅ አጨራረሱ ያማረለት፤ የተመሰከረለት ሰው ነው።

## የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም ከተቃጠለች በኋላ ባለው ጊዜ በተለይም ከ85 እስከ 90 ዓ.ም. እንደሆነ ይገመታል። በመጽሐፉ ውስጥ የተጻፈበት ጊዜና ቦታው ግልጽ ባይሆንም ከየቤተ ክርስቲያን ታሪክ መገንዘብ የሚቻለው የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው በኤፌሶን ከተማ እንደሆነ ነው። ይህንን መጽሐፍ ሲጽፍ ዮሐንስ በእድሜው በሰማኒያዎቹ ዓመታት እንደ ነበር ይስላል።

## የተጻፈው ለማን ነው?

በመጽሐፉ ውስጥ ለማን እንደተጻፈ አልተነገረም። ሆኖም ከመልእክቱና ከአቀራረቡ ለመገንዘብ የሚቻለው የተጻፈው ለሚያምኑና ማመን ለሚፈልጉ ሁሉ ነው። እውነትን ለማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ እውነት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ያምን ዘንድ የተጻፈ



መጽሐፍ ነው። የዮሐንስ ወንጌል የሚያተኩረው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ዘመን ውስጥ በተመረጡ ጊዜያትና ሁኔታዎች ላይ ነው።

መጽሐፉ ለተጻፈላቸው የሚያስገነዝበው:-

1. ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ፤
2. ለኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት መልስ መስጠት ወይም እርሱንና ትምህርቱን በእምነት መቀበል እንደሚያስፈልግ፤
3. በእምነት የተቀበለው ሰው የዘላለም ሕይወት እንደሚያገኝ፤ ነው።

## ቁልፍ ቃላት

በመጽሐፉ ውስጥ አትኩሮት የተሰጣቸው ሃሳቦች ወይም ቃላት ቃል፣ ብርሃን፣ ጨለማ፣ እውነት፣ ሕይወትና ፍቅር የተሰኙት ናቸው።

## የመጽሐፉ ዓላማ

ይህ ወንጌል ለምን እንደተጻፈ ጸሐፊው ዮሐንስ በመጽሐፉ ውስጥ በግልጽ አስቀምጧል። በ20:31 «ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል» ይላል። ስለዚህ የተጻፈበት ምክንያት ከዚህ እንደምንረዳው:-

1. ኢየሱስ መሲሕ ወይም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማሳወቅ
2. በኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ያምኑ ዘንድ
3. የሚያምኑት የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኙ ነው።

ስለሆነም የመጽሐፉ ዋና ዓላማ የዘላለም ሕይወት የሚገኘው የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሆነ ማሳወቅ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በመጽሐፉ ውስጥ በ1:1-18፣ 2:1-11፣ 4÷46-54፣ 6÷5-14፣ 6÷16-21፣ 9:1-12፣ 11:1-44፣ 19:1-20፤30 ላይ ጎልቶ ይታያል።

## መልእክቱ

የዮሐንስ ወንጌል ዋና ትኩረት ከሚያደርግባቸው ርዕሶች መካከል የሚከተሱት ይገኛሉ፡፡

ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ
ለ. የዘላለም ሕይወት
ሐ. ማመን (እምነት)
መ. ትንሣኤ

## ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ ይህ ከዘላለም ጀምሮ ያለው ልጅነት ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መግለጥ የዮሐንስ ወንጌል ዋና መልእክት ሲሆን ይህን በተለየ ሁኔታ የሚገልጡ ስምንት ምልክቶች[2] ወይም ተአምራት በመጽሐፉ ውስጥ አሉ፡፡ እነዚህም:-

**1. ውኃን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ (ዮሐ 2፥1-11)**

ይህ በገሊላ ቃና ሠርግ ላይ የተፈጸመው ምልክት ጌታ ካደረጋቸውና ከተጻፉት ተአምራት የመጀመሪያው ነው፡፡ በዚህ ተአምራት ኢየሱስ ክብሩን ገለጠ፡፡ ደቀ መዛሙርትም በእርሱ አመኑ፡፡ በዚህ ምልክት መነሻነት ደቀ መዛሙርት እርሱ ከመምህር በላይ መሆኑን እንደ ተገነዘቡና በእርሱም እንዳመኑ እናያለን፡፡

**2. ከንጉሥ ቤት የሆነ የአንድ ሹምን ልጅ መፈወሱ (ዮሐ. 4፥46-51)**

ልጁ የታመመበት ከንጉሥ ቤት አንድ ሹም ነበር፡፡ ሹሙም ልጁን ይፈውስለት ዘንድ ኢየሱስን ጠየቀው፤ ፈወሰውም፡፡ ጌታ የታመመውን ልጅ በመፈወሱ በበሽታ ላይ ሥልጣን እንዳለው ከማሳየቱም በላይ የሁሉም ሰዎች (የአይሁድ ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም) ፈዋሽና አዳኝ፤

---

[2] Arround the signs are clustered the teachings which interpret ... spiritual truth. In the signs appear the revelation of God, in belief, the reaction that they ought to evoke, in life the result that belief brings. Merrill C. Tenny, John: the Gospel of Belief, pp. 33-34.



ለሰው ሁሉ የሚያስብና የሚጠነቀቅ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህ ጌታ ያደረገው ሁለተኛው ተአምር ነበር፡፡

**3. ከ38 ዓመት ጀምሮ የታመመ በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ የነበረ አንድ ሰው መፈወሱ (*5፥1-15*)**

ይህ ሰው የታመመው በጣም ለረጅም ጊዜ (ለ38 ዓመት) ነው፡፡ መታመሙ በብዙዎቹ ዘንድ የሚታወቅ ነው፡፡ ጌታ ይህን ተአምር ያደረገው በሰንበት ቀን ነበር፡፡ ከዚህ የተነሣ አይሁድ ሰንበትን ሽሯል በማለት ኢየሱስን ለመግደል ተነሣሱ፡፡ እንዲሁም እግዚአብሔርን አባቴ በማለት ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሏል በሚል ሊገድሉት ፈለጉ (5፥18)፡፡

**4. አምስት ሺህዎችን መመገቡ (6፥5-14)፤**

ጌታ እነዚህን በሺህዎች የሚቆጠሩትን የመገበው ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ ነበር፡፡ ይህ ተአምር በአንድ ጊዜ ለብዙ ሺህዎች የተዳረሰና የታወቀ ነው፡፡ በዚህም የሚጠበቀው ነቢይ ወደ ምድር መምጣቱን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አይሁድ ይህን ተአምር ካዩ በኋላ ይህስ በእርግጥ ነቢይ ነው፤ ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ይህ ነው ማለት ጀመሩ፡፡

**5. በውኃ ላይ መጓዙ (*6፥16-21*)**

በዚህ አስደናቂ የውኃ ላይ ጉዞው ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃን ጨምሮ በተፈጥሮ ላይ ሥልጣን እንዳለው ያሳያል፡፡ በባሕር ላይ ዓሣ በማጥመድ ልምምድ ያላቸው፣ ስለ ውኃ ባሕርይ ብዙ የሚያውቁ የእርሱ ደቀ መዛሙርት በባሕር ላይ በእግራቸው እየተራመዱ ሊጓዙ አይችሉም፡፡ እንኳንስ በውኃ ላይ መጓዝ በጀልባ መሄድም ምን ያህል አዳጋች የሚሆንበት ጊዜ እንዳለ ደቀ መዛሙርቱ ያውቃሉ፡፡ ጌታ ግን በባሕሩ ላይ ተራመደ፡፡ በዚህ ምልክት እርሱ ከመስጠም በላይ፤ ከባሕር ማዕበል በላይ የሆነ ሥልጣን እንዳለው አሳየ፡፡

**6. ከመወለዱ ጀምሮ እውር የነበረውን ሰው መፈወሱ (9÷1-41)::**

ተአምራት ሁሉ አስደናቂዎች ቢሆኑም ይህኛው ደግሞ በዓይነቱ ለየት ያለ ነው:: ልዩነቱም ብርሃንን የመለሰለት ወይንም እንዲያይ ያደረገው በእድሜው መካከል ለመጣበት ችግር ሳይሆን ከመወለዱ ጀምሮ ብርሃን አይቶ ለማያውቅ ሰው መሆኑ ነው:: ጨርሶ ብርሃን አይቶ ለማያውቅ ሰው ዓይንን (ብርሃንን) ሰጠው:: ይህ እንደገና የመፍጠር ሥራ ነው::

**7. ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን ከሞት ማስነሣቱ (ዮሐ 11÷1-44)::**

ኢየሱስ ክርስቶስ ፈዋሽ እንደሆነ በገሊላና በይሁዳ ሁሉ ይታወቅ ነበር:: በዚህ ተአምር ደግሞ እግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለሞተ፣ ለተቀበረና ለሸተተ እንደገና ከሞት ማስነሣት ሕይወትንም መስጠት የሚቻለው እንደሆነ አሳየ:: በሥጋ ላይ ያለ ህመምን መፈወስ፤ የጎደለ የሰውነት ክፍልንም ማሟላት ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም መስጠት የሚችል መሆኑን አሳየ:: በዚህም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ገለጠ::

**8. ከሙታን ተለይቶ መነሣቱ (ዮሐ 20÷1-29)**

ይህ ከተአምራት ሁሉ የላቀው ተአምር ራሱ ሞትን ድል ማድረጉ ነው:: ይህ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት የተናገረው ሁሉ እውነት እንደሆነና እንደሚፈጸምም ሁነኛ ማረጋገጫም ነው:: በዚህም የሰውን ልጆች ኃጢአት እንደሚያስወግድና ላመኑበት የዘላለምንም ሕይወት እንደሚሰጥ የተናገረውን ሁሉ የሚያረጋግጥ ተአምር ነው:: ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ብዙዎች አይተውታል (ዮሐ 19-29፤ 21÷1-24):: ስለዚህም ብዙዎች በእርሱ አመኑ (20÷29)::

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሌላው መግለጫ፣ ***እኔ ነኝ*** እያለ የተናገረው እና ያስተማረው ነው:: በዚህም እርሱ አልፋና ኦሜጋ፤ የመጀመሪያና የመጨረሻ፤ እግዚአብሔር መለኮት መሆኑን መግለጹ ነው:: ***እኔ ነኝ*** በማለት የተናገራቸው የሚከተሉት ናቸው::

- እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ (6÷35)
- እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ (8÷12፣ 9÷5)
- እኔ የበጎች በር ነኝ (10:7)
- መልካም እረኛ እኔ ነኝ (10:11፣14)



- ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ (11÷25)
- እኔ መንገድ፤ እውነትና ሕይወትም ነኝ (14÷6)
- እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ (15÷1)

በእነዚህና በሌሎችም ብዙ ምልክቶችና ማስረጃዎች ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አሳይቶአል::

## ለ. የዘላለም ሕይወት

«እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸው መጣሁ» (10÷10) እንዳለው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ለእኛ ሕይወት ሊሰጠን ነው:: እንዲሁም እኔ መንገድ፤ እውነትና ሕይወት ነኝ (14÷2-3፣6) ብሏል:: በተጨማሪ ስለ ዘላለም ሕይወት 3÷15-16፣36፤ 4:14፤36፤ 5: 24፤39-40፤ 6÷27፤40፤47፣54፣58፤ 8÷51፤ 10÷10፤27-30፤ 11÷25-26፤ 12÷25፣49-50፤ 20÷30-31 ይመልከቱ:: የዘላለም ሕይወት የማግኛው መንገድ ይህን ሕይወት ለመስጠት በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው::

የዘላለም ሕይወት በዚህ ምድር ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚጀምር ሆኖ ከሞትም ባሻገር ለዘላለም የሚቀጥል መጨረሻ የሌለው ሕይወት ነው:: «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ» (3:16) እንደሚል የዘላለም ሕይወትን ማግኘት ማለት አለመጥፋት ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም መሆን ማለት ነው:: ዘላለማዊነት የእግዚአብሔር የማንነቱ መግለጫ ሲሆን የዘላለም ሕይወት ያላቸው ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንደሚኖሩ ያመለክታል::

## ሐ. ማመን (እምነት)

የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ የተጻፈበትና ጌታ በምድር ላይ ምልክቶችንና ተአምራትን ያደረገበት ዓላማ ሰዎች ሁሉ በእርሱ ያምኑ ዘንድ ነው (ዮሐ 20÷31)::

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ለሰው ልጆች የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት ነው:: የዘላለም ሕይወት የመቀበያው መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በማመን ነው::

ማመን:- ወደ ምድር የመጣውን የእግዚአብሔር ልጅ መቀበል ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ተረድቶ፣ እርሱ የሚሰጠውን የዘላለም

ሕይወት የመቀበያው መንገድ እምነት ነው:: ስለ ማመን 1÷12፣50፤ 2÷11፣23፤ 3÷15-18፤ 4÷39-42፣46፣48-53፤ 5÷24፣47፤ 6÷30፣47፣64፤ 8÷24፣31፤ 9÷38፤ 10÷25-42፤ 11÷25-27፤ 12÷37-46፤ 14÷11-14፤ 16÷9፤ 17÷8፤ 20፤20፤25-30 ይመልከቱ::

ማመን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በአእምሮ ከመገንዘብ ወይም ከማወቅ የሳቀ ነው:: የአእምሮ እውቀት ብቻውን አያድንም፤ የሚያድነው የእርሱን ማንነት በማወቅ መቀበልና ንስሐ በመግባት (ከኃጢአት በመመለስ) እርሱን መከተል ነው:: ይህም በብርሃን መመላስ ነው (8÷14)፤ ቃሉን መጠበቅ ነው (8÷51)::

ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሰው ማለት የእርሱን ማንነት የተቀበለ፤ በእርሱ ላይ እምነቱን ያሳረፈ ወይም የሚታመንበት፤ የሚከተለውና የሚታዘዘው ማለት ነው::

## መ. ትንሣኤ

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሞተ በምድር ሁሉ የታወቀ ነበር:: በመስቀል ላይ መሞቱን ብዙዎች መስክረዋል:: በዚያም የነበረው ሕዝብ ሁሉ (19÷20)፤ ሊቀ ካህናትና የአይሁድ መሪዎች (19÷21)፤ ይከተሉ የነበሩት (19÷25-27)፤ የሮም ወታደሮች (19÷23-24፣32-34)፤ የቀበሩትም የአርማትያው ዮሴፍና ኒቆዲሞስ (19÷38-42) መስክረዋል:: በዚያን ወቅት ጌታ ኢየሱስ በሞተ ጊዜ መሞቱ የታወቀ ነበርና ብዙዎች ደቀ መዛሙርት ተበተኑ ወይም በርቀት በፍርሃት ውስጥ ነበሩ (ማቴ 26÷56፤ ዮሐ 18÷13፣15)::

እንደ ሌላ ማንኛውም ሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ ግን ከሞት ጋር አላበቃም:: እርሱ በድል ከሙታን ተለይቶ ተነሣ:: መቃብሩን ያዩ መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐንስና ጴጥሮስ መቃብሩ ባዶ እንደሆነ ተናገሩ (20÷1-9):: መግደላዊት ማርያምም ጌታን አየችው (20÷10-18):: ከዚያም ደቀ መዛሙርት አዩት (20÷19-29፤ 21÷1-23)::

የጌታ ትንሣኤ እርግጠኛ ስለሆነ፤ የደቀ መዛሙርት ሕይወት ከትንሣኤው በኋላ በጣም ተለወጠ:: ትንሣኤ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና የተናገረውን ሁሉ ያረጋገጠ ትልቅ ምልክት ወይንም ተአምር ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ «እውነት» እንደሆነ ተናግሮ ነበር (14÷6) ትንሣኤው ይህን አረጋገጠ፤ እንደተናገረው መሆኑን::



ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንደሚኖረው አስተምሮ ነበር (3÷16-18):: ይህ ተስፋ እውነት መሆኑንና ለሚያምን ሁሉ ይህ የዘላለም ሕይወት ተስፋ እንዳለው እርሱ ከሙታን በኩር ሆኖ በመነሣቱ አረጋገጠ::

ሞቶ የነበረው ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28÷20) ሲል ዛሬም የእርሱ ከሆኑት ጋር በሁሉም ቦታ አብሮ እንዳለ ማረጋገጫ ነው:: እንዲሁም «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ» (11÷25) እንዳለው በእርሱ ለምናምን ሁሉ የሕይወት ትንሣኤ እንዳለን ያስረግጥልናል::

## በመጽሐፉ ውስጥ ብዙ ጊዜ የተጠቀሱ ሰዎች

ኢየሱስ፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ደቀ መዛሙርት፣ የጌታ እናት ማርያም፣ ሌላዋ ማርያም፣ አልአዛር፣ መግደላዊት ማርያም፣ ጲላጦስ::

## የመጽሐፉ አስተዋጽዖ

የዮሐንስ ወንጌል በሦስት ትልልቅ ክፍሎች ሊከፈል ይችላል::

1. የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መልበስ (መሆን)ና ለአገልግሎት መዘጋጀት (1፡1-2:11)::

2. የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱና አገልግሎቱ፤ (2፡12-12፡50)

3. የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤው፤ (13፡1-21፣25)

# ምዕራፍ አንድ

በዚህ ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ሆኖ (የሰውን ሥጋ ለብሶ) ወደ ዓለም ሲገባ እንመለከታለን:: ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ መለኮትነቱን አልተወም:: እርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር ነው:: የዓለም ፈጣሪና ደግፎ የሚያኖራትም ነው::

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በግልጽ እንደምንመለከተው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው:: በሥጋ የተገለጠ ቃል ነው:: ለሚያምኑት የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ ነው:: በጨለማ ላይ ብርሃንን የሚያበራ ብርሃን ነው:: ለሚከተሉት ጸጋን የሚሰጥ ነው:: እርሱ እውነት ነው:: እርሱ የእግዚአብሔር ክብር በሙላት ያለበት መለኮት ነው::::

*1፥1 በመጀመሪያ፡-* በመጀመሪያ ከተሠራው በፊት የነበረ መጀመሪያ፤ ከሁሉ አስቀድሞ የነበረ፤ ከዘፍ 1፥1 በፊት የነበረ መጀመሪያ:: መጀመሪያ ከሌለው ከዘላለም ጀምሮ ያለ:: ይህ ከዘላለም ያለው ቃል በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለፈጠረው (ዘፍ 1:1) ሁሉ ፈጣሪ ነው::

*1፥1 ቃል ነበር፡-* ቃል በግሪክ ሎጎስ[3] የተባለው በብሉይ ኪዳን መዝ 33፥6 ላይ እንደተገለጸው «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ» በሚለው ውስጥ ይገኛል::

በግሪክ ቋንቋ አገባብ ቃሉ በሁለት መንገድ ጥቅም ላይ ይውላል:: አንደኛው፤ የሰውን አስተሳሰብ/ሃሳብ ሲያመለክት፤ ሁለተኛው ደግሞ ንግግርን (ከአፉ የሚወጣውን ንግግር) ያሳያል:: ስለሆነም የቃሉ አጠቃቀም ዓለማት የሚገዙበት ወይም የሚተዳደሩበትን ጽንስ ሃሳብ ወይም አሠራር/አስተሳሰብ ያመለክታል:: ግሪኮች (አይሁድም) ሎጎስ ወይም ቃል የሚለውን የሰውን ሀሳብ የሚገልጥ ትርጉም እንዳለው አድርገው ይጠቀሙበታል::

ሆኖም በዮሐንስ ወንጌል ቃል የሚገልጸው ሰው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው (1፥14) ስለሆነ አገባቡ/አጠቃቀሙ ከንግግር ወይም ከሀሳብ/አስተሳሰብ የተለየ ሁኔታ አለው:: ይህ ሰው የሆነው ራሱ የዓለማት ፈጣሪም ነው:: የእግዚአብሔር መገለጥ ነው:: ሁሉም ነገር ተጋጥሞ የሚኖረው በእርሱ ነው (ቆላ 1፥17)::

---

[3] Logos

ቃል የሆነው ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ በመካከላችን የተገለጠው እግዚአብሔር፤ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለእኛ ይገልጥልናል። ይህም የእግዚአብሔር ሃሳብ ማለት ቃሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የማይታየው አምላክ ምሳሌ ነው (ቆላ 1÷15)። የእርሱ የክብሩ መንጸባረቅ ነው (ዕብ 1÷3)። እርሱ ራሱ እግዚአብሔር የሆነ እግዚአብሔርን የሚገልጥ ነው። እግዚአብሔር አብን ለእኛ የገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

***1+1 ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።*** በዚህ አገላለጥ ዮሐንስ ቃልንና እግዚአብሔርን አብረው እንደ ነበሩ ያሳያል። ቃል ልጁ ኢየሱስ ነው። ስለሆነም ቃል (የእግዚአብሔር ልጅ) እና እግዚአብሔር አብ በአንድ ላይ ነበሩ። ከመጀመሪያው (ከዘላለም) የእርስ በእርስ ተዛምዶ፤ አንድነት፣ ኅብረት አላቸው። እርሱ በአባቱ እቅፍ ነበር (1÷18) ማለትም ከእርሱ ጋር በቅርበት፤ አብሮ፤ በኅብረት ነበረ።

***1+1 ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።*** ይህ የሚገልጸው ቃል ማለትም ልጁ ከእግዚአብሔር ጋር መኖሩን፣ ኅብረት ማድረጉን ብቻ ሳይሆን ራሱ ቃል እግዚአብሔር መሆኑን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው።

***ቃልም እግዚአብሔር ነበር*** የሚለው ቃልም መለኮት ነበር ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት ነው፤ አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር ተብሏል፤ (1÷1፤48፤ 20÷28)። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ (1÷2)።

ለዘላለም ሕያው የሆነ እግዚአብሔር፣ መጨረሻ እንደሌለው ሁሉ መጀመሪያም የለውም። ቃልም (የእግዚአብሔር ልጅ) በጊዜ አቆጣጠር መጀመሪያ ከሌለው መጀመሪያ ከእግዚብሔር ጋር አብሮ ይኖራል። በእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስና በእግዚአብሔር አብ መካከል የጊዜ መቀዳደም ወይም መበላለጥ ሳይኖር ከመጀመሪያ አብረው እንዳሉ ያስረግጥልናል።

***1+3 ሁሉ በእርሱ ሆነ።*** ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ፤ ሁሉንም የፈጠረ ነው። የተፈጠሩት ሁሉ፤ የተፈጠሩት በእርሱ በኩል ነው (1ቆሮ 8÷6፤ ቆላ 1÷16፤ ዕብ 1÷2)። በተፈጠሩበትም ሁኔታ እንዲኖሩ እርሱ በቃሉ ይደግፋቸዋል። ስለሆነም ፍጥረት ሁሉ በእርሱ ሥር በመሆን ይገዛል፤ በእርሱ ፈቃድና ጠባቂነት ይተዳደራል።



***1+4 በእርሱ ሕይወት ነበረች።*** ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ ነውና የተፈጠረው ሁሉ ሕይወትን ያገኘው ከቃል ነው። እርሱ የሕይወት ምንጭ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ላሰው ሁሉ የመኖር ሕይወትን ሰጥቷል። እርሱ ወደ ምድር የመጣው ለፈጠረው ሰው (በምድር እንዲኖር ሕይወትን ለሰጠው) የዘላለም ሕይወት ለመስጠት ነው። የዘላለም ሕይወት የሚሰጠውም በእርሱ ለሚያምነው ነው።

***1+4 ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።*** እርሱ ከሚሰጠው ሕይወት ውስጥ ልዩ ዓይነት ብርሃን አለ። ይህ ከሕይወት ጋር አብሮ ያለው ብርሃን ጨለማን የሚያሳውቅ፣ ኃጢአትን የሚገልጥ ብርሃን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሄደበት ቦታ ሁሉ እርሱ ብርሃን ነውና ብርሃንን ያመጣ ነበር (3÷21፤ 8÷12)። እዚህ ላይ *ብርሃን* የሚለው የሚያመለክተው መንፈሳዊ መረዳትን፣ መንፈሳዊ ግንዛቤን ነው። ብርሃን ጨለማ መሆኑን ከማሳየት አልፎ የጨለማውን መጨለም እንደሚገልጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ያለው ብርሃን የጨለማውን ምንነት ለመረዳት የሚያስችል ብርሃን ነው። ጌታ ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር ሲነጋገር ስለ ዕውርነት የሚናገራቸው (ለምሳሌ በ9÷35-40) ሆን ብለው ከእውነት ለመራቅ የሄዱትን የእንቢታ መንገድ ሲያሳይ ነው። የሚያዩ የሚመስሉ ነገር ግን የማያስተውሉ ማለት ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን በሰው ላይ ሲበራ ኃጢአተኛነትን ይገልጣል። ከእርሱ ክብር አንጻር ሰዎች ሁሉ በምን ያህል ጨለማ ላይ እንዳለን እንድንገነዘብ ይረዳናል። ኢየሱስ ለሰው ዘር (ለሰው ሁሉ) ሕይወትን የሚሰጥ ብርሃን ነው።

***1+5 ብርሃንም በጨለማ ይበራል፡-*** *ይበራል* የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሁን ጊዜን ነው። በቁጥር 4 ደግሞ ***በእርሱ ሕይወት ነበረች+ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች*** ሲል፤ *ነበረች* የሚለው ቃል የሚያሳየው የኃላፊ ጊዜን ነው። ይህም ማለት ኢየሱስ ሰውን ሁሉ ሲፈጥር፡- የመፍጠርን ጊዜ ያመለክታል። ለሁሉም ሕይወትን መስጠቱን ያሳያል። አሁን ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ***ብርሃንም በጨለማ ይበራል*** ሲል የኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ምድር መምጣትና ብርሃን መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ የሰው ሁሉ ፈጣሪ በመሆኑ ሕይወትን ሰጥቷል። የሰው ሁሉ አዳኝ ስለሆነ አሁን በጨለማ ላይ ያበራል። በአሁኑ ጊዜ ዓለም በጨለማ ውስጥ ናት። ጨለማውም ኃጢአት፤ ማለትም ከእግዚአብሔር መራቅ ወይም መለየት ነው። ብርሃኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ማዳን ነው። የዚህ ዓለም ገዥ የማያምኑትን «ዓይን» አሳውሯልና ዓለም በጨለማው ውስጥ ናት (2ቆሮ 4÷4፤ ኤፌ 5+8)።

***1+5 ጨለማም አላሸነፈውም::*** ጨለማው ኃይለኛ፤ ብርቱ ነው:: ብርሃንን የሚቋቋም ጨለማ፤ ድቅድቅ ጨለማ ነው:: ሆኖም በጨለማው ላይ የሚያበራው ደግሞ እጅግ ኃይለኛና በቀጣይነት የሚበራ ስለሆነ ያሸንፋል፤ ጨርሶ አይሸነፍም:: ጨለማው ቢሆንስት ቢያግደውና ቢያሸንፈው በወደደ ነበር፤ ሊያጠፋው አይችልም:: የተፈጥሮ ብርሃን በጨለማ ላይ ሥልጣን እንዳለው ብርሃን ጨለማን እንደሚገፍ እንዲሁ በመንፈሳዊውም ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ያመጣው ብርሃን በዚህ ዓለም ገዥ ሥራ ላይ በማብራት ያሸንፋል:: ***አላሸነፈውም*** የሚለው ቃል በጨለማና በብርሃን መካከል የነበረውን (ያለውንም) ግብ ግብ ወይም ትግል ያመለክታል::

ጨለማው በጨለማው አለቃ በሰይጣን መሪነት ያለ የኃጢአተኝነት ሕይወት ነው:- በኃጢአት መኖር፤ እግዚአብሔርን መቃወም ነው:: በጨለማ ውስጥ ያሉ በኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውን ብርሃን ሊቀበሉ አይፈልጉም:: ይሁን እንጂ ጨለማው ምንም ያህል ድቅድቅ ቢሆን ከኢየሱስ የሚመጣው ብርሃን በጨለማው ላይ ሥልጣን አለው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን በማንኛውም የሰይጣን አሠራርና ጨለማ ላይ የማሸነፍ ሥልጣን አለው፤ በርትቶ ያሸንፋል::

***1+6 ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ::*** የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ ከቁጥር 1-5 ባለው ክፍል *ቃል* ስለሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ማንነት ከገለጠ በኋላ አሁን ደግሞ ለዚህ ቃል (የእግዚአብሔር ልጅ) መልእክተኛ ሆኖ በፊቱ ስለ ሄደው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ይናገራል:: ይህ ዮሐንስ የተላከ ሰው ነው:: የተላከውም በእግዚአብሔር ነው:: ዮሐንስ ወደ ዓለም ስለሚመጣው ብርሃን፤ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲናገር አስቀድሞ የተላከ ሰው ነበረ::

***1+7 ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ::*** የዮሐንስ መጥምቁ ተልዕኮ መመስከር ነው:: ምስክርነቱም ሁሉም (ሰው ሁሉ) በእርሱ እንዲያምኑ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመሰክር ነው::[4] ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያመለክት የተላከ ነው:: ስለ እርሱ መምጣት በዘመናት ሁሉ ብዙዎች መስክረዋል:: ከእነዚህ ምስክሮች ቀዳሚው ወይም ትልቅ የሆነው የእርሱ መንገድ ጠራጊ የተባለው (ኢሳ 40፤3፤ ሉቃ 7:28) ዮሐንስ ነው:: የሚመሰክረውም ስለ ብርሃን ነው:: ብርሃኑም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በዚህ ብርሃን ሰው ሁሉ ያምን ዘንድ ስለ ብርሃን ይመሰክራል::

---

[4] መጥምቁ ዮሐንስ ከሴት ከተወለዱት ሁሉ ታላቁ ሰው እንደሆነ ጌታ በሉቃ 7:28 ተናግሯል::



***1+8 ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ እርሱ ብርሃን አልነበረም::*** መጥምቁ ዮሐንስ የተላከበት ዓላማ ራሱ ብርሃን ሆኖ እንዲያገለግል አልነበረም፤ ስለ ብርሃኑ መምጣት እንዲናገር እንጂ:: ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የዓለም ብርሃን በጨለማ ላይ የሚያበራ ብርሃን:: ዮሐንስ ግን ብርሃን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣቱንና መዳንም የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑን ይህን ሊያስገነዝብ ለዚህ ተልዕኮ የመጣ ሰው ነው:: ስለሆነም በኢየሱስ ክርስቶስ እና በመጥምቁ ዮሐንስ መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ ሐዋርያው ዮሐንስ በወንጌሉ ያስገነዝበናል:: የዓለም ብርሃን አንድ ነው:: እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

«እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» (ማቴ 5:14) ሲል እኛ በእርሱ የምናምን ብርሃን ሆነናል፤ እርሱን ተክተናል ማለት ሳይሆን የእርሱ ብርሃን በውስጣችን ስለ ገባና ስለሚኖር የእርሱን ብርሃን የምናንጸባርቅ/የምናሳይ የእርሱን ባሕርይ የምንገልጥ ሆነናል ማለት ነው:: ሰው በኃጢአት ከመውደቁ የተነሣ በውስጡ ብርሃን የለም:: በሰው ውስጥ ያለው ጨለማ ነው፤ ኃጢአት ነው:: ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ኃጢአቱን ሲያይና በእርሱ ሲያምን የእርሱ ብርሃን በውስጡ ያድራል:: የዚያ ብርሃን ተካፋይ ስለሚሆን ያን ከኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘውን ብርሃን ያንጸባርቃል::

ስለሆነም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ማንም ቢሆን ስለ ብርሃን እንደሚመሰክር እንጂ ራሱን ብርሃን አድርጐ ሊያቀርብ አይገባውም:: ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ የነበረውን ጨለማ ስላስወገደለት ከብርሃኑ ብርሃንን ያገኘ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ከራሱ ያልሆነን ብርሃን ያገኘና የተቀበለውን የሚያንጸባርቅ ብርሃን ነው:: የዚህ ብርሃን ዓላማ ሁልጊዜ ወደ እውነተኛውና ዋናው ብርሃን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማመልከት ነው:: ስለሆነም «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ሲል የኢየሱስ ክርስቶስን ብርሃን በዓለም ላይ በማብራት ሰዎች ዓይናቸውን ገልጠው ብርሃን የሆነውን ኢየሱስን እንዲያዩ ታደርጋላችሁ ማለቱ ነው::

***1+9 ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር::*** እውነተኛው ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ዮሐንስ መጥምቁ በመጣና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም መመስከር በጀመረ ጊዜ እውነተኛው ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም እየመጣ አገልግሎቱን ሊጀምር ነበር:: ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ዓለም የመጣው እውነተኛው ብርሃን የሚያበራው ላለባት ምድር ለገሊላ ወይም ለናዝሬት ብቻ ሳይሆን ***ለሰው ሁሉ*** ነው:: ***ለሰው ሁሉ*** ሲል አይሁድንም አሕዛብንም ያጠቃልላል:: እያንዳንዱ ሰው ለመኖር ሕይወትን ከእርሱ እንዳገኘ

ሁሉ ብርሃንንም ከእርሱ ዘንድ ያገኛል። ይህ እውነተኛ ብርሃን ከብርሃን ሰጪ መሰል ነገሮች፤ ከአስመሳይ ብርሃኖች የተለየ ነው። የዓለም ብርሃን አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለሆነም ማናቸውም ብርሃን ሰጪ የሚመስሉት ሁሉ ራሳቸው በጨለማ የሆኑ፤ የጨለማው ክፍሎች ናቸው።

***1፥10 በዓለም ነበረ።*** ወደ ዓለም[5] የመጣው ብርሃን ኢየሱስ እርሱ ወደ ሠራው ዓለም[6] መጣ። ዓለም ሁሉ የተሠራው በእርሱ ነውና። ሆኖም ***ዓለሙም አላወቀውም 1፥10።*** እርሱ ራሱ ወደ ሠራው ዓለም በመጣ ጊዜ ዓለም[7] ማለትም የሰው ዘር ማንነቱን አላወቀውም፤ ፈጣሪውን አላወቀውም። ምክንያቱም ጨለማው እይሉ ነበርና በጨለማው ታውረው ነበርና። ዓለም በጨለማ ውስጥ ስላለች ብርሃንን ማየት ተስኗታል።

***1፥11 የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። የገዛ ወገኖቹም*** የሚለው አርሱ ወገን ወደሆነበት ማለት ሲሆን ልክ ወደ ቤቱ መጣ፤ ወደ ራሱ ቤት መጣ እንደማለት ነው። ይህ ደግሞ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን አለመቀበል አጉልቶ ያሳያል። ወደ ገዛ ቤቱ የመጣን ሰው እንኳን ደህና መጣህ ብሎ እንዳለመቀበል ነው።

የገዛ ወገኖቹ የሚለው የሚያመለክተው የሰው ዘርን ሁሉ ሆኖ በተለይም እይሁድን (እስራኤልን) ነው። ወደ እስራኤል መጣ፤ እይሁድም አልተቀበሉትም። ይህ አለመቀበላቸው በ12፥37-41 ባለው ተገልጿል። እንደማይቀበሉትም አስቀድሞ በነቢዩ ኢሳይያስ ተነግሮ ነበረ (ኢሳ 53፥1-3)። የገዛ ወገኖቹ ቢገፉትም፤ ባይቀበሉትም የተቀበሉት ደግሞ ነበሩ። ለተቀበሉት ሁሉ ግን በረከትን አዘጋጅቷል። መቀበል ማለት በኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ማመንና እኔንም አድነኝ ብሎ ወደ እርሱ መቅረብ ነው።

***1፥12 ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።*** እነዚህ የሚቀበሉት የኢየሱስን አዳኝነት፣ ብርሃንነት የሚያምኑና ለራሳቸውም አዳኜ ነው ብለው የሚቀበሉት ናቸው። እነዚህ የልጅነት ሥልጣን የነበራቸው

[5]The term <world> can mean different things depending on its context. The NIV Study Bible lists 6 different usages; these are: - the universe, the earth, the people on earth, most people, people opposed to God, or the human system opposed to God's purposes.
[6] The universe
[7] The human system opposed to God's purposes.



አይደሉም። በማመናቸው ምክንያት እና ከአመኑበት ጊዜ ጀምሮ የሚሰጣቸው የልጅነት መብት ነው።[8] ይህ በአመኑበት ጊዜ የሚያገኙት «መታወቂያ» ወይም መብት እንደማለት ነው። ሥልጣኑ፤ ልጅ (የቤተሰብ አባል) የመሆን ሥልጣን ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ለመጠራት መንገዱ እምነት ነው። ***በስሙ ለሚያምኑት*** እንደሚል በኢየሱስ ስም ማመን ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና እርሱ በገባው ተስፋ ላይ ማመን ማለት ነው። <u>ማመን ማወቅንና መቀበልን በአንድ ላይ የያዘ</u> ቃል ነው። የሚያምን ሰው ምን እንደሚያምን አስቀድሞ ያወቀና ያወቀውን ደግሞ ለራሱ እውነት ነው፤ እኖርበታለሁ ብሎ የተቀበለ፤ በዚያም መሠረት የሚተዳደር ማለት ነው። ማመን = ማወቅ + መቀበል ወይም መኖር ነው።

***1፥13 ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደምና ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።*** ከእግዚአብሔር መወለድ ከሰው የሥጋ ፈቃድ ወይም ተፈጥሮአዊ ሰው በሚገኝበት መንገድ የሚገኝ ልጅነት አይደለም። እግዚአብሔር ባዘጋጀው መንገድ በማመን የሚገኝ መንፈሳዊ መወለድ ነው። ይህ መወለድ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር በነጻ የሚሰጠው የልጅነት ሥልጣን ነው።

***1፥14 ቃልም ሥጋ ሆነ፦*** ይህ ቃል በመጀመሪያ የነበረው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው ነው (1፥1)። ይህ በመጀመሪያ የነበረና በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው ***ቃል ሥጋ ሆነ፡*** ሥጋ ወሰደ። የመለኮት ሁለተኛው አካል የሰው ሥጋ መውሰዱንና ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ያስገነዝበናል። ሥጋ ሆነ[9] ማለት ሰው ሆነ

[8] በመሠረቱ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለትም በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው። እያንዳንዱ ሰው ሕይወትን ያገኘውና መኖሩም በእርሱ ስለሆነ በመፈጠር የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እንዲሁም በእርሱ የሚያምን ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና አዳኝነት ለሚያምኑ ሰዎች የሚሰጥ ሥልጣን ነው።

[9] *ቃል ሥጋ ሆነ* ሲል በግሪኮች ፍልስፍና መሠረት ቃል ማለት አስተሳሰብ ወይም ንግግር የሚልን ትርጉም ስለሚይዝ ሃሳብ ወይንም ንግግር ሥጋ ሆነ ሲል የእነርሱን ፍልስፍና መጣሱን ወይም መቃረኑን ነው። ምክንያቱም የተጻፈው እውነትን ለማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ ነው። እውነት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። እውነት እርሱ ነውና። እውነት የሆነው እርሱ ነውና። እውነት እርሱ ነውና። The Greek philosophical meaning of the term *word* as <reason> could refer to anything that wasn't flesh. To say <the Word became flesh> broke all the rules - which is exactly what God did. LEBC <u>Ibid.</u> p.12.

ማለት ነው::[10] ዮሐንስ በ1ዮሐ 4÷3 መልእክቱ ላይ እንደገለጠው «ኢየሱስ በሥጋ እንደተገለጠ የማያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም»:: ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው በሥጋ ነው:: ይህም ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ከፊል ሰውና ከፊል መለኮት ሆነ ማለት አይደለም:: በቆላ 2÷9 ላይ በግልጽ እንደተጻፈው መለኮትነቱ በሙሉነት በሙላት በእርሱ ላይ ነበረ:: ስለዚህ ሙሉ መለኮት ወይም ፍጹም አምላክ ነበረ:: በሰውነቱም እንዲሁ በፍጹምነት ማለትም ፍጹም ሰው ነበረ::[11]

***1:14 ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ፡-*** የሚለው ሥጋ የሆነውን ቃል ይገልጻል:: ጸጋ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነፃ ስጦታን ሲያመለክት እውነት ደግሞ እርግጠኛነትን፣ ሐቅን፤ ማስመሰል የሌለበትን ትክክለኛነት ያሳያል:: ብርሃን የበራላቸው ሰዎች ይህን ጸጋና እውነት ይቀበላሉ፤ የጸጋውና የእውነቱ ተካፋይ ይሆናሉ::

***1÷14 በእኛ አደረ፡- አደረ*** የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን የነበረውን የማደሪያ ድንኳን ያስታውሳል:: በሕዝቡ መካከል መገኘቱን፣ ማደሩን ከሕዝቡ ጋር መሆኑን ለመግለጥ እግዚአብሔር የማደሪያ ድንኳን ሥሩልኝ ብሎ ነበር:: በዚያ የማደሪያ ድንኳን እግዚአብሔር ይገኛል:: በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመካከላችን አደረ፣ ተገኘ፣ ኖረ:: አማኑኤል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገጠ እግዚአብሔር፤ መለኮት በሙላት የሚኖርበት ሰው ነው::

***1÷1፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየ::*** በመካከላችን ባደረው ሥጋ በሆነው ቃል የእግዚአብሔር ክብር በሙላት ነበረበት:: በብሉይ ኪዳን በማደሪያው ድንኳን የእግዚአብሔር ክብር እንደተገለጠ በአዲስ ኪዳን በዚህ ሥጋ በሆነው ቃል ላይ

[10] *ሥጋ ሆኖ* የሚለውን ፍጹም ሰው ሆነ ወይም የሰውን ሥጋ ወሰደ ማለት አይደለም የሚል ዶሴቲዝም የተባለ የስህተት ትምህርት በታሪክ ውስጥ ተነስቶ ነበር:: Docetism - a heracy that denied that Jesus truly had a human body. The Docetists claimed that the Son of God merely *seemed* human; he was not truly human. Ibid. P.10.

[11] Before Christ came, people could know God partially. After Christ had come, people could know God fully because he became visible and tangible. (Heb 1:1-3). Christ is the perfect expression of God in human form. The two most common errors that people make about Jesus are minimizing his humanity or minimizing his divinity. Jesus is both divine and human. Ibid. p.10-11



በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ክብር በሙላት አድሮአል:: ይህ ጸጋንና እውነትን የተሞላ ነው::

***አንድ ልጅ*** የሚለው መጠሪያ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የዋለ ሲሆን እርሱ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ መሆኑን ያመለክታል:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ በሚጠራበት ዓይነት የልጅነት አጠራር ወይም ደረጃ የሚጠራ ከእርሱ ሌላ ማንም የለም:: የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነት ከዘላለም ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነት በመፈጠር አይደለም፤ በመሆን ነው:: ይህም ከዘላለም በአብና በወልድ መካከል ያለ ተዛምዶ ነው:: ስለዚህ አንድያ ልጅ የሚለው መጠሪያ ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅነት የሚያመለክት ለእርሱ ብቻ የሚውል መጠሪያው ነው::

የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር የፍጹምነት፤ የቅድስና፣ የታላቅነት፣ የብርሃን መግለጫ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ***ክብር*** የእግዚአብሔርን በእርሱ መገኘት/መታየት ያመለክታል:: ይህ የእግዚአብሔር ክብር ሰው ሊረዳው በሚችለው ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጠለት የክብር መታየት ነው::[12] ጴጥሮስ «ከገናናው ክብር የእርሱን ግርማ አይተን» (2ጴጥ 1÷16-17) እንደሚል ይህ ግርማ የተሞላበት፤ ወደር የሌለው ገናናነት ማለት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በገናና ክብር የተሞላ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነው::

***1÷15 ዮሐንስ ስለ እርሱ መሰከረ፣ እንዲህም ብሎ ጮኸ፡-*** የዮሐንስ ተግባር መመስከር ነው:: በምስክርነቱ የሚናገረው ዮሐንስ ቀድሞ እንደ መጣ፣ ከእርሱ በኋላ የሚመጣ ኢየሱስ ***እርሱ ከእኔ በፊት ነበርና***

[12] የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ከተገለጠባቸው ጥቂት ሁኔታዎች የሚከተሉት ይገኛሉ::

- እረኞች ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ክብር መስክሩ፤ ወይም አዩ (ሉቃ 2÷9-14)::
- ኢየሱስ ክርስቶስ የሠራቸው ምልክቶች ወይንም ተአምራት ክብሩን ይገልጣሉ (ዮሐ 1÷11)::
- የእግዚአብሔር ክብር በኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጧል (ዮሐ 7÷18፤ 11÷4፤ ዕብ 1÷3)::
- ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የተለየ ክብር አለው (ዮሐ 17÷50:: የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር በተራራው ላይ ተገልጦ ነበር (ማቴ 17÷2-8፤ ማር 9÷2-8፤ ሉቃ 9÷28-30):: ደቀ መዛሙርት የጌታን ክብር ተካፍለዋል (ዮሐ 17÷22)::
- ኢየሱስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቡ፤ ኢየሱስ በሞቱ መክበሩ እንደሆነ ያሳያል (ዮሐ 7÷39፤ 12÷23-28፤ 13÷31፤ 17÷5):: የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና እርገት ክብሩን ይገልጣል (ሉቃ 24÷26፤ የሐዋ 3÷13፤ 7÷5፤ 1ጢሞ 3÷16)::
- የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር በመመለሱ (ሁለተኛ ሲመጣ) በፍጹምነት ይገለጣል (ማር 8÷38፤ 13÷26)::

***ለእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል 1፥15*** በማለት ነው። ከዮሐንስ በኋላ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮሐንስ ይልቅ የከበረ መሆኑንና እንዲሁም በምድራዊ ጊዜ አሰላል ምንም እንኳን ለሚመሰክርላቸው ሰዎች ኢየሱስ የሚመጣው ከዮሐንስ በኋላ ቢሆንም፤ ኢየሱስ ግን ከዮሐንስ በፊት እንደነበረ ይናገራል። ይህም ዘላለማዊ ሕልውናውን ሲገልጽ ነው። ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰው በመወለዱ ከእድሜ አቆጣጠር አንጻር ከዮሐንስ በኋላ ቢሆንም እርሱ ግን ከዘላለም ስለሆነ ዮሐንስ ስለ እርሱ ሲመሰክር፦ ***ከእኔ በፊት ነበርና*** ይለዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጥምቁ ዮሐንስ፣ የከበረ በመሆኑ፣ እንዲሁም ከእርሱ በፊት የነበረ ስለሆነ የበለጠ የላቀ ነው።

***1፥16 እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀበለን።*** በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ያለው ሙላት ፍጹም ነው። ለሁሉም የሚሆን፤ ሁሉንም የሚሞላ፤[13] ምንም የማይጐድልበት ነው። በ1፥14 ላይ እንዳየነው እርሱ ጸጋንና እውነትን ተሞልቷል። ከዚህ ከእርሱ ሙላት ለእኛ በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል። ይህ ጸጋ በእምነት ለሚቀበሉት የሚሰጣቸው የነጻ ስጦታ ነው። ***እኛ ሁላችን*** ሲል ሁሉን አማኞችን ሲያመለክት፣ እርሱም ጸሐፊውን ዮሐንስን፤ ሐዋርያትንና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን ሁሉ ነው። ከዚህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ሁሉም አማኝ ይቀበላል።

አንድ ሰው ግን የክርስቶስን ሙላት ሁሉ ሊቀበል፣ ሊያስተናግደውም አይችልም፤ አቅም አይኖረውም። የክርስቶስ አካሉ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከሙላቱ ትሞላለች (ኤፌ 1፥23)። መንፈሳዊ ኃይል፣ እውቀት፣ ጥበብ ሁሉ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይገኛል። ስለዚህ ከእርሱ ሌላ ማንንም መፈለግ የለብንም። የሚሰጠውም ጸጋን በጸጋ በማደል፣ በማብዛት፣ በዚያው ላይ በመደረብ በመጨመር ሁልጊዜ በጸጋ ይሰጣል። ስለሆነም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋን የተሞላ ስለሆነ አማኞች በጸጋ ማነስ ወይም ጉድለት መቸገር የለባቸውም፤ መጠየቅና ከእርሱ መቀበል ሁልጊዜም መሞላት ይችላሉ። ስለዚህ ባዶነት የሚሰማው ወይም ጸጋ ያነሰው ሰው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅረብ፤ ከጸጋውም ይቀበልና ይሞላ።

---

[13] ኢየሱስ ክርስቶስ በሁሉም ረገድ ሙሉ ስለሆነ ከሙላቱ ለማንም ሰው ይሰጣል ስለዚህ ጉድለቱን የሚያውቅ እንደሚያስፈልገውም ደግሞ ፍላጐት ያለው ከኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ይቀበል ዘንድ እርሱን ሊጠይቅ ይገባዋል። በክርስቶስ የመለኮት ሙላት በሙሉነት በፍጹምነት ይኖራል (ኤፌ 1፥23፤ 3፥19፤ ቆላ 1፥19፤ 2፥9) የእግዚአብሔር ሙላት በክርስቶስ ስለሚኖር እኛም ማናቸውም የሚያስፈልገን መንፈሳዊ በረከት ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን። ጥበብ፣ ምሕረት፣ ፍቅር ሌላም ኃይል እርሱ ሁሉን በሁሉ መንገድ ይሞላል (ኤፌ 1፥23)። ከዚህ ሙሉ ከሆነ ክርስቶስ ለሌላው ሰጥቶ ከማይጐድልበት፤ እኛ ልንቀዳ/ልንቀበል በእርሱ ስጦታ ልንሞላ ያስፈልገናል።



***1፥17 ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።*** ጸጋና እውነት የተሞላውና (1፥14) ጸጋን በጸጋ ላይ የሚሰጠው (1፥16) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በብሉይ ኪዳን በሙሴ የተሰጠውን ሕግ በእርሱ መምጣት በጸጋ ለወጠው ወይም አሳደገው። የሙሴ ሕግ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፍርድ ያመለክታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ የእግዚአብሔርን ምሕረት፤ ፍቅርና ይቅርታ ይዞ መጣ። ይህ ጸጋ ነው።

ሕግ የእግዚአብሔርን ባሕርይና ፈቃዱን ይገልጻል። ሕግን ለመፈጸም ጸጋ ያስፈልጋል። ሕግን ሁሉ የፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ 5፥17) በእርሱ ለሚያምኑት ሕግን ለመፈጸም ጸጋን ሰጣቸው። የሕግ መሰጠት፤ በኃላፊ ጊዜ ሆነ፣ የጸጋ መሰጠት የአሁን ጊዜ ነው። የሕግ መሰጠት ነበር ሆኖአል፤ የጸጋ መሰጠት ደግሞ የአሁን ጊዜ በመሆኑ ***ሆነ*** ተባለ። እንግዲህ ***እውነት*** ሕግን የጣሰ በሕይወት መኖር እንደሌለበት ሲገልጽ ***ጸጋ*** ደግሞ ይቅር መባላችንን፤ መዋጀታችንን ያውጅልናል።

***1፥18 መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም።*** በብሉይ ኪዳን ለምሳሌ በዘጸ 24፥9-11 ባለው ክፍል የእስራኤል ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን እንዳዩት የሚናገር ቃል አለ። ***እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም*** ሲል ታዲያ እነዚህ ሽማግሌዎችስ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። እግዚአብሔር ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ውስጥ ስለሚኖር ሰው አይቶት በሕይወት ሊኖር አይችልም (ዘጸ 33:20)። ስለሆነም ከሰው እግዚአብሔርን በሙላት ያየው ማንም የለም። የእስራኤል ሽማግሌዎች እንዳዩት የተገለጸው እንግዲያውስ እርሱ በአንድ ቦታ በመገኘቱ የሚኖረውን ክብሩን ማለትም ለጊዜው የተገለጠውን ክብር ሊሆን ይችላል።

የእርሱን ክብር ያየው ኢየሱስ ማለት አንድ ልጁ ብቻ ነው። ስለ ክብሩም ***በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው 1:18*** ማለትም ተናገረው/ አሳየው። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ በሰዎች መካከል እየኖረ እግዚአብሔርን ገለጸው፤ አሳየው። ወልድን ያየ አብን አይቷል (ዮሐ 14:9) እንደሚል። ስለሆነም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ካልሆነ በስተቀር ስለ እግዚአብሔር መረዳት አይቻልም። ***እቅፍ*** የሚለው ቃል ሥዕላዊ አገላለጽ ሲሆን ሕፃን በወላጁ እቅፍ ውስጥ በፍቅር፤ በመጠጋጋት እንደሚኖር ዓይነት በአብና በወልድ መካከል ያለውን የአንድነትና የመቀራረብ መጠን የሚያሳይ ነው።

***1፥19 አንተ ማን ነህ?*** ይህን ጥያቄ ለመጥምቁ ዮሐንስ ያቀረቡለት ካህናትና ሌዋውያን ነበሩ። የእርሱን ማንነት ለመረዳት በጠየቁት ጊዜ መጥምቁ ዮሐንስ የሚናገረው እርሱ የተላከ መሆኑን፣ ምስክር ብቻ መሆኑን ነው። ዮሐንስ የራሱን ማንነት ያወቀና ያንንም ለሰዎች በትክክል ያስረዳ ሰው ነው። የጠያቂዎቹም መብዛትና የሰዎችን የማወቅ ፍላጎት ተንተርሶ ለራሱ ስምና ቦታ ወይም ዝና ያልሰጠ ሰው ነው።

***1፥20 እኔ ክርስቶስ አይደለሁም።*** ከዚህ ከዮሐንስ አመላለስ መገንዘብ የሚቻለው የሃይማኖት ሰዎች ካህናትና ሌዋውያን የተቀባውን መሢሑን ይጠብቁ የነበረበት ጊዜ እንደ ነበር ነው። እንደዚህ ይጠባበቁ ለነበሩ ሰዎች የሚሰጣቸው መልስ ደግሞ ያ የምትጠብቁት መሢሕ ወይም ክርስቶስ እኔ አይደለሁም በማለት ነው። ሕዝቡ በግልጽ እንዲያውቅለት የፈለገው ነገር እርሱ የተቀባው ወይም መሢሑ አለመሆኑን እንዲሁም ለሚመጣው መሢሕ መንገድ የሚያዘጋጅ መሆኑን ነው።

ፈሪሳውያን ካህናትና ሌዋውያን ብሉይ ኪዳንን የሚያውቁ፣ በብሉይ ኪዳንም ሕግና ትንቢት መሠረት የሚሆነውን የሚጠባበቁ ናቸው። የሚጠባበቁት እንደ እግዚአብሔር ቃል በሆነ መረዳት አልነበረም። እንዲህና እንዲህ ነው ብለው በራሳቸው ሥዕል መሲሕ ይጠብቁ ነበር። የሚጠበቀው መሢሕ አለመሆኑን በተነገረው ጊዜ እንግዲያውስ ***ኤልያስ ነህን? 1፡20*** አሉት። በሚል 3፡1 እና 4፡5-6 በተነገረው ትንቢት መሠረት አይሁድ የኤልያስን መምጣት ይጠባበቁ ነበረ። ዮሐንስ የመጣው በኤልያስ መንፈስ (ሉቃ 1፡17) ነበረ። ይህም መንገድ የሚያዘጋጅ ነው። በኤልያስ መንፈስ መጣ እንጂ ራሱ ግን ኤልያስ አልነበረም። እርሱ ኤልያስ ***አይደለሁም 1፡21*** ብሎ መልስ ሰጥቷል።

***1፥21 ነቢዩ ነህን?*** ይህ የጠያቂዎቹ 3ኛ ግምት ነው። የሚጠበቀው መሢሕ ካልሆንክ፣ ኤልያስም ካልሆንክ እንግዲያው ማነህ? ነገረን ሲሉት ነው። ይህን ጥያቄ ያነሱት በብሉይ ኪዳን ወደፊት እንደሚመጣ በሙሴ በኩል ስለተነገረው ነቢይ (ዘዳ 18፡15) ማሰባቸው ሳይሆን አይቀርም። የዮሐንስ መልስ ግን ለዚህም ***አይደለሁም*** የሚል ነው።

***1፥22 እንኪያስ ማን ነህ?*** በፈሪሳውያን ግምት ስለ መጥምቁ ዮሐንስ በቅደም ተከተል ሦስት ግምቶች ነበሯቸው። ሦስቱንም የሚጠብቁት በቅደም ተከተል የተነገሩ ስለነበሩ ነው። ለሦስቱም የሰጠው መልስ ***አይደለሁም*** በማለት በመሆኑ ማንነቱን ለማወቅ ይጓጓሉ። ሦስቱ የቀረቡለት የማንነት ጥያቄዎች ትልቅነትን የሚያመለክቱ ናቸው። ከሦስቱም አንዱንም እንኳ ለመውሰድ ዮሐንስ አልከጀለውም። እርሱ በተልዕኮው በማንነቱ የረካና ደስ ያለው ሰው ነው።

እርሱ ስለ ራሱ የሚሰጠው መልስ ***በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምጽ እኔ ነኝ 1፥23*** በማለት ነው። ስለዚህ የሚጮህ ሰው አስቀድሞ በነቢዩ ኢሳይያስ ተነግሮ ነበር (ኢሳ 40፡3)።

ያ ወቅት አይሁድ የመሢሑን መምጣት የሚጠባበቁበት ዘመን ስለሆነ (ሉቃ 3፥15) ዮሐንስም ተከታዮችን እያገኘ ስለ ነበረና ስለ እርሱም ማንነት ለመጠየቅ የጓጉ ብዙዎች ስለ ነበሩ ጊዜውንና አጋጣሚውን ተጠቅሞ፣ አዎ እኔ መሢሑ ነኝ ቢል ለአጭር ጊዜም ቢሆን ተከታዮች ባፈራ ስምንም ባገኘ ነበር። ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ ትልቅ የሆነው ዮሐንስ ግን በተሰጠው የመልእክተኛነት የአገልግሎት ድርሻ የረካ ማንነቱን ያወቀ ለሚጠይቁትም ያንኑ የሚገልጥ ነበር።

መጥምቁ ዮሐንስ በተጠየቀ ጊዜና ሲመሰክር በተደጋጋሚ አስረግጦ የሚናገረው፡- እርሱ ክርስቶስ አለመሆኑን፤ እርሱ በኢሳይያስ እንደተነገረው በምድረ በዳ ድምፅ፤ በፊቱ የሚሄድ መስካሪ እንደሆነና የመሢሑን መምጣት የሚያውጅ እንደሆነ ነበር። የዮሐንስ መጥምቁ አመላለስ፣ በዚህ ዘመን ለምንኖር ክርስቲያኖች በተለይም አገልጋዮች ማንነታችንን በማወቅና በማንነታችን ረክቶ ስለመኖር ጥሩ ትምህርት ይሰጠናል። ዮሐንስ አገልግሎቱን ከጀመረ ጊዜ አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ ሆኖ ነበር የጨረሰው። ስጌታ ካገለገሉት ሰዎች ሁሉ (ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ) ስለ አገልግሎቱ ትንቢት የተነገረለት መጥምቁ ዮሐንስ ነው። በጌታም ዘመን የነበረና የጌታንም መምጣት ያወጀና ያስተዋወቀ ትልቅ አገልጋይ ነው። ያም ሆኖ ***በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ እኔ ነኝ*** በማለት እራሱን በዚህ ብቻ በመግለጽ አገልግሎቱን የፈጸመ ሰው ነው። እኛም በተሰጠን አገልግሎት እና ባለንበት ሁኔታ ልንረካ ያስፈልገናል።

***1፥24-25 ስለ ምን ታጠምቃለህ?*** መጥምቁ ዮሐንስ ከሦስቱ (ክርስቶስ፤ ኤልያስ ወይም ነቢዩ) አንዱ አለመሆኑን ስለ ራሱ በገለጠ ጊዜ ለምን እንደሚያጠምቅ ይጠይቁታል፤ ማለትም አንተ የሚጮህ ሰው ድምፅ ከሆንክ ማጥመቅህ ምን ማለት ነው የሚል ነው። የሚሰጣቸውም መልስ እርሱ ለሚመጣው መሢሕ መንገድ የማዘጋጀቱን ሥራ እየፈጸመ መሆኑን ነው። ስለሚመጣው ንስሐና ይቅርታ በምሳሌ የሕዝቡን ልብ እያዘጋጀ ነበር። የኃጢአት ይቅርታ የሚመጣው በመሢሑ በእግዚአብሔር ልጅ በኩል ነው። እንዲሁም መንገድን

የሚያዘጋጀው ዮሐንስ ለሚመጣው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መንገድን እያዘጋጀ ነበረ:: *ስለ ምን ታጠምቃለህ?* ብለው ለጠየቁት ዮሐንስ ሲመልስ:- *እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል 1+2* ይላቸዋል:: መሢሑ በመካከላቸው ተገኝቷል:: እርሱ መሢሑ እንደሆነ እይሁድ ገና አላወቁትም:: ይህም ወገኖቹም አልተቀበሉትም (1÷11) የሚለውን የበለጠ ያብራራዋል::

*1+27 እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ:-* የጫማን ጠፍር መፍታት በኅብረተ ሰቡ ዘንድ በጣም አነስተኛ ተብሎ ለሚቆጠር ሰው ወይም ለአገልጋይ የተተወ ሥራ ነው:: በዚሁ ዓይነት አገላለጽ ዮሐንስ ስለ ራሱ የሚገልጠው ከጌታ አንጻር እጅግ ታናሽ እና አገልጋይ ወይም ባሪያ መሆኑን በመገንዘብ ነው:: እርሱ ታላቅ ነውና ያንን እንኳ ለማድረግ ለእኔ ክብር ነው፤ አይገባኝም ሲል የራሱን ዝቅተኛነት በመረዳት ይገልጻል:: ኢየሱስ ክርስቶስ መጥምቁ ዮሐንስን «ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ ትልቁ ነው» (ዮሐ 7÷28) ብሎታል:: ከመለሎቹ፣ ከብጤዎቹ ከሴት ከተወለዱት መካከል ዮሐንስ ትልቅ ነው:: ይህ ከምድር ሰዎች ሁሉ ትልቅ የሆነው ሰው ባለ ብዙ ግርማ ባለ ብዙ ክብር ከሆነው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሲወዳደር የማይገባው እጅግ ትንሽ ነው::

*1+27 ከእኔ ይልቅ የሚከብር:-* ራሱን በማወዳደር የኢየሱስን ታላቅነት የእርሱን ታናሽነት ሲገልጥ ነው:: ክብርን የማይሻማ፣ በማንነቱ የሚረካ ሰው ነው ዮሐንስ::

*1+29 እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ:-* ይህ ከብሉይ ኪዳን ለፋሲካ በዓል ከሚደረገው ደም ማፍሰስና፣ *መቃኑ* መቀባት ጋር የተዛመደ ነው (ዘጸ 12)::: እንዲሁም እስራኤላውያን እንዲያደርጉ ከታዘዙት የኃጢአት *መሥዋዕት* ጋር ይዛመዳል (ዘሌ 14÷12፣ 21÷24፣ ዘኁ 6÷12):: ዮሐንስ ኢየሱስን *የእግዚአብሔር በ* ብሎ ሲጠራው እያመለከተ ያለው ስለ ሰው ኃጢአት የሰው ምትክ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ስለሚቀርበው መስዋዕት ነበር:: ይህም እግዚአብሔር ራሱ ያዘጋጀው መስዋዕት እንደሆነም ጭምር ነው:: በብሉይ ኪዳን ለኃጢአት መሰዋዕት እንዲሁም ለፋሲካ በዓል ከእንስሳት ወገን ይቀርብ እንደ ነበረ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ያዘጋጀው በግ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው:: እንዲሁም የሚመጣው መሢሕ ለመታረድ እንደሚነዳ በግ እንደሚሆን (ኢሳ 53÷7) ተነግሮ ነበር::

በብሉይ ኪዳን በየጠዋቱና ማታው የሚታረድ በግ ለመስዋዕት የሚቀርብ በግ ነበር:: ስለ ሕዝቡ ኃጢአት በቤተ መቅደስ የሚቀርብ



መስዋዕት ነበረ ዘጸ 29÷38-42:: ይህ በመስዊያው ላይ በየዕለቱ ይቀርባል:: በአዲስ ኪዳን መስዋዕቱን ራሱ እግዚአብሔር አዘጋጀ:: ፍጹም የሆነ መስዋዕት፣ ነውር የሌለበት መስዋዕት:: በዚህም የሰውን የዓለምን ኃጢአት ሁሉ አስወገደ:: እርሱ ራሱ ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ (ኢሳ 53÷4-9፤ 1ጴጥ 2፡24):: በእርሱ የሚያምን ሁሉ ኃጢአቱ ይወገድለታል:: የኃጢአትንም ኃይል በዚህ አጠፋ:: ስለሆነም እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለናል (1ቆሮ 5፡7):: የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ማለትም በዓለም የሚገኘውን ሕዝብ ሁሉ ኃጢአት ለማስወገድ በቂ ነው:: ኃጢአታቸው የሚወገድላቸው ግን በእርሱ የሚያምኑት ናቸው:: እርሱ የኃጢአትን ዋጋ ከፍሏል::

*1÷30 ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው::* ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀደም ሲል በ1:15 ላይ ገልጾ ነበር:: እርሱ በዚያ ቦታ ከመምጣቱ በፊት ተገኝቶ የተናገረው ቃል ነው:: አሁን በሚቀጥለው ቀን *በነገው 1÷29* ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚያ በመጣ ጊዜ አስቀድሜ የነገርኳችሁ ይህ ሰው ነው ሲል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይናገራል:: ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮሐንስ በፊት የነበረ *መሆኑን* (ዘላለማዊነቱን)፤ ከእርሱ ይልቅ የከበረ *መሆኑን* (አምላክነቱን) ሲገልጥ ነው:: መጥምቁ ዮሐንስ ትሑት ሰው ነው::

*1÷31 እኔም አላውቀውም ነበረ:-* ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ማለትም መሢሑ መሆኑን ሳያውቀው እንደኖረ እና አንድ ቀን ግን እንዳወቀው ሲገልጥ *እኔም አላውቀውም ነበር 1:31፤33* ይላል:: ዳሩ ግን ባያውቀውም መምጣቱን ይጠባበቅ ነበር:: የመጠባበቂያውም መንገድ ለእርሱ የተሰጠውን አገልግሎት በመፈጸም ነው:: አገልግሎቱን እየፈጸመ ሳለ ያ የማይታወቀው ግን የሚጠበቀው ኢየሱስ መጣ::

*1÷31 ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ በውኃ እያጠመቅሁ እኔ መጣሁ::* የመሢሑን መገለጥ ዮሐንስ ይጠብቃል:: ይገለጥም ዘንድ እየናፈቀ የእርሱን አገልግሎት በውኃ ማጥመቁን ጀምሮ ቀጥሏል:: ይህን የሚያደርገው፤ መንገድ የመጥረግ ሥራውን ጀምሮ ነበር:: አገልግሎቱን እየፈጸመ ሳለ ከሚጠመቁት መካከል እንደ አንዱ ሆኖ ሊጠመቅ ኢየሱስ መጣ:: እስከዚያን ጊዜ ድረስ ዮሐንስ የሚመሰክረው *እኔም አላውቀውም ነበር 1:33* ብሎ ነው::

*1:32 መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ:-* ይህንን ባየ ጊዜ ሌላ ድምፅ ወደ ዮሐንስ መጣ፤ እንዲህ የሚለው:- *መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፡ በመንፈስ*

***ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ፤ 1÷33።*** በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የመንፈስን መውረድ ያዩት ዮሐንስና ኢየሱስ ናቸው (ማቴ 3÷16)።

ስለዚህ ሁኔታ በማቴ 3:17 ያለውን ስንመለከት «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚልም ድምፅ አብሮ እንደ ነበረ እናያለን። ዮሐንስ በኢየሱስ ላይ ሲወርድና ሲኖርበት ካየው ***መንፈስና ይህም*** ማን እንደሆነ ካገኘው ምስክርነት ወይም ድምጽ በመነሣት ***እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬያለሁ 1:34*** ይላል። ዮሐንስ የሚጠመቀውን ማንነት ሳያውቀው ኖሮ ድንገት እንዲያጠምቅ የላከው እርሱ ማለትም እግዚአብሔር ስለ ተናገረው ነው። እንዲያጠምቅ የተላከው ዮሐንስ ***በእግዚአብሔር የተላከ 1:6*** ነበር።

ዮሐንስን እንዲያጠምቅ የላከው እግዚአብሔር የሚጠመቀውን የኢየሱስን ማንነት ***እርሱ ነው 1:33*** በማለት ይነግረዋል፤ ስለዚህም መስከረ። እግዚአብሔር ለዮሐንስ የሚጠመቀው ኢየሱስ መሢሑ እንደሆነ የገለጠው መንፈስ በመሢሑ ላይ እንዲወርድና እንዲኖርበት በማድረግ ነው። ***ሲወርድበትና ሲኖርበት 1:33*** የሚለው አንድ ጊዜ ቅጽበታዊ የሆነ መምጣት ብቻ ሳይሆን ከመጣ በኋላ በኢየሱስ ላይ መኖሩን፣ አብሮ መሆኑን ሲያስገነዝብ ነው። እርሱ መንፈስ የሚኖርበት ነው (ኢሳ 11÷1-2፤ 61÷1-)።

***1:33 በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው።*** የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበትን ተልዕኮ ያመለክታል። ይህ አብ የሰጠውን ተስፋ ተቀብሎ በበዓለ ሃምሳ ቀን ስለሚያፈሰው ብቻ ሳይሆን (ሐዋ 1÷8፤ 2÷4) የኢየሱስ ክርስቶስን አጠቃላይ አገልግሎት የሚያሳይ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በእርሱ ለሚያምኑት የዘላለም ሕይወት ሊሰጥ ነው። የዘላለም ሕይወትን ማግኘት መንፈስን ከመቀበል ተለይቶ አይታይም። ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ነውና። ዳግመኛ መወለድም በመንፈስ ነውና። የዮሐንስ መጥምቁ በውኃ ማጥመቅ የማዘጋጀት ወይም መንገድን የመጥረግ አገልግሎት ነው። ለንስሐ መንገድን የመጥረግና የማዘጋጀት አገልግሎት ነው። ይህ የኃጢአትን መታጠብ ወደፊት በሚመጣው መንፈስ ቅዱስ በሚያጠምቀው በመሲሁ በኩል የሚገኘውን የኃጢአት መታጠብ የሚያመለክት ነው። ይህ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው የኃጢአት ይቅርታን የሚሰጥ እንዲሁም የዘላለምንም ሕይወት የሚሰጥ እርሱ ነው።

ዮሐንስ ***አይቻለሁ መስክሬያለሁ*** እንደሚል እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉ ሁሉ ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ



እንዲመሰክሩ መንፈስ ያስችላቸዋል (1ቆሮ 12÷3)። «ኢየሱስ ጌታ ነው» ማለት የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ነውና።

***1÷35 ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ቆመው ነበር፦*** እነዚህ ደቀ መዛሙርት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ናቸው። እነርሱም፦ እንድርያስ (1÷41) እንዲሁም ዮሐንስ (የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ) ነበሩ። እነዚህ ሁለቱም ሰዎች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እስካመለከታቸው ጊዜ ድረስ መጥምቁ ዮሐንስንም ሲከተሉት ነበር። እነዚህ የዮሐንስ የነበሩ ደቀ መዛሙርት ለምን እርሱን ትተው ወደ ኢየሱስ ሄዱ? ይህ ዮሐንስ እንዲሆን የፈለገውና ትክክለኛውም አገልግሎት ነበር። እውነተኛው የዓለም ብርሃን በመጣ ጊዜ እርሱን ይከተሉ የነበሩ ሰዎች ወደሚበልጠው ወደ ኢየሱስ ይሄዱ ዘንድ ዮሐንስ ያመለክት ነበር። ከእርሱ ተከታዮች እንኳን ሳይቀር ወደ ኢየሱስ እንዲሄዱ ያደርግ ነበር። ዮሐንስ ለኢየሱስ መንገድን የሚጠርግ መንገድን የሚያሳይ ራሱ መንገድ ያልሆነ ሰው ነው።

***1÷36 ኢየሱስም ሲሄድ ተመልክቶ፦ እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ።*** ይህን ቃል ዮሐንስ መጥምቁ የሚነግራቸው ለራሱ ደቀ መዛሙርት ነው። ያ የምታዩት እውነተኛው መንገድ የምንጠብቀው መሲህ፤ ወደ እርሱ ሂዱ ማለቱ ነው። ስለሆነም ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ***ኢየሱስን ተከተሉት 1:37።*** ወዲያውም ከዮሐንስ ወደ ኢየሱስ ዘወር አሉ። ኢየሱስንም መከተል ጀመሩ። ***ኢየሱስም ሲከተሉት አይቶ ምን ትፈልጋላችሁ? አላቸው 1:38።*** ከዚያም መኖሪያውን በጠየቁት ጊዜ መጥታችሁ እዩ ብሎ ራሱ ይዟቸው ተመልሶ ሄደ። ***መጥተው የሚኖርበትን አዩ፤ በዚያም ቀን በእርሱ ዘንድ ዋሉ 1:40።*** ሁለቱ የዮሐንስ የነበሩ ደቀ መዛሙርት እንድርያስና ዮሐንስ የጌታ ደቀ መዛሙርት ሆነው ራሳቸውን ከመስጠታቸው በፊት አንድ ቀን ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አሳልፈዋል። በዚህ ቀን የሚኖርበትን ለማየት ነበር የሄዱት።

በሌላ ቦታ እንደምናየው «ለቀበሮዎች ጉድጓድ፣ ለወፎች መሳፈሪያ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም» (ማቴ 8:20፤ ሉቃ 9:58) እንዳለ የጌታ መኖሪያው የት እንደሆነ አልተገለጠም። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ከዋሉ በኋላ እንድርያስ ***መሢሁን አግኝተናል 1:42*** የሚል ነው። አብሮ በመዋል ያለ መረዳት ነው። የሚጠበቀውን መሢህ እንዳገኘ ቀድሞ የነገረው ለወንድሙ ለጴጥሮስ ነው። ወዲያው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ተገነዘበ። እንድርያስ ለወንድሙ ለመመስከር የቸኮለ ደቀ መዝሙር ነው።

መጥምቁ ዮሐንስ የራሱን ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን እንዲከተሉ ሲያመለክት የኢየሱስን ማንነት ሲገልጥላቸውና እንዲከተሉትም ሲፈቅድላቸው ወይም ሲተዋቸው ለተልዕኮው የነበረውን ታማኝነት ይገልጣል:: ከእርሱ ይልቅ ሲልቅ የሚገባው የተገባው ኢየሱስ በመጣ ጊዜ የላቀ መሆኑን በአንደበቱ ከመናገር በተጨማሪ የራሱንም ደቀ መዛሙርት ሳይቀር አሳልፎ ለእርሱ ይሰጥ ነበር:: በዛሬውም ዘመን አገልጋዮች፥ እረኞችም ሁሉ ሰዎችን መንከባከብ፤ ማሳደግ፤ መጠበቅ ተገቢ የመሆኑን ያህል ሁሉም ሰዎች ወደ ኢየሱስ እንዲመለከቱ፤ የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቃል:: ደቀ መዝሙር ማድረግ ለራስ ሳይሆን፤ ለጌታ ነው::

***1፥38 ኢየሱስም ... ምን ትፈልጋላችሁ? አላቸው::*** ለምን ኢየሱስን መከተል እንደፈለጉ እንዲያውቁና ለመከተላቸው ትክክለኛ ዓላማ እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል:: ኢየሱስን ለምን መከተል ፈለጉ? ይህ ጥያቄ ዛሬም ቢሆን ሁላችን የምንጠይቀው ጥያቄ መሆን አለበት:: ለምን ኢየሱስን መከተል ጀመርኩ? ለምን እርሱን እከተላለሁ? በዚህ መጽሐፍ በሌሎች ቀጣይ ምዕራፎች እንደምናየው ሰዎች ኢየሱስን ይከተሉት የነበሩት ስለ ብዙ ዓላማ ነው::

- አንዱ ዓላማ እርሱ ተአምር ሠሪ፣ ድንቅን የሚያደርግ ስለሆነ፤ ተአምራትና ድንቅን ለማየት፤
- ሌላው ደግሞ እርሱ ብዙዎችን ይመግብ ስለ ነበረ፣ ምግብ ፍለጋ፤
- ፈዋሽ ስለ ነበረ ለመፈወስ፤
- እንዲሁም ንጉሥ ስለ ሆነ መሪ፣ ምድራዊ መሪ እንዲሆንላቸው የፈለጉ ነበሩ::

ለተለያየ ዓላማ የተከተሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ:: ግን ብዙዎቹ ከእርሱ ጋር አልዘለቁም፣ አልቀጠሉም:: የሚከተሉበትን ዓላማ አጥርተው ያወቁ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያመኑና ከእርሱም ጋር ለመኖር የወሰኑት ግን እስከ መጨረሻ ዘለቁ:: ስለሆነም አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ያለበት ስለሚደረግለት ፈውስ፣ ስለሚያገኘው በረከት ወይም ስለሚያየው ድንቅ ነገር ሳይሆን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ አዳኝ፣ እውነት፤ እርሱ ብቻ መንገድ ስለሆነ በዚያ መንገድ በመሄድ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ሲሆን ይገባል::

አንተስ አንባቢ ሆይ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ትከተላለህ? ለምን ትከተለዋለህ? ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን የምንከተለው በትክክለኛው ምክንያት ማለትም እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፤ እርሱ መንገድ፤ እውነትና ሕይወት ስለሆነ ነውን?:: ይህን በማመንና በመቀበል ካልሆነ በስተቀር የምንከተለው እኛ ሳንሆን እርሱ



እንዲከተለን ልናደርግ ፈልገናል ማለት ነው:: ይህም ማለት ፍላጐታችንን እስካሟላልን፤ እስከደገፈን፣ «እስከባረከን» ድረስ እንከተለዋለን፤ ያን ካላደረገ ግን ውሳኔያችን ሌላ ይሆናል ማለት ነው::

***1፥42 አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና፦ መሢሕን አግኝተናል አለው::*** ከኢየሱስ ጋር ውሎ ሲመለስ የአንድርያስ የመጀመሪያ ተግባር ወንድሙን ማግኘት ነው:: ስምዖን በኋላ ጴጥሮስ የተባለውን ወንድሙን አግኝቶ የነገረው የሚጠበቀው መሢሕ (ክርስቶስ/ የተቀባ) ተገኝቷል የሚል ነበር:: ከነገረውም በኋላ ኢየሱስ ያለበትን አይቷልና ***ወደ ኢየሱስ አመጣው 1፡ 43::*** ስለ ኢየሱስ ነገረውና ወደ እርሱ አቀረበው፤ ልክ መጥምቁ ዮሐንስ (የአንድርያስ የቀደመ አስተማሪው) ሲያደርገው እንደ ነበረው ማለት ነው:: መጥምቁ ዮሐንስ አንድርያስን ወደ ኢየሱስ አመለከተው፤ አንድርያስም ወንድሙን ጴጥሮስን ወደ ኢየሱስ አመጣው:: እንድርያስ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ የሚያመጣ ደቀ መዝሙር ነበር:: ከዚህ ቦታ በተጨማሪ በ6፥4-9 እና በ12፥20-22 ባሉት ክፍሎች ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ያመለክት ነበር:: ወደ ኢየሱስ ያቀርብ ነበር::

***1፥43 አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ፤ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው፤ ትርጓሜውም ጴጥሮስ ማለት ነው::*** ጴጥሮስ ስምዖን ከሚለው የዕብራይስጥ ስሙ በግሪክ ኬፋ (አለት ወይም ጴጥሮስ) ወደሚለው ስም የተለወጠለት ገና ወደ ጌታ እንደመጣ ነበረ:: ይህም የስም ለውጥ ወደፊት ጴጥሮስ የሚሆነውን ሲያመለክት ነው:: በማቴ 16፥16-18 እንደ ተነገረው ጴጥሮስ ክርስቶስ በሚሠራት ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው [illegible] ነው:: በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስ እንደ አምድ የሆነ ሰው ነው (ገላ 2፥9፤ ኤፌ 2፥20፤ 1ጴጥ 2፥4-5)::

***1፥44 ኢየሱስ ... ፊልጶስንም አገኘና፦ ተከተለኝ አለው::*** እንድርያስና ዮሐንስ በመጥምቁ ዮሐንስ አመልካችነት ወደ ኢየሱስ መጡ:: ከእርሱም ጋር ሆነው የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሆኑ:: አንድርያስ ጴጥሮስን ወደ ኢየሱስ አመጣው:: ኢየሱስ ደግሞ ፊልጶስን በቀጥታ ተከተለኝ ብሎ ይጠራዋል:: አራተኛው ደቀ መዝሙር መሆኑ ነው:: ***ፊልጶስም ከአንድርያስና ከጴጥሮስ ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበረ 1:45::*** እነዚህ ሰዎች ምናልባት እርስ በእርስ የሚተዋወቁ ሲሆኑ ይችላሉ::

***1:45-46 ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ ... የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው::*** እንድርያስ ለወንድሙ ለጴጥሮስ እንደነገረው ሁሉ ፊልጶስ ደግሞ ለናትናኤል በተመሳሳይ ሁኔታ ይነግረዋል::

ፊልጶስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከገለጠው ቃል ማለትም ***ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን 1:46*** ሲል ፊልጶስ የመሢሁን ማንነት ከመጻሕፍት የተማረ፤ ያወቀና መምጣቱን የሚጠባበቅ ሰው እንደ ነበረ ያመለክታል:: ሙሴ ስለሚመጣው መሢህ በዘዳ 18፥15-18 ጽፏል:: ነቢያትም ስለዚሁ ነቢይ/መሲሕ ተናግረዋል:: እንዲሁም በሉቃ 3:23 እንደተገለጠው የዮሴፍ ልጅ ተብሎ ይታወቅ ነበረ::

ናትናኤል ኢየሱስን የጠየቀው ***ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? 1:47*** በማለት ነው:: በዚያን ዘመን ናዝሬት የሮም ወታደር ጦር ሠፈር የነበረባት ከተማ ነበረች:: ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ ናዝሬትን አይወዱም ነበር:: ናዝሬት የተናቀች ወይም የተጠላች ከተማ ነበረች:: በተጨማሪም መሢሑ የሚጠበቀው ከቤተ ልሔም ነው (ሚክ 5፥2) የሚለውን ያውቃሉ:: ኢየሱስም የተወለደው በቤተ ልሔም ነው::

***1፥47 መጥተህ እይ፦*** የሚጠበቀው መሢህ ኢየሱስ እንደሆነ ፊልጶስ እርግጠኛ ስለሆነ ራስህ በመምጣት አረጋግጥ በማለት ለናትናኤል ይመልስለታል:: ከእርሱ ጋር ለመከራከር ወይም ለማስረዳት ጊዜ አልወሰደም:: ወደ ኢየሱስ የመጣ መልሱን ራሱ በቀጥታ ያገኛልና ***መጥተህ እይ*** ወይም ራስህ ወስን የሚል ነው:: ይህ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የማቅረቢያ ጥሩ መንገድ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ሲነገራቸው የተለያዩ ጥቃቅን ጥያቄዎችን ሊያነሱ ይችላሉ:: ብዙ ማስረጃም ይፈልጉ ይሆናል:: ከፊልጶስ የመመስከሪያ መንገድ የምናስተውለው ግን ሰዎችን ወደ ራሱ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማስጠጋትና ራሳቸው እንዲወስኑ መምከር የተሻለ መሆኑን ነው:: እንዳለውም ናትናኤል ራሱ ወሰነ:: እውነት መሆኑንም አረጋገጠ:: ከናዝሬት መልካም ነገር አይወጣም በሚለው ብቻ ተይዞ ቢቀር ኖሮ ናትናኤል መሢሁን ባላወቀውም ነበር::

የፊልጶስን ምክር ሰምቶ ግን ወደ ኢየሱስ በመምጣቱ ኢየሱስን ባገኘው ጊዜ ***መምህር ሆይ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ! አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ! 1:50*** በማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በትክክል ይገልጣል:: እነዚህ ወደ ጌታ የመጡት የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ስለ ኢየሱስ ከተናገሩት መካከል:-

- ***መሲሕ 1:42!***
- ***የናዝሬቱ ኢየሱስ 1:46!***
- ***መምህር 1:50!***
- ***የእግዚአብሔር ልጅ 1:50!***
- ***የእስራኤል ንጉሥ 1:50*** ብለውታል::



ስለሆነም እነዚህ ደቀ መዛሙርት የዮሐንስ የነበሩትና ሌሎችም ስለሚመጣው የዓለም አዳኝ የሚያውቁት ነገር ብዙ እንደ ነበርና ይጠባበቁም እንደ ነበር ነው::

እነ እንድርያስና ዮሐንስ የኢየሱስ ተከታዮች የሆኑት በአስተማሪያቸው በመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት አማካይነት ነው:: የእንድርያስ ወንድም የሆነው ጴጥሮስ የጌታ ተከታይ የሆነው በወንድሙ በእንድርያስ ምስክርነት ነው:: ፊሊጶስ ደቀ መዝመር የሆነው ኢየሱስ እንዲከተለው ስለ ጠራው ነው:: ናትናኤል ደግሞ ተከታይ የሆነው በፊልጶስ ምስክርነትና ጌታ ስለ እርሱ በገለጠው መሠረት ነው:: ይህ የምስክርነት ሁኔታ ለወንጌል ስርጭት ጥሩ ምሳሌ ወይም ሞዴል ይሆናል:: እንደኛው ያወቀውን ለሌላው ማሳወቅ፤ ከቤተሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ጌታን ሲያገኝና ሲያውቅ ና! ***መጥተህ እይ*** ማለት:: እንዲህ ዓይነት አገልግሎት አንድ ለአንድ አገልግሎት ሊባልም ይችላል:: አንድ ሰው ለአንዱ መንገር፤ አንድ ሰው ከቤተ ሰቡ ውስጥ ለሌላው ማሳወቅ ጥሩ ወንጌልን የመመስከሪያ መንገድ ነው::

***1፥48 ተንኰል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ፦*** ኢየሱስ ናትናኤልን እንዲህ ብሎ የተናገረው ገና ወደ እርሱ እንደመጣ ነበረ:: የናትናኤልን ማንነት ማን ነገረው? እንዴትስ አወቀ? እስራኤል የተጠራው የእግዚአብሔር ወገን እንዲሆን፤ ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆን ነበር (ዘጸ 19:5):: እስራኤላውያን ግን ይህን ጥሪያቸውን አላከበሩም:: በየዘመናቱ የተነሱትን ነቢያት የገደሉ፤ በአመጽ የሄዱ ናቸው:: ከእነርሱ መካከል ግን እንደ ናትናኤል ዓይነቶች ጥቂት እንደ ነበሩ ያመለክታል::

***1፥49 ፊልጶስ ሳይጠራህ፥ ከበለስ በታች ሳለህ፥ አየሁህ::*** የናትናኤልን የውስጥ ባሕርይ ብቻ ሳይሆን የተጠራበትን ጊዜና የነበረበትን ቦታ ሁሉ ኢየሱስ እውቋል:: እርሱ በጊዜ ላይ፣ በቦታ ላይ፣ በእውቀት ላይ ጌታ ነው:: እውቀቱ ሙሉ ነው:: ጌታ ኢየሱስ እኛንም ያውቀናል:: ባለንበት ቦታ በማንኛውም ጊዜ የውስጥ ማንነታችንን እርሱ ያውቃል:: እመጸኛ ና በተንኰል የምንኖር ብንሆንም እርሱ ያውቀናል::

***ከበለስ በታች አየሁህ*** የሚለው አገላለጽ፤ በቀደመው የአይሁድ አገላለጽ መሠረት መጽሐፍን (ብሉይ ኪዳንን) ስታነብ ወይም ቃሉን ስታጠና አየሁህ የሚል መረዳትን ይሰጣል::[14]

---

[14] According to Jewish tradition, the expression <to sit under the fig tree> was a euphemism for meditating on the Scriptures. Thus Jesus

የጌታ ደቀ መዛሙርት መጻሕፍትን ሕግና ነቢያትን የሚያውቁ ስለ ነበሩ ጌታ በመጣ ጊዜ አብረውት ሲሆኑ ማንነቱን ለመለየት አልተቸገሩም:: ወዲያው በተገቢው ስም ይጠሩታል:: ከመጽሐፍ የተነገረለትን መጠሪያም ጠርተው ይገልጹታል:: ስለሆነም ናትናኤል ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ (መዝ 2:7)፤ የእስራኤል ንጉሥ (መዝ 2:6፤ ሶፎ 3:15) እንደተባለ ያውቃል::

***1፥51 ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ::*** ቅን ሰው ናትናኤል ጌታን ባየው ጊዜ በአንድ ቀን ብዙ ተደነቀ፤ በመጻሕፍትም የጠበቀው ተሟላለት፣ ደስም አለው:: ***ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ*** የሚለው መልስ ከጌታ ጋር የሆነ ሁልጊዜም ካየው የበለጠ ነገርን በማየት ይቀጥላል ማለት ነው:: ለጌታ ነገር መጨረሻ ወይም ገደብ የለውም:: ማደግ:- ወደ እርሱ ሙላት ልክ ማደግ ነውና፤ ጌታ ሁልጊዜም ሰውን ያስደንቃልና በመደነቅ ትቀጥላለህ ሲለው ነው::

***1፥52 ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወርዱና ሲወጡ ታያላችሁ አለው::*** ይህ ያዕቆብ ካየው ራእይ ጋር ተመሳሳይነት ያለው አገላለጽ ነው (ዘፍ 28:12-):: ያዕቆብ ከቤቱ ወጥቶ አባቱንም አታልሎ፣ በረከትን ከተቀበለ በኋላ በመንገድ ላይ በሕልሙ መላእክት ሲያገለግሉት ይመለከታል:: በዚህ ክፍል የምንረዳው ለናትናኤልና ለሌሎችም ሰማይ ይከፈትላቸዋል:: እነርሱ ራእይና መገለጥ ከሰማይ የሆነ ነገርን ያያሉ (ሐዋ 10:11፤ ራእ 4:1፤ 19:11) እና ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ በሰማይና በምድር መካከል የመገናኛ መስመር ወይም መሰላል እንደሆነ ያሳያል:: ወደ ሰማይስ ማን ይወጣል፤ ከሰማይስ ማን ይወርዳል? (3:13) ከአንዱ ከእግዚአብሔር ልጅ በስተቀር::

የሰማይ መከፈት እግዚአብሔር የሚያደርገው ታላቅ በረከት ነው:: እግዚአብሔር ሰማይን ከፍቶ ልጁን ይልካል፤ በረከትን ይልካል፤ ወደ ሰማይም መገናኘት የሚቻለው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ይመስገን::

---

had seen Nathaniel studying the scriptures before Philip had called him to come and see Jesus. Ibid. p.27.



# ምዕራፍ ሁለት

በምዕራፍ ሁለት ጌታ ኢየሱስ የሠራውን ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መቀየር የመጀመሪያ ምልክት ወይም ተአምር እናያለን:: ***ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊና ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ 2፥11::***

***2፥1 በገሊላ ቃና ሠርግ ነበረ::*** በቀደመው የአይሁድ ባሕል አንድ ሠርግ ለአንድ ሳምንት ያህል ጊዜ ይቆያል (ዘፍ 29:27-28):: በዚያ ሠርግ የኢየሱስም እናት ነበረች:: የወይን ጠጅ እንዳለቀ መጀመሪያ የተገነዘበችው እርሷ ነች::

***2፥3 የወይን ጠጅ እንዳለቀም ባወቀች ጊዜ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም:-*** በማለት ማርያም ለኢየሱስ ትነግረዋለች:: ወደዚህ ሰርግ ኢየሱስም፣ ደቀ መዛሙርቱም ታድመው ነበር:: በቀደመው ባሕል መሠረት በአንድ ከተማ ሰርግ ሲደረግ በከተማው የሚኖረው ሕዝብ ወይም በአካባቢው ያለው ሁሉ ወደ ሰርግ ስለሚጠራ ሲሆን ይችላል ጌታ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ሰርጉ የታደሙት:: በሰርግ መካከል ለእድምተኞቹ የሚሆን በቂ መጠጥ ባይዘጋጅ ወይም በድንገት በመካከል ቢያልቅ ለአዘጋጆቹ በጣም የሚያስደነግጥና የሚያሳፍር ነገር ነው:: ስለዚህ የጌታ እናት ሁኔታውን ተረድታ ኢየሱስ አንድ ነገር እንዲያደርግ ትጠይቀዋለች:: ማርያም ኢየሱስን ***የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም 1:3*** ስትለው እንዲኖራቸው አንድ ነገር እድርግ ማለቷ እንደሆነ ግልጽ ነው:: ስለሆነም ለችግሩ ከእርሱ ዘንድ መፍትሔ እንደሚኖር እውቃለች ማለት ነው::

እዚህ ላይ ስለ ጌታ ማንነትና በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ስለ ነበረውም ድርሻ ማየት እንችላለን:: ጌታ ወንጌልን ለመስበክ እና ለዓለም መድኃኒት ለመሆን በእብ የተላከ ነው:: ይህን ሲፈጽም ሳለ በማኅበራዊ ኑሮም ውስጥ በኅብረተ ሰቡ መካከል የሚገኝባቸውም ሁኔታዎች ነበሩ:: ወደ ሰርግም ተጠርቶ በዚያ በመገኘት ክብሩን ገልጧል:: በሚገኝባቸው ቦታዎችና ሁኔታዎች የተላከበትን ዓላማ ይፈጽማል:: እንዲሁም የአገልግሎት ጠቅላላ ዘመኑ አጭር (ሦስት ዓመት ተኩል ያህል) ስለሆነ በዚህ ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አገልግሎ «ተፈጸመ» ለማለት የሚቸኩል ቢሆንም በሰርግ ለመገኘት ሳይቀር ጊዜ ነበረው::

***2፥4 ኢየሱስም አንቺ ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት::*** ኢየሱስ የማርያም ልጅ ነው:: ስለዚህ ማርያም

ልጁን አንድ ነገር አድርግ ብላ ስትጠይቀው ወዲያው አንድ ነገር እንዲያደርግ እንጠብቃለን:: ***ከአንቺ ጋር ምን አለኝ*** የሚለው የጌታ መልስ የሚያመለክተው እኔ የመጣሁት አባቴ ለላከኝ ተልዕኮ ነው፤ ያንን ተልዕኮ የምፈጽመው እርሱ በሰጠኝ የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ነው እንደ ማለት ነው:: በጊዜው ላደርግ የሚገባኝን ያንኑ በዚያው ሰዓት፣ በዚያው ጊዜ አደርጋለሁ፣ በእርሱ እንደታዘዝኩት አደርጋለሁ ማለት ይሆናል:: ስለሆነም ከአባቱ ከአብ ዘንድ የተሰጠው የሥራ ዝርዝርና ሁኔታ ከእናቱ ከሚሰጠው ወይም ከሚጠየቀው የተለየ እንደሆነ ያመለክታል:: ሰዎች አንድ ነገር እንዲያደርግ በጠየቁት ጊዜ ወይም እንዲሆን ሲፈልጉ እርሱ የሚሠራው በሰዎች ምኞትና ፍላጐት ሳይሆን በአባቱ ፈቃድና ጊዜ መሠረት እንደሆነ ያመለክታል:: ስለሆነም ሌላም ጊዜ፣ ጊዜዬ አልደረሰም እያለ ተናግሯል፤ (7÷3-6፤8፣30፤ 8÷20፤ 12÷23፤ 13÷1፤ 17÷1)::

***ጊዜዬ ገና አልደረሰም 2÷4፤*** የሚለው በዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታይ አንድ ጉልህ ሀሳብ ነው:: የሚያመለክተውም የእርሱን የመክበሪያ ጊዜ በተለይም ሞቱንና ትንሣኤውን ነው:: ይህም የሚያሳየው ጌታ አገልግሎቱን የሚያከናውነው ከጊዜ አንጻር እንደ ሆነና ሁሉም አገልግሎቱ ወደዚያ አቅጣጫ፣ ወደዚያ ማሟላት እንደሚሄድ ነው::

***2÷5 የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው::*** ማርያም አንዳች ነገር እንዲያደርግ ኢየሱስን ከጠየቀችው በኋላ ምን እንደሚያደርግ አልነገራትም:: ነገር ግን እርሱ ***የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ*** ብላ ለአገልጋዮች ትነግራቸዋለች:: ምንድነው የሚያደርገው ብሎ ከመጠየቅ በፊት እርሱ የሚያዘውን ለማድረግ መዘጋጀት ይህ የእምነት እርምጃ ነው:: እግዚአበሔር በሕይወታችን ያለውን ዓላማ ዝርዝር አስቀድሞ ላይነግረን ይችላል:: እግዚአብሔር ሲያደረግ የሚወደውን አስቀድሞ ባይነግረንም እርሱ የሚያደርገው ትክክልና መልካም ስለሆነ የሚሰንን እያደረግን ምን እንደሚያደርግ ልብ በማድረግ ማየት ይገባናል:: ስለዚህ አስቀድሞ መታዘዝና በመታዘዝ የሚገኘውን ውጤት መመልከት ዋጋ አለው::

***2:6 የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር::*** የአይሁድ የማንጻት ልማድ ምግብ ከመብላታቸው በፊትና በኋላ እጆቻቸውን የሚታጠቡበት ሥርዓት ነው (ማቴ 15÷1-2):: ማናቸውምን ነገር መንካት ያረክሳል የሚል አስተሳሰብም ስለ ነበረ ያልታጠበ ሰው ያልነጻ ወይም ርኩስ እንደሆነ ይቆጠራል:: እነዚህ ጋኖች ***እያንዳንዳቸው ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር 2÷6፡***



***2÷7 ኢየሱስም ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው::*** ጋኖቹ ባዶ በመሆናቸው ተጋባዦቹ የሚጠጡት አልነበራቸውም:: ማርያምም ባዶነታቸው እንዲቀየር አንድ ነገር ጌታ እንዲያደርግ ጠይቃዋለች:: ጌታ ***ውኃ ሙሉአቸው*** ይላል:: እነርሱም ውኃ ሞሉአቸው:: ማርያም የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ እንዳለቻቸው ማድረጋቸው ትልቅ የእምነት እርምጃ ነው:: ምክንያቱም ኢየሱስ ጋኖቹን እንዲሞሏቸው ያዘዘው በውኃ ነውና ውኃ ደግሞ ለእድምተኞች የሚሆን መጠጥ አይደለም:: የመጀመሪያው እርምጃ ለተአምራቱ መንገድን ያዘጋጃል::

ጌታ የሰጣቸውን ትዕዛዝ ተከትለው አገልጋዮቹ ***እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው 2÷7::*** እስከ አፋቸው በመሙላታቸው በውኃው ላይ ሌላ የሚጨመር ነገር እንዲገባበት ቦታ አላስተረፉም:: ስለዚህ የተሞላው ሙሉ በሙሉ ውኃ ነበር:: ውኃው ወደ ወይን ጠጅ ተቀየረ::

ኢየሱስ ባዶ ጋኖችን እንዲሞሏቸው ሲያዝ እርሱ ከሙላቱ ባዶን ነገር (ባዶን ሕይወት) የሚሞላ እንደሆነ ያመለክተናል:: እርሱ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ባዶውን የሚሞላ ነው:: ጌታ ጉደሎውን ሲሞላ እስከ አፉ ድረስ ጢም አድርጎ፣ አትረፍርፎ ነው::

ባዶ እንስራ በውኃ ተሞልቶ ውኃው ወደ ወይን ጠጅ በመለወጡ ተአምር ሂደት ውስጥ የአገልጋዮቹ ድርሻ ትልቅ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ወይን ጠጁን በሌላ መንገድ እንዲገኝ ማድረግ ቢወድ ይቻለዋል:: እንዲሁ ከመሬት ቢያፈልቀው፤ እንደ መና ከሰማይ ቢያዘንበው፤ በነፋስ እንዲመጣ ቢያደርግ፣ ሌላም መንገድ ቢጠቀም እርሱ በሁሉም ላይ ጌታ ነው:: በዚህኛው ተአምር ግን ሰዎች በአፈጻጸሙ ሂደት ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው አድርጎአል:: ሰዎች እርሱ በሚሠራው ድንቅ ሥራ ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ የእግዚአብሔርን መልካምነት ያሳያል:: ለሰዎች ደስታና በረከት ይሆን ዘንድ በዚህ አገልግሎት ውስጥ ሰዎች ድርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ጋኖቹን ውኃ የመሙላት ድርሻ ለራሳቸው ጥቅም ነው:: እነርሱ ያንን ባያደርጉ ጌታ ራሱ በወደደው መንገድ ጋኖቹን ውኃ ሊሞላ ይችላል:: በአጠቃላይ በአገልግሎት የአገልጋዮች ድርሻ እንደ እነዚህ ሰዎች መሙላት ነው:: ጌታ ያሰበውን የሚፈጽምበት የራሱ መንገድና ሥልጣን ሁልጊዜ አለው:: ቢያደርጉት ተአምር ያያሉ፣ ደስ ይላቸዋል፣ የሥራውም ተካፋዮች ይሆናሉ::

***2÷10 መልካሙን የወይን ጠጅ፡-*** አሁን በጌታ ቃል የተዘጋጀው የወይን ጠጅ ቀድሞ መሸራውና እድምተኞቹ ይጠጡት ከነበረው የወይን ጠጅ መልካም የሆነ፣ ጥሩ ጣዕም ያለው ሆኖ ተገኘ:: ይህ ምልክት በአንድ በተወሰነ የሰው ፍላጐት ወይም ችግር ላይ የተገለጠ የእግዚአብሔር

ኃይልና ሥልጣን ነው። በዚህ ምልክት (ተአምር) ውስጥ በአንድ ጊዜ የተፈጸመው ብዙ ነገር ነው። ባዶው መሞላቱ፣ የተሞላው ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ፣ የተሠራው ወይን ጠጅ ደግሞ መልካም መሆኑ። ጌታ የሚያደርገው ነገር ሁሉ መልካም ነው። የእርሱ ቃል ያለበት፣ የእርሱ ሃሳብ ያለበት በእርሱ ትእዛዝ የተፈጸመ ነገር እጅግ ያማረ ነው።

***2፥10 አስቀድም መልካሙን ... በኋላ መናኛውን፡-*** ይህ የሰው ሥራ ነው። መጀመሪያ መልካም በሚሆን አጀማመር ጀምሮ በውስጡ መልካምነት ስለሌለ መናኛ ይሆናል። ሕይወትም እንዲሁ ነው። መልካም የጉብዝና ወራት ወደ እርጅና ይለወጣል። በጉብዝና ወራት ጌታን ያወቀ ሰው በመልከም ሽምግልና ይጨርሳል ያለዚያ ሕይወቱ ከንቱና መናኛ ይሆንበታል። በሕይወት መካከል ኢየሱስ ሲመጣና ባዶውን ሲሞላ መጨረሻውን መልካም፤ የሚጣፍጥ፣ ያማረ እድርጐ ይቀይረዋል። ኢየሱስ ሕይወትን ከመናኛነት ወደ ጣፋጭነት፤ ከከንቱነት ወደ መልካምነት ይቀይራል።

***2፥9 ከወዴት እንደመጣ አላወቀም፡-*** ያ የሰርግ ጊዜ እጥረት፣ ባዶነት የተሞላበት ጊዜ ነው። አሁን ግን ለማንጻት የሚውሉ ጋኖች እንኳ ተሞልተው እጥረቱ ወደ መትረፍረፍ ተለውጧል፤ መልካም የወይን ጠጅም ለእድምተኞቹ እየቀረበ ነው። ይህ የወይን ጠጅ ከወዴት እንደ መጣ አሳዳሪውና ሙሽራው አለማወቃቸው፤ ይልቁንም እንዴት እንደ አለመጠየቃቸው ያስገርማል። መልካም ነገር ሆኖላቸው ተገኘ፣ ***ከወዴት እንደመጣ*** አላወቁም። የመልካሙ ነገር ተጠቃሚዎች የመጣበትን ምንጭ ግን አላወቁም። እንዲሁ የብዙ ሰዎች አኗኗር ይኸው ነው፡- በተፈጥሮ ሕይወት የሰጣቸውን ጌታ አለማወቅ።

***2፡11 ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ። ደቀ መዛሙርትም በእርሱ አመኑ።*** የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር በሙላት የሚገለጠው ወደፊት በሚሆነው በሞቱና በትንሣኤው ሆኖ እንዲሁም በሚያደርጋቸው ምልክቶች (ተአምራት) ክብሩን ይገለጥ ነበር። ምልክቶቹ የእርሱን ማንነት ማለትም ሁሉን ቻይነቱን፤ በሁኔታዎችና በተፈጥሮም ላይ ታላቅነቱን የሚገልጹና ክብሩን የሚያሳዩ ነበሩ።

ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ካደረጋቸውና በአራቱም ወንጌሎች ከተጻፉት 35 ያህል ምልክቶች (ተአምራት) መካከል የመጀመሪያው ነው። ይህም ምልክት የተገለጠው በዮሐንስ ወንጌል ብቻ ነው። ይህ ምልክት የተደረገበት ዋና ዓላማ ጌታ ኢየሱስ ክብሩን ለመግለጥ ነው።



ጌታ ያደረጋቸው ተአምራት ሁሉ፣ አንድን ሁኔታ ማለትም እጦትን (ችግርን) ከማቃለል፤ በአካል ላይ ያለ ጉድለትን ከመሙላት፣ በሽተኛን ከመፈወስ ወይም ረሃብን ከማስገወድ እና ከማጥገብ ያለፈና የላቀ ዓላማ አላቸው። ተአምራቱ ጌታ ኢየሱስ ለእያንዳንዱ ሰው በእያንዳንዱ ሁኔታ ያለውን ታላቅ ፍቅርና ርኅራኄ ያሳያሉ። ሁሉም የሰውን ችግርና ፍላጐት ከማሟላት በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጡ ናቸው። ይህም ሰዎች የእርሱን ማንነት በመረዳት እንዲያምኑና የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኙ የሚመራቸው ነው።

ኒቆዲሞስ «እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሲያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን» (3:2) እንዳለው ምልክቶቹ የእርሱን ማንነትና ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱን የሚያሳዩ ነበሩ። የሚያደርጋቸው ምልክቶች እርሱ ፈጣሪ ወይም የፈጠረውን የሚያድስ እንደሆነም ያሳያሉ። ለምሳሌ እውር ሆኖ ለተወለደው ሰው ብርሃንን ሲሰጠው (እንዲያይ ሲያደርገው) እንደገና መፍጠሩ ነው። ሽባውን ቀጥ ብሎ እንዲቆም ሲያደርገው እርሱ በሰው አካል (ጤንነት) ላይ ጌታ እንደሆነ ያሳያል። የሚፈጥር እንዲሁም የሚያድስ ጌታ ነው።

ጌታን ይከተሉት የነበሩት ግን ተአምራት የሚደረግበትን ዋና ዓላማ ይስቱ ነበር። ለምሳሌ በ6፥14-15 እንደምንመለከተው ሰዎች ንጉሥ ሲያደርጉት ፈለጉ። እርሱ ከዘላለም ንጉሥ ነው። ወደ ምድር የመጣው ግን ንጉሥ ለመሆን ወይም በሰዎች ላይ ለመንገሥ ሳይሆን መሢሕ፣ አዳኝ ሆኖ፤ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ነው። በሮም ቅኝ ግዛት ውስጥ ስለ ነበሩ፤ ከቅኝ ግዛት ነፃ እንዲወጡ የሚመራቸውን ጦረኛ መሪ፣ የጦር መሪ ወይም ንጉሥ ይፈልጉ ነበረ። እንዲህ ያለ የተሳሳተ መረዳት ኖሮአቸው ወደ እርሱ ሲቀርቡ እነርሱን ትቶ ይሄድ (ይለይ) ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ያደረጋቸው ምልክቶችና ተአምራት የእርሱን ማንነትና ክብር የሚገልጹ ነበሩ። የምልክቶቹን ዝርዝርና ምን ጥቅም ወይም ትርጉም እንዳላቸው እንደሚከተለው ከዚህ በታች እንመለከታለን።

1. ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ (2:1-11)፡- በዚህ ኢየሱስ ክብሩን ገለጠ። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርትም በእርሱ አመኑ። ይህ የኢየሱስን መናኛውን ማጣፈጥ፤ ጣዕም የሌለውን ጣዕም የመስጠት ኃይል ያሳያል።

2. ከንጉሥ ቤት የሆነውን ሹም ልጅ ፈወስ (4÷46-54):- በዚህ ርኅራኄን ለአይሁዳዊ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም አደረገ። በዚህም ስውዬው/ሹሙ ከነቤተሰቡ በእርሱ አመነ። ልጁ የተፈወሰበትን ሰዓት ጠይቆ እንደተረዳው፣ ጌታ ልጅህ ተፈውሷል ባለበት ጊዜ ነበርና፣ ኢየሱስ በቦታና በጊዜ የተገደበ እንዳይደለ ስለ እርሱ ማንነት ይገልጣል። ኢየሱስ የጊዜና የቦታ ጌታ ነው።

3. ኢየሱስ ሽባውን ፈወሰ (5÷1-16):- ይህም ኢየሱስ በበሽታ ላይ፣ በአካል ጉዳተኝነት ላይ ሁሉ ሥልጣን እንዳለው ያሳያል።

4. ኢየሱስ አምስት ሺህ ሕዝብ መገበ (6: 5-14):- ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ፍላጐት ሁሉ የማሟላት፣ ጥቂቱንም የማብዛት ሥልጣን፣ ኃይል እንዳለው ያመለክታል።

5. ኢየሱስ በውኃ ላይ ሄደ (6÷17-21):- ይህም በተፈጥሮ ኃይላት ላይ፣ በውኃ፣ በማዕበል፣ በነፋስ፣ በወጀብ፣ እና በአጠቃላይ በተፈጥሮ ላይ ሥልጣን እንዳለው ያሳያል።

6. ኢየሱስ ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የነበረውን ፈወሰው (9:1-7):- ይህም ኢየሱስ በመወለድ በሚመጡ ችግሮችና በአጠቃላይ «በዕድለ ቢስነት» ላይ ኃይል እንዳለው፣ እንደገና መፍጠር፣ መሥራት ወይም ማደስ እንደሚችል ያመለክታል።

7. ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሣው (11:1-45):- ይህም ኢየሱስ በሞት ላይ ሥልጣን እንዳለው ያሳያል።

8. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እጅግ ብዙ ዓሣ እንዲያጠምዱ አደረገ (21:1-14)። ይህም ኢየሱስ በተፈጥሮ ላይ በባሕር፣ በየብስ፣ በየትኛውም ስፍራ ባለ ሁሉ ላይ እውቀትና ሥልጣንም እንዳለው ያመለክታል።

***2፥11 ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።*** የምልክት ወይም ተአምራት የማድረግ አንዱ ዓላማ ሰዎች ወደ እምነት እንዲመጡ ነው። በተደረገው ምልክት ተደንቀው እንዲቀሩ ብቻ ሳይሆን፣ ይህን ወዳደረገው ጌታ እንዲጠጉ እምነታቸውንም በእርሱ ላይ እንዲያኖሩ ለመርዳት ነው። ጌታ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ እንደለወጠ ባዩ ጊዜ

በተፈጥሮ ላይ ሥልጣን ያለው ጌታ መሆኑን በመረዳት ደቀ መዛሙርትም በእርሱ አመኑ[15]::

***2+12 ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፡-*** ቅፍርናሆም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተደጋጋሚ የቆየባት ከተማ ነች:: ቅፍርናሆም ስለ ብዙ ነገር ትታወቃለች:: ደቀ መዝሙር እንዲሆን ጌታ ማቴዎስን የጠራው ከቅፍርናሆም ነበር (ማቴ 9:9):: የብዙ ደቀ መዛሙርትም ቤት እዚያ ነበር (ማቴ 4:13-19):: በጊዜው የነበሩ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ቤትም እዚያ ነበር (ማቴ 4÷46):: ሆኖም በዚያ ከተማ የነበሩ ሰዎች የማያምን ልብ ነበራቸውና ጌታ ገስጿቸዋል (ማቴ 11:23፤ ሉቃ 10:15)::

***2+13 የአይሁድ ፋሲካም፡-*** ፋሲካ በዓመት አንድ ጊዜ ኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅደስ የሚደረግ በዓል ነው:: ለፋሲካ እያንዳንዱ አይሁዳዊ ወንድ ሁሉ ወደዚህ ቦታ እንዲሄድ ይጠበቃል (ዘዳ 16÷16):: ፋሲካው የአንድ ቀን ቢሆንም በዓሉ አንድ ሳምንት የሚፈጅ ነው:: በዚህ አንድ ሳምንት አይሁድ እባቶቻቸው በግብፅ ምድር በባርነት የኖሩበትን ሁኔታና እግዚአብሔር ከዚያ እንዴት ነፃ እንዳወጣቸው የሚያስቡበት ጊዜ ነው (ዘጸ 12:1-14)::

***2+14 በመቅደስ፡-*** ይህ ሰሎሞን ያሰራው ቤተ መቅደስ በባቢሎናውያን ከፈረሰ በኋላ (2ነገ 25):: ከምርኮ የተመለሱት በዘሩባቤል መሪነት እንደገና ያሠሩት ቤተ መቅደስ ነው:: ሁለተኛው ቤተ መቅደስ እንደገና የተሠራው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ515 ዓ.ዓ አካባቢ ነው:: ከዚያም ጌታ በመጣ ዘመን ቤተ መቅደሱ ታድሶ ነበረ፤ ይህ ቤተ መቅደስ የሚገኘው በኢየሩሳሌም ነው::

***2+14 በሬዎችና በጎችን ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ::*** በዘዳ 12÷5-7 እንደተገለጠው እያንዳንዱ መሥዋዕት አቅራቢ ከራሱ መንጋ መካከል ነውር የሌለበትን እንስሳ በማምጣት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ታዘው ነበር:: ወደ ኋላ ግን መሥዋዕት አቅራቢው ለመሥዋዕት የሚሆነውን ገዝቶ እንዲያቀርብ እዚያው ቤተ መቅደስ አካባቢ ገበያ እንዲኖር ካህናት ሕግ አውጥተው ነበረ:: ይህ ምናልባት እንስሳ ለሌላቸው ወይም በተለያየ ምክንያት ለማምጣት ለማይችሉት በቅርበት እንዲያገኙ በማለት አስበው ይሆናል:: ይሁን እንጂ ይህ ቀስ በቀስ ገበያው ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲገባ የአምልኮውን ቦታ እንዲይዝ አደረገው:: ቤተ መቅደሱንም ገንዘብ

[15] <The belief manifested by the disciples at this time was progressing but not complete.>. Tenny, Ibid.

የሚለወጥበትና እንስሳት የሚሸጡበት ገበያ እስኪመስል ድረ
ለወጠው:: በዓሉን ለማክበር ከተለያዩ ሀገሮች ወደ ኢየሩሳሌ
የሚያመጡትን የተለያየ ሀገር ገንዘብ ለዋጮች ወደ እስራኤላዊ
ገንዘብ ይለውጡ ነበር:: በዚህ ውስጥ ግን ቅንነት የሌለበት አሠራ
ጉልቶ እንደ ነበረ ማገናዘብ ይቻላል:: ይልቁንም መቅደሱ ወደ ገበያነ
በመለወጡ የአምልኮ ቦታው የንግድ ቦታ ሆኗል::

***2፥15 የገመድም ጅራፍ አበጅቶ:-*** መሲሑ በመጣ ጊዜ ቤቱ
እንደሚያጠራ በሚል 3:1-3 ተነግሮ ነበረ:: ጌታ ኢየሱስ ወደ ቤ
መቅደስ ሲመጣ ከሌላው ሰው በተለየ ሁኔታ የቤቱን መቆሸ
አስተዋለ:: ሌላው ሕዝብ ሁሉ ካህናቱን ጨምሮ እንደ ልማ
አድርገው ይቆጥሩት የነበረውን ሁኔታ ለእርሱ ግን መጽዳት (መወገድ
ያለበት የቆሸሸ ቦታ እንደሆነ አየ:: ***በጐችንም በሬዎችንም ከቤ
መቅደስ አወጣቸው፤ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ 2:15::*** ጌታ
ያስቆጣው ነገር ቤተ መቅደስ የንግድ ቦታ ስለሆነ ነበር:: የተሠራበት
ዓላማ የሳተና ለሌላ አገልግሎት በመዋል ላይ ያለ እንደሆነ ተመለከተ
እርምጃም ወሰደ:: ያወጣቸው ከመቅደስ ነበረና ገበያው በመቅደ
ውስጥ ነበረ፤ በጐቹ መቅደስ ውስጥ ለሽያጭ ቀርበው ነበር::

የፋሲካ በዓል እስራኤላዊ ሁሉ እርሾን ከቤቱ የሚያስወግድበት ጊ
ነው:: እርሾ ሊገኝ አይገባውም (ዘጸ 12:17-20):: እርሾ የኃጢአ
ምሳሌ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌ
ቤተ መቅደስ ተገኝቶ ቤቱን ማጽዳቱ እዚያ ላሉትም ሁሉ ስለማጽዳ
በምሳሌያዊነት የሚያስተምር ነው:: ኃጢአት ኢየሱስ ክርስቶስ
ያስቆጣዋል:: ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ስለሚኖረ
አምልኮ ግድ ነበረው፤ ቅንዓትም ነበረው:: እግዚአብሔር ንፁህ አምላ
ነውና የእርሱ ቤተ መቅደስ ለእርሱ አገልግሎት ብቻ ሊው
ይገባዋል::

ጽድቅን የሚወድ አመጽን ይጠላል፤ ጽድቅን የሚወድ በኃጢአት ላ
ይቆጣል:: ይህ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይ ነው፤ ማስመሰ
ወይም መቻቻል ሳይሆን ኃጢአትን ማስወገድና ቤትንና ሕይወት
ማጽዳት ያስፈልጋል:: በኃጢአት ላይ የማይቆጣ አገልጋይ የጌ
<u>ባሕርይ ያለው አገልጋይ አይደለም</u>::

በአዲስ ኪዳን የአማኞች ሰውነት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደ
ስለሆነ እያንዳንዱ አማኝ ሰውነቱን በንጽህና፣ በጽድቅ ሲጠብቅ
እግዚአብሔርን በሚያከብር ሁኔታ ሊይዘው ያስፈልጋል:
እግዚአብሔርን ከማያከብር ነገር ጋር ሰውነቱን እንዳቀይጥ
እንዳያደባልቅ መጠንቀቅ ይኖርበታል:: እንዲሁም በቤተ ክርስቲያ



ውስጥ ንጹህ ያልሆነ አምልኮ፤ ልምምድና ሌሎች የተቀየጡ ነገሮች ሲኖሩ ይህን ፈጥኖ በማጽዳት ቤተ ክርስቲያንን ለጸሎት ብቻ ማዋል ተገቢ ነው::

***2፥15-16 ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ፡ ርግብ ሻጮችንም:- ይህን ከዚህ ውሰዱ! የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት አላቸው::*** ጌታ ኢየሱስ የአባቴን ቤት ሲል እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነም እየተናገረ ነው:: እንዲሁም ይህ ቤተ መቅደስ ለምን ዓላማ እንደተመሠረተና ለምን አገልግሎት እንደሚውልም ሲገልጽ ነው:: የቤተ መቅደሱ ዓላማ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚጸልዩበት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ የሚመጡበት ቦታ ነው:: ይህ ቦታ ግን በዓመታት ውስጥ ዓላማውን ስቶ መልኩን ቀይሮ ነበር::

***2፥17 የቤትህ ቅናት ይበላኛል:-*** ይህ ቃል ቀደም ሲል በመዝ 69:9 የተነገረ ነበረ:: ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጸመ:: ቤተ መቅደሱ የንግድ ቤት በመሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤቱ ንጽህና የነበረውን ቅንዓት ያሳያል:: ***የአባቴን ቤት 2:15-16*** በማለቱ ቤቱ የእርሱ (የአባቱ) መሆኑን ይገልጻል:: ቤተ መቅደሱ መጀመሪያ በሰሎሞን በኋላም በዘሩባቤል መሪነት ሕዝቡ ገንዘብ አዋጥቶ፣ እንጨትንም ሰብስቦ የሠራው ሕንጻ ነው:: የቤተ መቅደሱ ባለቤት ግን እግዚአብሔር ነው:: የእግዚአብሔር ንብረት ነው:: የእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ ደግሞ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ሲገልጥ፤ ለእርሱ አገልግሎት ሲውል ይገባዋል::

***2፥18 ስለዚህ አይሁድ ይህን ስለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ? አሉት::*** አይሁድ ምልክት ይፈልጋሉ (1ቆሮ 1:22):: አንድን ነገር ለማረጋገጥ ምልክት ይሻሉ:: ምልክትን ቢፈልጉም የተደረገውን ምልክት አይተው ሊያምኑ የወደዱ አልነበሩም:: በምልክቶች እውነትን ለማወቅ አልፈለጉም:: ጌታም እንዳለው ሰው እንኳ ከሞት ቢነሳ እነርሱ እስከማያምኑ ድረስ ልባቸውን አደንድነው ነበረ (ሉቃ 16:31):: ጌታ ኢየሱስ ራሱ አመጣጡና በመካከላቸው *ሥጋ* ለብሶ መገኘቱ በራሱ ምልክት ነው፤ እነርሱ ግን ሊቀበሉት አልወደዱም:: ይህን በጠየቁት ጊዜ ጌታም ***ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፡ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው 2፥19***፡ ይህን የተናገረው ጌታ ስለ ራሱ ሞትና ከሙታን ስለ መነሳቱ ነበር:: ይህም እንደሆነ ደቀ መዛሙርት ቀይተው አስተዋሉ 2፡22::

***2፥21 እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር::*** ጌታ ይህን በተናገረ ጊዜ እነርሱ ምልክትን ፈልገው ሲጠይቁት የተናገረውን

አላስተዋሉም:: እርሱ የተናገረው እነርሱ የእርሱን ሰውነት እንደሚያፈርሱትና እርሱ ግን በሦስት ቀን ውስጥ እንደሚያስነሳው ነበረ:: እነርሱ ግን በኢየሩሳሌም ስለ ቆመው ከድንጋይ ስለ ተሰራው ቤተ መቅደስ መሰላቸው:: በአዲስ ኪዳን የሰውነት መፍረስ እንደ መሞት ተደርጐ በምሳሌያዊ አነጋገር ይነገር ነበር (2ቆሮ 5÷1-4፤ 2ጴጥ 1÷13-14):: ይህ ሰውነታችን ጊዜያዊ መኖሪያችን ስለሆነ ሞት ይህን ሰውነት ያፈርሰዋል፤ ኢየሱስ ግን ያስነሳዋል::

***2÷20 ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበረ:-*** ጌታ በመጣ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበረውን ቤተ መቅደስ ዘሩባቤል ከ500 ዓመታት ያህል በፊት አሰርቶት ነበር:: ይህ አርባ ስድስት ዓመት ደግሞ በዘሩባቤል የተሠራው ቤተ መቅደስ በሄሮድስ መታደስ የጀመረበት ጊዜ መሆን አለበት::

***2÷22 ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጻሕፍትና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ::*** ደቀ መዛሙርት ከጌታ የሚሰሙ ከእርሱም የሚማሩ ሆነው ሳለ የሚናገራቸውን ሁሉ ግን ያልተረዱበት ጊዜ አለ:: ጌታ ስለ መቅደሱ መፍረስና በሦስተኛው ቀን መነሣት የተናገረው የበራላቸው (የገባቸው) ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ነው:: በዚህ ጊዜ በብሉይ ኪዳን የተነገረው (መዝ 22:7-17) እውነት እንደሆነ አመኑ:: እርሱ የተናገራቸውን ሁሉ የሚያሳስበው የእውነት መንፈስ (ዮሐ 14÷26) የተናገረው ምን እንደነበረ ጌታ ከተነሣ በኋላ አብርቶላቸዋል ማለት ነው::

***2÷23 ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ:-*** አይሁድ ምልክትን ይፈልጋሉና በተደረገው ምልክት ብዙዎቹ በእርሱ እንዳመኑ እናነባለን:: ይሁን እንጂ ቀጥሎ ካሉት ቁጥሮች እንደምንገነዘበው እምነታቸው ሙሉ አልነበረም:: ስላዩት ምልክት ብቻ ያመኑ ናቸው:: ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ተአምር ሰሪ ወይም እንደ አንድ ትልቅ ነቢይ አድርገው ቆጥረውታል እንጂ እርሱ መሲሑ የእግዚአብሔር ልጅ አዳኝ እንደሆነ ያልገባቸው ብዙዎች ናቸው:: ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ እምነት በተሳሳተ ምክንያት ወይም ዓላማ ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ይቻላል:: እርሱ ስለሚያደርገው (ወይም ስለሚያደርግላቸው) ነገር ብቻ አምነው የሚከተሉ እማኞች መሆናቸው ነው:: እርሱን በመከተላቸው ተአምር ያያሉ፤ ለእነርሱም የሚደረግላቸው ነገር ይኖራል:: ጌታ ግን ሰዎች በእርሱ እንዲያምኑ የሚፈልገው ስለ እርሱ ማንነት ማለትም ስለ መሲሕነቱ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ መሆኑ ነው::



***2:24-25 ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና::*** እርሱ ያደረገውን ምልክት አይተው ብዙ ሰዎች በስሙ እንዳመኑ ተመልክተናል (2:23):: ያመኑትን ሁሉ እያንዳንዳቸውን በውስጣቸው ያለውን ጌታ ያውቅ ነበር:: ለምን ዓላማ እንዳመኑ ወይም ለማመን እንደወሰኑ ያውቅ ነበር:: ሰውም ሊነግረው አያስፈልገውም ነበረ:: ያመኑበትን ምክንያትም ስለሚያውቅ ሰዎቹ በማመናቸው አይተማመንባቸውም ነበር:: በምን ያህል ጥልቀት ስለ እርሱ እንዳወቁ፤ በምን ያህል መስጠት እንዳመኑ እርሱ ራሱ ያውቅ ነበር:: የሰው ልብ ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል? የሰውን ልብ የሚያውቅ ጌታ ብቻ ነው (1ሳሙ 16:7፤ መዝ 139፤ ኤር 17:9፤ ሐዋ 1÷24):: በመንገድ የሚንጠባጠቡ (ወደ ኋላ የሚመለሱ) እንዳሉ ያውቃልና (6÷66)::

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው፤ ፍጹም አምላክ ነው:: በምድር በኖረበትም ጊዜ አምላክነቱን አልተወም:: በራሱ ፈቃድ ክብሩን ትቶ የባሪያን መልክ ሲወስድ (ፊል 2:5-9) አምላክነቱን አልተወም፤ ስለዚህ ስለ ሰው ያውቅ ነበር፤ ማንም ሊነግረው አያስፈልገውም ነበር::

# ምዕራፍ ሦስት

***3፥1 ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ።*** በዚያ ዘመን በአይሁድ መካከል የተለያዩ ክፍሎች ነበሩ። የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች በተለያየ ቡድን የተከፈሉ ነበሩ።

- አንደኛ የፈሪሳውያን ወገን ነው (ማቴ 5፥20፤ 23፥1-36፤ ሉቃ 6፥2፤ 7፥36-47)። እነዚህ ከአይሁድ ወገን ለጥቃቅን ሕግ ሳይቀር አጥብቀው የሚጠነቀቁ ናቸው። የአይሁድን ሕግና ልማዶችን የሚጠብቁ ነበሩ።
- ሁለተኛ ሰዱቃውያን ናቸው (ማቴ 3፥7፤ 16፥11-12፤ ማር 12፥18)። ብዙ ካህናት ከሰዱቃውያን ወገን ነበሩ። ከመጻሕፍት ክብሉይ ኪዳን አምስቱን የሙሴን ሕግ ብቻ የሚቀበሉ ነበሩ። ከአይሁድ መካከል በሀብት ከፍ ያለ ደረጃ ላይ እንዳሉ የሚታወቁ ነበሩ። ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉም ናቸው።
- ሦስተኛ የሕግ አስተማሪዎች ናቸው (ማቴ 7፥29፤ ማር 2፥6፤ 2፥16)። እነዚህ የታወቁ የሕግ ተርጓሚዎች ናቸው። በተለይም ሕግንና ልማዶችን የሚተረጉሙና የሚያስረዱ ናቸው።
- አራተኛ ቀናተኞች ነበሩ (ሉቃ 6፥15፤ ሐዋ 1፥14)። እነዚህ ደግሞ ከአይሁድ መካከል የነፃ አውጪነት ስሜት የነበራቸውና እስራኤልን ከሮማውያን ግዛት ነፃ ለማውጣት የሚፈልጉ ነበሩ።

ኒቆዲሞስ ሕግን አጥብቀው ከሚጠብቁ ፈሪሳውያን ወገን የነበረ ***የእስራኤል መምህር 3፥10*** ነበር። ከፈሪሳውያን ወገን ብቻ ሳይሆን፤ የአይሁድም አለቃ በመሆኑ ሥልጣን የነበረው ሰው ነው። የአይሁድ አለቃ የተሰኘበት አካል እንደ ምክር ቤት[16] ሲሆን ሰባ አንድ አባሎችን /መሪዎችን የያዘ ሸንጎ ነው።

***3፥2 እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ:-*** ኒቆዲሞስ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎችን የያዘ ትልቅ ሰው ነበር። ይህ ሰው ወደ ኢየሱስ ***በሌሊት*** መጣ። ኒቆዲሞስ ከእርሱ መሰል ብዙ ፈሪሰውያን የተለየ ባሕርይ የነበረው ሰው ነው። አብዛኛዎቹ ፈሪሳውያን ጌታን ለማጥመድ

[16] Sanhedrin



ይከታተሉት የነበሩና የሚያምኑትንም ሊያስፈራሩ የነበሩ ናቸው። ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ የመጣው በማኅበር ሳይሆን ለብቻው፤ በቀን ሳይሆን በሌሊት ነው። ይህን ሲያደርግ በሌሎች ሊታይ የፈለገ አይመስልም። ሌሎች ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ጋር ቢያዩት በኒቆዲሞስ ላይ ትልቅ ችግር ሊፈጥሩበት ይችላሉ። በሌሊት በመምጣቱና ለብቻው ኢየሱስን በማግኘቱ ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ከጌታ ጋር ሊነጋገር ችሏል።

***3፥2 መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን።*** ኒቆዲሞስ የሄደው ለብቻው ሲሆን ***እናውቃለን*** ማለቱ ብዙዎችን ወክሎ እንደሚናገር ይመስላል። ጌታ ለኒቆዲሞስ የሰጠው ምላሽ «ትክክል ነህ ወይም አይደለህም» የሚል ሳይሆን ራሱ ኒቆዲሞስ ማድረግ ስለሚገባው ነገር ነው።

***3:3 ኢየሱስም መለሰ:- እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።*** ይህ የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስን ጨምሮ ለሰው ሁሉ የተነገረ ቃል ነው። ማንም ሰው ቢሆን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት ዳግመኛ መወለድ ያስፈልገዋል የሚል ነው። ***የእግዚአብሔር መንግሥት*** በእርሱ ገዢነት ሥር ሆኖ መተዳደርን የሚያሳይ ነው። የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት የመንግሥቱ ዜጋ መሆንን በመንግሥቱ ውስጥ መገኘትን፣ መኖርን ያመለክታል።

ጌታ ***ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ*** በቀር እንዳለው የእግዚአብሔር መንግሥት አባል የመሆኛው መንገድ ዳግመኛ መወለድ ብቻ ነው። ዳግመኛ መወለድ ማለትም በንስሐ ወደ እግዚአብሔር በመመለስና የኃጢአትን ይቅርታ በመቀበል የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ነው። ለሚያምኑት የእግዚአብሔር መንግሥት በውስጣቸው ወዲያው ይጀመራል (ሉቃ 17፥21)። ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት በእርሱ ውስጥ ነበረች፤ (ሉቃ 17:21)። ስለዚህ በእርሱ የሚያምኑ ዳግመኛ ይወለዳሉ፤ የመንግሥቱ አባሎች (ዜጎች) ይሆናሉ። እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ ለማመን በሚያደርገው ውሳኔው የሚያገኘው ጸጋ እንጂ አይሁዳዊ በመሆኑ የሚሰጠው አይደለም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲናገር ከዚህች ምድር አይደለችም ብሏል (18:36)።

***3፥4 ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?*** ኒቆዲሞስ የመሰለው ሁለተኛ ከሰው ስለ መወለድ ነው። ዳግመኛ ስለ መወለድ ወይም ስለ

*መንፈሳዊ መታደስ* ቀደም ሲል ነቢያትም ተናግረው ነበር (ሕዝ 36÷25-27፤ ኤር 31÷31-34፤ ኢዩ 2÷28-32)። ይህ እንደገና መወለድ ሕይወትን እንደገና እንደ አዲስ *መጀመር* ነው። ይህም ከእናት ማኅፀን ለሁለተኛ ጊዜ መወለድ ማለት ሳይሆን ከላይ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሆነ *ዳግመኛ* በመወለድ ሕይወትን እንደ አዲስ *መጀመር* ነው። እንደገና መወለድ የዘላለም ሕይወትን ማግኘት ነው።

***3÷5 ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።*** አሁንም ጌታ የሚናገረው ወደ እግዚአብሔር *መንግሥት* የመግቢያው መንገድ በመወለድ እንደሆነ ነው። ከእናት ማኅፀን በሆነው *የመጀመሪያ* መወለድ ሰው ወደ እግዚአብሔር *መንግሥት* እንደማይገባና ወደ *መንግሥቱ* ለመግባት ሁለተኛ መወለድ እንደሚያስፈልግ አስረግጦ ይነግረዋል።

***ከውኃና ከመንፈስ*** ስለሚለው ሐረግ (ቃል) የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ወይም ማብራሪያ ጸሐፊዎች የተለያየ መረዳት እንዳላቸው ይናገራሉ። ለምሳሌ፡-

አንደኛው፡- ውኃ የሚያመለክተው በተፈጥሮ ያለውን መወለድ ሲሆን፤ መንፈስ ደግሞ መንፈሳዊውን መወለድ ነው። ስለዚህ ሁለት መወለዶች አሉ። የመጀመሪያው በአካል የሆነው መወለድ ከውኃ፤ ሁለተኛው መንፈሳዊ የሆነው መወለድ ከመንፈስ የሚል ነው። ለዚህ ማስረጃ ***ከሥጋ የተወለደ ሥጋ፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፤*** 3:6 የሚለውን ይጠቅሳሉ።

ሁለተኛው፡- ውኃ የሚያመለክተው ጥምቀትን፤ መንፈስ ደግሞ ከመንፈስ እንደገና መወለድን የሚለው ነው። በዚህ አባባል መሠረት አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በውኃ መጠመቅና መንፈስ ቅዱስን መቀበል አለበት የሚል መረዳትን ይሰጣል። ይህ አስተሳሰብ ገፋ ተደርጐ ሲወሰድ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት አንድ ሰው በውኃ መጠመቅ ያስፈልገዋል የሚልን ፍቺ ያስከትልና ጥምቀት ለደህንነት አስፈላጊ ነው ወደሚል ትርጓሜ ያደርሳል።

ሦስተኛው፡- ውኃም ሆነ መንፈስ የሚያመለክትው መጠመቅን ነው። አንደኛው በውኃ ሁለተኛው በመንፈስ ቅዱስ የሚል ነው። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ድርጊቶች በቅደም ተከተል ወይም በተለያዩ ጊዜያት የሚፈጸሙ አድርጐ ያቀርባቸዋል።



እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ *ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር* ሲል ሁለት ድርጊቶችን ማመልከቱ ይሆን? ወይስ አንድ ድርጊት በተለያየ አገላለጽ መቅረቡ? አንዳንዶቹ እንደሚሉት ውኃ የሚለው ራሱ የመንፈስን ሕይወትን የማጠብ (የማንጻት) ተግባርን የሚያሳይ ለላ መግለጫ ነው (ዮሐ 7÷37-39)።[17]

***3÷6 ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።*** ከሥጋ ማለትም ከሰው የተወለደ ሰው ነው የሚሆነው፤ ይህ መልስ ኒቆዲሞስ ***ሁለተኛ ሰው ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? 3:4*** በማለት ለጠየቀው መልስ ይሆናል። ከሰው እስከተወለደ ድረስ ሁለተኛም ይሁን ሌላ ጊዜ ያው ሰው፤ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ሆኖ ይቀራል እንደ ማለት ነው። ነገር ግን ሰው ዳግመኛ ሲወለድ እግዚአብሔር መንፈሱን በዚያ ሰው ውስጥ ያደርጋል። (እንደገና የተወለደ ወይም ለእርሱ ጥሪ የነቃ መንፈስ ይሰጠናል)። ይህም የመለኮት ሥራ ስለሆነ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆንን ሥልጣን ይሰጠናል (1፡ 12)። ከመንፈስ መወለድ በሰው ችሎታ፤ አቅምና ሥልጣን ውስጥ ያለ ነገር አይደለም።

***3÷8 ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል÷ ድምፁንም ትሰማለህ÷ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።*** ከመንፈስ የተወለደ የሚለውን ጌታ ኢየሱስ ሲያብራራው በነፋስ ምሳሌ ይናገራል። ***ወደሚወደው*** የሚለው በሰው ፈቃድ፤ ቁጥጥርና ሥልጣን ሥር አይደለም ማለት ነው። ከመንፈስም መወለድ እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ልክ እንደ ነፋስ በራሱ ፈቃድና ሥልጣን የሚሄድ የወደደውን የሚያደርግ ነው። እርሱ በነፈሰበትና በአረፈበት ቦታ ለሰው አዲስ ሕይወትን ይሰጣል (ውጤቱ) ይታያል። የሚታየው ሲነፍስ ሳይሆን በነፈሰበትና ባረፈበት ቦታ የዚያን ሰው ሕይወት በመለወጡ ነው። ነፋስ ሲነፍስ ድምፁ ይሰማል፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ እንደማይታወቅ እንዲሁ መንፈስ አይታይም ነገር ግን የሰውን ሕይወት ይለውጣል። ሰው ነፋስን መቆጣጠር እንደማይችል ሁሉ የእግዚአብሔርንም መንፈስ መቆጣጠር አይችልም። የነፋሱን መነሻና መድረሻ ማወቅ እንደማይቻል የእግዚአብሔርን መንፈስ አሠራር መቆጣጠር አይቻልም። ከመንፈስ የሆነ ሕይወት አስደናቂ ሕይወት ነው።

[17] ውኃ የእግዚአብሔርን ቃልም የሚመለክትበት ሁኔታ አለ። በኤፌ 5:25-26 ቤተ ክርስቲያንን «በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንደ ቀደሳት» እንደሚል። እንዲሁም ቲቶ 3:5።

***3፥10 አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን?*** የእስራኤል መምህር የሆነ ሰው ብሉይ ኪዳን ዳግመኛ ስለ መወለድ የሚናገረውን ሊያውቅ ይጠበቅበታል (1ሳሙ 10፥6፤ ኢሳ 12፥15፤ ኤር 31፥33፤ ሕዝ 36፥25-27፣37፤ ኢዩ 2፥28-29)። ኒቆዲሞስ የአገልግሎት ሥልጣኑ መምህር ነው፣ የእስራኤል መምህር ግን ራሱ አያውቅም ነበር። የእስራኤል መምህር ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቆ እንዲያውቅ ይጠበቅበት ነበር። ጌታ በ5፥39 ላይ ቃሉን ስለሚያውቁት የቃሉን ትርጉም ግን ስለሚስቱት እንደተናገረው መምህር በመሆኑ ጥቅሶቹን ያውቃቸው ይሆናል፤ ነገር ግን ትርጉማቸውን አልተረዳም። በዚህም ዘመን መምህር ወይም አስተማሪ ተብለው በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ሹመት የሚሰጣቸው ሰዎች እጅግ በማስተዋል ቃሉን መረዳት፣ ማጥናትና ማስተማር ይኖርባቸዋል። ማዕረጉ ኖሯቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል የማያወቁ ወይም እውነተኛ ምንነቱን ያልተገነዘቡ ላለመሆን። (እግዚአብሔር ይርዳን)።

***3፥12 ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?*** ስለ ምድራዊ ነገር ለምሳሌ በድምፁ ስለሚሰማና የሚያደርገው ውጤቱም ስለሚታይ ስለ ነፋስ ነግሬያችሁ በምድራዊ ምሳሌ ካልተረዳችሁ እንደ ማለት ነው። የእስራኤል መምህር የሆነው ኒቆዲሞስ ይህን መረዳት ካልቻለ ስለ ሰማያዊ እውነት ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራማ እንዴት መረዳት ይችላል። እምን ሰማያዊ ነገርን ሰው ሊረዳው አይችልም። ነገር ግን የጌታን ቃል በመቀበል ለሚያምን ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ያበራለታል፤ ያስረዳዋል።

***3፥13 ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።*** ስለ ሰማያዊ ነገር ለመናገር ጌታ የተገባው ነው፤ ምክንያቱም ከሰማይ የወረደ ነውና፤ የሰማይን ነገር ያውቃልና፤ ከሰማይም የወረደው እርሱ ብቻ ነውና። ያየውንና የሚያውቀውን ይናገራል። ***ከሰማይ ከወረደው*** ሲል ሰውን ለማዳን ከዘላለም መኖሪያው ከላይ ከፍ ካለው ዝቅ ወዳለው ወደ ታችኛው እንደመጣ ያሳየናል። በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ (ማቴ 6፥9) በማለት እንዳስተማረ ከሰማይ የወረደው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አብ (ከአብ ጋር) በሰማያት የሚኖር ነው። ስለ ሰማይ የሆነውን የሚያውቅና የሚገልጥ እንዲህ ዓይነት አስተማሪ ማንም የለም። የእስራኤል አስተማሪ ኒቆዲሞስና ሌሎችም ይህን አያውቁም። ጌታ ኢየሱስ ራሱን የሚጠራበት አንዱ ስም ***የሰው ልጅ*** ብሎ ነው (1፥51፤ ማቴ 26፥64)። ቀደም ሊልም በዳን 7፥13 ተገልጦ ነበር።



***3፥14-15 ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።*** የሰው ልጅ ከሰማይ የወረደውና ሥጋ የለበሰው እንዲሞት ወይም እንዲሰቀል የተገባው ነው። ሙሴ በምድረ በዳ የነሃስ እባብ የሰቀለው እስራኤላውያንን እባብ በነደፋቸው ጊዜ ለመድኃኒትነት ነው። «እግዚአብሔርም ሙሴን እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ሰቀል፤ የተነደፈውም ሁሉ ሲያየው በሕይወት ይኖራል አለው» (ዘኁ 21፥8)። ያን ጊዜ በሕይወት የመኖሪያው መንገድ የተሰቀለችውን የነሃስ እባብ ***ማየት*** ነበር። የተሰቀለውን እባብ ያየ እንደሚድን ከተነደፈበት እንደሚፈወስ እንዲሁ በአዲስ ኪዳን ደግሞ በተሰቀለው በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ከኃጢአት በሽታው ለዘላለም ይፈወሳል። ደህንነት የሚገኘው የተሰቀለውን ኢየሱስን በእምነት በማየት (በመቀበል) ነው። የሚያምንበት ከኃጢአት መነደፍ ነፃ ይወጣል፣ ይቅርታ ያገኛል፤ የዘላለም ሕይወት ያገኛል።

***3፥16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።***ይህ ስለ ሁሉም ሰው የተነገረ ቃል ነው። የማመንንም ውጤት ያሳያል። ይህ ጥቅስ የዮሐንስ ወንጌል ዓላማ ተብሎ ሊቆጠር የሚችል ጥቅስ ነው። ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔርን ፍቅር ልጁንም የላከበትን ምክንያት ይገልጣል። ***ዓለሙን ሁሉ*** የሚለው ሰውን ሁሉ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ሰው ሁሉ የተዘረጋ፤ የሚሄድ ፍቅር ነው። ይህ ዋጋ የሚከፍል ፍቅር ነው። እርሱ መውደዱን የገለጠው አንድያ ልጁን ወደ ዓለም በመላክ በተግባር ነው። እግዚአብሔር ለፍቅር የከፈለው ዋጋ እጅግ ክቡር ነው።

***በእርሱ የሚያምን*** የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያውቅና እምነቱን በእርሱ ላይ የሚያኖር ማለት ነው። እምነቱን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚያኖርና በእርሱ ቃል መሠረት የሚኖር (የሚተዳደር) ሰው ይድናል ማለት ነው። ይህ ስጦታ ለዓለም ሁሉ ስለሆነ ***በእርሱ የሚያምን ሁሉ*** (ማንም ሰው) የዘላለምን ሕይወት ያገኛል። እግዚአብሔር ዓለሙን የወደደው ***እንዲሁ*** ነው፤ ማለትም በዓለም ያየው መልካም ነገር ስላለ ሳይሆን በጸጋው ከራሱ በሆነ መውደድ ነው። ይህ ከሰው የሚያገኘውን ምላሽ በመጠበቅ ያልሆነ መውደድ ነው። የራሱን ጥልቅ ፍቅር ብቻ የመግለጥ መውደድ ነው።

እግዚአብሔር ዓለሙን ባይወድና ልጁን ባይልክ ኖሮ የሰው ልጅ ፍንታው ከመጥፋት ሌላ ምን ይሆን ነበር? (ማር 4፤38፤ ሉቃ 13፤3፣5፤ ዮሐ 10፤28፤ ሮሜ 2፤12፤ 1ቆሮ 1፤18፤ 2ጴጥ 3፤9)።

እግዚአብሔር ሰውን ለዘላለም ከመጥፋት የሚታደግ አምላክ ነው:: ለመታደግም ልጁን ልኳል:: ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ ለዘላለም ከሚኖር ይልቅ ፍቅሩን በመቀበልና በማመን ለዘላለም በሕይወት ለመኖር ሲመርጥ ይገባዋል::

***3÷17 ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና::*** ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የተላከው ዓለምን ለማዳን ነው፤ በዓለም ለመፍረድ አይደለም:: ዓለም ተፈርዶበታል (16÷9):: ኢየሱስ የመጣው የተፈረደበትን ዓለም ለማዳን ነው:: ከዚህ ከፍርድ ነፃ መሆን የሚቻለው በአዳኙ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው:: ሁሉም ሰው ወደ ንስሐ እንዲመጣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ነው (2ጴጥ 3÷9)::

***3÷19 ፍርዱም ይህ ነው::*** በሰው ሁሉ ላይ ሊመጣ ያለው ፍርድ በምን ላይ እንደ ተመሠረተ ወይም ለምን እንደሆነ ይገልጻል:: ፍርዱም በማያምን ሰው ይፈረድበታል የሚል ሲሆን ምክንያቱም ***በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል 3:18::*** ሊያድነው በመጣውና የእግዚአብሔርን ፍቅር በሚገልጠው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያላመነ ይፈረድበታል:: ያውም አሁን የተፈረደበት ነው::

***3÷19 ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ:-*** ይህ ፍርድ በብርሃንና በጨለማ መካከል የሚለይ ፍርድ ነው:: ***ብርሃን ስለ መጣ*** ማለት ብርሃን የሆነው ኢየሱስ መምጣቱን ያሳያል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ነው:: በብርሃን ተመስሎም መገለጹ እርሱ እውነት መሆኑንና ከኃጢአት ፈጽሞ የተለየ መሆኑን ይገልጻል:: እርሱ ብርሃን ስለሆነ በሰው የምናምነውን የእያንዳንዳችንን መንገድ ያበራልናል፤ ስለ እግዚአብሔርም የበለጠ እንድናውቅ ውስጣችንን ያበራል:: ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ለመፍረድ አይደለም:: ሆኖም የእኛን በጨለማ ውስጥ መሆን በእርሱ ብርሃን በእጅጉ ይታወቃል:: በብርሃን መመላለስ የማይወድ በጨለማ ውስጥ ይኖራል:: ይህም ተፈርዶበታል::

***3:20-21 ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፤ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጐ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል!*** ለብርሃን መገለጥን ወይም ወደ ብርሃን መምጣትን የሚፈሩ ሰዎች የጨለማ ሥራቸው እንዳይገለጥ የሚፈልጉ ናቸው:: ብርሃን ሁሉን ነገር ይገልጣል፤ እንዲታይም ያደርጋል (ኤፌ 5÷13-14)::

ዘኀጢአትና በአመፅ መቀጠል የሚፈልጉ ሰዎች ይህን ሥራቸውን ብርሃን እንዳይገልጣቸው በድብቅ ወይም በጨለማ ያደርጉታል።

እንዲሁ በብርሃኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን የማይወዱ በጨለማ ሥራቸው ለመቀጠል የሚፈልጉ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ተፈርዶባቸዋል። የፍርዱም መሠረት ይኸው በጨለማ ለመኖር መውደዳቸውና ወደ ብርሃን ለመምጣት አለመፈለጋቸው። በአንጻሩ ግን እውነትን (ትክክል) የሚያደርጉ ክርስቶስን ይወዳሉ ራሳቸውን ለማስመርመር ወደ እርሱም ለመምጣት አይፈሩም። ፊትነኝ ለማለት ወደ እግዚአብሔር ይመጣሉ። ብርሃን = እውነት።

***3፥22-23 ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ይሁዳ አገር መጣ ... ያጠምቅ ነበረ። ዮሐንስም ደግሞ በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን ... ያጠምቅ ነበር***። በአንድ ጊዜ በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ጥምቀት ይደረግ ነበር። አንዱ በይሁዳ ሌላው ደግሞ በሄኖን። ሄኖን በሳሌም አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ሲሆን ***በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና 2:23*** እንደሚል ሄኖን ብዙ ምንጮች ያሉበት ቦታ ማለት ነው። ***ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ይሁዳ አገር መጣ በዚያም ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ ያጠምቅ ነበር 3:221*** ሲል እንደ ዮሐንስ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን በውኃ ያጠምቅ ነበር ወይ? የሚል ጥያቄ ብናነሳ «ዳሩ ግን ደቀ መዛሙርቱ እንጂ ኢየሱስ ራሱ አላጠመቀም» (4፡2) ስለሚል መልሱ ኢየሱስ ሰዎችን አላጠመቀም ነው። ደቀ መዛሙርቱ ሲያጠምቁ ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብሮ ነበር። እርሱ ግን ራሱ ሰዎችን በውኃ አላጠመቀም ነው። የጌታ ደቀ መዛሙርት ያደርጉት የነበረው ጥምቀት እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ዓይነት ሰዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ መንገድ የሚያዘጋጅ የንስሐ ጥምቀት ሊሆን ይችላል።

***3፥23 ዮሐንስ ገና ወደ ወኅኒ አልተጨመረም ነበርና።*** መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ወኅኒ የተጨመረው ሄሮድስን የፊልጶስ ሚስት ሄሮድያዳ ስአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ አልተፈቀደም (ማቴ 14፡4) ስላለው ነበር። በመጨረሻም ሄሮድስ በተወለደበት ቀን የሄሮድያዳ ልጅ ዘፍና ምን እንዲሰጣት በጠየቃት ጊዜ በእናቷ ተመክራ የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ በወጭት ስለ ጠየቀች ሄሮድስ የዮሐንስን ራስ አስቆረጠ። ታሪኩን በማቴዎስ ከ14፡1-12 ይመልከቱ።

***3፡26 ሁሉም ወደ እርሱ ይመጣል አሉት።*** ይህን ለመጥምቁ ዮሐንስ የሚናገሩ አይሁድ ናቸው። የአይሁድ አለቆችና ካህናት ሰዎች ኢየሱስን መከተል ሲጀምሩ በቅንዓት ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር። ዮሐንስ እንደ እነርሱ በቅንዓት የተያዘ መስሎአቸው ***ሁሉም ወደ እርሱ***

***ይመጣሉ 3:26*** ብለው ነገሩት። ዮሐንስ ግን ሰው ሁሉ ወደ ኢየሱስ መሄዱ ትክክል እንደሆነ ያረጋግጥላቸዋል። የዮሐንስም አገልግሎት የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ ማመልከት ነበርና።

***3፥27 ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው አንዳች ሊቀበል አይችልም።*** ሰው መልካምን ነገርን ሁሉ የሚቀበለው መልካም ከሆነው ከብርሃናት አባት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው (ያዕ 1:17)። የመልካም ነገር ምንጩ እግዚአብሔር ነው።

***3፥28 እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፤ ነገር ግን፦ ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ።*** ዮሐንስ ይህን ቀደም ሲል በ1:20 ላይ ገልጾ ነበር። አሁንም ደግሞ ያነግራቸዋል። ማንነቱን ለሰው ሁሉ ይገልጻል- እርሱ ክርስቶስ እንዳልሆነና ከእርሱም የሚያንስ መሆኑን፤ ሰዎች ኢየሱስ ማን እንደሆነ ይረዱ ዘንድ መንገድ የሚያሳይና ለአፍታም ዮሐንስ መሲሑ እንዳይመስላቸው የሚከላከል ሰው ነው።

***3:29 ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል።*** ዮሐንስ ስለ እርሱ ማንነትና ከጌታ ኢየሱስ ጋር ስላለው ግንኙነት የተጠቀመበት ምሳሌ ነው። ራሱን ያየው እንደ ሚዜ አድርጎ ነው። ሚዜ ሙሽራ አይደለም፤ የሙሽራው አገልጋይ እንጂ። ራሱን በሚዜ ምሳሌ ያቀረበው ዮሐንስ ***እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል 3:29-30*** ይላል። የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አገልጋዩን ዮሐንስን ደስ አሰኘው። እርሱን በማየቱ ደስታው ተፈጸመ።

የዮሐንስ አገልግሎት መንገድን የማስተካከል አገልግሎት ነው (1:23፤ ማር 1:2-3)። ለሚመጣው መሲሕ አዋጅ ነጋሪ ነው። በምድረ በዳ የሚጮህ ድምፅ ነው። የዮሐንስ ሩጫ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመጣ በመጮህ መናገር ነበር። ይህን እያደረገ ቆይቶ የሚጠበቀው (ሙሽራው) ኢየሱስ ስለ መጣ ***ደስታዬ ተፈጸመ*** ይላል። ***ተፈጸመ*** የሚለው ቃል ሩጫውን የጨረሰ፣ የተሰጠውን አገልግሎት ያጠናቀቀ ሰው ንግግር ነው። ይህን ሲናገር ዮሐንስ የሩጫውን ርቀት ያውቀ፤ ከተፈቀደለትም ርቀት በላይ ለመሮጥ ያልፈለገ ሰው እንደሆነም እናስባለን። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ስለ ተገለጠ ዮሐንስ እያነሰ፤ እያነሰ፤ ኢየሱስ ደግሞ እየላቀ ሲሄድ ያስፈልጋል።

***እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ*** የሚለው የሚያመለክተው የአገልግሎት መበላለጥን ብቻ አይደለም። የሚያንሰው አገልግሎቱ ብቻ ሳይሆን ራሱ ዮሐንስም ነው። ኢየሱስ ሊልቅ ዮሐንስ ደግሞ ሊያንስ ያስፈልጋል። ዮሐንስ እርሱ እንዲያንስ መወደዱ ምን ዓይነት ትሕትና ነው። ብዙ

ተከታዮችን አፍርቶ፤ ደቀ መዛሙርት በዝተውለት በሕይወቱና አገልግሎቱ ከፍታ[18] ላይ በነበረበት ሰዓት ድንገት የሚጠበቀው ስለ ተገለጠ አገልግሎቱ ራሱ ሲያንስ እንደሚገባው የሚናገር ትልቅ የክርስቶስ ባሪያ ነው:: መጥምቁ ዮሐንስ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የተሰጠውን ጥሪና ድርሻ ምን እንደሆነ በትክክል ያወቀ እና በዚያም መሠረት የኖረ ሰው ነው:: የእርሱ ድርሻ ሚዜነት ነው::

***3:31 ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው::*** ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ***ከሁሉ በላይ*** የሚለው ከሁሉም ነገሮች፣ ሁኔታዎች እንዲሁም ከሁሉም ሰዎች በላይ ነው የሚል ትርጉም አለው:: ይህ በላይነትንና ቀዳሚነትን ያሳያል:: በላይነት ከፍ ያለ መሆኑን፤ ቀዳሚነት ደግሞ የቀደመ፣ የመጀመሪያ መሆኑን:: ***ከምድር የሆነው የምድር ነው የምድሩንም ይናገራል 3:31::***

***3:31 ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው::*** ዮሐንስ ከሰው ልጆች ከተወለዱት ሁሉ ከፍ ያለ ትልቅ ቢሆንም (ማቴ 11:11) ሰው ነው፣ እርሱም ከምድር ነው:: ማንም ሰው በእድሜ፣ በማዕረግ፣ በእውቀት፣ በሥልጣን፣ በምንም መመዘኛ አጅግ ከፍ ያለ ቢሆንም ያ ሰው ምድራዊ ብቻ ነው:: ከሰማይ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ከሁሉም በላይ ነው:: ከሰማይ መጥቷልና::[19] ዮሐንስ ምድራዊ ምስክር ነው፤ ኢየሱስ ሰማያዊ ምስክር ነው:: ስለዚህ የኢየሱስ ሥልጣን ከዮሐንስ ሥልጣን ይበልጣል::

እዚሁ 3:31 ላይ ***'ከላይ የሚመጣው'*** የሚለውና ***'ከሰማይ የሚመጣው'*** የሚለው ድግግሞሽ ይመስላል:: ሀሳቡ ተመሳሳይነት ቢኖረውም አንዳንዶች እንደሚሉት ***ከላይ የሚመጣው*** የሚለው ከሁሉ በላይ መሆኑን መለኮትነቱን ሲያመለክት ***ከሰማይ የሚመጣው*** የሚለው ደግሞ በላሰማዊነትን ሲያመለክት ነው::

***3:32 ያየውንና የሰማውን ይህን ይመሰክራል፥ ምስክሩንም የሚቀበለው የለም::*** ከሰማይ የሚመጣው በሰማይ ያየውን ይመሰክራል:: በሰማይ የሰማውን ይመሰክራል:: ስለዚህ ምስክሩ

---

[18] Climax

[19] The Repetition is worshipful and the small change is instructive. <From above> emphasis, Jesus' divine nature, while <from heaven> indicates his preexistence. In other words, Jesus already was in what we call the beginning; he was with God and he was God. LEBC Ibid. pp 70-71.

እውነተኛ ነው (ዮሐ 8፥14-30)። ይህም ሆኖ ግን አይሁድ እርሱን ገፉት እንጂ አልተቀበሉትም (ዮሐ 1፥10-11፤ 3፥11፤ 12፥37-)።

***3፥33 ምስክሩን የተቀበለ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ አተመ።*** አተመ ማለት አረጋገጠ፤ ተቀበለው የሚል ትርጉም አለው። ከላይ የመጣውን የኢየሱስን ምስክርነት የተቀበለ ሰው የላከውን የእግዚአብሔርን እውነተኛነት አወቀ፤ ኢየሱስ ከሰማይ የመጣው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እርግጠኛ ሆነ ማለት ነው። እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ ማተም - እርሱ ልጁን እንደላከ መቀበልን በእርግጥም እግዚአብሔር ልጁን ላከ ብሎ ማረጋገጥ ነው። እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና።

***3፥34 እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና።*** ይህ ቃል ቀደም ሲል በቁጥር 32 የተነገረውን የሚያሰረግጥ ቃል ነው። ከእግዚአብሔር የመጣ የሚናገረው የላከውን ቃል ነው። የራሱን ቃል አይናገርም (5፥19-)። በኢየሱስ ላይ የመጣው እግዚአብሔር የላከው መንፈስ በእርሱ ላይ አረፈ ኖረም (1፥33)። መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ ስለ ወረደ፣ ስለ ሞላው፤ በእርሱ ላይ ስለሚኖርም ሁልጊዜ የእግዚአብሔር የሆነውን ይናገራል። እግዚአብሔር ለልጁ የላከው መንፈስ ያልተመጠነ፤ ያልተሰፈረ፤ ሙሉ የሆነ ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ለሁልጊዜ በሙላት ስለሚኖር ኢየሱስ ሁልጊዜም የሚናገረው የእግዚአብሔርን ቃል ነው።

***3፥35 አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል።*** እግዚአብሔር አብ ለልጁ ያልሰጠው፤ ያልገለጠለት ነገር የለም። በአብና በወልድ በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት የዘላለም የፍቅር ግንኙነት (ተዛምዶ) በመሆኑ ሁሉንም አባት ለልጁ ገልጦለታል። እዚህ ላይ እኛም ልብ ልንለው የሚያስፈልግ ትልቅ እውነት አለ። በፍቅር ውስጥ ግልጽነት አለ። በፍቅር ውስጥ እውነተኛነት አለ፤ መደባበቅ የለም። እግዚአብሔር ሊሠራ ያቀደውን ሁሉ ለልጁ ሰጥቶታል። ስለሆነም ሥራውን በፈጸመ ጊዜ የሰጠኸኝን ሁሉ ፈጸምኩ ብሎ ኢየሱስ ወደ አባቱ ይጸልያል (17፥1-4)።

***3፥36 በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።*** እዚህ ላይ ***አለው*** የሚለው ቃል የአሁን ጊዜን የሚያመለክት መሆኑን ልብ ማለት ይጠቅማል። የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል አይልም፤ ***አለው*** እንጂ። በእግዚአብሔር ልጅ ያመነ አንድ ሰው የዘላለም ሕይወት እንዳለው የሚያውቀው ከሞተ በኋላ በሰማይ በሚሰጠው ፍርድ ሳይሆን አሁን በምድር እንዳለ የዘላለም ሕይወት እንዳለው ከዚህ ከእግዚአብሔር ቃል

የተነሳ ማመን አለበት። እንዲሁም «ልጁ ያለው ሕይወት አለው» (1ዮሐ 5፡11)። እዚህም ላይ «ያለው» የሚለውና «አለው» የሚለው የአሁን ጊዜ አገላለጾች ስለሆኑ በልጁ የሚያምን በአሁኑ ጊዜ (ከአመነበት ጊዜ ጀምሮ) የዘላለም ሕይወት እንዳለው እርግጠኛ ይሆናል ማለት ነው።

እንግዲህ የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው አንድ ሰው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። ይህ ዳግመኛ መወለድ ነው። አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግመኛ ሲወለድ ወዲያው የዘላለም ሕይወት ስለሚሰጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ይሆናል። ሆኖም እዚህ ላይ አንድ ቁልፍ የሆነ ሃሳብ መዘንጋት የለበትም። በልጁ ማመን ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከማወቅ ወይም በአንደበት ከመናገር ያለፈ መሆኑን ነው። ይህም ማወቅ፤ መቀበልና በተቀበሉትም መሠረት መኖር ነው። እምነት በተግባር ይገለጻልና። በተግባር ያልተገለጠ እምነት ወይም የሕይወት ለውጥ የሌለበት እምነት ከሆነ ከመጀመሪያውም እምነትነቱ አጠራጣሪ ነው።

***3፡36 የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም። ይህ*** ሕይወት የዘላለም ሕይወት ነው። እያንዳንዱ ሰው ስለ ውሳኔው ተጠያቂ ይሆናል። ኢያሱ «የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ» (ኢያ 24፡15) እንዳለው የማመን ወይም የአለማመን ምርጫው ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ መብትና ነፃ ፈቃድ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን የሚመክረው «ዛሬ ሕይወትን ምረጡ» (ዘዳ 30፡15-20) ብሎ ነው። ሕይወትን የመረጠ የዘላለም ሕይወት አለው፤ ሕይወትን ያልመረጠ የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ነው። በምድርም በሕይወት እያለ (ሳይሞትም) በእግዚአብሔር ቁጣ ውስጥ ነው፤ ከሞተም በኋላ የእግዚአብሔር ቁጣ ያገኘዋል ማለት ነው።

በኢየሱስ ማመን ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ በታሪክ ውስጥ የነበረ አንድ ጥሩ መምህር ወይም ነቢይ ነበረ ብሎ መቀበል አይደለም። በርካታ የሃይማኖት መሪዎችና ነቢይ ነኝ የሚሉ ተነስተዋል በማናቸውም ግን አያታመንባቸውም። እውነተኞቹ በእግዚአብሔር የተላኩ ነቢያት ሁሉ እንደ ዮሐንስ መጥምቁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት፤ ስለ እርሱ ታላቅነትና የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ተናግረዋል። በአጠቃላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፤ በእርሱ እንደተላከ ማመንና በመስቀል ላይ የሞተው ለዓለም ኃጢአት መሆኑን በመገንዘብ እያንዳንዱ ሰው ስለ ኃጢአቱ ንስሐ በመግባት ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ነው።

# ምዕራፍ አራት

በዚህ ምዕራፍ ከ1-26 ባለው ክፍል ኢየሱስ ከአንዲት ሳምራዊት ሴት ጋር በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ሲነጋገርና ከንግግሩም በኋላ የሆነውን እንመለከታለን። በዚህም ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ይገልጻል (4፥10)። ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ለሚያምንበት ሰው ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ (4፥14) ነው። እንዲሁም እርሱ የሚጠበቀው መሢሕ (4፥25-26) ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነና በመንፈስና በእውነት መመለክ እንዳለበትም ያስተምራል።

***4፥1 ኢየሱስ ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛሙርት ያደርጋል፣ ያጠምቅማል ማለትን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ ጌታ ባወቀ ጊዜ፡-*** የጌታ ኢየሱስ ታዋቂነት እያደገ መምጣቱ ለፈሪሳውያን እረፍትን አልሰጣቸውም። ዮሐንስ ማጥመቅ በጀመረ ጊዜ ሥጋት ስለነበረባቸው እንዲጠይቁት ሰዎችን ልከውበት ነበር (1፥19-28)። ዮሐንስ ግን ወደ ኢየሱስ አመለከተ፣ ስለሚመጣው መሢሕ ነገራቸው። የራሳቸውን ቦታና ክብር በተከታይ ብዛት የሚለኩት ፈሪሳውያን ኢየሱስ ከዮሐንስ የበለጠ ብዙ ተከታዮች እያገኘ በመጣ ጊዜ እረፍት አላገኙም። የጌታ ***ደቀ መዛሙርት*** በምዕራፍ አንድ የጠራቸውን አሥራ ሁለቱ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ብዙ ተከታዮች (ደቀ መዛሙርት) ነበሩ። ለምሳሌ ሰባ ሁለት በቅርብ የሚከተሉት (ሉቃ 10፥1-12) እንዲሁም በቁጥር ብዙ የሆኑ ነበሩ (ሉቃ 9፥57-62፤ ዮሐ 6፥66)።

ቀደም ሲል «ስለ ሰው ማንም እንዲመሰክርለት አያስፈልገውም ነበርና፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበር» (2፥24-25) የሚለውን ተመልክተናል። በሰው ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ ጌታ አሁን ደግሞ ***እንደ ሰሙ ባወቀ ጊዜ*** ሲል ሌሎች መጥተው እንደነገሩት ያመለክታል። ኢየሱስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ይህም ያሳየናል።

እዚህ ላይ አንባቢው አንድ ነገርን ቢያስተውል መልካም ነው። የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት ብዛትና የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ብዛት ያዩና ያወዳደሩ ፈሪሳውያን ***ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛሙርት*** ሲሉ ዮሐንስንና ኢየሱስን እኮ አበላልጠዋቸዋል። አንዱ ከሌላው በደቀ መዝሙር ብዛት እንደሚበልጥ እየተናገሩ ነው። በሰው አስተሳሰብ እንዲህ ዓይነቱ ማወዳደር ወደ እርስ በእርስ ውድድርና ምናልባትም ፉክክር እንዲደርሱ የሚያደርግ ሁኔታ ነው። አንዳንድ ጊዜ

በአገልግሎት ላይ ሰዎች በሚሰጡት አስተያየትና የማበላለጥ ሁኔታ አገልጋዮቹ ራሳቸው እንኳ ያን ማበላለጥ ባያስቡትም ከሰዎች አስተያየት የተነሣ መፎካከር ይጀምሩ ይሆናል:: ነገር ግን ከዮሐንስ ንግግርና ሕይወት የምናየው ባለውና በተሰጠው የሚረካ የራስን መስመር ጠብቆ የሚሮጥና የሚፈጽም ሰው መሆኑን ነው::

***4፥2-3 ዳሩ ግን ደቀ መዛሙርቱ እንጂ ኢየሱስ ራሱ አላጠመቀም***: ፈሪሳውያን ኢየሱስ ያጠመቀ መስላቸው:: እንዲሁም በ1፥33 ላይ መጥምቁ ዮሐንስ እንደተናገረው መሲሑ የመጣው በመንፈስ ቅዱስ ለማጥመቅ ነው:: ይህ ከዮሐንስ በውኃ የማጥመቅ አገልግሎት የተለየ ነው:: ስለዚህ ጌታ በውኃ አላጠመቀም:: (የ3:22 ን ማብራሪያ ይመልከቱ)::

***4፥4 በሰማርያም ሊያልፍ ግድ ሆነበት::*** በሰማርያ ማለፍን አስፈላጊ ሆኖ አገኘው እንደማለት ነው::

ጌታ ከይሁዳ ወደ ገሊላ እየሄደ ነው 4:2:: ከይሁዳ ወደ ገሊላ የሚሄዱ አይሁድ አብዛኛውን ጊዜ በመካከል በሚገኘው በሰማርያ ላለማለፍ በሌላ ዙሪያ ወይም ረጅም መንገድ ይሄዱ ነበር:: ምክንያቱም ሳምራውያን በአይሁድ ዘንድ የተጠሉ ነበሩና::[20] የሰማርያ ሰዎች የአይሁድና የሌላ ዘር ደም ያላቸው ቅይጥ በመሆናቸው አይሁድ ንፁህ አድርገው አይቆጥሯቸውም፤ እንደ ርኩስ ያዩአቸዋል::

ከምዕራፉ ለማገናዘብ እንደምንችለው ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማርያ መሄድ ***ግድ*** የሆነበት የሰማርያ ሰዎች እንዲያምኑ ነው:: ***የሰማርያ ሰዎችም ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት፤ በዚያም ሁለት ቀን ያህል ኖረ 4፥40*** እንደሚል፤ በዚያ ማለፍ ግድ የሆነበት የሰማርያ ሰዎች የዘላለምን ሕይወት ያገኙ ዘንድ ነው ማለት ይቻላል::

---

[20] Where did these prejudices come from? Samaria was a region between Judea and Galilee where Jews of <mixed blood> lived. In Old Testament days, when the northern kingdom of Israel with its capital at Samaria fell to the Assyrians, many Jews were deported to Assyria. King Sargon of Assyria repopulated the northern kingdom with captives from other lands to settle the territory and keep the peace (2 Kings 17:24). These captives eventually intermarried with the few Jews who remained in the land to form a mixed race of people who became known as some Smaritans. The Jew hated the Samaritans because they were no longer <pure> Jews. The Jews who lived in the southern kingdom felt these Jews had betrayed their people and nation through intermarriage with foreigners. Ibid. pp 77-78.

ሳምራውያን የእይሁድ ደም ስላለባቸውና ለአይሁድም የቀረቡ ስለ ሆኑ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ያውቃሉ:: በተለይም የሙሴን መጻሕፍት፤ ለምሳሌ *አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ 4፥20* የተባለው የገሪዛም ተራራ (ዘዳ 27፥1-14) ማለት ነው:: *አባቶቻችን* ብለው የሚጠሯቸው አብርሃም፤ ይስሐቅና ያዕቆብንና የእስራኤልን ልጆች ነው::

***4፥5 ሲካር ወደምትባል የሰማርያ ከተማ መጣ:-*** በዘፍ 33፥19 *መሠረት ያዕቆብ* በሴኬም አቅራቢያ *መሬት ገዝቶ ነበረ:: ያንንም ቦታ* ለዮሴፍ ሰጠው (ዘፍ 48፥22፤ ኢያ 24፥32):: እስራኤላውያን የዮሴፍን አጥንት ከግብጽ አምጥተው በዚያ ቀበሩት:: በዚያ ቦታ ይህ ጉድጓድም እንዳለ እናያለን:: ስለዚህ ሳምራውያን ይህን የውኃ ጉድጓድ ከፍተኛ ግምት ይሰጡታል:: አንድም ውኃ የያዘ በመሆኑ፤ እንዲሁም የአባታችን ብለው የሚጠሩት የያዕቆብ ጉድጓድ መሆኑ::

***4፥6 ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጉድጓዱ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበረ::*** ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ በመንገዝ ላይ ነው፤ ቀኑም እኩለ ቀን የሐሩር ጊዜ ነው:: ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ደከመው፤ በጉድጓዱም አጠገብ ተቀመጠ:: ከይሁዳ ወደ ገሊላ ሲሔድ ሲካር ለመድረስ በግምት የሁለት ቀን ያህል የእግር ጉዞ እንደሚፈጅ ይገመታል:: ስለዚህ ኢየሱስ በዚያ ቀን ደክሞታል:: *ደክሞ* የሚለው ቃል የእርሱን እውነተኛ ሰው መሆን[21] ያሳየናል:: አንዳንዶች «ሰው መሰል ነበር» እያሉ እንደሚናገሩት ሳይሆን ኢየሱስ ሲጓዝ ሰው እንደመሆኑ ይደክመው፣ ይርበው፤ ውኃም ይጠማው ነበር::

***4፥7 ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች::*** በጉድጓዱ አጠገብ አስቀድሞ ደርሶ የተቀመጠ በዚያ *ማለፍ ግድ* የሆነበት ኢየሱስ ነበረ:: ከዚያም ሴቲቱ ወደዚያ ጉድጓድ መጣች::

***4፥8 ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበርና::*** ይህም በተጨማሪነት ጌታ ኢየሱስ ምግብ የሚያስፈልገው ከእኛ እንደ አንዱ ሰው መሆኑን ያስገነዝበናል:: ደቀ መዛሙርቱ ከከተማ ከተመለሱ በኋላ ጌታን *መምህር ሆይ ብላ ብለው ለመኑት 4፥31::* በኋላም *የሚበላው አንዳች ሰው አምጥቶለት ይሆንን? ተባባሉ 4፥33::* ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነው::

[21] True humanity

***4፥9 ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ?*** ሴቲቱ ሳምራዊነቷን በመገንዘብ ይህን የመደነቅ ጥያቄ የምታቀርበው ኢየሱስ አይሁዳዊ ሰው መሆኑን አውቃ ነው። ***አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና 4፥9***፡ እርሱ ውኃ ስለጠየቃት ተደንቃለች። ***አይተባበሩም*** የሚለው ቃል ለምሳሌ በአንድ ዕቃ እስመብላትን ወይም እስመጠጣትን ያመለክታል። ሳምራውያን በበሉበት ወይም በጠጡበት አይሁድ አይበሉም፣ አይጠጡም። ይህንም ሴቲቱ ታውቃለች። ያ ግድግዳና ልዩነት መኖሩን በማወቅ ውኃ እጠጪኝ ስላላት ተደንቃለች። «ይህን የልዩነት ግድግዳ አልፌህ ከእኔ እንዴት ውኃ ጠየቅህ» ማለቷ ነው። ኢየሱስ በሰማርያ ***ማለፍ ግድ*** የሆነበት ይህን ግድግዳ በማለፍ ከሰማርያ ሰዎችን በእርሱ እንዲያምኑ ሊጠራ ነው። አለመተባበራቸው ለመነጋገር እንኳ እስከሚጸየፉ ድረስ ይደርስ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ሴቲቱን ያነጋገራት በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረውን ትልቅ የልዩነት ግድግዳ አልፎ ነው። ለአንድ አይሁዳዊ ሳምራዊን (ያውም ሳምራዊትን ሴትና ታሪኳ ጥሩ ያልሆነን) ማነጋገር እንደ ጸያፍ በተቆጠረበት ዘመንና ባሕል ጌታ ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ይፈጽም ዘንድ አደረገው።

ይህ በዚህ ዘመን ላለነው ክርስቲያኖች ትምህርትና ምሳሌ ነው። በዘመናችን በዜጐች መካከል በቀለም፣ በመልክ፣ በቁመና፣ በቋንቋ፣ በተለያየ የትምህርት ደረጃ፣ ወይም በመሰል ልዩነቶች ምክንያት መበላለጥ፣ መናናቅ፣ ያለመቀራረብ ግድግዳዎች ይታያሉ። ከጌታ አገልግሎት የምንማረው ወንጌል የልዩነት አጥርን የሚዘል፣ ግድግዳን ሁሉ አልፎ የሚሄድና «ልዩ ወደሆነው» የሚዘረጋ መሆኑን ነው። በየትኛውም ደረጃ፣ ጐሳ፣ ባሕል ወይም እምነት ያሉት እግዚአብሔርን ያውቁ ዘንድ ግድግዳን አልፎ፣ አጥርን ዘሎ ሄዶ ወንጌልን መናገር ይገባል። ሁሉም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች ናቸውና። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን የላከው ዓለሙ ሁሉ (ሰው ሁሉ) እርሱን በማመን ይድን ዘንድ ነውና።

***4፥10 ኢየሱስም መለሰ፡- የእግዚአብሔርን ስጦታና ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ አንቺ ትለምኚው ነበርሽ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር አላት።*** ይህች ሴት ያላወቀቻቸው ነገሮች እሱ።

- አንደኛው የእግዚአብሔርን ስጦታ አላወቀችም። የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ኢየሱስን አላወቀችም። የእግዚአብሔር ስጦታ የዘላለም ሕይወት ነው።

- ሁለተኛ ሰጪውን አላወቀችም። ሰጪው እርሷን ያነጋግራት የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ***የሕይወት ውኃ*** ሰጪ

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰመነው ሁሉ የሕይወት ውኃን ይሰጣል። የሕይወት ውኃን የማግኛው መንገድ እርሱን መጠየቅ ብቻ ነው።

***የሕይወት ውኃ*** እግዚእብሔርን በመፈለግ የተጠማች ነፍስ እርሱን በማወቋ የምታገኘው የውስጥ እርካታ ነው፤ የመንፈስ እርካታ። ይህን የነፍስ ጥማት የሚያረካ አንድ ብቻ ነው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ።

ስለ ሕይወት ውኃ አስቀድሞ በብሉይ ኪዳንም ብዙ ተነግሮ ነበር። ለምሳሌ:-

- «ከቤትህ ጠል ይጠግባሉ፥ ከተድላህም ፈሳሽ ታጠጣቸዋለህ። የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና፤ በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን» (መዝ 36፥8-9)።
- «ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች» (መዝ 42፥1-2)።
- «ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች አድርገዋልና፤ እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል፥ የተቀደዱትንም ጉድጓዶች፥ ውኃውን ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል (ኤር 2፡13-)።
- «አቤቱ፥ የእስራኤል ተስፋ ሆይ፥ የሚተዉህ ሁሉ ያፍራሉ፤ ከአንተም የሚለዩ የሕይወትን ውኃ ምንጭ እግዚአብሔርን ትተዋልና በምድር ላይ ይጻፋሉ» (ኤር 17፡13-)።

***የሕይወት ውኃ*** ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ሕይወት አስቀድሞ ከእርሱ ዘንድ ተሰጠን። በኋላም የዘላለም ሕይወት በልጁ በኩል ለሚያምን ሁሉ ይሰጣል። ሌሎች ሕይወትን የሚሰጡ፣ እንሰጣለን የሚሉ ሁሉ ግን ቃሉ እንዳለ የተቀደዱ ጉድጓዶች ውኃ የማይዙ ጉድጓዶች ናቸው፤ ከንቱ ተስፋ ብቻ። ውኃ ያላቸው ቢመስሉም ውስጣቸው ግን ሕይወት የሌላቸው ናቸው።

***4፥11 የሕይወት ውኃ ከወዴት ታገኛለህ?*** ውኃ የለመናት እርሱ «ውኃ» ሰጪ እንደሆነ ሲነግራት አስደንቋታል፤ ደግሞም መቅጃ አልያዘም። እንደ እርሷ የተዘጋጀ ዕቃም የለውም፤ ውኃ ለማውጣት ***ጉድጓዱም ጥልቅ ነው።*** ውኃ የሚገኝበት መንገድ መቅጃ በመያዝ እንደሆነ ታውቃለች። ስለዚህ «ውኃ» ሰጪ መሆኑ ስላስደነቃት ማንነቱን መጠየቅ ትጀምራለች።

***4፥12 በእውኑ አንተ ይህን ጉድጓድ ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን?*** አባታቸው ያዕቆብ ውኃ የሚሰጥ ጉድጓድ ሰጣቸው፡፡ ሴትዮዋን የሚያነጋግራት ደግሞ ማንነቱን የምትጠይቀው የሕይወትን ውኃ የሚሰጥ እንደሆነ ነግሯታል፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው ጉድጓድ ከሰጣቸው የሚበልጥ መሆን እንዳለበት ገምታለች፡፡ ይህን ለማወቅ ***ትበልጣለህን?*** ብላ ትጠይቀዋለች፡፡

***4፥13 ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል፦*** አንድ ጊዜ ምግብ የሚበላ መልሶ እንደሚርበው ሁሉ ውኃ የሚጠጣም መልሶ ይጠማል፡፡ በአካላዊው ዓለም ረሃብና ጥማት ሁልጊዜ የሚኖር ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ከያዕቆብ ጉድጓድ የምትቀዳው ውኃ የሳምራዊቷን ሴት የውኃ ጥማት ለአጭር ጊዜ ያረካል፡፡ ተመልሳ ለመቅዳት ወደ ጉድጓዱ ትመጣለች፡፡ ይህንን አዘውትራ ታደርገዋለች፡፡ እንዲሁ በሥጋ ሕይወት የሚደረጉ ፍላጐትን የማሟያ መንገዶች ሁሉ አንድ ጊዜ የተደረጉት ሁሉ ለሁልጊዜ አይበቁም፤ ሌላው ቀርቶ ሳምራዊቷ ሴት እንኳ አምስት ባሎች ነበሯት፡፡ በሥጋ ሰውነታችን እንደሚራብ እንደሚጠማ ሁሉ ነፍሳችንም ትራባለች ትጠማለች፡፡ ነፍስን ግን የሚያረካት መንፈሳዊ ነገር የሕይወት ውኃ ነው፡፡ የሕይወት ውኃን ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ይሰጣል፡፡ ጌታ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም እንዳለ ከዚህ ውኃ የሚጠጣ አንድ ጊዜ የጠጣው ለሁልጊዜ ነው፡፡

***4፥14 እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ፡፡*** ከያዕቆብ ምንጭ ቀድቶ የሚጠጣ ሁልጊዜም መቅዳት፤ ሁልጊዜም መጠጣት ያስፈልገዋል፡፡ ምናልባትም ራሱ ምንጩ ይደርቃል፡፡ ጌታ ኢየሱስ የሚሰጠው ውኃ ግን ለዘላለም እያስጠማም እንዲሁም ***የውኃ ምንጭ በእርሱ ውስጥ*** እዲፈልቅ ያደርጋል፡፡ ምንጩ የማይደርቅ በነፍስ ውስጥ እየፈለቀ የሚኖር ሁልጊዜ የሚያረካ ይሆናል፡፡ መንፈሳዊ ጥማትን ያረካል፡፡

***ለዘላለም አይጠማም*** ሲል ከዚህ ኢየሱስ ከሚሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሰው ምንም ችግር አይደርስበትም ማለት አይደለም፡፡ ጌታ «በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬያችኋለሁ፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» (ዮሐ 16፡33) እንዳለ በዓለም ውስጥ የሚኖር ክርስቲያን መከራ ይኖርበታል፡፡ እንደ ሌላው እንደ ማንኛውም ሰው ምግብ ያስፈልገዋል፤ ውኃም ይጠማል፡፡ በኢየሱስም ስለሆነ ከዓለም መከራ ይጨመርበታል፡፡ ይህ ግን በውስጡ የሚፈልቀውን የሕይወት ውኃ ምንጭ አይደፍነውም፤ አይዘህ ብሎታልና፡፡ በአማኝ ውስጥ ሁልጊዜ

የሚኖረውና የሚፈልቀው የሕይወት ውኃ ምንጭ ድልን አሸናፊነትን ይሰጠዋል፡፡

*4፥15 ጌታ ሆይ፥ እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ አለችው፡፡* ውኃን መቅዳት በዚያን ዘመን ከባድ ሥራ ነው፡፡ ትልቅ የውኃ መቅጃ ወይም እንስራ ተሸክሞ በቀን ወደ ውኃ ጉድጓድ መመላለስ፤ ያውም በቀትር፡፡ ለሁልጊዜ የሚሆን ውኃ አንድ ጊዜ ብታገኝ ኑሮዋን ያቃልልላታል፡፡ ስለዚህ ይህች ሴት ትልቁ ጊዜያዊ ችግሯ መጠማትና ውኃ ለመቅዳት ወደ ጉድጓዱ መመላለስ ስለሆነ ለዚህ ጊዜያዊ ችግሯ መፍትሔ እንዳገኝች አስባ ትጠይቀዋለች፡፡ ጌታ ግን ከጊዜያዊ ችግር ያለፈ ለዘላለም የሚሆንን ውኃ ስለምታገኝበት መንገድ ነገራት፡፡

*4፥16 ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ፡-* ሴትዮዋ *ውኃ ስጠኝ 4:15* ብላ ስትጠይቀው የምትጠብቀው መልስ እሺ ወይም አይሆንም የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ጌታ ግን የንግግሩን ርዕስ ሕይወትን በጠቅላላ ወደሚለውጥ አቅጣጫ ይቀይረዋል፡፡ ውኃ ከመቅዳት ያለፈ የሕይወቷን የውስጥ ጉዳይ የሚነካ ርዕስ ያነሳል፡፡ ሴትዮዋ በየዕለቱ ውኃ ከመቅዳት ያለፈ የሕይወት ችግር አለባት፡፡ ጌታ ይህን ጥያቄ ሲያነሳ ስለ እርሷ የግል ሕይወት ሳይቀር እንደሚያውቅ መግለጡም ጭምር ነው፡፡ *ሴቲቱ መልሳ፡- ባል የለኝም አለችው 3፥17*፡

*4፥18 ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤ አምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት፡፡* ጌታ በተደጋጋሚ ባሎችን እንዳገባች ኃጢአተኛ ኑሮዋን ይገልጥባታል፡፡ ግን ደግሞ እውነተኛነቷን *መልካም ተናገርሽ* እንዲሁም *እውነት ተናገርሽ* በማለት ይገልጻል፡፡ ስለ ኃጢአተኛነቷ አልወቀሳትም፤ ያደረግሽው ትክክል ነውም አላላትም፡፡ በዚህ ንግግሩ እውነት የሆነውን ስለ ገለጠላት ወዲያው የተናጋሪውን ማንነት ማስተዋል ትጀመራለች፡፡

*3፥19 ጌታ ሆይ አንተ ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ አለችው፡፡* ነቢይ ስትል በሰው ሕይወት ውስጥ የተደበቀውን (ያለፈውን ታሪክ) የሚያውቅ ማለቷ ነው፡፡ ነቢይ እግዚአብሔር ሲገልጥለት ይህን ያውቃል፡፡ ጌታን ነቢይ ማለት በቂ ገላጭ አይደለም፤ ከነቢይ በላይ ነውና፡፡ ሌሎችም ንጉሥ ያሉት አሉ እርሱ ግን ከንጉሥ በላይ ነው፡፡ ጌታ አዳኝ እንደሆነ እርሷ እስክትገነዘብ ድረስ በንግግሩ ቀጥሏል፡፡

***4፥20 አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም፦ ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ።*** ኢየሩሳሌም የአምልኮ ቦታ እንደሆነ ከዘዳ 12፥5፤ 2ዜና 6፥6፣ 7፥12፤ መዝ 78፥67-68 እንመለከታለን። ይህች ሴት ***በዚህ ተራራ*** ስትል ገሪዛም ተራራን ማለቷ መሆን አለበት (ዘዳ 11፥26-29፤ 27፥1-8)። አምልኮ መደረግ ያለበት በገሪዛም ተራራ ነው በሚሉት ሰማርያውያንና በኢየሩሳሌም ነው በሚሉ አይሁድ መካከል የቆየ ክርክር ስለ ነበረ ሴትዮዋ አይሁዳዊ ነቢይ ስላገኘች ይህን እንዲያረጋግጥላት መጠየቋ ነው። ጌታ ከአቀረበችው አማራጭ አንዱን በመውሰድ ትክክለኛው ይኸ ነው አይላትም። ወደ ላቀ ሕይወት ይመራታል እንጂ። በታሪክ ውስጥ በሰማርያውያንና በአይሁድ መካከል መለያየት ነበረ። ቤተ መቅደሱ እንደገና በሚሠራበት ጊዜ ሰማርያውያን በሥራው እንዳይካፈሉ አይሁድ ከልክለዋቸዋል (ዕዝ 4፥1-2)።

***4፥21 በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል።*** ስግደት በኢየሩሳሌም ወይም በገሪዛም ተራራ መሆኑ ይቀራል፤ ሌላ ምዕራፍ ይጀመራል፤ ***አሁንም ሆኗል 4፡23*** በማለት ወደ ሌላ ደረጃ ወይም ምዕራፍ መድረሱን ያሳያል። ለእግዚአብሔር አብ የሚቀርብ አምልኮ በቦታ የተወሰነ ሳይሆን በመንፈስ የሚደረግ መሆኑን ይገልጽላታል።

***4፥22 እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን።*** እዚህ ላይ ጌታ ***እኛ*** ብሎ መግለጹ እርሱ ከአይሁድ ወገን መሆኑን ያመለክታል። መዳን (መባረክ) ከአይሁድ እንደሆነ በመጽሐፍ ውስጥ ተገልጧል (ዘፍ 12፥3)። በዚያን ዘመን አይሁድና ሰማርያውያን ስለ አምልኮ የማያውቁት አለ። ሰምራውያን ያነቧቸው የነበሩት መጻሕፍት ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉትን አምስት መጻሕፍት ብቻ ስለ ነበረ፣ በተቀሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ አምልኮ የተገለጠውን አያውቁም ነበረና ሙሉ መረዳት አልነበራቸውም። እግዚአብሔርን ለማምለክ መፈለጋቸው ጥሩ ሆኖ ሳለ የሚያመልኩትን በትክክል አያውቁም።

***4፥23 በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል።*** ከአይሁድም ከሰማርያውያንም ስሆኑ ለእግዚአብሔር በእውነት ለሚሰግዱ ጊዜው ደረሰ፤ ለአብ ***በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት*** ጊዜ ነው እርሱም አሁን ነው። አይሁድና ሰምራውያን በአንድ ላይ ለአብ በእውነት የሚስግዱበት ጊዜ በክርስቶስ በኩል ነው። የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሁለቱን ያዋሃደ ከሁለቱም አንድ አዲስ ሰው ያመጣ ክርስቶስ ነው (ኤፌ 2፥14-16)።

በክርስቶስ የመጣው እውነተኛው ስግደት ***በመንፈስና በእውነት 4:24*** የሆነ ሁለት ቁልፍ ባሕርያት አሉት።

- ***በመንፈስ፡-*** በመንፈስ የሚለው ስለ ሰው የውስጥ ማንነቱ (መንፈሱ) ሲያመለክት መንፈስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ቀጥተኛ ግንኙነት ያሳያል። ይህ በሰው ውስጥ ከሚፈልቀው የሕይወት ምንጭ ውኃ ጋር በመያያዙ የሚኖረው ቀጥተኛ ግንኙነት ነው። በሥጋ በየትም ቦታ ሆነን በመንፈሳችን ከእግዚአብሔር ጋር የምናደርገው ግንኙነት ነው። ይህ በመንፈስ የሚሆነው ስግደት ዳግመኛ በተወለደው ሰው ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ እማካይነት የሚሆን ስግደትና ግንኙነት ነው።
- ***በእውነት፡-*** ማለት ደግሞ ማስመሰል ወይም ግብዝነት በሌለው እውነተኛነት ማለት ነው። እውነት ወደሆነው እግዚአብሔር እውነት በሆነው በቃሉ መሠረት መቅረብ፣ ለእርሱም መስገድ ማለት ነው። በአንጻሩ በእውነትና በመንፈስ ያልሆነ አምልኮ አስመሳይነት ያለበት፣ ያልሆኑትን ሆኖ ለመገኘት የሚጥርና ከእግዚአብሔር ጋር ሕያው ግንኙነት የማያደርግ አምልኮ ነው።

***4፥24 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።*** በዚህ ቁጥር መሠረት ስግድት የሚገባው ***እግዚአብሔር*** ነው። እንዲሁም ስግደት የሚገባው ***አብ*** እንደሆነ ***ለአብ የማትስግዱበት ጊዜ 4፥21፤ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ 4፥23፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤ 4፥23*** ከሚሉት እንገነዘባለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ መካከል ትልቅ መንፈሳዊ መልእክት አለ። ስግደትን ከሥላሴ አካላት የመጀመሪያው ለሆነው ለአብ[22] ማቅረብ ለእግዚአብሔር[23] ማቅረብ ነው።

***መንፈስ*** የእግዚአብሔር ማንነት መግለጫ ነው። እግዚአብሔር እንደ ሰው በቦታና በጊዜ የተወሰነ አይደለም። የሰው ዓይነት አካላዊ አቋምም ያለው አምላክ አይደለም። እርሱ በሁሉም ቦታ አለ። በሁሉም ቦታ በማንኛውም ጊዜ ሊመለክ ይችላል። እግዚአብሔር መንፈስ ነውና አይደክምም። እርሱ ሁሉን ያውቃል። ስለዚህ ለእግዚአብሔር በመንፈስ መስገድ ማለት መንፈስ ከሆነው ከእርሱ ጋር በመንፈስ የሆነ ግንኙነትን፣ ስግደትን ማቅረብ ማለት ነው። በ3፡6 እና 8 እንዳየነው በመንፈስና በእውነት የሆነ አምልኮ የሚጀምረው ከመንፈስ ቅዱስ

---

[22] God the Father

[23] The Godhead, The Divine God

ዳግመኛ ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ዳግመኛ ሳይወለዱ እውነተኛ አምልኮና በመንፈስ የሆነ ስግደትን ማቅረብ አይቻልም።

***4፥25 መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው።*** ሳምራውያን አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ብቻ ያላቸው ሲሆን በዘዳ 18፥15-18 ያለው ክፍል ስለሚመጣው ነቢይ ስለሚናገር በዚያ መሠረት ተስፋ ያደርጋሉ። ነገር ግን ሙሉ መረዳት አልነበራቸውም፣ የሚመጣው መሲሕ ከአይሁድ እንደሚሆን የተገነዘቡ አይመስልም።

***4፥26 ኢየሱስ የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት።*** የአይሁድ አለቆችና ፈሪሳውያን ጌታን ማን እንደሆነ ብዙ ጊዜ ይጠይቁት ነበረ። ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ መሲሑ እንደሆነ በቀጥታ ሲነግራቸው አልወደደም (ስምሳሌ 10፥24)። የኃጢአተኛ ኑሮ ስኖረች ከሳምራውያን ወገን ስሆነችዋ ለዚህች ሴት ግን ቀጥታ ራሱን ይገልጥላታል።

***4፥27 ደቀ መዛሙርቱ መጡና ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ፡-*** ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ የሄዱት ደቀ መዛሙርት (4፥8) በተመለሱ ጊዜ ጌታ ***ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ***፡ ይህ በጊዜውና በዚያ አካባቢ የነበረውን ባሕላዊ ሁኔታ ያመለክታል። አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና (4፥9) ኢየሱስ የሳምራዊት ሴት ማነጋገሩ በጊዜው የነበረውን የልዩነት ግድግዳ አልፎ መሄዱን ያሳያል። ጴጥሮስ ምንም ንፁህ ያልሆነ በልቼ አላውቅም (ሐዋ 10፡14) እንዳለው። ያም ቢሆን ግን የጌታቸውን ማንነትና አስተሳሰቡን ያውቁ ነበርና ***ስለ ምን ትናገራታለህ? ያለ ማንም አልነበረም 4፥27***።

***4፥28 ሴቲቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች።*** ለሴቲቱ እንስራዋ ትልቅ ህብቷ ነው። ጌታን ***የምትቀዳበት የለህም*** ብላ የምትናገረው እርሷ ግን እንስራ ነበራት። ስለዚህ ትልቅ መጣሪያዋ ነው። ጌታ ካነጋገራት በኋላ ግን ከዚህ የሚበልጥ ነገር ሆኖላታልና ይህንም ቢሆን ትታ ተመለሰች። ይህች ሴት እንስራዋን ትታ መሄዷ ልትቀዳ ከመጣችው ውኃ ይበልጥ ከውስጧ የሚፈልቀውን ምንጭ ምን ያህል እንደተጠማች ያመለክታል። እንዲሁም እንስራዋን ትታ መሄዷ የምትመለስ መሆኗንም ያሳያል።

***4፥29 ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፡-*** ሴትዮዋን ያስደነቃት የቀደመ ታሪኳን ስለነገራት ነው። ከአይሁድ ወገን የሆነ ይህ ሰው የእርሷን ታሪክ የሚያውቅ ከሆነ ***እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን አለች 4፥29።*** ፊልጶስ ናትናኤልን መጥተህ እይ (1፡47) እንዳለው

ይህችም ሴት ወደ ከተማ ሄዳ ሰዎቹን ***ኑና እዩ 4፡29*** አለች፡፡ ይህ ሰዎች የራሳቸውን ውሳኔ እንዲያደርጉ ጥሩ የመጋበዣ መንገድ ነው፡፡ የተሰያየ አስተሳሰብ የሚኖራቸውን ሰዎች ራሳቸው ወደ ኢየሱስ መጥተው ሰምተውና አይተው እንዲወስኑ ማድረግ፡፡ ***እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? 4፥29*** የሚለው ይህ አባባሏ ለሰሚዎች የበለጠ ጉጉት የሚፈጥር ነው፡፡ ስለ ክርስቶስም የሚያወቁ፣ የሚጠባበቁም እንደሆኑ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም፣ ***ከከተማ ወጥተው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር 4፥30***፡

***4፥31 ደቀ መዛሙርቱ መምህር ሆይ፥ ብላ ብለው ለመኑት፡፡*** ደቀ መዛሙርቱ ከጌታ ጋር ከይሁዳ ወደ ገሊላ እየሄዱ ናቸው፡፡ ጌታም በሰማርያ ሲካር በሚባለው ቦታ የውኃ ጉድጓድ አጠገብ ደክሞት እንደ ተቀመጠም ያውቃሉ፡፡ እነርሱም ምግብ ሊገዙ ሄደው ምግብም አምጥተዋል፡፡ ምግብ እንደሚያስፈልገው ስለሚያውቁ ***ብላ ብለው ለመኑት፡፡*** የጌታ መልስ ግን እነርሱ የጠበቁትን ዓይነት አይደለም፡፡ ***እናንተ የማታወቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ አላቸው 4፥32***፡

***4፥33 ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ፡- የሚበላው አንዳች ሰው አምጥቶለት ይሆንን? ተባባሉ፡፡*** የሳምራዊቷ ሴት ስለ ሕይወት ውኃ ሲነግራት (4፥10) በእንስራ ተቀድቶ ስለሚያዘው ውኃ ታስብ ነበር፡፡ እንዲሁም ደቀ መዛሙርት የአባቱን ፈቃድ ስለማድረግ ሲነግራቸው እነርሱ ስለሚበላ ምግብ ያስቡ ነበር፣ ሰዎች አይደሉ!! ***የምበላው መብል ለእኔ አለኝ*** ሲል በዚያ ሰዓት ለሴትዮዋ የገለጠላትንና የከተማውም ሕዝብ ወደ እርሱ መምጣታቸውን ሁሉ እርሱን የሚያጠግበው መንፈሳዊ መብል ሆኖለታል፡፡

***4፥34 የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው*** - እንዳላቸው በዚያ ሰዓት በሰማርያ ለማለፍ ግድ የሆነበት ምክንያት እየተፈፀመ ነው፡፡ የላከውን የአብን ፈቃድ እየፈፀመ ነው፡፡ ይህ ለእርሱ መብሉ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውና የኖረውም የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ ነው፡፡ በዚህም መንፈሳዊ እርካታን አግኝቷል (17፡4)፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ማለት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራስን ማስገዛት፣ በእግዚአብሔር ሃሳብ ዕቅድ መሠረት መኖር ማለት ነው፡፡

ስለዚህ የአባቱን ፈቃድ መፈጸም ለኢየሱስ ክርስቶስ መብሉ ነው፤ ደስታንም ይሰጠዋል፡፡ እዚህ ላይ ***የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ*** ነው ሲል ፈቃድ፤ ማድረግና መፈጸም የሚሉትን ቃላት እናያለን፡፡ ፈቃዱ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ***ሥራ***

ነው:: የአገልጋዩ ምኞት ወይም ሃሳብ አይደለም:: የተሰጠው *ሥራ* ደግሞ ከተጀመረ በኋላ እየተሠራ መቀጠል አለበት:: ተጀምሮ የተወለነ ደረጃ ሄዶ «ሲፈጽመው አቃተው» (ሉቃ 14:30) እንዳተባለው እንዳይሆን:: ስለዚህ ማድረግ አንድን ተግባር መሥራት (ማከናወን) ሲሆን፤ መፈጸም ደግሞ በዚያ ተግባርና ሥራ ላይ እስከ ግብ (መጨረሻ) ድረስ መድረስ ነው:: ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ «ተፈጸመ» (ዮሐ 19:30) ሲል አብ የሰጠውን ተግባር ሥራ አጠናቀቀ ማለት ነው:: *ሥራን መሥራት* (መጀመር) ብቻ ሳይሆን መፈጸም (በሙሉ ማጠናቀቅ) ይገባል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በ17፥4 ጌታ ኢየሱስ «እኔ ልሠራው የሰጠኸኝን *ሥራ ፈጽሜ* በምድር አከበርሁህ» እንዳለ በመንፈሳዊ አገልግሎት:-

- እንደኛ የላከውን *ፈቃድ ማወቅ*፤
- ሁለተኛ *ያንን ፈቃድ ማድረግ*፤
- ሦስተኛ *ያንን ፈቃድ* ወይም *ሥራ መፈጸምን* ይጠይቃል::

***4፥35 ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም ይመጣል ትሉ የለምን?*** ይህ ሁኔታ የገበሬዎችን መጠባበቅ የሚያሳይ ነው:: ብዙ ጊዜ በይሁዳ አካባቢ የሚዘሩ አዝመራዎች በአራት ወር ጊዜ ውስጥ የሚደርሱ ናቸው:: አራት ወር *ሥራው* ተጀምሮ የሚያልቅበት ጊዜ ነው::

***4፥35 ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ::*** ይህን በተናገረ ጊዜ ሰዎች ከከተማ ***ወደ እርሱ ይመጡ ነበር 4፥30::*** እነዚህ ከጌታ ለመስማት የሚመጡ በመጨረሻም ለማመን የሚዘጋጁ ናቸው:: የነጣ እርሻ ናቸው::ሰዎች ሕያው ዘር የሚዘራባቸው እርሻዎች ናቸው:: ሰዎች ወንጌልን ሲሰሙ የሚታጨዱ አዝመራዎች ናቸው:: ሰዎችን ለመታጨድ እንደደረሰ አዝመራ አድርጐ መቁጠር ከሰማያዊ እይታ አንጻር ለሰዎች ማሰብ ነው::

***4፥36 የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል፥ የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው የዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል::*** የሚያጭደው ደመወዙ ደስታ ነው፤ በማጨዱ ደስ ይለዋል:: ሰዎችን ወደ ዘላለም ሕይወት መምራት:: ስለሆነም የሳምራውያን መታጨድ ወይም ማመን ጌታን ምን ያህል ደስ እንዳሰኘው ያመለክታል::

ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ አሁን የሚዘራም የሚያጭድም ነው:: በሰማርያዊት ሴት በኩል ዘራ:: ከከተማም ወደ እርሱ የሚመጡት የሰማርያ ሰዎች በእርሱ አመኑ ስለዚህ አጨደ:: በአጠቃላይ ***የሚዘራና***

*የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል* ሲል የሚዘራው የተለየ የሚያጭደውም ሌላ ቢሆን ለዘላለም ሁለቱም በአንድ ላይ በሥሩት ደስ ይላቸዋል፡፡ በአንድ ላይ ይሆናሉና፡፡

***4፥38 እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ፡፡*** የጌታ ደቀ መዛሙርት ጌታ በሳካቸው ጊዜ በተለይም ጌታ ካረገ በኋላ በነበራቸው አገልግሎት እጅግ እንዳጨዱ እናስተውላለን፡፡ ለምሳሌ በበዓለ ሃምሳ ቀን ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች እንዲሁም ከዚያ በኋላ ብዙዎች ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ በወንጌል እንዳመኑ እንረዳለን፡፡ ይህ ማጨድና ይህ ሁሉ አዝመራ ጌታ እንደተናገረው ቀደም ብለው በመዝራት ከደከሙት ሰዎች የተገኘ ውጤት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ***ሌሎች ደከሙ*** የተባለላቸው በብሉይ ኪዳን የነበሩ ነቢያትና የጌታን መምጣት ይናገሩ፣ ያዘጋጁ፣ መንገድ ይጠርጉ የነበሩትን ሁሉ ማለት ይሆናል፡፡

በአሁኑም ዘመን በወንጌል አገልግሎት በአንድ ቦታ ሰዎች ጌታን ሲቀበሉ በዚያች ቀን በሰሟት ቃል ብቻ ሳይሆን እንደሚችል ልብ ማለት ይጠቅማል፤ ትሑትም ያደርጋል፡፡ ሰዎች ለብዙ ጊዜ በተለያየ መንገድ ወንጌልን ሲሰሙ፣ ጽሑፍ ሲያነቡ፤ በሬዲዮም ሆነ በሌላ መንገድ ከሰዎች ሲሰሙ እንዲሁም የክርስቲያኖችን አካሄድ ሲያዩ ኖረው አንድ ቀን ወደ ውሳኔ ይደርሳሉ፡፡ አንድ ቀን ለማጨድ የሚደርሱት ብዙ ጊዜ በተለያየ መንገድ ከተዘራው ወንጌል የተነሳ ነው ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የወንጌል አገልግሎት የተያያዘና የተደጋገፈ ነው፡፡ አንዱ የዘራውን ማን መጥቶ እንደሚያጭድ አይታወቅም፡፡ እግዚአብሔር ግን ያውቀዋል ለአገልጋዮቹም ደመወዛቸውን ይከፍላል፡፡

***4፥39 ሴቲቱም ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት፡፡*** የሰማርያ ሰዎች የተሳቡት በአንዲት ሴት ምስክርነት ነው፡፡ ***ኑና እዩ*** ያለቻቸው ***ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን*** በማለቷ፡፡ በአንዲት ሴት ምክንያት የከተማው ሰዎች አመኑ፡፡ አንድ ሰው እውነትን ለከተማ ለማድረስ በቂ ነው፡፡ ኑና እዩ ብሎ ለማወጅ፤ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን፤ የዘላለም ሕይወት ምንጭን እንዲጠጡ ለመጋበዝ በቂ ነው፡፡

***4፥40 በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት፡፡*** ሰዎቹ ወደ እርሱ ከመጡ በኋላ ጌታን ***በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት***፡፡ አይሁዳዊው ሰው በሰማርያ ከተማ እንዲገባ በእነርሱም ዘንድ እንዲኖር በአይሁዳውያንና በሰማርያውያን መካከል ከነበረው ልዩነት አንጻር የማይታሰብ ነው፡፡ ኢየሱስን ግን የቀረበውና ያወቀው ሁሉ የሚወደው መሆኑን በዚህ

እንመለከታለን:: በአንድ ከሰዓት በኋላ ከአንድ ሰው ተነሥቶ የከተማው ሰው ሁሉ እስኪሰወጥ ድረስ እዝመራን ማጨድ::

***4፥42 እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና፤ እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን::*** የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የነበሩት እንድርያስና ዮሐንስ በኢየሱስ ዘንድ ከዋሉ በኋላ (1፥40) የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ወሰኑ:: እዚህ ደግሞ ኢየሱስ ሁለት ቀን ያህል ከእነርሱ ጋር ከኖረ በኋላ ሰዎች እርሱ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን አሉ:: እነ እንድርያስ መሲሑን አግኝተናል ብለው ነበር:: እነዚህም ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ አናውቃለን አሉ:: ወደ ኢየሱስ የቀረበና አብሮት የዋለ ሰው የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ይረዳል:: ስለዚህ ሰዎች ወደ ኢየሱስ እንዲቀርቡ ማድረግ እርሱን የበለጠ እንዲያውቁትና ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል::

እነዚህ ሰዎች ***እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና*** ማለታቸው ትክክለኛ የመንፈሳዊ እድገት አቅጣጫ እንደያዙ ያሳየናል:: በመጀመሪያ በኢየሱስ ያመኑት ከሴትዮዋ ምስክርነት የተነሣ ነበረ:: በዚያው ሳይ ብቻ አላቆሙም፤ ወደ ኢየሱስ ቀረቡ፣ ሰሙት፤ አሁን የራሳቸውን ውሳኔ አደረጉ:: በመንፈሳዊ እድገት በሌላው ምስክርነት ወደ ኢየሱስ የመጣ ሰው ራሱ ሰምቶት፣ ተረድቶት የራሱን ውሳኔ አድርጎ ከክርስቶስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ማድረግ ሲጀምር በእድገት መንገድ ላይ ነው ማለት ነው:: በሌላ ሰው ምስክርነት ላይ ብቻ ያልቆመ ራሱ ግን በቀጥታ ግንኙነት በማድረግ ከወይኑ ግንድ ጋር የተጣበቀ መሆኑ ነው::

***ከሁለቱ ቀኖች በኋላም ከዚያ ወጥቶ ወደ ገሊላ ሄደ 4፥43:*** ቀደም ሲል በምዕራፍ አራት መጀመሪያ ላይ እንዳየነው ጌታ ይሁዳን ትቶ ወደ ገሊላ ይሄድ ነበር:: በሰማርያ ሁለት ቀን ከዋለ በኋላ (4፥40) አሁን ደግሞ ጉዞውን ወደ ገሊላ ይቀጥላል::

***4፥44 ነቢይ በገዛ አገሩ እንዳይከበር ኢየሱስ ራሱ መስክሮአልና::*** ጌታ በይሁዳ እያለ ከዮሐንስ ይልቅ ብዙ ደቀ መዛሙርትን ያደረጋል (4፡1) እንደተባለው ዝናው እየወጣ ነበረ:: ስለሆነም ይሁዳን ትቶ ወደ ገሊላ ሄደ:: በገሊላ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፤ ወይም እንደ ነቢይ ሳይሆን እንደ አንድ ተአምር ሠሪ (ምልክት አድራጊ) ብቻ ቢቆጥሩትም ወደ እዚያ ሄደ:: የሚገባውን ክብር አልሰጡትም:: በአጠቃላይ ኢየሱስ ወደ ወገኖቹ መጣ እነርሱም አልተቀበሉትም (1፡11):: የገሊላ ሰዎች የተቀበሉት ራሳቸው በኢየሩሳሌም ስለ ነበሩና ያደረገውን ስላዩ ነው (4:45)::

***4፥46 ልጁ የታመመበት ከንጉሥ ቤት አንድ ሹም፡-*** ቅፍርናሆም ጌታ ከነበረበት ከገሊላ ቃና ከ30 ኪሎ ሜትር በላይ ይርቃል። ይህ ሰው አይሁዳዊ ያልሆነ ከሕዝብ ወገን የሆነ ሳይሆን አይቀርም። ወደ ኢየሱስ መጣና ***እንዲፈውስለት ለመነው 4፥47***።

***4፥49 ጌታ ሆይ ብላቴናዬ ሳይሞት ውረድ አለው።*** ይህ ሹም ኢየሱስን ይዞ ሊሄድ የተዘጋጀ ነበረ። የጌታ መልስ፡- ***ሂድ ልጅህ በሕይወት አለ 4፥50*** የሚል ነበረ። ጌታ ልጁ ወደ ታመመበት ሄዶ ሊፈውሰው የሚችለውን ያህል ባለበትም ቦታ ሆኖ ቃሉን ቢልክ ይፈወሳል። አሁን ግን ጌታ በተናገረው ቃል መሠረት ***ኢየሱስ የነገረውን ቃል አምኖ ሄደ 4፥50***፡ ይህ ሰው ኢየሱስ እንደሚፈውስ አመነ፤ ጠየቀ፤ ሳይሞት እንዲወርድለት ለመነው፤ ኋላም ***ኢየሱስ የነገረውን ቃል አምኖ ሄደ።*** የሚያስደንቅ እምነት።

***4፥53 ልጅህ በሕይወት አለ ባለው በዚያ ሰዓት እንደሆነ አወቀ።*** ከገሊላ ቃና ቅፍርናሆም ለመሄድ የተወሰነ ጊዜ ይጠይቃል። ይህ ሹም ወደ ኢየሱስ መጥቶ ከለመነው በኋላ፡- ***ሂድ ልጅህ በሕይወት አለ*** ያለው ሰዓት ***ሰባት ሰዓት 4፥52*** ነበረ። በመንገድም ባሮቹ አግኝተው ልጁ የተፈወሰበትን ሰዓት ሲጠይቃቸው ጌታ ባለበት ሰዓት መሆኑን አረጋገጡለት። ኢየሱስን ተአምር ለማድረግ (ምልክት ለመሥራት) ርቀት አይወስነውም። እርሱም የጊዜና የቦታ ጌታ ነውና። ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር የሚሠራበትን መንገድ ማንም ሊወስን አይችልም። እርሱ ቢወድና አብሮ ሄዶ ቢፈውሰው ወይም ባለበት ቦታ ሆኖ ቢናገር እርሱ የወደደውን ያደርጋል። የሚፈወስበትን መንገድ እንደወደደ ለእርሱ መተው ነው። መቼ ወይም ምን ሰዓት እንደሚያደርገውም እርሱ ይወስናል። እኛ ከምሕረቱ ተቀባዮች ብቻ ነን።

***4፥53 እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር አመነ።*** ይህ ምልክቱን ተከትሎ ወደሚፈለገው ግብ የደረሰን ሰው ያሳያል።

***4፥54 ሁለተኛ ምልክት ነው።*** የመጀመሪያው ምልክት በገሊላ ቃና ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠው ነበር (2፥1-11)። ይህ ደግሞ በገሊላ ቃና ያደረገው ሁለተኛው ምልክት ነው።

***ምልክት፡-*** ቃሉ እንደሚያሳየው አመልካች ነው። የተፈጸመው ነገር የሚያመለክተው ወይም የሚያሳየው አቅጣጫን ነው። ያን ምልክት አድራጊው መሲሑ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ነው። ምልክቶቹን ብቻ አይቶ በእነርሱም ተገርሞ እዚያ ከቆመ የምልክቱን ዓላማ በትክክል አለመረዳት ነው። የንጉሡ ቤት ሹም

የልጁ መፈወስ ይህ ምልክት ነው። ውጤቱም የልጁ መፈወስ ብቻ ሳይሆን ሰውዬው ከነቤተሰቡ ማመኑ ነው። ማናቸውም ጌታ የሚሰራቸው ምልክቶች፤ ድንቅና ተአምራት ትልቁ ዓላማቸው ከተፈጸመው ምልክት የተነሣ ሰዎች ለእግዚአብሔር ክብርን እንዲያመጡ፣ የማያምኑም እንዲያምኑት ለማድረግ ነው።

# ምዕራፍ አምስት

የመሲሑ መምጣት ስለሚታወቅበት መንገድ ብሉይ ኪዳን አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። በዚህ ምዕራፍ መሲሑ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣቱን የሚያረጋግጡ መንገዶችን ማለትም መፈወስ፤ ሕይወት መስጠት፤ መፍረድን እናያለን።

***5፥1 ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፥ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም መጣ።*** የአይሁድ ወንዶች ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ ሦስት በዓላትን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። ለፋሲካ በዓል፤ ለበዓለ ኀምሳና ለዳስ በዓል።

***5፥3 የውኃውን መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበረ።*** ቦታው በኢየሩሳሌም ***በበጎች በር አጠገብ ቤተ ሳይዳ መጠመቂያ 5፡1*** ነው። (የበግ በር በነህ 3፥1፣32፤ 12፥39 ተገልጿል)። እነዚህ በተለያየ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ወደዚህ ቦታ የሚሄዱት ጤናማ ይሆኑ ዘንድ ለመፈወስ ነው። የሚፈወሱበት ጊዜ የመጠመቂያው ውኃ ሲንቀሳቀስ ነው። የሚፈወሉበትም ሁኔታ ውኃው ሲንቀሳቀስ ወይም ሲናወጥ በመጀመሪያ የገባ ሰው ነው። የመፈወሳቸው መጠን ወይም ደረጃ ከማናቸውም ደዌ ነበር። በዚህም መጠመቂያ አጠገብ ይተኙ የነበሩት ሰዎች ከደዌያቸው እንዲፈወሱ ቶሎ ለመግባት እርስ በርስ በመሽቀዳደም የሚጠባበቁ ናቸው። የበሽታቸውም ዓይነት ረዳት ካልኖራቸው በስተቀር ወደ ውኃው ለመግባት በሚያስቸግር ደዌ የተያዙ ዓይነት ናቸው።

***5፥4 የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውኃውን ያናውጥ ነበርና፤*** ስለዚህ እያንዳንዱ በደዌ የተያዘ ሰው ፈውሱን ለመቀበል የጌታ መልአክ ወርዶ ውኃውን የሚያናወጥበትን ጊዜ ይጠባበቅ ነበረ። ፈዋሹ ጌታ ነው (የጌታ መልአክ)።

***5፥5-6 ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፥ ... ይህ ሰው ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ 5፡5*** የታመመ ነው። በዚህም ሁኔታ ***ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ አውቆ ልትድን ትወዳለህን? አለው 5፥6።*** ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው የሚያስፈልገውንና አንድ ሰው በምን ሁኔታ ለስንት ጊዜ እንደኖረ ያውቃል። በሰው ልብ ያለውን ያውቃል። ***ልትድን ትወዳለህን? ከሚለው*** ከኢየሱስ ጥያቄ የምናስተውለው ሰው ለመፈወስ



ፈቃደኛ መሆን እንዳለበት ነው። መዳን መፈለጉ ግልጽ ቢመስልም በሽተኛው ግን ፈቃደኝነቱን እንዲገልጽ ይጠበቅበታል። ይህ ሰው ለሰላሳ ስምንት ዓመት ተኝቶ የኖረ ስለሆነ በሽታውና እንደዚያ መተኛቱ ለእርሱ የሕይወቱ ዓይነት ነው። አብዛኛውን የእድሜ ዘመኑን በደዌ ተመትቶ ተኝቶ ስለ ኖረ ከዚህስ በኋላ ምን ያህል ዕድሜ ሲቀረኝ ነው? ብሎ ሲያስብ ይችላል። ይህ ሰው ከመኖር ይልቅ ለሞት የቀረበ ነው ማለት ይቻላል። በጌታ ግን ተስፋ አይቆረጥም። በየትኛውም የእድሜ ዘመን ደርሶ ፍጹም ጤናማ ሲያደርግና ተስፋን ሲያለመልም ይቻለዋል።

***5፥7 ሰው የለኝም ... ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል።*** ሽባው ሰው የሚፈልገውና የሚጠብቀው የጌታ መልአክ ውኃውን ካንቀሳቀሰ በኋላ በመጀመሪያ ወደ መጠመቂያው የሚያስገባውን ረዳት ነው። እያነጋገረው ያለው ደግሞ ***የጌታ መልአክ*** እንዲወርድ የሚያደርገውን ጌታ ነው። ውኃ ልትቀዳ እንደሄደችው ሳምራዊት ሴትና ምግብ ሲገዙ እንደሄዱት ደቀ መዛሙርት ይህም ሰው የጌታን ጥያቄ የተረዳው «ሰዋዊ በሆነ» (በተለመደው) መንገድ ነው። ሴትዮዋ መቅጃ የለህም አለችው። ደቀ መዛሙርቱ የሚበላው ሌላ ሰው አምጥቶለት ይሆናል ብለው አሰቡ። ይህም ***ሰው የለኝም*** አለ። ጌታ ግን ውኃ ለሚፈልግ የሕይወት ውኃን ለመስጠት፣ ይህን ሽባ ደግሞ ለመፈወስ ሥልጣን አለው።

***5፥8 ተነሣና አልጋህን ተሸከመህ ሂድ አለው።*** ሽባው ሰው ከጠበቀው ዓይነት የተለየ እርዳታ ጌታ ሰጠው። ***አልጋህን ተሸከመህ ሂድ*** ሲለው ከዚህ በኋላ በኖረበት ሁኔታ እንዳይኖር ታሪኩንና አድራሻውን ቀየረለት። የዚህን ሰው ታሪክና እንዴት እንደተፈወሰ ስንመለከት ስለ ጌታ አሠራር ብዙ እንማራለን።

- ኢየሱስ ***ወደ በጎች በር*** አጠገብ ወደዚያ ቦታ ሄደ። ኢየሩሳሌም ብዙ በሮች አሉአትና ከሌሎቹ አንዱን በወሰደ ነበር። ነገር ግን የታመሙት ደዌ ያለባቸው ወደሚቀመጡበት (ወደሚተኙበት) ሄደ።
- ለረጅም ዘመን ተኝቶ የኖረን ይህን በሽተኛ ቀርቦ አነጋገረው። ለስውዬው ያለውን መውደድና ማሰብ እንዲሁም ሃዘኔታ ይገልጣል። ይህ ተጠባብቆ ወደ ውኃ የሚያስገባው ረዳት የሌለውን ሰው አይቶ ጌታ ሲያነጋግረው መቅረቡ ርኅራኄውን ያሳያል።
- ይህን ሰው ለመርዳት ጌታ እንደሚፈልግ ይነግረዋል፣ ሰውዬውንም ፈወሰው።

ክርስቲያኖች ስለ አገልግሎት የጌታን ፈለግ መከተል ይገባናል:: የተቸገሩት ወዳሉበት በመሄድ ለመቅረብና ለማነጋገር መፈለግ፤ የጌታን መልካምነት መግለጽ፣ የጌታን ፈውስ እንዲቀበሉ መርዳት::

***5፥10 ያም ቀን ሰንበት ነበረ::*** ለዚህ ሰው ሰላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ እያንዳንዱ ቀን «ሰንበት» ነበረ:: መልአኩ ውኃውን የሚያናውጠው በሰንበት ቀን ቢሆንና በዚያ ቀን በመጀመሪያ የገባው ሰው ቢፈወስ የአይሁድ አለቆች ምንም ባላሉት ነበረ:: መልአኩ ውኃውን እንዲያናውጥ የሚያዝዘው ጌታ ግን በመካከላቸው ሆኖ ሲፈውስ ግን ስለ ሰንበት ምክንያት ሊከሱት ፈለጉ::

***5፥10 ሰንበት ነው አልጋህንም ልትሸከም አልተፈቀደልህም አሉት::*** በሰንበት ቀን ሰው አልጋውን ተሸክሞ እንዳይሄድ የሚከለክል ሕግ በብሉይ ኪዳን አይገኝም:: ይህ ሕግ ግን አይሁድ ራሳቸው ባወጧቸው ዝርዝር ሕጎች ውስጥ የጨመሩት ሕግ ነው:: ከዚህም የተነሣ ራሳቸው ያወጡትን ሕግ ስላልጠበቀ ሊከስሱት ተነሱ::[24] ለሰው ጤንነትን መመለስን ወይም ሙሉ ሰው ማድረግን ሥራ እንደ መሥራት አድርገው ይቆጥሩት ነበር::

ወንጌላትን ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ በሰንበት ቀን ሰባት ጊዜ ሰዎችን ፈውሷል:: ይህን ሲያደርግ በብሉይ ኪዳን የተሰጠውን ሕግ መተላለፉ አለመሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል:: በዚህ በሰንበት ቀን በመፈወስ ጌታ ለአይሁድ የሚያስተምራቸው ከሕጉ ባሻገር ያለውን የሰንበትን ምንነት ነው::

ጌታም አንድ ጊዜ ለአይሁድ ሲያስረዳቸው እንዲህ አለ፤ «ጌታም መለሰ:- እናንተ ግብዞች ከእናንተ እያንዳንዱ በሰንበት በሬውን ወይስ አህያውን ከግርግም ፈትቶ ውኃ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን? ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአስራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እስራት ልትፈታ አይገባምን? አለው:: ይህን ሲናገር ሳለ የተቃወሙት ሁሉ አፈሩ (ሉቃ 13፥15-16):: ሰው በሰንበት ጤንነት ሲመለስለት አይገባም ብለው መከራከራቸው

[24] Caring a mat on the Sabbath did not break any Old Testament law; instead, it broke the Pharisees' legalistic application of God's command. The regulation against carrying something on the Sabbath was the last thirty-nine rules in the <tradition of the elders> that speculated the kinds of work prohibited on the Sabbath. This was just one of hundreds of rules the Jewish leader had added to the Old Testament law. Ibid. p.103



እውነተኛው ብርሃን ሲበራላቸው ድርጊቱ ወይም አስተሳሰባቸው የሚያሳፍራቸው ነው:: ሰንበትን መጠበቅ ማለት ዋና ዓላማው እግዚአብሔርን ማክበር ነው:: ይህ ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን በማድረግም ይገለጻል (ማር 1፥21-28፣29-31፤ ማር 3፥1-6፤ ሉቃ 13፥10-17፣ 14፥1-6፤ ዮሐ 5፥1-18፤ 9፥1-16)::

***5፥14 ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኃጢአት አትሥራ አለው::*** በኃጢአት ምክንያት የዘላለም ሕይወትን ማጣት ለሰላሳ ስምንት ዓመት በአልጋ ተኝቶ ከመኖር የበለጠ ነው:: ለዚህ ሰው ለዘላለም በገሃነም እሳት ከሚደርሰበት ስቃይ አንጻር ለሰላሳ ስምንት ዓመት በደዌ መተኛት ምንም አይደለም፤ እጅግ ትንሽ ነው:: ስለሆነም በመንፈሳዊው ሕይወቱ እንዲፈወስ ንስሐ በመግባት ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት:: ስለዚህ ጌታ የሚነግረው በሥጋው ፈውስ ማግኘቱ በቂ አለመሆኑን ነው - መንፈሳዊ ፈውስን ማግኘት ይገባዋል:: በሥጋ ፈውስ ላይ ብቻ አትኩሮ ሌላውን መርሳት የቅርቡን ማየት ብቻ ይሆናል::

ይህ ሰው ይህን ዓይነት ለረጅም ዓመት አልጋ ላይ እንዲተኛ ያደረገው ኃጢአቱ ሲሆን እንደሚችል ፍንጭ ይሰጣል:: ይህ ደግሞ በ9፥3 ላይ ዕውር ሆኖ ስለተወለደው ሰው «እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት ስለ ሠሩ አይደለም» ከሚለው ቃል ጋር አይቃረንም:: እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአተኞች አይደሉም፤ ወይም ኃጢአት ሠርተው አያውቁም አላለም - በልጁ የደረሰበት የመጣበት ዕውርነት በኃጢአት ምክንያት አይደለም እንጂ:: ስለዚህ የኃጢአት አንዱ ውጤት መከራ ወይም ሕመም እንደሆነ ማስተዋል እንችላለን:: እንዲሁም ሁሉም መከራ ወይም ሕመም በኃጢአት ምክንያት የሚመጣ እንዳይደለም አብረን እናጤናለን::

***5፥16 አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር::*** ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ጊዜ ጀምሮ በስደት የኖረ ሰው ነው:: ገና በሕፃንነቱ ሄሮድስ ያሳደደው ነበር:: ከዚያም አገልግሎቱን ሲጀምር የሃይማኖት ሰዎች፣ የካህናት አለቆች፣ ጻፎችና ፈሪሳውያን:: ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፤ የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም (1:11):: ነቢይ በገዛ አገሩ እንደማይከበር የተናገረው ጌታ ኢየሱስ ነው (ሉቃ 4:24):: ስለዚህ ጌታ እየተሰደደ የኖረ ሰው ነው:: አሁንም በዚህ ቦታ አይሁድ ማሳደዳቸውን ጀመሩ፤ ይህም በሰንበት ቀን ሰው ፈውሷል በሚል ነው::

***5፥17 አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ::*** ጌታ ይህን የተናገረው ሰንበትን ሽረሃል ሲሉት ነው:: አይሁድ ጌታ ኢየሱስን

የከሰሱት በሰንበት ቀን ሥራን ሠርተሃል ብለው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የመለሰላቸው በሰንበት ያረፈው እግዚአብሔር ***እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ*** በማለት ነው። በዘፍ 2፥2-3 «እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በስድስተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛ ውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና። እንዲሁም በዘጸ 20፥8-11 «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» ይላል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል፣ ቀድሶታልም። ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ***አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ*** አለ። እዚህ ላይ እናስተውል:- አባቴ በሰንበት አላረፈም አላለም። ይህን እንዴት እንረዳዋለን?

***እስከዛሬ ይሠራል*** ማለት መሥራት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ መሥራት አላቋረጠም እንደ ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ በዘፍ 2፥2-3 ዐረፈ ይላልና፤ ያረፈው ከምንድን ነው? የሚሠራውስ ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ ይገባል። እግዚአብሔር ያረፈው ከመፍጠር ሥራ ነው። የፈጠረውን የመጠበቅና የማኖር ወይም የመደገፍን ሥራ ግን አላቆመም። ሰንበት መጠበቅን በሚመለከት በማር 2፥23-28 ባለው ክፍል ውስጥ የጌታ ደቀ መዛሙርት እሸት እየቀጠፉ ሲበሉ ፈሪሳውያን ያልተፈቀደ አድርገዋል ብለው ነበር። ጌታ ሲመልስላቸው ግን ከካህናት በቀር መብላት ያልተፈቀደውን የመሥዋዕት እንጀራ ዳዊትና አብረውት የነበሩት እንደበሉ ከነገራቸው በኋላ «ሰንበት ስለሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም» (2:27) አላቸው። እንዲሁም «የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው» (2:27-28) አላቸው።

እዚያ ላይ ጌታ የሚነግራቸው ሰንበትን የመጠበቅ ሕግ ተሽሯል በማለት ሳይሆን ሰንበትን ስለ መጠበቅ ሊገነዘቡት የሚገባቸውን ነገር እንዳለ ነው። ሰንበት ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው፤ የክርስቲያን ሥራም ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው። በሰንበት የግል ሥራዎቻችንን አቁመን እረፍት ማድረግና ቀኑን ለእግዚአብሔር መቀደስ ይገባል። በሰንበት መልካምን ማድረግ ማለት በሬን ፈትቶ ወይም አህያውን ፈትቶ ውኃ እንደማጠጣት እንዲሁም የታመመን ሰው ከእስራቱ እንዲፈታ ማድረግ አልተከለከለም።

በተጨማሪም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ንግግሩ እግዚአብሔርን አባቴ ብሎ ስለጠራውና እርሱ እንደሚሠራ እኔም እሠራለሁ በማለቱ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን በዚህም ያመለክታል። ይህ ምን ማለቱ እንደሆነም ለሚያዎቹ አይሁድ ገብቷቸዋል። በዚሁ ንግግሩ ራሱን



ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ማደረጉ እንደሆነ የገባቸው አይሁድ ስለዚህ ይከሱታል። እንዲህ ብለው:-

***5፥18 ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከሉ:- እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።*** ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከሉ እግዚአብሔርን መስደቡ መሰላቸው። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ስም የሰደበ እንዲወገር በሚለው መሠረት (ዘሌ 24፥15-16) አይሁድ ሊገድሉት ፈለጉ። ሆኖም ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አስረግጦ በመናገርና ምልክትን በማሳየት ቀጠለ።

***5:19 አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም። ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና።*** በዚህ ላይ ሁለት ጉልተው የሚወጡ ሃሳቦች አሉ:-

1. ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም
2. አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ያደርጋል

አብ የሚያደርግውን ሁሉ ወልድ ካደረገ፣ ወልድ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። በችሎታ መበላለጥ የሌለበትን እኩልነት ያሳያል። ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አለመቻሉ በእኩልነት ያለ አንድነትን ያመለክታል። ይህም አብና ወልድ ሁለቱም አንድ ባሕርይ (አንድ ሃሳብ) እንዳላቸው ያሳየናል።

***5፥20 አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል***:- ይህ በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነትና እኩልነት ይገልጻል። ***አብ ወልድን ይወዳልና ሲል*** አብና ወልድ የእርስ በእርስ ኅብረታቸው በፍጹም ፍቅር ላይ የተመሠረተ፤ አንድነታቸው በፍቅር የተያያዘ እንደሆነ ያሳየናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱን ፈቃድ በሙሉ የፈጸመው ከእርሱ ጋር በነበረው ኅብረትና የእርስ በርስ ፍቅር የተነሣ ነው። ***የሚያደርገውን ሁሉ*** ሲል ደግሞ ***ሁሉ*** ሙሉነትን ወይም ፍጹምነትን ያመለክታል። ይህም በሙሉ ለወልድ ያሳየዋል ማለት ነው። ይህም እኩል ማወቅን ያመለክታል። ስዚህም ቀጥሎ ባለው ክፍል የመለኮታዊ ሥራዎችን የማድረግን ምሳሌዎችን ይሰጣል። አንዱ ሕይወት መስጠት ነው።

***5፥21 አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል።*** ሕይወትን መስጠት ሙታንንም ማስነሣት መለኮታዊ ተግባር ነው።

ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። አብ ያደርገዋል፤ ኢየሱስ ክርስቶስም ያደርገዋል።

በአብና ወልድ መካከል ያለው አንድነት በመጠኑም ቢሆን በኢየሱስ ክርስቶስና በአማኞች መካከል ሊኖር ስለሚገባው መቀራረብ ፍንጭ ይሰጣል። እርሱ እንዲሆን የሚፈልገውን እኛ እናደርግ ዘንድ እርሱን ልንወደው፣ ልንታዘዘው፣ ልንሰማው ያስፈልገናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ልንሠራ የሚገባውን እንዲያሳየን እርሱን መጠየቅ ይገባናል። ስለዚህ በአንድ ሁኔታ ውስጥ ስንሆን በዚህ ሁኔታ ኢየሱስ ምን ያደርግ ነበር? በዚህ ሁኔታ እኔስ ምን እንዳደርግ ይወዳል? ብሎ መጠየቅ ትክክለኛውን ምርጫ ለማድረግ ያግዛል። እርሱ የሚፈልገውንና የሚወደውን እንድናደርግም ይረዳናል። ይህ ደግሞ ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረታችንን ያሳድጋል።

***5፥20 ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል።*** ከዚህ የሚበልጠው ሥራ ቀጥሎ የተገለጠው ሙታንን ማስነሣት፤ ሕይወትን መስጠት እንዲሁም ሌላ ሥራ ሁሉ ይሆናል።

- እግዚአብሔር ብቻ ይፈርዳል (መዝ 7፥6-17፤ 9፥7-8፤ ኢዩ 3፥12)። መሲሑ በመጣ ጊዜ ለመፍረድ ሥልጣን ይኖረዋል (ዳን 7፥13-14፤ ኤር 23፥5-6)። ኢየሱስ ለመፍረድ ሥልጣን አለው (ዮሐ 5፥27)።

- እግዚአብሔር ብቻ ሕይወትን ይሰጣል (ዘፍ 1፥20-27፤ ዘዳ 32፥39፤ 1ሳሙ 2፥6፤ 2ነገ 5፥7)። መሲሑ ሕይወትን የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል (ዳን 7፥13-14)። ኢየሱስም ሕይወት እንደሚሰጥ አሳይቷል (ዮሐ 5፥21፤ 28፥39)።

- የሚፈውስ እግዚአብሔር ብቻ ነው (ኢሳ 35፥3-7)። መሲሑ ሲመጣ ይፈውሳል (ኢሳ 53፥4-5፤ 61፥1-3)። ኢየሱስ ደግሞ ፈዋሽነቱን አሳይቷል (ዮሐ 5፡8፤ 20፥26)።

***5:22-23 ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።*** የወደደንና ነፍሱን ስለ እኛ አሳልፎ የሰጠ ጌታ፤ እርሱ ደግሞ ፈራጃችን ነው። ፍርድ መስኮታዊ ተግባር ነው። ይህን የመፍረድ ሥልጣን ለልጁ ሰጥቶአል (ሐዋ 17:31)። በዚህም ወልድ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ክብር እንዳለው ያሳያል። ለአብ የሚገባው



ክብር ሁሉ ለወልድም ነው። አብን የማያከብር ወልድን አላከበረም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አላከበረም። አብና ወልድ በክብር እኩል ናቸው። ስለሆነም ጉልበት ሁሉ ይንበረከክለታል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ምላስ ሁሉ ይመሰክራል። ስለዚህም ጌታ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገው በቀኙም አስቀመጠው (ፊል 2፥9-11)።

እንግዲህ እዚህም ላይ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በማወቅ (በመቀበል) የማያከብሩት ሁሉ እግዚአብሔር አብንም አላከበሩትም ማለት ነው። ምክንያቱም የላከው አብ ነውና። ኢየሱስ ደግሞ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነውና። ስለዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር እምናለሁ ብለው ኢየሱስ ክርስቶስን ግን ከአስተማሪዎች አንዱ ነው ወይም ከነቢያት አንዱ ነው የሚሉ እነዚህ እግዚአብሔርን የናቁ ሰዎች ናቸው። የኢየሱስ ክርስቶስም ጠላቶች ናቸው።

***5:24 ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።*** ይህ ፍርድ ወደፊት የሚሆን ስለሆነ ***አይመጣም*** ይላል። ከሞት ወደ ሕይወት መሻገር ደግሞ በማመን ጊዜ ጀምሮ የሚፈጸም ስለሆነ የዘላለም ሕይወት ***አለው*** በሚል በአሁን ጊዜ ይገልጻል። በአሁኑ ጊዜ በኢየሱስ ያመነ፣ የኢየሱስን ቃል የሚሰማና የላከውን የሚያምን አሁን ከአመነበት ጊዜ ጀምሮ ***የዘላለም ሕይወት አለው።*** እንዲሁም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ወደፊት በሚያምኑትና በማያምኑት መካከል በሚሆነው ፍርድ ***ወደ ፍርድ አይመጣም።*** አሁን ስላመነ የዘላለም ሕይወትን አግኝቷልና።

መስማት ማመንን ያስከትላል (ሮሜ 10፥17)። ማመን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት ደግሞ በላከው በእግዚአብሔር አብ ማመንም ነው። ይህም በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነት ያሳያል። በ3፥18 ላይ እንዳየነው ይህች ምድር የተፈረደባት ነች። ከዚህ ፍርድ የሚያመልጡት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚድኑት ናቸው። የዚህች ዓለም ፍርድ በገሃድ የሚታየው ወደፊት በሚኖረው ፍርድ ላይ ነው። ከፍርድ ማምለጥ የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው። «እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን። ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየትን ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን» (ቆላ 1፥13-14) እንደሚል በኢየሱስ ያመኑ ሰዎች ከጨለማ ሥልጣን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት የፈለሱ ያመለጡ፣ የዳኑ ናቸው። የዚያ መንግሥት ዜጎች የሚሆኑ የኃጢአትን ስርየት ያገኙ ብቻ ናቸው።

***5፥25 ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ።*** ይህ የወደፊቱ ጊዜና የአሁኑ ጊዜ በአንድ ላይ ሆኖ እንመለከታለን። ***ይመጣል*** የወደፊት ነው። ***ሆኗል*** የአሁን ጊዜ ነው። የሚመጣው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሲያሳይ፤ አሁን የሆነው ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጸመውን ይገልጻል። በልጁ የሚያምን ከሞት ወደ ሕይወት ስለ መሻገሩ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ወደፊት ***ይመጣል*** የተባለው (ተብሎ የነበረው) እዚህ ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት አሁን ***ሆኗል*** (መጥቶላቸዋል)። ውኃ ልትቀዳ ለሄደችው ሴት መጥቶላታል። በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ መጥቶላቸዋል።

በእካል የሞቱት ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበትና ከመቃብራቸው የሚነሱበት ጊዜ ይመጣል። ይህ በአንድ መልኩ ለሁሉም ሰው የሚሆነውን ከሙታን መነሣት ያመለክታል። የሞቱት ደግሞ በትንሣኤ ቀን ይነሳሉ 11፡25-26። ይህ ለማንኛውም ለሞተ ሰው ሁሉ በትንሣኤ ቀን የሚሆን ነው። በሁለተኛ መልኩ ግን በትንሣኤ ቀን ከሚነሡት በምድር እያሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ሕይወት ያገኙት በሕይወት ይኖራሉ። ሌሎች ግን የእግዚአብሔር ልጅ ይፈርድባቸዋል። እነዚህ አሁንም በሕይወት አሉ። እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፡- ***በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና 5፥28-29።***

***5:26 አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና።*** በራሱ ሕይወት ያለው[25] እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ ራሱ በራሱ የሚኖር ለመኖር ሌላ የማያስፈልገው ነው። ይህም አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው ወልድ በራሱ ሕይወት አለው። ሰዎች እና ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በራሳቸው ሕይወት የላቸውም። ሰው ሕይወትን የተቀበለው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሲፈጥረው እፍ ስላለበት ነው። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ» (ዘፍ 2፡7)። ስለሆነም ሰው በራሱ ሕይወት የለውም፤ ሕይወት ከእግዚአብሔር የተሰጠው ነው። ኢየሱስ ግን ራሱ ሕይወት ነው (14:6)። እርሱ ሕይወትን (የዘላለም ሕይወትን) ይሰጣል። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም (1ዮሐ 5፡12)።

[25] Self existing



***5፥27 የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው።*** ኢየሱስ እንዲፈርድ ሥልጣን የተሰጠው እርሱ የሰው ልጅ ስለሆነ ነው። ***የሰው ልጅ*** የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው መሆን (ሥጋ መልበስ) የሚያመለክት ነው። ሁሉም ሰው ለኢየሱስ ክርስቶስ ተጠያቂ ነው (ፊል 2፥5-11)።

ቀደም ሲል ***ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና 3፥17*** የሚለውን ተመልክተናል። ይህ በ5፥27 ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን እንደ ተሰጠው የሚናገር ሲሆን በ3:17 ደግሞ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም እንዳልላከው ይገልጻል። እንዲሁም በ8፥15-16 እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም የላከኝ አብ ከኔ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና፤ እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው ይላል። እነዚህን ጥቅሶች በአንድ ላይ ወስደን ስናያቸው የሚከተለውን ማገናዘብ እንችላለን። ኢየሱስ የመጣው ለመፍረድ አይደለም። የእርሱ መምጣት ግን ሰዎችን ለንስሐ እንዲጠራ በመሆኑ ጥሪውን ለመቀበል በማይፈልጉት ላይ ፍርድን ያስከትላል።

***5፥30 እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ፤ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።*** አብና ወልድ በእውቀትና በሥልጣን እኩል መሆናቸውን ተመልክተናል። አሁን ደግሞ በአብና በወልድ መካከል ያለውን የፈቃድ አንድነት እናያለን። የአብ ፈቃድ የሆነው የወልድም ፈቃድ ነው። ይህ በሥላሴ መካከል ስላለው አንድነት እንዲሁም የተግባር ልዩነት[26] ተጨማሪ መረዳትን ይሰጠናል። እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ በሥላሴ አካላት መካከል እያንዳንዳቸው የሚሠሩት ሥራ እንዳላቸው ቢታወቅም ይህ የሥራ ክፍፍል እንጂ ከችሎታ አንጻር የተደረገ የሥራ ድርሻ አይደለም። በመካከላቸው ባለው ፍቅር የሚኖረውን አንድነትና የሥራ ድርሻ ያመለክታል።

***5፥31-32 እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም፤ ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው፥ እርሱም ስለ እኔ የሚመሰክረው ምስክር እውነት እንደሆነ አውቃለሁ።*** ይህ አገላለጽ በዘዳግ 15፥6 እና 19፥15 የአንድን ነገር እውነትነት ለማረጋገጥ ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች እንደሚያስፈልጉ የተጻፈውን ያሳስባል። በተገለጸው መሠረት እንደ ሰው ለአይሁድ መናገሩ ነው። ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው ሲልም አብን መጥቀሱ ነው (5፥36)።

[26] Destinction

በዚህ ምዕራፍ እስከ አሁን ባሰው ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር እኩል እንደሆነ ገለጸ (5፥18)። ሕይወትን ይሰጣል (5፥24)። የሕይወት ምንጭ ነው ( 5፥26)። በኃጢአትም ላይ ይፈርዳል (5፥27)። እነዚህ ማስረጃዎች ኢየሱስ ክርስቶስ መሰከት መሆኑን ይገልጻሉ። ከዚህም በተጨማሪ አርሱ መሰከት ለመሆኑ ማስረጃዎች (ምስክሮች) ይጠራል። እነርሱም:-

1. *መጥምቁ ዮሐንስ* (5፥33-35)፤
2. የራሱ የኢየሱስ *ሥራ* (5፥36)፤
3. አብ፤ የአብ ምስክርነት (5፥37)
4. *መጻሕፍት* (5፥39-40)
5. *ሙሴ* (5፥45-47) ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ምስክሮች በአንድ ላይ የሚያስረዱት ኢየሱስ ክርስቶስ ሊታመንበት የተገባ የአግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ነው።

***5፥33-34 እናንተ ወደ ዮሐንስ ልካችኋል እርሱ ለእውነት መስክሮአል። እኔ ግን ከሰው ምስክር አልቀበልም፥ እናንተ እንድትድኑ ይህን እላለሁ እንጂ።*** ዮሐንስ መጥምቁ ከሰው የመጀመሪያው ምስክር ነው (1:6-8)። እይሁድ የዮሐንስን ማንነት ለማወቅ መልእክተኞችን ልከው ነበረ (1:19-)። ዮሐንስ የመሰሰላቸው:- «አኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ ከአኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው» (1፥27) በማሰት ነበር። እንዲሁም በሌላ ቦታ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። አርሱ ሊልቅ አኔ ግን ላነስ ያስፈልጋል (3፥29-30) በማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስክሮአል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከስው የሆነ ምስክር ምንም አያስፈልገውም። መጥምቁ ዮሐንስን ምስክር አድርጐ የጠቀሰው ለአይሁድ ጥቅም ለመዳናቸው እንዲሆን ነበረ። ጌታም ስለ መጥምቁ ዮሐንስ:- ***እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ 5:35*** ይላል። መንደዱ የአገልግሎቱን ዓይነት ያሳያል:- በምድረ በዳ መኖሩን የሚጮህ መሆኑን እንዲሁም የተቀበለውን መከራ። መብራት መሆኑ ደግሞ አርሱ ብርሃን አለመሆኑን እየገለጸ፣ ሰዎች ንስሐ በመግባት ከጨለማው እንዲወጡ ብርሃን የሆነውን ኢየሱስን እንዲያምኑ ምስክር የሆነ ሰው አንደነበረ ያስረዳል። ዮሐንስ ብርሃን አልነበረም (1፥8)። አርስ ብርሃንን የሚያንፀባርቅ ነበር።

***5፥35 እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ።*** አይሁድ በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ደስተኞች ነበሩ። ይሁን እንጂ መልእክቱ በትክክል አልገባቸውም። ቢገባቸው ኖሮ የእርሱ ማብራት



ወደ ዋናው ብርሃን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያመለክት ስለሆነ የእግዚአብሔር በግ የሆነው ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከ እንደሆነ በተገነዘቡና ባመኑበት ነበረ። እንዲሁም ጌታ ስሰበሰጠ ምስክር ሲነግራቸው ***እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክር የሚበልጥ ምስክር አለኝ 5:35*** ይላቸዋል። እርሱም:-

***5፥36 አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ፥ ይህ የማደርገው ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና።*** በእርሱ የሚያምኑትን ከጨለማ ግዛት ወደ ልጁ መንግሥት ያፈልሳል። የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሠራው ሥራ መሰከታዊ ነው። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ የተላከ ለመሆኑ ምስክር ነው።

***5፥37 የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል።*** እግዚአብሔር አብ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ መስክሮአል። ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀበት ጊዜ «በአርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» (ማቴ 3፥17) በማለት መስከረ። እንዲሁም በተራራው ልብሱ እጅግ ነጭ ሆኖ በተለወጠበት ጊዜ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምጽ መጣ» (ማቴ 17፥5)። በዮሐንስ 12፥28 ላይ «አባት ሆይ፥ ስምህን አክብረው» ብሎ ሲጸልይ መልሱ «አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ»። ስለዚህ አብ ስለ ኢየሱስ በተደጋጋሚ መስክሮአል። ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን በላከው ማመን ነው። ኢየሱስን አስመቀበል የላከውን አብን አለመቀበል ነው።

***5፥37 ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፥ መልኩንም አላያችሁም!*** ከጌታ ጋር ይነጋገሩ የነበሩት አይሁድ የእግዚአብሔርን ድምፅ አልሰሙም ፊቱን (ወይም መልኩን) አላዩም። በብሉይ ኪዳን ሙሴ የአግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶአል (ዘጸ 33፥11)። እንዲሁም እስራኤላውያን (ዘዳግ 12፥4)። ሙሴ የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት ፈልጐ ነበረ።እርሱ ሲያልፍ ጀርባውን እንጂ ፊቱን ያይ ዘንድ አልፈተቀደለትም (ዘጸ 33፥15-23። ሙሴና አባቶቻቸው ያዩትን አይሁድ አላዩም። ይልቁን አይሁድ ያዩት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው (ዕብ 1፥1-3)። ለነገሩማ በእነርሱ ጊዜ የተገለጠው የበለጠ ነው። ይሁን እንጂ በእርሱ ለማመን አልወደዱም።

***5፥38 እርሱም የላከውን እናንተም አታምኑምና በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም።*** አብ የላከው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አርሱን ግን አልተቀበሉትም። የእግዚአብሔር ቃል በአፃቸው ቢኖርም በልባቸው ስለሌለ/ ስለማይኖር (8፥31፣ 15፥7) ኢየሱስ ክርስቶስን

አልተቀበሉትም:: በእነርሱ ዘንድ ያሰውን የቃሉን ትርጉም አልተረዱም::

***5፥39 እናንተ በመጻሕፍት የዘላሰም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው::*** አይሁድና ፈሪሳውያን ሕግን በመጠበቅ ቃሉን አክባሪዎች መሆናቸውን ሰማሳየት ብዙ ጥረት ያደረጋሉ:: እስከ ጥቃቅኗ ነጥብ ወይም ነቁጣ ድረስ ይመረምራሉ:: የሕግን ዋና መልእክት ግን አልተረዱም:: ሕግን በመጠበቅ ሕይወት የሚገኝ ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ባላስፈሰገው ነበር:: ሐዋርያው ጳውሎስ:- «ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? አይደለም:: ሕያው ሊያደርግ የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ ከሕግ በሆነ ነበረ:: ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን ከሆነው የተስፋ ቃል ሰሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል» (ገላ 3፥21-22) ይላል::

አይሁድ መጻሕፍትን በመመርመር የዘላሰም ሕይወት እንደሚኖራቸው ያስባሉ:: ነገር ግን በመጻሕፍት በራሳቸው የዘላለም ሕይወት የሰም:: መጻሕፍት የዘላለም ሕይወት የሚገኝበትን መንገድ ያመለክታሉ፣ ይመሰክራሉም:: ***እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው 5፥39*** እንዳለ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩ ናቸው:: የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው:: መጻሕፍት እንደ ዮሐንስ መጥምቁና እንደ ሌሎችም ምስክሮች ሁሉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሰክሩ ናቸው:: ሕግ በራሱ ሕይወት አይሰጥም::

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ይህንን እውነት ማስተዋል ያስፈልጋል:: ሁልጊዜም ቢሆን የመጻሕፍት የመጨረሻ ግብ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመልከት ነው:: ከዚህ ያነሰ ነገር ሁሉ ወደ ዓላማው ያልደረሰ ይሆናል:: መጻሕፍትን ሰእውቀት ወይም ሰታሪክ መረጃነት ብቻ ማንበብ ዓላማውን የሳተ ትጋት ነው:: በእንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስን ባነበብንና ባጠናን መጠን የበለጠ ኢየሱስን እያወቅነው ከሄድን የመጻሕፍት ዓላማ ግቡን ይመታል::

***5፥40 ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም::*** መጻሕፍትን በማንበብና ሕግ ሰመጠበቅ በመሞከር ብቻ የዘላለም ሕይወት እንደሚገኝ ስለሚመስላቸው መጻሕፍት በሚያመለክቱት አቅጣጫ ሄደው፣ አቅጣጫው ወደሚደርስበት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አይቀርቡም:: ወደ ኢየሱስ መምጣት አሰመውደድ የዘላለም ሕይወት የሚሰጠውን (1፥4፣ 5፥25፣ 14፥6) አሰመፈለግ



ነው:: መጻሕፍትን መውደድና ማጥናት ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ማወቅ ካላደረሰ ጥቅም የሰውም፤ መስመሩን ስቷል ማሰት ነው::

***5:41-42 ከሰው ክብርን አልቀበልም፤*** በ5፥34 ላይ ***ከሰው ምስክር አልቀበልም*** እንዳለ እንዲሁም ከሰው ክብር አልቀበልም ይላል:: እርሱ ራሱ ክብሩ ሙሉ ነው::

***5፥41-42 ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፍቅር በራሳችሁ እንደ ሌላችሁ አውቃችኋለሁ::*** ይህ ኢየሱስ የሚያውቀው ነገር እነርሱ እግዚአብሔርን የሚወዱ እንዳልሆኑ ነው:: የእነርሱ ፍቅር «ሰሃይማኖታቸው»፤ «ሰሕጋቸው»፤ «ሰመጽሐፋቸው» ነው:: መጽሐፋቸውን ያነባሉ፤ ሕጋቸውን ይጠብቃሉ:: ሕጋቸውንና መጽሐፋቸው መውደዳቸው ግን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አልመራቸውም:: እግዚአብሔርን እንዲወዱ የላከውንም እንዲወዱ አላደረጋቸውም::

***5፥43 እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝምም፤*** እግዚአብሔርን እንደማይወዱ ምልክቱ እግዚአብሔር የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን አሰመቀበላቸው ነው:: ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በእብ ስም ነው:: ጌታ ***ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ 5፥43*** [27] እንዳሰው ምርጫቸው በተቃራኒው ነው::

***5፥44 እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር የምትቀባበሉ ከአንዱም ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ፥ እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ?*** ጌታ እዚህ ላይ የሚነግራቸው በእርሱ ሰማመን እንቅፋት የሆነባቸው ምክንያቱ ምን እንደሆነ ነው:: በመካከላቸው አንድ ሰው የተሰየ አስተሳሰብ እስከማይኖረው ድረስ እርስ በርስ ተያይዘውና ተጠባብቀው፣ ተቆላልፈው የሚኖሩ ሰዎች መሆናቸውን ያሳያል:: ያንዱ መኖር በሌላው ተቀባይነት ወይም ክብር እስካገኘ ድረስ፤ በቡድን ወይም ማኅበራዊ ተቀባይነት ላይ የተመሠረተ ኑሮ ነበር:: ስለዚህ አንዱ የሚያምነው ሌሎቹ ያንን አስተሳሰቡን እስካከበሩለት ድረስ ነበር ማሰት ነው:: አንድ ሰው ትክክል የሚሆነው በተከታዮቹ ትክክል መስሎ እስከተቆጠረ ድረስ ስለሆነ ግምገማውም

[27] Very likely Jesus was referring to other persons who claimed to be the Messiah. Because they fit the mistaken image of what the Messiah was supposed to accomplish (political liberation), people eagerly received them. Many men made such a claim. For example in A.D. 132 Simeon ben Kosebah claimed to be the Messiah, and his claim was upheld by Akibah, the most eminent rabbi the day. Ibid. p.118.

ሆን ውጤቱ «ስዋዊ» ይሆናል። ይህ አይነት የቡድን መከባበርና ተቀባይነት መፈለግ ሰው የእግዚአብሔርን ድምፅ እንዳይሰማ የሚከላከል ነው።

በሌላ ቦታ ሐዋርያው ጳውሎስ «ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንዶች ጋር ራሳችንን ልንቆጥር ወይም ራሳችንን ልናስተያይ አንደፍርምና። ነገር ግን እነርሱ ራሳቸው ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ አያስተውሉም» (2ቆሮ 10፥12) እንዲሁም «እግዚአብሔር የሚያመሰግነው እንጂ ራሱን የሚያመሰግን እርሱ ተፈትኖ የሚወጣ አይደለምና» (10፥17-18) ብሏል። ስለዚህ ክርስቲያን በኑሮውና በሚያደርገው ውሳኔ የመጀመሪያ ጥያቄው ይህ ምርጫዬና ውሳኔዬ እንደ እግዚአብሔር ቃል ነው ወይ? በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ወይም ሞገስ የሚያገኝ ነው ወይ? ማለት ነው። በምድር ማንም ባይቀበለው እንኳ እግዚአብሔር ከተቀበለው ያ በቂ ነው። በአንጻሩ በምድር አለቆች ጓደኞች የአገሩ ሰው ሁሉ የተቀበለው ሃሳብ ቢሆን እግዚአብሔር ግን የናቀው ከሆነ የተናቀ ሆኖ ይቀራል።

እነዚህ አይሁድ ከአቻዎቻቸው (ከብጤዎቻቸው) ክብርን ስለሚጠብቁ የሚኖሩት በብጤዎቻቸው የመቀባበል ክብ ውስጥ ነው። ከዚያ ክብ ሊወጡ አይችሉም። መሰኪያው ኅብረተ ሰብ በሆነበት የእግዚአብሔር የሆነውን አንድ ሰው እንኳን ሲቀበለው አይችልም ማለት ነው። ክርስቲያኖች ከእንዲህ ዓይነት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ከሚቃወም ሕይወትና አኗኗር መራቅ አለብን። ክርስትና ማኅበራዊ ተቀባይነት የማግኛ መንገድ አይደለም። ክርስትና ከእግዚአብሔር ጋር መስማማትና ለእርሱ መለየት እንዲሁም የእርሱ ከሆኑት ጋር በፍቅርና በመንፈስ አንድነት መኖር ነው። የመንፈሳዊ አንድነትና ኅብረት መሠረቱ እግዚአብሔርን ማዕከላዊ ያደረገ ሲሆን ብቻ ነው።

***5:45 እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ። የሚከሳችሁ አለ! እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው።*** እስከ አሁን እንዳየነው ጌታ አሁን ስለ እርሱ ማንነት ዮሐንስ መጥምቁን፣ መጻሕፍትንና አብን ያቀርባል። አሁን ደግሞ ሌላ ምስክር - ሙሴን። ጌታ ወደ ረጅም ተራራ በወጣ ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ የታዩት (ማቴ 17:3) ምናልባት ሙሴ እርሱ በተናገረውና በጻፈው መሠረት ያልተቀበሉትን መክሰሱ ሊሆን ይችላል። ***ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁኝ ነበር! እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና 5፥46*** እንዳለው ሙሴ የተናገረው ስለ ኢየሱስ ነበር። ይህ ቃል ለአይሁድ እጅግ በጣም አስደንጋጭ ይሆናል። ምክንያቱም ስለ ጽድቅ ሲያስቡ ሙሴን ተስፋ ያደርጋሉና። የሙሴን ሕግ ስለጠበቁ የሚጸድቁ ይመስላቸዋልና። ነገር ግን ሙሴ ያመለከተው ወደሚመጣው መሲሕ ወደ ኢየሱስ ስለሆነና



ኢየሱስ ደግሞ በመጣ ጊዜ አይሁድ ስላልተቀበሉት እርሱ ከሳሻቸው ነበር።

***5፥47 እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?*** ሙሴ የጻፈው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዘፍ 3፥15፤ ዘኍ 21፥9፣ 24፥17፣ ዘዳ 18፥15-18)። እንዲሁም በአዲስ ኪዳን በሉቃ 24፥22 ላይ እናገኛለን። ሆኖም ግን አይሁድ ጌታ ኢየሱስን አልተቀበሉትም። ስለዚህ ሙሴ የጻፈውን ካልተቀበሉ ጌታ ኢየሱስንም አልተቀበሉትም ማለት ነው።

# ምዕራፍ ስድስት

በዚህ ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ አምስት ሺህ ሰዎችን ሲመግብ ከ1-15 ባሰው ክፍል እናያለን:: ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማርያ የያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ ስለ ሕይወት ውኃ ምንጭ ደቀ መዛሙርቱን አስተምሮአል:: አሁን ደግሞ ስለ ሕይወት እንጀራ ያስተምራቸዋል::

***6÷1 ኢየሱስ ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ ተሻገረ::*** የገሊላ ባሕር 20 ኪሎ ሜትር በ12 ኪሎ ሜትር ያህል ነው:: ***የጥብርያዶስ ባሕር 6:1*** የሚሰው ስያሜ የተሰጠው በሄሮድስ አንቲጳስ ሲሆን ለሮም ንጉሥ ጥብርያዶስ ክብር ነበር::

***6÷2 በበሽተኞችም ያደረገውን ምልክቶች ስላዩ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት::*** በዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ ላይ የምናያቸው ምልክቶችና ተአምራት ጥቂቶቹን ብቻ ነው:: በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ ሌሎችም ብዙ ምልክቶች እንደ ነበሩ ከ20:30 እንገነዘባለን::

***6÷3 ኢየሱስም ወደ ተራራ ወጣና በዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ::*** ጌታ በብዙ አጀብና በብዙ ሕዝብ መካከል ቢመላለስም ከደቀ መዛመርቱ ጋር ለብቻ የሚሆንበት ጊዜ ነበረው:: በሌላም ጊዜ እንዲህ ያደርግ ነበር (ማር 6:31):: የብዙ ሕዝብ መከተል የአገልግሎቱን መስፋት አመልካች ቢሆንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለብቻ መሆኑ እነርሱ የበለጠ እንዲያውቁትና እንዲማሩ የበለጠ ጊዜና ሁኔታ ይሰጣቸዋል:: ኢየሱስ ወደ ሰማይ የሚሄድበት ጊዜ ስለቀረበ የአገልግሎቱ እደራ ተቀባዮች ደቀ መዛሙርት ከእርሱ ጋር መሆን ያስፈልጋቸዋል::

***6÷5 ኢየሱስም ዓይኖቹን አንሥቶ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየና:: ፊልጶስን፡- እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው::*** ጌታ በተለይ ፊልጶስን የጠየቀው ከቤተ ሳይዳ ስለ ነበረ ሲሆን ይችላል (1:44):: እነርሱ ከነበሩበት ቦታ ቤተ ሳይዳ 14 ኪሎ ሜትር ያህል ብቻ ስለሚርቅ እንጀራ መገዛት ካለበት ስለ አካባቢው ፊልጶስ የተሻለ ሀሳብ ይኖረዋል ብሎ እንደ ሰው ማሰብ ይቻላል::



***6÷6 ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው[28] ይህን ተናገረ::*** ይህ ፈተና ፊልጶስን ለመጣል ሳይሆን እምነቱን ለማሳደግ የቀረበ ስለሆነ ከዚህ የሚገኘውን ትምህርት መማር ነበረበት:: ምክንያቱም፡- ***እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ እንኳ እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰለት 6:7::*** እንደ ሰው ፊልጶስ ጉበዝ የሂሣብ ሰው ነው:: ለእስራኤላውያን ለወር ሙሉ ሥጋ እሰጣቸዋለሁ ብሎ እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ «ሙሴም፡- እኔ በመካከላቸው ያለሁ ሕዝብ ስድስተ መቶ ሺህ እግረኛ ናቸው ... እነርሱን የሚያጠግብ ...» (ዘኁ 11:21-22) ከወዴት ይመጣል እንዳለው ነበር:: በሙሴ ጊዜ ድርጭቶች በነፋስ እንደ መጡ (በዘኁ 11:31) ጌታ ለሰዎች የሚበሉትን እንጀራና ዓሣ ከምንም (ከባዶ) በትዕዛዝ ቃል ሊያመጣው ይቻለው ነበር:: እዚህ ደግሞ ጌታ ያለውን ትንሽ ወስዶ ሲያበዛው እናያለን:: ሁለቱም ተአምር ነው::

***6:9 አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና፡-*** ይህ ብላቴና ብቻ ምግብ እንዴት ያዘ? እንዴትስ ሳይበላው ቆየ? የያዘው እንጀራና ዓሣ ለራሱ ምሳ የያዘው ሲሆን ይችላል:: ሌላ የሚገርመው ነገር ያ ብላቴና ለራሱ የያዘውን ለኢየሱስ መስጠቱ ነው:: ብላቴናው እንጀራውን በመስጠቱ ገንዘብ የተቀበለ አይመስልም:: የተአምር ተካፋይ ሆነ፤ ከሕዝቡ ጋር አብሮ የራሱን እንጀራና ዓሣ ሳይበላ አይቀርም፤ ምንም አልጐደለበትም:: ምናልባት ሌሎችም እንደ ብላቴናው ምግብ ይዘው ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሲኖሩ ይችላሉ:: ብላቴናው ግን ያለውን ያንን አቀረበ፤ በጌታ እጅ ለአምስት ሺህ ሰው የሚበቃ ሆነ::

***6:10 ቁጥራቸውም አምስት ሺህ የሚያህል ነበር::*** አምስት እንጀራ ለአምስት ሺህ ሰው፡- አንድ እንጀራ ለአንድ ሺህ ሰው እንደ ማለት ነው:: ይህን በአገራችን የእንጀራ አገጋገር ዓይነት ብናስበው አንድ እንጀራ ለአንድ ሺህ ሰው እንኳንስ ለምግብነት በእንጀራው ላይ የሚኖሩ ዓይኖች ቢቆጠሩ አምስት ሺህ ይሆኑ እንደሆነ እንጃ:: ጌታ የባረከው ጥቂቱ ለብዙ ጊዜ ወይም ለብዙ ሰው ይበቃል::

---

[28] The word *test (peirazo)* ... refers to a proving experience like Jesus'testing in the wilderness or Abraham's test over the sacrifice of Isaac. In all thasa cases, God allowed the test to occur, not expecting failure, but placing the person in a situation where his or her faith might grow stronger. Jesus did not want Philip to miss what he was about to do. Ibid. p. 123.

***6:11 ኢየሱስም እንጀራውን ያዘ አመስግኖም፡-*** ጌታ መጀመሪያ ወሰደው፤ ተረከበው፤ የራሱ አደረገው፤ በራሱ እጅም አበዛው፤ አብዝቶ መልሶ ለሚሰጡት ደቀ መዛሙርት ሰጣቸው፡፡ ጌታ በእጥረታችን ላይ በረከትን (ማብዛትን) እንዲያደርግ ስንፈልግ ያንን አለን የምንለውን አስቀድመን ለጌታ በማስረከብ ይህ ትንሽ ነገር የአንተ ከአንተ የሆነ ነው ልንለውና እንዲባርክልን ልንጠይቀው ይጠበቅብናል፡፡ የሚበዛው በእርሱ እጅ ሲገባ፤ ሲናገርበት (ሲባርከው)ና መልሶ ሲሰጠን ነው፡፡ አልዓዛርን ከመቃብር ለማስነሣት እግዚአብሔርን አመስገነ (11:41)፡፡ በእጁ ስላለው ጥቂት ነገር እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ ለአልዓዛር ሕይወትን፤ ለእነዚህ ደግሞ ምግብን ሰጠ፡፡ ሁለቱም የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ሰጦታውን ያሳስባል፡፡ ጥቂቱንም የሰጠ እግዚአብሔር ነው፡፡

በምግብ ማመስገን ልማዳዊ ነገር አይደለም፡፡ አመስግኖ መብላት የክርስቲያን መለያ ተደርጎ የሚቆጠር ልማዳዊ ተግባር አይደለም፡፡ አመስግኖ መብላት በእጃችን ያለው (በፊታችን የቀረበው) ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስለሆነ ለጪውን ይህን ሰለ ሰጠኸን ተመስገን ማለት ነው፡፡ በኤማሁስ መንገድ ይሄዱ የነበሩ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ተስፋ የቆረጡት የሚያነጋግራቸው ጌታ እንደሆነ የለዩት እንጀራውን አንስቶ ባርኮ በቆረሰው ጊዜ ነበር (ሉቃ 24:30)፡፡ ለእንጀራ ማመስገንና መባረክ ጌታ ያደርገው ነበረ፡፡ ክርስቲያኖችም የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌ በመከተል ስለ ምግብ እግዚአብሔርን ሲያመስግኑ እርሱ እንዲባርክላቸው ሊጠይቁት ይገባል፡፡

***6:13 ከበሉትም ከአምስቱ የገብስ እንጀራ የተረፈውን ቍርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ፡፡*** አምስት እንጀራ ለአምስት ሺህ ሰዎች ተዳርሶ መጥገባቸው ብቻ ሳይሆን፤ የተረፈው አሥራ ሁለት መሶብ መሙላቱ ሌላ ተአምር ነው፡፡ በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጠን (1:16) እንደሚል በአንድ መስጠት ላይ ጨምሮ አብዝቶ መስጠት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፡፡ አትርፎ መስጠት፤ ጠግቦ ማትረፍ መትረፍረፍ፡፡ በእያንዳንዱ ደቀ መዝሙር ልክ የሚሆን አንዳንድ መሶብ የተረፈ ቁርስራሽ ተሰበሰበ፡፡

***6÷14 ሰዎቹ ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ፡- ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ፡፡*** እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን የተከተሉት ቀደም ብለው ምልክቶች ስላዩ ነበር (6:2)፡፡ አሁን ደግሞ ሌላ ምልክት ተጨመረላቸው፡፡ ስለሆነም ኢየሱስ ***ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው*** በማለት ተናገሩ፡፡ ለረሃባቸው ምግብ የሚሰጣቸውና ምልክት የሚያደርግ ነቢይ አገኘን ብለው ሲያነግሡት ፈለጉ (6:15)፡፡ ኤልሳዕ ሃያ እንጀራ ለመቶ ሰው እንዲሆንና



እንዲተርፍም እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት አድርጎ ነበር (2ነገ 42-44)፡፡ ስለዚህ ኢየሱስን እንደ ኤልሳዕ ዓይነት ሌላ ነቢይ አድርገው ቆጥረውት ይሆናል፡፡ ያኛው አንዱን እንጀራ ለአምስት አበዛ፤ ይህኛው ደግሞ አንዱን ለአንድ ሺህ፡፡ ነቢይ አሉት እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነም አልተረዱም፡፡

***6:15 ኢየሱስ ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደ ተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ፡፡*** ሊያነግሡት የፈለጉት ጌታ የመጣበትን ዋና ዓላማ ያልተረዱ፤ ባዩት ነገር ብቻ የተደነቁና በዕለታዊ ፍላጎታቸው መርካት ብቻ የተደሰቱ አይሁድ ናቸው፡፡ ሀሳባቸውን እንዲያደርጉ በእጃቸው አልተያዘላቸውም፡፡ የእርሱ መንግሥት በተደረገው ተአምር ተደንቀው በተሰባሰቡ ሰዎች የሚመሠረት አይደለም፡፡ የመጣው ሰምድራዊ መንግሥት ንጉሥነት አይደለም፡፡ ስለዚህ ተልዕኮውን ይፈጽም ዘንድ አውቆ ***ፈቀቅ አለ፡፡*** ከዚህም በፊት ንጉሥ እንዲሆን በዲያብሎስ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር (ማቴ 4÷1-11)፡፡

ከአምስት ሺህ እጃቢ ተለይቶ ለብቻ ወደ ተራራ መውጣት!! የሕዝቡ አካሄድ ጥሩ እንዳይደለ ሲያይ ጌታ ለብቻው ***ፈቀቅ አለ፡*** ከዚህ ለአገልጋዮች የሚሆን ትልቅ ትምህርት እናገኛለን፡፡ አገልጋዮች በእጃቸው ተአምራት ሲደረግ፤ አድናቂና ተከታይ ሲበዛ ያን ጊዜ ለብቻ መሆንን መፈለግ መልካም ነው፡፡ ከአድናቂ ብዛት በመራቅ ሃሳብን ሰብስቦ በጸጥታ በእግዚአብሔር ፊት መሆንና እንደገና ለአገልግሎት መዘጋጀት መልካም ነው፡፡ ያለ መለመኑና ያለ ጊዜው የመጣ ድጋፍ ለስህተት ይጥላል፤ ከጌታ ያልሆነ ሙገሳ ወደ ትዕቢት ይገፋል፡፡

***6÷16-17 በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር ወረዱ፥ በታንኳም ገብተው በባሕር ማዶ ወደ ቅፍርናሆም ይመጡ ነበር፡፡*** ደቀ መዛሙርቱ አብዛኛዎቹ አካባቢውን የሚያውቁ እንዲሁም የተለማመዱ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ፡፡ ስለዚህ በዚያ ባሕር ላይ መሄድ አይፈሩም፡፡ ጴጥሮስም ከዚህ በፊት ሌሊቱን ዓሣ ሲያጠምድ ነበረ (ሉቃ 11÷31)፡፡

***6÷17 አሁንም ጨልሞ ነበር፤ ኢየሱስም ገና ወደ እነርሱ አልመጣም ነበረ፡-*** በማር 4÷35-41 ላይ የተገለጠው የባሕር መታወክ ከዚህ ከአሁኑ ሁኔታ በፊት እንደ ተፈጸመ ቀደም ተከተሉን ስናጤን እንረዳለን፡፡ በዚያኛው መታወክ ጊዜ ኢየሱስ በታንኳ ውስጥ ነበር፤ አሁን ግን ገና ወደ እነርሱ አልመጣም ነበረ፤ ብቻቸውን ነበሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ***ብርቱ ነፋስም ስለነፈሰ ባሕሩ ተናወጠ 6:18፡፡***

***6፥19 ኢየሱስ በባሕር ላይ እየደሄደ ወደ ታንኳይቱ ሲቀርብ አይተው ፈሩ፡፡*** ባሕሩ በብርቱ ነፋስ እየተናወጠ ነው፡፡ በዚህ በነፋስ በሚናወጥ ባሕር ላይ ደቀ መዛሙርቱ በታንኳ ስመቅዘፍ እየሞከሩ ነው፡፡ ጊዜውም ጨልሟል፡፡ ብዙ ብርቱ ነገሮች ገጥመዋቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ ኢየሱስን በባሕር ላይ ሲራመድ በማየታቸው ፈሩ፡፡ ኢየሱስ በባሕር ላይ መሄድ ብቻ ሳይሆን በሚናወጥ ባሕር ላይ ረጅም ርቀት ማለት የገሊላን ባሕር ግማሽ (***ሀያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ***) ያህሉን ሄዶታል፡፡

***6፥20 እርሱ ግን፡- እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው፡፡*** በብርቱ ነፋስ በሚናወጥ ባሕር ላይ ተራምዶ በመምጣት ***አትፍሩ*** ብሎ ማጽናናት የሚችል ***እኔ ነኝ*** የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ መለኮት ነው፡፡ ኢየሱስ ***እኔ ነኝ***[29] ሲል እግዚአብሔር ለሙሴ «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ» (ዘጸ 3፡14) ብሎ ከገለጸለት ጋር ተመሳሳይ የማንነት መግለጫ ነው፡፡

***6፥21 ወዲያው ታንኳይቱ ወደሚሄዱበት ምድር ደረሰች፡-*** ኢየሱስ ወደ እነርሱ ከመምጣቱ በፊት ደቀ መዛሙርቱ ከምድር ሩቅ ነበሩ፡፡ ከማርቆስ 6፥48 እንደምንነዘበው ይህ ጊዜ ከሌሊቱ ዘጠኝ ወይም አሥር ሰዓት ስለነበረ የገሊላ ባሕር ግማሽ ያህል ርቀት ስመጓዝ ረጅም ጊዜ ፈጅቶባቸዋል፡፡ ሆኖም በብርቱ ነፋስ ሲናወጡ የነበሩት በኢየሱስ መመጣት ምክንያት ***ወዲያው*** (በቅጽበት) ደረሱ፡፡

***6፡27 ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤*** ዘላስማዊነት ስሌለው ስጊዜዊ ነገር ራስን አሳልፎ መስጠት «መብል ስሆድ ነው ሆድም ስመብል ነው፡፡ ሁለቱንም እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል» (1ቆሮ 6፡13) እንደተባለው ነው፡፡ ለዘላለም ሕይወት (የሚኖር መብል) ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

***6፡27 እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታል፡-*** ማለትም አርግጠኛ እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ማተም ፊርማን ማሳረፍና ማረጋገጥ ወይም ማጽደቅ ነው፡፡ የእግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የዘላለም ሕይወት እንደሚገኝ ነው፡፡ የዘላለምን ሕይወት ለማስገኘት ተስፋ የሚሰጡ ሌሎች ሁሉ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ

[29] The literal reading for <It is I> is <I am> (Greek, *ego eimi*); it is the same as saying <the I AM is here> or <I, Yahweh, am here.> Ibid. 129.



የታተመ ማረጋገጫ የላቸውም፤ ማረጋገጫው ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

***6፥28 የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ አሉት?*** ሕዝቡ ***ሥራ*** በሚለው ቃል ላይ ብቻ በማትኮር ***ምን እናድርግ?*** ብለው ይጠይቁታል፡፡ እርሱ ግን ይህ የዘላለም ሕይወት በሰው ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚሰጥ መሆኑን ነግሯቸው ነበር፡፡ እንደገናም ጌታ በመመለስ፡- ***ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው 6፥29***፡ ደህንነትን ለማግኘት ከሰው የሚጠበቀው ሥራ አንድ ብቻ ነው፤ ይህም በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው፡፡ ደህንነት እግዚአብሔር በነፃ የሚሰጠው ስጦታ ነው፡፡ ይህን ስጦታ (ጸጋ) የመቀበያው መንገድ እምነት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ያለ ሌላ ደህንነትን ለማስገኘት የሚደረግ ጥረት ሁሉ ከንቱ ነው፡፡ ምክንያቱም ጽድቅ በሰው ጥረት አይገኝምና፡፡

ሰው የቱንም ያህል መልካም ለማድረግ ቢሞክር በሰው ዘንድ መልካምነት ስለሌለ በእግዚአብሔር ፊት ለማጽደቅ የሚበቃ ነገር ሊያቀርብ አይችልም፡- «ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው» (ኢሳ 64፡6) እንደሚል፡፡ እንግዲህ ሰዎች የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት እንዲሠሩት የታዘዘው ሥራ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የሚቻለው በሥራ ሳይሆን ጴጥሮስ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» (ማቴ 16፥16) ያለውን በመቀበልና በእርሱ በማመን ብቻ ነው፡፡ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ፈቃድን፣ ሀሳብን፤ ምኞትን ሁሉንም ነገር ለእርሱ በማስረከብ በእርሱ ስመመራትና ስመተዳደር መምረጥን ያጠቃልላል፡፡

***6፥30 አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ?*** ይህን የሚጠይቁት እንጀራን ከበሉ በኋላ ስለሆነ ምናልባት ሁልጊዜም እንጀራን እየባረከ እንዲሰጣቸው ፈልገው ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም በመቀጠል፡- ***ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራን ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ አሉት 6፥31***፡፡ ኢየሱስን ይከተሉ የነበሩት ሕዝብ እንጀራ የበሉት አንድ ቀን ነው፡፡ አባቶቻቸው ግን በምድረ በዳ በነበሩባቸው ዓመታት ሁሉ መናን ይበሉ ነበረ (ዘጸ 16፥24-25)፡፡ ስለዚህ ዋና ጥያቄያቸው ለአባቶቻችን እንጀራን በየቀኑ ይሰጣቸው ከነበረው ከሙሴ አንተ በምን ትልጣለህ? ማለታቸው ነው፡፡

***6፥32 እውነት እውነት እላችኋለሁ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚለጣችሁ እባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራን የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም::*** አይሁድ ለአባቶቻቸው መናን የሰጣቸው ሙሴ እንደሆነ አድርገው ይቆጥራሉ:: ከሙሴ በሳይ ያለውን ዋናውን ሰጪ አሳወቁትም:: ጌታ ኢየሱስ ክርሰቶስ ወደ ትክክለኛው መረዳት ያመጣቸዋል:: በምድረ በዳ እስራኤልን የመራ ሙሴ ሳይሆን እግዚአብሔር ነው (ዘጸ 13፥17-18):: መናን የሰጠም እግዚአብሔር ነው:: ሙሴ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (መልእክት ተቀባይና አድራሽ ወይም አገልጋይ) ነበረ:: በእነዚህ በሁለቱ ሃሳቦች መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ ማስተዋል እጅግ ይጠቅማል::

የሕዝቡ መሪ እግዚአብሔር ነው:: ሙሴ ግን በእግዚአብሔር መሪነት ሥር ያለና እርሱን ሰምቶ ሕዝብን የሚመራ ለው ነበር:: መልካምን ነገር የሚለጥ እግዚአብሔር ነው:: በምድረ በዳ ለሕዝቡ መናን ከሰማይ ያዘነበ እርሱ ነው:: ሙሴ ደግሞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መና ሲሰጥ እንደሚወድ ተረድቶ ሕዝቡ ያንን ማለትም እግዚአብሔር የሚሰጠውን እንዲሰበስብ የተናገረ ሰው ነው::

ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ባለማስተዋል የምንሄድባቸው መንገዶች አሉ:: አንድ ሰው ለበሽተኛ ጸልዮ ለውየው ቢፈወስ ህሳባችን ከሚጸልየው ሰው ጋር ይያያዝና አውቀንም ሆነ ሳናውቅ ምስጋናና አክብሮታችን ለሰውዬው ይሆናል:: ትክክለኛው መረዳት ግን መልካም ነገር ሁሉ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር መሆኑን በማወቅና ሰውዬው ከበሽታው እንዲፈወስ የፈቀደውና ኃይልን የሳከ እግዚአብሔር እንደሆነ በመገንዘብ ክብርና ምስጋናን ለእግዚአብሔር ማምጣት ነው:: ይህም ከስህተትና ከትዕቢት ይጠብቃል::

***6፥33 የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው::*** አባቶቻቸው ከለማይ የሚወርድን እንጀራ በልተዋል:: ከሰማይ የወርደውን ለአርባ ዓመታት ያህል የበሉት ያ እንጀራ የሚጠፋ መብል ነው (6:27):: ለአባቶቻቸው የወረደው እንጀራ ለተወሰነ ዘመን በምድራዊ ሕይወት አቆያቸው:: እግዚአብሔር የሳከው ከሰማይ የወረደው እንጀራ (ማለትም ኢየሉስ ክርስቶስ) የዘላለም ሕይወትን የሚሰጥ ነው::

***6፥34 ጌታ ሆይ፡ ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት::*** ጥያቄያቸው ልክ ሳምራዊቷ ሴት «ውኃ እንዳልቀዳ ወደዚህም እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ» (4:15) ብላ እንደጠየቀችው ነው:: በየዕለቱና ለዘወትር



የሚበሉት እንጀራ ይፈልጋሉ፤ የጌታ ንግግር ግን ከዚህ ያለፈ ነበረ:: ስለዚህ ጌታ:- ***የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም 6፥35*** አላቸው:: የሕይወት እንጀራ የሚፈልጉ ሰዎች ፍላጐታቸውን የሚያገኙት ወደ እርሱ በመምጣት በእምነት በመቀበል ነው:: ***ስጠን 6፥34*** ብለው ለጠየቁት ጌታ የሚላቸው ***እኔ ነኝ*** ብሎ ነው:: እርሱ የሁልጊዜ እርካታን ይሰጣል::

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ***እኔ ነኝ*** እያለ በተደጋጋሚ ራሱን የገለጸበት መንገድ በብሉይ ኪዳን ጌታ እግዚአብሔር ማንነቱን «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ» ብሎ በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን ከገለጠበት መንገድ ጋር ይመሳሰላል:: በዚሁ መጽሐፍ ጌታ ኢየሱስ ***እኔ ነኝ*** በማለት የገለጠበትን ክፍልና ምን ትርጉም እንዳለው አጠር ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው እንመለከታለን::

- **የሰው ልጅ 6፥27:-** ይህ የመሲሑ ሌላ መጠሪያ ሲሆን፤ ይህም የእርሱን ሰው መሆን ያመለክታል:: ጌታ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ራሱን በዚህ ስም ጠርቶአል::

- ***የሕይወት እንጀራ 6፥35:-*** የእርሱን ሕይወት ሰጪነት ይገልጻል:: ሕይወት ሰጪ እርሱ ብቻ ነው::

- ***የዓለም ብርሃን 8፥12:-*** ብርሃን የመንፈሳዊ እውነት መግለጫ ነው:: እውነትን ለሚፈልግ ሁሉ አንድ እውነት አለ፤ ይህም ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

- **የበጎች በር 10፥7:-** የእግዚአብሔር በጎች ወደ ተሰበሰቡበት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግቢያው በር ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፤ በማመን ነው::

- ***መልካም እረኛ 10፥11:-*** ይህ የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ምሪትና ጥበቃ ያሳያል::

- ***ትንሣኤና ሕይወት 11፥25:-*** ኢየሱስ ክርስቶስ ሙታንን ለማስነሣት ኃይል እንዳለውና ብቸኛ ሕይወት ሰጪ መሆኑን ይገልጻል::

- ***መንገድ፣ እውነት፣ ሕይወት 14፥6፡*** ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበትን ምክንያት በማጠቃለል ይገልጻል። እንዴት? ለሚለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፤ ምን? ለሚለው እውነት የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ የሚያስገኘው ደግሞ ሕይወትን እንደሆነ ያሳያል።

- ***የወይን ግንድ 15፥1።*** ይህ መጠሪያ «እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ» ከሚለው ጋር ይያያዛል። ቅርንጫፍ በሕይወት የሚኖረው ከግንዱ ጋር እስከተያያዘ ድረስ እንደሆነ እንዲሁ አማኞች ሕይወት የሚኖራቸው ከቅርንጫፉ ጋር ሲያያዙ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል። ስለሆነም በመንፈሳዊ ሕይወት አማኞች ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጥገኞች መሆናቸውን ያስረዳል።

***6፥36 ነገር ግን አይታችሁኝ እንዳላመናችሁ አልኋችሁ።*** ጌታ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ አይተውታል። ያደረገውን ምልክት ሁሉ ተመልክተዋል። እያዩ አላመኑም። ሰው ምልክቶች አይቶ የሚያሳዩትን አቅጣጫ ተከትሎ በመሄድ ወደ ኢየሱሰ ከልደረሰ በስተቀር ምልክቶች በራሳቸው ወደ ኢየሱስ አያደርሱም። ስለዚህ ከሰው እርምጃ ይጠበቃል።

***6፥37 አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡-*** አብና ወልድ በደህንነት ሥራ ውስጥ አብረው የሚሠሩና ለአንድ ዓላማ አንድነት እንዳላቸው ያሳየናል።

***6፥37 ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም።*** አብ በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ለወልድ ይሰጠዋል። በአብና በወልድ መካከል አንድ ሃሳብና በአንድ ላይ መሥራት አለ። አብ ወደ ኢየሱስ ያመጣውን ያን ኢየሱስ ደግሞ ይጠብቀዋል። ስለዚህ ወደ ኢየሱስ ከመጣን እርሱ እንደሚጠብቀን እርግጠኞች መሆን አለብን።

***6፥38 ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና።*** ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ ከድንግል ማርያም እንደተወለደ እናውቃለን። እርሱ ፍጹም አምላክ ነውና የመጣው ከሰማይ ነው። በእርሱና በአብ መካከል ያለ የፈቃድ አንድነት አለ።

***6፥39 ከሰጠኝም ሁሉ አንድስ ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው።*** ኢየሱስ ክርስቶስ



የመጠበቅ አቅሙ ፍጹም የሆነ ***አንድስ ስንኳ*** እንዳይጠፋ አድርጎ ነው።
በእርሱ ያመኑት እያንዳንዳቸው በነጠላና ሁሉም በአንድነት በኃይሉ የተጠበቁ ናቸው። ማንም ኃይለኛ ከእርሱ እጅ ሲያወጣቸው አይችልም። ሆኖም ***ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ ወደፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም 6፡66*** እንደሚል ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ ኢየሱስን መከተል ቢያቆሙ እነዚያ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥበቃ ውስጥ ለመቆየት ያልወደዱ ናቸው።

***6፥40 ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።*** በ3፥16 ላይ ቀደም ሲል እንዳየነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ***(የአባቴ ፈቃድ)*** በልጁ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ነው። ይህ በመጽሐፍ የተገለጸ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ***በእርሱ የሚያምን ሁሉ*** እንደሚል የዘላለም ሕይወት የሚሰጠው ለሚያምን ለማናቸውም ሰው ነው። ***በመጨረሻው ቀን ማለትም*** በትንሣኤ ቀን የሚነሣው እያንዳንዱ (ሁሉም) ሰው ነው።

***6፥41-42 አይሁድ፡- ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ ስላለ ስለ እርሱ አንጐራጐሩና፡- አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን? እንግዲህ፡- ከሰማይ ወርጃለሁ እንዴት ይላል? አሉ።*** የአይሁድ አንዱ ችግራቸው እናውቃለን ባይነት ነው። ጠንቅቀው ያወቁ የሚመስላቸው፤ እናውቃለን የሚሉትን አጥርተው ባለመረዳታቸው ስህተት ውስጥ የገቡ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ***እርስ በርሳችሁ አታንጐራጕሩ 6፥43*** አላቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ የዮሴፍ ልጅ መባሉ (ሉቃ 3:23፤ 4:22) የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ዮሴፍ በሥጋ አባቱ አልነበረም፤ አባቱ እግዚአብሔር ነው፣ እርሱ የተፀነሰው በመንፈስ ቅዱስ ነውና። መጻሕፍት ስለ እርሱ ድንግል እንደምትፀንስ ልጅም እንደምትወልድ ስሙም አማኑኤል እንደሚባል (ኢሳ 7:14) የሚለውን እንኳ አላስተዋሉም። ቃሉን አንብበዋል ሙሉ መልእክቱን ግን አልጨበጡም ስለዚህ በስህተት ጎዳና ነጎዱ።

***6፥45 ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ተብሎ በነቢያት ተጽፎአል እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።*** ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣ በአብ የተሳበ፤ ከአብ የሰማና የተማረ ነው። ***የላከኝ አብ ካሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም 6፥44።*** በደህንነት ሥራ ትልቁ ድርሻ ያለው እግዚአብሔር ነው። እርሱ ሰውን ይስባል፣ ይናገራል፣ ያስተምራል። ሲሳብ የመጣ፣

ሲነገረው የሰማ፣ ሲማር ያስተዋለ ወደ እግዚአብሔር ይመጣል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናል::

*ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ* እንደሚሆኑ በኢሳ 54፥13 እንዲሁም በኤር 31፥31-34 ተጽፎአል:: *መማር* የሚለው *መሰማትንና* ማስተዋልን አብሮ *ያጠቃልላል*:: እግዚአብሔር ለሕዝቡ በተለያየ *መንገድ ያስተምራል*:: ዋናው *መንገዱ* አሁን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው:: *መንፈስ ቅዱስም ጌታ ያስተማረውን ያሳስባል*::

*6፥46 አብን ያየ ማንም የለም ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ እርሱ አብን አይቶአል::* ከእርሱ ዘንድ ከመጣው ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ከሰው እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም ነው (ዮሐ 1፥18፤ 1ጢሞ 6፥15-16)::

*6፥47-48 እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው:: የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ::* የዘላለምን ሕይወት አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ባመነበት ጊዜ ያገኛል - ***አለው*** ይላልና:: ይህ ፍጹም እርግጠኛ ነው:: *በእኔ የሚያምን* የሚለው ቃል (ሐረግ) ቀጣይነትን - አንድ ጊዜ አምኖ *ማቆም* ሳይሆን ሁልጊዜ በማመን *መቀጠልን ያሳያል*:: ለሚያምን *የሕይወት እንጀራ* ማለትም የዘላለም ሕያወትን የሚሰጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ይህን እንጀራ የሚበላ አይሞትም::

*6፥49-51 አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም:: ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው:: ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው::* በሙሴ በኩል የወረደውን መና የበሉ አባቶቻቸው ሁሉ ሞቱ:: ያም እንጀራ (*መና*) የዘላለምን ሕይወት እንዲሰጥ የተላከ አልነበረም:: መና ለጊዜው ሕይወትን የሚያቆይ ምግብ ነበር:: ለዘላለም በሕይወት የሚያኖር *ከሰማይ የወረደ እንጀራ* ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህ እንጀራ ሰውን በሕይወት የሚያኖረው ሲበላ ነው፤ ማለትም በእምነት ሲቀበሉት ብቻ ነው:: አይሁድ ይህን መና (እንጀራ) አይተውታል፤ በመካከላቸውም ነበረ፤ ነገረ ግን አልተመገቡትም ማለትም በእርሱ አላመኑም:: ስለዚህ የዘላለምን ሕይወት ሊቀበሉ አልወደዱም::

*6፥51 እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው::* በእርሱ ሞት በኩል ዓለም ሕይወትን እንድታገኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሞቱ ሲያመለክት ነው::



***6፥53 የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም::*** ጌታ ኢየሱስ ስለ ***ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው 6፥51*** ባለ ጊዜ አይሁድ ***እንዴት ይችላል? ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ 6:52***: ጌታም ሕይወት ከራሳቸው እንደማይገኝና ሕይወት የሚገኘው የእርሱን ***ሥጋ*** በመብላት ደሙንም በመጠጣት እንደሆነ ገለጠላቸው:: ሰው በራሱ ሕይወት የለውም:: ሕይወት ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጥ ነው:: የእርሱ ***ሥጋ ስለ ዓለም ሕይወት 6:51*** የሚሰጠው ነው:: ይህን እንጀራ (የኢየሱስ ክርስቶስን ***ሥጋ***) የበላ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው ለእርሱ ኃጢአት እንደሆነ በእምነት የተቀበለ ሰው የዘላለም ሕይወት አለው::

***6፥54-55 ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ:: ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና::*** ሥጋውን መብላትና ደሙን መጠጣት የተያየዘው ከዘላለም ሕይወት ጋር ነው:: በሌላም ቦታ በተደጋጋሚ የሚያምን ሁሉ በሕይወት ይኖራል (3:16) ብሎ እንደተናገረው በእርሱ የሚያምነው የዘላለም ሕይወት ያገኛል:: ስለሆነም በኢየሱሰ ማመን ማለት የእርሱን ***ሥጋ*** መብላት ደሙንም መጠጣት ማለት ሲሆን ይህም በመስቀል ላይ በሞተውና ደሙን ባፈሰሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት ነው::

***6፥56 ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ::*** ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን (ሲቀበል) በእርሱ ውስጥ መኖር ይጀምራል:: እንዲሁም ኢየሱስ በሰውዬው ውስጥ ይኖራል ማለት ነው::[30] ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ምሥጢር ስለሆነ በሥጋዊ አእምሮአችን ልንረዳው የምንችለው አይደለም:: እውነተኛ የሆነው ጌታ ግን ስለተናገረ እናምነዋለን:: እርሱ በእኛ ይኖራል፤ የሚያምኑትም በእርሱ በኢየሱስ ይኖራሉ::[31] በሌላም ቦታ «ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ

---

[30] < ... <mutual indewelling> ( that is, a simulataneous indewelling of two persons in each other, also known as <coinherence>). When we receive Jesus, he lives in us and we live in him. Ibid. p.139.

[31] እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ «ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆኑ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም» (1ቆሮ 6:15) የሚለው ከዚህ ጋር ይስማማል::

እይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ (1ቆሮ 6:19-20) ይላል።

***6፥57 ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው[32] እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።*** በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነት በእኛ ሕያውነት ተመሳሳይነት እንረዳለን። በሌላም ቦታ ***አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና 5፥26*** እንዳለ። አብ ሕያው ነው (ለዘላለም አለ) ወልድም ሕያው ነው (ለዘላለም አለ)። በዘላለማዊ የአብና ወልድ ተዛምዶ ውስጥ ወልድ ከአብ የተነሣ በሕይወት ይኖራል። እንዲሁም በኢየሱስ የሚያምን ሁሉም ሰው ከአመነበት ጊዜ ጀምሮ ከኢየሱስ የተነሣ ሕያው ይሆናል።

***6፥58 ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል።*** ይህ ጥቅስ ጌታ ስለ እንጀራ መናገር፣ ማስተማር የጀመረውን የሚያጠቃልል ጥቅስ ነው። እርሱ ሕይወትን የሚሰጥ እንጀራ እንደሆነና እባቶቻቸው ከበሉት እንጀራ የተለየ እንደሆነ ያሳያል። መናን የበሉ ሞቱ፤ ኢየሱስ የሚሰጠውን እንጀራ የሚበሉ ለዘላለም ይኖራሉ። መና የተሰጠው ለአባቶቻቸው በወል ነው፤ የዘላለም ሕይወት የቀረበው ለሰው ሁሉ ነው፤ የሚሰጠው ግን እንጀራውን ሲበላ ለሚወድ ለእያንዳንዱ ሰው ነው።

***6፥60 ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ፦ ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል? አሉ።*** ንግግሩ ከባድ ነው፤ ነገር ግን እውነት ነው። እነዚህ ሰዎች እውነት የሆነውን ለመቀበል መድፈር ነበረባቸው። እውነትን የሚፈልግ ትምህርቱ ከባድ ቢሆንም ከእውነት ጋር ለመኖር፣ ለመጣበቅ ይወስናል። ብዙዎች ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተሉት እንጀራ ስለሰጣቸውና እነርሱ ሳሰቡትና ለተመኙት የማንገሥ ዓላማ የሚሆን ሰው ያገኙ ስለመሰላቸው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ማንነቱንና የመጣበትን ዓላማ ሲገልጥላቸው ከሚፈልጉት አንጻር ተስማሚ ስላልሆነላቸው አንጐራጐሩ። የራሳቸው ፍላጎትና መለኪያ ነበራቸው።

[32] <I live by the Father - Being one with him>, WEN. <which is to be understood of Christ, not as God, but as Mediator, and as man. ... As man, he had his human life from God, and was preserved and upheld in it by him; and he laid it down at his command, and at his death committed his soul or spirit to him; and which was restored unto him, and is continued with him. Gill.



***6፥62 እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል?*** ይህ ***የሰው ልጅ*** ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ ከሰማይ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ (1:1-2፤ 17:5)። ወደ ምድር የመጣው ሰውን ለማዳን ነው - ሰዎች ግን አላመኑበትም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ***አስቀድሞ ወደ ነበረበት*** ሊመለስ ነው። እነዚህ ሰዎች ተመልሶ ሲወጣ ቢያዩ ያምኑ ይሆን? ያለማመናቸው ምክንያት ራሳቸው በሀሳባቸው የሳሉትና የሚፈልጉት መሲሕ በመኖሩ ነው። የኢየሱስ አኗኗር ደግሞ እነርሱ እንደተመኙት ሳይሆን አብ እንደላከው በመሆኑ ወደ ሰማይ ሲወጣ ቢያዩም አይቀበሉም።

***6፥63 ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።*** ጌታ ኢየሱስ ***ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ 6፥56*** ብሎ የተናገረውን ቃል በቁሙ በመተርጎም የሰውን ሥጋ እንደ መብላትና ደሙንም እንደ መጠጣት አድርገው ስለቆጠሩት ***ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው 6:60*** ተባባሉ። ይህን በማብራራት የሚነግራቸው ***ሥጋ ምንም አይጠቅምም*** በማለት ነው። ቀደም ሲል ለኒቆዲሞስ ***ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው 3፥6*** በማለት አስረድቶት ነበረ። በሰው ሀሳብና ጥረት የሆነ ነገር መንፈሳዊ የሆነ ነገርን እያስገኝም ሲል ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ***ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።*** ስለሆነም ቃሉን የሚከተል በቃሉ ሕይወት ያገኛል። ይህ ሕይወትን የሚሰጥ ቃል መንፈስ ነውና።

***6፥64 ኢየሱስም የማያምኑት እነማን እንደ ሆኑ አሳልፎ የሚሰጠውም ማን እንደ ሆነ ከመጀመሪያ ያውቅ ነበርና።*** እያንዳንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ይታወቃል። ሊከተለው የጀመረውም ለምንና እስከ የት ድረስ መከተል እንደሚፈልግ ***ከመጀመሪያ*** ያውቃል። ስለሆነም ***ከእናንተ አንዱ ዲያብሎስ ነው ብሎ 6፥70*** የአስቆሮቱ ይሁዳ ወደፊት ስለሚያደርገው መግለጹ ነው።

***6፥65 ከአብ የተሰጠው ካልሆነ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም።*** ምልክትን አይተው ጌታን ይከተሉ የነበሩት ብዙዎቹ ከእርሱ ጋር አልጸኑም። ምንም ምልክት ሳያዩ የሚያምኑም አሉ። በኢየሱስ የሚያምኑ ከአብ ለኢየሱስ የተሰጡ ናቸው። ቀደም ሲልም በ6:37 እና 6:44 ይህንን ተናግሯል። ከዚህም በኋላ ***ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ 6፥66።*** ወደ ኋላ የሚመለሱት የራሳቸውን ምርጫ አደረጉ።

***6፥67 እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?*** ይህ የጌታ አጠያየቅ ብዙዎች እየሄዱ ነው፡- እናንተስ ምንድነው ሀሳባችሁ? ምርጫው የእናንተ ነው እንደማለት ነው። ወደ ኋላ የተመለሱ ብዙ ናቸው፤ ከቀሩትም ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ገና ጥሎ የሚሄድ (ያውም አሳልፎ የሚሰጠው) አለ። ኢየሱስን ለመከተል ሰው የራሱን ምርጫና ፈቃድ እንደሚያደርግ ሁሉ ሳለመቀጠል (ወደ ኋላ ለመመለስ) ሊመርጥ ይችላል። ስለምርጫው ግን ተጠያቂ ይሆናል።

***6፥68-69 ጴጥሮስ፡- ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ! አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ አምነናል፣ አውቀናል*** በማለት መለሰለት። ይህ ትክክለኛ መረዳትና ምርጫ ነው። ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ስለ ተረዳ ሊከተለው ወሰነ። በሌላም ቦታ «አቅም አንሶት» ነው እንጂ ሊከተሰው በራሱ ቁርጥ ውሳኔ አድርጓል።

***ወደ ማን እንሄዳለን?*** የሚለው የጴጥሮስ ንግግርና ምርጫ ለእኛም ነው። ጴጥሮስ ***አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፣ እኛም አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል፤ አውቀናልም 6:68፣*** አለ። በእርሱ እናምናለን የምንል ሁሉ የእርሱን ማንነት በትክክል በመገንዘብ ከእርሱ ጋር መጽናት አለብን። በዚህ ዘመን ሰው የዘላለም ሕይወት የሚያገኝበትን መንገድ የሚያሳዩ አስመስለው ራሳቸውን የሚያቀርቡ ብዙ ሰዎችና ሃይማኖቶች አሉ። ሆኖም ከጌታ ኢየሱስ ሌላ ማንም የዘላለም ሕይወትን ሊሰጥ የሚችል፤ ወደ እግዚአብሔርም የሚያደርስ መንገድ እንደሌለ ልንገነዘብ ይገባል።

***6፥70-71 ከእናንተ አንዱ ዲያብሎስ ነው ... አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ አለውና።*** የአስቆሮቱ ይሁዳ የደቀ መዝሙርነት ወይም ሐዋርያነት ምርጫ/ጥሪ ደርሶታል። እንደ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ከጌታ ጋር አብሮ ሆኗል። እንዲያውም የገንዘብ መያዝ ኃላፊነት ሁሉ ተሰጥቶታል። ሆኖም በ13፡2 እና 27 ላይ እንደተመለከተው ዲያብሎስ በአስቆሮቱ ይሁዳ ውስጥ ኢየሱስን አሳልፎ የመስጠትን ሀሳብ አስቀመጠ። ስለዚህ ይሁዳ የዲያብሎስን ሀሳብ ወሰደ፤ ለዲያብሎስም ታዘዘ። ስለዚህ በዲያብሎስ ቁጥጥር ሥር ሆነ። ለሁሉም ሰው ምርጫንና ዕድልን መስጠት የጌታን አሠራርና ትዕግሥት ያሳያል። እያንዳንዱ ሰው የራሱን መንገድ እንዲወስን ምርጫ አለው። ከጌታ ምርጫ ጋር ተስማምቶ በመኖር እስከ መጨረሻ የሚዘልቅ ያ ሰው የዘላለም ሕይወትን ያገኛል።



# ምዕራፍ ሰባት

በዚህ ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ በበዓል ላይ በመገኘት የእግዚአብሔርን መልካምነት ያስተምራል፤ የአይሁድ አለቆች እርሱን ማሳደድ ቀጥለዋል።

***7:1 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለ ነበር በይሁዳ ሊመላለስ አይወድም ነበርና በገሊላ ይመላለስ ነበር።*** ኢየሩሳሌም የሚገኘው በይሁዳ አውራጃ ነው። በዚያ የነበሩ አይሁድ ኢየሱስን ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር (5፥58)። ***የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር 7:2።*** ኢየሱስ በዚህ ሰዓት በይሁዳ ለመገኘት ስላልወደደ ከዚያ ርቆ በገሊላ ቆየ። ***እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ 7፥8*** እንደሚል የሚሞትበት ጊዜ ገና ስላልደረሰ ወደ ይሁዳ ለመሄድ አልወደደም። ጊዜው በደረሰ ጊዜ ግን ራሱ ወደዚያ ለመሄድ ተነሣ። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በሞቱ ለሰው ልጆች ደኅንነት ለመስጠት ቢሆንም እግዚአብሔር ካዘጋጀለት ጊዜ በፊት ግን ለመሞት አልወደደም።

ከዚህ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ (የተሰጠንን ሥራ) ማከናወን ብቻ ሳይሆን ከጊዜው በፊት አለመቅደምና በጊዜው ማድረግም አስፈላጊ እንደሆነ እንማራለን። ለክርስቲያን አንዱ ከባድ የሕይወት ፈተና የእግዚአብሔርን ጊዜ በትዕግሥት ሆኖ መጠባበቅ ነው። እንዲህ ሲሆን ጌታ ***እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ 7፥8*** እንዳለውና ወደ ይሁዳ መሄድ እንዳልወደደው ጊዜያቸው እስኪደርስ ድረስ ከአንዳንድ ሁኔታዎች መሸሽ ያስፈልጋል (ማቴ 2:13)፤ ጊዜው ሲደርስ ደግሞ ወደ ሁኔታው ለመቅረብ መውደድም ይገባል (ሐዋ 21፡13)። እግዚአብሔር እንዲሸሽ እየፈለገ «ይጠብቀኛል» በማለት ያለጊዜው ቢቀርብ እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። እንግዲህ አስተዋይ ሰው ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር ይስማማ ዘንድ ስለ ምሪት እርሱን ይጠይቃል፤ በጊዜውም ያደርጋል።

***7፥2 የአይሁድም የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር።*** ይህ በዓል የሚከበረው በመስከረም ወር አካባቢ ምርት በሚሰበሰብበት ወይን በሚለቀምበት ጊዜ ነው (ዘጸ 23፥16፤ ዘሌ 23፥43)። በዚህ ጊዜ እስራኤላዊ ወንድ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በዳስ ውስጥ ለአንድ ሳምንት በማሳለፍ

*6፥67 እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?* ይህ የጌታ እጠያየቅ ብዙዎች እየሄዱ ነው፡- እናንተስ ምንድነው ሀሳባችሁ? ምርጫው የእናንተ ነው እንደማለት ነው። ወደ ኋላ የተመለሱ ብዙ ናቸው፤ ከቀሩትም ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ገና ጥሎ የሚሄድ (ያውም አሳልፎ የሚሰጠው) አለ። ኢየሱስን ለመከተል ሰው የራሱን ምርጫና ፈቃድ እንደሚያደርግ ሁሉ ሳለመቀጠል (ወደ ኋላ ለመመለስ) ሊመርጥ ይችላል። ስለምርጫው ግን ተጠያቂ ይሆናል።

*6፥68-69 ጴጥሮስ፡- ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እምነናል፣ አውቀናል* በማለት መለሰለት። ይህ ትክክለኛ መረዳትና ምርጫ ነው። ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ስለ ተረዳ ሊከተለው ወሰነ። በሌላም ቦታ «አቅም አንሶት» ነው እንጂ ሊከተለው በራሱ ቁርጥ ውሳኔ አድርጓል።

*ወደ ማን እንሄዳለን?* የሚለው የጴጥሮስ ንግግርና ምርጫ ለእኛም ነው። ጴጥሮስ *አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፣ እኛም አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እምነናል፤ አውቀናልም 6:68፣* አለ። በእርሱ እናምናለን የምንል ሁሉ የእርሱን ማንነት በትክክል በመገንዘብ ከእርሱ ጋር መጽናት አለብን። በዚህ ዘመን ሰው የዘላለም ሕይወት የሚያገኝበትን መንገድ የሚያሳዩ አስመስለው ራሳቸውን የሚያቀርቡ ብዙ ሰዎችና ሃይማኖቶች አሉ። ሆኖም ከጌታ ኢየሱስ ሌላ ማንም የዘላለም ሕይወትን ሊሰጥ የሚችል፤ ወደ እግዚአብሔርም የሚያደርስ መንገድ እንደሌለ ልንገነዘብ ይገባል።

*6፥70-71 ከእናንተ አንዱ ዲያብሎስ ነው ... አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ አለውና።* የአስቆሮቱ ይሁዳ የደቀ መዝሙርነት ወይም ሐዋርያነት ምርጫ/ጥሪ ደርሶታል። እንደ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ከጌታ ጋር አብሮ ሆኗል። እንዲያውም የገንዘብ መያዝ ኃላፊነት ሁሉ ተሰጥቶታል። ሆኖም በ13፡2 እና 27 ላይ እንደተመለከተው ዲያብሎስ በአስቆሮቱ ይሁዳ ውስጥ ኢየሱስን አሳልፎ የመስጠትን ሀሳብ አስቀመጠ። ስለዚህ ይሁዳ የዲያብሎስን ሀሳብ ወስደ፤ ለዲያብሎስም ታዘዘ። ስለዚህ በዲያብሎስ ቁጥጥር ሥር ሆነ። ለሁሉም ሰው ምርጫንና ዕድልን መስጠቱ የጌታን አሠራርና ትዕግሥት ያሳያል። እያንዳንዱ ሰው የራሱን መንገድ እንዲወስን ምርጫ አለው። ከጌታ ምርጫ ጋር ተስማምቶ በመኖር እስከ መጨረሻ የሚዘልቅ ያ ሰው የዘላለም ሕይወትን ያገኛል።



# ምዕራፍ ሰባት

በዚህ ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ በበዓል ላይ በመገኘት የእግዚአብሔርን መልካምነት ያስተምራል፤ የአይሁድ አለቆች እርሱን ማሳደድ ቀጥለዋል።

*7:1 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለ ነበር በይሁዳ ሊመላለስ አይወድም ነበርና በገሊላ ይመላለስ ነበር።* ኢየሩሳሌም የሚገኘው በይሁዳ አውራጃ ነው። በዚያ የነበሩ አይሁድ ኢየሱስን ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር (5፥58)። *የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር 7:2።* ኢየሱስ በዚህ ሰዓት በይሁዳ ለመገኘት ስላልወደደ ከዚያ ርቆ በገሊላ ቆየ። *እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ 7፥8* እንደሚል የሚሞትበት ጊዜ ገና ስላልደረሰ ወደ ይሁዳ ለመሄድ አልወደደም። ጊዜው በደረሰ ጊዜ ግን ራሱ ወደዚያ ለመሄድ ተነሣ። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በሞቱ ለሰው ልጆች ደኅንነት ለመስጠት ቢሆንም እግዚአብሔር ካዘጋጀለት ጊዜ በፊት ግን ለመሞት አልወደደም።

ከዚህ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ (የተሰጠንን ሥራ) ማከናወን ብቻ ሳይሆን ከጊዜው በፊት አለመቅደምና በጊዜው ማድረግም አስፈላጊ እንደሆነ እንማራለን። ለክርስቲያን አንዱ ከባድ የሕይወት ፈተና የእግዚአብሔርን ጊዜ በትዕግሥት ሆኖ መጠባበቅ ነው። እንዲህ ሊሆን ጌታ *እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ 7፥8* እንዳለውና ወደ ይሁዳ መሄድ እንዳልወደደው ጊዜያቸው እስኪደርስ ድረስ ከአንዳንድ ሁኔታዎች መሸሽ ያስፈልጋል (ማቴ 2:13)፤ ጊዜው ሲደርስ ደግሞ ወደ ሁኔታው ለመቅረብ መውደድም ይገባል (ሐዋ 21:13)። እግዚአብሔር እንዲሸሽ እየፈለገ «ይጠብቀኛል» በማለት ያለጊዜው ቢቀርብ እግዚአብሔርን መፈታተን ነው። እንግዲህ አስተዋይ ሰው ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር ይስማማ ዘንድ ስለ ምሪት እርሱን ይጠይቃል፤ በጊዜውም ያደርጋል።

*7፥2 የአይሁድም የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር።* ይህ በዓል የሚከበረው በመስከረም ወር አካባቢ ምርት በሚሰበሰብበት ወይን በሚለቀምበት ጊዜ ነው (ዘጸ 23፥16፤ በዘሌ 23፥43)። በዚህ ጊዜ እስራኤላዊ ወንድ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በዳስ ውስጥ ለአንድ ሳምንት በማሳለፍ

ከግብጽ ሲወጡ በምድረ በዳ የሄዱባቸውን ጊዜያት ያስባሉ:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በአሳት አምድ አንደመራቸው መብራትን በማብራት፤ በምድረ በዳ ውኃ አንደሰጣቸው በድንጋይም ላይ ውኃ በማፍሰስ ያስቡታል::

***7፥3-5 ወንድሞቹም፡- ደቀ መዛሙርትህ ደግሞ የምታደርገውን ሥራ እንዲያዩ ከዚህ ተነሣና ወደ ይሁዳ ሂድ፤ ራሱ ሊገለጥ እየፈለገ በስውር የሚሠራ የለምና:: እነዚህን ብታደርግ ራስህን ለዓለም ግለጥ አሉት:: ወንድሞቹ ስንኳ አላመኑበት ነበርና::*** እነዚህ ወንድሞቹ እነማን ናቸው?[33] ከደቀ መዛሙርቱ የተለዩ ናቸው:: ምክንያቱም ወንድሞቹ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ይናገሩ ነበርና ከደቀ መዛሙርቱ ሌላ መሆናቸውን ያሳየናል:: በሌላ ቦታ ማር 3፥21፤ 31-35 ስለ ወንድሞቹ ተገልጿል:: እንደገናም «እናቱና ወንድሞቹ መጡ» (ማር 3፥31) እንዲሁም «ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር» (ሐዋ 1፥14) ይላል:: በሌላም ቦታ አይሁድ «ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞችስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እህቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን?» (ማቴ 13፥55) በማለት ይናገራሉ::

እነዚህ የጌታ ወንድሞች በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ያመኑ አልነበሩም:: እንዲያውም ***ራስህን ለዓለም ግለጥ*** እያሉ ይሳለቁበት ነበር:: ሆኖም ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስ ወንድሙ ለሆነው ለያዕቆብ ታየ (1ቆሮ 15፡7)፤ ያዕቆብም በኢየሩሳሌም የነበረች ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበረ (ሐዋ 15፥13)::

***7፥6 ጊዜዬ ገና አልደረሰም፥ ጊዜያችሁ ግን ዘወትር የተመች ነው::*** ጌታ ስለ ጊዜ በተደጋጋሚ ተናግሮአል:: (2፡4፤ 7፡30፤ 8፡20):: ጊዜዬ አልደረሰም ሲል ሰሞት አልፌ የምሰጥበት ሰዓት ገና ነው ማለቱ ነው:: ጌታ የሚያደርገውን የሚያደርገው በእግዚአብሔር ፈቃድና ጊዜ እንጂ በሰዎች ግፊት አይደለም:: ወንድሞቹም እንኳን ***ራስህን ግለጥ*** ባሉት ጊዜ እነርሱ እንዳሉት አላደረገም:: የእግዚአብሔርን ጊዜ ይጠብቃል:: አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል ***እርሱ ወዴት ነው?***

[33] ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞች ነበሩት? ወይስ አልነበሩትም? የሚል ክርክር አልፎ አልፎ ይሰማል:: «አሉት» ብሎ መናገር የእናቱን የማርያምን ክብር እንደሚያጎድፍ ተደርጎም ይቆጠራል:: በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፍ «ከተጻፈው አትለፍ» ይላል:: እዚህ ላይ ትልቁ ቁም ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ማርያም በድንግልና የጸነሰችው፤ በድንግልናም የወለደችው ልጇ መሆኑን ማወቅና ማመኑ ላይ ነው:: ኢየሱስ የዓለም አዳኝና መድኀኒት የሆነው ከድንግል ስለተወለደ ነው:: ትውልድ ሁሉ ብፅዕት የሚላት፤ ከሴቶች መካከል የተባረከችው የጌታችን እናት ማርያም ከሴቶች ሁሉ የተለየች ናት::



***እያሉ በበዓሉ ይፈልጉት ነበር:: 7፥11::*** እርሱም ይህን አውቆ ተሰወረ:: የኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜ አጠቃቀም በአብ በለጠው «የጊዜ ሰሌዳ» መሠረት ነበር::

በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚመላለስ ሰው ጊዜው የሚወሰነው በእግዚአብሔር ነውና:: የእግዚአብሔርን ጊዜ ይጠብቃል:: በራሱ ፈቃድ የሚኖር ሰው ግን የፈለገውን በፈለገው ጊዜ ለማድረግ ለራሱ ምርጫ የተተወ ሰው ነው:: ስለሆነም ***ጊዜያችሁ ግን ዘወትር የተመች ነው 7፥6*** ይላቸዋል::

ጊዜ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ትልቅ ሀብት ነው:: ጊዜን በእግዚአብሔር ፈቃድ መጠቀም ደግሞ ዘመንን መዋጀት ነው:: ይህን ትልቅ ሀብት በአግባቡ ልንጠቀምበት ያስፈልጋል (ዘጸ 20፥8-11፤ ኤፌ 5፥15-21፤ ፊል 4፥4-9፤ ቆላ 4:2፣ 5-6):: በእግዚአብሔር ምሪት ውስጥ ለመሄድ የሚወድ ሰው የሚሄድበትን አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን የሚንቀሳቀስበትን ፍጥነትም ከእግዚአብሔር ጋር በማስማማት የሚያደርግ ነው::

***7፥7 ዓለም እናንተን እንዲጠላ አይቻለውም፤ እኔ ግን ሥራው ክፉ መሆኑን እመሰክርበታለሁና እኔን ይጠላኛል::*** በጨለማ የሚኖሩትን የሚጠላቸው አይኖርም:: ምክንያቱም የሚጠላው (ጠይው) እና የሚጠላው (ተጠይው) ሁለቱም ከዓለም (ከጨለማ) ናቸውና:: በሌላ በኩል ዓለም (ጨለማ) ብርሃንን ይጠላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ስለሆነ ጨለማን ይገልጣል (3፥19-21):: መጽሐፍ «በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ» (2ጢሞ 3:12) ይላል:: እዚህ ላይ ኃይለ ቃሉ «እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ» የሚለው ነው:: የእግዚአብሔርን ብርሃን እያበሩ ለመኖር የሚወዱ በተግባራቸው ጨለማውን (ክፉን ሥራ) ይገልጣሉ:: ክፉ የሚሠሩት ደግሞ ሥራቸው ሲገለጥባቸው አይወዱም፤ ስለዚህም ያሳድዷቸዋል:: በመሆኑም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ በዓለም እንደሚጠላ ማወቅ አለበት (15:18-25)::

***7፥10 በዚያን ጊዜ እርሱ ደግሞ በግልጥ ሳይሆን ተሰውሮ ወጣ::*** ወንድሞቹ ***ራስህን ለዓለም ግለጥ 7፥4*** ብለው የተናገሩት በግልጥ እንዲታይ ነው:: ለዚህም ***ጊዜዬ ገና አልደረሰም 7:6*** ብሎ ነበር:: ሆኖም ኢየሱስ ***ተሰውሮ ወጣ 7፥10::*** ስለሆነም ***ጊዜዬ ገና አልደረሰም*** ሲላቸው በግልጥ ለመውጣት አሁን ጊዜው አይደለም ማለቱ ነው እንጂ ከነጭራሹ በዚህ ጊዜ ወደ በዓሉ አልወጣም ማለቱ አልነበረም::

***7፡12 በሕዝብም መካከል ስለ እርሱ ብዙ ማንጎራጎር ነበረ፡-*** በበዓሉ ላይ የተገኙ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተለያየ አስተሳሰብ ነበራቸው፡፡ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ይሉ የነበረውን በ7፥10-41 ባለው ክፍል እንደሚከተለው እናያለን፡፡

- ደግ ሰው ነው ቁ.12
- ሕዝቡን ያስታል ቁ.12
- ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል? ቁ.15
- ጋኔን አለበት ቁ.20
- ምልክት የሚያደርግ ቁ.31
- ነቢዩ ቁ.40
- ክርስቶስ ቁ.41 የሚሉ ነበሩ፡፡

እነዚህ እርስ በርስ የሚቃረኑ አመለካከቶች ስለ አንዱ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጡ ናቸው፡፡ ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ስለ ጌታ ማንነት ትክክለኛ መረዳት የነበራቸው ቢሆን እንኳን ***አይሁድን ስለ ፈሩ ማንም ስለ እርሱ በግልጥ አይናገርም ነበር 7፥13፡፡***

***7፥15 ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል? ብለው ይደነቁ ነበር፡፡*** መጻሕፍትን የማወቂያው አንዱ መንገድ መማር ነው፡፡ መማር ያስፈልጋል ይገባልም፡፡ አይሁድን ያስደነቃቸው ኢየሱስ ክርስቶስ እነርሱ ወደሚያውቁት ትምህርት ቤት ሳይሄድ ይህን ሁሉ እውቀት ማግኘቱ ነው፡፡ ሌላ አስተማሪም እንዳለ አልተገነዘቡም፡፡ እርሱ ግን ***ትምህርቴስ ከላከኝ ነው 7፥16*** በማለት መለሰላቸው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ያስተምራል፡፡

ሰው ሁሉ (ክርስቲያን) የእግዚአብሔርን ቃል ቢያጠና እንዲሁም ከአስተማሪዎች ሥር ቁጭ ብሎ ቢማር ተገቢ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን አንድ ሰው ትምህርት ቤት ገብቶ ካልተማረ በስተቀር ምንም አያውቅም ወይም የተማረ አይሆንም ማለት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መንገድ ያስተምረዋልና፡፡ ጳውሎስ በገማልያል እግር ሥር የተማረ ሲቅ ነበር፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስ «የተማሩ አልነበሩም» (ሐዋ 4፡13)፡፡

ጌታ ***ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም 7፥16*** ሲል በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነትም ይገልጻል፡፡ አብ የሚያውቀውን ወልድም ያውቃል፡፡ ከአብ የተላከ ስለሆነ የአብ የሆነው ሁሉ የእርሱ ነው፡፡ ስለዚህ ከአብ የማይመጣ የራሱ የሆነ ትምህርት የለውም፡፡



***7፥18 ከራሱ የሚናገር የራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ግን እርሱ እውነተኛ ነው፡፡*** ኢየሱስ ክርስቶስ ለራሱ ክብር አልመጣም፡፡ የመጣው አብን ሊያከብር ነው፡፡ አብን የሚያከብረውም የአብን ፈቃድ ሲያደርግ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ሊያከብር የሚወድ ሰው ፈቃዱን የሚያውቅ ብቻ ሳይሆን ለመታዘዝም የተዘጋጀ ሰው መሆን አለበት፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቁ አንድና የመጀመሪያ ደረጃ ነው፡፡ የተረዳውን ያንን ፈቃድ ለማድረግ መፈለጉና ማድረጉ ሁለተኛ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ ለማድረግ የማይወድም ይኖራልና (ሉቃ 12፡47)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ለማክበር የመጣ ስለሆነ የአብን ፈቃድ ያወቀ ያንንም ፈቃድ ለማድረግ የተጋ ነበር፡፡

***7፥19 ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ከእናንተ ግን ሕግን የሚያደርግ አንድ ስንኳ የለም፡፡ ልትገድሉኝ ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?*** በሙሴ ሕግ «አትግደል» (ዘጸ 20፥13) የሚል አለ፡፡ የሙሴን ሕግ እንጠብቃለን እያሉ አይሁድ ኢየሱስን ሊገድሉት ተዘጋጅተዋል፡፡ ስለሆነም ሕግን አታደርጉም ይላቸዋል፤

***7፥23 የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰንበት መገረዝን የሚቀበል ከሆነስ ሰውን ሁለንተናውን በሰንበት ጤናማ[34] ስላደረግሁ ትቆጡኛላችሁን?*** በሙሴ ሕግ መሠረት አንድ ሕፃን ከተወለደ በስምንተኛው ቀን ከሥጋው ሸለፈት ሊገረዝ ይገባዋል (ዘሌ 12፥3)፡፡ ሕፃኑ ከተወለደ ስምንተኛው ቀን በሰንበት ዕለት የሚውል ከሆነ ቀኑ ሰንበትም እንኳን ቢሆን ይገርዙት ነበር፡፡ ጌታ እዚህ ላይ እንደሚገልጠው ይህን በማድረጋቸው ሰንበትን እንዲቀድሱ የተሰጠውን ሕግ መተላለፋቸው አልነበረም፡፡ እንግዲህ አይሁድ በሰንበት ቀን መግረዛቸውን ሰንበትን መጣስ አድርገው ካልቆጠሩት፣ በሰንበት ሰውን ሙሉ ጤነኛ ማድረጉ ምን ያህል ትክክል በሆነ? ስለዚህ ***ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ 7፥24*** አላቸው፡፡

***7፥27 ነገር ግን ይህ ከወዴት እንደሆነ እውቀናል፤ ክርስቶስ ሲመጣ ግን ከወዴት እንደሆነ ማንም አያውቅም፡፡*** ኢየሱስ ክርስቶስ ከወዴት እንደሆነ አይሁድ በእርግጠኛነት ያወቁ መሰሏቸዋል፡፡ እነርሱ በአፈ ታሪክ ይነገር የነበረውን «መሲሕ ሲመጣ ከወዴት እንደሆነ አይታወቅም» የሚለውን ይዘው መሆን አለበት፡፡ መጽሐፍ ግን የሚመሰክረው መሲሑ ሲመጣ የሚታወቅ እንደሆነ ነው (ሚል. 5፥2)፡፡ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠበቀው መሲሕ እንደሆነና

[34] የሰውን ሁለንተና ጤናማ ማድረግ የኢየሱስ ክርስቶስን የመፍጠር ወይም እንደገና የመሥራት ኃይል ያሳያል፡፡

ከእግዚአብሔር እንደ መጣ፤ ከድንግል እንደ ተወለደ፤ ለእረኞች እንደተገለጠላቸው፣ የሰገልም ሰዎች ከምሥራቅ መጥተው እንደ ሰገዱለት፣ እንዲሁም የእርሱን መምጣት ሲጠባበቁ የነበሩ ነቢያት ስምዖንና ሐና ሕፃኑ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ የሚጠበቀው መሲሕ እርሱ እንደሆነ እንደተናገሩ (ሉቃ 2:25-36) ሲናገሩ እነዚህ ግን አልተገነዘቡም:: ስለዚህ በማያውቁት ነገር እርግጠኞች ሆኑ:: ጌታ ግን:-

*7+28-29 እኔንም ታውቁኛላችሁ ከወዴትም እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፤ እኔ በራሴ አልመጣሁም ነገር ግን እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው፤ እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ ብሎ ጮኸ::* እነርሱ *ከወዴት እንደሆነ ማንም አያውቅም 7:27* የሚሉት መሲሁ ከወዴት እንደሆነ ኢየሱስ ከአብ ዘንድ መምጣቱን ሲነግራቸው *ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና* በማለት ነው:: አይሁድ ያላወቁትና ለማወቅም ያልፈለጉት ነገር ኢየሱስ ከሰማይ ከአብ ዘንድ እንደመጣ ነው::

*7+30 ሊይዙት ይፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አልጫነበትም::* ኢየሱስን ሊይዙት ከፈለጉ ቆይተዋል፤ *ጊዜው ገና ስላልደረሰ* እስከ አሁን የማንም እጅ በእርሱ ላይ ሊያርፍ አልቻለም:: ወደፊት የሚይዙበት ጊዜ ይመጣል:- የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ (ሉቃ 22:53)::

*7+31 ከሕዝቡ ግን ብዙዎች አመኑበትና:-* እርሱን ከመከተል ወደ ኋላ የተመለሱ ነበሩ (6:66):: የሚቃወሙትና ሊገድሉት የተዘጋጁም አሉ:: እንዲሁም በእርሱ የሚያምኑ ነበሩ:: እውነት እየተገለጠ ሲመጣ ሰዎች እውነተኛው ማንነታቸው ይገለጣል፤ በሰዎች መካከል መለያየትም ይሆናል::

*7+33-34 ኢየሱስም ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ወደ ላከኝም እሄዳለሁ:: ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም፤ እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አለ::* ጌታ ወደፊት ስለሚሆነው ሞቱ መናገሩ ነበር:: *ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝም* ሲል ለንስሐ ጊዜ ተሰጥቶአችኋል ጊዜውም ያልፍባችኋል ለማለት ይመስላል:: ይህንን በቀጥታ በመተርጐም ወደሌላ ሥፍራ ስለመሄድ የተናገረ መስሎአቸው ኢየሱስን ሊይዙት የመጡት የፈሪሳውያን ሎሌዎች:- *እኛ እንዳናገኘው ይህ ወዴት ይሄድ ዘንድ አለው? በግሪክ ሰዎች መካከል ተበትነው እንደሚኖሩት ሊሄድና የግሪክን ሰዎች ሊያስተምር አለውን? 7+35* አሉ:: ጌታ የተናገረው ስለ ሞቱ ነው:: በዚያን ዘመን ብዙ አይሁድ



ከሀገራቸው ወጥተው በግሪክ አገር ተበትነው ይኖሩ ነበር:: ስለዚህ ኢየሱስ ግን ወደዚያ በመሄድ ግሪኮችን የሚያስተምር መሰላቸው::

*7+37 ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን:-* ይህ የበዓሉ መጨረሻ ስምንተኛ ቀን ነው:: የዳስ በዓል ሲጠናቀቅ እግዚአብሔር አባቶቻቸውን እንዴት እንደመራና እንደጠበቀ በማሰብ አይሁድ በዓል የሚያደርጉበት ታላቅ ቀን ነው:: በምድረ በዳ መና እንደመገባቸው፣ ድንጋዩንም መትቶ ውኃ እንዳፈለቀ (ዘጸ 17፥1-7) የሚያስቡበት ቀን ነው:: በዚህ ጊዜ ነበር ጌታ ኢየሱስ በስምንተኛው ቀን ተነስቶ ቆሞ:- *ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ 7+37* ብሎ የተናገረው::

*7+38 በእኔ የሚያምን: መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል::* በመሲሑ በኩል ሕይወት የሚሰጥ በረከት እንደሚመጣ በኢሳ 12፥2-3፣ 44፥3-4፣ 58፥11 ላይ ተገልጧል:: *ይህ በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ 7:39* ነው:: ይህም ለሚያምኑት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጥ ሲናገር ኢየሱስ እርሱ መሲሑ እንደሆነ መግለጹ ነው:: መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ ነውና::

*7+39 ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና::* ይህ የሚፈልቀው የሕይወት ውኃ ወንዝ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው:: መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ የሚኖር ሕይወትን የሚሰጥ ነው:: ይህ በአማኞች ውስጥ የሚኖረው *መንፈስ ገና አልወረደም* ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የሚወርደው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ፤ ከተነሣና ከዐረገ በኋላ ነበርና::

*7+40-41 ይህ በእውነት ነቢዩ ነው ... ክርስቶስ ነው ... ክርስቶስ በእውኑ ከገሊላ ይመጣልን?* አሁንም በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ:: እያንዳንዱ ያወቀውን፤ የገመተውን እንዲሁም አውቃለሁ ብሎ የሚያስበውን ይናገራል::

*ክርስቶስ ከዳዊት ዘር፤ ዳዊትም ከነበረባት መንደር ከቤተ ልሔም እንዲመጣ መጽሐፍ አላለምን? 7:42* እያሉ የተጻፈውን እናውቃለን የሚሉ፤ መጻሕፍትን በማስረጃነት የሚጠቅሱና ትርጉሙም እንዲህ ነው ብለው የሚናገሩ ሰዎች እጥፍ ስህተተኞች ናቸው:: ምክንያቱም:-

- የተጻፈውን እናውቃለን የሚሉ የተጻፈውን ግን ያላስተዋሉ በመሆናቸው ነው::

* የተጻፈውን ሁሉ እናውቃለን ብለው ስለሚያስቡ ሌላ እውነት የለም በማለታቸው::

***መጽሐፍ አላለምን?*** የሚሉት መሲሑ ከዳዊት ዘር መሆኑንና ከቤተ ልሔም እንደሚሆን እውነት ነው:: ኢየሱስ የዳዊት ልጅ ነው (ማቴ 1÷2-28፤ ሮሜ 1÷3-4):: የተወለደው በቤተ ልሔም ነው (ማቴ 2÷1-6፤ ሉቃ 2÷1-11):: እንዲሁም መዝ 89÷3-4፣ 132÷11፤ ኢሳ 9÷6-7፣ 11÷1፣ ሚኪ 5÷2 ይመልከቱ:: ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም ከተወለደ በኋላ ወደ ግብፅ ተሰደደ:: ከዚያም የዮሴፍና የማርያም ከተማ በሆነው በገሊላ ናዝሬት አደገ (ማቴ 2÷12-13):: ከዚያ በኋላ የይሁዳው ኢየሱስ ወይም የቤተ ልሔሙ ኢየሱስ ሳይሆን የገሊላው ሰው ወይም የናዝሬቱ ኢየሱስ እየተባለ ይታወቃል (ማቴ 2:23፤ ማር 10:47፤ ዮሐ 1:45):: ስለሆነም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጻሕፍት የነበራቸው መረዳት ከፊል ነው:: ራሳቸው ስተው ሌሎችንም ያስቱ ነበር:: አስተማሪዎች እጥፍ ፍርድ አለባቸው (ያዕ 3:1) ሲል ይህን ያስገነዝባል::

ይህም ሁሉ ተደርጐ በኢየሱስ ማንነት ያመኑ ወይም ሊከተሉ የሚወዱ ሰዎች ነበሩ:: ***ከእርሱ የተነሣ በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ 7፥43::*** ይህም አይሁድ ሲያደርጉ የፈለጉትን በሙሉ ልባቸው እንዲያደርጉ አላስቻላቸውም::

***7፥47 እናንተ ደግሞ ሳታችሁን?*** ይህን የሚናገሩት ፈሪሳውያን ናቸው:: አለቆችም ፈሪሳውያንም እንዲይዙት ሎሌዎችን ወደ ኢየሱስ ልከው ነበር:: እነዚህ ሎሌዎች ኢየሱስ የሚናገረውን ከሰሙ በኋላ ኢየሱስን ሳይዙት: ***ወደ ካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን መጡ 7፥45***: በመደነቅም ***እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም ብለው መለሱ 7፥46***: በዚህ አመላለሳቸው ፈሪሳውያን ተቆጥተው ***ከአለቆች ወይም ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለን? 7፥48*** በማለት ይጠይቋቸዋል:: ይህም ማለት እናንተ ሎሌዎች ሆናችሁ ስለ እርሱ ንግግር እንዴት ታደንቃላችሁ እስቲ ከእኛ ከአለቆችና ፈሪሳውያን የእርሱን ትምህርት የተከተለና በእርሱ ያመነ ማንን አይታችኋል? ማለታቸው ነው::

በኢየሱስ ያመኑ ነበሩና ፈሪሳውያን ስለ እነርሱ:- ***ሕግን የማያውቀው ይህ ሕዝብ ርጉም ነው 7፥49*** አሉ:: ***ርጉም*** የሆኑትስ ሕግን እናውቃለን እያሉ ሕግ የሚያመለክተውን ኢየሱስን ያላመኑ፣ ትክክል ያደረጉትን ሰዎች ደግሞ እየረገሙ ያሉ እነርሱ መሆናቸውን አላስተዋሉም (5:38-40)::



***7፥51 ሕጋችን አስቀድሞ ከእርሱ ሳይሰማ ምንስ እንዳደረገ ሳያውቅ በሰው ይፈርዳልን? አላቸው::*** እነዚህ ፈሪሳውያን ሕዝቡ ሕግን አያውቅም ሲሉ (7÷49) ራሳቸው ያወጡትን ሕግ እንኳ ራሳቸውም እንደማያከብሩት ይገልጻል:: ይህ ከመናገር (ከመወሰን) በፊት መስማት እንደሚያስፈልግ የሚናገረው ሕግ የተመሠረተው ደግሞ በዘዳግ 1÷16 ነው:: በዚህ ሕግ መሠረት በማንም ሰው ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት መጀመሪያ ሰውዬው እንዲጠየቅና መልስ እንዲሰጥ አግባብ መሆኑን የሚገልጽ ነው::

ይህን መልስ ለፈሪሳውያን የመለሰው ከእነርሱ አንዱ የሆነው ኒቆዲሞስ ነው:: ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ጌታ የመጣ ፈሪሳዊ አለቃ ነበረ (3÷1-21):: ከፈሪሳውያን መካከል ሆኖ በድብቅ የሚያምን ሰው ነበረ 7:50-52:: ጌታም ከሞተ በኋላ ኒቆዲሞስ መቶ ኪሎ ግራም ያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል አምጥቶ እንደ አይሁድ አገናነዝ ባሕል ከሽቱ ጋር ደባልቆ በተልባ እግር የከፈነው ሰው ነው( 19÷39-40)::

ኒቆዲሞስ በሰጠው አስተያየት ፈሪሳውያን:- ***አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነቢይ ከገሊላ እንዳይነሣ መርምርና እይ አሉት 7፥52::*** ፈሪሳውያን መጻሕፍትን ማለትም ብሉይ ኪዳንን በመንተራስ ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሕ እንዳልሆነ ለማሳየት ጥረት አድርገዋል:: የሚያቀርቡትም አንዱ ምክንያት፣ ኢየሱስ ከገሊላ ከሆነ፣ ከገሊላ መሲሕ እንደማይመጣ መጻሕፍት ይመሰክራሉ ብለው ነው::[35] እነዚህ መጻሕፍትን እየጠቀሱ የሚናገሩ ሰዎች መጽሐፍ ራሱ ስህተት ስለ መሆናቸው ይመሰክርባቸዋል:: ምክንያቱም:-

ኢየሱስ የተወለደው በዳዊት ከተማ በቤተ ልሔም ነበረ (ሉቃ 2÷4-11፤ ሚክ 5÷2)::

መጻሕፍት ከገሊላ ስለሚመጣ መሲሕ ይናገራል:: በኢሳ 9÷1-2 ባለው ክፍል «ነገር ግን ተጨንቃ ለነበረች ጨለማ አይሆንም፣ በመጀመሪያው ዘመን የዛብሎንንና የንፍታሌምን ምድር አቃለለ፤ በኋለኛው ዘመን ግን በዮርዳኖስ ማዶ በባሕር መንገድ ያለውን የአሕዛብን ገሊላ ያከብራል:: በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው» ይላል:: በዚህ ገሊላ እንደሚከበር ብርሃንም

---

[35] ከዚህ ቀደም ነቢያት ለምሳሌ ዮናስ (2ነገ 14:25)፤ ኤልያስ (1ነገ 17:11) ከገሊላ እንደነበሩ የታሪክ (መልክዓ ምድር) አጥኚዎች ይናገራሉ::

እንደሚወጣለት ተናግሯል። ይህም በማቴ 4፡13-16 ተጠቅሷል። በገሊላና በአካባቢው እንዴት ለሚሰው «ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናልና። ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» (ኢሳ 9:6) ሲል ያ የሚመጣው ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሑ እንደሆነ ይመሰክራል።

ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለማስር ፈልገው የላኳቸው ሎሌዎች ሳይቀር በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ተማረኩ። በመካከላቸውም በኢየሱስ ያመነ ኒቆዲሞስ ነበረ። ከፈሪሳውያን መካከልም ሳይቀር በእርሱ ለማመን የሚፈልጉና ልባቸውን የከፈቱ ብርሃን የበራላቸው ነበሩ።



# ምዕራፍ ስምንት

***8:3 ጻፎችና ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ።*** ሕግ አናውቃለን የሚሉ እነዚህ የሕግ አስተማሪዎች በመሠረቱ በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ ሲያመጡ ሰውዬውንም አብረው ይዘው ባመጡት ነበረ።የሰውዬውን ኃጢአት እንደ ኃጢአት አልቆጠሩትም!!! ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመጧት እርሱን ለማጥመድ ነበረ። እነዚህ ስለማመንዘር ኃጢአት ሴትዮዋን ሲከሱ ራሳቸው ደግሞ ያሰባቸውን ኃጢአት አልተመለከቱም። ሌላው ደግሞ መጽሐፍ እንደሚል አንዱን ሕግ የተላለፈ ሌላውን ተላልፏል (ያዕ 2:10)። ከኃጢአት የሚበልጠው ትልቁ ኃጢአት ደግሞ መሲሑን አለመቀበላቸውና ሊገድሉት መፈለጋቸው ነው።

***8፥5 አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ?*** በሙሴ ሕግ መሠረት በምንዝርና የተገኘ ሰው ተወግሮ ይገደል ይላል። ሲያመነዝሩ የተገኙት ሁለቱም ይገደላሉ (ዘሌ 20፡10፤ ዘዳ 22፡22-24)። ፈሪሳውያን ኢየሱስን ሲያጠምዱት የመጡት ሴትዮዋን «አትግደል« ቢል የሙሴን ሕግ ተላልፈሃል ለማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ «ግደሏት» ቢል ምናልባትም ለሮም ገዥዎች የሮምን ሕግ ተላልፎ ሰው እንድንገድል አዘዘን በማለት ሊከሱት ነው። አይሁድ ማንንም እንዲገድሉ አልተፈቀደላቸውምና (18፡31)። ከዚህ የተነሣ አይሁድ ዘንድ ኢየሱስ ከሁለት አንዱን ይወስናል በሚወስነው በዚያም እናጠምደዋለን ብለው ተዘጋጅተው ነበረ።

***8፥6 ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ።*** በምድር ላይ የጻፈው ምናልባት እነርሱ እንዲያነቡት ይሆናል። ምክንያቱም ***መላልሰው በጠየቁት ጊዜ 8፥6*** ይላልና ለመጻፍም ጥቂት ጊዜ እንደወሰደ ይመስላል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምን ይሆን የጻፈው? ምናልባት ሴትዮዋን የከሰሱትን ሰዎች ስም ዝርዝርና በስማቸው አንጻር የእያንዳንዳቸውን ኃጢአት ይሆንን? ምናልባትም የማመንዘር ኃጢአታቸውን ይሆንን? ሊሆን ይችላል (ኤር 17:13)!!!

***8፥7 ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት፡-*** ባላቸው ጊዜ ከሳሾቹ ለመውገር አልደፈሩም። ጌታ በሰጠው መልስ ወጋሪዎቹ አስቀድመው ራሳቸውን እንዲመረምሩ አደረገ እንጂ ሕጉን

አልጣለም፣ አትወገርም አላለምና። እንዲሁም ትወገርም ብሎ ትእዛዝ አልሰጣቸውም። የሴትዮዋን ሥራ አልተቀበለውም፤ አላጸደቃትም። የከሳሾቹዋን ልብ ግን መረመረ።

***8፥8 ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ።*** ከዚህ በኋላ ከጌታ ጋር ለመነጋገር እንኳ አልደፈሩም። ምክንያቱም ***ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞቹ አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ 8፥9***፡ አካሄዳቸውም በመጀመሪያ ትልቁ/ ሽማግሌው ከዚያ በቅደም ተከተል ነበር። ምናልባትስ ሽማግሌዎቹ የበለጠ ኃጢአተኛ ቢሆኑስ? እንግዲህ ይህችን ሴት ያመጧት ጻፎችና ፈሪሳውያን ራሳቸው ከኃጢአት ነጻ አለመሆናቸውን ደፍረው በኢየሱስ ፊት መግለጽ አልቻሉም። ስለዚህ ከሳሾቹ ሁሉ ጥለዋት ሄዱ።

***8፥11 እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከእሁንም ጀምረሽ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።*** ***ደግመሽ*** የሚለው አሁን የሰራሽው ኃጢአት ነው ከአሁን ወዲያ ወደፊት በእንዲህ ዓይነት ኃጢአት አትገኚ፤ አሁን ግን እኔ ምሕረት አድርጌልሻለሁ ሲል ነው። ጌታ ይህችን ሴት በድንጋይ ከመወገር አዳናት። እንዲሁም ከዚያም ከሚበልጠው ከኃጢአቷ አዳናት።

ኃጢአት ፍርድ ያስፈልገዋል። ጌታ በሰጠው መልስ ለሴትዮዋ ኃጢአተኛነቷን ነግሯታል። ሁላችሁም ኃጢአት አለባችሁና እርሱዋን ተዋትም አላለም። የከሳሾቹን ትክክለኛ ማንነት ግን ገለጠባቸው። በሰው የሚፈርድ ሰው ራሱን መመርመር ይኖርበታል። በሌላው ላይ ለመፍረድ የሚነሣ እርሱ በኃጢአት ውስጥ የሚገኝ እንዳይሆን ስለ ራሱ መጠንቀቅ አለበት። ያለዚያ የሁሉ ዳኛ የሆነው እግዚአብሔር የጽድቅ ፍርዱን ያሰጣል።

***8፥12 እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም።*** ብርሃን የእግዚአብሔርን ቅድስና ያመለክታል (መዝ 27:1፤ 36:9፤ ሐዋ 9:3፤ 1ዮሐ 1፥5)። እንዲሁም ብርሃን መንፈሳዊ መረዳትን ይሰጣል፣ ለሰዎች እግዚአብሔርን ያሳያል። ሕይወትና ብርሃን የተያያዙ ናቸው። ጌታ ኢየሱስ ***እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ*** ሲል ለአይሁድ ብቻ ያልሆነ ለአሕዛብም ብርሃን እንደሚሆን በኢሳ 1፥16 ቀደም ሲል ተነግሯል። ጨለማ በኃጢአት መኖርን ሲያመለክት ከዚህ ጨለማ በመውጣት በብርሃን ለመመላለስ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መቅረብን ያመለክታል። እርሱን የሚከተል በብርሃን ይሄዳል።



***8፥13 ፈሪሳውያንም፦ አንተ ስለ ራስህ ትመሰክራለህ፤ ምስክርነትህ እውነት አይደለም አሉት።*** ይህን ሲሉ አይሁድ ቀደም ሲል በ5:31 እንደተገለጠውና በዘዳ 19:15 እንደተጻፈው ሁለት ወይም ሦስት ምስክር ማስፈለጉን መናገራቸው ነበረ። ያላስተዋሉት ነገር የኢየሱስን ማንነት ነው። እርሱም ***እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴት እንድሄድ አታውቁም አላቸው 8፥14***፡ እንዳላቸው የማያውቁት ብዙ ነገር እያለ ያወቁ መስሏቸው በማያውቁት ላይ ፍርድ ይሰጣሉ። እርሱ ከአብ እንደወጣ አላወቁም።

***8፥15 እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ፦*** ቀደም ሲል ጌታ ለእነዚህ ሰዎች ***ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ 7፥24*** ብሏቸው ነበረ። አሁንም ያንኑ እንደገና ይነግራቸዋል። ***ሥጋዊ ፍርድ*** በሥጋዊ ዓይን በታየው ላይ ተመሥርቶ ብቻ መበየን ነው። ይህ «ሰው እንደሚያይ እግዚአብሔር አያይም» (1ሳሙ 16:7) የሚለውን ቃል ያሳስበናል።

***8፥16 የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው።*** ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ለመፍረድ ሳይሆን ለማዳን ቢሆንም የእርሱ የራሱ ወደ ምድር መምጣት ግን ፍርድን ግድ ይላል። ምክንያቱም እርሱን የማይቀበል ለፍርድ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷልና። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም ሲመጣ የፈራጅነት ሥልጣኑን ትቷል ማለት አይደለም። እርሱ የሰው ልጅ ነውና እንዲፈርድ ሥልጣን ከአባቱ ተሰጥቶታል (5:28)።

***8፥17-18 የሁለት ሰዎችም ምስክርነት እውነት እንደሆነ በሕጋችሁ ተጽፎአል። ስለ ራሴ የምመሰክር እኔ ነኝ፥ የላከኝም አብ ስለ እኔ ይመሰክራል።*** በዚህም አነጋገሩ ጌታ ሕጋቸውን (እንዲሁም ስለ ምስክር የብሉይ ኪዳኑን ሕግ) መሻሩ አይደለም። እንዲያውም ስለ እኔ የሚመሰክሩት ***እኔ ... የላከኝም አብ*** ማለትም ሁለታችንም ነን ማለት ነው። ልጁ የመጣው ከአብ ዘንድ ነው (8:14)፤ በአብ ነው የተላከው (8:16-17)። «አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታወቁ ዘንድ» (10:38)፤ እንዲሁም «አንተ አባት ሆይ አንተ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ» (17:21) እንዳለ የላከው አብ ደግሞ አብሮ ከወልድ ጋር መጥቷልና ስለ እርሱ ይመሰክራል።

***7:19 አባትህ ወዴት ነው?*** ብለው ለጠየቁት ***እኔንም ወይም አባቴንም አታወቁም፤ እኔንስ ብታወቁኝ አባቴንስ ደግሞ ባወቃችሁ ነበር 8፥19***

ብሎ ይመልስላቸዋል:: የሚያዩትን ኢየሱስን ለማወቅ ባመፈለጋቸው የማያዩትን አብን ሊያወቁት አይችሉም:: ኢየሱስን ቢያውቁት ኖሮ አብንም ባወቁት ነበር::

***8፥20 ጌታ ይህን ያስተማረው በመቅደስ ግምጃ ቤት[36] አጠገብ ነበረ::*** ይህ ቦታ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን የምድረ በዳ ጉዞ የሳከውን የእሳት ዓምድ ለማመልከት (ዘጸ 13፥21-22) ትልልቅ መብራቶች ወይም መቅረዞች የሚገኙበት ቦታ ነበርና ስለ ብርሃን አስተማረ (8:12):: የእሳት ዓምድ በምድረ በዳ የእግዚአብሔርን መገኘት ጥበቃውንና ምሪቱን ያመለክት ነበር::

***8፥21 እኔ እሄዳለሁ ትፈልጉኛላችሁም በኃጢአታችሁም ትሞታላችሁ፤ እኔ ወደምሄድበትም እናንተ ልትመጡ አትችሉም::*** እንዲህ ዓይነት ንግግር ጌታ ቀደም ሲልም በ7፥31 ላይ እና 33-35 ባለው ተናግሯቸው ነበር:: መሲሑን በመጠበቅና በመፈለግ ላይ ናቸው:: መሲሑ ግን መጥቷል እየተናገራቸውም ነው:: ከሄደ በኋላ ሊያገኙት አይችሉም:: በእርሱ ሳላላመኑ በኃጢአታቸው ይሞታሉ:: ከሞቱና ትንሣኤ በኋላ እርሱ የሚሄደው ወደ አባቱ ነውና በእርሱ ያላመኑ ከእርሱ ጋር ሊሆኑ አይችሉም::

***8፥22 እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም ማለቱ ራሱን ይገድላልን? እንጃ አሉ::*** ከዚህ ቀደም ***ወደ ግሪኮችም ሄዶ ያስተምራል 7፥34-36*** ብለው ነበር:: አሁን ደግሞ ***ራሱን ይገድላልን?*** አሉ:: የሚናገራቸው ሊገባቸው አልቻለም:: ምክንያቱም ***እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም 7:23*** አላቸው:: እንደነዚህ ሰዎች ከታች (ከምድር) የሆነ መንፈሳዊ ምሥጢርን ሊረዳ አይችልም (ዮሐ 3፥6፤ 1ቆሮ 2፥11-15)::

***8፥24 እኔ እንደ ሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው::*** እኔ የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለሙሴ ሲገለጥለት «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ»[37] ብሎ ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለመቀበል ባለመፈለጋቸው እነዚህ ሰዎች በራሳቸው ላይ የመንፈሳዊ ሞት ፍርድ መፍረዳቸው ማለትም በኃጢአታቸው መሞታቸው ነው::

***8፥26 ስለ እናንተ የምናገረው የምፈርደውም ብዙ ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን የላከኝ እውነተኛ ነው፤ እኔም ከእርሱ የሰማሁትን ይህን ለዓለም እናገራለሁ::*** ስለ እነርሱ ብዙ የፍርድ ቃል ያልተናገረው አብ እንዲናገር የሰጠውን ብቻ ስለተናገረ ነው:: ቃሉም ***እውነተኛ*** ነው:: የሚናገረውም ስእነርሱ ስአይሁድ ብቻ ሳይሆን ***ለዓለም*** ሁሉ ነው::

***8፥27 ስለ አብ እንደ ነገራቸው አላስተዋሉም::*** እነዚህ አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ እንደ መጣ፤ በአብ እንደ ተላከ ለማመን ፈቃደኞች ስላልሆኑ የሚናገራቸውን ሁሉ ሊያስተውሉ አልቻሉም:: የላከው አብ ከእርሱ ጋር መጥቷል (8፡16፤29)፤ ስለዚህ በራሱ ምንም አያደርግም (8፡28፤42)::

***8፥28 የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ::*** በዚያን ዘመን በነበረው አነጋገር ***ከፍ ከፍ*** ማድረግ የሚያመለክተው በመስቀል መሞቱን ነው:: ***ታውቃላችሁ*** የሚለው ደግሞ ኢየሱስን በመስቀል ላይ ከገደሉት በኋላ ያን ጊዜ ያምናሉ ማለት ሳይሆን እርሱ ከአብ የተላከ መሆኑ ይረጋገጣል ማለት ነው::

***8፥31 በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ::*** በኢየሱስ የማመን አንዱ ምልክት ለእርሱ መታዘዝ ነው:: ጌታም በእርሱ ላመኑት አይሁድ ሲናገር የእርሱ ደቀ መዛሙርት የመሆናቸው ምልክት በቃሉ ከኖሩ ወይም ቃሉን በመታዘዛቸው መሆኑን ነው:: ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች እንደምናየው አንዳንዶቹ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሆነው አልቀጠሉም:: ኢየሱስን ለመከተል በእርሱ ማመን ብቻ ሳይሆን በእርሱ ማመን የሚያስከትለውን ዋጋ አብሮ ለመክፈል መተመን አስፈላጊ ነው (ሉቃ 14፡23-25)::

በቃሉ መኖር ከሁሉ አስቀድሞ በእርሱ ማመንና ከእርሱ ጋር መጣበቅን ያመለክታል:: የእርሱ ደቀ መዝሙር ደግሞ ኢየሱስን በማወቅ ያድጋል:: እርሱ እውነት ነው፤ እርሱ ሰዎችን ከኃጢአት እስራት ነፃ ያወጣል (1:17፤ 8፡34፤ 14፡6):: ስለዚህ ለእርሱ መኖር ከእርሱ ጋር ተጣብቆ መቆየትንና መዝለቅን ያመለክታል::

---

[36] This area was part of the Court of Women (a court in the temple where women were permitted to go). This court held thirteen trumpet-shaped containers for collecting various dues and offerings-seven of the boxes were for the temple tax; the other six were for freewill offerings. LEBC Ibid. p.175

[37] The I Am መለኮትነትን ይገልጻል (ዘጸ 3፥14፤ ዘዳ 32፥39፤ ኢሳ 43፥10)::

***8፥32 እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል።*** እውነትን ማወቅ እግዚአብሔር ለሰው የገለጠውን ማወቅ ነው። እግዚአብሔር ለሰው የገለጠው ትልቁ መገለጥ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው። ስለዚህ እውነትን ማወቅ ማለት ኢየሱስን ማወቅ ነው። እርሱንም ማወቅ ከኃጢአት ነፃ የሚያወጣው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ መረዳት (መቀበል)ና ለእርሱ መታዘዝ ነው። ይህ ከኃጢአትና ከሞት መንፈሳዊ (እውነተኛ) ነፃነትን ይሰጣል።

ትልቁ ***አርነት*** መውጣት የኃጢአት ባሪያ ከመሆን ነው። ***አርነት*** መውጣት ማለት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ነፃ የሆነ ሰው መሆን፣ ለማድረግም የሚችል ሰው መሆን ማለት ነው። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ይገኛል። አርነቱ ከኃጢአት ሲሆን ነፃነቱ ደግሞ የጽድቅ ነው።

***እውነትም አርነት ያወጣችኋል 8፥32*** ያለውን ***ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ 8፥36*** ይላል። እዚህ ላይ ***ልጁ*** እና ***እውነት*** የሚሉት በተመሳሳይ ሁኔታ አርነት እንደሚያወጡ ተገልጧል። ስለሆነም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት እስራት ነፃነትን የሚሰጥ እውነት ነው። ስለዚህ ለሰው ልጅ እውነተኛ ነፃነት የሚጀምረው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከኃጢአት እስራት በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቅ ነው። ልጁ አርነት ያወጣው ደግሞ ከኃጢአት ነፃ ወጥቷልና የኢየሱስ ክርስቶስን ፈቃድ የሚያገለግል የእርሱ ባሪያ ይሆናል ማለት ነው። የእውነት መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ስለሚኖር ወደ እውነት ሁሉ ይመራል (16፥13)።

***8፥33 የአብርሃም ዘር ነን ለአንድም ስንኳ ከቶ ባሪዎች አልሆንም አንተ፡- አርነት ትወጣላችሁ እንዴት ትላለህ? አሉት።*** እንደ አይሁድ አስተሳሰብ «አርነት ትወጣላችሁ» መባላቸው ማንነታቸውን ወይም ክብራቸውን የሚነካ ነገር አድርገው ነው የቆጠሩት። ጌታ የነገራቸው ግን እውነት የሆነውን ነበር - በኃጢአት ባርነት ሥር ነበሩና።

በዚህ ዘመን አይሁድ (ከነዓን) በሮማውያን ቅኝ ግዛት ውስጥ የነበሩ ቢሆንም የራሳቸው የውስጥ አስተዳደር (ነፃነት) ስለ ነበራቸው ባርነት የሚለውን አልተረዱም። ከሁሉም በላይ አብርሃም ጻድቅ ሰው ስለ ነበረና የእርሱ ጽድቅ ለልጆቹ ለእስራኤላውያን ሁሉ እንደ ሆነ አድርገው ያስቡም ስለ ነበረ ከባርነት አርነት መውጣት የሚለው ሊገባቸው አልቻለም። ከአብርሃምም የተነሣ «መንፈሳዊ ኩራትም» ነበረባቸው። እነርሱ ያሰቡት ባርነት የሥጋ ነው፣ ጌታ የሚነግራቸው ከነፍስ (መንፈሳዊ) ባርነት ነፃ ስለ መውጣት ነው። ነፃ የሚወጡት



ከኃጢአት ነው። ምክንያቱም፣ ***ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው 8፥34።***

***8፥35 ባሪያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘለዓለም ይኖራል።*** አይሁድ ***የአብርሃም ዘር ነን 8:33*** ማለታቸው የአብርሃም ጽድቅ ለእኛም ነው ማለታቸው ነበረ። እነርሱ ያላስተዋሉት ነገር ግን በትውልድ ሐረግ ከአብርሃም ዘር ቢሆኑም የአብርሃም ጽድቅ ወደ እነርሱ አለመውረዱን ነበር። እነዚህ አይሁድ አብ በላከው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላላመኑ የእግዚአብሔር ልጆች አልሆኑም ባሪያዎች እንጂ፡- የኃጢአት ባሪያዎች። የአብርሃም ዘር ወይም የእርሱ ልጆች ነን ማለት የሚችሉት በጽደቅ (በእምነት) ልጆቹ ሲሆኑ ነበር። እነርሱ ግን የኃጢአት ባሪያዎች ሆነዋል። ስለዚህ ***ለዘላለም በቤት*** አይኖሩም፤ በውጭ ናቸው።

***8፥37 የአብርሃም ዘር መሆናችሁንስ አውቃለሁ ነገር ግን ቃሌ በእናንተ ስለማይኖር ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ።*** በዘር ሐረግ የአብርሃም ዘር ናቸው፤ በጽድቅ ግን ኢየሱስን ለመግደል የተነሳሡ ስለሆነ የአብርሃም ዓይነት ጽድቅ በእነርሱ ውስጥ የለም። እነርሱ የአብርሃም ልጆች ቢሆኑ ኖሮ የአብርሃም ልጅ የሆነውን ኢየሱስን (ገላ 3፡16) ሊገድሉት ባልተዘጋጁም ነበር።

***8፥36 ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።*** ከኃጢአት እስራት ነፃ መውጣት የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ «በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና» (ገላ 3፡26) እንዲሁም «እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ» (ገላ 3፡29) ይላል። እንግዲህ የአብርሃም ዘር መሆን የሚችሉት በመንፈሳዊ አገላለጽ የክርስቶስ ቢሆኑ ነበረ። ክርስቶስን ሳይቀበሉ የአብርሃም ዘር (በሥጋ) ቢሆኑ አይበቃም።

***8፥38 እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤ እናንተ ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።*** አይሁድ የአብርሃም ልጆች ነን (8፡33) ይላሉ። ጌታ ደግሞ የሰይጣን ልጆች ናችሁ ይላቸዋል። ***አባታችሁ*** የሚለው ሰይጣንን ነው። ምክንያቱም ጌታን ሊገድሉት በመፈለጋቸው። ሰይጣን ***ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ 8:44*** ነውና የእርሱን ባሕርይ በመያዛቸው የእርሱ ልጆች መሆናቸው ነው። የሰይጣን ልጆች መሆናቸውን ተግባራቸው ይገልጻል። በዘር የአብርሃም

ልጆች መሆናቸውን ቢቀጥሉም በተግባራቸው ግን የዲያብሎስ ልጆች እንደሆኑ ጌታ አስረግጦ ይነግራቸዋል።

*8፥39 የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር።* የአብርሃም ልጆች መሆናቸውን በተግባር አሳሳዩም። አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ ታዘዘም (ዘፍ 12፥1-4፣ 15፥16፣ 22፥1-4)። የእግዚአብሔርን መልእክተኞች ተቀበለ (ዘፍ 18፥1-8)። አይሁድ ግን ከእግዚአብሔር በተላከው አላመኑም፤ አልተቀበሉትምም።

*8፥40 ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም።* የአብርሃም ልጆች አለመሆናቸው አብርሃም ከሠራው ጽድቅ የተለየ እነርሱ ሰውን ለመግደል መፈለጋቸውና መዘጋጀታቸው ነው። አብርሃም የእግዚአብሔርን መልእክተኞች ተቀበለ። እነዚህ ግን ከእግዚአብሔር የሰማውንና እውነት የሚናገራቸውን ሰው ሊገድሉ ፈለጉ። እዚህ ላይ ጌታ ኢየሱስ ራሱን *ሰው* ብሎ መጥራቱን ልብ ማለት ይጠቅማል። እርሱ ፍፁም ሰው ነው። ስለሆነም ጌታ፡- *እናንተ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ አላቸው 8፥41*። የአይሁድ መልስ ግን *እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም አንድ አባት አለን እርሱም እግዚአብሔር ነው አሉት 8፥41*። ይህ አባባላቸው እኛ እንደ ሰማርያውያን አልተቀየጥንም፤ የአብርሃም ልጆች ነበርን እስካሁንም ልጆች ነን ማለታቸው ይሆናል።

*8፥42 እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና።* እነዚህን አይሁድ ጌታ በተደጋጋሚ የሚላቸው እናንተ ይመስላችኋል እንጂ የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም ነው። በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች ብትሆኑ ኖሮ እኔ ደግሞ ከእግዚአብሔር የተላክሁ ነኝና እኔንም በወደዳችሁኝ ነበር። እኔን ልትቀበሉኝ ያልቻላችሁት የእናንተ አባት እግዚአብሔር ስላልሆነ ነው ማለት ነው። ዝም ብሎ መከራከር ነው እንጂ ይህን ሁሉ ካለ በኋላ አልገባቸውም።

*8፥43 ንግግሬን የማታስተውሉ ስለ ምንድን ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው* በማለት ይነግራቸዋል። እነርሱ ንግግሩን ሊሰሙ የማይፈልጉት አስቀድመው እርሱን ለመግደል ድምዳሜ ላይ ስለ ደረሱና አእምሮአቸውን ስለዘጉ ነው።



*8፥44 እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ።* ጌታን ሊገድሉት እንዲፈልጉ ይህን ሀሳብ የሰጣቸው ገዳይ የሆነው ዲያብሎስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል ያነሳሣ ዲያብሎስ ነው (6፡70-71፣ 13፥27)። መጽሐፍ «ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና። ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (1ዮሐ 3፡8) ይላል። ኃጢአትን ማድረግ ደግሞ የዲያብሎስ ሥራ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የዲያብሎስን ሥራ ይገልጣል።

የእነዚህ ሰዎች ሀሳብ እና መነሣሣት ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል ነው። ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው። ዲያብሎስ የእውነት ገዳይ ነው። አስቀድሞ እውነትን ገድሎ ሀሰት ያደርገዋል። ከዚያም ሰውን ይገድላል።

አይሁድ *አባታችን እግዚአብሔር ነው 8፥41* ይላሉ። ነገር ግን በተግባራቸው የዲያብሎስ ልጆች ሆነዋል። እርሱ ሀሳባቸውን ገዝቶታል፤ ውሸትን አስተምሮአቸዋል። ሕግን ለመፈጸም የተዘጋጁ አስመስሎ በመጽሐፍ የተጠላውን ሰውን ለመግደል ተዘጋጅተዋል። ስለዚህ ሰይጣን ሀሳቡን ለማድረግ የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ሆነዋል።

*8፥46 ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?* ሰይጣን «የእፍ መፍቻ ቋንቋው» ሀሰት እንደሆነ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ደግሞ ሁልጊዜ እውነትን ይናገራል። እርሱ ኃጢአትን አላደረገምና ማንም «ይህን ኃጢአት አድርገሃል» ብሎ የሚናገረው አልነበረም። እርሱ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ መሆኑን በዚህም አሳይቷል። እውነትን ይናገራል፤ እነርሱ ግን ሊቀበሉት አልወደዱም፤ ልባቸውን አደንድነዋልና (12፡39-40)። ይህም የእግዚአብሔር ልጆች አለመሆናቸውን ያመለክታል። ከዚህ በኋላ አይሁድ በቀጥታ ጌታን ይሳደቡ ጀመር።

*8፥48 ሳምራዊ እንደ ሆንህ ጋኔንም እንዳለብህ በማለታችን እኛ መልካም እንል የለምን? አሉት።* አይሁድ ራሳቸውን የአብርሃም ዘር አድርገው ሲቆጥሩ ሳምራውያን ግን ከሌላ ዘር ጋር በጋብቻ የተደባለቁ በመሆናቸው ንፁህ እንዳልሆኑ ይቆጥሩአቸው ነበር። ጌታን በዚህ አጠራር *ሳምራዊ ነህ* ይሉታል - የተናቀ ሰው ለማለት። እንዲሁም ጋኔን አለብህ በማለት በተደጋጋሚ ሰደቡት (7፡20፣ 8፡52፣ 10፡20)።

*8፥49 ጌታም መለሰ፡- እኔ ጋኔን የለብኝም፤ ነገር ግን አባቴን አከብራለሁ እናንተም ታዋርዱኛላችሁ አለ።* ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜ

አብን ያከብራል:: እነርሱ ግን እንዲህ ያለውን ሰው ጋኔን አለብህ በማለታቸው ምን ያህል ዝቅ አድርገው እንደ ገመቱት ያሳያል:: አቤት አለማወቅ!!

***8፥50 እኔ ግን የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የሚፈልግ የሚፈርድም አለ::*** አብ ለልጁ ክብር ይፈልጋል፤ ልጁን የማያከብሩትንም (የሚያዋርዱትን) ይፈርድባቸዋል (ማቴ 12:31-31))::

***8፥51 ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አያይም::*** የጌታን ቃል መጠበቅ ማለት መስማትና መታዘዝ ማለት ነው:: መታዘዝ ደግሞ በእርሱ ላይ መደገፍና ከእርሱ ጋር ተጣብቆ መኖር ማለት ነው:: እንዲህ አይነቱ ***ለዘላለም ሞትን አያይም*** ሲል በሥጋ የሚኖረውን ሞት አለመሞት ማለት ሳይሆን ሁለተኛውን (መንፈሳዊ) ሞት አይሞትም ማለት ነው::

***8፥53 በእውኑ አንተ ከሞተው ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን?*** ለእነርሱ የመጨረሻ ትልቁ ሰው አብርሃም ስለሆነ ***ከሞተው ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን?*** ብለው ይጠይቃሉ:: አብርሃም እንኳን ሞቶአል ሲሉ ነው:: ኢየሱስ ግን ለዚህ የሚሰጣቸው መልስ ***እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው:: የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው 8:54*** ይላቸዋል:: የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነው እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ያከብራል:: እነርሱ አምላካችን ይሉታል፤ ኢየሱስ ደግሞ አባቴ ይለዋል:: እንደ ሌላው ሰው «አባታችን» ብሎ አይጠራውም ***አባቴ*** ይላል እንጂ:: በአብና በወልድ መካከል ያለው አባትና ልጅነት ብቸኛ (ልዩ) ነው:: በመፈጠር ያልሆነ ከዘላለም የሆነ አባትና ልጅነት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ አንድያ ልጁ ነው::

***8:55 አላወቃችሁትም፤ እኔ ግን አውቀዋለሁ:: አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ:: ዳሩ ግን አውቀዋለሁ ቃሉንም እጠብቃለሁ::*** አይሁድ ይህን ሁሉ ክርክርና ሙግት የጀመሩት እግዚአብሔርን ባለማወቃቸው ነው:: መጻሕፍትን ያነባሉ ሆኖም ቃሉን አይጠብቁም:: ከአብ ዘንድ የመጣው ልጁ አብን ያውቀዋል፤ ቃሉንም ይጠብቃል::

***8፥56 አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ፥ አየም ደስም አለው::*** አብርሃም የአይሁድ አባት ነው:: እርሱ የጌታን መምጣት በሩቅ አየ፤ ተሳለመውም (ዕብ 11:8-13):: በዚህም አብርሃም ደስ አለው:: ***ቀኔን*** ሲል የእርሱን (የኢየሱስ ክርስቶስን) ወደ ምድር መምጣት ማለት ነው:: ይህም በሩቅ ተገልጦለታል::



በዚህ አባባሉ አይሁድ ተቆጥተው:- ***ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት 8፥57***: የእርሱን ፍጹም አምላክነት ያለመረዳታቸውን በግልጽ ያሳያል::

***8፥58 አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ***: ጌታ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም ከተወለደ እዎ ገና አምሳ ዓመት አልሞላውም:: ነገር ግን ፍጹም አምላክ የሆነው ኢየሱስ አብርሃም ሳይወለድም ከዘላለም አለ:: እዚህ ላይ ልብ እንበል:: አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርሁ አላለም፤ ***እኔ አለሁ***[38] ነው ያለው:: ኢየሱስ ክርስቶስ መጀመሪያ ስለሌለው ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ነበርኩ አይልም፤ ሁልጊዜ ስላለ ***አለሁ*** ይላል:: በእርሱ ዘንደ የኃላፊ ጊዜ የሌለው ከዘላለም ያለና የሚኖር አምላክ መሆኑን ያስገነዝባል:: እንዲሁም የእግዚአብሔር መጠሪያ የሆነው «***እኔ ነኝ***» (ዘጸ 3:14) ለኢየሱስ ክርስቶስም በቀጥታ መዋሉ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑንን ያሳያል::

***8፥59 ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ::*** በብሉይ ኪዳን ሕግ እግዚአብሔርን የሰደበ በድንጋይ ይወገራልና (ዘሌ 24:16) ሕግን የሰጣቸውን ***ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ::*** እቤት አለማስተዋል!!! የሄደው በመካከላቸው አልፎ ነው:: በመካከላቸው ሲያልፍ ግን ***ተሰወራቸው***: እግዚአብሔር ደብቀው ወይም እንዳያዩት ሆነ ማለት ነው::

[38] <Before Abraham was born, I am!> NIV.

# ምዕራፍ ዘጠኝ

በዚህ ምዕራፍ ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የነበረውን ሰው ኢየሱስ ሲፈውስ እንመለከታለን:: በእርሱ መፈወስ መነሻነት ጌታ ስለ መንፈሳዊ ዕውርነትና እርሱ የዓለም ብርሃን እንደሆነ ሲያስተምር እናያለን::

ጌታ ኢየሱስ በአንድ አካባቢ ከሚታይ ነገር ወይም ሁኔታ ተነስቶ ታላቅ መንፈሳዊ እውነት ያስተምር ነበር:: ለምሳሌ:- በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ የነበረችውን ሳምራዊት ሴት እርስ የሕይወት ውኃ እንደሆነ ገለጠላት (4:10):: አምስት ሺህ ሕዝብ ከመገበ በኋላ እርሱ የሕይወት እንጀራ እንደ ሆነ ተናገረ (6:35):: አይሁድ ሙሴ ድንጋዩን መትቶ ውኃ ያወጣበትን በሚያስታውሱበት የዳስ በዓል ላይ በመገኘት ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ ብሎ አስተማረ (7:35):: እንዲሁም አይሁድ እግዚአብሔር በምድረ በዳ በእሳት ዓምድ የመራቸውን ያበራላቸውን በሚያስታውሱበት በዓል ላይ ላይ ተገኝቶ:- እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ እኔንም የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም አለ (8:12)::

በተመሳሳይ መንገድ በዚህ ምዕራፍ እንደምናየው ዕውር ለሆነው ሰው ብርሃን ሲሰጠው የዓለም ብርሃን ነኝ ብሎ ተናገረ (9:5):: ይህ የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዕውር ለሆኑ የሥጋ ዓይኖች ብርሃን መስጠት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ዕውርነትን አስወግዶ በብርሃን እንድንመላለስ የሚያደርግ ጌታ ነው:: በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ መንፈሳዊ ብርሃን ያላቸው ናቸው::

***9፥1 ሲያልፍም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ::*** በሌላ ቦታ እንደምናየው ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ እንደሚያልፍ ስላወቀ የጠየቀውና የዳዊት ልጅ ማረኝ ብሎ የጮኸው ዕውሩ በርጤሜዎስ ነበር (ማር 10:46-52):: በዚህ ሁኔታ ደግሞ ዕውሩን ያየውና የጠየቀው ኢየሱስ ነው:: ጌታ ሁሉንም ሰው፤ እርሱን ማየት የማይችሉትንም ያያቸዋል::

9:2 ***ደቀ መዛሙርቱ:- መምህር ሆይ፥ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራው ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ? ብለው ጠየቁት::*** ደቀ መዛሙርቱ ይህን ጥያቄ ያነሡት በሽታ ከኃጢአት ወይም ከእርግማን እንደሚመጣ የሚናገረውን የመጽሐፍ ክፍል (ዘጸ 15:26) በማስታወስ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን በብሉይ ኪዳንም በሚገባ እንደምናስተውለው ሁሉም ሕመም ወይም በሽታ ከአመፀኛነት ወይም ከኃጢአተኝነት የሚመጣ እንዳይደለ የኢዮብ ሕይወት ለዚህ ምሳሌ ይሆናል:: ደቀ መዛሙርት ***ኃጢአት የሠራው ማን ነው?*** ብለው ሲጠይቁ ማወቅ የፈለጉት ዕውርነቱ በኃጢአት ምክንያት የመጣ ከሆነ ኃጢአት የሠራው ማን እንደሆነ ነው:: እርሱ ከሆነ ከመወለዱ በፊት ሲሆን ነው፤ ያለዚያም ወላጆቹ::

***9፥3 የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም::*** ከጌታ አመላለስ እንደምናስተውለው እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአተኞች አይደሉም አላለም:- ያለው ግን ይህ ዕውርነት በልጁ ላይ የመጣበት በእርሱ ወይም በእነርሱ ኃጢአት ምክንያት አይደለም ነው:: ይህ ግን የሆነው የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው ማለትም ለዚህ ሰው በሚሆንለት ምክንያት እግዚአብሔር እንዲከበር ነው:: ስለዚህ ጌታ የመለሰው ዕውርነቱን ምን አመጣው? ሳይሆን ለምን ዓላማ ሆነ? የሚለውን ነው::

ሰውዬው ዕውር ሆኖ የተወለደው በኃጢአት ምክንያት ለመሆኑ ፈሪሳውያን እርግጠኞች ናቸው:: ***አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወለድህ 9፥12*** ብለውታልና:: ነገር ግን በዚህ ሰው መፈወስ ምክንያት እግዚአብሔር ክብሩን ገለጠ፤ ወንጌል ተሰበከ:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእውሩን ዓይን ካበራ በኋላ የዓለም ብርሃን መሆኑንም ተናገረ::

***9:4 ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ትመጣለች::*** እዚህ ላይ ***ቀን*** የሚያመክተው ኢየሱስ በምድር እንዲሠራ የተላከበትን ጊዜ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሳለ ብርሃን በምድር ነበረ፣ ቀን ነበረ:: ***ሌሊት ትመጣለች*** እንዳለው ጌታ የሚሞትበት ጊዜ እየመጣች ነበረ፤ ያቺ ሌሊት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ[39] በምድር በአካል የማይሆንባት ጊዜ ናት::

ይህ ሥራን በትጋትና በፍጥነት የመሥራትን አስፈላጊነት ያሳየናል:: ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የተሰጠን ቀን (የተመቻቸ) ሁኔታ ይኖራል:: ወደፊት እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በምድራችን ወይም በአካባቢያችን ላይመጣ ይችላል:: ስለዚህ ዛሬ ባለው ሁኔታ የተሰጠንን ሥራ በሙሉ ኃይል መሥራትና መጨረስ ያስፈልጋል:: የተከፈተው በር ሳይዘጋ ሥራን መሥራትና «ተፈጸመ» ማለት ከጌታ የምንማረው የአገልግሎት ትጋት ነው::

[39] In His humanity

***9፥5 የዓለም ብርሃን ነኝ።*** መሲሑ ሲመጣ የዕውሩን ዓይኖች እንደሚያበራ በብሉይ ኪዳን ተነግሮ ነበር (ኢሳ 29፥11፣ 35፥5፣ 42፥7)። ኢየሱስ የዕውሩን ዓይኖች ሲያበራ እርሱ የሚጠበቀው መሲሕ እንደሆነ ያመለክታል። ዕውሩን ካበራ በኋላ ***የዓለም ብርሃን*** መሆኑን ሲገልጽ በፊታቸው ከተደረገው ምልክት ጋር የሚዛመድ ትምህርት ይሆናል- በጨለማ ላለው ብርሃንን የሚሰጥ መሆኑን ያስገነዝባል።

***9፥6-7 ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና፦ ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው።*** ኢየሱስ የዕውሩን ዓይኖች ያበራው በቀጥታ ምራቁን በመቀባት አይደለም። ምራቁን የተጠቀመው ***ጭቃ*** ለማድረግ (ለማበጀት) ነው። በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባ ከዚያም ***ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው።*** ከዚህ ሁኔታ ሁለት ነገሮችን መገንዘብ እንችላለን።

- *የመጀመሪያው፦* ዕውሩን ሂድና በሰሊሆም *መጠመቂያ ታጠብ* ሲለው ጭቃውን በዓይኑ እንዳደረገ ወደ ሰሊሆም ለመሄድ እምነትን ይጠይቃል።
- ሁለተኛው፦ *ጌታ ጭቃውን ያበጀው በሰንበት ቀን* ነበር። ይህም *ለፈሪሳውያን «ሥራ» መሆኑ* ነው። ስለዚህ ለፈሪሳውያን ስለ ሰንበት ምንነት ለማስተማር ነው።

***9፥7 ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፤ ትርጓሜውም የተላከ ነው።*** ይህ ሰው ጭቃው በዓይኖቹ እንደተደረገበት ጌታ ባዘዘው መሠረት ***ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ 9፥7***። አያየ ከመጣ በኋላ ስለዚህ ሰው ማንነት ብዙ ንግግርና የተለያየ ሀሳብ ይቀርባል። አንዳንዶቹ እርሱ ዕውር የነበረው ነው ሲሉ ሌሎችም አይደለም አሉ። ***እርሱ፦ እኔ ነኝ አለ 9፥10***። ሰዎችም ***ዓይኖችህ እንዴት ተከፈቱ? 9፥10*** ብለው ሲጠይቁት ኢየሱስ ያደረገውን ይገልጽላቸዋል።

***ሰሊሆም***[40] የግሪክ ቃል ሲሆን ሽሎም[41] ከሚል የዕብራይስጥ ቃል የመጣ ነው። ትርጓሜውም የተላከ ማለት ነው። ***ሰሊሆም*** (የተላከ) የሚለው ቃል መጠመቂያው የተሠራበትን ሁኔታ[42] የሚያሳይ ሲሆን ጌታም ወደ ***ሰሊሆም*** እንዲሄድ ሲያዘው እርሱ ከአብ ዘንድ የተላከ መሆኑንም ለማመልከት ሲሆን ይችላል።

***9፥12 ያ ሰው ወዴት ነው? ሲሉትም አላውቅም አለ።*** የተፈወሰው ሰው ማን እንዳዳነው ***አላውቅም*** ያለው ምናልባት ዓይኑ ከበራለት በኋላ ኢየሱስን ገና አላየውም ይሆናል። ከመጠመቂያው ሲመለስም ኢየሱስን አግኝቶት እንደሆነ አልተገለጸም። ስለዚህ የት እንደ ሄደ አያውቅም። ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን የተለመደ ምርመራና ጥያቄአቸውን ይቀጥላሉ።

***9፥14 ኢየሱስም ጭቃ አድርጎ ዓይኖቹን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበረ።*** ከፈሪሳውያን መካከል ይህን ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው አሁን «እንኳን ደስ ያለህ» ያለው አልነበረም። እንዲያውም ምርመራቸውን ቀጠሉ። ፈጥነውም ***አንዳንዶቹ፦ ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም አሉ 9፥16***። በፈሪሳውያን መካከል መለያየት ሆነ። ይህን ሰው በእነዚህ ዓመታት ሁሉ ማንም ስለ እርሱ ግድ ያለውና ያነጋገረው ሰው ላይኖር ይችላል። ነገር ግን አንድ ቀን ኢየሱስ ባየው ቀን ከተረሣበት ተነሣ። ታላቅ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆነ።

ጌታ በሰንበት ቀን ጭቃ ያበጀው ስለ ሰንበት ምንነት ሲያስተምራቸው ፈልጐ ይሆናል። ሰውን ሙሉ ጤናማ ማድረግ የታሰረ በሬ ወይም አህያን እንደ መፍታትና ውኃ እንደማጠጣት እንደሆነ ተናግሮ ነበርና (ሉቃ 13፡15)።

***9፥16 ኃጢአተኛ ሰው እንደ እነዚህ ያሉ ምልክቶች ሊያደርግ እንዴት ይችላል?*** የዕውርን ዓይን መክፈት በሰው ጥበብ የሚደረግ አይደለም። ይህን ያደረገው «የእግዚአብሔር ሰው» መሆን አለበት ማለታቸው ነው። እነዚህኞቹ ያሉት እውነት ነው።

***9፥17 ዕውሩን፣ አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተው ስለ እርሱ ምን ትላለህ?*** በማለት ምንነቱን ያውቅ እንደሆን ሲጠይቁት የሰውየው መልስ አጭር ነው - ***ነቢይ ነው አለ 9፥17***። ቀደም ሲል ***ኢየሱስ የሚባለው ሰው 9፡11*** ብሎ ነበር አሁን ደግሞ ያ ኢየሱስ የሚባለው ሰው ነቢይ እንደሆነ ይመሰክራል። ይህንም ሁሉ ከተነጋገሩ በኋላ፣ ***አይሁድ የዚያን ያየውን ወላጆች እስኪጠሩ ድረስ ዕውር እንደ ነበረ እንዳየም ስለ እርሱ አላመኑም፥ 9፥18***። ወላጆቹን አስጠርተው

---

[40] siloam
[41] Shiloah
[42] The pool of Siloam had been built by King Hezekiah. His workers had built an underground tunnel from the Spring of Gihon in the Kidron valley outside of Jerusalem. This tunnel channeled the water into the pool of Siloam inside the city walls.... (2Kin 20:20; 2Chr 32:30). These waters may symbolize the work that Jesus, the sent one, had come to do. They provided the deliverance and healing sent by God. LEBC Ibid. p.195.

ባነጋገሩ ጊዜ የወላጆቹ መልስ ይህ ዓይኑ የበራለት ሰው ልጃቸው እንደሆነና ዕውርም እንደ ነበረ ገለጹላቸው። እንዴት ሊያይ እንደቻለ በጠየቁዋቸው ጊዜ የወላጆቹ መልስ ***ጠይቁት እርሱ ሙሉ ሰው ነው እርሱ ስለ ራሱ ይናገራል አሉ 9፥21።*** ምክንያቱም ***ወላጆቹ አይሁድን ስለ ፈሩ ይህን አሉ 9:22።***

***9፥22 እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚመሰክር ቢኖር ከምኩራብ እንዲያወጡት አይሁድ ከዚህ በፊት ተስማምተው ነበርና።*** የልጁ ወላጆች ***ጠይቁት*** የሚለውን መልስ የሰጡት ለልጃቸው ብርሃን የሰጠው ሰው ማን እንደሆነ ስላላወቁ ሳይሆን አይሁድ ከምኩራብ እንዳያስወጡዋቸው ስለ ፈሩ ነው። ከማኅበሩ፣ ከዕድሩ መገለልን[43] በመፍራት የልጃቸውን ዓይን ያበራውን ማንነት ከመግለጽ ደበቁ። እነርሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ለመናገር ባይወዱም ሥራው ግን ይናገራል፣ ያውጃል። ማንም ሊደብቀው የማይችለው ሥራ ተሠርቷል።

እኛም ባለንበት ዘመንና አካባቢ ሁሉ እንዲህ ዓይነት ተመሳሳይ ድርጊቶች በክርስቲያን እማኞች ላይ ይፈጸማል። እውነትን ስለ ተናገሩ ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ስላሉ ከእድር እንዲገለሉ፣ ቀባሪ እንዳያገኙ ሌላም ሌላም ነገር እንዲደረጉ የሚያደርጉ አካባቢዎች አሁንም ይኖራሉ። ይህ አዲስ ነገር አይደለም። የመስደድ አንዱ መልክ ነው።

***9፥24 እግዚአብሔርን አክብር ይህ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን አሉት።*** ያን ሰው እንደገና ጠርተው ያነጋግሩታል። ***እግዚአብሔርን አክብር*** ማለታቸው እውነቱን ተናገር እንደ ማለት ነው (ኢያ 7፥19፤ ኤር 13፥16)። ጌታ ኢየሱስ ቀደም ብሎ ***ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? 8፥46*** በማለት ጠይቋቸው ማንም አልመለሰለትም ነበር። አሁን ግን ኃጢአተኛ ነው ይሉታል። ሆኖም ዕውር የነበረው ሰው ሲመልስላቸው፡- ***ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም ዕውር እንደ ነበርሁ አሁንም እንዳይ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ አለ***

[43] Jewish regulations stipulated two kinds of excommunication: one that would last for thirty days until the offender could be reconciled and one that was a permanent <ban> accompanied by a curse. Because the synagogue controlled every aspect of life (civic, recreational, legal, and religious), an individual cut off the synagogue would suffer severe isolation. ... In Jesus' day, there was alsoa kind of informal prohibition against any Jew who would confess Jesus to be the Christ. Ibid. p.198.



***9፥25***: የዚህ ሰው አመላለስ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዓይኖቻቸውን የከፈተላቸው ሰዎች የሚናገሩት ዓይነት መልስ ነው።

ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ማንነት ሙሉ ግንዛቤ ላይኖራቸው ይችላል፤ ደግሞም አይኖራቸውም። ሆኖም ያላቸው መረዳት በእነርሱ ሕይወት የተሠራውን ለመናገር ይበቃቸዋል። እነርሱ ኃጢአተኞች (ሰላም የሌላቸው) እንደ ነበሩ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበሉ በኋላ ግን በእግዚአብሔር ሰላም እንደተሞሉ፤ ዓላማ ያላቸው ሰዎች እንደ ሆኑ ይናገራሉ። በዝርዝር እንኳ ባይሆን ***ይህን አንድ ነገር*** እንደሚያውቁ ይናገራሉ። ይህም የእርሱን በጐነት መናገር ነው (1ጴጥ 2፥9-10)።

ይህን ሰው ፈሪሳውያን ደጋግመው በጠየቁት ጊዜ፡- ***ስለ ምን ዳግመኛ ልትሰሙ ትወዳላችሁ? እናንተ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ልትሆኑ ትወዳላችሁን? አላቸው 9፥27***: ዕውር በነበረው ሰው ግንዛቤ ደጋግመው መመርመራቸው ምናልባት እርሱን ለመከተል ፈልገው ይሆናል የሚል ይመስላል። እነርሱ ግን ደጋግመው የሚጠይቁት ይህን ሰው ምስክር ለማድረግ ስለፈለጉ ነው። ራሱ ተፈወስ የተባለው ሰው እንዲህ ብሏል ብለው በኢየሱስ ላይ ጥፋት ወይም በደል ለማግኘት ነበር። ሆኖም የዚህ የተፈወሰው ሰው አመላለስ እረፍት አልሰጣቸውም።

***9፥28 እኛ ግን የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን፡-*** ብለው ይመልሳሉ። እነዚህ ሰዎች ደጋግመው የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን ይላሉ (6:31-33)። ያላስተዋሉት ነገር ሙሴ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መናገሩን ነው። በእርግጥ የሙሴን መጻሕፍት የሚያነቡትና እርሱን የሚከተሉት ቢሆኑ ኖሮ ኢየሱስን ይቀበሉት ነበር። ሙሴ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስክሮአልና (5፥45-47)።

አይሁድ ይህን ሰው ደጋግመው በጠየቁት መጠን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው መረዳት እያደገ ነው የመጣው። በ9፥11 ላይ ***ኢየሱስ የሚባለው ሰው*** አለ። በ9፥17 ላይ ***ነቢይ ነው አለ።*** በ9፥32-33 ላይ ደግሞ ***ይህ ሰው ከእግዚአብሔር*** ነው አለ። ማስረጃውም ***ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይኖች ማንም እንደ ከፈተ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አልተሰማም 9:32*** የሚል ነው። በመጨረሻም በ9፥35-36 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንደሚያምን ገለጸ፤ ለኢየሱስም ***ሰገደለት***: ስለዚህ ይህ ሰው ኢየሱስን አስቀድሞ እንደ ፈዋሽ ሰው አድርጎ ከተረዳው እርሱ ስግደት የሚገባው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እስከ መግለጽ ድረስ ተናገረ። ይህን ለመግለጽ ወላጆቹ አልደፈሩም። ከአይሁድ ምኩራብ መገለልን ፈርተው ነበርና።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አንድ ሰው ሕይወት መምጣት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ ታላቅ ሰውጥ ይሆናል:: መታሰብ ይሆናል:: ዋጋም ያስከፍላል:: የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት የማይቀበሉ ደግሞ ይህን ሰው ደጋግመው መጠየቅና ማሳደድ እንደ ጀመሩ ጌታን በተቀበለ ሰው ሕይወትም ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሊመጡ ይችላሉ::

***9፥39 የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ አለ::*** የሚያዩ የሚመስላቸው እውነትን ለማየት የማይወዱ የታወሩ ናቸው፤ ተፈርዶባቸዋልና:: ይህ ሰው ግን ዓይኑ የተከፈተለት በእውነተኛው ብርሃን በኢየሱስ አመነ፤ ስለዚህ የማያይ የነበረው አየ::

***9፥35 አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው::*** ዕውር የነበረውን ሰው ይህን ጥያቄ የሚጠይቀው ኢየሱስ ራሱ ነው:: ብርሃን የሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ይህ ሰው እውቆአል:: ይህ እውቀት ግን አይበቃም:: እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ተረድቶ ሊሰግድለትም ያስፈልጋል:: ስለዚህ ጌታ ወደ ትክክለኛው መረዳት እንዲቀርብ ማንነቱን ይገልጽለታል:: በተረዳም ጊዜ ***ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ አለ ሰገደለትም 9፥38***:

ቆርነሌዎስ ለጴጥሮስ ሊሰግድለት ሲፈልግ ጴጥሮስ እንደከለከለው እናውቃለን (ሐዋ 10:25):: እንዲሁም ዮሐንስ ለመልአኩ ሊሰግድለት ሲፈልግ መልአኩ እንደከለከለው እናነባለን (ራዕ 19:10፤ 22፤8-9):: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አምላክን፤ ስግደትን የሚቀበል አምላክ ስለሆነ ይህ ሰው ሰገደለት:: ዲያብሎስ ኢየሱስን የፈተነው ወድቀህ ብትሰግድልኝ በማለት ነበር:: የጌታ ኢየሱስ መልስም ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል (ማቴ 4:10) የሚል ነበር:: ስለዚህ ስግደት ለጌታ ለእምላክ ብቻ የሚደረግ ነው:: ይህ ዕውር የነበረው ሰው ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰገደለት እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ስለተረዳ ነው::

***9፥39 የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ::*** በ3፥17 ላይ ጌታ የመጣው ለማዳን እንጂ ለፍርድ እንዳይደለ ተናግሯል:: በዚህ ቦታ ደግሞ ***ለፍርድ መጣሁ*** ይላል:: ይህ ታዲያ ይቃረናልን? አይቃረንም:: ምክንያቱም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጌታ ራሱን እየገለጸ ያለው የዓለም ብርሃን እንደሆነ ነው:: ብርሃን ደግሞ ጨለማን ይለያል:: እርሱ ብርሃን በመሆኑ ጨለማው ይለያል፤ ይታወቃልና፤ ይህ መለየት በራሱ መፍረድ ነው:: የእርሱ መምጣት የታወሩትን (ማለትም በኃጢአት ጨለማ ያሉትን) ያሳያል:: ስለሆነም



ንግግሩ የገባቸው ፈሪሳውያንም ይህን ሰምተው:- ***እኛ ደግሞ ዕውሮች ነንን? አሉት 9፥40***:

***9፥41 ዕውሮችስ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር፤ አሁን ግን:- እናያለን ትላላችሁ፤ ኃጢአታችሁ ይኖራል::*** መንፈሳዊ ዕውርነት በኃጢአት መኖር ነው:: በኃጢአት መኖር ማለት ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አለማመንና አለመቀበል ነው:: ዕውር መሆኑን ያወቀ መድኃኒት ፍለጋ ይመጣል:- ይህ ዕውር የነበረውን ሰው ጌታ ጭቃ ቀብቶ እንዲታጠብ ሲያዘው ሄዶ እንደታጠበና ብርሃንም እንዳገኘ ማለት ነው:: ነገር ግን እያለሁ ብሎ የሚያስብ ብርሃንን አይፈልግም:: በዚህ ደግሞ ዕውር መሆኑ ይታወቃል:: በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሳይሆን ከራሴ በሆነ ብርሃን አያለሁ የሚል ያ ሰው ዕውር ነው:: ምክንያቱም ***የዓለም ብርሃን 8፥12*** ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው::

# ምዕራፍ አሥር

እግዚአብሔር የሕዝቡ እረኛ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘፍ 48፥15፣ 49፥24፤ መዝ 23፥1፣ 80፡1፤ ኢሳ 40፥11፣ 53፥6፤ ኤር 31፥10፤ 1ጴጥ 2፥25)። በግና እረኝነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ በምሳሌነት ተገልጠው የምናያቸው አስረጂ ምሳሌዎች ናቸው (ለምሳሌ 2ሳሙ 5፥2፤ 1ነገ 22፥17፤ ዘካ 10፥2)። እረኝነት በእስራኤል በጣም የታወቀና ብዙ ሕዝብ የሚሠራው ሥራ ነው። የእስራኤል አባቶችም በግ ጠባቂዎች ነበሩ (ዘፍ 46፥32፣ 47፥3)።

በምዕራፍ 10፥1-21 ኢየሱስ መልካም እረኛ እንደሆነ ይናገራል። አይሁድ በቀላሉ የሚገነዘቡትን ምሳሌ በመጠቀም ኢየሱስ እርሱ እውነተኛ እረኛ መሆኑን ያስረዳቸዋል። በዚህ ስለ በግና እረኛ በቀረበው (10፡1-21) ትምህርት ምሳሌዎቹ የሚወክሉትን (የሚያሳዩትን) እንደሚከተለው ማዛመድ ይቻላል። መልካም እረኛው ክርስቶስ ነው። በጎች ከአይሁድ የሆኑ አማኞች ናቸው። በረቱም የአይሁድ እምነት ሊሆን ይችላል። በሩ የሕይወት በር የሆነው ኢየሱስ ነው። ሌሎች በጎች ከአሕዛብ የሆኑ አማኞች፤ በር ጠባቂው እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል። በቀሪው የምዕራፉ ክፍል ደግሞ የአይሁድ አለቆች ኢየሱስ ክርስቶስን በቤተ መቅደስ ሊይዙትና ሊገድሉት እንዳሰቡ እንመለከታለን።

***10፥1 ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው።*** በምሽት በጎችን ከሌቦችና ከአውሬዎችም ለመጠበቅ በረት ውስጥ ይከማቻሉ። በረቶች ብዙ ጊዜ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ የተሠሩ ዙሪያ ገብ የሆኑ አጥሮች ሲሆኑ እንደየአካባቢው ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ ዋሻዎችም ይሆናሉ። የበረቱ በር አንድ መሆኑ፣ አንድ ብቻ መሆኑ ለእረኛው በጎችን ለመጠበቅ የተሻለ ነው። አንዳንድ ጊዜ ብዙ እረኞችም ቢሆኑ በጎቻቸውን በየተራ ለመጠበቅ እንዲችሉና እረፍት እንዲያገኙ በአንድ በረት ውስጥ ያከማቿቸው ነበር።

***10፥2 በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው።*** በዚህ ክፍል በር እና ***የበጎች እረኛ*** ሁለቱም በምሳሌነት የሚያገለግሉት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ



ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የበጎች በረት በር ነው። እረኛውም እርሱ ነው። በዚህ በር የማይገባ ሁሉ ሌባ ወይም ወንበዴ ነው። በዚያን ዘመን የነበሩ ፈሪሳውያንና ጻፎች በኢየሱስ ክርስቶስ ሳያምኑ በሌላ መንገድ በጎችን ለማውጣት የሚፈልጉ ነበሩ። በበሩ በኢየሱስ በኩል አልመጡምና ወንበዴዎች ናቸው። በጎችን ለመምራት የሚፈልጉት ወደ እግዚአብሔር ጥበቃ ሳይሆን ወደ ራሳቸው ምኞትና ዓላማ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ወደ ሕይወት የምንገባበት በር ነው። ለሁልጊዜውም የሚጠብቀን እረኛችን ነው።

***10፥3 ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።*** እውነተኛው እረኛ እንደ መጣ በታወቀ ጊዜ በር የሚጠብቀው ለእረኛው በሩን ይከፍትለታል። በበረቱ ውስጥ ካሉት በጎች የእርሱ የሆኑትን እርሱ ይጠራቸዋል፤ በጎቹም እረኛቸውን በድምፁ ያውቁታል። በበረኛውና በእረኛው መካከል መተዋወቅ አለ። በረኛው እረኛውን ያውቀዋል፤ በበረኛውና በበጎች መካከልም መተዋወቅ አለ፤ በጎች የእረኛቸውን ድምፅ ያውቃሉ። በጐቹን ጠርቶ የሚወስዳቸው ለማሰማራት ነው። ይህም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ማስገባትን ያመለክታል። ጌታ በመጣ ጊዜ ከአይሁድ መካከል የእርሱን ድምፅ ለምተው የተከተሉት ነበሩ። እነዚህ በበረት ውስጥ ከነበሩት በጐች መካከል የእረኛቸውን ድምፅ ለይተው የሚከተሉት ናቸው።

***10፥4 የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል።*** በምሳሌው እንደምንረዳው በበረቱ ውስጥ ያሉ ሁሉ የእረኛውን ድምፅ ሰምተው አይከተሉትም። ድምፁን የሚያውቁት የእርሱ የሆኑት ብቻ ይከተሉታል። ጳውሎስ «ከእስራኤል የሚወለድ ሁሉ እስራኤል አይደለምና፣ የአብርሃምም ዘር ስለሆኑ ሁላቸው ልጆች አይደሉም» (ሮሜ 9፥6-8) እንዲሁም «የተስፋ ቃል ልጆች ሆነው ይቆጠራሉ እንጂ እነዚህ የሥጋ ልጆች የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም» (9፥9) እንዳለው ማለት ነው።

***10፥5 ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፥ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።*** በጎቻቸውን በአንድ በረት ውስጥ ያስቀመጡ እረኞች እየመጡ በጐቻቸውን ሲጠሩ ድምፃቸውን የሰሙ የእነርሱ በጐች ወደ እረኞቻቸው ይሄዳሉ። የክርስቶስ የሆኑ በጐች የጌታን ድምፅ ያወቁ ***ከሌላው ይሸሻሉ።*** እረኛው አንድ ብቻ ነው ሌሎች ሌቦች የሆኑ ብዙ ናቸው።

***10+7 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ::*** የዘላለም ሕይወት የሚኝበት የደኅንነት መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: በገሀዱ ዓለም የበጎች እረኛ በጎችን በአንድ ቦታ ከሰበሰበ በኋላ በአቅራቢያቸው ሆኖ ከነጣቂ፣ ከወንበዴ፣ ከሌባ፡ ይጠብቃቸዋል:: እንዲሁም በመንፈሳዊው ዓለም በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሰው ለዘላለም በእርሱ ጥበቃ ሥር ይሆናል::

***10+8 ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፡-*** እነዚህ ክርስቶስ እንደሆኑ እየተናገሩ የመጡ ወይም በራሳቸው ስም የመጡ (5፥42) ያለዚያም በዚያን ጊዜ መሪዎች ነን ብለው የሚያስቡትን ያመለክታል:: እነዚህ ስለ መንጋው ጤንነት የማያስቡ በራሳቸው ሕግ የተያዙና ስለ ራሳቸው ኑሮ የሚጨነቁ ነበሩ (ማቴ 23፥13፤ 24፥5):: እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን በር አበጅተዋል፤ እረኞቹም ራሳቸው ሆነዋል:: ጌታ ስለእንደነዚህ ዓይነቶች የሚናገረው ወደ ሕይወት የማያደርሱ ***ሌቦችና ወንበዴዎች*** ናቸው ብሎ ነው::

***10+8 ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም::*** እነዚህ ሁሉ በእረኛው ስም የሚመጡ (ሀሰተኛ ክርስቶሶች) ድምፅ አላቸው:: አስመስለው የሚናገሩ ናቸው:: ነገር ግን እውነተኛ በጎች የእረኞቻቸውን ድምፅ ስለሚያውቁ አልተከተሏቸውም::

***10+9 በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል::*** በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደኅንነት አለ:: በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነፃነት አለ፣ ተዘልሎ መቀመጥ አለ፣ መሰማርያም አለ:: በገሀዱ ዓለም እረኛው ለበጐች የሚያስፈልጋቸውን እንደሚያዘጋጅላቸው ሁሉ መልካሙ እረኛ ኢየሱስም በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ መኖሪያ (መሰማሪያ) ያዘጋጅላቸዋል::

***10+10 ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም::*** ይህ ሌባ ዲያብሎስ ነው:: ሌቦችና ወንበዴዎች የተባሉ የእርሱ ባሕርይ ያላቸው የእርሱ ተከታዮች የሆኑ እርሱም አባታቸው የሆነ ሰዎች ናቸው:: የዚህ ሌባ ባሕርይ መስረቅ፤ መግደል፤ ማጥፋት ነው:: የሚችለውን ያህል በመውሰድ ይሰርቃል፤ ሰራሱ ሊወስድ ያልቻለውን ይገድላል:: በእነዚህ በሁለቱ ያልተከናወነውን ያጠፋዋል:: ይህ ባሕርይ «እረኞች ነን» የሚሉ ስለ ራሳቸው ብቻ የሚያስቡ፣ ለበጐች የማይጠነቀቁ ሰዎች መግለጫ ነው:: በብሉይ ኪዳን እንዲህ የሚያደርጉ የሕዝብ መሪዎች፤ እረኞች፤ ሀሰተኛ ነቢያት (ኤር 10፥21-22፣ 12፥10፤ ዘካ 11፥4-17) ነበሩ:: አሁንም ይኖራሉ::



***10+10 እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ::*** የኢየሱስ መምጣት ከሌባው ባሕርይ ፈጽሞ በተቃረነ መንገድ ሕይወትን ለመስጠት ነው:: ሌባው ለማጥፋት፤ ለመግደል መጣ፤ ኢየሱስ ሕይወትን ለመስጠት መጣ:: የሚሰጠውም ሕይወት የበዛና የተትረፈረፈ ነው:: ሰው የበጎች እረኛ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን (ሲታመን) የተትረፈረፈ ሕይወት ያን ጊዜ ይጀምራል:: የተትረፈረፈ ሕይወት ለእያንዳንዱ አማኝ ኢየሱስ የሚሰጠውና ለዘላለም የሆነ ሕይወት ነው:: ስለ መልካሙ እረኛ በመዝሙር 23 እናነባለን:: የተረፈው ጽዋ (23፥5) የሚትረፈረፍ የሕይወትን ሙሉነትን ያሳያል:: ይህ መትረፍረፍ ሰው አስቦ ሊደርስበት የማይችል የሙላት መጠን ነው::

***10+11 መልካም እረኛ እኔ ነኝ:: መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል::*** መልካም እረኛ ከሌላው እረኛ (ምንደኛ) ወይም ከሌቦችና ወንበዴዎች ለበጎች ባለው ፍቅር የተለየ ነው:: መልካም እረኛ ለበጎቹ ካለው ፍቅር የተነሣ ራሱን ስለ በጎች የሚያኖር ነው:: መልካም እረኛ የሚወጣው በበሩ ነው:: መልካም እረኛ ሲመጣ በረኛው ያውቀዋል፤ ይከፍትለታል:: መልካም እረኛ በበጎቹም የታወቀ ነው፤ ይከተሉታልም::

***10+12 እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል::*** የመልካም እረኛ መመዘኛ ወይም ባሕርይ ለበጎቹ መጠንቀቅ ነው - ***ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል 10:11*** እንዲሁም 10:15፤17፤18):: ይህም እረኛው ለበጐቹ ያለውን ፍቅር ያሳያል:: በጐቹን የማይወድ ሞያተኛ ስለሚያገኘው ጥቅም (ገንዘብ) ብሎ በእረኝነት ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው:: እንዲህ አይነቱ ጠባቂ በሥራው ላይ የሚቆየው ጥቅሙ እስከተሟላለት ድረስ ብቻ ነው - ለበጎች ፍቅር የለውምና::

***ተኩላ*** ለበጐች የማይራራ በጭካኔ የሚሄድ የሀሰት አስተማሪ ምሳሌ ነው:: ***ሞያተኛው*** በጐችን በመጠበቅ ተግባር ላይ የተሠማራበት ዋና ዓላማ ስለሚያገኘው ክፍያ ወይም ደመወዝ ስለሆነ ስለ በጐቹ ግድ የለውም:: ስለዚህ ነጣቂ በመጣ ጊዜ ራሱ አስቀድሞ ይሸሻል:: ***ሞያተኛ ስለሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል 10:13::***

ይህ ምሳሌ በቤተ ክርስቲያን በመሪነት ላይ ላሉ ሰዎች ትምህርቱ ቀጥተኛ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማገልገል ላይ ያሉ በተለይም የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በአገልግሎት የተሰማሩት ቦታው የሚያስገኝላቸውን ደመወዝ ወይም ቀለብ በመፈለግ ከሆነ ሞያተኛ

መሆናቸው ናቸው:: ምክንያቱም የመጠበቅ ሥራቸው የሚወሰነው ከቀሰቡ መኖርና በቀለቡ መጠን ላይ ስለሚሆን ነው:: በጐቹን በመውደድ[44] የሚያገለግሉ ግን ግንኙነታቸው ከበጐቹ ጋር ስለሆነ፤ የአገልግሎታቸው መጠን በሚያገኙት ቀለብ ላይ አይመሠረትም:: የእነርሱ ትልቁ ደመወዝ የበጐች መጠበቅና መሰማራት ስለሆነ ተግተው ይጠብቃሉ:: በዚህም የበጐች እረኛ ደስ ይሰዋል::

***10:14-15 መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ እብም እንደሚያውቀኝ እኔም እብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች እኖራለሁ::*** በመልካም እረኛና በሞያተኛ መካከል ሁለት ትልቅ ልዩነቶች አሉ:: አንደኛው የማወቅ (የመተዋወቅ) ሁለተኛው ደግሞ ግድ የመሰኘት ናቸው:: በመልካሙ እረኛ በኢየሱስ ክርስቶስና የእርሱ በሆኑት አማኞች መካከል ያለውን መተዋወቅ በአብና በወልድ ባለው መተዋወቅ መስሎታል:: እረኛው በጐቹን በስም ጠርቶ እንደሚያውቃቸው ኢየሱስም በራሱ የሚያምኑትን ያውቃቸዋል፤ እነርሱም እርሱን ያውቁታል:: መልካሙ እረኛ ስለ ፍቅር ያደርጋል፤ ሞያተኛው ስለሚሰጠው ቀለብ ያደርጋል:: ሐዋርያው ጳውሎስ «የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለኛል» (2ቆሮ 5:14) ሲል ይህ የሞያተኛ አባባል እለመሆኑ ግልጽ ነው:: ሞያተኛው ደግሞ «ስለማገኘው ጥቅም (ገንዘብ) ግድ ይለኛል» የሚል ነው::

***10÷16 ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች እሉኝ፤ እነርሱንም ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምፄን ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ::*** አይሁድ ያሉበት አንድ በረት ነው:: ከዚህኛው ያልሆነው በረት ከአሕዛብ የሚያምኑትን ያመለክታል:: ከዚህኛው በረት የሆኑትንና ***ከዚህም በረት ያልሆኑን*** በጐች የሚያመሳስላቸው ሁለቱም የእረኛቸውን ድምፁን መስማታቸው (ማወቃቸው) ነው:: ለሁለቱም አንድ እረኛ አላቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: «በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ» (ኤፌ 2÷16) እንደሚል ሁለቱም በአንድ በረት ውስጥ ይጠቃለላሉ:: ይህ በኤፌ 2÷14-15 «ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ» እንዳለ ከዚህኛው በረት የሆኑትንና ከዚህኛው በረት ያልሆኑትን ሁለቱንም በአንድ በረት ውስጥ አደረገ፤ አንድ አዲስ ሰው ፈጠረ:: ይህችም ቤተ ክርስቲያን ነች::

[44] በዮሐ 21:15-17 ባለው ክፍል ጴጥሮስ ስለ በጎች አደራ ከመቀበሉ በፊት ጌታን (የበጎችን መልካም እረኛ) ይወድ እንደሆነ ጌታ ጠይቆት ነበር:: በጎችንም የበጎቹን ባለቤት (እረኛ) የሚወድ መሆን አለበት::



በዚህኛው በረት የነበሩትን ካወጣ በኋላ ከዚህ በረት ያልሆኑትን ያመጣል:: ድምፁን ሰምተው የመጡት በአንድ በረት ውስጥ ይሆናሉ:: ***ሁለቱም አንድ መንጋ ይሆናሉ*** - አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን:: አንድ የሚያደርጋቸውም በሩ አንድ መሆኑ፤ በአንድ በረት መጠቃለላቸውና ከሁሉም በላይ እረኛቸው አንድ ስለሆነ ነው:: አንድ እረኛ ያላቸው ሁሉ አንድነት አላቸው:: እነዚህ በአንድ በረት ውስጥ ሆነው ድምፁን የሚለዩ ናቸው:: የክርስቶስ የሆኑት በጎች ክርስቶስን ያውቁታል:: የአንድነታቸው መሠረቱ አንድ እረኛ ያላቸው በጎች መሆናቸው ነው::

***10÷17 ነፍሴን ደግሞ እንሣት ዘንድ እኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል::*** አብ ወልድን የወደደበትን ምክንያት ይገልጥልናል:: ወልድ ነፍሱን ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆኑ ወዶታል::

***10÷18 እኔ በፈቃዴ እኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም:: ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ:: ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ::*** ነፍስን መውሰድ የሚችል መስኮት ነው፤ ነፍስን የሰጠ መስኮት ነው:: ኢየሱስ እርሱ መስኮት ነውና በራሱ ሕይወት አለው:: ስለዚህ የእርሱን ነፍስ ማንም ሊወስድበት አይችልም፤ በፈቃዱ ግን ነፍሱን ሊሰጥ መጣ:: ነፍሱን ለመስጠት ወይም ለማኖር ከአብ የተሰጠው ሥልጣን አለው:: ይህ ክፍል የኢየሱስ ክርስቶስን ሞትና ትንሣኤን ይናገራል:: ነፍሱን ራሱ አሳልፎ ሰጠ እንጂ ነፍሱን ማንም አልወሰደበትም::

***10÷20 ከእነርሱም ብዙዎች:- ጋኔን አለበት አብዶአልም ስለ ምንስ ትሰሙታላችሁ? አሉ:: ሌሎችም ይህ ጋኔን ያለበት ሰው ቃል አይደለም!*** አሉ:: ***ጋኔን የዕውሮችን ዓይኖች ሊከፍት ይችላልን? አሉ::*** በአይሁድ መካከል እንዲህ ዓይነት መለያየት ተደጋገመ (7:43፤ 9:16):: የዕውሮችን ዓይኖች ሲሉ በምዕራፍ ዘጠኝ የተፈጸመውን ምልክት መጥቀሳቸው ነው::

***10÷22 በኢየሩሳሌምም የመቅደስ መታደስ በዓል ሆነ::*** ጌታ በዳስ በዓል ላይ ተገኝቶ ሰዎችን አስተምሮአል:: አሁን ደግሞ የመቅደስ መታደስ[45] በዓል ሆነ:: ጊዜው ***ክረምትም ነበረ 10÷22::*** በከነዓን ምድር ክረምት የሚሆነው በታህሣሥና አካባቢው ባሉት ወራት ነው::

[45] <... the Feast of Dedication in December. This feast was not one of the official festivals in the Old Testament. It was instituted by Judas Maccabeus in 165 B.C. to commemorate the cleansing of the temple after Antiochus Epiphananes had defiled it by sacrificing a pig on the

***10፥24 አይሁድም እርሱን ከበው፡- እስከ መቼ ድረስ በጥርጣሬ ታቆየናለህ? አንተ ክርስቶስ እንደ ሆንህ ገልጠህ ንገረን አሉት።*** አይሁድና ፈሪሳውያን ከጌታ ብዙ ትምህርትን ሰምተዋል። ብዙ ምልክትም አይተዋል። ባደረጋቸው ምልክቶችና ባስተማረውም የእርሱን ማንነት ገልጿል። አሁንም ግን ሊያጠምዱት ስለሚፈልጉ እንደ ገና ይጠይቁታል። አይሁድ መሲሑን የሚጠብቁት ከሮማውያን አገዛዝ ነፃ እንዲያወጣቸው ስለሆነ ይህ (ኢየሱስ) መሲሑ ከሆነ ይምራን፣ ይንገሥልን፣ ነፃም ያውጣን ብለው መፈለጋቸው ነው። የሀገር መሪ ሊያደርጉት እንጂ የነፍሳቸው አዳኝ እንደሆነ አልገባቸውም። ገና በአገልግሎቱ መጀመሪያ ዮሐንስ መጥምቁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (1፡29) ብሎ ነበር። ከአብ ዘንድ የተላከ የኃጢአት መድኃኒት ነው።።

***10፥25-26 ነገርኋችሁ አታምኑምም እኔ በአባቴ ስም የማደርገው ሥራ ይህ ስለ እኔ ይመሰክራል እናንተ ግን እንደነገርኋችሁ ከበጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም።*** ጌታ እያደረገ ያለው ሥራ ወይም ምልክት ስለ እርሱ የሚመሰክር ነው። ትምህርቱም ወደ እርሱ ያመለክታል። ያም ሆኖ ግን ሊሰሙት አልፈለጉም። መስማትና መከተል የክርስቶስ በጎች ባሕርይ ነው። እነዚህ የሚናገረውን ይሰማሉ ነገር ግን ድምፁን ተከትለው ከእርሱ ጋር አይሄዱም። ስለሆነም የእርሱ አይደሉም።

***10፥27-28 በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄ ማንም አይነጥቃቸውም።*** መስማት ወደ መከተል ካደረሰ የክርስቶስ የሆኑ በጎች ምልክት ነው። እርሱ ይጠብቃቸዋል፤ አይጠፉም፤ ማንም አይወስዳቸውም። የሚሰሙት ካልተከተሉት የእርሱ አይደሉም ማለት ነው። ድምፁን ሰምተው የሚከተሉት ስጦታ ይቀበላሉ። ይህም ከእነርሱ ያልሆነ ጌታ ብቻ የሚሰጣቸው ስጦታ ነው። ስጦታውም የዘላለም ሕይወት ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ የታወቀ በግ መሆን ምንኛ በረከትና ክብር ነው። ከሚከተሉትም ከማይከተሉትም ከብዙ በጎች መካከል በእርሱ መታወቅ። እርሱ እያንዳንዳቸውን ያውቃል። ስለዚህ ክርስቲያን በየትኛውም ሁኔታ፤ በማንኛው ቦታና አገር ቢሆንም በመልካሙ እረኛ በኢየሱስ የታወቀ ነው፤ ያስማራዋል።

---

altar of burnt offering. ... This is also the present-day Feast of Lights called Hanukkah.> Ibid. P. 215.



***10፥29 የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴ እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።*** ቀደም ሲል በ3፡31 ላይ «ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው» የሚለውን እናስታውሳለን። እንዲሁም «ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው» ብሏል። ከላይ የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ ከሁሉ በላይ ነው። እዚህም ላይ እንዲሁ ይላል። የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ግን ከሁሉ ይበልጣል። እንግዲህ በጎች በእርሱ ጥበቃ ውስጥ መኖራቸው እርግጠኛ ነው። የተረጋገጠውም ከሁሉ የሚበልጠው አብ እንዲጠብቃቸው ለኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰጠው ነው። ***ማንም*** ሲል ሰው ብቻ ሳይሆን መላእክትም ቢሆኑ የሚለውን ይጨምራል።

***10፥30 እኔና አብ አንድ ነን***፡ ይህ በአብና በወልድ መካከል ያለውን የዘላለም አንድነት ያሳያል። በሁለቱ መካከል ያለው የአባትና የልጅነት ዘላለማዊ ተዛምዶ ነው። ጌታ ኢየሱስ ***እኔና አብ አንድ ነን*** ሲል እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር ወልድ አንድ አካል ናቸው አላለም። በሥላሴ ውስጥ እግዚአብሔር አብ አንድ አካል ነው። እግዚአብሔር ወልድ ሁለተኛ አካል ነው። እያንዳንዳቸው እኔነት ያላቸው ሁለት አካላት ናቸው እንጂ አንድ አካል አይደሉም። በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ፍፁም አንድነት ነው። የባሕርይ አንድነት፣ የዓላማ አንድነት የፍቅር አንድነት፣ በመለኮት እኩልነት፣ በዘላለማዊነት እኩልነት አላቸው። በመለኮት እኩል ስለሆኑ አብ የሚያውቀውን ሁሉ ወልድ ያውቀዋል፤ አብ የሚሠራውን ሁሉ ወልድ ይሠራዋል።

***10፥31 አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።*** ከዚህም በፊት ድንጋይ አንስተው ነበር (5፡17-18፣ 8፡58-59)። እንደ ቀደሙት ጊዜያት ሁሉ አሁንም አልወገሩትም፣ አልያዙትም ***ከእጃቸውም ወጣ 10፥39***፡ ስምን ትወግሩኛላችሁ? ብሎ ሲጠይቃቸው፡- ***ስለ ስድብ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ በማድረግህ ነው እንጂ 10፥33*** በማለት ይመልሱለታል። እነዚህ ሊወግሩት የፈለጉ ሰዎች መስማትንስ ሰምተው ነበር፤ አላመኑበትም እንጂ። እርሱም ራሱን አምላክ አድርጎ መናገሩ ገብቷቸዋል። በእርግጥ አምላክ ነውና።

***10፥34-36 እኔ፡- አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክትካላቸው፥ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን፡- ትሳደባለህ ትሉታላችሁን?*** በብሉይ ኪዳን የተነገረው እውነት መሆኑንና ማንም ሊሽረው እንደማይችል ያስረዳል - ***መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና***።

ይህ ***አማልክት ናችሁ አልሁ*** ተብሎ የተጻፈው በመዝሙር 82 ነው። በዚያ ክፍል እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲያስተዳድሩ በሕዝቡም ላይ እንዲፈርዱ የተሾሙትን ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሹመት ሲያመለክት «አማልክት» ብሎ ይጠራቸዋል። እነዚህ አማልክት የተባሉት ለሕዝብ ፍርድን እንዲሰጡ ሀሳቡን እንዲያስፈጽሙ እግዚአብሔር የሾማቸው መሪዎች (አለቆች ወይም ዳኞች) ናቸው። እነርሱ ሰዎች ናቸውና እንደ ሰው የሚሞቱ፣ የሚወድቁ አማልክት ናቸው (82፥7)፣ የሚፈረድባቸውም ናቸው (82፥1)። በሌላም ቦታ ዘጸ 4፥16 እና 7፥1 ላይ ሙሴ እንደ አምላክ እንደሚፈርድ ተናግሯል።

ጌታ ኢየሱስ ይህን የመዝ 82፥6ን ጥቅስ በመጥቀስ የሚናገረው «እንኳንስ እኔ የሚሞቱና የሚፈረድባቸው ሰዎች እንኳን አማልክት ተብለዋል» ሲል ነው። ስለሆነም ***እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን ትሳደባለህ ትሉታላችሁን?*** አላቸው። አብ ኢየሱስ ክርስቶስን ቀድሶታል፣ ፈቃዱን እንዲያደርግ ወደ ዓለም ልኮታል። እርሱ ከአማልክት በላይ ነው።

***10፥38 እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ።*** ማወቅ አንድ ደረጃ ነው፣ ማስተዋል ደግሞ ያወቁትን ማገናዘብና መቀበል ነው። ማወቅ የመጀመሪያውን ደረጃ ሲያመለክት፣ በዚህ ቦታ ማስተዋል ደግሞ በአወቁት መቆየትን፣ መቀጠልን ያመለክታል። ጌታ ለትምህርቱ ማረጋገጫ ይሰጥ ነበር፣ አንዳንዶችም ከእርሱ ጋር ሆነው እርሱን በማየት ያምኑ ነበሩ። እንዲሁም ጌታ ምልክትንና ተአምራትን በማድረጉ ኃይሉን ይገልጥ ነበር። ይህ ሁሉ እርሱ በአብ እንደተላከ የሚያረጋግጥ ነው። ይህን ቢያውቁም እንኳን ብዙዎቹ ለማስተዋል ወይም ለመቀበል አልፈለጉም። ***አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ*** ሲል ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለውን አንድነት በድጋሚ ይገልጻል። እንዲሁም 14፥10፣ 17፥21ን ይመልከቱ።

***10፥39 ደግመው ሊይዙት ፈለጉ፤ ከእጃቸውም ወጣ።*** አይሁድ ***እርሱን ከበው 10፥24*** ነበረ። ነገር ግን ሊይዙት አልቻሉም፣ ከእጃቸው ወጣ፤ ምክንያቱም የጌታ ጊዜ ገና አልደረሰምና አልተያዘላቸውም። ይህ በተደጋጋሚ ያደረጉት ሙከራ ነው።

***10፥41 ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጥተው፡- ዮሐንስ አንድ ምልክት ስንኳ አላደረገም፥ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነበረ አሉ።*** ዮሐንስ መንገድ የሚጠርግ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ ነበረ (1:23)። ከእርሱ ይልቅ ስለሚልቀው ስለ ኢየሱስ



ተናገረ። ዮሐንስ ያን ጊዜ የተናገረውም እውነት እንደሆነ ስለ ዮሐንስ የሚመሰክሩ ሰዎች አሁንም አሉ። ዮሐንስ በምስክርነቱ ወደ ኢየሱስ አመለከተ። ሰዎችም በዚህ ምልክት ተከትለው ኢየሱስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ ***በዚያም ብዙዎች በእርሱ አመኑ 10፥42***፡

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

በዚህ ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሞተው ሕይወትን የሚሰጥ «ትንሣኤና ሕይወት» መሆኑን ይገልጻል:: ለሞተውና ለተቀበረው ለአልዓዛር ሕይወት ሰጠው[46]:: በዮሐንስ ወንጌል እስከ እዚህ ምዕራፍ ድረስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ሰጪ መሆኑን ለተለያዩ ሰዎች ገልጿል::

- ለኒቆዲሞስ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ነገረው (3÷46)፤
- ለሳምራዊቷ ሴት የሕይወት ውኃ (4÷11)፤
- የታመመውን የሹሙን ልጅ በሕይወት አቆየው (4:50)
- ለተራቡት የሕይወት እንጀራ እንደሆነ አስተማራቸው (6÷35)፤
- በኢየሩሳሌም በዓል ያከብሩ ለነበሩት እይሁድ የሕይወት ውኃ ምንጭ እንደሆነ አስተማራቸው (7÷38)::
- ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር ለነበረው ሰው የሕይወት ብርሃን መሆኑን አሳየ (8÷12፤ 9÷35-38)::
- ይከተሉት የነበሩት ሰዎች/በጎች የተትረፈረፈ ሕይወት መሆኑንም አስተማረ (10÷10-11)::

የአልዓዛር ከሙታን መነሣት ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት የመስጠት ኃይል እንዳለው፤ ሙታንን የሚያስነሣ እንደሆነ ምልክት ነው:: የአልዓዛር ከሞት መነሣትና ሌሎች ምልክቶች ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ናቸው::

***11+1 ከማርያምና ከእኅትዋ ከማርታ መንደር ከቢታንያ የሆነ አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ታሞ ነበር::*** ማርያምና ማርታ እህትማማቾች ናቸው፤ ወንድማቸውም አልዓዛር ይባላል:: ስለ እነዚህ ሰዎች ወላጆች የተገለጠ ነገር የለም:: አልዓዛር በታመመ ጊዜ ኢየሱስ ጌታ ዮሐንስ

[46] ከአልዓዛር ሌላ በወንጌላት ውስጥ ሰዎችን ጌታ ከሞት እንዳስነሣ እናያለን:: የኢያኢሮስን ልጅ (ማቴ 6:18-26፤ ማር 5:41-42፤ ሉቃ 5:40-56)፤ የመበለቷን ልጅ ሉቃ (7:11-17)::



ያጠምቅበት ወደ ነበረው ወደ ዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ቤተ ራባ በሚባል ቦታ ነበረ (10:40)::

***11÷2 ማርያም ጌታን ሽቱ የቀባችው እግሩንም በጠጕርዋ ያበሰችው ነበረች::*** ያደረገችው ነገር በዮሐ 12:1-7፣ በማቴ 26-13ና ማር 14:3-9 ተገልጦአል::

***11÷3 እኅቶቹ ጌታ ሆይ: እነሆ÷ የምትወደው ታሞአል ብለው ወደ እርሱ ላኩ::*** የታመሙ እንዲፈወሱላቸው ወይም የሞቱትን እንዲያስነሣላቸው ሰዎች ኢየሱስን ሲጠይቁ «ብትወድስ» ይላሉ እንጂ እንደ ማርያምና ማርታ ***የትምወደው*** አላሉም:: የአላላኩ ዓይነት የሚወደው ስለ ታመመ በፍጥነት እንዲመጣ የሚያደርግ ይመስላል:: የኢየሱስ መልስ ግን እነ ማርታ እንደጠበቁት አይመስልም::

***11+4 የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ::*** ይህ ሕመም ለሞት አይደለም የሚለውን የስሙት ደቀ መዛሙርቱ አልዓዛርን ለሞት አያደርሰውም ያለ መሰላቸው (11:11)::

መልእክቱን ከማርያምና ማርታ ወደ ኢየሱስ ያመጡት ሰዎች ጌታ የሰጠውን መልስ ሰምተው ተመልሰው ሲነግሯቸው በማርያምና ማርታ ቤት የሚሆነውን ደስታና ሀዘን መገመት ይቻላል:: መልእክተኛው ቶሎ መልእክቱን አድርሶናአልዓዛር ሳይሞት ደርሶ ከሆነ በአንድ በኩል ኢየሱስ ለሞት አይደለም ብሏል የሚለው ቃል ቢያስደስታቸውም በሌላ በኩል ይህ የተስፋ ቃል አለን አያሉ አልዓዛር ግን እየደከመ ነው፤ ወዲያውም ሞተ:: ይህ ደግሞ በውስጣቸው ትልቅ ጥያቄ ሲያመጣባቸው ይችላል::

በሌላም በኩል ***የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ*** የሚለው ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር ስለነበረው ሰው የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ (9:3) ካለው ጋር ተሳሳይነት አለው:: አልዓዛር የታመመው ኢየሱስ በእርሱ ላይ በሚፈጽመው ምልክት ለእግዚአብሔር ክብር ያመጣ ዘንድ ነው:: ዕውር የነበረው ሰው ኢየሱስ በሚፈጽመው ሥራ የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው:: በሁለቱም ሁኔታ እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ ነው::

***11÷5 ኢየሱስም ማርታንና እኅትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር::*** ኢየሱስ እያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ይወድ ነበረ:: እንዲሁም እኅቶቹ የምትወደው (11:3) ታሟል ብለው የላኩበት ትክክል ነው - ***ይወድ***

*ነበር::* ከዚህም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛርን እየወደደው ግን ፈጥኖ ወደ እርሱ እንዳልመጣ እናገናዝባለን::

***አልዓዛርንም ይወድ ነበር*** የሚለው የኢየሱስን ቶሎ አለመምጣት ያጉላዋል:: እንደ ሰው አስተሳሰብ ከሆነ ቤተሰቡን ይወድ ስለ ነበረ ኢየሱስ በቦታው ቶሎ ደርሶ አልዓዛር ከመሞቱና ቤተ ሰቡም በሀዘን ከመመታቱ በፊት የታመመውን ይፈውሳል ብሎ ማሰብ ትክክል ይሆናል:: ይህ ሰው እንዲሆንለት የሚመኘው ነው:: ሆኖም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያደርገው ነገር ለአባቱ የበለጠ ክብር የሚያመጣለትን ሁኔታና ጊዜ ይጠብቅ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ከፍተኛ ክብር የሚያመጣው በመቆየቱ እንደሆነ አውቋል:: ስለዚህ ቶሎ አልሄደም::

***11+6 እንደ ታመመም በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ኖረ::*** አልዓዛርና እህቶቹን ይወድ እንደ ነበረ በቁ.5 አይተናል:: መታመሙን ከሰማም በኋላ ጌታ ቶሎ አልሄደም:: እንዲያውም ***ሁለት ቀን ኖረ::*** በእነዚህ ቀናት ውስጥ በእነ ማርታ ቤተ ሰብ የሚሆነውን እርሱ ያውቃል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም እንኳን ሰዎችን ቢወድ በሚያደርገው ተግባር ግን በሰዎች ጊዜና ሀሳብ አይገፋፋም:: ይህ ቢሆን ኖሮ እናቱ ስትጠይቀው «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» (2:4) ባላሰም ነበር፤ ወይም ወንድሞቹ ሲገፋፉት (7÷3-10)፤ ከእነርሱ ጥያቄ የተነሣ ሀሳባቸውን በፈጸመ ነበር:: ነገር ግን ጌታ የሚያደርገውን ሁሉ የሚያደርገው በአባቱ ጊዜና በአባቱ ፈቃድ መሠረት ነው::

የኢየሱስ ክርስቶስ *ሁለት ቀን* መዋል (*መዘግየት* ብንለው) ለእግዚአብሔር ክብር እንዲያመጣ ሰዓላማ ነው:: ይህም ለእርሱ ከፍተኛ ክብር የሚያመጣ ተግባር ከትክክለኛው ጊዜ ጋር ሊገጣጠሙ ማለት ነው:: ስለሆነም አንድ ፈውስ፤ *ሥራ*፤ ምልክት ወይም ተአምር መቼ ቢሆን እንደሚሻል እግዚአብሔር ከእርሱ ፈቃድና ክብር አንጻር ይመርጣል:: የአንድ አገልጋይ ተግባር ከእግዚአብሔር ፈቃድና ጊዜ ጋር በመስማማት ማገልገል መሆኑን ማስተዋል አለበት:: በመጨረሻም ክብሩ ለእግዚአብሔር ነው::

***11÷7 ለደቀ መዛሙርቱ:- ወደ ይሁዳ ደግሞ እንሂድ አላቸው::*** ጌታ ኢየሱስ አልዓዛር እንደታመመ በሰማ ጊዜ በነበረበት ቦታ ሁለት ቀን እንደ ዋለ ተመልክተናል:: አሁን ግን የእግዚአብሔር ጊዜ ስለ ደረሰ ወደ ቢታንያ ለመሄድ ደቀ መዛሙርቱን ***እንሂድ*** ይላቸዋል:: በይሁዳ አይሁድ ኢየሱስን በድንጋይ ሊወግሩ ፈልገው ነበር (10÷31):: በሌላ በኩል ጌታ የነበረበት ቦታ ብዙዎች እርሱን ተቀብለውታል፤ በእርሱ



አምነዋል (10÷42):: ይህን ቦታ ትቶ ሊወግሩት ወደሚፈልጉት ቦታ ለመሄድ መነሣት ወደ ሞት እንደመሄድ ነው:: ከዚህም የተነሣ ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ኢየሱስን:- ***መምህር ሆይ፥ አይሁድ ስጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር፥ ደግሞም ወደዚያ ትሄዳለህን? አሉት 11፥8***: ጌታ ኢየሱስ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና ጊዜ በእርሱ ላይ ምንም ነገር እንደማይሆን ያውቅ ነበርና ሊወግሩት ወደሚፈልጉት ወደ አይሁድ ለመሄድ አላመነታም::

***11÷9 ቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት አይደለምን?*** የደቀ መዛሙርት ጭንቀት አይሁድ በጌታ ላይ ሊያደርጉ ስለሚችሉት ጉዳት በማሰብ እንዳይሄድ መምከራቸው ነው:: ይህ የስው ጥንቃቄ ነው:: ጌታ ደግሞ የሚሰጣቸው መልስ ያለ እግዚአብሔር ጊዜ በእርሱ ላይ ማንም ምንም ሊያደርግ እንደማይችል የሚያስገነዝብ ነው::

እያንዳንዱ ቀን ***አሥራ ሁለት ሰዓት*** እንዳለው የታወቀ የመሆኑን ያህል ስዓቱ (ቀኑ) የሚያልቅበትና ጨለማ የሚመጣበት ጊዜ አለው:: የጌታ ቀን ማለትም እርሱ በምድር ላይ የነበረበት ጊዜ ወደ ፍጻሜው እየተቃረበ ነው:: ከመሞቱ ማለትም ቀኑ ከመጨለሙ በፊት የሚሠራው ተግባር አለ::

***11÷9-10 በቀን የሚመላለስ ቢኖር የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናከልም፤ በሌሊት የሚመላለስ ቢኖር ግን ብርሃን በእርሱ ስለ ሌለ ይሰናከላል::*** ይህ ማንም ሰው ሊረዳው ከሚችለው ቀላል ምሳሌ ተነስቶ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚነግራቸው የጠለቀ ምስጢር ነው:: ብርሃን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና በእርሱም መኖር ትክክለኛ መንፈሳዊ ሕይወት ነው:: የዓለም ***ብርሃን*** የሆነው ኢየሱስ እርሱ በመካከላቸው እስካለ ድረስ ብርሃናቸው ነው (1÷4፤ 8:12፤ 9:5):: በአንጻሩ በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ይሰናከላሉ:: የብርሃን ምንጬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

በብርሃን ለመመላለስና ላለመሰናከል የሚመርጥ ሰው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ይምጣ:: በሕይወት ለሚነጥሙ የተሰያዩ ምርጫዎችና ውሳኔ ለማያስፈልጋቸው ጉዳዮች ኢየሱስ ምን ይላል? በፊቴ ለተደቀነ ለዚህ ነገር ምን ይመርጣል? ብሎ መጠየቅ ነው:: እርሱ ባለበት ጨለማ የለም፣ እርሱ በመረጠው መሰናከል የለም::

***11÷11 ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል፤ ነገር ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ*** ሲል ደቀ መዛሙርቱ ለዚህ የሰጡት ምላሽ:- ***ተኝቶስ እንደ ሆነ ይድናል 11÷12*** በማለት ነው:: ጌታ ***ተኝቶአል*** ሲል ስለ ሞት

መናገሩ እንደ ነበረ አልገባቸውም (11÷12-13)። እንዲሁም ዳን 12÷2፤ 1ቆሮ 12÷30፣ 15÷20፤51፤ 1ተሰ 4÷14ን ይመልከቱ። እርሱ ያለውን እንዳልተረዱት በማየት ጌታ:-

***11÷14-15 በግልጥ:- አልዓዛር ሞተ፤ እንድታምኑም በዚያ ባለ መኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤*** አላቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛር ወዳለበት እንዲመጣ የተጠራው አልዓዛር እንደታመመ ነበር። ጌታ ሳይመጣ ***አልዓዛር ሞተ።*** አልዓዛር የሞተው ኢየሱስ በሞት ላይ ሥልጣን እንዳለው ለደቀ መዛሙርቱና ለሌሎችም ለማሳየትና ከዚህ ሥራ ለእግዚአብሔር ክብር ለማምጣት ነው።

የአልዓዛር ከሞት መነሣት ጌታ ካደረጋቸውና በዮሐንስ ወንጌል ከተገለጹት ስምንት ምልክቶች መካከል አንዱ ነው። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ትንሣኤና ሕይወት እንደ ሆነ የሚገልጥ ምልክት ወይም ተአምር ነው። ኢየሱስ ራሱን ከሞት የማስነሣት ሥልጣን አለው (10÷18)። እንዲሁም የአልዓዛር ከሞት መነሣት ጌታ ኢየሱስ የሚሞቱትንም ሁሉ ከሞት እንደሚያስነሣ ያሳያል። እርሱ ሙታንን እንደሚያስነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው በተደጋጋሚ ተናግሯል (5÷21፤ 6÷40፤54፤ 8÷51፤ 10÷17-18፤27-28)።

አልዓዛርን ተኝቷል ሲል ደቀ መዛሙርቱ እንቅልፍ መሰላቸው፤ ሞትን እንደ እንቅልፍ የሚቆጥር ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነውና። ምክንያቱም በሞት ላይ ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ስለሆነ። በደቀ መዛሙርቱና በሌሎችም ሰዎች እይታ ሞት የመጨረሻ ነገር ነው። ስለዚህ ከሞት ሰውን ማስነሣት ወይም መቀስቀስ አይቻልም። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሆኑት ትንሣኤ መኖሩን ለሚያምኑ፣ ሞት እንቅልፍ ነው።

***11÷15 እንድታምኑም በዚያ ባለ መኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል።*** እዚህ ላይ የጌታ ደስታ ምንድን ነው? አልዓዛር በታመመበት ቦታ ቢኖር ኖሮ ከመሞቱ በፊት ሲያስነሣው በቻለ ነበር። በሌላም በኩል ጌታ ኢየሱስ ***በዚያ ባለመኖሬ ... ደስ ይለኛል*** በማለትም ይናገራል። ከማርያምና ማርታ ሁኔታ አንጻር ይህ ደስታ እንቆቅልሽ ነው። እነርሱ በሃዘንና በልቅሶ ላይ ናቸውና።

አሁን ግን አልዓዛር ከሞተ ቆይቷል፤ ሲያስነሣውም እየሄደ ነው። የጌታ ደስታም ይህ ሁኔታ ደቀ መዛሙርቱ በእምነታቸው የሚያድጉበት ስለሆነ ነው። ጌታ የታመሙትን ሲፈውስ፣ ሌሎች ምልክቶች (ተአምራት) ሲያደርግ ደቀ መዛሙርት አይተዋል። የሞተንም ሰው ሲያስነሣ ተመልክተዋል- ለምሳሌ:- ጣሊታ ተነሺ



(ማር 5:41) ያላት። ነገር ግን የሞተ፤ የተቀበረና በመቃብር ውስጥ የሰነበተን ሲያስነሣ ገና አላዩም። ስለዚህ አሁን ጌታ ኢየሱስ የሚያደርገው ተአምር የደቀ መዛሙርትን እምነት ይጨምራል። እርሱ በእርግጥም የትንሣኤ ጌታ እንደሆነ እንዲያምኑ ይረዳቸዋል። ጌታ የሚያደርገውን በራሱ ጊዜ ያደርጋል። ሲያደርግም እጅግ ውብ አድርጐ ይሠራዋል።

***11÷16 ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ።*** ይህን የሚለው ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የሆነው ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ነው። ቶማስ ሌሎች ደቀ መዛሙርትን ሁሉ ከጌታ ጋር አብረው ወደ ይሁዳ እንዲሄዱ ሲያነሣሣ እንመለከታለን። ***እንሂድ*** የሚለው ለመሞትም ጭምር ነው። ምክንያቱም በይሁዳ ያሉት አይሁድ ጌታን ሊገድሉት እንደሚፈልጉ የታወቀ ነውና። ቶማስ ከጌታ ጋር አብሮ ለመሆንና ቢያስፈልግም ለመሞት የተዘጋጀ ቆራጥ ደቀ መዝሙር ነበር ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ቶማስ የሚታወቀው ትንሣኤን የተጠራጠረ ደቀ መዝሙር በመሆኑ ነው (20÷24-25)።

ቶማስ ***ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ*** ሲል ሌሎች ደቀ መዛሙርትም በውስጣቸው የሚያስቡትን መናገሩ ሳይሆን አይቀርም። ቶማስ ከጌታ ጋር አብሮ በመሄድ ለመሞትም ቢሆን የተዘጋጀ ጌታን የሚወድና ደፋርም ሰው እንደነበር እናያለን። እንዲሁም ደቀ መዛሙርት ለጌታ ያላቸውን ታማኝነት እንመለከታለን። የጌታ ደቀ መዝሙር መሆን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላልና። ፊታቸው ሞት እያለ ለመሞትም ቢሆን ጌታን ተከትለው ይሄዱ ነበር።

***11÷17 ኢየሱስም በመጣ ጊዜ በመቃብር እስከ አሁን አራት ቀን ሆኖት አገኘው።*** በአይሁድ ልማድ አብዛኛውን የሞተ ሰው የሚቀበረው በዕለቱ ነው። ሀዘን የደረሰበትን ቤተ ሰብ ተሰባስቦ ለቅሶ መድረስና ማጽናናት የአይሁድ ልማድ ነበርና ብዙዎች ወደ ማርታና ወደ ማርያም መጥተው ነበር። ***ማርታም ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው ወጣች፤ 11÷20።***

***11÷21 ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፡-*** ይህ አባበሏ በአንድ በኩል ቅሬታ ነው፤ በሌላ በኩል ልመናም ይመስላል። በዚህ አነጋገሯ ማርታ የምትገልጸው ኢየሱስ እዚህ ብትኖር ወይም ቶሎ ብትመጣ ኖሮ አልዓዛር እንዳይሞት ታደርግ ነበር የሚል ሀሳብ ነው። እንዲህ ዓይነቱን አገላለጽ ማርያምም በተመሳሳይ ሁኔታ በ11÷32 ላይ ትላለች።

እዚህ ላይ የማርታንና የማርያምን አቀራረብ ልብ ብሎ ማስተዋሉ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ሁለቱ እህትማማቾች የሚወዱት ወንድማቸውን አጥተዋል፤ ስለዚህ በሀዘን ላይ ናቸው፡፡ ሁለቱም ጌታ ኢየሱስን ሲያገኙት የሚሉት ተመሳሳይ ቃል ***አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፤ 11፥21፣ 32*** የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ በዚያ ቦታ ባለመኖሩ ምክንያት ወንድማቸው እንደሞተ ይገልጣሉ፡፡ ሁለቱም ሃዘን ከተቀመጡበት ተነስተው የመጡና በሃዘን ላይ የነበሩ ቢሆንም ጌታን ሲያገኙት ግን በአቀራረባቸው በሁለቱ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ማርታ ጌታን እንዳገኘችው ወደ ንግግሯ ስትሄድ፣ ወይም በቀጥታ ጥያቄዋን ስታቀርብ ማርያም ግን ጌታን ስታገኘው መጀመሪያ በእግሩ ላይ ወደቀች (11፥32)፡፡ በእግሩ ላይ መወደቋ፣ የኢየሱስን ጌትነት መግለጿ ለእርሱ ክብር ለግደት የሚገባው መሆኑን በማወቅ ያንን በድርጊት ማሳየቷ ነው፡፡ መጀመሪያ ለግደት ከዚያም ጥያቄ፣ ማርያም ከጥያቄ በፊት አምልኮን ታስቀድማለች ማለት ነው፡፡

በሌላም ጊዜ ጌታ ወደ ቤታቸው በመጣ ጊዜ ማርታ ፈጥና የሄደችው ወደ ማገልገሉ ነበር፡፡ ትኩረቷ አገልግሎት ላይ ነው፡፡ ማርታ አገልግሎት የሚበዛባትና የምትባክን ሴት፣ ቁጭ ብላ ከጌታ ለመስማት ጊዜ የማይኖራት ሴት ነች (ሉቃ 10፥38-42)፡፡ በዚያን ሰዓት ማርያም ያደረገችው በእግሩ ሥር ቁጭ ብላ እርሱን መስማት ነው፡፡ አሁንም በእግሩ ሥር መውደቅ (መሆን) ነው፡፡ ለማርያም ቀዳሚው ነገር ለጌታ መስገድ (ክብር መስጠት) እና እርሱን ማድመጥ ነው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት እህትማማቾች በተመሳሳይ ሁኔታ (ችግር) ውስጥ እያሉ ያንን ችግር የሚረዱበትና ለጌታም ያላቸው አቀራረብ በጣም የተለያየ ነበር፡፡

በዚህም ዘመን ያለን እኛ ክርስቲያኖች ከማርያምና ማርታ ሁኔታ የምናስተውለው ትልቅ ነገር አለ፡፡ ጌታን ማገልገል እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ግን ቀዳሚ መሆን አለበት፡፡

***11፥22 አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ፡-*** ስትል በአሁን ጊዜ በጌታ ላይ እምነት እንዳላት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በ11፡24 እና 39 በተገለጸው መሠረት የማርታን እምነት ስንመለከት በአሁኑ ጊዜ ኢየሱስ አልዓዛርን ሊያስነሣው እንደሚችል ያመነች አይመስልም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል እንዳለው፤ እግዚአብሔር እንደሚሰማውና የሚጠይቀውንም እንደሚሰጠው ብታውቅም አልዓዛር እንደታመመ ቢደርስ ኖሮ ያንን ኃይሉን ሊገልጥ ይችል እንደ ነበረ ያሰበች ይመስላል፡፡



***11፥23 ኢየሱስም፡- ወንድምሽ ይነሣል አላት፡፡*** የጌታ ንግግር በአሁኑ ጊዜ ነው፤ አሁን አስነሣዋለሁ ማለት ነው፡፡ የማርታ መልስ ደግሞ ለወደፊቱ ማለትም፡- ***በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ 11፥24*** የሚል ነበር፡፡ ይህም ስለ ወደፊቱ የዘላለም ሕይወት የምታምነውን መግለጿ ነው፡፡

***11፥25-27 ኢየሱስም፡- ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚለሽን? አላት፡፡*** እስካሁን ባየናቸው ክፍሎች በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ላገኛት ለሳምራዊት ሴት እርሱ መሲሑ እንደሆነ የሕይወትን ውኃ እንደሚሰጥ ገልጦላታል (4፡25-26)፡፡ ዕውር ለነበረውም ሰው የሰው ልጅ እንደ ሆነና ብርሃንን እንደሚሰጥም ነግሮታል (9፡35-37)፡፡ አሁን ደግሞ እርሱ ትንሣኤና ሕይወት እንደ ሆነ ለፋ አድርጎ ይገልጻል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ***ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ*** ሲል የእርሱን ማንነት የሚናገረው ልክ እግዚአብሔር ለሙሴ በዘጸ 3፡14 እንደተናገረው በአሁን ጊዜ «***ነኝ***» በማለት ነው፡፡ ያለና የሚኖር እግዚአብሔር ሁልጊዜም በአሁን ጊዜ ይናገራል፡፡ ማርታ እንድም ***ነበር*** በሚል በኃላፊ ጊዜ ወይም ***እንዲነሣ አውቃለሁ*** በሚል በወደፊት ጊዜ ትናገራለች፡፡ ኢየሱስ ደግሞ እኔ ***ነኝ*** ብሎ በአሁን ጊዜ ይናገራል፡፡ እርሱ የትናንትናና የወደፊት ብቻ ሳይሆን የአሁን (የዛሬ) ጌታ ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ***ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ*** ሲል ሁለት ትልልቅ ሃሳቦችን በአንድ ላይ እንመለከታለን፡፡

- አንደኛው፡- እኔ ትንሣኤ ነኝ፡- ማለትም ***የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል 11፥25***፡
- ሁለተኛው እኔ ሕይወት ነኝ፤ ***ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ 11፥26***፡

ስለዚህ በእርሱ የሚያምን የዘላለም ሞትን አያይም፡፡ አልዓዛር በኢየሱስ የሚያምን ነበር፤ ስለዚህ ቢሞትም በሕይወት ይኖራል፡፡ ማንኛውም አማኝ (የሞተውን ጨምሮ) ለዘላለም አይሞትም፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነቱና ሕያው ይሆናል፡፡ በዚህ አነጋገር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አይኖርም አላለም፡- ለሰው ሁሉ በሥጋ መሞት አለ፡፡ በሥጋ የሞተ በኢየሱስ ያመነ ከሆነ ለዘላለም በሕይወት ይኖራል፡፡ እርሱ ትንሣኤ ነውና ይነሣል፡፡ እርሱ ሕይወት ነውና የዘላለምን ሕይወት ይሰጠዋል፡፡

***11÷27 አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አኔ አምናለሁ።*** ይህ ትክክለኛ እምነትና መረዳት ነው። አይሁድ ሊቀበሉት ያልፈለጉት እውነት ነው። ጌታ ደቀ መዛሙርቱን «እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ?» ብሎ በጠየቀ ጊዜ ጴጥሮስ የሰጠው ትክክለኛው መልስ ይህን ***አንተ ... ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ*** ነህ የሚለውን ነው (ማቴ 16:16)።

እህትማማቹ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የነበራቸው መረዳት ታላቅ ነው። መልእክት ሲልኩበት፤ ወደ ሰፈር በመጣ ጊዜ ሲጠይቁት፣ ድንጋዩንም አንሱ ሲላቸው፣ የሚመልሱለት ጌታ ሆይ (11:3፤22፣33) በማለት ነው። እንዲሁም ኢየሱስ እርሱ፡- መምህር (11:28)፣ ክርስቶስ (11:27)፣ የእግዚአብሔር ልጅ (11:27) እንደሆነም ያምኑ ነበር።

***11÷32 ማርያምም ኢየሱስ ወዳለበት መጥታ በአየችው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ፡- ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜም ባልሞተም ነበር አለችው።*** እንደ ማርታ ሁሉ ማርያምም ***ወንድሜም ባልሞተም ነበር*** ስትል የአልዓዛር ጉዳይ አሁን ታሪክ ሆኗል ማለቷ ነው። ተመልሶ በሕይወት መኖር ይችል እንደሆነ አታውቅም። ኢየሱስ እንዲያስነሣውም አልጠየቀችም። የማርያም አጠያየቅ ቀደም ሲል በ11:22 ላይ ማርታ ኢየሱስን እንደጠየቀችው ቃል በቃል አንድ ዓይነት ጥያቄ ነው። ልዩነቱ በአቀራረብ ላይ አስቀድማ ***በእግሩ ላይ ወድቃ*** ነው። ይህ ትሕትና ያለበት አቀራረብ ነው። ከሀዘን ቦታ፣ ከለቅሶ ተነስቶ የመጣ ሰው የሚቀድመው ማልቀስ ነው፣ ማርያም ግን ያስቀደመችው በጌታ እግር ስር መውደቅን ነው። ከዚያ መጠየቅን ከዚያም ለቅሶዋን።

***11÷33 ኢየሱስም ... በመንፈሱ አዘነ በራሱም ታወከ።*** የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞም ፍጹም ሰው ነው። ስሜት አለው፤ ስሰው ያዝናል። ***ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ 11÷35***: ኢየሱስን እንዲያለቅስ ያደረገው ምናልባት የእነ ማርያም ሀዘንና ለቅሶ እንዲሁም አብረዋቸው ያሉት ሲያለቅሱ ስላየ በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚያስፈልገው ትልቅ ነገር ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ስሜት የሚያውቅ፤ ሀዘን የሚያሳዝነው፤ ከሰውም ጋር የሚያለቅስ እንደሆነ መገንዘቡ ላይ ነው።

በዚያ ቦታ የነበሩ አይሁድም የኢየሱስን ማልቀስ፣ እንባ ማፍሰስ ተረድተው፡- ***እንዴት ይወደው እንደ ነበረ እዩ 11÷36*** አሉ። የሚወደው አልዓዛር ስለ ሞተ፣ ስለዚያ ምክንያት ስሜቱ ተነክቶ



እንዳለቀሰ መሰሳቸው። ይህም ማለት ምናልባት ምነው ቀደም ብዬ ሳይሞት በደረስኩ ኖሮ፣ እይነት የጸጸት ለቅሶ እንደሆነ ያሰቡ ይመስላል። ኢየሱስ ግን አልዓዛር ከመሞቱ በፊት ያልመጣው ለደቀ መዛሙርት እምነት መጨመር ሲል እንደሆነ በ11÷14-15 ባለው ተመልክተናል። የሚደርገውን ቢያውቅም ያለቀሰው ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስሜታችንን የሚያውቅ፣ ሀዘናችንን የሚረዳ ፍጹም ሰው ስለሆነ ነው። እርሱ በሀዘናችን ከእኛ ጋር የሚሆን የውስጥ ስሜታችንን የሚያውቅ ነው።

***11÷37 አንዳንዶቹ፡- ይህ የዕውሩን ዓይኖች የከፈተ ይህን ደግሞ እንዳይሞት ያደርግ ዘንድ ባልቻለምን ነበርን? አሉ።*** የዕውሩን ዓይኖች እንደከፈተ በምዕራፍ ዘጠኝ አይተናል። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች የሚሉት በዕውርነት ላይ፣ ሥልጣን ስላለው ሰው እንዳይሞት ለማድረግስ ሥልጣን የለውምን? ማለታቸው ነው። ይህ የአንዳንድ ሰዎች አነጋገር ማርታና ማርያም ከነበራቸው አስተሳሰብ ጋር ተመሳሳይነት ይታይበታል። እንዳይሞት ማድረግ ይችል ነበር የሚለውን እንጂ አሁን ሊያስነሣው ይችላል የሚለውን ገና አልተገነዘቡም ነበር።

የማርታና የማርያም ሁኔታና የአልዓዛርም ከሞት መነሣት በዛሬው ዘመን ላለን ክርስቲያኖች ምን ትርጉም ይሰጠናል? ይህን የምናነበው እንደ አንድ ታሪካዊ ድርጊት ሳይሆን፣ ኢየሱስ ለምናምነው ሁሉ የዛሬም ጌታ መሆኑን እንድንገነዘብ ነው።

አልዓዛርን ያስነሣው ዛሬም በእኛ ሕይወት እንደ ፈቃዱ ተአምራትን ሊያደርግ ሥልጣን እንዳለው መገንዘብ ያስፈልገናል። እኛን እየወደደን እንደሚወደንም እያወቅን በጸሎትም እየለመንነው ለአንዳንድ ችግሮቻችን ፈጥኖ መልስ ላይሰጠን ይችላል፣ ይቆይብናል። ከዚህም የተነሣ ሁኔታዎች ተባብሰው ጉዳዮቻችን ያለቀላቸው፣ የሞቱ፣ የተቀበሩ ይሆናሉ። በእነዚያ ላይ እንዳይሞቱ ለማድረግ ወይም ወደ ሕይወት ለማምጣት ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ይቻለዋል።

ማርታና ማርያም እምነታቸው ያረፈው የተወሰኑ ሁኔታዎች ቢሟሉ ማለትም አልዓዛር ከመሞቱ በፊት ኢየሱስ ቢደርስ በሚል ላይ ነበር። በመካከል ግን ሞት ገባ። ስለዚህ እንደገና ሕይወት ሊሰጠው እንደሚችል አላወቁም። የማይቻል የሚመስለው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ተችሎታል። ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈጽሞ ተስፋ አይቆረጥም። እኛ እንደ ማርታና ማርያም ***ነበር***፣ ብንል እርሱ ደግሞ ***ነኝ*** ይላል። በመጻጻት ስለ ትናንት ብንናገር ኢየሱስ ክርስቶስ በሕያውነት ስለ ዛሬ ይናገራል።

***11+38 ኢየሱስም ደግሞ በራሱ አዝና ወደ መቃብሩ መጣ::*** ይህ በድጋሚ ኢየሱስ በሁኔታውና በሰዎች የተሰማውን ስሜቱን ይገልጣል:: ***አዝና*** እንደነበር ቀደም ሲል በ11÷33 ሳይም አይተናል::

***11+38 ወደ መቃብሩ መጣ፤ እርሱም ዋሻ ነበረ፤ ድንጋይም ተገጥሞበት ነበር::*** በዚያን ዘመን የነበሩ መቃብሮች አብዛኛውን ጊዜ ከዋሻ የሚሠሩና ድንጋይ የሚገጠምባቸው ነበሩ:: ጌታ ኢየሱስንም የቀበሩት በእንዲህ ዓይነት መቃብር ውስጥ ነው (ማቴ 27:60፤ ዮሐ 19:41):: ጌታ ወደ መቃብሩ ከመጣም በኋላ በዋሻው ላይ የተገጠመውን ድንጋይ፤ ***ድንጋዩን አንሡ 11+39*** አላቸው:: በዚህ ጊዜ ***ማርታ:- ጌታ ሆይ+ ከሞተ አራት ቀን[47] ሆኖታልና አሁን ይሸታል አለችው 11+39***: የማርታ አነጋገር በአንድ በኩል እውነትነት አለው:: ከሞተ ሰሰ ሰነበተ ሥጋውም መፍረስ ስለሚጀምር ሽታ ይኖረዋል:: ማርታ ግን ያላስተዋለችው ጌታ አስቀድሞ የተናገራትን ነው::

***11+40 ኢየሱስ:- ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርሁሽምን? አላት::*** የእግዚአብሔርን ክብር ስለ ማየት በድጋሚ ነገራት:: የመጀመሪያ የምትወደው ታማሚ ብለው መልእክት በላኩ ጊዜ የጌታ መልስ:- ***ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው 11:4*** ብሎ ነበር:: ሆኖም የእግዚአብሔር ክብር የመገለጫው መንገድ በየት በኩል እንደሆነ ማርታ አላስተዋለችም:: አልዓዛር ከመሞቱ በፊት ኢየሱስ መጥቶ ከሕመሙ ቢያስነሣው አንዱ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ መንገድ ነው:: እንደ ሞተና ከመቀበሩ በፊት ደርሶ ቢያስነሣው ይህም ሌላ መንገድ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የመረጠው እግዚአብሔርን የማክበሪያ መንገድ ግን አልዓዛር ከሞተና ከሸተተ በኋላ ትንሣኤ መስጠትን ነው::

***11+41-42 አባት ሆይ+ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ:: ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ::*** አምስት ሺህዎችን ሰዎች ሲመግብ ጌታ አመሰግኖ ነበር:: አሁንም አልዓዛርን ከማስነሣቱ በፊት እግዚአብሔርን ያመሰግናል:: እግዚአብሔር አብ እንደሚሰማው ኢየሱስ እርግጠኛ ነበረ:: የሚሰማውም ሁልጊዜ ነው::

[47] ጌታ ወደ ቢታንያ በመጣ ጊዜ አልዓዛር ከሞተም አራት ቀን ሆኖት ነበር (11+39):: በሌላ በኩል ሁለት ቀን ዋለ (11:6) ይላልና አራት ቀን የሆነው እንዴት ነው? የሚል ሀሳብ ሊኖር ይችላል:: ይህ ሲታሰብ መልእክተኞቹ ጌታ ወዳለበት ለመምጣት አንድ ቀን ወስዶባቸው ቢሆን፤ ከዚያም ጌታ በቆየበት ቦታ ሁለት ቀን ከዋለ፤ እርሱ የመጣው በአራተኛው ቀን ነው ማለት ነው:: ስለሆነም አልዓዛር የሞተው እህቶቹ ወደ ኢየሱስ መልእክት ከላኩ በኋላ ምናልባት ወዲያው ሊሆን ይችላል::



***አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ 11÷42***: ጌታ የሚያደርገውን ሁሉ ያደርገው የነበረው ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች ጥቅም ነው:: የሰዎች ጥቅም ማመናቸው ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነና በእርሱ እንደተላከ እንዲያምኑ ነው:: ይህን ሲያምኑ ይጠቀማሉ የዘላለምን ሕይወት ያገኛሉ:: ስለዚህ ይህን ማለቱ ለእኛ ጥቅም ወይም ***በዚያ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ 11+42*** ጥቅም ነው::

***11+43 አልዓዛር ሆይ÷ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ::*** የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ለሙታን ሕይወትን ይሰጣል፤ ሙታንም የእርሱን ድምፅ ይሰማሉ:: ጌታ:- እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው (5÷25) እንዳለ:: የሞተውና አሁን ይሸታል የተባለው አልዓዛር የኢየሱስ ክርስቶስን ድምፅ ሰማ:: ኢየሱስ ሲናገር የሞተው ስሙንም ያውቃል፤ ሲጠራም ይሰማል፤ የታዘዘውንም ያደርጋል:: የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ሕይወት ይሰጣልና:: ስለሆነም የሞተውን አልዓዛርን ***ወደ ውጭ ና*** ብሎ ይጠራዋል:: በዋሻው የተገጠመውን ድንጋይ ደግሞ ሰዎችን አንሱት ብሎ ያዛቸዋል:: ጌታ ለድንጋዩም ቢናገር ድንጋዩ በራሱ ከዋሻው በር በተነሣ ነበር:: ነገር ግን በጌታ አሠራር ለሰዎች እምነትና ጥቅም እንዲሆን፤ በተአምር አሠራር ውስጥ ሰዎችም ድርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ ያለዚያ ሁሉንም ነገር ራሱ በራሱ ቢሠራው ይችላል::

***11÷44 የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበረ::*** አልዓዛር የወጣው ልክ ሰዎች ወደ ዋሻው ባስገቡት ሁኔታ ነው:: ወደ ዋሻው አስገብተው ለመቅበር ብዙ ሰዎች በሥራው እንደ ተካፈሉ መገመት ይቻላል:: ከመቃብሩ በሚወጣበት ጊዜ ግን ያገዘው፤ ያንቀሳቀሰው የለም:: ያወጣው የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ብቻ ነው:: እንዲሁም ከአለበት ዋሻ ሲወጣ በአየር ላይ ተንሳፎ መውጣቱን ልብ ማለት ይጠቅማል::

በአንድ ጊዜ እየሆነ ያለው ብዙ ተአምር ነው:: የሞተው የራሱን ድምፅ ሲጠራ መስማቱ፤ የሞተው ሰው በእግሩ ሳይሆን በመንሳፈፍ ወደ ውጭ መውጣቱ፤ የተፈጥሮ ሕግን ሽሯል:: የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ነውና:: ወደ ውጭ በመጣ ጊዜ የእልዓዛር እጆችና እግሮች ተገንዘዋል፤ ፊቱም በጨርቅ ስለ ተጠመጠመ አያይም፤ ነገር ግን ወደ ታዘዘው ቦታ መጣ::

***11÷44 ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው::*** ቀደም ሲል ኢየሱስ ***ድንጋዩን አንሡ 11÷39*** እንዳለ አሁን ደግሞ ፍቱት ይላል:: ከመቃብሩ ወደ

ውጭ እንዲወጣ ያዘዘው ጌታ፣ በዚያው የትእዛዝ ቃል እንዲፈታ ማድረግ ለእርሱ ቀላል ነው። ነገር ግን የጌታ አሠራር ሁሉን ሊያደርግ በሚችለው ተግባር ውስጥ በምሕረቱ ሰዎች አብረውት እንዲሠሩ ድርሻም እንዲኖራቸው፤ በኋላም ለእርሱ ምስክር እንዲሆኑ ያደርጋል። አልዓዛርን የፈቱት ምናልባት አስቀድመው የገነዙት ሰዎችም ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህም ለእነርሱ ተጨማሪ ማስረጃ ይሆናቸዋል።

የአልዓዛር መነሣት ኢየሱስ የሞተን ሰው እንደሚያስነሣ ብቻ ሳይሆን፣ የፈረሰንም ገላ እንደገና ሕይወት እንደሚሰጠው ያሳያል። ከዚህ ታላቅ ተአምር የተነሣ አይሁድ ሁሉ «ግልብጥ ብለው» በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያምኑ ማሰብ ቀላል ነገር ነው። ነገር ግን የሆነው እንዲህ አልነበረም። በጌታ ያመኑ ቢኖሩም ሊገድሉት የሚፈልጉ ደግሞ ነበሩ።

***11፥45 ከአይሁድ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን፡-*** ጌታ ሲያስተምር ሰው ምርጫ ቢስ (መሐል ሰፋሪ) ሆኖ አይቀርም። ከሁለት አንዱን ይመርጣል - ወይ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናል ያለዚያ የእርሱ ጠላት ሆኖ ይቆማል። ለማመን የማይወስን ሰው ከአመኑት ጋር አይቆጠርምና። ይህ በወንጌል በተደጋጋሚ የምናየው ሁኔታ ነው። ፈሪሳውያን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማጥመድና ለመግደል አጥብቀው ምክንያት ይፈልጉ ነበር (8፥37፣40፤ 12፥1)። ***ሸንጎ[48] ሰብስበው 11፥47*** ተመካከሩ።

***11፥47 የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ሸንጎ ሰብስበው፡- ምን እናድርግ? ይህ ሰው ብዙ ምልክቶችን ያደርጋልና፡-*** በማለት ይመካከራሉ። ማንም ሊሸሽገው የማይችል ምልክት በመደረጉ ከዚህ ምልክት የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምነው መቀበል ሲገባቸው እነርሱ ግን አሁንም በቅንዓት ተውጠዋል። እውነትን ለመሸፈን አሁንም ይጣጣራሉ።

አይሁድ የኢየሱስ ክርስቶስን መሲሕነት ለማረጋገጥ ምን ምልክት ታደርጋለህ? እያሉ ይጠይቁት ነበረ። ጌታ ደግሞ በተደጋጋሚ ምልክቶችን ያደርጋል፣ አድርጓል። ምልክቶቹ የሚያሳምኑ እንደሆኑ ግን ፈሪሳውያን ሳይቀሩ፣ ***ብዙ ምልክቶች ያደርጋል 11፥47*** በማለት

[48] The Sanhedrin wes the highest ruling leading authority among the Jews in Judea. It was composed of seventy-one members: The high priest presiding over seventy religious leaders; the majority of whom were Sadducees and the minority, Pharisees. Ibid. p.238



ይናገራሉ። ሆኖም እንደጠየቁት ምልክቶችን ካዩ በኋላም አይሁድ ሁሉ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አላመኑም።

***11፥48 ሁሉ በእርሱ ያምናሉ፤ የሮሜም ሰዎች መጥተው አገራችንን ወገናችንንም ይወስዳሉ፡-*** እነርሱን ያሰጋቸው ሁለት ነገር ነው።

- አንደኛ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ምልክት በማድረግ ከቀጠለ ፈሪሳውያንን የሚከተል ሕዝብ ሳይኖር ነው፤ ስለዚህ ለእነርሱ ክብርና ሞገስ ሊጐድልባቸው ነው።

- ሁለተኛ ደግሞ በዚያን ወቅት በሮም ቅኝ ግዛት ሥር ስለ ነበሩ ያስፈራቸው አንድ ሰው ብዙ ተከታዮች አፍርቶ ከተነሣ ምናልባት የሮም አለቆች በአይሁድ ላይ መከራ ሊጨምሩብን ይችላሉ የሚል ሥጋት ነው። ይህም ምናልባት ይህ ሰው በሮም አገዛዝ ላይ ተቃውሞ ቢያስነሣ በሕዝቡ ላይ መከራ ሊጨምር ይችላል የሚል አስተሳሰብ ወይም ሽፋን ይዘው ነው።

ፈሪሳውያን ይህን ምክንያት ያቅርቡ እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚጠበቀው መሲሕ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ካመኑ ይመጣብናል ብለው ለሰጉበትም ችግር አብሮ መፍትሔ እንዳለው በተገነዘቡ ነበር። ስለሆነም እነርሱን ያሳሰባቸው ዋና ነገር የቦታቸው ጉዳይ፣ የክብራቸው ጉዳይ፣ ተከታይ የማጣታቸው ጉዳይ ነው።

***11፥49 በዚያችም ዓመት ሊቀ ካህናት የነበረው ቀያፋ፡- ያቺ ዓመት***[49] ኢየሱስ ክርስቶስ የተያዘባትና የተገደለባት ዓመት ናት።

***11፥50 ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፉ አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ ይሞት ዘንድ እንዲሻለን አታስቡም አላቸው።*** የሊቀ ካህናት ቀያፋ አባባል በአይሁድ ሕዝብ ላይ ችግር ከሚመጣ ***አንድ ሰው*** ቢሞት ይሻላል ለማለት ነው። ይህን ሲናገር ቀያፋ የታየው ነገር ያለውን ሥርዓት አስጠብቆ ማቆየት ነው። አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል የሚል ሀሳብ ያቀረበው የቆየውና እነርሱ የተቀበሉት የፈሪሳውያን ሥርዓት ከሚናጋ ማለቱ ነበረ። እርሱ

[49] Since Caiaphas served as a high priest for eighteen years (A.D. 18 to 36), the expression *that year* refers to that one year in which Jesus was crucified. The office of higher priest was originally instituted by God to be a life time position (Num 35:25); but the Romans did not want any one person to become too powerful, so they appointed high priests and placed a new one in a position whenever they wanted. Ibid. p.240.

ባያውቀውም በዚህ ንግግሩ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚፈጸም እውነት ነገር ተናገረ:: *ይህንም የተናገረ ከራሱ አይደለም፤ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ነበርና ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ ሊሞት እንዳለው ትንቢት ተናገረ 11፥51*::

ቀያፋ የሚናገረውን በማስተዋል አልተናገረም፤ በማመንም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አልተናገረም:: ካሰበት የኃላፊነት ቦታ የተነሣ ግን ይህ መልእክት (*ትንቢት*) በውስጡ አለፈ:: ከፈሪሳውያን አንዱ የሆነው ቀያፋ የተናገረው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲገደል በመወሰን ነው:: በውስጡ የተላለፈው መልእክት (*ትንቢት*) ግን በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምክንያት ብዙዎች እንደሚድኑ፣ ለብዙዎች የዘላለም ሕይወት እንደሚገኝ ትንቢት መናገሩ ነበር:: የተናገረው በኃጢአት ወይም በአመፅ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን በእርሱም ንግግር በኩል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሌሎች ለሰዎች ምትክ ሆኖ እንደሚሞት ማመልከቱ ነበር::

*41፥52 ስለ ሕዝቡም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች ደግሞ በአንድነት እንዲሰበስባቸው ነው እንጂ::* ከዚህ ትንቢት የምናስተውሰው:-

1. የኢየሱስ ሞት *ሕዝቡን (እስራኤልን)* ከመንፈሳዊ ሞት ለማዳን መሆኑን፤

2. በእርሱ ሞት ምክንያት የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሁሉ እንደሚሰበሰቡ ሲያመለክት ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ከአይሁድም ከአሕዛብም የሆኑ ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ::

*11፥53 ከዚያ ቀን ጀምረው ሊገድሉት ተማከሩ::* ሊገድሉት ውሳኔ ያደረጉት ሊቀ ካህኑ ቀያፋ በሰጠው ሃሳብ መነሻነት ነው:: እርሱን ለማጥመድ ምክንያት ሲፈልጉበት ቆይተዋል:: ብዙ ጊዜ ሊይዙት ሞክረው የእግዚአብሔር ጊዜ ስላልደረሰ ጌታን ሊይዙት አልቻሉም ነበረ:: አሁን ለመግደል ተማከሩ:: ጊዜውም እየተቃረበ መጥቷል:: በዚህም ምክራቸው ምክንያት፣ *ኢየሱስ በአይሁድ መካከል ተገልጦ አልተመላለሰም 11፥54*:

*11፥54 በምድረ በዳ አጠገብ ወዳለችው ምድር፥ ኤፍሬም ወደምትባል ከተማ ሄደ፤ በዚያም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ::* ቀደም ሲል ወደ ይሁዳ ሲመጣ፣ አይሁድ ሊገድሉት እንደሚፈልጉ ቶማስ ተናግሮ ነበረ (11:8):: በአልዓዛር ከሙታን መነሣት ምክንያት አይሁድ



ለመግደል የነበራቸው ፍላጐት ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ጌታም በዚህ ውሳኔአቸው ምክንያት ጊዜው እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ በዚያ ኖረ:: *የካህናት አለቆችም ፈሪሳውያንም ይይዙት ዘንድ እርሱ ያለበትን ስፍራ የሚያውቀው ሰው ቢኖር እንዲያመለክታቸው አዘው ነበር 11፥57*፡ በዚህ ትእዛዝና መጠባበቅ ሁኔታ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣል፤ በኢየሩሳሌምም በፋሲካ በዓል ላይ ይገኛል::

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

በምዕራፍ አሥራ ሁለት በአንድ በተዘጋጀ የእራት ግብዣ ላይ ማርያም የጌታን እግር ሽቱ ቀብታ በጠጉሯ ስታብስ እንመለከታለን:: ይህ የእራት ግብዣና እግሩንም በሽቱ መቀባት የሆነው ብዙዎች አይሁድና ፈሪሳውያን ኢየሱስን ሊገድሉት በሚፈልጉበት ጊዜ ነው:: ጌታን የሚያሳድዱትና ሊገድሉትም የሚፈልጉ ብዙዎች በሆኑበት ሁኔታ ጥቂቶች ደግሞ እርሱን ያወቁ፣ የሚወዱት፣ የሚከተሉት የሚጋብዙትና ለመቃብሩ ያዘጋጁት የነበሩ ነበሩ::

***12፥1 ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን፡-*** ይህ የፋሲካ በዓል ጌታ በምድር ሳለ የሚያከብረው የመጨረሻው የፋሲካ በዓል ነው::

***12፥1 ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ::*** ቢታንያ በኢየሩሳሌም ከአራት ኪሎ ሜትር በማይበልጥ ርቀት ላይ የምትገኝ ቦታ ነች:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛርን ካስነሣው ጥቂት ቀናት ወይም ሳምንታት ብቻ ሆኗል:: የአልዓዛር መነሣት ገና ትኩስ ዜና ነው:: ይህም ምልክት ብዙ አይሁድ በኢየሱስ እንዲያምኑ ምክንያት ሆኗል:: በሌላ በኩል የአይሁድ አለቆችን ግን አስቆጥቷቸዋል:: ስለዚህም እስከ ጊዜው ድረስ ጌታ ኢየሱስ ቢታያን ለቆ ወደ ኤፍሬም ከተማ ሄዶ ነበር (11:53-54):: አሁን ወደ ኢየሩሳሌም ለፋሲካ በዓል ሲሄድ በቢታንያ በኩል አለፈ::

***12፥2 በዚያም እራት አደረጉለት፤ ማርታም ታገለግል ነበር፤ አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ::*** ይህ እራት የት እንደተደረገ በዚህ ክፍል ውስጥ አልተገለጸም:: ከማቴ 26:6-13 እና ከማር 14:3-9 ባሉት ክፍሎች ማገናዘብ እንደምንችለው ይህ እራት የተደረገው በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል:: ስምዖን ከለምጹ ስለ ነፃ በዚህ ደለታ ከሞት የተነሣውን አልዓዛርንም ከእነ እህቶቹ ጠርቶ ለጌታ እራት ማድረጉ ይሆናል::



***12፥3 ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤[50] በጠጉርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ::*** ይህ ሽቱ ጥራቱ ከፍተኛ ነው:: ደግሞም ሽቱው ውድ ነው:: እንዲህ ዓይነት ሽቱ በዚያን ዘመን ነገሥታት የሚቀቡት ዓይነት ውድ ሽቱ[51] ነው:: ማርያም ሽቱ ከመግዛትና በጌታ እግር ላይ ከማፍሰስ አልፋ ***በጠጉርዋም እግሩን አበሰች::*** «ሰዎች ስለማቀርበው ሽቱ ምን ሀሳብ ይኖራቸው ይሆን?» ብላ አስቀድማ ብትጠይቃቸው ኖሮ ምናልባትም ባልገዛችው ከገዛቸውም የጌታን እግር በጠጉሩዋ ባላበሰችው ነበር::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለጌታ የሚያቀርቡት ስጦታና የሚፈጽሙት ድርጊት ከተለያየ ዓላማ አንጻር በሌሎች ዘንድ የከበረ ተደርጐ ላይቆጠር ይችላል:: መለኪያው መሆን ያለበት ይህን የማደርገውን ነገር የማደርገው ለጌታ ክብር ነውን? እርሱስ ይቀበለዋልን? እንጂ ሰዎችን ለማስደሰትና ተቀባይነት ለማግኘት ከሆነ መለኪያው «ምድራዊ» ነው::

***12፥4-5 ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ፡- ይህ ሽቱ ስሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው? አለ::*** ከማቴ 26፥8 እና ማር 14:4 እንደምንገነዘበው ይሁዳ የተናገረው ምናልባት በሌሎችም ደቀ መዛሙርት ውስጥ የነበረ ሀሳብ ይመስላል:: ይሁን እንጂ ሌሎቹ ለድሆች በእርግጥ በማሰብ እና በመቆርቆር የጠየቁት ሊሆን ቢችልም የይሁዳ ሀሳብ ግን በምን ላይ እንደ ተመሠረተ ተገልጧል:: ማርያም ያደረገችው ሽቱ መቀባት በቤት ሳሉት ሁሉ የታወቀ ሆነ፤ ሽቱው ቤቱን ሁሉ ሞልቶታልና:: በቤት ያሉት በሽታው ደስ ይሳቸዋል (ከይሁዳና ከአንዳንዶች በስተቀር)::

ይሁዳ ገንዘብን በሚመለከት ድካም የነበረበት ሰው ነው:: ለዚሁ ጉዳይ የተሾመ ገንዘብ ያዥ ሆኖ እያለ ገንዘብን የሚሰርቅ፤ ይህም በውስጡ አድጐበት በኋላ ጠልፎ የጣለው ኃጢአት ነው:: ***ይህ ሽቱ ስሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው?*** ብሎ ሲናገርም እየዋሸ ነበረ:: የሚዋሸው በራሱ ማንነት ላይ ነው:: በልቡ ሌላ ሆኖ እያለ በምላሱ ተቃራኒውን የሚናገር ሰው መሆኑ ነው:: የሐሰት አባት

[50] ይህ ሽቱ መቀባት በማቴ 26፥6-13 እና በማር 14፥3-9 ከተገለጠው ጋር ይስማማል:: በሉቃ 7፥36-50 ከተገለጠው ጋር ግን ጥቂት ልዩነት አለው:: በሉቃስ የተገለጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በጀመረበት ጊዜ አካባቢ እንደሆነ ይገመታል:: አሁን በዮሐንስ አሥራ ሁለት የምናየው ግን በአገልግሎቱ የመጨረሻ ሳምንት የተደረገ ነው::

[51] Nard was used to annoint kings; Mary may have been annointing Jesus as her kingly Messiah. Ibid. p.247.

የሆነው ዲያብሎስ በእንዲህ ዓይነቱ ሰው ስመጠቀም ይቀሰዋል። ውሸትን በራሱ እስተናግዷልና የውሸት አባትም መሣሪያ ያደርገዋል።

በዚህ ድርጊት መጠየቅ የነበረበት ሽቱው ሰንት ያወጣል? ሳይሆን በመደነቅ ሰው ሰኢየሱስ ያሰውን ፍቅርና አክብሮት እንዴት ይገልጸዋል የሚል መሆን ነበረበት። ማርያም አክብሮቷን የመግሰጫ መንገድ በእግሩ ላይ ሽቱን ማፍሰሰና በጠጉርዋም ማበስ ነው።

ከማርያም ድርጊት ሰሰ ገንዘብ አጠቃቀም ትምህርት እናገኛሰን። ይህ በጌታ እግር ላይ የፈሰሰው ሽቱ የተገዛው ***ለሦስት መቶ ዲናር*** በብዙ ዋጋ ነው። ይሁዳ ግን ጌታውን አሳልፎ የሰጠው በሰላሳ ብር ብቻ ነው። በውድ ዋጋ የክበረ ሽቱ ተገዝቶ በጌታ እግር ሥር ማፍሰስ በገንዘብ አጠቃቀም ላይ ሰው ሊያደርገው የሚገባ ትልቅ ነገር እንደሆነ ያሳያል። ይህም ባሰን ነገር ሁሉ እርሱን ማክበር ማሰት ነው። አሰን የምንሰውን ገንዘብ፣ ጊዜ፣ እውቀትና ሌላም የክበረ ነገር ሁሉ በጌታ እግር ሥር ማድረግ፣ ሰጌታም ክብር ማዋል ትክክሰኛ የሀብት አጠቃቀም ነው።

በዚህ ክፍል ውሰጥ (ቁ. 2-4) ማርታ፤ እልዓዛር፤ ማርያምንና ይሁዳ ተጠቅሰዋል።

***ማርታ*** ሌላም ጊዜ እንዳደረገችው (ሉቃ 10፥38-42) ሰማገልገል ተነሣች። ራሷን ሰማገልገል የሚገባት እድርጋ የምትቆጥር ሴት ልትሆን ትችላሰች። ማገልገሉ ይልቁንም ኢየሱስን ማገልገል እጅግ የከበረ ተግባር ነው። ግን ከማርያም አንጻር ማርታ የሚጐድላት ባሕርይ እንዳለ በግልጽ ይታያል። ጉድለቷም ከአገልግሎቷ በፊት መስማት፣ መማር እና ሰጌታ የሚገባውን አክብሮት መግሰጽ ይቀድም እንደ ነበረ ልብ አሰማሰቷ ነው።

ይህ እራት የተደረገው ሰጌታ ክብር ሆኖ፣ እልዓዛርም አብሮ በእራት ላይ እንደተቀመጠ እናያሰን። ***አልዓዛር*** ከጌታ ጋር በማዕድ መቀመጡ ጌታን ምን ያህል ይወደው እንደ ነበረ የሚያመሰክት ነው።

***ማርያም*** በጌታ ያሳትን እምነትና ታላቅ አክብሮት ሽቱ በመቀባት ትገልጣሰች። ሰሴት ጠጉሯ ክብሯ ሆኖ እያሰ (1ቆሮ 11፡14-15)፣ በዚያ ክብሯ በሆነው ጠጉር የጌታን እግር ታብሰ ነበር። ብዙ ዋጋ በመክፈል እምልኮን ሰግደትን ሰጌታ ማቅረብ የምታውቅ ሴት ነች።

በዚህ እራት ላይ የተገኘ ***የአሰቆሮቱ ይሁዳ*** በጥያቄ መሰል አቀራረብ ማርያም የምታደርገውን ይቃወም ነበር። ዮሐንስ የይሁዳን አባባል



ከምን የተነሣ እንደሆነ ባይገልጽ ኖሮ ከአሥራ ሁሰቱ አንዱ የሆነው ደቀ መዝሙር ያቀረበው ሀሳብ ሰድሆች የሚያስብና የሚቆረቆር ታላቅ «መንፈሳዊ» ሰው ባስመሰለው ነበር። ሰድሆች ማሰብ ተገቢ ሆኖ እያሰ ይሁዳ ያንን ያሰው ***ሌባ ስለ ነበረ*** እንደሆነ መገሰጡ፣ ቃልና ልብ የተሰያዩበት ሰው እንደሆነ ያሳያል። ይሁዳ ማርያምን አባካኝ አድርጐ ገምቷታል፤ ማባከንስ ወደ ከረጢት ከሚገባው መስረቅ ነው።

በአጠቃላይ እልዓዛር፣ ማርያምና ማርታ እንዲሁም የአሰቆሮቱ ይሁዳ ሰኢየሱስ ቅርብ ከሆኑ እርሱንም ከሚከተሉ ሰዎች መካከል ነበሩ። ይሁን እንጂ ሰኢየሱሰ ያሳቸው አመሰካከትና ቀረቤታ ከተሰያየ ዓላማ አንጻር መሆኑን እናሰተውላሰን። ከቅርብ ተከታዮቹ መካከል ጌታን አሳልፎ ስመሰጠት የተዘጋጀ ይሁዳም ነበረና።

ስለዚህ ከኢየሱስ ክርሰቶሰ ጋር አብሮ መውጣትና መግባት፣ ሰእርሱም ቅርብ ሆኖ መገኘት በራሱ በቂ እይደሰም። ያ ቀረቤታ በውስጥ ካሰ የልብ ሀሳብና በረጅም ጊዜ ከሚደረግ «የስሌት እንቅስቃሴ» አንጻር መታየት ይኖርበታል። በተከፋፈሰ ልብ እና በእንቢተኝነትም መሄድ ይቻላል። እንደ ይሁዳ መጨረሻው የማያምር ጉዞ ሊኖርም ይችላል።

***12፥6 ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም።*** በሰው ዘንድ ሰድሆች መልካም አሳቢ መምሰል በውስጠኛው ልብ ግን በክፋትና መርዝ የተያዘ (ሐዋ 8:23፤ ዕብ 12:15) ሰው መሆን እንዲህ ዓይነት የይሁዳ ባሕርይ (የአሰመሳይነት ሕይወት) ዛሬም በጌታ ደቀ መዛሙርት መካከል እንዳይገኝ መጠንቀቅ ይኖርብናል። ይህንን ደግሞ ማን ያውቃል? ልብን የሚያውቅ እግዚአብሔር ግን ሰውን ሁሉ ይመዝናል። እግዚአብሔርን በንግግር ብዛት እና በጥሩ ቃላት ማታሰል አይቻልም።

ይሁዳ ሰድሆች ርኅራኄ የሌሰው ሌባ ሰው ነው። ከከረጢት የሚሰርቅ ሰው ሰድሆች ሊራራ አይችልም። የሚያሰደንቀው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ የይሁዳን ማንነት (ሌባ መሆኑን) እያወቀ ገንዘብ ያዥ ማድረጉ ነው (13፡29)። ጌታ ሰሰው ሁሉ በተሰጠው ጸጋ (ወይም በችሎታው) እንዲሰማራና እንዲያገለግል ዕድል ይሰጠዋል። እግዚአብሔርን በመፍራት በተሰጠው መስመር ታማኝ ሆኖ መገኘት ደግሞ ከዚያ ሰው ይጠበቃል። ባይሆን እንድ ቀን ይገሰጣል። የጌታ ጻድቅነት ሰሰው ሁሉ እድልን መሰጠቱ፣ በርንም መክፈቱ ነው።

አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እስተያየትና ትችት የሚሰጡ ሰዎች በውስጣቸው በሌላ ዓላማ የሚገፋፉ ሊሆኑ ይችላሉ። በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ አብረው የማይሰሩ፣ ስለ ተሠራው

እስተያየት ለመስጠትና ለመተቸት ግንባር ቀደሞች ሊሆኑ ይችላሉ:: እግዚአብሔር ከእንዲህ ዓይነት የአስመሳይነት ሕይወት ይጠብቀን::

*12፥7-8 ኢየሱስም:- ለምቀበርበት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ::* ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም የሚሄድበት ጊዜ ደርሷል:: ማርያም ይህን የናርዶስ ሽቱ መቀባቷ ለመቃብሩ እንደማዘጋጀት ነው (ማቴ 26፥12፤ ማር 14፥8):: ጌታ ከሞተ በኋላ ኒቆዲሞስና የአርማትያው ዮሴፍ የኢየሱስን ሰውነት በሽቱ ቀብተዋል (ዮሐ 19፥39):: ስለዚህ ማርያም የጌታን እግር በሽቱ መቀባቷ ለመቃብሩ እያዘጋጀች ነው ማለት ነው::

እዚህ ላይ *ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና* ብሎ ጌታ የተናገረው ግድ የለም ድሆችን ችላ በሏቸው ማለቱ አይደለም:: ይህ ፈጽሞ አይደለም:: ይሁዳን ጨምሮ ሌሎች የጌታ ደቀ መዛሙርት ሁሉ በየቀኑ ድሆችን የሚረዱበት ብዙ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች እላቸውና በእነዚያ ሁኔታዎች ተጠቅመው ድሆችን ሊረዷቸው እንደሚችሉ፤ ጌታን ግን የሚያገኙት አሁን ብቻ መሆኑን ሲገልጽላቸው ነው::

ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን መውደድና አክብሮት እንዴት እንግለጽለት? ማርያም ብዙ ዋጋ የሚያወጣ ሽቱ ገዝታ በኢየሱስ እግር ላይ ማፍሰሷ በሰዎች ዘንድ የተወደደ ነገር አልነበረም:: ጌታ ግን ተቀብሎታል፣ ለመታሰቢያም እንደሚሆን ተናግሯል (ማር 14፥9):: በዛሬውስ ዘመን ሕያው የሆነውን ኢየሱስን ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ያለውን ጌታን እንዴት እናክብረው? አክብሮታችንንስ እንዴት እንግለጽለት? ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ብሎ ያዘዘንን ጌታ በመታዘዝና በተሰማራንበት ቦታና መስክ ሁሉ በታማኝነት በማገልገል ለእርሱ ያለንን ፍቅርና አክብሮት መግለጽ እንችላለን:: መታዘዝ መስቀል መሸከም ስለሆነ ዋጋ ያስከፍላል::

*12፥10-11 የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ፥ ከአይሁድ ብዙዎች ከእርሱ የተነሣ ሄደው በኢየሱስ ያምኑ ነበርና::* ጌታ ምልክቶችንና ተአምራትን ያደርግ የነበረው እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሰዎች እንዲያውቁና ሕይወት እንዲሆንላቸው ነበረ:: ይህ የገባቸው በአልዓዛር ከሞት መነሣት ምክንያት የኢየሱስን ማንነት ተረድተው በኢየሱስ ያምኑ ነበረ:: የካህናት አለቆች ይህ አላስደሰታቸውም፤ ይልቁንም ከተለያዩ ሀገሮች አይሁድ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጡበት ጊዜ በመሆኑ የኢየሱስ ዝና



ይበልጥ የሚወጣበት ጊዜ እንደሆነ አለቆቹ ፈርተዋል:: ስለዚህ አልዓዛርንም ጭምር ለመግደል ፈለጉ::

ከሕግ መርምረው በማግኘት የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት መገንዘብ የነበረባቸው የካህናት አለቆች፤ የሕግ አዋቂዎች ፈሪሳውያን ነበሩ:: ምክንያቱም መጻሕፍት ስለ ኢየሱስ ይመሰክራሉና (5:39):: ብዙ አይሁድ ለእነርሱ የነበራቸውን ታማኝነት እየተዉ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ነበርና ሊገድሉት ፈለጉ (11፥50-53)::

ለመሆኑ አይሁድ ለካህናት ታማኞች የሚሆኑላቸው ለምንድን ነው? የካህናት ተግባር የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል ነው:: አይሁድ ለካህናት ታማኞች ሆኑ ማለት ለእግዚአብሔር ታማኞች ሆኑ ማለት መሆን ነበረበት:: ካህናት ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡ፣ መንገድን የሚያሳዩ ፈቃዱን የሚገልጡ ስለሆኑ እግዚአብሔርን ለሕዝቡ የሚያስተዋውቁ መሆን ነበረባቸው:: እነኚህ ካህናት ግን የተዘረጋ ጃንጥላ የያዘውን ሰው በእርሱ ትይዩ ያለውን ሰማይ እንዳያይ እንደሚሸፍነው እንዲሁ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዳያይ፣ ወደ እርሱም እንዳይቀርብ መጋረጃዎች ሆነው ነበር:: አሁን ይህን ጃንጥላ የሚገለብጥና የሚያስወግድ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ መስመሩ ሲከፈት እነዚያ እረፍት አላገኙም:: ለዚህም ኢየሱስንና ምስክር የሆነውን አልዓዛርንም ጭምር ሊገድሉ ይወስናሉ::

አንድ ኃጢአት ወደ ሌላው ይመራል:: የይሁዳ ሌብነት ኢየሱስን እንዲሸጠው እንዳደረገው ሁሉ የካህናት አለቆች ኢየሱስን አለመቀበል እርሱንና አልዓዛርንም እንዲገድሉት እስኪስማሙ ድረስ ወሰዳቸው:: አልዓዛርን ሊገድሉት የፈለጉት ምንም ስላደረጋቸው ሳይሆን፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣንና ኃይል ሕያው ምስክር በመሆኑ ነው:: ሕጉማ አትግደል ይላል:: ካህናት ግን ለመግደል ይስማማሉ::

*12፥12-13 ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ በሰሙ ጊዜ:- የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡና:- ሆሣዕና፤ በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው እያሉ ጮኹ::* አይሁድና የካህናት አለቆች ኢየሱስን ሊገድሉት እያሰቡና እየተዘጋጁ ባሉበት ወቅት ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ ሁኔታ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ:: የአልዓዛርን መነሣት ያዩ (የሰሙ) ሰዎች ለሌሎች ይናገሩ ስለ ነበረ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማየት ብዙዎች ወደ ኢየሩሳሌም ተሰብስበው ነበር::

በቢታንያ እራት ካደረጉለት በኋላ በሚቀጥለው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጥ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ:: ፋሲካ ቀርቦ ስለ ነበረ ብዙ አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም እየመጡ ነበረ:: ከተለያዩ ሀገሮች የሚመጡ አይሁድ

መንገዱን ሁሉ ያጣብቡታል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱም ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም እየመጣ ነው:: ሌሎች ደግሞ የእርሱን መምጣት አውቀው *የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ* መያዛቸው ታላቅን ሰው ለመቀበል የሰላምና የደስታ ምልክት ማድረጋቸው ነው:: *ሆሣዕና* ማለትም እግዚአብሔር ይክበር፣ እግዚአብሔር ይመስገን እንደማለት ነው:: አይሁድ እግዚአብሔርን አያመሰገኑ ደስታቸውን የገለጡት ለእስራኤል ንጉሥ ንጉሥ አገኘን ብለው ነው:: በእነርሱ ስሌት ይህ የእስራኤል ንጉሥ ከነበሩበት ቅኝ ግዛት ነፃ የሚያወጣቸው እንደሆነ ስላሰቡ ደስታቸው ትልቅ ሆኗል:: ይህንም ከመዝ 118÷25-26 እና ሶፎ 3÷15 እንዲሁም ቀደም ሲል ዮሐ 1÷49 ከተጻፈው ጋር አዛምደውታል::

እነዚህ አይሁድ እግዚአብሔርን የሚያከብሩት ንጉሥ ስለ ሰጣቸው መሆኑ እስከዚህ ድረስ ትክክል ሆነው ሳሉ፤ የተሰጣቸውን ንጉሥ የመንግሥቱን ምንነት ግን አልተገነዘቡም:: ስለ ኢየሱስ ንጉሥነት ትክክለኛ ግንዛቤ አላገኙም:: እነርሱ የጠበቁትና የፈለጉት በሮም ሄሮድስ የሚባል ንጉሥ እንደ ነበረ በተመሳሳይ ደረጃ በእስራኤል ኢየሱስ የሚባል ንጉሥ እንዲኖር ነው:: የኢየሱስ መንግሥት ግን ከዚህ ምድር እንዳልሆነች አላወቁም:: እነርሱ የፈለጉት እስራኤልን ወደ ቀደመ ክብሯ የሚመራት፣ ከቅኝ ግዛት ነፃ የሚያወጣት መሪ ነው:: በነቢያት አፍ የነገረውን አላስተዋሉም:: ስለሆነም ወደ ኋላ ላይ ኢየሱስ የጠበቁት ዓይነት ንጉሥ እንዳልሆነ ሲመለከቱት ብዙዎቹ ከእርሱ ሸሹ፤ ምኞታቸውን አላሟላላቸውም::

***12÷14-15 ኢየሱስ የአህያ ውርንጫ አግኝቶ በእርሱ ተቀመጠ::*** ንጉሡ ወደ ኢየሩሳሌም እየመጣ ነው:: አልዓዛርን ከሞት ያስነሣው እንደሆነ ብዙዎች አይተዋል፣ ሰምተዋል:: ሆኖም ወደ ኢየሩሳሌም እየገባ የነበረው ***በአህያ ወርንጫ*** ስለሆነ ከአመጣጡ ጀምሮ አይሁድ በሚፈልጉት ዓይነት አልነበረም:: በዘመኑ እንደ ነበሩ የህገር መሪዎች በሰረገላ ሆኖ በብዙ ሠራዊት ታጅቦ አልመጣም:: ***በአህያ ውርንጫ*** መምጣቱ እንደ ድል አድራጊ (እንደ አሸናፊ) ሳይሆን እንደ ትሑት ሆኖ መምጣቱን ያሳያል (ዘካ 9÷9):: የእርሱ አመጣጥ በነቢያት በተነገረው መሠረት ***አንቺ የጽዮን ልጅ አትፍሪ! እነሆ፥ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ይመጣል ተብሎ እንደ ተጻፈ 12÷14-15*** ነው:: የተጻፈውና ሕዝቡ የጠበቀው የተለያየ ነው:: ሕዝቡ የፈለጉት የኢየሱስ አመጣጥ እነርሱ በሚፈልጉት ዓይነት እንዲሆንላቸው በመሆኑ ተሰናከሉበት:: በምድር ላይ ወደ ነበረ ዙፋን ከፍ አላለም:: እርሱ ከፍ ከፍ ያለው ወደ መስቀል ነው:: ይህ ጌታም ወደ ኢየሩሳሌም የገባበት ሁኔታ ለአይሁድ፣ ለደቀ መዛሙርትም እንኳ ሳይቀር አልገባቸውም ነበር::



***12÷16 ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር በመጀመሪያ አላስተዋሉም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይህንም እንዳደረጉለት ትዝ አላቸው::*** እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ቀደም ሲል በ2÷22ም ተገልጧል:: ደቀ መዛሙርት አንዳንዱን ነገር የሚያስተውሉት ዘግይተው ነበረ:: ***ኢየሱስ ከከበረ በኋላ*** ማለት ከትንሣኤ በኋላ ማለት ነው:: ከትንሣኤ በኋላ በብሉይ ኪዳን የተጻፉትን ትምህርቶችና ጌታ ያደረጋቸውንም ነገሮች ደቀ መዛሙርት ያስተውሉ ነበረ (14÷6፤ ሉቃ 24÷25-35፣ 44-48)::

***12÷19 እነሆ፥ ዓለሙ ከኋላው ተከትሎት ሄዶአል ተባባሉ::*** ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ጌታ የገባው በክብር ነበር:: የዘንባባ ዝንጣፊ የያዙ ሰዎች:- ክብር ለእግዚአብሔር ሆሣዕና እያሉ ንጉሥሽ መጥቷል ይላሉ:: ሌሎችም አልዓዛርን ያስነሣው ሰው እንደሆነ ስለ እርሱ ይመሰክራሉ:: ይህንን ለመስማት፣ ማንነቱን ለማየት ብዙዎችም ወደ እርሱ መጥተዋል:: ይህን ያዩ ፈሪሳውያን የበለጠ በቁጭት ውስጥ ናቸው:: ሰው ሁሉ ኢየሱስን መከተል እንደ ጀመረ ሲያዩ፣ ***እነሆ፥ ዓለሙ ከኋላው ተከትሎት ሄዶአል*** በማለት የቁጭትና የምጸት ቃል መናገራቸው ነው::

ኢየሱስን ለማየት የመጡትና የሚከተሉት ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በመረዳት አልነበረም:: ከመጀመሪያው ጌታ ከተገለጠበት ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስን ሰዎች እንዳይከተሉት ይከላከሉ ነበረ:: ሊያስቆሙት በፈለጉ መጠን፣ ታዋቂነቱ እየጨመረ ሄደ:: ስለዚህ ጥረታቸው ሁሉ ከንቱ ሆነባቸው::

ከዚህ በኋላ ባለው ክፍል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን መሞት እንደተገባው ይገልጣል ከ12÷20-36 ባለው:: እንዲሁም እግዚአብሔር አብ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሲነጋገርም ይሰማል:: እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገር ሰዎች የሰሙት ሦስት ጊዜ ነው::

የመጀመሪያው:- በተጠመቀ ጊዜ፣ ማቴ 3÷13-17፤ ማር 1÷9-11፤ ሉቃ 3÷21-22:: ሁለተኛው ደግሞ:- ጌታ በተራራ ላይ በተለወጠና ልብሱም ባንጸባረቀ ጊዜ፣ ማቴ 17÷1-13፤ ማር 9÷2-13 እንዲሁም ሉቃ 9÷28-36:: ሦስተኛው ደግሞ፣ አሁን ነው፤ ዮሐ 12÷28-29::

***12÷20 በበዓሉም ሊሰግዱ ከወጡት አንዳንዶቹ የግሪክ ሰዎች ነበሩ:-*** እነዚህ የግሪክ ሰዎች በግሪክ የነበሩ አማኞች ወይም ግሪክኛ የሚናገሩ አይሁድ ሊሆኑ ይችላሉ:: እግዚአብሔርን የሚፈሩ አሕዛብ ወይም ወደ

ይሁዲነት የተለወጡ ግሪኮች ሊሆኑ ይችላሉ:: በዓመት ሦስት ጊዜ በሚደረጉ ትልልቅ በዓላት አይሁድና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችም ከኢየሩሳሌምም ውጭ ከብዙ ሀገሮች ወደ ኢየሩሳሌም ይመጡ ነበር::

ጌታ ለሚያደርገው ነገር ጊዜና ሁኔታን ይመርጣል:: ይህን በዓል ተጠቅሞ ስለ እርሱ ማንነት በስፋት ያስታውቃል:: ለምሳሌ:- በበዓለ ኀምሳ ቀን በኢየሩሳሌም የነበሩት ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ ደቀ መዛሙርት በልሳኖች እግዚአብሔርን ሲያከብሩ ሰምተው እንደተደነቁና ይህንም ዜና ወደሚሄዱባቸው አካባቢዎች ሁሉ ወስደው እንዳደረሱ እንገነዘባለን:: አሁንም ከግሪክ የመጡ ሰዎች ኢየሱስ አልዓዛርን ከሙታን እንዳስነሣውና ይህ የእስራኤል ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ውርንጫ ሲገባ ስላዩ በሚመለሱበት ቦታ ሁሉ ይህን ይናገራሉ::

ጌታ ከመሰቀሉ በፊት በመጨረሻዎቹ ቀናት እርሱን ሊያዩ የሚፈልጉ የግሪክ ሰዎች መኖራቸው፣ እንዲሁም ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጡ ***የግሪክ ሰዎች*** መኖራቸው እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያለውን ዓላማ ያሳየናል:: እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጠው ለምድር ሁሉ የእርሱን አምላክነት እንድታስታውቅ ነበር:: እስራኤል የእርሱ የካህናት መንግሥት በመሆን ምሕረቱንና አዳኝነቱን ለአሕዛብ ሁሉ እንድትገልጥ ነበር (ዘጸ 19÷5):: ምንም እንኳ እስራኤል ይህን ጥሪና ተልዕኮዋን ባትፈጽምም እንደ እነዚህ የግሪክ ሰዎች፣ ቆርኔሌዎስ (ሐዋ 10)፣ ልድያ (ሐዋ 16:14) ዓይነት እግዚእብሔርን የሚፈሩ አሕዛብ ግን ነበሩ::

***12÷21 እነርሱም ከገሊላ ቤተ ሳይዳ ወደሚሆን ወደ ፊልጶስ መጥተው:- ጌታ ሆይ÷ ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን ብለው ለመኑት::*** የግሪክ ሰዎች ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ወደ ፊልጶስ መምጣታቸው ምናልባት ፊልጶስ የግሪክ ስም ስላለው ወይም ግሪክኛ ስለሚችል ሊሆን ይችላል:: ገሊላ ቤተ ሳይዳ ለግሪክ ሀገር የቀረበችም ስለሆነች ፊልጶስ ግሪክኛ ይችል ይሆናል:: የግሪክ ሰዎች ኢየሱስን ለማየት ያቀረቡትን ጥያቄ ***ፊልጶስ ለእንድርያስ ነገረው 12÷22***: ፊልጶስ ከእንድርያስ ጋር መቀራረብ እንደ ነበረው በ1÷40-44፤ በ6÷7-8፣ እንዲሁም በማር 3÷18 እናያለን:: ***እንድርያስና ፊልጶስ መጥተው ለኢየሱስ ነገሩት 11÷22::*** የጌታ መልስ ደግሞ:-

***12÷23 የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሶአል*** የሚል ነው:: የሰው ልጅ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ የሚከብረው በሞትና ትንሣኤ በኩል ነው:: በዚህ አገላለጽ ጌታ ኢየሱስ ሁልጊዜ በዓላማው ላይ ጸንቶ እስከ



ፍጻሜ የሚሄድ መሆኑን ያሳየናል:: እንደ ፈሪሳውያን አነጋገር ዓለም ሁሉ ተከትሎታል (12÷19)፤ ከአሕዛብም ግሪኮች ሲያዩት ፈልገዋል (12÷20-)፤ ዝናው ስለወጣ ሰዎች የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ሊያነግሡት በሚፈልጉበት ጊዜ እርሱ ግን እየተናገረ ያለው ስለ ሞቱ ነው:: የአባቱን ፈቃድ ይፈጽም ዘንድ ወደ ሞትም እንኳ ለመሄድ ሁልጊዜ ዝግጁ የሆነ ጌታ ነው::

***12÷23 ሰዓቱ ደርሶአል::*** በተደጋጋሚ ጌታ ሲናገር ገና ጥቂት ጊዜ እንዳለ ሰዓቱ እንዳልደረሰ ሲያስረዳ ነበረ፤ አሁን ግን ***ሰዓቱ ደርሶአል*** አለ:: ይህ ሰዓት መድረስ ከአጀቡ ብዛት የተነሣ ወደ ዙፋን የሚመጣበት ጊዜ አይደለም፤ የሚሞትበት እንጂ::

***12÷24 የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች::*** ጌታ ይህን የሚናገረው ስለ ራሱ ሞትና በሞቱም ምክንያት ስለሚገኘው ፍሬ ነው:: ስንዴ በመሬት ላይ በወደቀች ጊዜ (በተዘራች ጊዜ)፣ ያቺ ቅንጣት ትሞታለች፤ ነገር ግን ከእርሷ ብዙ ፍሬዎች ይገኛሉ:: ጌታ ኢየሱስ በመሞቱና በመነሣቱ የሚገኘው ፍሬ በመስቀል ላይ ሳይሞት እንዲሁ በምድር ንጉሥ ቢሆን ኖሮ ሊገኝ ከሚችለው ፍሬ እጅግ የተለየና የላቀ ነው:: የእርሱ ሞት ለእኛ ብቸኛ የሕይወት መንገዳችን፣ ሕይወት የምናገኝበት መንገድ ነው::

***12÷25 ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል÷ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል::*** ይህ ምርጫን ስለማስተካከል ነው:: በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም የሚኖረውን ሕይወት በማወቅና በመመዘን መምረጥ ነው:: በዚህ ዓለም የምናደርገው ምርጫ የዘላለም ውጤት አለው:: ጌታን ለመከተል የሚወድ ሰው ምርጫውን ያወቀና ያስተካከለ መሆን ይኖርበታል:: የአሁኑን ጊዜ ከሚመጣው ጋር በማስተያየት አሁን የሚያደርገው ምርጫ የዘላለም ውጤት እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል:: ***ነፍሱን የሚወድ*** ማለት ለጌታ ከሚኖረው ፍቅርና ታማኝነት በላይ የራሱን ሕይወት መውደድ ነው:: እንዲህ ሲሆን ይህን የወደዱትን ነፍስ ለዘላለም ማጣት ይኖራል:: እውነተኛ የጌታ ደቀ መዛሙርት ግን ጌታን የሚወዱና ስለ ጌታ ብለው በነፍሳቸው ላይ የሚመጣውን መከራና መገለል ለመቀበል የቆረጡ መሆን አለባቸው::

ጌታ ኢየሱስ ነፍስን ስለ መጥላት ሲያስተምር በአንጻራዊ መልኩ ራሳችንን ከምንወደው የበለጠ ክርስቶስን እንድንወድና ለእርሱ እንድንኖር አስረግጦ ሲናገር ነው:: ለራሳችን ደስታና ምቾት መኖር

የራሳችንን ነፍስ መውደድ ነው። ለራሳችን ይህን ለናደርግ ነፍሳችንን የወደድናት ይመስለናል እንጂ፣ ለዘላለም ለጥፋት እያዘጋጀናት ነው ማለት ነው።

እዚህ ላይ ነፍስን መጥላት ማለት ለመሞት መፈለግ ወይም ሞትን መምረጥ፣ ለኑሮ ግድ የሌለው ሰው መሆን፣ ደስታን አለመፈለግ ማለት ሳይሆን ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በሚያከብር ጉዳና መሄድና ዋጋ የሚያስከፍል ሁኔታ ሲመጣ እርሱን የሚያስከብረውን ለማድረግ መቁረጥ ማለት ነው። ይህ እንዴት ይሆናል? አዎ! ሰው ሁልጊዜ ራስ ወዳድ ነውና ይህ በሰው ዘንድ የሚቻል አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር በሚያስችለው ጸጋ ይቻላል። ስለዚህ ራስን ለእግዚአብሔር መስጠትና በእርሱ ማስቻል መደገፍ ይገባል።

*12፥26 የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።* ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ማለት በእርሱ ማመንና እርሱ የተጓዘበትን መንገድ ለመሄድ መምረጥ ስለሆነ በትሕትና ጎዳና እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል። ኢየሱስን ልንከተለው ስንመርጥ ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር አብረን ወስነናል ማለት ነው። እንዲህ ሲሆን ከእርሱ ጋር ለዘላለም አብሮ የመሆን ብድራት አለው። በእግዚአብሔርም መከበር አለ። እግዚአብሔር የሚያከበረውን ሰው ለእርሱ የዘላለም ሕይወት ይሰጠዋል፣ ከእርሱም ጋር ለዘላለም እንዲኖር ያደርጋል።

*12፥27 አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ።* ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ የሚሞትበት ሰዓት ስለ ደረሰ *ነፍሴ ታውካለች* አለ። በሌላም ቦታ *በራሱም ታወከ 11፥33* የሚል አይተናል። ይህ የነፍሱ መታወክ ፍጹም ሰው ለመሆኑ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ስለሆነም *አባት ሆይ ከዚህ ሰዓት አድነኝ* በማለት ይጸልያል። እንደ ሰው ከሚመጣበት መከራ መዳንን የፈለገ ቢሆንም የመጣው የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ ነውና *ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ 12:27* አለ። ከመስቀል ሞት እንዲድን አልለመነም (ሮሜ 8፥32)፤ የመጣው ለዚህ ዓላማ እንደሆነ ያውቅ ነበረ። የዓለምን ኃጢአት እንደሚሸከም (2ቆሮ 5፥21) ያውቃል። ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ምንም እንኳ በፊቱ ያለው መከራና ሞት ከብዶት ከዚያ ሰዓት መዳንን እንደ ሰው ቢፈልግም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን ግን ይመርጣል።



*12፥28 አባት ሆይ፥ ስምህን አክብረው።* ጌታ ከዚያ ሰዓት ወይም ሁኔታ ለመዳን የጠየቀ ቢሆንም ወዲያው ደግሞ አባቱን የሚለምነው ስሙን ያከብረው ዘንድ ነው። ይህም ማለት የመጣበትን ዓላማ በመፈጸም በዚህ እግዚአብሔር እንዲከብር ነው።

*12፥28 አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።* እግዚአብሔር ስሙን የሚያከብረው በልጁ መታዘዝ በኩል ነው (13፥31-32)። እንዲሁም ስሙን የሚያከብረው ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ቀድሞ ወደ ነበረው ክብሩ ሲመለስ ነው (17፥5)። ይህ *አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ* የሚለው ከሰማይ የመጣው ድምፅ የሚሰማ ነበረ። ነገር ግን ምን ማለት እንደሆነ (ቃላቱን ወይም ትርጉሙን) ሰዎች ሲሰሙት አልቻሉም። ስለዚህ *ነጐድጓድ ነው አሉ 12፥29*፡ እንዲሁም *ሌሎች፡- መልአክ ተናገረው አሉ 12፥29*፡ ኢየሱስ አብ እንደሚያከብረው ስለሚያውቅ ይህን ድምፅ መስማት አያስፈልገውም። ስለሆነም *ይህ ድምፅ ስለ እናንተ መጥቶአል እንጂ ስለ እኔ አይደለም፤ 12፥30*፡

*12፥31 አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል።* ይህ *አሁን* ኢየሱስ ከምድር ከፍ ከፍ የሚልበት (በመስቀል ላይ የሚሞትበት) ጊዜ ነው። እርሱ በመስቀል ላይ ሲሞት በዚህ ዓለም ላይ *ፍርድ* ይመጣል። ጌታን በመቃወም የሄዱት የካህናት፣ አለቆች፣ ፈሪሳውያንና ሌሎችም ሁሉ እንዲሁም *የዚህ ዓለም ገዥ* የተባለው ሰይጣን የሚጣልበት ጊዜ ነው።

*የዚህ ዓለም ፍርድ* ማለት *የዚህ ዓለም ገዥ* የሆነው ሰይጣን ወደ ውጭ የሚጣልበት ጊዜ ነው (14፥30፤ 26፥11፤ 2ቆሮ 4፥4፤ ኤፌ 2፥2፤ 6፥12፤ ራእ 12፥9)። የዚህ ዓለም ገዥ የሆነው ሰይጣን ኃይል አለው። ሰይጣን የሰዎችን አእምሮ የሚቆጣጠር፣ የሚገዛ፣ ሰዎች በክርስቶስ እንዳያምኑ የሚያደርግ ሀሰትን የሚናገር ነው። የእርሱ ዋና መሣሪያ የሆነው ሞት ድል የሚነሣበት ጊዜ ደረሰ። በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ዲያብሎስ መሣሪያውን አጣ። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ል አድርጐ ሥልጣኑን ገፎአል (1ቆሮ 15፥26፤ ቆላ 1፥13-14፤ ዕብ 2፥14)።

የዚህ ዓለም ገዥ የተባለው ሰይጣን ሳያቋርጥ በእግዚአብሔር ሀሳብ ላይ ተቃዋሚ ሆኖ የቆመ ነው። የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚቀበሉትንና የእርሱ የሆኑትንም በርትቶ ለመቃወም የሚተጋ ነው። እርሱ ማንንም ሰው የሚፈትን ቢቻለውም ሀሰትን በመናገርና የብርሃን መልአክ መስሎ በመቅረብ ለመጣል የሚፈትን ክፉ ነው። ሔዋንን በገነት

ያልተፈቀደውን እንድትበላ አታለላት (ዘፍ 3:6፤ 2ቆ 11:3)። ጌታ ኢየሱስን በምድረ በዳ ፈተነው (ማቴ 4፥1-11)።

ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ (2ቆሮ 4፥4) ነው። ሆኖም ተሸንፎአል (ዮሐ 12፥31)፤ ወደ ውጭ ተጥሏል። እያንዳንዱ አማኝ ከሰይጣን የሚደርስበትን ተቃውሞ ለመቋቋም የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መልስ መስጠት ይገባል። እንዲሁም ራስንም ከኃጢአትና አመፅ መጠበቅ ያስፈልጋል። በአመፅና በኃጢአት ውስጥ የሚኖር ሰው የዚህን ዓለም ገዥ ውጊያ ለመቋቋም አቅም ያንሰዋል። ኃጢአት በማድረጉ የእርሱን ሀሳብ ማስተናገድ ጀምሯልና።

***12፥32-33 እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ። በምን ዓይነትም ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያመለክታቸው ይህን ተናገረ።*** ሌላም ጊዜ ጌታ ስለ ራሱ ሞት ሲናገር ***ከፍ ከፍ*** በሚለው ቃል ገልጾታል (3፥14፤ 8፥28)። ይህ አገላለጽ በዚያን ዘመን የነበረውን በስቅላት መሞት የሚገልጽ አባባል ነው። እንዲሁም አይሁድ ሊወግሩት እንደፈለጉት በድንጋይ ተወግሮ ሳይሆን (8፥59) ተሰቅሎ እንደሚሞት ያሳያል። ***እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ*** እንዳለ የኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ ማለት ለሁሉም ሰው ጥቅም ነው። ሆኖም ሰው ሁሉ ደኅንነትን ያገኛል ማለት አይደለም። በ5፥26-29 ያለውን ይመልከቱ። «ማንም ቢወድ» (ሉቃ 9:23) እንደተባለ ደኅንነትን ማግኘ ት በምርጫ ነው።

***12፥34 ሕዝቡ፡- እኛስ ክርስቶስ ለዘላለም እንዲኖር ከሕጉ ሰምተናል፤ አንተስ የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ይል ዘንድ እንዲያስፈልገው እንዴት ትላለህ? ይህ የሰው ልጅ ማን ነው?*** ከጥቂት ጊዜ በፊት ሆሣዕና በማለት የእስራኤል ንጉሥ ብለውት ነበር። ይህ ንጉሥ እንዲሆን የጠበቁትንና የፈለጉትን ሰው ***ከፍ ከፍ*** እንደሚል ይነግራቸዋል። እርሱ የሚናገራቸው ስለ ሞቱ እንደ ሆነ ስለ ተረዱና ስለ መሲሑ እናውቃለን ካሉትና ከሚጠብቁት የተለየ ስለሆነባቸው ይህን ጥያቄ አነሡ።

ከብሉይ ኪዳን መሲሑ በሕይወት እንደሚኖርና ለዘላለም እንደሚገዛ እንብበዋል (መዝ 72፥17፤ ኢሳ 9፥6-7፤ ሕዝ 37፥26-28)። ኢየሱስ የሚጠበቀው መሲሕ እንደሆነ ስላወቁም የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ወደ መሲሑ መጥተዋል። ሆኖም መሲሕ እንደሚሞት ሲገምቱ ስላልቻሉ ግራ ተጋቡ። ስለዚህ ***የሰው ልጅ ማን ነው?*** ብለው ጠየቁ።



እነዚህ ሕግ እናውቃለን የሚሉ አይሁድ እውቀታቸው ትክክል፤ ግን ከፊል ነው። ሙሉውን እውነት ስላላወቁ በነገሩ ተሰናከሉ። የሚመጣው መሲሕ ለዘላለም እንደሚኖር እንደተነገረ ሁሉ አስቀድሞ ግን በግ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል፤ ለመታረድ እንደሚነዳ መከራ እንደሚቀበል፤ እንደሚታረድ (እንደሚሞት) ተነግሮ ነበር (ኢሳ 53:7)። እነዚህን ሁለት እውነቶች በማያያዝ አንድ ሙሉ እውነት እንደሚሆን አላገናዘቡም።

***12፥35-36 ኢየሱስም፡- ገና ጥቂት ጊዜ ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው። ጨለማ እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤ በጨለማም የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም። የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ እመኑ አላቸው።*** ኢየሱስ በምድር ላይ ሲመላለስ ብርሃን ነበረ። በእርሱ የሚያምኑትም ***የብርሃን ልጆች*** ይባላሉ። የጌታ ጊዜው ስለደረሰ ጨለማ ሲሆን ነው ስለዚህ ጨለማው ከመምጣቱ በፊት በኢየሱስ እንዲያምኑና በብርሃን እንዲመላለሱ ይነግራቸዋል። በብርሃን መመላለስ ብርሃን በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ መመላለስና እርሱን በመታዘዝ መኖር ነው። ከኃጢአት መራቅ ውስጥን ለእርሱ በማስመርመር በእውነተኛነት መኖር ነው። ***በጨለማም የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም*** አቅጣጫ የለውም፤ ስለዚህ ይሰናከላል። ብርሃን በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ የሚሄድ ሰው መንገዱን ያውቃል መድረሻውንም ያውቃል፤ ስለዚህ አይሰናከልም። የሕይወት ትርጉም የገባው ሰው ነው።

***12፥36 ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ሄደና ተሰወረባቸው።*** ከዚህ ጊዜ በኋላ ሊያገኙት አልቻሉም ማለት ነው። በሕይወታችን የምናገኛቸው መልካም ምርጫዎች ሁሉ ለሁልጊዜ የሚጠብቁን አይደሉም። ብርሃን እያለ በብርሃን ማመንና በብርሃን መመላለስ እንጂ በጌታ ለማመን በይደር ማቆየት «የመዳን ቀን ዛሬ ነው» (2ቆሮ 6:2) የሚለውን የጌታን ቃል መጣስ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ቀን ይቀጥራሉ፤ ወይም በዕድሜአቸው ከተወሰነ ዓመት በኋላ ሊያደርጉት እንደሚያስቡ ይናገራሉ። ያ ምርጫና ቀን ግን ከእነርሱ ጋር ሳይቆይ ይችላል፤ ቢፈልጉ የማያገኙት ጊዜም ይመጣል። ስለዚህ ብርሃን እያለ በብርሃን መመላለስ ቀን እያለ በቀን መሥራት ጊዜን መጠቀምና ምርጫን አስተካክሎ በዚያ መኖር ተገቢ እርምጃ ነው።

***12፥37-38 ነገር ግን ይህን ያህል ምልክት በፊታቸው ምንም ቢያደርግ፤ ... በእርሱ አላመኑም።*** የምልክቶች መደረግ ዋና ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲመሰክሩና ሕዝቡም በእርሱ እንዲያምኑ ነው። ጌታ ያደረገው ምልክት ሰዎች ሁሉ በእርሱ እንዲያምኑ በቂ ማስረጃ ናቸው። የዕውሩን ዓይን

ማብራቱ፣ 38 ዓመት የታመመውን መፈወሱ፣ አልዓዛርን ከሙታን ማስነሣቱ፣ መሽተት የጀመረውን የሞተ አካል (ሥጋ) እንደገና ሙሉ ሰው ማድረጉና ሌሎችም ተአምራት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ በቂ ማስረጃዎች ናቸው። የሚበዙት አይሁድ ግን በኢየሱስ ለማመን ፈቃደኞች አልነበሩም። ስለዚህም ሁኔታ ቀደም ብሎ በኢሳይያስ በኩል ተናግሮ ነበር።

***12፥37-38 ጌታ ሆይ፥ ማን ምስክርነታችንን አመነ? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?*** ይህን ኢሳይያስ የተናገረው በኢሳ 53፥1 ላይ ነው። ***የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?*** የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ክንድ[52] ተብሎ እንደተጠራ ያመለክታል። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት ክንዱ ቢሆንም አይሁድ ይህን መገንዘብ ተሳናቸው። ይህም እንደሚሆን ቀደም ሲል በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል ተነግሮ ነበር። ***እንዲህ ተብሎ፤ በዓይኖቻቸው እንዳያዩ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ እንዳይመለሱም፥ እኔም እንዳልፈውሳቸው፥ ዓይኖቻቸውን አሳወረ ልባቸውንም አደነደነ 12፥39-40***፡ ይህ ክፍል የሚገኘው በኢሳ 6፥9-10 ሲሆን በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ተጠቅሶ እናየዋለን (ማቴ 13፥14፤ ማር 4፥12፤ ሉቃ 8፡10፤ ሐዋ 28፡26)።

***12፥41 ክብሩን ስላየ ኢሳይያስ ይህን አለ ስለ እርሱም ተናገረ***[53]። ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር ጌታ ነው። እርሱ እግዚአብሔር ነው ኢሳይያስ ያየው የኢየሱስን ክብር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነውና።

በኢየሱስ ጊዜ የነበሩ አይሁድ በኢሳይያስ ጊዜ እንደነበሩት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ***ይህን ያህል ምልክት 12:37*** ቢያደርግም ሊያምኑ አልፈለጉም። ***በእርሱ አላመኑም 12:38*** ሲል በኢየሱስ አላመኑም ማለት ነው።

***ልባቸውንን አደነደነ 12:39-40*** የሚለውን እንዴት እንደረዳዋለን? ለማመን ስላልፈለጉ እግዚአብሔር ያንኑ ምርጫቸውን እንዳያምኑ በማድረግ አጸናላቸው ማለት ነው። እንዲሁም ዘጸ 9፡12፤ ሮሜ 1፥24-28፤ 2ኛ ተሰ 2፡9-12 ያሰውን ይመልከቱ።

[52] <... Jesus was the arm of the Lord (the one through whom God demonstrated his mighty power)>. Ibid., p.262.
[53] Isaiah said this because he saw Jesus' glory and spoke about him. NIV.



ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ እርሱ ራሱ ማንነቱን እየነገራቸውና ምልክትን እያሳያቸው በእርሱ ያላመኑ ብዙዎች ነበሩ። እርሱ እየሰበከ የማያምኑ ከሆነ፣ እኛማ በዚህ ዘመን ያለን ብንሰብክ ማን ይሰማናል? ማንስ ይቀበለናል? ብለን እናስባለን። በእርግጥ የሰው ልብ ክፉ ነውና ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰብክ እንኳ ያልተቀበሉትና አጥብቀው የተቃወሙ ብዙዎች ነበሩ። የአማኞች ድርሻ ወንጌልን መዝራት ላልሰሙትም ሁሉ እንዲሰሙ ማድረግ ነው። እያንዳንዱ ሰው ሰምቶ ስለሚወስነው ነገር ራሱ ተጠያቂ ይሆናል። ስለዚህ ታማኝ የክርስቶስ ምስክር ሁልጊዜ በታማኝነት ወንጌልን እየሰበከ ይቀጥላል።

***12፥42-43 ከዚህም ጋር ከአለቆች ደግሞ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ነገር ግን ከምኩራብ እንዳያስወጡአቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩትም፤ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና።*** አለቆች የእስራኤል መሪዎች ነበሩ (3፥1)። ከእነዚህ ብዙዎች በኢየሱስ አመኑ። ሆኖም የእነዚህ ሰዎች እምነት ደካማ ነበር። የሚያምኑትን ለመግለጽ አልፈለጉም። ፍርሃታቸውም አይሁድ ከምኩራብ እንዳያስወጡአቸው ነው። እነዚህ በሰዎች መነቀፍን፣ መጠላትን፣ መሰደድን የማይፈልጉ በእግዚአብሔር ማመንንና የሰውን ክብር የፈለጉ (5፥44) ናቸው። ሁለቱ ግን አብረው አይሄዱም በእግዚአብሔር ማመን የመረጠ ሰው የሰውን ክብር አይፈልግም። የሰውን ክብር የሚፈልግ የእግዚአብሔርን ክብር አያገኝም። ሰውን መፍራት ወጥመድ ነው (ምሳ 29:25)።

የሰውን ክብር መውደድ የሚለው በአንዳንድ መከራና ስደት በሞላባቸው ሀገሮች የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ሁኔታ ላያመለክት ይችላል። በሀገር ደረጃ ክርስትናንን በሚቃወሙ ሀገሮች ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡት በአነስተኛ ቁጥር በመሆን በቤት ውስጥ ነው። ይህ ወንጌልን ጠብቆ ለማቆየትና ለማስፋፋት ትልቅ መንገድ ወይም ስትራቴጂ ነው። እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች በተያዙ ጊዜ የሰውን ክብር አልፈለጉምና እምነታቸውን ለመግለጽ ማንነታቸውን ለማሳወቅ ቢያስፈልግም መከራ ለመቀበል የወሰኑ ናቸው። በዚህ ክፍል የምናያቸው አይሁድ ግን ተመሳስለው ለመኖር የፈለጉ ፈሪሳውያን ***ከምኩራብ እንዳያስወጡአቸው*** ብለው «ዝም ያሉ» ናቸው። ስለ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጌታ ኢየሱስ በማቴ 10፥32-33 ያስተማረውን ይመልከቱ።

***12፥44-45 በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤ እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል።*** በዚህም ክፍል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር ያለውን አንድነት አስረግጦ ይናገራል። እርሱ በአብ የተላከ

ነው (14፥9-11)። እርሱ አብን የሚያሳይ የሰውን ሥጋ የለበሰ መለኮት ነው። ስለዚህ በልጁ በኢየሱስ የሚያምን በአብ ማመኑ ነው። እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያስፈልገው ነገር እምነታችን በአብ፣ ወይም በወልድ አይደለም፤ በአብ ስናምን በወልድ ማመናችን ነው፤ በወልድ ስናምን በአብ ማመናችን ነው። እምነታችን በአብ ወይም በወልድ አይደለም። እምነታችን በአብና በወልድ ነው። (እምነታችን በአብ፤ በወልድ፤ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ነው።) ስለዚህ እግዚአብሔር አምናለሁ የሚል ሰው በኢየሱስ የሚያምን መሆን አለበት፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና አዳኝነት ሳያምን በእግዚአብሔር አምናለሁ የሚል የእርሱ እምነት ከንቱ ነው።

***12፥46 በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።*** የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ በጨለማና በብርሃን መካከል ያለውን ትግል ያሳያል። ጨለማው ኃይለኛ ነው፤ ብርሃንን ግን አላሸነፈውም። ወደ ዓለም የሚመጣው ብርሃን፤ የመጣውም እርሱ ኢየሱስ ጨለማን የገፈፈ ከጨለማም ጋር ታግሎ ያሸነፈ የዓለም ብርሃን፣ ነው። ስለሆነም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን በብርሃን ይመላለሳልና የዲያብሎስን የጨለማ ግዛት የካደ ከጨለማውም ወደ ብርሃን የወጣ (የተነጠቀ) ሰው ነው።

***12፥47-48 ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የምፈርድበት እኔ አይደለሁም። የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል።*** ጌታ ወደ ምድር የመጣው ለመፍረድ አለመሆኑን ቀደም ሲል በ3፡17፤ በ8፡15-16 ባለው ተናግሯል። እርሱ የተናገረውን ቃል የማይቀበል ሁሉ ቃሉ በመጨረሻው ቀን እንደሚፈርድበት አስረግጦ ይናገራል። እንዲሁም 3፥31-36፤ 5፥22-23፤ 26፡26-30፤ 9፡39 ይመልከቱ።

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን ለዘላለም ሕይወት ደኅንነት የሚገኝበትን መንገድ ለማሳየት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁለተኛ ገዜ ይመጣል። ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ ከሚመጣባቸው ዋና ዓላማዎች አንዱ በሰዎች ለመፍረድ ነው። ያላመኑት በኢየሱስ ስላላመኑ ይፈረድባቸዋል። በእርሱ የሚያምኑት ለዘላለም ሕይወት ትንሣኤ ያገኛሉ (1ቆር 15፡51-57፤ 1ተሰ 4፡15-18፤ ራእ 1፥1-8)። ኢየሱስን ለመቀበል ያልወደዱና የገፉት ደግሞ የዘላለም ፍርድን ይቀበላሉ (ራእ 20፡11-15)።



***12፥49 እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውን ትእዛዝ ሰጠኝ።***[54] በቆላ 2፥9 «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና» እንደሚል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም (ሙሉ) መለኮት ነው። እንዲሁም ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነው። በፍጹም ሰውነቱ የአባቱን ትእዛዝ ለመፈጸም ተላከ። ትእዛዙንም ለማድረግ የራሱን ፈቃድ ተወ፤ የባሪያንም መልክ ወሰደ (ፊል 2፥5-9)። ስለሆነም በምድር እያለ የተናገረውን ***ከራሴ አልተናገርሁም*** በማለት ይገልጻል። ይህም ማለት የተላክሁበትን ዓላማ እፈጽም ዘንድ የላከኝ አብ እንድናገረው የሰጠኝን ተናገርኩ፤ አደርገውም ዘንድ ያዘዘኝን አደረግሁ ማለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ይለማል ፈጽሞም ይታዘዘዋል። በአንዳንዶች ዘንድ ***የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውን ትእዛዝ ሰጠኝ*** ስለሚል የሚታዘዝ ከሆነ ከአብ ስለሚያንስ መሆን አለበት የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። ይህ አስተያየት የሰው አእምሮ የሚፈጥረው እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው አይደለም። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ መለኮት ነውና በመለኮትነቱ ከአብ አያንስም። እግዚአብሔር ባዘጋጀው የዘላለም እቅድ መሠረት ደግሞ ይህ ከሥላሴ ሁለተኛው አካል የሆነው ኢየሱስ ሰውን ከኃጢአት ለማዳን የሰውን ሥጋ መልበስ ነበረበትና በዚህ ተልዕኮው የአብን ፈቃድ ያደርጋል። ሰው ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እንዳለበት ሁሉ ኢየሱስም ወደ አባቱ ሲጸልይ አንተ የምትወደው ይሁን እያለ ፈጽሞ ፈቃዱን ለአባቱ አስገዝቷል።

***12፥50 ትእዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደሆነች አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረውን አብ እንደነገረኝ እንዲሁ እናገራለሁ።*** ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው በእርሱ ለሚያምኑት የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት ነው። ***ትእዛዙም*** ይኸው ***የዘላለም ሕይወት*** ነው። አብ ለልጁ የነገረው የዘላለም ሕይወት እንዲሰጥ ስለሆነ ያንኑ ይናገራል። እርሱ የሚናገረውን መቀበል ደግሞ የዘላለም ሕይወት መቀበል ነው (3፥16-17፣ 35-36፤ 5፥24-29፤39-40)።

---

[54] Some, like the Jehovah's Witnesses have used verses like this to say that Jesus was not God because he was so subordinate to the Father. But Jesus' essential divine being has not been subordinate to the Father - in all things he was equal with God (Phil 2:5-6); rather, Jesus coordinated his will to fully comply with the Father's will. Thus to respond to Jesus is to respond th God. To believe in Jesus is to believe in God. To reject Jesus is to reject God. Ibid. pp. 265-266.

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ከምዕራፍ 1-13 ያለው ክፍል በጌታ ኢየሱስ አገልግሎት የነበረውን ሦስት ዓመት ያህል ጊዜ ይሸፍናል። ከምዕራፍ 13-19 ያሉት ስድስት ምዕራፎች ደግሞ በአንድ ምሽት የሆነውን ያጠቃልላሉ።

***13፥1 ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደ ደረሰ አውቆ፥ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው።*** በምድር ላይ የሚቆይበትን የመጨረሻ ሰዓት ያሳለፈው የወደዳቸውን ደቀ መዛሙርቱን በማስተማር፣ በማበረታትና በማጽናናት ነበር። ***ዓለም*** የሚለው ቃል በዮሐንስ ወንጌል ሁለት ትርጉም አለው።

- የመጀመሪያው፡- በ3፥16 እንደተገለጠው ሁሉ «እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ወዶአልና» እንደሚል በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች (የሰውን ዘር) ሁሉ ማለት ነው። እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እንዲልክ ያደረገው ይህ ዓለምን ሁሉ (ሰውን ሁሉ) መውደዱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩን ትቶ የመጣውና ሰው የሆነው ከዚህ ፍቅር የተነሣ ሰውን በመውደዱ ነው።

- ሁለተኛው ደግሞ ዓለም፡- ዓለማዊነትን በአጠቃላይ ኃጢአትን ያመለክታል። በዓለም ውስጥ ያለውን እግዚአብሔርን የማያከብር አስተሳሰብ፥ አመለካከት፥ አመጽና ኃጢአትን ይገልጻል። «ማንም ዓለምን ቢወድ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ አይኖርም» (1ዮሐ 2፡15-17) እንደሚል፥

አንደኛው ዓለምን ለመዋጀት ምክንያት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ለመጣላትና ለመኮነን ምክንያት ነው። እግዚአብሔር ዓለሙን ይወዳል፥ ኃጢአትን ይጠላል። ይህ የእግዚአብሔር ባሕርይ የኢየሱስ በሆኑት ሁሉ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የነበረው ፍቅር በጊዜ ያልተገደበ (ጊዜያዊ) አለመሆኑን ሲያመለክት ***እስከ መጨረሻው ወደዳቸው ይላል።*** ሰዓቱ ደርሶ እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ ደቀ መዛሙርቱን ወደዳቸው።



ከእነርሱም ከመለየቱ በፊት ይህንን ፍቅሩን ለእያንዳንዳቸው ለመግለጽ ወደደ።

ፍቅሩንም የገለጸበት መንገድ እነርሱን ያስደነቀ አዲስ መንገድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን በፍጹም ፍቅር እንደሚወዳቸው ለመግለጽ የመጨረሻውን ጊዜ ተጠቀመ። እነዚህ ለደቀ መዛሙርት እንዲህ ዓይነት ፍቅር የሚገባቸው ሆነው አይደለም። ከእነርሱ የሚጠብቀው ምላሽ አልነበረም። ከደቀ መዛሙርቱም መካከል እርሱን አሳልፎ ሊሰጠው ያለው አብሮ አለ፤ የሚክደው ጥለውትም የሚሸሹት ሁሉ እዚያው ውስጥ አሉ። ይህ ሁኔታ ፍቅር የሚመነጨው ከሰዎች ከሚጠበቅ ምላሽ ሳይሆን ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ያስገነዝባል።

***13፥2 እራትም ሲበሉ፡-*** ይህ እራት ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የሚበላው የመጨረሻ እራት ነው። በዚህም ምሽት ስለ ጌታ እራት[55] ምንነትና ወደፊትም ለመታሰቢያ እንዲያደርጉት ለደቀ መዛሙርቱ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል። (እንዲሁም ማቴ 26፥17-30፤ ማር 14፥12-26፤ ሉቃ 22:7-39 ይመልከቱ)። ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብ የጀመረው እራቱ ከመበላቱ በፊት እንደሆነ ከ13፥26 እና 30 እንገነዘባለን።

***13፥2 ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ከአገባ በኋላ፡-*** ቀደም ሲል በ6፥70 ላይ እንዳየነው ኢየሱስ ክርስቶስ አስቆሮቱ ይሁዳን ዲያብሎስ ብሎት ነበር። ምክንያቱም ይሁዳ ከዲያብሎስ ጋር ተስማምቶ ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጥ ስለሆነ ነው። አሁን እንደምናየው ደግሞ ዲያብሎስ በይሁዳ ልብ አሳብን አስገባ። ቀጥሎም በ13፥27 እንደምንመለከተው ራሱ ዲያብሎስ በይሁዳ ውስጥ ገባ።

***13፥3 ኢየሱስ አብ ሁሉን በእጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደ መጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ፥*** ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ***እንደ መጣ*** ማለትም ከአብ ዘንድ እንደ መጣ እንዲሁ ወደ አብ ይሄዳል። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ዘንድ ይወጣል ማለት ከእብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣል (15፥26-27)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን የመሄጃው ጊዜ ደርሶአል። የእግዚአብሔር ልጅ ከየት እንደ መጣ ያውቃል፥ ወዴትም እንደሚሄድ ያውቃል። እርሱ ከመምጣቱ በፊት የነበረበትን ሁኔታና ቦታ ይገልጽልናል። ሲሄድም

[55] ቅዱስ ቁርባን

የት እንደሚሄድና በምን ሁኔታ እንደ ነበረ ይነግረናል:: በነበረበትና በሚሄድበት መካከል ያለው ጊዜ በምድር የነበረበት ጊዜ ነው:: የነበረው በእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: እርሱ እግዚአብሔር ነው:: በምድር የነበረው ደግሞ መዋረድ፤ ራሱን ባዶ በማድረግ፤ ለመስቀል ሞት በመታዘዝ (ፊል 2÷6-8)፤ ሲመለስ የሚሆነው አስቀድሞ በነበረ ክብሩ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጥ ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም መጥቶ፣ ራሱን ባዶ አድርጐ ለመስቀል ሞት የታዘዘ የሆነው ሰው ሁሉ በእርሱ ስለሚያምን አልነበረም:: ለሚያምኑት ምርጫቸውን ላደረጉት የዘላለም ሕይወትን ይሰጣቸዋል:: ነገር ግን ሰው ሁሉ በእርሱ አላመነም፤ የተቃወሙት ብዙዎች ነበሩ:: ራሱን ከፍቅር የተነሣ ሰጠ:: በእኛም አገልግሎት የምናገለግለው አገልግሎታችንን ሰው ሁሉ ስለሚቀበለው አይደለም፣ የማይቀበሉት ብዙዎች ይኖራሉ:: በፍቅር ተነሣስተን ስናገለግል የጌታን ምሳሌነት መከተላችን ነው::

***13÷4 ከእራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ፥ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ፡-*** ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ጌታ፤ መምህር እንዲሁም አገልጋይ ነበረ:: ይህ ጌታ የሆነ ኢየሱስ የባሪያን መልክ ወሰደ:: ለእራት ከተቀመጡት ሰዎች መካከል የማበሻ ጨርቅ ወስዶ መታጠቅና ለእራት የተሰበሰቡትን እግር የማጠብ ተግባር የመምህሩ አይሆንም፤ ከሁሉም እንዲያጥብ የማይጠበቀው እርሱ ነው:: በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው፤ በእግዚአብሔርም መልክ ሲኖር የነበረው ቃል (1፡1) በምድር የሰውን ሥጋ ከለበሰ በኋላ የደቀ መዛሙርቱን እግር ለማጠብ ***ማበሻም ጨርቅ ታጠቀ!*** አገለገለ::

***13÷5 በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፥ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበት የማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ::*** በቀደመው ዘመን በከነዓን እግር ማጠብ የተለመደ ተግባር ነበር:: ሰዎች ብዙ ጊዜ በባዶ እግራቸው ወይም ነጠላ ጫማ አድርገው በአቧራማ፣ አሸዋማ ቦታ ስለሚሄዱ እግራቸው ይቆሽሻል:: ስለዚህ ወደ ቤት ሲገቡ እግራቸውን ማጠብ የተለመደ ነገር ነው:: እንግዳ ወደ ቤት ሲገባ እግሩን ለማጠብ አለመሞከር ጥሩ መስተንግዶ ያለመስጠት ምልክት ነው (ሉቃ 7÷44):: ይሁን እንጂ የእንግዳን እግር ማጠብ የቤት ውስጥ አገልጋይ ተግባር ተደርጐ ይወሰዳል (1ሳሙ 25÷41):: ተማሪዎች (ማለት ደቀ መዛሙርት) የአስተማሪዎችን እግር እንዲያጥቡ ይጠበቃል:: መምህራን ግን የተማሪዎቻቸውን እግር እንዲያጥቡ ፈጽሞ አይታሰብም:: ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ እግራቸውን ሊያጥብ ሲነሣ



ይህ በዝቅተኛ ደረጃ ያለ ሰው ተግባር ተደርጐ ስለሚቆጠር የጌታን አገልጋይነት በጉልህ ያሳያል::

ከደቀ መዛሙርት መካከል በእግዚአብሔር መንግሥት ታላቁ ማን እንደሚሆን እርስ በእርስ ሲከራከሩ ጌታ ኢየሱስ ራሱን ዝቅ አድርጐ እግር ለማጠብ መጀመሩ «አስደንጋጭ» ይሆንባቸዋል:: እነርሱ ስለ ትልቅነት ካላቸው ስዕል (መረዳት) የተለየ ነውና:: የጌታ ኢየሱስ ባሕርይ ከሰው ታላቅ ተብሎ ከመጠራት ፍላጐት ፈጽሞ የተለየ እንደሆነ ያሳያል (ማቴ 20÷20-24፤ ማር 9÷33-34፣ 10÷35-44፤ ሉቃ 22÷24-30)::

አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን በአገልጋዮች መካከል ታላቅ ማነው? ማን «በወንበሩ» ላይ ይቀመጥ? የሚል ፉክክር እና ውድድር ይኖራል:: በአንጻሩ ዝቅተኛ ነው የተባለውን ሥራ እኔ መሥራት አለብኝ በሚል እርስ በርስ ውድድር የሚደረግበት ጊዜ አይታይም:: የዚህ መድኃኒቱ የጌታን የትሕትና መንገድ መከተል ነው:: ጌታ መምህርና ጌታ ሆኖ ሳለ ዝቅተኛውን ተግባር በመፈጸም «አገልጋይነትን» አሳየ::

***13÷6 ጌታ ሆይ፥ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን?*** ይህን የጠየቀው ስምዖን ጴጥሮስ ነው:: ሌሎቹ እግራቸውን ባጠባቸው ጊዜ ምን እንዳሉ አልተገለጠም:: ምናልባትም በዝምታ ተቀብለውት ይሆናል:: ስምዖን ግን አንተ ጌታ ሆነህ ሳለህ የእኔን የባሪያህን ወይም የደቀ መዝሙርህን እግር እንዴት ታጥባለህ? ሲል ጠየቀው:: የጌታም መልስ ስጥያቄው ቀጥተኛ ሳይሆን፣ ***እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፥ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ 13÷7*** የሚል ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ሊያስተምራቸው ያላስተዋሉትና በኋላ ጌታ ኢየሱስ ከሞተና ከተነሣ በኋላ የሚያገናዝቡት ብዙ ነገር ነበረ፤ ይህ አንዱ ነው:: በእርግጥም ጴጥሮስ በኋላ በዘመኑ ይህን ተገንዝቧል:: በ1ጴጥ 5÷5-6 ባለው ክፍል «ሁላችሁም እርስ በእርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ» ሲል ጌታ ያደረገው ትሕትና ትዝ እያለው መሆን አለበት:: አንዱ ለሌላው ዝቅ ማለትን ከጌታ ተማረ፣ አስተዋለ::

***13÷8 ጴጥሮስም፡- የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው::*** በዚህ አመላለሱ ጴጥሮስ ማንነቱን የተገነዘበ ሰው እንደሆነ ማየት ይቻላል:: ጴጥሮስን በጣም የቸገረው ነገር ጌታው (እንደ ባሪያ) ዝቅ ብሎ እግሩን ሊያጥብ ወደ እርሱ መምጣቱ ነው:: ስነገሩማ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው ቃል ሰው ሆኖ ሲመጣ ያን ጊዜ የባሪያን መልክ ወሰደ፤ በሰዎችም መካከል ተመላለሰ:: አሁን ደግሞ

ከሰዎችም ዝቅተኛውን አገልግሎት ለመስጠት ራሱን ዝቅ አደረገ:: ጴጥሮስ በዚያን ጊዜ ያላስተዋለው ወደፊት የሚረዳው ቁም ነገር መምህር ወይም መሪ የሆነ ሰው አገልጋይ መሆን እንዳለበት ነው:: የሚያገለግላቸውን ወይም የሚመራቸውን ሰዎች ለመጥቀም ዝቅተኛ የሆነውንም ሥራ ለመውሰድ የማይከብደው መሆን እንዳለበት ነው::

***13፥8 ካላጠብሁህ፥ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም::*** ይህ እግር ማጠብ በእግር ላይ ያለውን ቆሻሻ ከማጽዳት በተጨማሪ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚመጣውን የማንጻት አገልግሎትን የሚያመለክት ነው:: ስለዚህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ***ዕድል*** ፈንታ የሚኖረው ሰው ከኃጢአቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኩል በእምነት ሲነጻ ነው:: ሰው ከእርሱ ጋር ዕድል ፈንታ የሚኖረውም እርሱ እያደረገ ባለው ውስጥ ሲያልፍና ትሕትናውን ሲማር እንደሆነም ሲያመለክት ይችላል:: ስለዚህ ጌታ እግሩን እንዲያጥብ የጠየቀው ጴጥሮስ ተቀበለ፤ የቆሸሸውን እግሩን ያጥበው ዘንድ ፈቀደ:: በዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ ለእርሱ ያደረገውን የማዳን ሥራ እና ትሕትናውን ተማረ:: ዕድል ፈንታው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንዲሆን የፈለገ ጴጥሮስ የሰጠው ፈጣን ምላሽ ***ጌታ ሆይ:- እጆችና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም 13፥9*** የሚል ነበር::

***13፥10 የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም፤ ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው፣ እናንተም ንጹሕ ናችሁ::*** አንድ ሰው ከታጠበ በኋላ ለውየው በዚያ ቀን ንጹሕ ነውና ሌላ የገላ መታጠብ አያስፈልገውም:: ይህ በጊዜውና በባሕላዊ ሁኔታ የነበረውንም የሚያመለክት ነው:: እግር ግን ስለሚንቀሳቀስ ከመሬቱ አቧራ የተነሣ ይቆሽሻል፤ ስለዚህ በየጊዜው መታጠብ ያስፈልገዋል::

በተመሳሳይ አገላለጽ በኢየሱስ ክርስቶስ መታጠብ ማለት በቃሉ መንጻት ማለት ነው፣ በእርሱ ማመን ማለት ነው:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ሀሳብ አንደገና ይመለስና «እናንተ ስለነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ» (15:3) ይላቸዋል:: ደቀ መዛሙርቱንና በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ የሚያነጻቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ነው፣ እርሱ የተናገረውን ቃል መቀበላቸው:: ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ጨለማን የሚያስወግድ ውስጥን የሚያነጻ ነው::

***13፥10 እናንተም ንጹሐን ናችሁ፥ ነገር ግን ሁላችሁም አይደላችሁም::*** ደቀ መዛሙርቱ ጌታ የተናገረውን ቃል ያመኑና የተቀበሉ ስለሆኑ ንፁሐን ናቸው:: ንጹሐን ሆነዋል:: ከመካከላቸው ግን በተቀበለው ቃል



የማይኖር የአስቆሮቱ ይሁዳ ስላለ ***ሁላችሁም አይደላችሁም*** ይላቸዋል:: (እንዲሁም 13፥18)::

***13፥11 አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ ነበርና፤ ስለዚህ:- ሁላችሁም ንጹሐን አይደላችሁም አለ::*** ምንም እንኳን ጌታ የይሁዳን እግር እንደ ሌሎች ደቀ መዛሙርቱ ቢያጥብም በሰማው ቃል ያልኖረ በመሆኑ ይሁዳ ንጹሕ አልነበረም::

***13፥12 ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን?*** ጌታ በሚታይ ሁኔታ ያደረገው እግራቸውን ማጠቡ ነው:: ነገር ግን ከዚህ አልፈው እንዲያስተውሉ የሚፈልገው ነገር አለ:: ስለዚህ ስለማስተዋላቸው ይጠይቃቸዋል:: በማጠቡ ትሕትናውን ለእነርሱም ያለውን ፍቅርና ማንጻት ሁሉ ገለጸላቸው:: ይህን ግን እንዲያስተውሉ ይፈልጋል:: እንዲያስተውሉት ከሚገባቸው መካከል አንዱ:- ***እኔ ጌታና መምህር ስሆን 13፥14*** የሚለውን ነው:: እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ በላይ ነው፣ አስተማሪያቸው ነውና:: ጌታም ነው:: እግራቸውን ማጠቡ ስለሚወዳቸው ነው:: እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያስፈልገው ነገር ኢየሱስ ጌታና መምህር ሆኖ እያለ የተከታዮቹን እግር ለማጠብ ራሱን ዝቅ ካደረገ ማንም በመሪነት ደረጃ ያለ ሰው የሚመራቸውን ሰዎች ዝቅ ብሎ ለማገልገል የማይከብደው መሆን እንደሚገባው ነው::

***13፥14 እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፤*** በማለት ያዛቸዋል:: ጌታ ካደረገው ለእርስ በርሳቸው የሚሆንን መዋደድናአንዱ ሌላውን ለማገልገል ትሕትናን ያስተምራል:: በተግባርም እንዲማሩ:- ***እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ 13፥15*** አላቸው:: ጌታ ትሕትናን፤ አንዱ ሌላውን ማገልገልን በምሳሌ አሳይቷል::

***13፥16 ባሪያ ከጌታው አይበልጥም፥ መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም::*** የጌታ ደቀ መዝሙር የሆነ ሰው በምድር ላይ በአገልግሎት ምንም ዓይነት ቦታ ቢደርስ፤ ማዕረግ ቢሰጠው፤ በየትኛ ውም ሀገርና ዘመን ቢኖር ምን ጊዜም የጌታ ባሪያ ነው:: ጌታ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ካደረገ ባሪያ የሆነ የእርሱ አገልጋይ ከጌታው ከክርስቶስ አይበልጥምና ይህን ምሳሌ ተገንዝቦ ሊያደርገው ይጠበቅበታል:: ሌሎችን ዝቅ ብሎ ለማገልገል አለመፈለግ ራስን ከክርስቶስ በላይ አድርጎ እንደማየት ይሆናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ትሕትናን እንጂ ትዕቢትን አላስተማረም::

እኛ ላለንበት ዘመንና ሀገር ተስማሚው የአገልጋይነት መግለጫ ምንድን ነው? እግር ማጠብ ነውን?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበበት ወቅት በዚያ አካባቢና ወቅት እግር ማጠብ እንግዳን የመቀበል የማክበር ትልቅ ትርጉምና ጠቀሜታ ነበረው:: በዚያ ባሕል የሚጠበቅና የሚፈለግም ነበር:: በዚያ ዘመን ብዙዎቹም ያለ ጫማ (ወይም በነጠላ ጫማ ብቻ) ይሄዱ ስለነበረ የቆሸሸን እግር ለማንፃት ይፈለጋል::

ጌታ ኢየሱስ እግር በማጠብ ያሳየው ምሳሌነቱ ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት በዓለም ዙሪያ የእርሱ ምስክሮች የሚሆኑት ሁሉ ትሕትናውንና ምሳሌነቱንም እንዲመለከቱና እንዲያሳዩ ጭምር ነው:: መጽሐፍ እንዳለ «የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» (ማር 10፥15፤ 1ጴጥ 2:21)::

ጌታ ኢየሱስ እግርን በማጠብ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማራቸውና ዛሬ ለእኛም ሊቀርልን የሚገባው ትልቁ ትምህርት «አገልጋይነት» ነው:: አገልጋይነት ሌላውን የሚጠቅም ነገር በፍቅር ማድረግ ነው:: አንድ ሰው ያለበት ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ ወይም ማዕረግ ሳያግደው (ሳይተናነቀው) ዝቅ ብሎ ሌላውን ለማገልገል መቻል ነው:: መሪ ሆኖ ሳለ መሪነቱን በአገልጋይነት ልብና ሁኔታ መፈጸም ነው::

በአሁኑ ዘመን አገልጋይነትን ለማሳየት እግርን ከማጠብ ሌላ እንደየአካባበቢው የተለያዩ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ:-

- የቤተ ክርስቲያን ሥራዎች እስከሆኑ ድረስ ሌሎች ሊሠሩ የማይፈልጓቸውን ዝቅተኛ የሚባሉ ሥራዎችን ለማድረግ ዝግጁ መሆን፤ ማድረግም ነው::
- በቅዱሳን መካከል ስለ መብትና ስለ ግል ጥቅሞች አለመሟገት፤
- የራስን ፍላጐት ከማሟላት በፊት ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ ማድረግ፤
- አንድ ሥራ ተሠርቶ ወደ ውጤት ሲደርስ በእኔ መሪነት/ እንቀሳቃሽነት ነው የተሠራው ስለዚህ ምስጋናው ለእኔ ይገባኛል አለማለት፤

እንዲህ ዓይነት እውነተኛ ትሕትናን የሚያሳዩ ተግባሮችን መሥራት ሊሆን ይችላል::



***13፥17 ይህን ብታውቁ፥ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ::*** በመንፈሳዊው አገላለጽ ብፁዕ፣ ደስተኛ፤ የተሳካለት ሰው መሆን የሚቻለው በማወቅ ብቻ ሳይሆን ያወቁትንም በማድረግ ነው:: በክርስትና ሕይወት ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ ከእግዚአብሔር የሆነ ደስታ ወይም በረከት የሚመጣው የተሰጠውን ተግባር በመፈጸም ነው:: ይህም ሌሎችን በማገልገል በኩል የሚገኝ ታላቅ ደስታ ነው::

እዚህ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር በተያያዘ ክርስቲያኖች ሊያስተውሉት የሚገባ ነገርም አለ:: ብዙ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት[56] አእምሮን የሚያሳድግ፤ እመለካከትን የሚያሰፋ ብቻ ይሆናል:: ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ «እውቀት» ያስገኛል:: እውቀት ግን <u>ብፁዕ አያደርግም</u>:: እንዲያውም እውቀት ያስታብያል (1ቆሮ 8:1):: ብፁዕነት የሚመጣው ያወቁትን በሥራ ላይ ሲያውሉት፤ በአገልግሎት ሲገለጥ ነው:: <u>እውቀት በትሕትና ሲገለጥ</u> አገልግሎት ይሆናል:: በትሕትና በተግባር ላይ የዋለ እውቀት ደግሞ ብፁዕ ያደርጋል:: ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር በተያያዘ ሊመጣ የሚችለውን ትዕቢት የማስወገጃው መንገድ ያወቁትን በትሕትና በአገልግሎት ላይ በማዋል ነው::

***13፥18 መጽሐፍ:- እንጀራዬን የሚበላ ተረከዙን በእኔ ላይ አነሣብኝ ያለው ይፈጸም ዘንድ:-*** ጌታ አልፎ እንደሚሰጥ ቀደም ሲል በመጽሐፍ ተገልጿል (መዝ 41፥9):: እዚህ ላይ የምናየው ተረከዝ የማንሣት አገላለጽ ምሳሌያዊ ነው:: ሣር ወይም ጥራጥሬ የሚሰጠውን ሰው ወደ ኋላ ለመምታት እግሩን በሚያነሣ ፈረስ ምሳሌ የተገለጸው የአስቆሮቱ ይሁዳ ድርጊት ነው:: ይሁዳ በጌታ መልካም ነገር ተደርጐለት እያለ እርሱን አሳልፎ ለመስጠት በእርሱ ላይ ተነሣ::

በመዝ 41 ዳዊት ይህን የተናገረው ባልንጀሮቹ እንዴት በእርሱ ላይ እንደተነሡ ሲገልጥ ነበር:: በዳዊት ላይ የቅርብ ወዳጆቹ ተነሡበት አኪጦፌልም ሳይቀር:: አኪጦፌል ዳዊትን ከተቃወመ በኋላ በመጨረሻ ሄዶ ራሱን ሰቀለ (2ሳሙ 16፥20፤ 17፥3፤23):: ይሁዳም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የነበረ የቅርብ ሰው ሆኖ ሳለ አሳልፎ ሰጠው:: ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ራሱን ሰቀለ::

***13፥19 በሆነ ጊዜ እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፥ ከአሁኑ ጀምሬ አስቀድሞ ሳይሆን እነግራችኋለሁ::*** ይሁዳ አሳልፎ እንደሚሰጠው ኢየሱስ ያውቅ ነበር (6፥64፣70፣71፤ ማቴ 17፥6፣22-23፤ 20፥17-19):: ደቀ መዛሙርቱ ባሉበት ጌታ ይህን የሚናገረው በኋላ

[56] Theological studies

እንዲያስተውሉ ነው (ሐዋ 1÷16):: ይህ ደግሞ በጌታ ላይ ያለ አምነታቸውን ያሳድጋል::

***13÷20 ማናቸውን የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል::*** በ13÷16 ላይ ስለ መልእክተኛ ጌታ ተናግሮ ነበር:: በዚህ ላይ ደግሞ ***የምልከውን*** ሲል ደቀ መዛሙርት ወደፊት የሚኖራቸውን ተግባርና ተልእኮ የሚያመለክት ነው:: እነርሱ የሚሄዱት ከጌታ ተልከው ነውና በመልእክተኛነታቸው የእርሱ እልጋዮች ይሆናሉ:: የእነርሱን ቃል የሚቀበል በኢየሱስ ያመነ ማለትም በላከው በእግዚአብሔር አብ አመነ ማለት ነው::

***13÷21 ኢየሱስ ይህን ብሎ በመንፈሱ ታወከ::*** ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ስመሆኑ ሌላ ማስረጃ ነው:: ምንም እንኳ የእርሱ አልፎ መሰጠት በመጽሐፍ የተነገረ እንደሆነ ቢያውቅም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በውስጡ እንደተሰማው ያሳያል:: ስለሆነም፣ ***እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል አለ 13÷21***:: ማንነቱን ያወቀ፣ ከእርሱ ጋር የኖረና በእርሱም የተገለገለ ሰው ከመካከል ወጥቶ ጌታውን አሳልፎ መስጠት የሚያስገርም ነገር ነው:: እርሱ ከጠራቸውና አብረውት ከኖሩት መካከል በጌታ ላይ እግሩን የሚያነሣ ሰው መሆን፣ ጌታን በመንፈሱ እንዲታወክ አደረገው::

ጌታን አሳልፎ የሚሰጠው ሰው ከመካከላቸው እንደሆነ ሲሰሙ ደቀ መዛሙርቱ ***እመንትተው እርስ በርሳቸው ተያዩ 13÷22***:: የጌታን ማንነት ያውቃሉ፣ የሚናገረውም እውነት እንደሆነ እርግጠኞች ናቸው:: ከእነርሱም መካከል ስለሆነ ***እርስ በርሳቸው*** አንተ ትሆን ወይስ አንተ ነህ ይህን የምታደርገው በሚል ዓይነት ሁኔታ ይተያያሉ:: ከአሥራ ሁለቱ መካከል ምናልባት አሳልፎ ለመስጠት የማይጠረጠረው ይሁዳ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም ይሁዳ፡- እንደኛየገንዘብ ኃላፊ ስለሆነና ሁለተኛ ደግሞ «ሰድሆች የሚቆረቆር መንፈሳዊ ሰው» ስለሆነ ነው::

በዚህ ሁኔታ የጴጥሮስ መልስ እንደተለመደው ፈጣን ነበር:: ጴጥሮስ በዮሐንስ በኩል ኢየሱስን ሊጠይቅ የወደደው ያ ሰው ማን እንደሆነ? ***ስለ ማን እንደተናገረ ንገረን 13÷24*** ብሎ ነው:: ያ ሰው ማን እንደሆነ ጌታ በስም ጠርቶ ቢናገር ጴጥሮስ ምን ዓይነት ምላሽ ሊኖረው እንደሚችል መገመት ይችላል:: በመካከላቸው ከነበረው ሁለት ሰይፍ ጴጥሮስ አንዱን ይዞ ነበርና (ሉቃ 22:38) ያን አሳልፎ የሚሰጠውን ሰው እንዴት ያህን ታደርጋለህ? ብሎ እዚያ ላይ «ዋጋውን» ሊሰጠው ፈልጎስ ቢሆን? እንኳንስ ከአሥራ ሁለቱ መካከል ጌታን አሳልፎ



የሚሰጥ ኖሮ ሊይዙትም እንኳን ከመጡት የሊቀ ካህናት ባሪያዎች መካከል ጴጥሮስ አንዱን በሰይፍ መትቶ ጆሮውን የቆረጠ «ተቆርቋሪ» ሰው ነው (ዮሐ 18÷10)::

***13÷25 እርሱም በኢየሱስ ደረት እንዲህ ተጠግቶ፡-*** በዚያን ዘመን ምግብ ሲበሉ ሁሉም ተቀምጠው የሚበሉ ቢሆንም በፋሲካ በዓል ግን ጋደም ብሎ ወይም ተጠግቶ መብላት የተለመደ ነበር::[57] ይህ ሰው በኢየሱስ ደረት ላይ የተጠጋው፡- ***ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር! ከደቀ መዛሙርቱ! አንዱ ነው 13÷23***: ጌታ አልዓዛርን ይወድ እንደነበረም ይታወቃል (11÷3):: ይህ ግን ***ከደቀ መዛሙርቱ! አንዱ*** ነበረ:: ይህ ሰው የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ዮሐንስ ነው:: ይህም ሰው ***ጌታ ሆይ ማን ነው? አለው 13:25::*** የጌታ መልስ ***ቁራሽ አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው ብሎ መለሰለት 13:26::***

***13÷26 ቁራሽም አጥቅሶ ለስምዖን ልጅ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ሰጠው::*** እንዲህ በማድረጉ አሳልፎ የሚሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ መሆኑን አስረዳ:: ስለዚህ አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳ መሆኑን በዚያን ወቅት የተረዳ ምናልባት በደረቱ ተጠግቶ የነበረው ዮሐንስ ብቻ ሊሆን ይችላል::

***13÷27 ቁራሽም ከተቀበለ በኋላ ያን ጊዜ ሰይጣን ገባበት::*** ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ አስገብቶ ነበር (13÷2):: አሁን ደግሞ ራሱ ገባ:: ከዚህ በኋላ አሳልፎ ለመስጠት የነበረውን አሳብ ሊፈጽመው ፈጠነ:: የአስቆሮቱ ይሁዳ የዲያስሎስን አሳብ በማስተናገድና ላዲያብሎስ መሣሪያ በመሆኑ በዚህ ድርጊቱ ተጠያቂ ነው::

***13÷27 እንግዲህ ኢየሱስ፡- የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ አለው::*** ጊዜው የፋሲካ በዓል ጊዜ ነው:: ይሁዳ ደግሞ ገንዘብ ያዥ ነው (12÷6):: ስለዚህ ጌታ ***ቶሎ ብለህ አድርግ*** ሲለው ***ከተቀመጡት ለምን ይህን እንዳለው ማንም አላወቀም:: ይሁዳ ከረጢቱን የያዘ ስለሆነ ኢየሱስ፡- ለበዓሉ የሚያስፈልገንን ግዛ ወይም ለድሆች ምጽዋት እንዲሰጥ ያለው ለአንዳንዱ መሰሏቸው ነበርና 13:28-29::*** በዓሉ ለሰምንት ቀን የሚቆይ የቂጣ በዓል ነው:: ስለዚህ ለዚያን ያህል ቀን የሚሆን እንዲገዛ የታዘዘ መስሏቸዋል ማለት ነው:: ***ወዲያውም ወጣ***

[57] In those days it was the custom for people to recline only at the Passover meal; usually they ate sitting up. The host would be at the head of the group, and a special guest to the right of the host would have his head near the host's chest. Ibid. p.278.

*ሌሊትም ነበረ 13፥30::* የወጣው አሳልፎ ሊሰጠው መሆኑን እያወቀ ለዚህም ተግባር ከመካከላቸው ሲወጣ እያየ አልከለከለውም፤ አላገደውም፤ ጌታ የመጣበትን ዓላማ ይፈጽም ዘንድ የተጻፈውንም እንዲያደርግ ነገረው እንጂ::

ይሁዳ ማንነቱን ከጓደኞቹ ደቀ መዛሙርት ደብቆ የኖረ ሰው ነው:: የመደበቂያው ስልት ደግሞ በጣም መንፈሳዊ በመምሰል ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ማንነቱን ያውቅ ነበር:: ዛሬም በክርስቲያኖች መካከል የራሳቸውን ማንነት ደብቀው ለመኖር የሚጥሩ ሰዎች ይኖራሉ:: ጊዜው ደርሶ ሁኔታው ካልገለጣቸው በስተቀር በጣም መንፈሳዊ በመምሰል የሚኖሩ ሲኖሩ ይችላሉ:: ኢየሱስ ግን ሁሉንም ሰው ያውቃልና የእያንዳንዱ ሰው ንግግርና ተግባር ከምን እንጻር እንደሆነ ይመዝነዋል:: እግዚአብሔር ልባችንን ያውቃልና (1ሳሙ 16፥7)::

*13፥31 ከወጣም በኋላ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- አሁን የሰው ልጅ ከበረ እግዚአብሔርም ስለ እርሱ ከበረ::* ይሁዳ ከአሥራ ሁለቱ ተለይቶ ከእራቱ ወጣ:: ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ዝግጅት ለማድረግ ሄደ:: በዚህ ጊዜ ጌታ *አሁን የሰው ልጅ ከበረ* ሲል ስለሞቱና ጊዜውም አሁን ስለመሆኑ መናገሩ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ይሞታል ከዚያም በሦስተኛው ቀን ይነሣል:: በዚህ የሰው ልጅ ይከብራል:: በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኩል እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ ለዚህ ወደ ምድር መጥቶአል::

*እግዚአብሔርም ስለ እርሱ ከበረ* ማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከበረ፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ የተላከው የአባቱን ፈቃድ ፈጽሟልና:: ማክበር በዚህ እገባብ የተላኩትን መልእክት ማድረስ፤ መፈጸም ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ዕቅድ በሚያስደንቅ ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መፈጸሙን ሲያመለክት ነው:: ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ደስታ መሆኑን ያሳያል::

*13:32 ወዲያውም ያከብረዋል፡-* የሚለው በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚፈጸመውን ትንሣኤና እርገቱን የሚያመለክት ይሆናል:: ይሁዳ ከመካከላቸው ወጥቶ ሄዷልና አሳልፎ መስጠቱን በቅርብ ጊዜ ስለሚፈጽም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ሕይወት የመጨረሻው ሰዓት እየሞላ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም መታዘዝ ሊገለጽ ነው:: ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሊከብር ነው:: እንዲሁም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በአብ ዘንድ የነበረውን ክብር ኢየሱስ ሊወስድ ነው:: ስለሆነም የሰው ልጅ ሊከብር ነው::



*13፥33 ልጆች ሆይ ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፤ ትፈልጉኛላችሁ፤ ለአይሁድም፡- እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አይቻላችሁም እንዳልኋቸው፥ አሁን ለእናንተ ደግሞ እላችኋለሁ::* ልጆች ብሎ ጌታ ደቀ መዛሙርትን ሲጠራቸው በእርሱና በደቀ መዛሙርቱ መካከል ያለውን የመቀራረብ መጠን ያሳያል:: እነርሱን ፈጽሞ ወደዳቸው እስከ መጨረሻም ወደዳቸው (13፥1):: ለእነርሱ የሚነግራቸው የመሄጃው ጊዜ እንደቀረበ *ጥቂት ጊዜ* ብቻ እንደቀረው ነው:: ኢየሱስ የሚሄደው ወደ አባቱ ነው (14፥6፣28):: ከእርሱ ጋር ለመሆን ወደ ቀደመ ክብሩ ይመለሳል (17፥5፤24):: በዚህ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው ክብር ደቀ መዛሙርቱ አብረው ሊሆኑ አይችሉም::

ስለሆነም፡- *እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አይቻላችሁም 13፥33* ይላቸዋል:: ይህን ቀደም ሲል ጌታ ለአይሁድ ብሎት ነበር አሁን ደግሞ ለደቀ መዛሙርቱ ጊዜው ሲደርስ ይላቸዋል:: ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ወደሚሄድበት ቦታ ወደ አብ ቀኝ ሊሄዱ አይችሉም::

*13፥34 እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ::* ይህ ትእዛዝ *አዲስ* የመዋደድ ትእዛዝ ነው:: ይህ መዋደድ በኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት የታየ ነው:: እርሱ በፍቅር ጠብቆ በአንድነት አቆይቷቸዋል:: እርሱ በሚሄድበት ጊዜ ያ ፍቅር እንዲቆይ በምሳሌነት አሳያቸው:: ስለዚህ እርስ በርስ እንዲዋደዱና ይህ ፍቅር በመካከላቸው እንዲቆይ ከመሄዱ በፊት የመጨረሻ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል::

በመሠረቱ መዋደድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትእዛዝነቱ አዲስ አይደለም:: በብሉይ ኪዳንም ባልንጀራን ስለ መውደድ ወይም እርስ በርስ ስለ መዋደድ ትእዛዝ አለ (ዘጸ 20፥12-17፤ ዘሌ 19፥18፣ 33-34፤ ዘዳ 5፥16-21፤ 22፥1-4):: እንዲሁም በአዲስ ኪዳን (ማቴ 5፥38-45፤ 7፥12፣ 23፥36-40፤ ሉቃ 10፥25-37):: ይህን ትእዛዝ አዲስ ያደረገው በኢየሱስ ምሳሌነት የተመሠረተ ስለሆነ ነው:: የፍቅርን ትእዛዝ በቃል የገለጸው ጌታ ራሱ በተግባር ደግሞ አሳያቸው:: ስለዚህም እንደ ወደድኋችሁ ይላቸዋል:: ልክ በትሕትና ዝቅ ብሎ ሌላውን ስለ ማገልገል ምሳሌ እንደተወላቸው እንዲሁም እርስ በርስ ስለ መዋደድ ደግሞ ምሳሌያቸው እርሱ ነው::

*13፥35 እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ::* ደቀ መዛሙርቱ እንዲኖራቸው ጌታ የሚያዛቸው አዲስ የመዋደድ ትእዛዝ የእርሱ ለመሆናቸው

ምልከት ነው። እርሱ ወዷቸዋልና፤ ፍቅርን አስተምሯልና፤ አሳይቷልምና የእርሱ የሆኑ ደግሞ ከክርስቶስ የተነሣ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ ይገባቸዋል። ስለ ክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል። ምስክሮች የሚሆኑት እርስ በርስ በመዋደዳቸው ነው። እርስ በርስ ሲዋደዱ የክርስቶስ መሆናቸውን ***ሰዎች ሁሉ*** ያውቃሉ፣ ዓለም ትረዳለች። የክርስቲያኖች የእርስ በርስ ፍቅር ተቃዋሚ በሆነው ዓለም ውስጥ አማኞችን በአንድ ላይ ጠብቆ የሚያኖር የማያምኑትን ወደ ክርስቶስ የሚስብ ጠንካራ ገመድ ነው። ፍቅር አንድ ሰው ከወንድሙ በሚያገኘው ጥቅም ላይ ያልተመሠረተ በጐ ኅሊና፤ ቅን አመለካከትና በተግባር የሚገለጽ መልካም ሥራ ነው።

***13፥36 ለምሃን ጴጥሮስም፦ ጌታ ሆይ፥ ወዴት ትሄዳለህ? አለው።*** መቼም ስምዖን የደቀ መዛሙርቱም አፍ ነው ማለት ይቻላል። ስሜቱን ለመግለጽ፣ ለመጠየቅ የማይዘገይ ሰው ነው። አሁንም ከሌሎቹ ይልቅ ጌታን የሚጠይቀው ስምዖን ነው። ቀደም ሲልም ኢየሱስን እንዲጠይቀው ለዮሐንስ ነግሮት ነበረ (13፥24)።

ጌታም ለስምዖን፦ ***ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም፥ ነገር ግን በኋላ ትከተለኛለህ ብሎ መለሰለት 13፥36***፡ አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞትና ትንሣኤ በኩል ወደ ክብር ሊሄድ ነው። በዚህ መንገድ ጴጥሮስ ኢየሱስን አይከተለውም። ***ነገር ግን በኋላ ትከተለኛለህ*** ሲለው ክርስቶስ በሄደበት መንገድ እንደሚከተለው ያመለክታል። አንደኛው ስለ በአሟሟቱ ነው (21፥15-19)። ሁለተኛው ደግሞ ከሞቱ በኋላ በክብር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሄድ መሆኑን ያመለክታል። በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሰው ሁሉ ከሞት በኋላ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በክብር ይሆናልና።

***13፥37 ጌታ ሆይ፥ አሁን ልከተልህ አለመቻሌ ስለምንድር ነው? ነፍሴን ስንኳ ስለ አንተ እሰጣለሁ አለው።*** ጴጥሮስ ኢየሱስን ይወደዋል። እንደሚወደውም ይገልጣል። ጌታ ስለ በጐቹ ራሱን አሳልፎ እንደሚሰጥ የተናገረውን ዓይነት (10፡11፣15፤17) ጴጥሮስም ቢያስፈልግ ስለ ጌታ ነፍሱን አሳልፎ ለመስጠት ምን ያህል ዝግጁ እንደሆነ ይገልጣል። በሌላም ቦታ ጌታ እንደሚሞት ሲናገር ጴጥሮስ «አይሁንብህ» (ማቴ 16:22) ያለው ኢየሱስን ይወድ የነበረ ደቀ መዝሙር ነው። ጴጥሮስ የሰውን አስበ እንጂ ሰነገሩማ ጌታን መውደዱ ነበረ። እንደ ጴጥሮስ አሳብ ኢየሱስ ከሚሞት እርሱ ስለ ኢየሱስ ነፍሱን አሳልፎ ቢሰጥ ይመርጥ ነበር። ምን ያደርጋል! የእርሱ ሞት የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ አይረዳም።



***13፥38 እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ አይጮኽም።*** ጴጥሮስ ለጌታ በአፍ የሚገለጽ ከፍተኛ ፍቅር አለው። ጌታን ሊይዘው የመጣውንም የሊቀ ካህናቱን ባሪያ ጆሮ እስከ መቁረጥ ድረስ የሚያደርስ ወኔ አለው። ይህ ፍቅርና ወኔ ግን አልዘለቀም። ጌታም ***ትክደኛለህ*** እንዳለው እንዲሁ ሆነ፤ የክህደቱም ዓይነት ኢየሱስን «አላውቀውም» እያለ ነው (ማቴ 26፥69-75፤ ማር 11፥66-72፤ ሉቃ 22፥54-62)። ወይ አለማወቅ!!!

በዚህ ምዕራፍ የጌታ ደቀ መዛሙርት ስለሆኑት ስለ አስቆሮቱ ይሁዳና ስለ ጴጥሮስ ድርጊት ተመልክተናል። ሁለቱም የጌታ ደቀ መዛሙርት ናቸው። የሁለቱም ተግባር ጥሩ አይደለም። የይሁዳ አሳልፎ መስጠት ነው፣ የጴጥሮስ ደግሞ መካድ። ይሁን እንጂ የሁለቱ ፍጻሜአቸው የተለያየ ሆኗል። ይሁዳ አሳልፎ ከሰጠው በኋላ ወደ ንስሐ አልተመለሰም። ጴጥሮስ ደግሞ አልቅሶ ተመለሰ።

የሁለቱንም ማንነት ጌታ ያውቃል፣ ሁለቱም ምን እንደሚያደርጉ አስቀድሞ ያውቃል። ያንን እንዳያደርጉ ሁለቱንም ሊከለክላቸው ይችል ነበር ብለን ማለብ እንደለው እንችላለን። ሰዎች የራሳቸውን ምርጫ ያደርጉ ዘንድ ጊዜ (ዕድል) ይሰጣቸዋል። እውነቱን ካወቁ (ከተረዱ) በኋላ የራሳቸውን ምርጫ እንዲያደርጉ ይተዋቸዋል። ለምርጫቸው ደግሞ ተጠያቂ ይሆናሉ። በንስሐ ለተመለሰው ጴጥሮስ ይቅርታን አድርጐለት ኃላፊነትንና አደራን ሰጠው (ዮሐ 21:15-57)፤ በራሱ ኃጢአት ሳይጸጸት የቀረው ደግሞ ከጌታ ዘንድ ፍርድ ይጠብቀዋል።

# ምዕራፍ አሥራ አራት

በደቀ መዛሙርቱ መካከል አስገራሚና አስደንጋጭ ሁኔታዎች እየሆኑ ነው:: አስገራሚው መምህራቸው ኢየሱስ የእነርሱን እግር ማጠቡ ሲሆን አስደንጋጩ ከሦስት ዓመት በላይ አብረውት ከነበሩት ደቀ መዛሙርት አንደኛው አሳልፎ የሚሰጠው መሆኑ፤ ሌላኛው ደግሞ የሚክደው መሆኑ ነው:: ስለዚህ በመካከላቸው ድንጋጤና መታወክ ይኖራል::

ጌታም የሚሄድበት ጊዜ መድረሱን ነግሯቸዋል:: ይህ ደግሞ ሌላ ፍርሃት የሚያመጣ ነገር ነው:: ሆኖም እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አድርገው እንዲቀጥሉ አጠንክሮ ያስተምራቸዋል:: እርሱ ሲሄድም ቦታ እንደሚያዘጋጅላቸው እንደሚመስስም በመናገር ያጽናናቸዋል:: በምዕ 14 በኢየሱስ ክርስቶስና በአብ መካከል ስላለው አንድነት የሚከተሉትን እናስተውላለን::

- ኢየሱስና አብ በባሕርይ አንድ ስለሆኑ አንዱን ያየ ሌላውንም አየ ማለት እንደሆነ፤
- ኢየሱስና አብ አንድ ስለሆኑ ኢየሱስ በአብ ውስጥ እንዳለ ሁሉ፣ አብም በእርሱ መኖሩን፤
- በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለቀረበ ጸሎት ሁሉ እግዚአብሔር መልስ እንደሚሰጥ፤

በዚህ ምዕራፍ ከቁ.15-31 ባለው ክፍል ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድ ተስፋ ይሰጣቸዋል:: ተስፋውንም ሲናገር እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሄደ በኋላ አጽናኝ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እንደሚመጣ እና እርሱ እንደሚያጽናናቸው ቁ.15-16፤ እንደሚመራቸው ቁ.17፤ እንደሚያስተምራቸው ቁ.26 ይነግራቸዋል:: ይህ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ የሚኖር ነው::

***14፥1 ልባችሁ አይታወክ:-*** በዚህ ወቅት ደቀ መዛሙርት ሁሉም በሁኔታው ሳይፈሩና ሳይደናገጡ አይቀሩም:: ከመካከላቸው ጌታን አሳልፎ የሚሰጥ እና የሚክድም መኖሩ ያስፈራቸዋል:: ኢየሱስ



ከእነርሱ ተለይቶ የሚሄድ መሆኑ አስደንጋጭ ነገር ነው:: ከሁሉም በላይ ጴጥሮስ የሚክድ ከሆነ፣ ሌላውማ ምን ያህል ይጸናል? የሚል ጥያቄ ያስነሣል:: ጌታ ለዚህ ሁኔታ የሰጠው መልስ እመኑ የሚል ነው::

***14፥1 በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ::*** ይህን ሁኔታ ጌታ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ የሚነግራቸው፣ ሁኔታው በተፈጸመ ጊዜ እንዳይደናገጡና ያመኑ እንዲሆኑ ነው:: ***ከሆነም በኋላ ታምኑ ዘንድ አሁን አስቀድሞ ሳይሆን ነግሬአችኋለሁ 14፥29*** እንዳለ:: ጌታ የሚነግራቸው በፊታቸው ባሉ ጥቂት እጅግ ከባድ ቀናት በእብ ያላቸው እምነት እንዳይወድቅባቸው ነው:: እርሱ የተናገረው ሁሉ ይሆናልና:: የእርሱ ሞት እንደሚሆን ሁሉ ትንሣኤውም ይሆናልና፡፡ ስለዚህ በቅርብ ጊዜ የሚፈጸመውን መከራና ሞት ብቻ አይተው እንዳይበተኑ፣ እንዳይፈሩ፣ ትንሣኤም እንደሚመጣ እንዲገነዘቡ ነው::

***14፥2 በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ::*** ይህኛው ቃል እርሱን ለሚከተል ሁሉ ለእያንዳንዱ ሰው የመኖሪያ ክፍል ወይም ቤት ይዘጋጅለታል የሚል ይመስላል:: ከዚህም የተነሣ በአንዳንድ የመጽሐፉ ማብራሪያ ጸሐፊዎች ዘንድ የሚታሰበው በሰማይ በአማኞች ቁጥር ያህል ቤቶች እንደሚኖሩ ዓይነት ተደርጎ ነው:: በሌላ በኩል እዚህ ላይ ትልቁ መልእክት አሁን በፍርሃት ላይ ያሉት የጌታ ደቀ መዛሙርት ወደ ሰማይ በሚሄደው ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚዘጋጅላቸው መኖሪያ እንደሚኖር ያረጋግጣል:: የዚያ መኖሪያ ዋናው ባሕርይ ከእርሱ ጋር መኖር ነው:: ***እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ 14፥3*** እንደሚል:: ያ ደግሞ የአባቱ ቤት ነው:: በላይ በሰማይ ያለ የእግዚአብሔር መኖሪያ:: በ13፥33 ላይ ደቀ መዛሙርትን «እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አይቻላችሁም» ብሏቸው ነበረ:: አሁን ደግሞ ***ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ 14፥3*** አለ::

***14፥2 እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር:-*** ጌታ የሚሆነውን ይናገራል ተስፋ ይሰጣል፤ የማይሆነውን ደግሞ አይሆንም ይላል:: በፊት የሆነውን ከደቀ መዛሙርቱ አልሸሸጋቸውም:: ስደትና መከራም እንደሚኖር አስጠንቅቋቸዋል (16፥2):: ሊነገራቸው የሚገባውንና እውነት የሆነውን ሁሉ ነግሯቸዋል:: እርሱ ሁልጊዜ እውነትን ስለሚናገር የታመነ ነው:: የታመነ ስለሆነ ስለ ወደፊት የተናገረው ሁሉ እውነት ነው:: ስለዚህ በላይ ስፍራ እንደሚያዘጋጅላቸው የነገራቸው እውነት ነው::

***14፥3 ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ፡፡*** ኢየሱስ ክርስቶስ ***ሁለተኛ*** የሚመጣበት አንዱ ምክንያት አማኞችን ለመውሰድ ነው፡፡ ለዘላለምም ከክርስቶስ ጋር እንዲኖሩ ይወስዳቸዋል፡፡ መጥቼ ***እወስዳችኋለሁ*** ሲል እነዚያን አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርትና ከእነርሱም በኋላ በእነርሱ በኩል የሚያምኑትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ሁለተኛ የሚመጣበት ጊዜ አይታወቅም፡፡

***14፥4 ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፥ መንገዱንም ታወቃላችሁ፦*** እርሱ መጥቶ ስለሚወስዳቸው የሚሄዱበትን መንገድ ያውቃሉ፡፡ እርሱ ወደሚሄድበት ይመራቸዋል፤ እርሱ መንገድ ነውና፡፡ ጌታ ይህን ሲል ***ቶማስ፦ ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄድበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው 14፥5፡፡*** የቶማስን ዓይነት ጥያቄ በ13፥36 ላይ ጴጥሮስም ጠይቆ ነበረ፡፡ ኢየሱስ የሚሄደው ወደ አብ ነው፣ መሄጃው መንገድ ደግሞ እርሱ ራሱ ነው፣ ይህን ቶማስ ገና አልተረዳም፡፡ አለመረዳቱን በመግለጹ ጌታ የሚቀጥለውን እንዲናገር ምክንያት ሆኗል፡፡

***14፥6 ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡*** ይህ መንገድ በቦታ ስም የሚጠራ አንድ የተወሰነ ሥፍራ አይደለም፡፡ ይህ መንገድ የሚወስደው ወደ ሕያው እግዚአብሔር ወደ አብ ነው፡፡ ወደ አብ የሚወስደው መንገድ ደግሞ ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አብ የሚወስደው ***መንገድ*** ነው፡፡ መንገዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ የሚደረሰውም ወደ እግዚአብሔር አብ ነው፡፡ ወደ አብ የሚደረሰው እውነተኛ በሆነ ተስፋ፤ በእግዚአብሔር ተስፋ ነው፡፡ ያ ***እውነት*** ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ሲጨበጥ የሚችል ተስፋ ነው፡፡ ይህ ተስፋ የዘላለም ሕይወትን የሚሰጥ ***ሕይወት*** ነው፡፡ ይህ ሕይወት በአሁኑ ጊዜ አንድ ሰው ሲያምን የሚያገኘው ሆኖ ለዘላለም የሚቀጥል ነው፡፡

ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወት የሚመራና የሚያደርስ ***መንገድ*** ነው (ዮሐ 1፥18፣ 8፥36፣ 10፥9፤ ቆላ 1፥15)፡፡ በጎዳና ላይ እንዳለ «መንገዱ ያውላችሁ ተከተሉት» እንደሚል አመልካች ምልክት (ቀስት) አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የእነ ዮሐንስ መጥምቁ አገልግሎት ነበረ፡፡ ኢየሱስ ግን ራሱ ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ ***መንገድ*** ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ መንገድ ጋር እኛ ኅብረት ስናደርግ መንገዱ ራሱ ወደ እግዚአብሔር ይወስደናል፤ እዚያም ያደርሰናል፡፡



በታሪክ ውስጥ በተለይም በአሁኑ ዘመን ስለ መቻቻል[58] ብዙ ይነገራል፡፡ በአንድ አካባቢ ወይም ሀገር የሚኖር ሕዝብ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ፤ አመለካከትና እምነት እንዲኖረው አይጠበቅምና በኅብረተ ሰብ ውስጥ አብሮ ለመኖር መቻቻል[59] በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ በጌታ ጊዜ የነበሩ አይሁድ እንኳ ጌታ በመካከላቸው እያለ አልተቀበሉትም፡፡ ስለ ትንሣኤ ሙታን የሚያምኑ ነበሩ አንዳንዶቹ ደግሞ አያምኑም ነበር፡፡ ይህ ማለት ታዲያ በመቻቻል ሰበብ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው መንገድ ኢየሱስ ብቻ ነው የሚለውን ለቀቅ በማድረግ (በማላላት) ብዙ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ ማሰብ አይደለም፡፡ ይህ ጨርሶ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይደለም፡፡

በሰማይም ወደሚኖረው አምላክ (ፈጣሪ) ለመድረስ የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ የተለያዩ እምነቶች ይናገራሉ፡፡ በሰማይ የሚኖረው ፈጣሪ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም እግዚአብሔር ተብሎ የሚጠራ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ነው፡፡ ይህ ፈጣሪ አንድያ ልጁን (ዮሐ 3፥16) የላከ እግዚአብሔር ነው፡፡ ይህ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን የምወደው ልጄ (ማቴ 3:17) ብሎ የጠራው ነው፡፡ ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ልጄ ብሎ የሚጠራ እግዚአብሔር ነው፡፡ ወደዚህ እግዚአብሔር የሚያደርሰው መንገድ ደግሞ አንድ ብቻ ነው፡፡ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለሆነም ሌላ መንገድ የለም፡፡ ስለዚህ በክርስትና እምነት የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ ***መንገድ*** መሆኑን አምኖ መቀበል ነው እንጂ መቻቻል የሚባል ነገር የለም፡፡

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው በሰማይ ወደሚኖረው የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሚያደርሰው ***መንገድ*** አንድ ብቻ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ይህንንም ያረጋገጠው ራሱ ከሙታን ተለይቶ በመነሣትና በአብ ቀኝ በመቀመጥ ነው፡፡ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱ ትምህርቱና የፈጸመው ሁሉ እውነት መሆኑን አረጋገጠ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ልዩ ነው፡፡ ስለዚህም ብቸኛ መንገድ ሊሆን ተገብቶታል፡፡ እንደ እርሱ ከሙታን የተነሣ ሰው በታሪክ ውስጥ አልተጻፈም፤ የለም፡፡

[58] Tolerance

[59] መቻቻል አጠር ባለ ሁኔታ አንድ ሰው የሌላውን ነፃነት እስካልተጋፋ (ወይም የማኅበረሰቡን ዋና እሴቶች (Core values) እስካልጣሰ) ድረስ ያመነውን አምኖ እንዲኖር መፍቀድ ማለት ነው፡፡

የሕይወት መንገድ አንድ ብቻ ነው ሲባል መንገዱን ማጥበብ እንደሆነ አድርገው የሚያስቡም ይኖራሉ:: አዎ የክርስትና መንገድ ጠባብ ነው:: ያ ጠባብ መንገድ ግን ሁሉንም ሰው ማስተናገድ የሚችል መንገድ ነው:: ጠባብ መሆኑ የክርስቶስን መንገድ መሄድ እግዚአብሔርን ማክበር ዋጋ የሚያስከፍል ስለሆነ ዋጋ ለመክፈል የወሰኑ ብቻ የሚሄዱበት መንገድ ስለሆነ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰው ለዓለም ሁሉ ስለሆነ መንገዱ ለሁሉም ሰው በቂ ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር ከሚያደርሱ መንገዶች አንዱ ሳይሆን ብቸኛው መንገድ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር ስለሚያደርሱ አማራጭ የደኅንነት መንገዶች አልተናገረም፤ አማራጮች የሉምና:: ያለው መንገድ አንድ ብቻ በመሆኑ ምርጫው ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ወይም አለመቀበል ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ ***እውነት*** ነው (1÷14፣17፣ 5÷19፣ 8÷29):: እግዚአብሔር አብን ማወቅ የሚቻለው እውነት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው:: የእርሱም ትምህርቱ ትክክለኛ ነው:: በእርሱ ውስጥ ውሸት፤ ጨለማ የለም:: ***እንዲህ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር 14÷2*** እንዳለ ስለሚሆነው ሁሉ እውነቱን ተናግሯል:: ስለዚህ ወደ አብ ለመድረስ እርሱ የተናገረውን ማመንና በቃሉም መኖር ይገባል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ***ሕይወት*** ነው (1÷4፣ 3÷15፣ 5÷26፣ 10÷10፣ 11÷25እ:: ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ለሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይሰጠዋል:: ከእርሱ በቀር ሌላ የሕይወት ምንጭ የለም::

***14÷7 እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁት ነበር::*** ከቁ.2-6 ባለው ክፍል ኢየሱስ ወደ አብ መድረሻ ብቸኛው መንገድ መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ ገልጾላቸዋል:: በቁ.7 እና ቀጥሎ ባለው ክፍል ደግሞ ኢየሱስን ማወቅ ማለት አብን ማወቅ እንደሆነ ያስረዳቸዋል:: (እንዲሁም 1÷18፤ ቆላ 1÷15፤ ዕብ 1÷3ን ይመልከቱ):: ይህን እውነት ደቀ መዛሙርት መገንዘብ ነበረባቸው:: ምክንያቱም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በነበራቸው የደቀ መዝሙርነት ጉዞ ይህን ሲያስተምራቸውና ሲገልጽላቸው ነበርና::

***14÷7 ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁትማል::*** ይህ የአሁኑ ማወቃቸው በማየት ላይ የተመሠረተ ማወቅ ነው:: ያላቸው ወደፊት ***ታውቁታላችሁ*** ብቻ ሳይሆን ***ከአሁንም ጀምራችሁ*** ነው:: ከዚያም ጊዜ ጀምሮ በማወቅ ማደግ እና ኅብረት ማድረግ እንደሚችሉ ያስረዳቸዋል:: ደቀ መዛሙርቱ ይህን ታላቅ እውነት አልተረዱም



ነበር:: ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ገና አልሞተም፤ አልተነሣም ነበር:: እንዲሁም ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበር::

***14:8 ፊልጶስ ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል፤ አለው::*** በቁ.7 ላይ አይታችሁትማል ብሎ ነበር ጌታ:: የፊልጶስ ጥያቄ ግን አሳየን የሚል ነው:: ***አሳየንና ይበቃናል*** የሚለው የፊልጶስ ጥያቄ ከፍተኛ ረሀብን ያመለክታል:: የፊልጶስ ጥያቄ ምናልባት የቀደሙ አባቶች እግዚአብሔርን እንዳዩት (ዘጸ 24÷9-10፣ 33÷18፤ ኢሳ 6÷1) እንዲሁ እርሱን ማየት መፈለጉ ነው:: ሆኖም ጌታ ቀደም ሲል የተናገረውን አልተረዳም:: የጌታ መልስ ግን:- ***አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቷል፤ እንዴትስ አንተ:- አብን አሳየን ትላለህ? 14÷9*** የሚል ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደሆነ እንዲሁም በሰው አካል የተገለጠውን ኢየሱስን ማየት አብን ማየትም እንደሆነ ገና አልበራለትም:: ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ የለበሰ እግዚአብሔር ነው (1÷14፤18)::

***14:10 እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?*** ይህ ቃል በእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስና በአብ መካከል ያለውን ፍጹም አንድነት ይገልጻል (እንዲሁም 10÷30፣38፤ 17÷21-24 ይመልከቱ):: ይህም ኢየሱስ በሁለቱ መካከል ያለውን ፍጹም አንድነት ለእኛ በሙላት እንደሚያሳይ ያመለክታል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ የለበሰ፣ በሥጋ ዓይን ሊታይ የሚችል አምላክ ነው:: እግዚአብሔርን በፍጹምነት ይገልጠዋል:: ኢየሱስ ክርስቶስና አብ በባሕርይ፣ በማንነት[60] አንድ ስለሆኑ በዓላማ አንድ ናቸው::

ስለሆነም ከዚህ አንድነት የተነሣ ኢየሱስ:- ***እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል 14÷10*** አለ:: የአንድነት ፍጹምነት የሚገለጥበት አንዱ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገረው በእርሱ ውስጥ የሚኖረው አብ የሚነግረውን መሆኑ ነው:: የፍጹም የአንድነታቸው መግለጫ አብ በኢየሱስ ውስጥ መኖሩ እንዲሁም ኢየሱስ በአብ ውስጥ መኖሩ ነው:: ይህ ለመረዳት አጅግ ከባድና ታላቅ ምሥጢር ነው:: መቼውንም ቢሆን የሥላሴን ምሥጢር በሙሉ ለመረዳት መሞከር ከንቱ ልፋት ይሆናል:: የሰው ውሱን አእምሮ የእግዚአብሔርን ማንነት በሙላት ለመረዳት አይችልምና:: ይህን መረዳትና ማመን ለደቀ መዛሙርትም የከበዳቸው ነገር ነበር::

---

[60] One in essence and purpose

ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ:- ***እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ 14፥11*** ይላቸዋል። የእግዚአብሔር ኃይል (ሀሳብ) ኢየሱስ ክርስቶስ በሠራቸው ምልክቶች ወይም ተአምራት ተገልጧል። እነዚህ ምልክቶች ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው። ስለሆነም ለደቀ መዛሙርቱ ምልክቶችን አይታችኋል፤ ከእነርሱ የተነሣ ***ስለ ሥራው እመኑኝ*** ነው።

***14፥12 በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።*** ኢየሱስ ያደረገው *ሥራ* እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚገልጥ፤ በአብ የተላከ እንደሆነ የሚመሰክር ነው። ኢየሱስ የሠራው *ሥራ* (ምልክቶችና ተዓምራት ሁሉ) የክርስቶስን ማንነት ለዓለም አሳይተዋል። አሁን ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚነግራቸው በእርሱ የሚያምኑ ከዚህ ***የሚበልጥ*** ነገር እንደሚያደርጉ ነው። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት የሚመሰክሩ *ሥራዎች* (ምልክቶች ወይም ተአምራትን) ስለማድረግ ይመስላል። ይህ ደግሞ ወንጌልን ለምድር ሁሉ ከማድረስ ጋር የተያያዘ ነው።

እነዚህ የሚበልጡ *ሥራዎች* ምንድን ናቸው? ጌታ ***የሚበልጥ*** *ሥራ* ያለው የሚያመለክተው ምናልባት ወንጌልን በብዙ ሀገሮች ስለ መሰበክ፤ በአገልግሎት ብዙ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ ማምጣት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ወደፊት ስለሚሠሩ አስደናቂ ተአምራት ሁሉ ሊያመለክት ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በስሙ እጅግ ታላላቅ ተአምራት ተደርገዋል። ይህ በመንፈስ ቅዱስ መውረድና ኃይልን በመልበሳቸው ምክንያት የተሠራ *ሥራ* ነው።

እዚህ ላይ የሚበልጠው *ሥራ* ምን እንደሆነ በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል። ይህ *ሥራ* እንዲህና እንዲህ ነው በማለት ዓይነቱን መናገር አዳጋች ቢሆንም ባሕርዩ ግን የክርስቶስን ማንነት የሚገልጥ መሆን አለበት። ያ *ሥራ* ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን መሆን አለበት። ደግሞስ ይህ የሚበልጥ *ሥራ* በደቀ መዛሙርቱ እንዴት ነው የሚሠራው? ከክፍሉ መገንዘብ እንደሚቻለው:-

- ይህን የሚሠሩ በእርሱ የሚያምኑ ናቸው (14፥12)።
- እንዲሁም በስሙ አብን የሚለምኑ ናቸው (14፥13)።
- ይህን የሚበልጥ *ሥራ* የሚሠራው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (14፥13)።



- ይህ የሚበልጥ *ሥራ* የሚሠራበት ዓላማ አብ በኢየሱስ እንዲከበር ነው (14፥13)።
- እንዲሁም ይህ የሚበልጥ *ሥራ* ***ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ 14፥14*** በሚለው ይጠቃለላል።

እንግዲህ እዚህ ላይ ማስተዋል የሚያስፈልገው:-

- የሚበልጠውን *ሥራ* የሚሠራው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን፤
- *ሥራውንም* የሚሠሩት ሰዎች አብን በኢየሱስ ስም መጠየቅ እንዳለባቸው፤
- አብም በደቀ መዛሙርቱ በኩል የሚበልጠውን *ሥራ* የሚሠራው ወልድ እንዲከበር መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል።

ስለሆነም ይህ <u>የሚበልጠው *ሥራ* የሚሠራው በደቀ መዛሙርቱ በኩል</u> መሆኑ የደቀ <u>መዛሙርቱን ታላቅነት አያመለክትም</u>። የሚያመለክተው አብ ወልድን ለማክበር በኢየሱስ ስም የሚጠየቀውን እንደሚያደርግና ይህም በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠ ሥልጣን መሆኑን ነው።

ይህ ሁሉ መሆኑ ኢየሱስ ወደ አብ ከመሄዱ ጋር የተያያዘ ነው፤ 14፥13። ከመከበሩ ጋር ማለትም *ሥራውን* ፈጽሞ በአብ ቀኝ ከመቀመጡ ጋር የተያያዘ ነው።

***14:14 አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።*** የሚበልጠውን *ሥራ* አድራጊው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አድራጊው ኢየሱስ ሆኖ በእርሱ የሚያምነውና የሚበልጥ ነገር ያደርጋል የተባለው የኢየሱስ መሣሪያ የሆነ ነው ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር እያለ እርሱ በቀጥታ ያደርግ ነበረ። አሁን ደግሞ፤ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ በእርሱ በሚያምኑት በኩል ሆኖ የሚበልጥ ነገር ያደርጋል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚጸልየው ሰው እኔ የምጸልየው ጸሎት እንደ ኢየሱስ ፈቃድ ወይም ሀሳብ ወይም እንደ ቃሉ የሆነ ጸሎት ነው ብሎ መናገሩ ነው። «እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንጸልይ ይሰማናል» (1ዮሐ 5፥14-15)። ***ማናቸውንም ነገር*** የሚለው ቃል የፈለግነውን ሁሉ፤ የምናስበውን ሁሉ መጠየቅ እንደምንችል የሚያመለክት ሁሉን አቀፍ አገላለጽ ቢመስልም ቀጥሎ ያለው ቃል ግን ***በስሜ*** ይላልና በስሙ የሚለመን ***ማናቸውንም ነገር*** ማለት ነው።

በስሙ የሚለመነው ***ማናቸውንም ነገር*** ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያከብር፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ መሆን አስበት:: ስሙን ተጠቅሞ ስሙን የማያከብር እንደ ፈቃዱ ያልሆነ ***ማናቸውንም ነገር*** መጠየቅ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለው ጸሎት እንደሚሆንም ማጤን ይገባል:: ስለዚህ ***ማናቸውንም ነገር*** የሚለው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ባሕርይ የሆነ ጥያቄ ማለት ይሆናል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ከፈቃዱ ውጭ፣ ከባሕይው ተቃራኒ የሆኑ ጸሎቶችን ሰምቶ አይመልስም::

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ማለት ከኢየሱስ ጋር ተስማምቶ የጸሎት ጥያቄ ማቅረብ ማለት ነው:: ስሙ እርሱነቱን፣ በሕርዩን ይገልጣል:: ከክርስቶስ ጋር በመስማማት እንደ ፈቃዱ የሆነ ጸሎት በማድረግ መጸለይ ማለት ነው:: እንደ ፈቃዱ ወይም እንደ ቃሉ የሆነ ጸሎት ደግሞ፣ እግዚአብሔር አብ የሚሰማው ጸሎት ነው:: በሌላም ቦታ ጌታ ሲናገር ጸሎትን የሚሰማው ለእርሱ ክብርን የሚያመጣ ሲሆን እንደሆነ በ4÷41፤ 7÷18፤ 8÷50፤54፤ 15÷7-8፣16፤ 16÷23-24 ባለው እንመለከታለን::

በኢየሱስ ስም መጸለይ ጸሎትን የመቋጫ ሐረግ ወይም የመዝጊያ ቃል አድርጎ በልማዳዊ ሁኔታ መጠቀም ማለት አይደለም:: ይህ ፈጽሞ አይደለም:: እንዲህ ዓይነቱ የጸሎት ሁኔታ «የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል» (2ጢሞ 3:5) እንደተባለው ይሆናል:: የጸሎት መልክ ያለው ልማዳዊ ንግግር፤ የጸሎትን ምንነት እና የስሙን አጠቃቀም ያልተገነዘበ ጸሎት ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስን ስም መጠቀም መቻል ታላቅ ክብር ነው:: ኢየሱስንም አውቀዋለሁ፣ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ ብሎ ክፉው መንፈስ በአስቄዋ ልጆች ላይ የተነሣባቸው (ሐዋ 19:15) የኢየሱስ ስም ታላቅነት በአጋንንት ዓለምም የታወቀ ስለሆነ ነው::

***14÷15-16 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ::*** ቀደም ሲል ደቀ መዛሙርቱ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ ነግሯቸው ነበረ:: አሁን ደግሞ እርሱን እንዲወዱት ይነግራቸዋል:: ኢየሱስን መውደድ ማለት እርሱን መታዘዝ ማለት ነው:: የዘላለም ሕይወት ከእግዚአብሔር ዘንድ በጸጋ (ማለትም እንዲሁ በነጻ) የሚሰጥ ነው:: የዘላለምን ሕይወት ያገኘ ሰው ይህን ሕይወት ለሰጠው ለኢየሱስ ክርስቶስ ይታዘዛል፤ የእርሱን ፈቃድ ያደርጋል:: ክርስትና የፍቅር ሕይወት፤ የፍቅር ጉዞ ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስን መውደድ የሚገለጸው እርሱን በመታዘዝ ነው::

***14÷15-16 እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል::*** ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብሮ በነበረበት



ጊዜ ሁሉ እርሱ አጽናኛቸው ነበር:: አሁን የእርሱ መሄጃው ደረሰ:: እርሱ በሚሄድበት ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ የሚያጽናናቸው፤ የሚያስተምራቸው፤ ያስፈልጋቸዋል:: ስለዚህ አብ ***ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል*** አላቸው:: እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን አጽናኝ ብቻ አላለም፤ ያለው ***ሌላ አጽናኝ*** ነው:: አጽናኝ ማለት በግሪክ ቋንቋ ጰራቅሊጦስ[61] ሲሆን ይህም ረዳት፤ ደጋፊ ወይም የሚያጽናና የሚል ትርጉም አለው:: ኢየሱስ ክርስቶስ አጽናኝ ነው (1ዮሐ 2÷1)፣ መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሆነ ***ሌላ አጽናኝ***[62] ነው:: ማጽናናቱ፣ መምራቱ፣ መምከሩ ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱ ግን ሌላ እኔነት ወይም አካል ያለው የሥላሴ ሦስተኛ አካል ነው::

ይህ አጽናኝ በደቀ መዛሙርቱ ውስጥ ሁልጊዜ የሚኖር (14÷16)፣ የሚመራቸው፣ የሚደግፋቸው፣ የሚያጽናናቸው ነው:: ይህ አጽናኝ ***የእውነት መንፈስ*** ይባላል ***14÷17***: ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔር እውነት የሆነውን ሁሉ የሚገልጽ ነው::

***14÷17 እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው::*** ዓለም ይህን መንፈስ ቅዱስን ልትቀበለው የማትችለው፣ ስለማታየውና ስለማታውቀው ነው:: የሚታየውንም ኢየሱስን ዓለም አልተቀበለችውም (1÷11-12):: ***ከእናንተ ዘንድ ስለሚሆን፣ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ 14÷17*** እንዳለ ደቀ መዛሙርትና ሌሎች አማኞች መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉታል:: የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከዓለም የወጡ ናቸው:: የክርስቶስ የሆኑ ስለሆኑ የመንፈስ ቅዱስን ማንነት ያውቃሉ ስለዚህ እርሱን ይቀበሉታል:: መንፈስ ቅዱስም በውስጣቸው ይኖራል:: መንፈስ ቅዱስ:-

- ከእኛ ጋር ይኖራል፣ በእኛም ውስጥ ይኖራል 14÷17::
- ያስተምረናል፣ 14÷26፤
- የኢየሱስን ቃል ያሳስበናል፣ 14÷26፤ 15÷26
- ስለ ኃጢአት ይወቅሰናል፣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ይገልጻል፣ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያውጃል፣ 16÷8::

[61] *Parakletos*

[62] The expression *another Counselor (allon parakletos)* means <another counselor of the same kind as the first>. This implies Jesus was the first Counselor. Ibid. p.295.

- ወደ እውነት ይመራናል፣ የወደፊቱንም ይገልጣል፣ ያስረዳል፣ 16፥13::
- ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርን ያመጣል፣ 16፥14፤

መንፈስ ቅዱስ የዘላለም አምላክ ነው፣ የሥላሴ ሦስተኛ አካል ነው:: እርሱ እግዚአብሔር ነው:: በምድር ላይ በብሉይ ኪዳን በሰዎች ላይ በመውረድ ኃይልን በመስጠት ሠርቷል:: በአዲስ ኪዳን በሰዎች (በአማኞች) ውስጥ ለመኖር ይመጣል:: ይህ ከበዓለ ሃምሳ ቀን ጀምሮ ሆኗል::

***14፥18 ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም:-*** ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ መጨረሻ ለወደዳቸው ደቀ መዛሙርቱ ያለውን ፍቅር፤ ጥበቃና ጥንቃቄ ያሳያል:: ጌታ የሚሄድ ቢሆንም፣ ደቀ መዛሙርቱን በትኗቸው አይሄድም::

- በአንድ በኩል በውስጣቸው እንዲኖር መንፈስ ቅዱስን ከአብ ሰምኖ ይልክላቸዋል:: ስለዚህ ሌላው አጽናኝ በውስጣቸው ኖሮ ያጽናናቸዋል:: ደቀ መዛሙርቱ ተስፋ ቢሶች አይሆኑም::

- ሁለተኛው ደግሞ:- ***ወደ እናንተ እመጣለሁ! 14፥18*** በማለት የመመለሱን ተስፋ ይሰጣቸዋል:: ይህም እንዳልተረሱ ያመለክታል::

ይህ ***ወደ እናንተ እመጣለሁ*** የሚላቸው ጌታ በቅርቡ ጊዜ ከሞቱ በኋላ ተነሥቶ ወደ እነርሱ እንደሚመጣና እንደሚያዩት ሊያመለክት ይችላል (20፡19-21-25):: እንዲሁም ወደ አብ ከሄደም በኋላ ሁለተኛ ሊወስዳቸው ስለ መምጣቱ ያሳያል (14፡3)::

***14:19 ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ::*** ይህ ***ገና ጥቂት ዘመን*** የሚለው በፊቱ ያለውን መከራ የመቀበል፣ የመስቀል፤ የመቀበርና የትንሣኤውን ጊዜ የሚያመለክት ነው (16፡16-23):: ከዚያ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ያዩታል:: ከሞት ከተነሣ በኋላ አይተውታል (20፡20፣26፤ 21፡1፣14)::

***14፥19 እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ::*** የደቀ መዛሙርቱና በአጠቃላይ የአማኞች ሕያው መሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሕያውነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ትንሣኤው ይህንን አረጋገጠ:: ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣ ሕያው ስለሆነ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ***ሕያዋን*** ናቸው:: ስለዚህ ትንሣኤ:- አማኞች የዘላለም



ሕይወት እንደሚያገኙ፣ ሕያዋን ሆነው እንደሚኖሩ ማረጋገጫ ማኅተም ነው::

***14፥20 እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ:: ያ ቀን*** የትንሣኤ ቀን ነው:: ከትንሣኤ በኋላ ደቀ መዛሙርት የሚያስተውሉት ትልቅ ነገር አለ:: ይኸውም ኢየሱስ በአብ እንዳለ (እንደሚኖር) ያስተውላሉ፣ እንዲሁም እነርሱ በኢየሱስ እንደሚኖሩ ያስተውላሉ:: ኢየሱስም በእነርሱ እንደሚኖር ይህን ማስተዋል ይጀምራሉ::

***14፥21 ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው! የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ፡*** እዚህ ላይ ትእዛዝን መጠበቅ፤ መውደድ፤ መወደድና መግለጥ በቅደም ተከተል የተገናኙ እንደሆነ እናያለን:: ትእዛዙን ***የሚጠብቃት*** እርሱን የሚወድ ሰው ነው:: ኢየሱስን የሚወደውን ሰው አብ ***ይወደዋል::*** ለተወደደ ሰው ደግሞ ኢየሱስ ራሱን ይገልጥለታል::

ኢየሱስን እወዳለሁ የሚል ሰው መውደዱን የሚገልጠው ትእዛዙን በመጠበቅ ነው:: ይህንን ስናደርግ ኢየሱስና አብ ይወዱናል:: ከዚህ ክፍል እንደምናስተውለው መገለጥ ያለው ከመታዘዝ በኋላ ነው:: መታዘዝ ወደ መገለጥ ይወስዳል፤ በሌላ አነጋገር ሰው የሚያውቀውን የእግዚአብሔርን ቃል እጠየበቀ ሲኖር የበለጠ እያወቀ ይሄዳል:: የሚያውቀውን እየታዘዘ ሲሄድ የበለጠ እየተገለጠለት ይኖራል ማለት ነው::

እዚህ ቁጥር ላይ እያለን አንድ ነገር እናንሳ:: አንዳንድ የሥላሴን ትምህርት ለመካድ የሚፈልጉ ክፍሎች:-

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አብ የተባለው በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ነው በሚል የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በመቃወም ያስተምራሉ:: በዚህ ቁጥር ላይ ብቻ እንኳ ይህ አባባላቸው ስህተት እንደሆነ ማስተዋል እንችላለን:: ጌታ ***የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ*** ባለው ***አባቴ ይወደዋል*** ሲል፤ እግዚአብሔር አብ እኔን (ማለት ኢየሱስን) የሚወደኝን ሰው ይወደዋል ማለት ሲሆን፤ ***እኔም እወደዋለሁ*** ሲል ደግሞ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን ሰው (ማለት የሚወደኝን ሰው) እኔም እወደዋለሁ ማለት ነው:: ስለዚህ የሚወደኝን ***አባቴ ይወደዋል***፤ እንዲሁም ***እኔም እወደዋለሁ*** ሲል ነው:: ስለዚህ አብና ወልድ ሁለት እኔነት ያላቸው የመለኮት አካላት እንደሆኑ ግልጽ ነው::

***14፥22 የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ፦ ጌታ ሆይ፥ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው? አለው***:: ይህኛው ይሁዳ የያዕቆብ ልጅ ነው (ሉቃ 6፥16):: ወደ ዓለም የመጣውን ብርሃን ተገልጦ መጣ ዓለም አልተቀበለውም፣ ከዚህ በኋላ ግን ራሱን በጠለቀ ሁኔታ የሚገልጠው በእርሱ ለሚያምኑት እንደሆነ ያሳያል:: ኢየሱስን ልትቀበለው ያልወደደች ዓለም ከሙታን ተነስቶ ቢመጣም እንኳ አትቀበለውም (ሉቃ 16፥31):: ስለዚህ ኢየሱስ እርሱን ለሚወዱትና ለሚታዘዙት ራሱን በጥልቅ ሁኔታ ይገልጽላቸዋል:: ሌላው ራሱን ለሚወዱት የሚገልጥበት መንገድ በሚቀጥለው ቁጥር እንደተገለጸው በሚወዱት ውስጥ በመኖር ነው::

***14፥23 የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን***: መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ በአማኞች ውስጥ ይኖራል (14፥17):: እንዲሁም በሚወዱት ውስጥ ኢየሱስ ይኖራል፤ አብም ይኖራል:: ስለዚህ አማኞች የሥላሴ መኖሪያ ናቸው ማለት ነው:: ይህ ለደቀ መዛሙርት ትልቅ ማጽናኛ ነው:: ***ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም 14፡18*** ብሏልና ወደ አብ ቢሄድም ኢየሱስ ክርስቶስ በሚታዘዙት ውስጥ እንደሚኖር ይህን ያስረግጥላቸዋል::

***14፥24 የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፦*** መታዘዝ ከፍቅር እንደሚመነጭ ያስገነዝባል:: ስለዚህ የመውደድ መጠናችን የሚገለጠው በመታዘዝ ሲሆን የምንታዘዘውም ኢየሱስን በወደድነው መጠን ነው ማለት ነው::

***14፥26 አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል::*** መንፈስ ቅዱስ የሚላከው በአብና በወልድ ነው (15፥26):: እንዲመጣ አብን የሚጠይቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (14፥15):: ይህ አጽናኝ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ የጀመረውን የማስተማር ሥራ ይቀጥላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸውንም ሁሉ ያሳስባቸዋል:: ጌታ ከተነሣ በኋላና መንፈስ ቅዱስም ከወረደ በኋላ ጌታ የተናገራቸው እየበራላቸው ግልጥ እየሆነላቸው ሄዷል:: መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ጌታ ያላቸውንና ያስተማራቸውን ስላሳሰባቸው አዲስ ኪዳንን ጽፈዋል:: ለምሳሌ ዮሐንስ ይህን ወንጌል የጻፈው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አብ ከሄደ ከረጅም ዓመታት በኋላ እንደሆነ ስለሚታወቅ ጌታ የተናገረውን ሁሉ አስቦ ለመጻፍ የቻለው መንፈስ ቅዱስ ስላሳሰበው፤ ስላስታወሰው ነው::



***14፥27 ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም:: ልባችሁ አይታወክ አይፍራም::*** ኢየሱስ ወደ አብ መሄጃው ሰዓት ቀርቧል:: ነገ የሚያመጣውን አለማወቅ ወደ መታወክ ይወስዳል:: ጌታ ግን ደቀ መዛሙርትን ***ልባችሁ አይታወክ፣ አይፍራ*** አላቸው:: ነገ የሚሆነውን የማያውቅና እርግጠኛ ያልሆነ ሰው ስለ ነገ ይጨነቃል፣ ይታወካል፣ ይፈራል:: ነገን የሚያውቅ ጌታ ሁሉን የሚችል እርሱ ኢየሱስ ሰላምን ሲሰጥና አትታወኩ ሲል ግን በእርግጥ ሰላም ይሆናል::

ደቀ መዛሙርቱ በራሳቸው ሰላም የላቸውም:: የነበሩበት ታንኳ እንኳ በማዕበል በተቸገረ ጊዜ ምን ያህል እንደፈሩ በሉቃ 8፥22-25 እናያለን:: ኢየሱስ ግን ማዕበሉን ጸጥ አሰኝቶ ለደቀ መዛሙርትም ሰላምን ሰጠ:: አሁን ደግሞ እርሱ በመሄዱ ምክንያት እንዳያዝኑና ልባቸውም እንዳይታወክ ልባቸውን የሚጠብቅ ***ሰላምን*** ለደቀ መዛሙርቱ ሰጥቷቸው ሄዷል:: ይህ ሰላም ዓለም ከሚሰጠው ሰላም የተለየ የክርስቶስ ሰላም ነው:: የክርስቶስ ሰላም እረፍትን፣ ጽናትን ይሰጣል:: ጌታ ከተነሣም በኋላ ደቀ መዛሙርትን ሲያገኛቸው «ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው» (20፥19)::

በዚህ ዓለም ላይ ችግር አለ:: ችግርን ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ለፊት ተጋፍጦ አሸንፎታል:: ከዚህም የተነሣ ሰላምን ለደቀ መዛሙርቱ ለመስጠት ይችላል (16፥33):: ስለዚህ ክርስቶስ የሚሰጠው ሰላም በእርሱ ሁሉን ቻይነት ላይ የተመሠረተ ነው::

በዓለም ያለው ሰላም እውነተኛ ሰላም ሳይኖር ሰላም፣ ሰላም የሚያሰኝ ነው (ኤር 6፥14):: እውነተኛ ሰላም እውነትን በማወቅ ይገኛል:: ከእውነት አያሸሽም:: እውነትን ማወቅ ማለት በኃጢአት ላይ ንስሐ ገብቶ በክርስቶስ ማመን ነው:: ክርስቶስ የሚሰጠው ሰላም ከክርስቶስ ጋር በሚኖር የተጣበቀ ግንኙነት የሚገኝ ነው::

***14፥28 እኔ እሄዳለሁ ወደ እናንተም እመጣለሁ እንዳልኋችሁ ሰማችሁ::*** ጌታ ኢየሱስ ይህን ***ወደ እናንተም እመጣለሁ*** የሚለው ቃል በ14፥3 እንደዚሁም በ14:18 ላይ ተናግሮታል:: በዚህ ምዕራፍ ብቻ ሦስት ጊዜ መናገሩ ነው:: መደጋገሙ የፍርሃትና የመታወካቸውን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን በተደጋጋሚ መናገሩ በአጽንዖት እንዲያስተውሉት ይሆናል::

በዚህ የጌታ ኢየሱስን ታላቅ የመሪነት ባሕርይ እናያለን::

ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ የሚሄድበት ጊዜ ሲደርስ የሚመራቸውን ደቀ መዛሙርት ሊመጣ ያለውን ነገሮ፣ አስረድቶ፣ አጽናንቶ አያዘጋጃቸው ነው፡፡ ሁኔታውን እንዳመጣጡ ተቀበሉት ብሎ በትኗቸው አይሄድም፡፡ ሊመጣ ያለውን ይነግራቸዋል፡፡ በዚያም ውስጥ እንዴት መሆን እንዳለባቸው ይመክራቸዋል፡፡

***14፥28 የምትወዱኝስ ብትሆኑ፣ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር፡፡*** ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ትቶ ወደ አብ መሄጃው ጊዜ ደርሶአል፡፡ ይህ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱን ፍርሃት ላይ ጥሏቸዋል፡፡ ወደ እብ መመለሱ ለደቀ መዛሙርቱ የደስታ ምክንያት ሊሆን ይገባ ነበር ማለት ነው፡፡ ***የምትወዱኝስ ብትሆኑ*** ብሎ እንደሚናገር በእርግጥም ወደ እብ መሄዱ ከሃዘን ይልቅ ደስ ሊያሰኛ ቸው ይገባ ነበር ማለት ነው፡፡

***አብ ከእኔ ይበልጣልና*** የሚለውን አንዳንዶች በአብና በወልድ መካከል እኩልነት እንደ ሌለ እድርገው ይመለከቱታል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም መለኮት መሆኑን ቀደም ሲል በብዙ ቦታዎች ተመልክተናል፡፡ በእግዚአብሔር እብና በወልድ መሀከል ፍጹም የሆነ የመለኮት እኩልነት አለ (ስምላሌ 10፥30ን ይመልከቱ)፡፡ እዚህ ላይ ጌታ ***አብ ከእኔ ይበልጣል***ና ሲል እርሱ የባሪያን መልክ ወስዶ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም የመጣ፤ በአብ የተላከ መሆኑን ሲያሳይ ነው፡፡ ስለ ተላከና የአባቱንም ፈቃድ ለማድረግ ስለመጣ በዚህ አንሶ እንደሚታይ ይመስላል፡፡ ይህ ግን የሚያሳየው የትሕትናውን መጠን ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የመለኮት ሙላት አለው፤ ከአብ ጋር እኩል ነው፡፡

***14፥30 ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና፡፡*** ጌታም ከምዕራፍ እሥራ ሁለት ጀምሮ እየነገራቸው ያለው ሰዓቱ እንደቀረበ ነው፡፡ በምዕራፍ አሥራ ሦስትም እራት ከበሉ በኋላ አሳልፎ የሚሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ተለይቷቸው ሄዷል፡፡

አሁን አስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ የሚሰጥበት ጊዜ ቀርቧል፡፡ ***የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና*** ሲል በ12፥31 ላይ እንደተናገረው ይህ ዲያብሎስ ነው፡፡ ዲያብሎስ በይሁዳ ውስጥ ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲሰቀል ለማድረግ ጊዜው ደርሷል፡፡ ***የዚህ ዓለም ገዥ ሥ***ልጣኑ ደግሞ በሞት ላይ ነው (ዕብ 2፥14)፡፡ ሰይጣን ቀደም ሲል ኢየሱስ ክርስቶስን ለማሸነፍ ፈትኖት ነበር (ማቴ 4)፡፡ እንዳላሸነፈው ሲያይ ለጥቂት ጊዜ ተለየው (ሉቃ 4:13)፡፡ አሁን ደግሞ እንደገና ይመጣል፡፡ የዚህ ዓለም ገዥ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ምንም ሥልጣን የለውም፤ ሊያሸንፈውም አይችልም፡፡ ምክንያቱም፦



***14፥30 በእኔ ላይም አንዳች የለውም፦*** ብሎ ጌታ ይናገራል፡፡ ሰይጣን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የገዥነቱን ሥልጣን ሊጭን ወይም ሊያስፋፋ ያልቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሕ.ፍች ኃጢአት ወይም በደል ስላላገኘበት ነው፡፡ ኃጢአት የሰይጣን የማሸነፊያ መሣሪያ ነው፡፡ በሰው ሕይወት ውስጥ ንስሐ ያልተገባበት ኃጢአት ካለ ሰይጣን በዚያ ሰው ሕይወት ለመጠቀም እግሩን የሚያሳርፍበት ቦታ ነው፡፡ ለመውረስ፣ ለማሸነፍ በዘያ በሉል ቀዳዳ እገኘ ማለት ነው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ግን ምንም ሊያገኝበት አልቻለም፤ እርሱ ፍጹም ነውና፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሞተው የአብን ፈቃድ ለመፈጸም ነው፡፡

***14፥31 ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ፥ አብም እንዳዘዘኝ፥ እንዲሁ አደርጋለሁ፡፡*** ለሞት ራሱን አሳልፎ የሰጠው በሰይጣን ሥልጣን ወይም መሣሪያ በሆነው ሞት በመሸነፉ ሳይሆን፤ በሞት በኩል ዓለምን እንዲያድን እግዚአብሔር ስለላከው ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጽ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ፡፡ ስለዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር የዘላለም ዕቅድ ክፍል ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት ሰይጣን በሞት ላይ የነበረውን ሥልጣኑን ሽሯል፡፡ እርሱ ሞትን አሸንፎ ተነስቷልና፤ ሞት ሊይዘው አልቻለም (16፥11፤ ቆላ 2፥15)፡፡

***14፥31 ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ፡፡*** ጌታ የመሞቻው ሰዓት እየቀረበ ነው፤ የአስቆሮቱ ይሁዳም አሳልፎ ሊሰጠው ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱን ፈቃድ ያደርግ ዘንድ ወደዚያ ወደ ዝግጅቱ ለመሄድ ***ከዚህ እንሂድ*** ይላል፡፡ ወደዚያው የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደሆነው ለመግባት ***እንሂድ፡፡***

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

በምዕራፍ አሥራ አምስት ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር ሲኖራቸው ስለሚገባው ኅብረትና የመቀራረብ መጠን በምሳሌ ያስተምራቸዋል። ምሳሌው የወይን ዛፍ ነው። ጌታ የሚያስተምርበት አንዱ መንገድ ቀን ተቀን የሚገኝ ምሳሌ ወስዶ ሰው በቀላሉ ሊያየውና ሊያገናዝበው በሚችለው ሁኔታ ታላቅ መንፈሳዊ እውነትን መግለጥ ነው። በዚህም ምዕራፍ የምናየው ይኸው ነው።

***15፥1 እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ።*** በብሉይ ኪዳን በመዝ 80፥8-17 ላይ የምናየው የወይን ምሳሌ በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተፈጸመ እናስተውላለን። ኢየሱስ ***እውነተኛው የወይን ግንድ*** ፍጻሜ ነው። አማኞች ሁሉ በእርሱ ላይ ሲኖሩ የእግዚአብሔር ሀሳብ መሙላት ተፈጸመ ማለት ነው። በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ ከግንዱ የሚወጡ ወይም የተጣበቁ ቅርንጫፎች ናቸው።

በብሉይ ኪዳን የወይን ተክል ፍሬያማነት እስራኤል የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራት በምድር ላይ ልታሳየው ስለሚጠበቅባት ፍሬ ምሳሌ ሆኖ ተመልክቷል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር መልካም ወይን ተከለ፣ ተጠነቀቀለትም፤ ወይኑ ግን አላፈራም። ይህም እስራኤል እግዚአብሔርን እንደሚገባ አለመውደዷን ይልቁንም በእርሱ ላይ እንደ አመፀችና እንደ ረሳችው ይገልጻል። (ኢሳ 5፥1-7፤ ኤር 2፥2፣21፤ 6፥9፤ ሕዝ 15፤ 17:5-10፤ 19፥10-14፤ ሆሴ 10፥1፤ 14:7 ይመልከቱ)።

***15፥1 ገበሬው አባቴ ነው።*** የወይን ግንድ ቅርንጫፎች እንዲያፈሩ ትጉህ ገበሬ ያስፈልገዋል። በዚህ ምሳሌ መሠረት ተንከባካቢው ማለትም ***ገበሬው*** እግዚአብሔር አብ ነው። በሌላም ቦታ እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር እንደሚል (1ቆሮ 3፥6፤ ቆላ 2፥19)።

***15፥2 ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል።*** ኢየሱስ የወይን ግንድ ነው፤ እግዚአብሔር አብ ደግሞ ቅርንጫፎቹ እንዲያፈሩ የሚጠነቀቅ ገበሬ ነው። ቅርንጫፎች በኢየሱስ አምነናል የሚሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ናቸው። በዚህ ምሳሌ ቅርንጫፎች ግን በሁለት ተከፍለው እናያቸዋለን።



- ፍሬ የሚያፈሩ፡- በእርግጥ በኢየሱስ የሚያምኑና እምነታቸውን በእርሱ ላይ በሙሉነት ያሳረፉ
- ፍሬ የማያፈሩ፡- ከእርሱ ጋር የተገናኙ ግን ፍሬ የማያፈሩ

ሁለቱም ከእርሱ ጋር የተገናኙ የግንዱ ቅርንጫፎች ሆነው ቀርበዋል። ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚገልጠው *በእኔ ያለውን* የሚለው የኅብረትን መጠን የሚያመለክተው ቃል ነው። የቅርንጫፎቹ ማንነት በማፍራታቸው ይታወቃል። ፍሬ የማያፈሩት በውጪያዊ ሁኔታ ያመኑ የሚመስሉ፣ ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ወይም ኅብረት የሌላቸው ናቸው። እነዚህን እግዚአብሔር ከግንዱ ያስወግዳቸዋል፤ ማለትም ይቆርጣቸዋል። ስለሆነም ከወይን ግንዱ ይለያያሉ ማለት ነው።

ለሰዎች ስለ ክርስቶስ አዳኝነት በመመስከር ወደ እግዚአብሔር ማምጣት ፍሬ የማፍራት አንዱ መንገድ ነው። ከዚህ ሌላ በአጠቃላይ ፍሬ ማፍራት የመንፈስ ፍሬን ማፍራት ወይም የክርስቶስን መልክ መያዝ ነው (15፥7፤ 11-12፤ ገላ 5፥22-24፤ 2ጴጥ 1፥5-8)።

***15፥2 ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል።*** ፍሬ የሚያፈራው ቅርንጫፍ ከወይን ግንዱ ጋር የተጣበቀና ፍሬ ማፍራት የጀመረ ነው። ይህም ዳግመኛ የተወለደና የክርስቶስን ባሕርይ እየያዘ በማደግ ላይ ያለ ክርስቲያን ምሳሌ ነው። ገበሬው እንዲህ ዓይነቱን ***አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል።*** ይኸኛው ማጥራት በቅርንጫፉ ላይ ያሉ አንዳንድ የቅርንጫፉን ክፍሎች መቁረጥ ነው። ይህ ማጥራት[63] ከማስወገድ[64] (ወይም መቁረጥ) ይለያል። ማጥራት - ቅርንጫፉ የበለጠ እንዲያፈራ የማያስፈልገውን ከቅርንጫፉ ላይ መጥረግ (መቀነስ) ነው። ማስወገድ ግን ራሱን ያን ቅርንጫፍ ቆርጦ ከግንዱ መለየት ነው።

ፍሬ የማያፈራው ከግንዱ ተቆርጦ ይጣላል። ከእርሻ ሙያ እንኳ ስመረዳት እንደሚቻለው ፍሬ የማያፈሩ ቅርንጫፎች በግንዱ ላይ መቆየታቸው ፍሬ የሚይዙትን ሌሎች ቅርንጫፎች የሚያዳክሙና የሚያበላሹ ይሆናሉ። በግንዱ ላይ መኖራቸው ይጐዳል እንጂ አይጠቅምም።

---

[63] Pruning – removing what does not bear fruit, and cultivating what does to increase fruit bearing. የወይን ተክል የሚያለሙ ገበሬዎች ይህን ያውቃሉ። ቅርንጫፎችን ማጥራት ማለትም በላያቸው ላይ ያሉ የማያስፈልጉ ክፍሎችን መቆራረጥ፤ ያ ቅርንጫፍ የበለጠ እንዲያፈራ ጥሩ መንገድ እንደሆነ ያውቃሉ።
[64] Cut off and tossed aside, separated, removed

ገበሬው እግዚአብሔር በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እንዲህ ዓይነት የማጥራትን ሥራ ይሠራል። ማጥራት (ሥርዓቱን እንዲያውቅ ማድረግ)[65] ሊሆን ይችላል። በባሕርዩ እግዚአብሔርን በመምሰል እንዲያድግ የሚረዳ ስለሆነ ፍሬ ማፍራት የጀመረው የበለጠ ያፈራል። ቅርንጫፍን ማጥራት ለጊዜው ለቅርንጫፉ ደስ የሚያሰኝ ነገር አይሆንም። ለማጥራት ተቆርጦ የሚወገድ የቅርንጫፍ ክፍል ስለሚኖር ለጊዜውም ቢሆን ቅርንጫፉ ጉዳት ይደርስበታል። ገበሬው ይህን ሲያደርግ ግን ከዓላማው አንጻር ነው። ብዙ ፍሬ እንዲይዝ ለማድረግ፣ መንገዱ «መግረዝ» ወይም ማጥራት ነው።

ይህ በክርስቲያናዊ ሕይወት የተለያየ መልክ ሊኖረው ይችላል። አንደኛው በእግዚአብሔር ዲሲፕሊን መደረግ ማለት ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ያለ እርሱ ምንም ማድረግ እንደማንችል እናስተውል ዘንድ፣ ይህ አለን፣ እንችላለን፤ የምንለውን ሁሉ ከእኛ በማስወገድ እግዚአብሔር ሊያጠራን ይችላል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን የበለጠ ፍሬያማ እንዳንሆን የሚጐትተንን ወይም የሚከለክለንን ነገር ሁሉ ከእኛ እያስወገደ የበለጠ በእርሱ ላይ እንድንታመንና ብዙ እንድናፈራ የማድረጊያው መንገድ ማጥራት ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ማጥራት በሕይወታችን ልንመረረው አይገባም። እንዲያውም ለጊዜው የሚያሳዝን ቢሆንም በብዙ እንድናፈራና ደስታን የሚያመጣ ስለሆነ በትዕግሥትና በምስጋና ልንቀበለው ይገባናል (ዕብ 12:11)።

***15፥3 እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ።*** ደቀ መዛሙርቱ ንጹሕ የሆኑት ከሰሙት የጌታ ቃል የተነሣ ነው። የወይን ዛፍ ንጹሕ እንዲሆን ማለትም ብዙ ፍሬን እንዲያፈራ እንደሚጠራ ወይም እንደሚገረዝ ሁሉ ደቀ መዛሙርትም ፍሬ ለማፍራት የደረሱ የተዘጋጁ ናቸው። ሁሉም ደቀ መዛሙርት ግን ንጹሕ አልነበሩም። የአስቆሮቱ ይሁዳ ከወይን ግንዱ የተቆረጠ፣ የተወገደ ቅርንጫፍ ነው።

***15፥4 በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ።*** በዚህ ምዕራፍ ውስጥ መኖር የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ተገልጿል። አማኞች <u>በኢየሱስ ክርስቶስ መኖር ወይም ተጣብቆ መገኘት</u> አለባቸው። መኖር የሁልጊዜ ተግባር ነው። መጀመር ብቻ ሳይሆን በቀጣይነት በዚያው ተጣብቆ መቀጠልን ያመለክታል። ይህ ከሁሉም አማኞች የሚጠበቅ ተግባራዊ እርምጃ ነው። ቀን ተቀን በሁሉም ሰዓት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ታምኖ ከእርሱም ጋር ተጣብቆ መኖር ነው። በክርስቶስ መኖር ማለት፦

[65] Discipline



- እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ማመን (1ዮሐ 4፥15)፣
- እርሱን የግል አዳኝና ጌታ አድርጎ መቀበል (1ዮሐ 1፥12)፤
- የእርሱን ትእዛዝ መፈጸም (1ዮሐ 3፥24)፤
- ሁልጊዜ በቀጣይነት በእርሱ በማመን መጓዝ (1ዮሐ 2፥24)፤
- የክርስቶስ ከሆኑት ጋር ኅብረት ማድረግ (ዮሐ 15:12) ነው።

***15፥4 ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባይትኖሩ አትችሉም።*** የወይን ቅርንጫፍ ፍሬ የሚያፈራው ከወይኑ ግንድ ጋር ተጣብቆ እስከኖረ ጊዜ ድረስ ነው። ይህ ባይሆን ግን ፍሬ አይኖረውም፣ ፍሬ አይሰጥም። እንዲሁ ክርስቲያን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሕያው የሆነ ግንኙነት ወይም መጣበቅ በየቀኑ ካላደረገ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ምንም ፍሬ ሊያፈራ አይችልም። በመሠረቱ ክርስቲያን ከራሱ የሆነ የሚያፈራው ፍሬ እንደሌለውም ያሳያል። ፍሬ ሊያፈራ የሚችለው ከክርስቶስ ከሚያገኘው ሕይወት፤ ምግብና ጉልበት ስለሆነ ከእርሱ ጋር ተጣብቆ ሲኖር ብቻ ፍሬን ያፈራል።

***15፥5 ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።*** በክርስትና እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገው ነገር ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግን ሲሆን ያ ሰው ፍሬን እንዲያፈራ ማድረግ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፣ ፍሬንም የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። ለምሳሌ የመንፈስ ፍሬ (ገላ 5፥22) በአማኝ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያፈራው ፍሬ ነው። ሰላም፤ ደስታ፤ ፍቅርና ሌሎችንም ፍሬዎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ የሚያፈራቸው ፍሬዎች ናቸው። የአማኙ ድርሻ መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ ይሠራ ዘንድ ከባሕርዩ ጋር ተስማምቶ ምቹ ሆኖ መገኘት ነው።

እንዲሁም ፍሬ ለማፍራት ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ብዙ «የነፍሳት ነዶ» ለመሰብሰብ ወይንም በተለወጠ ሕይወት የዓለም ብርሃን ለመሆንና እግዚአብሔርን ለማስከበር የሚቻለው ከእርሱ ጋር የቀረበ ኅብረት ሲኖር ነው። ይህ በእርሱ መኖር ነው። መኖር የማያቋርጥ የሁልጊዜ ተግባር ነው። ስለሆነም ***ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና*** የሚለው በእርግጥም ማንም ሰው በምድር ላይ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ከሰጠው እድሜ፣ እስትንፋስ፣ እውቀት፣ ጉልበት የተነሣ ስለሆነ ነው። በተለይ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያከብር ሥራ ለመሥራት ያለ እርሱ አይቻልም። ብዙ ሰዎች በክርስቶስ ሳይኖሩ መልካም ነገሮችን ለማድረግ ይጥራሉ። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት

ያለው ፍሬ ማፍራት የሚቻለው ከክርስቶስ ጋር በመጣበቅ ከሆነ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ጥረቶች ሁሉ በእግዚአብሔር መለኪያ ፍሬ ቢስ ይሆናሉ። ይህ እንግዲህ በክርስትና ሕይወት ልናስተውለው የሚገባ ቁልፍ ትምህርት ነው።

***15፥6 በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፥ ያቃጥሉአቸውማል።*** በእርሱ የማይኖር ቅርንጫፍ ሲታይ የተጣበቀ ይመስላል። ነገር ግን የወይን ግንዱ ከሚሰጠው ሕይወት ጋር በመያያዝ ሕይወትን እያገኘ አይደለም። ስለዚህ ይደርቃል።

ከወይን ግንዱ ተቆርጠው የሚጣሉ ቅርንጫፎች ምን ዓይነት ናቸው? ወይም እነማን ናቸው? በሚል ብዙ ውይይቶች ተደርገዋል። የተለያዩ ትርጉሞችም ተሰጥተዋል። እነዚህን በሚመለከት የሚቀርቡት ሦስት ትርጉሞች እንደሚከተለው ጠቅለል ተደርገው ቀርበዋል።

**አንደኛው፦ አማኞች የነበሩና ወደ ኋላ የተመለሱ ናቸው።** እነዚህ ቅርንጫፎች እውነተኛ አማኞች የነበሩና ደኅንነታቸውን የጣሉ ወይም ያጡ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ትርጉም ታሳቢ የሚያደርገው ቅርንጫፎቹ አስቀድመው ከክርስቶስ ጋር የተጣበቁ ስለነበሩ የሚጣበቁት ስላመኑ መሆን አለበት የሚል ነው። ይህ በሮሜ 11፥20-22 እና ዕብ 6፥8 ከተጠቀሰው ጋር ይስማማል። እንዲህ ከሆነ ይህ አተረጓጐም ከዮሐ 3፥16፤36፤ 5፥24፤ 10፥28-29፤ ሮሜ 8፥1 ካለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጋር የሚቃረን አይሆንም ወይ? የሚል ጥያቄ የሚያነሡ አሉ።

**ሁለተኛው፦ የሚያጡት ሽልማት ብቻ ነው።** የሚቆረጡትና የሚቃጠሉት ቅርንጫፎች ሽልማታቸውን የሚያጡ አማኞች ናቸው የሚል ነው። እነዚህ ቅርንጫፎች ደኅንነት አላቸው፤ ደኅንነታቸውን አያጡም፤ በፍርድ ቀን ግን ሽልማታቸው ያጣሉ (1ቆሮ 3፥15)። እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ደግሞ 1ቆሮ 3፥15 ሽልማትን ስለማጣት ቢናገርም በዮሐ 15 ያለው ሃሳብ ግን ተቆርጦ ስለመለየት በመሆኑ ሽልማት ብቻ ማጣት መቆረጥና መቃጠል ተደርጐ መተርጐም የለበትም የሚል ነው።

**ሦስተኛው፦ ቀድሞውንም ዳግመኛ አልተወለዱም ነበር።** እነዚህ የሚቃጠሉ ቅርንጫፎች አማኞች እንደ ሆኑ በአፋቸው ሲመሰክሩ የነበሩ ነገር ግን በእርግጠኝነት ዳግመኛ ያልተወለዱ ነበሩ የሚል ነው። ለዚህም የአስቆሮቱ ይሁዳ እንደ ምሳሌ ይወሰዳል። አስቆሮቱ ይሁዳ



ቅርንጫፍ «መስሎ» የኖረ ሰው ነገር ግን በእርግጥ በኢየሱስ ያላመነ ሰው ነበር- ስለዚህም ተቆረጠ የሚል ነው። የዚህኛው አተረጓጐም ትልቅ ችግር እስከ መጨረሻዋ እሳልፎ እስከሚሰጥባት ደቂቃ ድረስ የአስቆሮቱ ይሁዳ በኢየሱስ ያላመነ መሆኑን ማን ያውቅ ነበር? የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ? ነው። ዱሮውኑ በኢየሱስ ስላላመነ ነው? ወይስ እምነቱን ስለካደ? የሚል ጥያቄም ያስከትላል። ቀድሞውኑም በኢየሱስ ያላመነ ከሆነ ደግሞ ይህ በሰው ዘንድ ሊታወቅ የማይችል እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀው እውነት ይሆናል።

እንግዲህ እንዲህ ዓይነት አስተያየቶች ሲቀርቡ የቆዩ ቢሆንም ክርክሮቹ ብዙ አይጠቅሙንም። ከዚህ ለትምህርታችን የምናገኘው ቁልፍ ነገር አመለካከቶቹ ምንም ይሁኑ ምን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመጣበቅና በእርሱ በመኖር በየዕለቱ ከእርሱ የሚገኘውን ሕይወት ካላገኘን መቆረጣችን እውን መሆኑን ነው። የሚቆረጡት ዱሮውኑም አማኝ ያልነበሩ ናቸው የሚለው «እንጃ ይሆን ይሆናል» ግን ከሰው ይህን ማን ሊያውቅ ይችላል? ይህን በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ደረጃ የሚታወቅ ነገር አይደለም። ስለዚህ በሰው ደረጃ የተገለጠውን ማድረግ ይበጀናል። ይህም ማንም ከግንዱ ጋር ተጣብቄአለሁ የሚል ሕይወትን ከግንዱ እያገኘ ተጣብቆ ካልኖረ ይቆረጣል። ለእኛ የሚበጀን ከእርሱ ጋር ተጣብቆ አብሮ መኖር ነው።

***15፥7 በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።*** እዚህ ላይ ቃሎች[66] የሚለው በግሪኩ «ሬማታ» ነው። ይህ ጌታ ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት ወይም ትምህርቶች ሁሉ ማለት ነው። (በሌላ ቦታ ቃል[67] (1:1) የሚለው የግሪክ ትርጉም ሎጎስ ሲሆን የእግዚአብሔርን ልጅ ማንነት ይገልጻል)።

በወይን ግንዱ ተጣብቀው የሚኖሩ ቅርንጫፎች ቃሉ በውስጣቸው እንዲኖር ያደርጋሉ፤ ምክንያቱም ያነጻቸው ቃሉ ነውና (15፥3)። ጌታ ***ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ*** ሲል በክርስቶስ ቃል መኖር ማለት ቃሉን ማወቅንና መጠበቅ ማለት ነው። ስለዚህ በቃሉ መኖር ማለት ቃሉን ማወቅ + ቃሉን መታዘዝ ነው።

***15፥8 ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል።*** በዚህ ክፍል እንደምናየው እግዚአብሔርን መጠየቅ የተያያዘው ብዙ ፍሬ ከማፍራት ጋር ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ

[66] (words) *Rhemata*
[67] *Logos*

መጠየቅና ፍሬ ማፍራት በ14፥13-14 ባለውም ተገልጿል፡፡ በእርሱ ስንኖር ሀሳባችንና ፍላጐታችን ሁሉ ከእርሱ ቃል ጋር ይስማማል፡፡ ስለዚህ እንደ ፈቃዱ እንጸልያለን፣ በስሙም እንጸልያለን፡፡

አንድ ሰው በክርስቶስ ሲኖር እንዲሁም የክርስቶስ ቃሎች በእርሱ ሲኖሩ ያ ሰው የሚጸልየው በእግዚአብሔር ዘንድ ይሰማለታል፡፡ በግል ስለሚያስፈልጉ ጉዳዮች መጸለይ አስፈላጊ ቢሆንም በዚህ ክፍል እንደምናየው ***የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል 15:7*** የሚለው የተያያዘው ***ብዙ ፍሬ*** ከማፍራትና ከእግዚአብሔር መከበር ጋር ነው፡፡ ከደቀ መዝሙር የሚፈለገው አንድ ትልቅ ነገር ስጌታው ብዙ ፍሬ ማፍራት ነው፡፡

***15፥9 አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ፡፡*** የአማኞች አኗኗር፡-

- በኢየሱስ ነው (15፥4)፤
- በቃሉ ነው (15፥7)፤ እንዲሁም
- በፍቅሩ ነው (15፥9)፡፡

የክርስቶስ ፍቅር ፍጹም ነው፤ ምሳሌነቱ በአባና በወልድ መካከል እንዳለው ፍቅር ነው፡፡ ይህን ፍቀር ተረድተንና ተቀብለነው በዚህ ፍቅር ውስጥ ልንኖር ተጠርተናል፡፡

***15፥10 እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ፡፡*** በፍቅር መኖርና ትእዛዝን መጠበቅ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው፡፡ ትእዛዝን የሚጠበቅ በፍቅሩ ስመኖር የወደደ ነው፡፡ በአብ የተላከው ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱን ***ትእዛዝ*** ጠበቀ፤ ስለዚህም በፍቅሩ ኖረ፡፡ ጌታም ለደቀ መዛሙርቱ ትእዛዙን እንዲጠብቁና በፍቅሩ እንዲኖሩ ሲያዛቸው እርሱ ራሱ ይህን ማድረጉን በተግባር አሳይቶ ነው፡፡ እርሱ የአባቱን ትእዛዝ ሲጠብቅ አይተዋልና እነርሱም ይታዘዙታል፡፡ እርሱ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱን እስከ መጨረሻ የወደዳቸው (ምዕ 13) እነርሱም እርስ በርሳቸው እንዲሁ እንዲያደርጉ ይነግራቸዋል፡፡ የጌታ አመራር ደቀ መዛሙርቱ የሚያደርጉትን በመናገር ማስተማር ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱ በማድረግ አሳይቶ ምሳሌነቱን እንዲከተሉ መንገር ነው፡፡

***15፥11 ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ፡፡*** ጌታ የመሄጃው ጊዜ ስለ ደረሰ ደቀ መዛሙርቱ እንዳያዝኑ ደስ ስለ መሰኘት ይነግራቸዋል፡፡ «ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም» (14፥18) ያላቸው አሁን ደግሞ ስለ ፍጹም



ደስታ ይነግራቸዋል፡፡ ክርስትና የሀዘን ኑሮ አይደለም፡፡ በክርስትና ውስጥ መገፋት፣ መሰደድ፣ መከራ መቀበል ቢኖርም ክርስትና ግን የደስታ ሕይወት ነው፡፡ ይህ ደስታ ወደ ፍጹምነት የሚያድግ ነው፡፡

ይህ ደስታ የክርስቶስ ደስታ ነው፣ ***ደስታዬ*** ይለዋል፡፡ በሌላም ቦታ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ (10፥10) በማለት የሚበዛ ሕይወት እንዳለ ሁሉ የሚፈጸም (ፍጹም የሆነ ወይም የሚያድግ) ደስታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል፡፡ ደስታ ሙሉ የሚሆነው ከክርስቶስ ጋር ያለው ኅብረት የጠነከረ ሲሆንና ሰው ዕለት ዕለት በፍቅሩ ሲኖር ነው፡፡ ይህም በክርስቶስ በመኖር፣ እርሱን በማገልገል፣ ብዙ ፍሬ በማፍራትና በመታዘዝ የሚገኝ ደስታ ነው፡፡

***15፥12 እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት፡፡*** ቀደም ሲል እንዳየነው ስለ ፍቅርና መዋደድ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ የሚናገረው እርሱ ራሱ አድርጎ በማሳየት ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱን እንደ ወደዳቸው ራሳቸው ምስክሮች ናቸው፡፡ «የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው» (13፥1) እንዳለ፡፡ ይህ ፍቅር በእርሱ ጊዜ ለነበሩ ለደቀ መዛሙርቱና ከዚያም በኋላ ለሚመጡ የጌታ ተከታዮች ሁሉ ምሳሌ የሆነ ፍቅር ነው፡፡ ደቀ መዛሙርት እርስ በርሳቸው ሲዋደዱ ጌታ በምሳሌ አሳየ፡፡

***15፥13 ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም፡፡*** ይህ የመጨረሻ የፍቅር መግለጫ ነው፡፡ ራስን ለወዳጁ አሳልፎ መስጠት፡፡ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» ሲል የመልካም እረኝነቱ አንዱ መግለጫ ነፍሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ መስጠቱ ነው (10:11)፡፡ ፍቅር ራሱን ለሌላው መሥዋዕት አድርጎ እስከ ማቅረብ ድረስ ይዘልቃል፡፡ «ገና ኃጢአቶች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል» (ሮሜ 5፥8)፡፡ ፍቅር በተግባር ይገለጻል፡፡ ሌላውን ለመጥቀም ማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡ የተቸገረን በመጠየቅ፣ በመርዳት፣ በማበረታታት እና የመሳሰሉትን ሁሉ ማድረግን ያቅፋል፡፡ ስለሆነም «እወድሃለሁ» ከሚል ዘይቤያዊ የቃል አገላለጽ ያለፈ ጥልቀት ያለው ነው፡፡

***15፥14-15 እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና፡፡*** ወዳጅነት የቀረበ ግንኙነት ያመለክታል፡፡ አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሏል (ያዕ 2፥23)፣

እግዚአብሔር ሲገልጥለት የሚወደውን ሁሉ የገለጠለት ሰው ነው:: እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚያደርጉትን ብቻ በመንገር ትእዛዝን ብቻ አላስተላለፈም:: ትእዛዝ ብቻ የሚሰጠው *ባርያ* (አገልጋይ) ነው:: ወዳጅ ግን የተሰጠው ትእዛዝ ለምን እንደሆነም ያውቃል:: እነዚህ ደቀ መዛሙርት ወዳጅነታቸው የሚሰጣቸው ትእዛዝ ለምን እንደሆነ የትእዛዝ ሰጪውን ሀሳብ ጭምር ስለሚያውቁ ነው:: ስለዚህ ቅርበት አላቸው:: እንዲሁም ባርያነታቸው ደግሞ ትእዛዝ ሰጪው ጌታ ስለሆነና የእርሱን ቃል ፈጻሚዎች ስለሆኑ ነው::

ስለዚህ በባርያና በወዳጅ መካከል ያለው ልዩነት በሰው ደረጃ ከሆነ ባርያ አገልጋይ ነው፤ ወዳጅ ደግሞ ጓደኛ፤ ምክር የሚጠየቅ ሰው ነው:: ከመለኮት ጋር በተያያዘ ሲነገር ደግሞ ክርስቲያን የጌታ ባርያም ወዳጅም ይሆናል:: ወዳጅነቱ የሚያደርገውን ለምን እንደሚያደርግ፣ የታዘዘውን ለምን እንደሚፈጽም ምስጢር ማወቁ ነው:: ባርያነቱ ደግሞ ታዛዥነቱ ነው::[68]

***15፥16 እኔ መርጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ::*** መመረጥና መሾም በእርሱ በኩል የተፈጸመ ተግባር ነው:: ደቀ መዛሙርት ለዚህ አገልግሎት ራሳቸውን አልመረጡም፣ ራሳቸውንም አልሾሙም:: በግንዱ ላይ ያለ እያንዳንዱ

[68] በዚያን ዘመን የነበሩ ሕግ አወቂዎችና ፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርቶቻቸውን እንደ ባርያዎቻቸው አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር:: ከዚህ አንጻር ጌታ የእርሱ የሆኑት ደቀ መዛሙርት የመምህራቸውን ሀሳብና ዕቅድ የሚያውቁ በመሆናቸው ከሌሎች የተለዩና ወዳጆቹ እንደሆኑ ሲያሳይ ነው::

It is the priviiege of friendship to be made acquainted with the plans wishes, and wants of the friend. This instance of friendship Jesus had given them by making them acquainted with the reasons why he was about to leave them, and with his secret wishes in regard to them. As he had given their this proof of friendship, it was proper that he should not withhold from them the title of friends. ... He had opened to them his mind; made known his plans; acquainted them with the design of his coming, his death, his resurrection, and ascension; and, having thus given them the clearest proof of friendship. Barnes. Christ's disciples serve him, but their service is not bondage, but that of love. Hence, they are friends instead of servants. PNT. In those days, the disciples of a rabbi were considered his servants. Jesus would now change thet relationship; the disciples were to be not his savants but his friends. Jesus considered them as friends because he had told them every thing he had heard from the Father. Ibid. p.313.



ቅርንጫፍ የሚኖር ፍሬ እንዲያፈራ ጌታ ይፈልግበታል:: ይህ ፍሬም የመንፈስ ፍሬ፤ የሚዘልቅ ታማኝነትና ጽናት፤ የወንድማማች መዋደድ፣ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣትና የመሳሰለውን ሁሉ ያጠቃልላል:: መመረጥ ከተልዕኮ ጋር የተያያዘ ነው:: የተመረጠ ሰው መመረጡን በፍሬው ያሳያል:: ፍሬ እንዲያፈራም ይላካል::

***አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ሲል*** ደቀ መዛሙርቱ ሲያቀርቡ የሚፈልጉትን ልመና ሁሉ ማለት ቢሆንም በተለይ ግን የሚኖር ፍሬ ከማፍራት ጋር የተያያዘ እንደሆነ እናስተውላለን:: በ15፥7-8 እንዲሁ እብን መስመን ብዙ ፍሬ ከማፍራት ጋር ተያይዞ ተመልክተናል:: ***ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ*** የሚለውም ፍሬ ማፍራት ከመሄድ ጋር ተያይዞ ይታያል:: እንዲሁም «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ» (ማቴ 28፥18-20) ከሚለው ጋር ይስማማል::

***15፥17 እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ::*** ጌታን ***ይህን አዛችኋለሁ*** ብሎ የመዋደድ ትእዛዝ የሚሰጣቸው ወዳጆቼ ብሎ ለሚጠራቸው ለደቀ መዛሙርቱ ነው:: ስለሆነም እርስ በርስ መዋደድ «ቢኖር ደግ፤ ባይኖርም ምንም አይደለም» የሚባል ምርጫ አይደለም፣ ትእዛዝ ነው:: ትእዛዝ ነው ስንልም ሰው ፈቅዱ እንዲያደርገው የሚጠበቅበት ነው ማለታችን ነው:: ትእዛዙን ለመፈጸም እርስ በርስ መዋደድ ያስፈልጋል:: በየሀገሩ ያሉ ክርስቲያኖች ጥላቻ በተሞላበት ባሕር ውስጥ እንዳሉ ደሴቶች ናቸው:: ዓለም እነርሱን አይቀበላቸውም:: እነርሱ ከዓለም የተለዩ መሆናቸውንና የክርስቶስ መሆናቸውን የሚመሰክሩበት መንገድ እርስ በርሳቸው በመዋደዳቸው ነው::

***15:18 ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ::*** ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ጠልቷል:: የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም:: አሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እብቱ ሲሄድ ዓለም በእርሱ ላይ የነበራትን ጥላቻ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ታደርጋለች:: ዓለም የሚጠላበት ምክንያት እነርሱ ከዓለም የተለዩ ስለሆኑ ነው፤ እንዲህ እንደሚል:- ***ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል 15:19::*** ደቀ መዛሙርት ከዓለም የተመረጡ፤ ከዓለም ስላልሆኑ ዓለም የሚጠላቸው ናቸው::

***ከዓለም መረጥኋችሁ*** ሲል እንደሌላው ሰው ሁሉ ኃጢአተኞች እንደ ነበሩ ሲያመለክት ***ከዓለም ስለ አይደላችሁ*** የሚለው በክርስቶስ በማመናቸው የክርስቶስ መሆናቸውን ያሳያል:: የክርስቶስ ስለሆኑ ደግሞ ክርስቶስን ያልተቀበለ ዓለም እነርሱንም አይቀበልም፣

ይጠላቸዋል። ክርስቶስን ገና ከሕፃንነቱ ጀምሮ ዓለም አልተቀበለችውም። ንጉሡ ሄሮድስ ሊገድለው ፈለገ (ማቴ 2፥13-16)፤ በአገልግሎት ዘመኑ ብዙዎች ተቃወሙት እንዲሁም ለሞት አሳልፈው ሰጡት። ኢየሱስ ክርስቶስን ያልወደደች ዓለም እርሱን የሚከተሉትን እንዴት ትወዳለች?

ዓለም የምትወደውና የምትጠላው አላት። የምትወደው የራሷ የሆኑትን (1ጴጥ 4፥3-4) የምትጠላው የራሷ ያልሆኑትን ነው። የራሷ ያልሆኑት ሁሉ የኢየሱስ የሆኑት ናቸው። ይህን የዓለምን ጥላቻ ክእርሷ ወገን ያለመሆናቸው ምልክት ስለሆነ ክርስቲያኖች በደስታ ሊቀበሉት ይገባል። በዓለም መጠላት የሚመጣ በመሆኑ በመጣ ጊዜ እንዳናዝን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ አስተምሮናል፤ በአንጻሩ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ሆነን የእርሱንም ስም ከፍ አድርገን ይዘን እየኖርን ዓለም ክወደደችንና በሙሉ ከተቀበለችን ያን ጊዜ ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ዓለምን መውደድ ወይም ከዓለም ጋር መወዳጀት የእግዚእብሔር ጠላት መሆን ነው (ያዕ 4:4፤ 2ጢሞ 3:10-12፤ 1ዮሐ 2:15-17፣ 3:1፣ 4:5-6)። ዓለምን መውደድ ኃጢአትን በማድረግ መኖር፣ መቀጠል እንዲሁም በክርስቶስ ማፈር፣ ስለ ክርስቶስ መነቀፍን አለመፈለግና የመሳሰለውን ሁሉ ያጠቃልላል። ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱን ዓለም ቢጠላቸው የሚያስደንቅ አይደለም። ምክንያቱም:-

***15፥20 ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዷችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደ ሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ።*** ደቀ መዛሙርት የክርስቶስ ስለሆኑ በክርስቶስ ላይ የደረሰው ጥላቻ በእነርሱም ላይ ይሆናል። እርሱን የሚያሳድዱ ደቀ መዛሙርቱንም ያሳድዳሉ፤ እርሱን የሚቀበሉ ደግሞ የእርሱ የሆኑትን ይቀበላሉ። ***ባርያ ከጌታው አይበልጥም*** ብሎ አስቀድሞ ተናግሯቸው ነበረ (13፥16)፤ እንዲሁም ማቴ 10፥24። ይህም በትሕትና አገልግሎቱ እርሱን ሊመስሉት እንደሚገባ ሊያስተምራቸው ነው። እንዲሁም ደቀ መዛሙርት በሚገባ ሊያጤኑት የሚገባቸው ነገር የክርስቶስ አገልጋዮች ሆነዋልና ዓለም እርሱን ያሳደደችው ክሆነ እነርሱ ክዚህ የተሻለ አቀባበል መጠበቅ እንደሌለባቸው ነው።

***15:21 የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ስለ እኔ ያደርጉባችኋል።*** አማኞች በወይን ግንድ ላይ ያሉ ቅርንጫፎች ናቸውና እነርሱን ማሳደድ ክርስቶስን ማሳደድ ነው። ያም ቢሆን ግን ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለም እንዲሄዱና ፍሬ እንዲያፈሩ ታዟል። ዓለም ደቀ መዛሙርትን የሚያሳድዱ አብን ካለማወቅ ነው። ግን ለምን አላወቁም?



እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው ተጨማሪ ነጥብ ***ስለ እኔ ያደርጉባችኋል*** እንዳለ ክርስቲያኖች የሚቀበሉት ስደት ስለ ክርስቶስ ብቻ መሆን እንዳለበት ነው። ሰው በራሱ ኃጢአትም መከራ ሊቀበል ይችላልና።

***15፥22 እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም።*** ይህን ሲናገር ጌታ ኢየሱስ አይሁድ እኔ ባልመጣ ኖሮ ኃጢአት አያደርጉም ነበር ማለቱ ሳይሆን የእኔ መምጣት ለኃጢአታቸው ሰበብ አሳጣቸው፤ የሚያመካኙት ነገር አጡ ማለቱ ነው። የአይሁድ ኃጢአት ያለመቀበል ወይም ኢየሱስን የመቃወም ኃጢአት ነው። ይህን በማድረጋቸው እግዚአብሔርን ተቃወሙት። እርሱ የላከውን ኢየሱስን ባለመቀበላቸው ኃጢአታቸው ተገለጠባቸው። ምክንያቱም:- ***እኔን የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል 15፥23*** እንዳለ። እንዲሁም:- ***ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደረግሁ፥ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል 15፥24***፤ ስለዚህ ምክንያት የላቸውም።

***15፥25 ነገር ግን በሕጋቸው:- በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።*** እነዚህ ሰዎች ምልክት እየፈለጉ እርሱም ምልክት እያሳያቸው፤ በጥላቻቸው ቀጥለዋል። እነዚህ ምልክቶች እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው። እንደ ኒቆዲሞስ ዓይነቶች ምልክቶችን አይተው ወደ ጌታ መጥተዋል (3፡2)። ሌሎች ግን ይህንም እያዩ ሊቀበሉት አልወደዱም። ይህም የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ ነው (መዝ 69፡4)። ኢየሱስ ክርስቶስን የጠሉት በከንቱ ነው፤ ያለ ምክንያት እንዲሁ ጠሉት። ያለ ምክንያት መጥላት (መዝ 35፡19)። በከንቱ የሚጠሉት ሰዎች ደግሞ ይህን በማድረጋቸው እግዚአብሔርን ያገለገሉ የሚመስላቸው ጊዜ አለ (8፡44)።

እግዚአብሔር ዓለሙን ያለ ምክንያት ወደደ፤ ወይም መልካምን ነገር ከዓለም ሳያይ እንዲሁ ወደደ። ዓለም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ምንም ምክንያት ሳይኖር፤ በከንቱ፤ እንዲሁ ጠላች። ዓለም በጥላቻ የተሞላች ነች፤ አለቃዋ ዲያብሎስ ነውና። እግዚአብሔር ደግሞ በፍጹም ፍቅር የተሞላ ነው፤ እንዲሁ ልጁን ላከልና።

ደቀ መዛሙርት ዓለም ሳይቀበላቸው ሲቀር ስለምን ምክንያት ነው ብለው መጨነቅ አይኖርባቸውም። እየሠሩ ያሉት መልካም መሆኑን ሁሉም ሰው እየመሰከረም ክርስቲያኖች ግን ***በከንቱ*** ይጠላሉ።

ምክንያቱም የሚሠሩት ተግባር መልካም ስላይደለ ሳይሆን፣ ዓለም ክርስቶስን ስለማትቀበለው ነው:: ይዚህም ሁኔታ ቢሆን የጌታ የሆኑት ሁልጊዜ መልካም በማድረግ መቀጠል አለባቸው:: ቀድሞውንም መልካምን ማድረግ የጀመሩት በዓለም ተቀባይነት ለማግኘት ወይም ለመወደድ ብለው ሳይሆን መልካም ማድረግ ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ባሕርያቸው በመሆኑ ነው::
ክርስቲያኖች በዓለም ውስጥ እየኖሩ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚተዳደሩ ሰዎች ናቸው:: እንግዲህ ዓለም የምትጠላን የጨለማውን መንግሥት ጥለን ብርሃን ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለመጣን ነው (ቆላ 1÷12-13)::

ይህን የዓለምን ጥላቻ እንዴት መቋቋም ይቻላል?

***15÷26 እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱ ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ ስመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል::*** በ14÷26 ላይ አብ አጽናኙን የእውነት መንፈስ በእርሱ ስም፣ በኢየሱስ ስም እንደሚልክ ተናግሮ ነበር:: አሁን ደግሞ የምናየው የእውነት መንፈስ የሆነውን አጽናኙን የሚልከው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ የሚልከውም ከአብ ዘንድ ነው፣ ማለትም ከአብ የሚወጣ ነው:: በ14÷26 እና 15÷26 ላይ የምንመለከተው መንፈስ ቅዱስን የሚልከው አብ እንደሆነ ነው:: በ15÷26 ደግሞ በተጨማሪነት የምናየው ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስን እንደሚልክ ነው:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን የሚልኩት አብና ወልድ ናቸው::

በዚህ ቁጥር መንፈስ ቅዱስ ***አጽናኝ*** እና ***የእውነት መንፈስ*** በሚሉ ስሞች ሲጠራ እናያለን::

***አጽናኝ***- የሚለው የሚያመለክተው መርዳትን፣ ማገዝን፣ ማጠናከርን፣ ማጽናናትን ሲሆን ይህም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያሳያል:: ***የእውነት መንፈስ*** ደግሞ ማስተማርን፣ መግለጥን፣ ማሳሰብን ያመለክታል፤ ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው:: የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለልብም ለአእምሮም ነው:: ማጽናናት ለልብ ማስተማር ለአእምሮ ስለሆነ:: ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ በማጽናናትና እንዲሁም እውነትን በማስተማር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰክራል::

***15÷27 እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ::*** ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ አገልግሎቱን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከእርሱ ጋር ስለ ነበሩ (ሉቃ 1፡2፤ ሐዋ 1፡21-22) እነርሱ ስለ ክርስቶስ የሚመሰክሩ ናቸው:: ለመመስከር ግን የሚያሳስባቸውና



የሚያበረታታቸው (የሚያጽናናቸው) መንፈስ ቅዱስ ***የእውነት መንፈስ*** የሆነው ***አጽናኝ*** ያስፈልጋቸዋል:: ይህ መንፈስ በእነርሱ ላይ ይመጣል:: ስለዚህ ስለ ኢየሱስ የሚመሰክሩት መንፈስ ቅዱስና ደቀ መዛሙርት ናቸው::

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

***16፥1 እንዳትሰናከሉ ይህን ነግሬአችኋለሁ።*** ጌታ ደቀ መዛሙርትን የጠራቸው ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ (እንዲዘልቁ) ነው። ተሰናክለው እንዳያወድቁ ወይም ከዚህ በፊት ሌሎች ጥለው እንደሄዱ ሁሉ (6፥66) እነዚህ ደግሞ ጥለው እንዳይሄዱ ይመክራቸዋል። እርሱ ራሱ መከራን እንደሚቀበል እነርሱም የእርሱ ተከታዮች በመሆናቸው መከራ እንደሚደርስባቸው፤ በሆነ ጊዜ ደግሞ ድንገተኛ ነገር እንደመጣባቸው እንዳይመስላቸው አስቀድመው አውቀው እንዲዘጋጁ ያሳስባቸዋል።

***16፥2 ከምኩራባቸው ያወጡአችኋል፤ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል።*** ደቀ መዛሙርት ከዓለም ከሚጠብቁት የስደት ዓይነት አንዱ አብረው ኅብረት ከሚያደርጉባቸው ቦታዎችና ሁኔታዎች (ከማኅበራዊ ኑሮ) መገለል ነው። ከዚያም በላይ እግዚአብሔርን ያገለገሉ እየመሰላቸው ደቀ መዛሙርትን የሚገድሉበት ጊዜ እንደሚመጣ ያስገነዝባቸዋል። ቀደም ሲል በ9፥22 እና 12፥42 ላይ እንዳየነው ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሑ እንደሆነ የሚናገሩት ሁሉ የአይሁድ አለቆች ከምኩራቦቻቸው እንደሚያስወጡአቸው ዝተው ነበር። ይህን የሚሰሩት «ለሃይማኖታቸው» ቀናተኞች በመሆናቸው ነው፤ እግዚአብሔርን ማመን ምን ማለት እንደሆነ ግን አልተረዱም።

ሳውል ይባል የነበረው ጳውሎስ ክርስቲያኖችን እያሳደደ የነበረው እግዚአብሔርን ያገለገለ መስሎት ነው (ሐዋ 9፥1-2፣ 26፥9-11፤ ገላ 1፥13-14፤ ፊል 3፥6)። ጌታ በደማስቆ መንገድ ከተገናኘውና ዳግመኛ ከተወለደ በኋላ ጳውሎስ፦ «አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ፣ አንገላችም ምንም ብሆን ይህን አደረገልኝ። ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን አደረግሁት ምሕረትን አገኘሁ» (1ጢሞ 1፥13) ይላል።

እዚህ ላይ ዓለም ክርስቲያኖችን ማሳደዷ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ በክርስቲያኖችም መካከል አንዱ ሌላውን የሚያሳድድበትን ሁኔታ አብሮ ማየት ይጠቅማል። ጉዳዩን በትዕግሥትና በፍቅር በመያዝ ወንድምን ማቅናትና መመለስ ሲቻል እንኳ በየምክንያቱ ማግለል፤ ማውገዝ



ሲፈጸም ይታያል። ይህን ሲያደርጉ ሰዎች እግዚአብሔርን እያገለገሉ የሚመስላቸው ከሆነ በደንብ ሊታሰብበት ይገባል። ምክንያቱም

***16፥3 ይህንም የሚያደርጉባችሁ አብንና እኔን ስላላወቁ ነው።*** የክርስቶስ የሆኑትን ሲያሳድዱ እግዚአብሔር አብን ለማስደሰት ወይም እርሱን እያገለገሉ እየመሰላቸው ያደርጉታል። ጌታ ግን የሚናገረው ይህን የሚያደርጉት በሁለታቸው መካከል ያለውን አንድነት ስላልተረዱ፤ አብ የላከውን ኢየሱስን ስላላወቁ ነው።

***16፥4 ጊዜው ሲደርስ እኔ እንደ ነገርኋችሁ ታስቡ ዘንድ ይህን ተናግሬአችኋለሁ።*** ይህን ቃል የሚነግራቸው የምድር አገልግሎቱን እየፈጸመ በነበረበት ሰዓት ነው። ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ለወደፊቱ እያዘጋጃቸው ስለነበረ ይነግራቸው የነበረው በዚያው ጊዜ የሚፈጸመውንና ወደፊትም በየጊዜው የሚሆነውን ሁሉ ነው።

***16፥4-5 ከእናንተም ጋር ስለ ነበርሁ በመጀመሪያ ይህን አልነገርኋችሁም። አሁን ግን ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ ከእናንተም ወዴት ትሄዳለህ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም።*** ይህን ማሳሰቢያና ምክር ሁሉ የሚሰጣቸው እርሱ ከመካከላቸው ተለይቶ ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት ስለደረሰ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በነበረ ጊዜ እርሱ ጠባቂያቸው፣ አጽናኛቸው፣ አስተማሪያቸው ነው። ደቀ መዛሙርት በኃላፊ ጊዜ (ቀደም ሲል) ወዴት ትሄዳለህ? ብለው ጠይቀውት ነበር (13፥36፤ 14፥5)። አሁን በ16 ፥5 ላይ እንደምናነበው ደግሞ በአሁኑ ጊዜ አልጠየቁትም። በመጠየቅ ፋንታ በኀዘን ተዋጡ።

***16፥6 ይህን ስለ ተናገርኋችሁ ኀዘን በልባችሁ ሞልቶአል።*** ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚሞት ቀደም ብሎ ነግሮአቸው ነበር (7፥33-34)። አሁን የሚሄድበት ጊዜ እንደደረሰ ሲነግራቸው አዘኑ። ይህ ኀዘን መሪያችን፣ ጌታችን ከመካከላችን ተለይቶን ሲሄድ እኛን ምን ይውጠናል? ምንስ እንሆናለን የሚል ጥያቄ በውስጣቸው መጥቶባቸው ሊሆን ይችላል። ወላጅ እንደ ሌላቸው ልጆች (14፥18) የሆኑ መሰላቸው።

***16፥7 እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።*** ለደቀ መዛሙርቱም የኢየሱስ መሄድ የተሻለ የሚሆነው ለምንድን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ በአንድ ጊዜ በአካል በአንድ ቦታ ይገኝ ነበረ። ኢየሱስ ከሄደ በኋላ ግን በሚልከው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ በምድር ዙሪያ በሁሉም ቦታ ይገኛል። ይህ የእግዚአብሔርን ሥራ ወደ ዓለም ሁሉ ይዞ ለመሄድ ያስችላልና ለደቀ መዛሙርት መልካም ነው።

ጌታ ወደ አባቱ የሚሄደው የተላከበትን ዓላማ ከፈጸመ በኋላ ነው:: የተላከበት ዓላማ መጨረሻው በመስቀል ላይ እንዲሞት ስለሆነ ይህ መሆን አለበት:: ከሞተ በኋላ ደግሞ በሦስተኛው ቀን ይነሣል፤ ከተነሣም በኋላ ወደ አብ ይሄዳል፤ ከዚያም መንፈስ ቅዱስን ይልካል:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የሚወርደው ኢየሱስ ክርስቶስ ከከበረ በኋላ ነው (12÷39):: የኢየሱስ ክርስቶስ መክበር በሞቱ፤ በትንሣኤውና በዕርገቱ ነው::

አጽናኙን መንፈስ ቅዱስን የሚልክ እግዚአብሔር አብ ነው (14÷26፣ 15÷26):: እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን የሚልክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (16÷7):: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን የሚልኩ አብና ወልድ ናቸው::

***16÷8-11 እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ ስለ ኃጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ፣ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው::*** በዚህ ክፍል የመንፈስ ቅዱስን የመውቀስ አገልግሎት (ተግባር) እንመለከታለን:: መውቀስ እውነትን መግለጥ ወይም አንድን ሰው ወደ እውነት መምራት ወይም መጋበዝ የሚለውን ሁሉ ያጠቃልላል:: የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ አገልግሎት የሚፈጸመው:-

- ዓሰም ኃጢአተኛ እንደሆነች በመግለጥ (ወይም በማጋለጥ) ነው:: ሰዎች ኃጢአተኛ መሆናቸውን ይገልጣል::
- የእግዚአብሔርን ጽድቅ በማሳየት:: የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሲያሳይ ሰዎች ኃጢአተኛነታቸውን እንዲያውቁ ያደርጋል::
- ከእግዚአብሔር ጽድቅ አንጻር ኃጢአተኛነታቸው የተሰማቸው ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ያደርጋል::

***16÷9-10 ስለ ኃጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው:-*** ሰዎች የሚፈጽሙት ትልቁ ኃጢአት በኢየሱስ ክርስቶስ አለማመን ወይም እርሱን መቃወም ነው (3÷18):: እርሱን የማይቀበሉና የሚቃወሙ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይተው ይኖራሉ::

***16÷9-10 ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ:-*** መንፈስ ቅዱስ አንዱ የሚገልጠው ነገር የጽድቅ መለኪያ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ነው:: በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ስለ ጽድቅ ዓሰምን የሚወቅሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር:: እርሱ ወደ አብ ከሄደ በኋላ ዓሰምን ስለ ጽድቅ የሚወቅሰው የሚመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው:: ይህም ጽድቅ የሚገኘ



ው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በማመን እንደሆነ ሲያሳይ ነው::

***16÷11 ስለ ፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው:-*** በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሰይጣን የተፈረደበት እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ያስረዳል:: ሰይጣን የሰዎችን አእምሮ በማሳወር እና በማታለል፣ በማደንደን እስከ ጊዜው ድረስ የሚቀጥል ቢሆንም (1ጴጥ 5÷8) እርሱ የተሸነፈና የተፈረደበት የመጨረሻውን ውሳኔ ለማግኘት ቀን የሚጠብቅ ጠላት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል (ራእ 20÷2፤7-10)::

ሰዎችን ስለ ኃጢአትና ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ መውቀስ እንዲሁም ሰይጣን እንደ ተፈረደበት ማስታወቅ መንፈስ ቅዱስ ከወንጌል ስርጭት ጋር በተያያዘ የሚፈጽማቸው ሦስት አገልግሎቶች ናቸው:: ሰይጣን የተፈረደበት ጠላት ነው:: ስለሆነም የእርሱ ጨለማ በአማኞች ውስጥ ያለውን ብርሃን አያሸንፈውም:: ሰይጣን የተፈረደበት እንደሆነ ከሚከተሉት ቁጥሮች እንመለከታለን::

1. «ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ» (ሉቃ 1÷18):: ከሰማይ ሰይጣንን የጣለው ትዕቢቱ ነው:: ለዘላለም ከክብር ወደቀ::

2. «የዚህ ዓሰም ፍርድ ደርሷል፤ አሁን የዚህ ዓሰም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል» (ዮሐ 12÷31):: በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በሰይጣን ላይ ድል ተገኝቷል::

3. «የዚህ ዓሰም ገዥ ስለ ተፈረደበት ...» (ዮሐ 16÷11) በማለት በሰይጣን ላይ ስለ ተላለፈው ፍርድ ጌታ ይናገራል:: ይህም «እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው» (ዕብ 2÷14) ::

4. «በሕይወታቸው ሁሉ በሞተ ፍርሃት በባርነት የታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ» (1ዮሐ 3፡8):: በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ሰይጣን በሞት ላይ የነበረው ሥልጣኑ ተሻረበት::

5. «የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (1ዮሐ 3፡8):: የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መምጣት ዓላማው የሰይጣንን ሥራ በማፍረስ ተፈጸመ:: «ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወደ አሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ:: ለዘላለም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ» (ራእ

20፥10)። የመጨረሻው መጨረሻ በዲያብሎስ ላይ ድሉ የሚረጋገጠው ወደ እሳቱ ባሕር በሚጣልበት ጊዜ ነው፤።

***16፥12 የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም።*** ጌታ ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ የመጨረሻ ጊዜ ላይ ደርሷል። አቅማቸውን በማየት ለደቀ መዛሙርቱ ያልነገራቸው ነገር አለ። ደግሞም በኀዘን ውስጥ ናቸው፤ ስለዚህ የሚነግራቸውን ሁሉ ለመሸከም ይከብዳቸዋል፤ ሊያስታውሱትም አይችሉም። ሆኖም ሊነግራቸው ያሰበውን ሁሉ ሳይነግራቸው አይቀርም። ይህን የሚያደርገው ግን በሚልከው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው።

***16፥13 እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።*** የእውነት መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ አንዱ ሥራው (አገልግሎቱ) ወደ እውነት ሁሉ መምራት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሄደ በኋላ የሚልከው መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያስተምራቸው የፈለገውን ግን መሸከም ባለመቻላቸው ምክንያት ያዘገየውን እውነት ለደቀ መዛመርቱ ያስተምራቸዋል፣ ያሳስባቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ እውነት ኢየሱስ ስለሆነ ወደ ኢየሱስ ይመራል፤ እርሱ የተናገረውን ለደቀ መዛሙርቱ ያሳስባል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች መንገድን የሚያሳይ እውነተኛ መሪ ነው። እርሱ ስለ እውነት ያስተምራል (1ዮሐ 2፥20)።

መንፈስ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመመስከር ያጸናል፣ የሚመጣውንም ይነግራቸዋል። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ነገር አለ። ደቀ መዛሙርቱ ከጌታ ጋር የነበሩ፤ ከእርሱም የተማሩ ቢሆኑም እንኳ ወደፊት የሚመጣውን እንዲተነብዩ ይህ ችሎታ ከራሳቸው የላቸውም፤ ወይም ይህ ሥልጣን ለእነርሱ አልተሰጣቸውም። የሚመጣውን ማወቅ መለኮታዊ ተግባር ስለሆነ ይህን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የሚመጣውን ለደቀ መዛሙርቱ የሚናገር መለኮት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው።

እዚህም ላይ ልብ እንበል። ትንቢት መናገር የጸጋ ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ በአዲስ ኪዳን ይሠራል (1ቆሮ 12፤ ኤፌ 4፥14)። ስጦታውን የሚቀበሉ ደግሞ አማኞች ናቸው። ስጦታው ያላቸው ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ሰምተውና ከእርሱ ጋር ተስማምተው የሚያገለግሉ ናቸው እንጂ በራሳቸው «ነቢያት» አይደሉም። በራሳቸው ነገን የሚያውቁና የሚናገሩ አይደሉም። ስለሆነም ስለሚመጣው ነገር ሰው መታመን፤ መስማትና መደገፍ ያለበት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ነው።



***16፥14-15 እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና። ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው።*** በዚህ ክፍል ስለ ሥላሴ አካላት አብ፤ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አንድነታቸውን እንዲሁም ልዩነታቸውን[69] እናያለን። መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ሲያከብር አብንም ማክበሩ ነው። ኢየሱስ የነገረውን ሲናገር አብ የነገረውን መናገሩ ነው ። በዚህ የሀሳብና የዓላማ አንድነትን እናያለን። መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው ከአብ እና ከወልድ የሚወጣውን ነው። ከአብ የሚወጣው ከወልድ የሚወጣ ማለት ነውና። እንግዲህ ለአብ የሆነው ሁሉ ለወልድ ስለሆነ አብና ወልድ እኩል መሆናቸውን በዚህም እናያለን።

***16፥16 ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና።*** ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን የማያዩበት ጊዜ ሞቶ እስከሚነሣ ያለው ጊዜ ነው። የሚያዩት ***ጥቂት ጊዜ*** ደግሞ ከትንሣኤ በኋላ ወደ አብ እስከሚያርግበት ያለው ጊዜ ነው። ከዚያም ወደ አብ ይሄዳል፣ ጌታ ይህን ሲላቸው ***ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ እርስ በርሳቸው፡- … ይህ ምንድር ነው? ተባባሉ 16:17።*** ስጥቂት ጊዜ የሚለው ምን እንደሆነ አልተረዱትምና ጥያቄ ላይ እያሉ ጌታ እንዲህ ይላቸዋል፡- … ***እናንተ ታለቅሳላችሁ ሙሾም ታወጣላችሁ፤ ዓለም ግን ደስ ይለዋል፤ እናንተ ታዝናላችሁ ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል 16:18-20።*** ይህ ቀደም ሲል በ16፥16 አታዩኝምም፣ ታዩኛላችሁም ካለው ጋር የሚዛመድ አገላለጽ ነው።

የሚያለቅሱበትና ሙሾ የሚያወጡበት ጊዜ እርሱን የማያዩበት ጊዜ ነው። በዚያን ጊዜ ***ዓለም*** (ኢየሱስን ያሳደዱትና የሰቀሉት) ለሁልጊዜ ያስወገዱት መስሏቸው ደስ የሚሰኙበት ጊዜ ነው። ያሁን እንጂ ***ኀዘናቸው ወደ ደስታ ይለወጣል*** እንዳለው ደቀ መዛሙርቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ደስ ይላቸዋል። ይህንም ሲያስረዳቸው፡- ***ሴት በምትወልድበት ጊዜ ወራትዋ ስለ ደረሰ ታዝናለች፤ ነገር ግን ሕፃን ከወለደች በኋላ ሰው በዓለም ተወልዷልና ስለ ደስታዋ መከራዋን ኋላ አታስበውም 16:21*** በማለት በምሳሌ ይገልጽላቸዋል። ልትወልድ የተቃረበች ሴት ወራትዋ ስለ ደረሰ ኀዘን ላይ ትሆናለች። ከወለደች በኋላ ግን ኀዘንዋን ትረሳዋለች፤ ሕፃን ታቅፋለችና። እንዲሁ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ኀዘናቸውን ይረሳሉ፤ ደስተኞች ይሆናሉ።

[69] Distinctions

***16÷22 ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።*** ጌታ ኢየሱስ አንድ ጊዜ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ለዘላለም በሕይወት ይኖራል፤ እንደገና መከራ አይቀበልም፤ አይሞትም። ስለሆነም ከእነርሱ የማይወሰድ ደስታ ይኖራቸዋል። መጽሐፍ እንደሚል «ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞት ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና። መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቷልና። በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል» (ሮሜ 6÷9-10)። እንዲሁም 2ቆሮ 2÷17፤ ዕብ 7÷24-²5 ይመልከቱ።

***16÷23 በዚያን ቀን ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።*** ከዐውዱ እንደምናገናዝበው ***በዚያን ቀን*** ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ በአብ ቀኝ የሚቀመጥበትና መንፈስ ቅዱስ የሚወርድበት ጊዜ ነው። ያም የደስታ ቀን ነው። ደቀ መዛሙርት እስከ አሁን ጥያቄያቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያቀርቡ፣ ስለሚያስፈልጋቸው ይጠይቁትና ይለምኑት ነበረ። ***በዚያን ቀን*** ግን የሚጠይቁት አብን ይሆናል። ይህ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሄዶ በአብ ቀኝ የሚቀመጥበት ጊዜ ነውና አብን በኢየሱስ ስም ይጠይቃሉ። ***አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ*** ሲል አብ የሚቀበለውን ጥያቄ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠየቅ ተገቢ መሆኑን ያመለክታል። አብን ደስ የሚያሰኘው ጥያቄ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ (እንደ ቃሉ) የሆነ ልመና ሲሆን ነው። እንደዚሁም 14÷13-14 እና 15÷7ን ይመልከቱ።

እዚሁ ላይ እግዚአብሔር አብን መጠየቅ በቀጥታ ያለ ሌላ መካከለኛ (ወይም አማላጅ) የሚደረግ እንደሆነ ማስተዋልም ይጠቅማል። እግዚአብሔር አብን ለመጠየቅ በሌላ «አማላጅ» በሚሆን ሰው በኩል ማለፍ አያስፈልግም።

***16÷24 ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።*** ጸሎት ደስታን ያመጣል። ደስታ ከጸሎት ጋር የተያያዘ ነው። የሚጸልይ ሰው ደስተኛ ሰው ነው። ደስታን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና። ደስታ የመንፈስ ፍሬ ነውና። ደቀ መዛሙርቱ እንዲጠይቁ ጌታ ያስተምራቸዋል፤ ያበረታታቸዋል። እንዲሁም በ1ዮሐ 5፡13-15 ያለውን ይመልከቱ።

***16÷25 ይህን በምሳሌ ነግሬአችኋለሁ፦*** ስለሚመጣው ጊዜ ለደቀ መዛሙርት በቀጥታ ቢነግራቸው የማይከብዳቸው ነገር ነው። ***የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም 16÷12*** ብሏቸዋልና። ስለዚህ በምሳሌ ይነግራቸው ነበር። ሆኖም ***ስለ አብ ለእናንተ በግልጥ የምናገርበት እንጂ ከዚያ ወዲያ በምሳሌ የማልናገርበት ሰዓት ይመጣል 16÷25*** አላቸው። ያ ሰዓት ጌታ ከትንሣኤ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የገለጠላቸውና ያስረዳቸውንም ያመለክታል (ለምሳሌ 20÷19-23)።

***16÷26-27 በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤ እናንተ ስለወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና።*** የደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ክርስቶስን መውደድ አብ እንደላከው ወይም ከአብ እንደ መጣ ማመናቸው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ እንደመጣ ማመን ማለት እግዚአብሔር እንደላከው ማመን ስለሆነ አብ እርሱ ራሱ ይወዳቸዋል። እንዲሁም ***በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤***[70] ሲል ወደ አብ በቀጥታ ለመግባት እኛ እንደተፈቀደልንም ያመለክታል። ስለሆነም ይህን በቀጥታ ወደ አብ ለመግባት (ጥያቄ ለማቅረብ) የተፈቀደውን በር ደቀ መዛሙርት እንዲጠቀሙበት ያስተምራቸዋል።[71] እንዲሁም በዕብ 10÷19-25 ያለውን ይመልከቱ።

***ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደ ወጣሁ*** የሚለው ቀደም ሲል በ15÷26 ላይ «ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ» ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት አለው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጣ፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ ነው። ይህም ወልድ ከአብ ዘንድ እንደ መጣ፣ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ዘንድ እንደ መጣ የሚያመለክት ቃል ነው። ቀጥሎ ***ከአብ ወጥቼ***[72] ***ወደ ዓለም መጥቻለሁ ደግሞ ዓለምን እተዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ 16፡28*** የሚለው ይህንኑ ያብራራዋል። ከአብ መውጣት ማለት ከአብ ዘንድ መምጣት ነው። ***ዓለምን እተዋለሁ*** የሚለው ወደ ቀደመ ክብሩ ወደ አብም መመለሱን ያመለክታል። ***ወደ ዓለም መጥቻለሁ*** የሚለው ደግሞ ሰዎች ወደሚኖሩበት ደኅንነት ለመስጠት መምጣቱን ይገልጻል።

---

[70] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም፦ «በዚያ ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ ይህም በእናንተ ፈንታ አብን እለምናለሁ ማለቴ አይደለም» ይላል።

[71] ይህ ማለት ታዲያ በሮሜ 8፡34 እና ዕብ 7÷25 ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ እንደሆነ ከተገለጠው ጋር ይቃረናል ማለት አይደለም። እኛ አባታችንን (አብን) እንለምናለን፤ ኢየሱስ ደግሞ ስለ እኛ ያማልዳል ማለት እንጂ።

[72] ከአብ ወጥቼ የሚለው Came from the Father, <u>NIV</u>. ይህም ሥጋ መልበሱን incarnated, He became a human being የሚለውን ትርጉም ይይዛል።

ይህን ሲናገር ራሳቸው ***ደቀ መዛሙርቱ፡- እነሆ፥ አሁን በግልጥ ትናገራለህ በምሳሌም ምንም አትነግርም 16፥29*** አሉት፡፡ ምክንያቱም ወደ አብ መሄዱ መሆኑን በግልጽ እየነገራቸው ስለ ነበረ ነው፡፡ ቀጥሎም፡- ***ሁሉን እንድታውቅ ማንምም ሊጠይቅህ እንዳትፈልግ አሁን እናውቃለን፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ወጣህ እናምናለን አሉት 16፥30፡፡*** እንዲህ የሚሉት ለምሳሌ በ***16፥19*** ላይ ***ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደወደዱ አውቆ እንዲህ አላቸው*** እንደሚል በሀሳባቸው ያሰቡትን ሁሉ ማወቁን ተረዱ፡፡ ሰው ሊጠይቅህ አያስፈልግም እንተ ሁሉን ታውቃለህ ማለት ነው፡፡ ሁሉን እንድታውቅ ሲሉትም ወደፊት ስለሚሆነው ሁሉ ይነግራቸው ነበርና በሰው ዘንድ የማይታወቀውን እርሱ ስለነገራቸው ጭምር ነው፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ሁሉን የሚያውቅ[73] እንደሆነ ተገነዘቡ፤ ለመለኮትነቱ እርግጠኛ ሆኑ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ወጣ እመኑ ማለት ነው፡፡

***16፥32 እነሆ፥ እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል፥ አሁንም ደርሶአል፤ ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለሆነ ብቻዬን አይደለሁም፡-*** እንዳለውም አይሁድ በጌቴሴማኒ ጌታን በያዙት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ጥለውት ተበተኑ (ማቴ 26፡56፤ ማር 14፡50)፡፡ ጥለውት መበተናቸው በዘካ 13፡7 የተነገረውን «እረኛውን ምታ፡ በጎቹም ይበተናሉ» የሚለውን ያሳስባል፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ጥለውት ቢሄዱም እርሱ ግን ብቻውን አልነበረም፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበርና፡፡

ክርስቲያን ምንጊዜም ቢሆን ብቸኛ አይሆንም፡፡ ሰው በሌለበት ቦታም እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር አለ፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ጌታን ጥለውት እንደሄዱ በመከራ ሰዓት ወገኖች ሁሉ የሚከዱቸውና ክርስቲያኖች ለብቻቸው የሚሆኑበት ጊዜ ይመጣል፡፡ በዚያን ጊዜ ሁሉ ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ይኖራል፡፡

***16፥33 በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ፡፡*** ደቀ መዛሙርት በዓለም ውስጥ የሚገኙ በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ***በእኔ ሳላችሁ*** የሚለው የሚያመለክተው በክርስቶስ ማመንን፤ በእርሱ መኖርንና የእርሱ መሆንን ነው፡፡ ***በዓለም ሳላችሁ*** ሲል ደግሞ በሥጋ በምድር ላይ መኖርን፤ መመላለስን ያሳያል፡፡

[73] omniscient



ክርስቲያኖች በዓለም ውስጥ የሚገኙ የክርስቶስ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ በዓለም ውስጥ እየኖሩ ከዓለም ስላይደሉ (የክርስቶስ ስለሆኑ) መከራ አለባቸው፡፡ ክርስቶስን ያልተቀበለች ዓለም የእርሱ የሆኑትንም ታሳድዳቸዋለች፡፡ በስደት ውስጥም ቢሆን የጌታ ምክር ***አይዞአችሁ*** ነው፡፡ ይህ ***አይዞአችሁ*** የሚለው ቃል የሚወጣው ዓለምን ካሸነፈው ከክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡ ተስፋው ሙሉ ነው፡፡ በእርሱ ወገን ያሉት በአሸናፊው መሪነት ሥር ስላሉ እርሱ አሸንፏልና እነርሱም አሸናፊዎች ናቸው፡፡ ከሚሆነው ነገር የተነሣ ሰላማቸው እንዳይወሰድ፤ የማታ ማታ በጌታ ድሉ የእነርሱ መሆኑን እንዲያውቁ ይነግራቸዋል፡፡ ስለዚህ ደስታቸው ፍጹም ይሆን ዘንድ እንዲሰምኑ አስተምሮአቸዋል፡፡

ጌታ በፊቱ ያለውን መከራውንና ትንግሥውን ሲያስብ፤ ገና በፊቱ ያለ ቢሆንም እንዳለቀ አድርጎ ይናገራል፤ ***አሸንፌዋለሁ*** ይላልና፡፡ አዎ ክርስቲያኖች ***አይዞአችሁ***፡ ይህ ቃል የመጣው ዓለምን ካሸነፈ ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህ ሰላማችሁ በእርሱ ይብዛ፡፡ አሜን፡፡

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ምዕራፍ አሥራ ሰባት የኢየሱስ ክርስቶስን የምልጃ ጸሎት የያዘ ምዕራፍ ነው:: ከአብ ጋር ስለ ደቀ መዛሙርቱና በአጠቃላይ እርሱን ስለሚከተሉት ሁሉ ያደረገውን ጸሎት እንመለከታለን:: ከጌታ በጸሎት ጉልህ ሆነው የሚወጡት ሦስት ነጥቦች:- ወደ አባቱ ስመመለስ ያለው ፍላጐት ወይም ናፍቆት፤ ደቀ መዛሙርቱ በዓለም ኦያሉ ከክፉ የተጠበቁ እንዲሆኑና አማኞች ሁሉ አንድ እንዲሆኑ ነው::

በምዕራፉ ውስጥ እንደምናስተውለው ዓለም የሰይጣን ኃይላት ከቅዱሳን ጋር የሚዋጉባት የውጊያ ቦታ ነች:: ሰይጣንና ሠራዊቱ የክርስቶስ የሆኑትን እጅግ ስለሚጠሉ በዚህ ጥላቻ በተሞላበት ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ደቀ መዛሙርቱን እግዚአብሔር በሰላም እንዲጠብቃቸው ጌታ ይጸልይላቸዋል:: ከክፉው የሚጠብቃቸው እነርሱን በመለየት (ወይም በመቀደስ)፣ በማንጻትና በእርሱ እውነት አንድ በማድረግ ነው::

***17፥1-2 አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ፥ በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠኸው፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብረው::*** በቀደሙት ምዕራፎች እንዳየነው ጌታ ሲናገር ሰዓቱ ወይም ጊዜው ገና አልደረሰም ሲል ነበረ (2፥4፤ 7፥6፤8፤30፤ 8፥20):: ጌታ ይህ እስኪሞላ ድረስ ሲጠብቅ ነበር:: ይህ ሰዓት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ የሚቀበልበት፣ የሚሞትበት ሰዓት ነው:: ጌታ የሚከብርበት ሰዓት ስለ ሞላ (13፥31) ***አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል*** አለ:: ሰዓቱ ስለደረሰም ***ልጅህ ያከብርህ ዘንድ ... ልጅህን አክብረው*** ይላል:: ይህም በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ ***የዘላለም ሕይወት*** እንዲሰጣቸው ነው:: አጠቃላይ ግቡም ለእአብ ክብር ይሆን ዘንድ ነው::

***ልጅህን አክብረው*** ብሎ የሚጠይቀው መጀመሪያ ወደ ነበረበት ክብሩ (ፊል 2፥5-11) እንዲመልሰው ነው:: እግዚአብሔር አብ ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ *በሥጋ ሁሉ ላይ* ሥልጣንን ሰጥቶታል:: ያም ሥልጣን በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የዘላለም ሕይወትን መስጠት ነው:: አሁን ከአብ የተሰጠውን *ሥራ* ጨረሰ:: የዘላለምም ሕይወት መስጠት በሙላት የሚፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲከብርና በአብ ቀኝ



ሲቀመጥ ነው:: ስለዚህ የኢየሱስ ጸሎት ለእነዚህ ሰዎች የዘላለም ሕይወትን ይሰጣቸው ዘንድ ከጥንት በነበረ መኖሪያው እንዲያከብረው አብን የሚጠይቅ ነው::

***17፥3 እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተ የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት::*** በዚህ ቁጥር መሠረት የዘላለም ሕይወት ማለት እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆነውን እግዚአብሔርን ማወቅ እንዲሁም እርሱ የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው:: ማወቅ የሚለው ቃል ማመንና በእምነት መኖርንም የሚያጠቃልል ቃል ነው::

እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆነው ማን ነው? ይህ እውነተኛው አምላክ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን የላከ አምላክ ነው፤ ከእርሱ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም:: እውነተኛ አምላክ አንድ ብቻ ነው:: ***ብቻ የሆንህ*** የሚለው እውነተኛው አምላክ አንድ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል:: ይህ ***እውነተኛ አምላክ*** በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንዲሰጥ ኢየሱስ ክርስቶስን የላከው ነው:: ከዚህ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም:: ስለዚህ የዘላለም ሕይወት የሚገኘው:-

1. እውነተኛ አምላክ የሆነውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን በማወቅ፤

2. ይህ እውነተኛ አምላክ የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ነው::

በተመሳሳይ ሁኔታ ማቴ 11፥27:- «ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፥ ከወልድም በቀር ወልድም ሲገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም» ይላል:: እውነተኛ የክርስትና እምነት አብንና ወልድን በማወቅ የሚገኝ እምነት ነው::

በምድር ላይ ከሚገኙ በጣም ብዙ «ሃይማኖቶች» የዘላለም ሕይወትን የሚያስገኘው ትክክለኛው የትኛው ነው? የሚል ጥያቄ ሰዎች ሊያነሱ ይችላሉ:: ለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ግልጽ ነው::

- እውነተኛው አምላክ አንድ ብቻ ነው (17፥3)::
- ይህ እውነተኛው አምላክ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን የላከ ነው:: ከዚህ ሌላ እውነተኛ አምላክ የለም::

- እንዲሁም የዘላለም ሕይወት ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጥ ስጦታ ነው::
- ይህን የዘላለም ሕይወት እንዲሰጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሥልጣን የተሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ የዘላለም ሕይወት የሚቀበል ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ሰው ብቻ ነው::
- የዘላለም ሕይወት የመቀበያውም መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በማመን ነው::

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው እውነት ይህ እንደሆነ መገንዘብና በዚህ መኖር እውነትን ማወቅ ነው::

***17፥4 እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ:*** ጌታ ኢየሱስ በምድር እያለ አብን ያከበረው እንዲሠራው የሰጠውን ሥራ በመፈጸም ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲላክ (ሥጋ ሲለብስ) የተሰጠው ሥራ ነበረው:: ያንን ሥራ በመፈጸሙ የላከውን አከበረው:: ይህ ሥራ የተፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞት ነው:: ስለዚህ በፊቱ ያለውን የመስቀል ሞት በማሰብ ያንም እንደሚፈጽመው በማወቅ ***ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ*** ይላል::

እዚህ ላይ እግዚአብሔርን ስለማክበር የሚቀርልን ትልቅ ትምህርት አለ:: ሰው በሕይወቱ እግዚአብሔርን የሚያከብረው እንዴት ነው?

እግዚአብሔርን የማክበሪያው አንዱና ትልቁ መንገድ እርሱ የሰጠውን ሥራ መሥራትና መፈጸም ነው:: ይህም የሚሆነው እርሱ ባዘጋጀው መንገድ መስመርን ጠብቆ በመሮጥና ወደ ፍጻሜም በመድረስ ነው:: ከሩጫ የሚያዘናጉ፣ ከመስመር የሚያስወጡ በርካታ ነገሮች በሕይወት ሊመጡ ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜም መልካም የሚመስሉ ነገሮች ይሆናሉ:: እግዚአብሔርን በሕይወቱ ለማክበር የቆረጠ ሰው ግን እርሱ የሰጠውን ሥራ ወይም አገልግሎት በመፈጸም ያከብረው ዘንድ ሁልጊዜ ዓይኖቹን በመንገዱ ላይ ያደርጋል:: ሩጫውንም እንደ ጌታ ኢየሱስ በትዕግሥት ሮጦ ይጨርሳል (ዕብ 12፡1-2)::

***17፥5 አሁንም፥ አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ::*** ቃል የሆነው እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: እርሱ እግዚአብሔር ነውና ሥጋ ከመልበሱ በፊት በእግዚአብሔር ዘንድ በክብር ይኖር ነበር (ዮሐ 1፡18):: እርሱ ከአብርሃምም በፊት ነበርና (8፡58):: ጊዜው ሲደርስ ከሴት ተወለደ (ገላ 4፡4)፤ ሥጋም ለበሰ፤ ከሰማይ ወረደ (ዮሐ



3፥13)፤ ክብሩን ትቶ መጣ (ፊል 2፥5-11)፤ በራሱ ፈቃድ ወደ ምድር ሲመጣ ክብሩን ተወ::

አሁን የሚጸልየው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ወደ ነበረው ክብር አብ እንዲመልሰው ወይም በእርሱ ዘንድ እንዲያከብረው ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ ጥያቄው እንደተመለሰለት እስጢፋኖስ ኢየሱስን በአብ ቀኝ ቆሞ እንዳየው ከገለጸው (ሐዋ 7፥56) እንረዳለን::

እዚህም ላይ ***በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ*** ከሚለው የምናስተውለው ሌላ ትልቅ እውነት አለ:: ***ክብር*** ያለው የት እንደሆነ እናስተውላለን:: ክብር ያለው የክብር ጌታ በሆነው እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲከብር የጠየቀው በእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ክብር አለ፤ መከበርም አለ:: ብርሃን የሚገኘው ብርሃን ባለበት (በበራበት) ቦታ እንደሆነ ሁሉ መንፈሳዊ ክብርም የሚገኘው እግዚአብሔር በተገኘበት ቦታ ነው:: እግዚአብሔር ባልተገኘበት ክብር የለምና:: እግዚአብሔር ያለው ሰው የከበረ ሰው ነው::

***17፥6-7 ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው:: የአንተ ነበሩ ለእኔም ሰጠሃቸው፤ ቃልህንም ጠብቀዋል:: የጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደሆነ አሁን ያውቃሉ::*** እነዚህ ሰዎች አብ ለእርሱ የሰጣቸው ደቀ መዛሙርቱ ናቸው (15፥19):: ለእነዚህ ኢየሱስ ያደረገው ስሙን መግለጥ ነው:- ***ስምህን ገለጥሁላቸው*** እንደሚል:: ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ማንነት ለደቀ መዛሙርቱ አስተዋወቀ፤ እንዲሁም ኢየሱስን ማየት አብን ማየት እንደሆነም አስተማረ (1፥18):: እነርሱ ደግሞ ቃሉን ተቀበሉ፤ በመጠበቅም ታዘዙ:: በተገለጠላቸው እውነት ለመኖር ፈቃደኞች ሆኑ::

***17፥8 ከአንተም ዘንድ እንደወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላከኸኝ አመኑ::*** ደቀ መዛሙርቱ ያደረጉት ቃሉን መቀበል፤ ኢየሱስ ከአብ ዘንድ እንደወጣ (እንደመጣ) ማወቅና ከአብ የተላከ መሆኑን ማመን ናቸው:: ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣ አድርገው ተቀበሉት:: ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ የተላከ እንደሆነ አመኑ (16፥28-30):: በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሰው ክርስቶስ በአብ እንደተላከ ያመነ ሰው ነው::

***17፥9 እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ ያንተ ናቸውና::*** እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ እንደሚወድ

የታወቀ ነው (3፥16)። ልጁንም ወደ ዓለም የላከው ዓለምን ስለሚወድ ነው። ጌታ በዚህ ላይ በተለይ የሚጸልየው ከአብ ስለ ተሰጡት ስለ እነዚህ ደቀ መዛሙርቱ ነው። የሚጸልይላቸውም ስለ ጥበቃ (17፥11) እና ስለ መቀደስ (17፥17) ነው።

***17፥10 የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው፤ እኔም ስለ እነርሱ ከብሬአለሁ።*** በዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር ያለውን አንድነትና እኩልነት እናያለን። እነዚህ ሰዎች የጌታ ደቀ መዛሙርት ተብለው የሚጠሩት ናቸው። እነርሱ ግን የአብም ናቸው። ስለዚህ እነርሱ የአብም የወልድም ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አብ ከተመለሰ በኋላ የሚከብረው ስለ እነርሱ ነው። እነዚህ ደቀ መዛሙርት የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ወደፊት በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ እየገለጹ የሚቀጥሉ ናቸው።

***17፥11 ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው።*** ኢየሱስ ወደ አባቱ ሲመለስ ደቀ መዛሙርቱን በምድር ትቷቸው ነው የሚሄደው። ክርስቶስን ያልተቀበለችው ዓለም እነዚህን ደቀ መዛሙርቱን ስለማትቀበል ታሳድዳቸዋለች። ስለዚህ በዓለም የሚሆንበት ጊዜ አብቅቶ ወደ አባቱ ለመመለስ ሰዓቱ ስለደረሰ የሚጸልየው እነዚህ ደቀ መዛሙርት የተጠበቁ እንዲሆኑ ነው። የመጠበቂያው መንገድ በአንድነት ነው። የአንድነቱ ምሳሌ (ወይም ሞዴል) ደግሞ በአብና ወልድ መካከል ያለው አንድነት ነው። የሚጠበቁትም በስሙ ነው።

ጌታ ሲጸልይ በስሙ ከመጠበቅ ጋር አብን ***ቅዱስ አባት ሆይ*** ብሎ መጥራቱ የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ (የተለየ) መሆኑን ያሳስበናል። ***ቅዱስ*** የእግዚአብሔርን የቅድስና ባሕርይ ሲያመለክት ***አባት*** ደግሞ በእርሱና አብ መካከል ያለውን የዘላለም የፍቅር ተዛምዶ ይገልጻል።

የእግዚአብሔር ስም እርሱነቱን ይገልጣል። የእግዚአብሔር ሥልጣን በስሙ ውስጥ አለ። ስሙ ይጠብቃል ***በስምህ ጠብቃቸው*** እንዳለ። «የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው፤ ጻድቅም ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል» (ምሳ 18፥10)።

ጌታ ከዚህ ለደቀ መዛሙርቱ ከጸለየው ጸሎት ስለ ጥበቃ[74] ትልቅ ትምህርት እናገኛለን። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ «የሚጠብቅህ አይተኛም» (መዝ 121:3)፤ «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው» (መዝ 23:1)፤

[74] Protection



«አንተ ለሳጠርሀለት ነው» (ኢዮ 1:10) የሚሉትን እናገኛለን። በእርግጥም በእርሱ ለሚታመኑት እግዚአብሔር እረኛቸው፣ አጥራቸው፣ ጠባቂያቸው ነው። ክፉው እልፎ እንዳይገባና ጉዳትም እንዳያደርስ ሌት ተቀን ጥበቃው በሕዝቡ ዙሪያ አለ። ፈርዖን እስራኤላውያንን ባሳደዳቸው ጊዜ እግዚአብሔር በምድረ በዳ በእሳት ዐምድ ጠብቋቸዋል። የእሳቱ ዐምድ በእነርሱ በኩል ብርሃን ሲሰጥ በግብጻውያን በኩል እሳት (ወይም የሚያስፈራ አጥር) ሆኖ እስራኤላውያንን ጠብቋል። የእግዚአብሔር ጥበቃ በሕዝቡና በሌላው መካከል በመግባት ይለያልና። ሌላው ወደ ሕዝቡ እንዳይመጣ አጥር ይሆናል።

በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ ለመቆየት የሚፈልግ ሰው የጠባቂውን ቅዱስነት መዘንጋት የለበትም። እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና በእርሱ ጥበቃ ውስጥ ሊሆኑ የሚወዱ ሁሉ እርሱን እንዲፈሩትና በቅድስናም እንዲኖሩ ይጠብቃል። በስሙ የተቀደሱትን እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል። በሌላም በኩል ክፉው ማን በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ እንዳለና ማን ደግሞ አጥሩን እንዳፈረሰ ያውቃል።

ክፉው በጥላቻውና በዓለም ገዥነቱ አጥሩን አልፎ አንዳች ጉዳት እንዳያደርስባቸው የእግዚአብሔር ጥበቃ በእርሱ በሚያምኑት ዙሪያ እንዲሆን ነው። ይህም እያንዳንዱ በወይን ግንዱ ላይ የተጣበቀው ቅርንጫፍ (አማኝ) በየቀኑ በሰላም እንዲኖር፣ በእረፍት እንዲሆን፤ ተዘልሎ እንዲቀመጥ ዋስትና ይሰጠዋል። ይህ ጥበቃ የተያያዘው ከደቀ መዛሙርት መቀደስ ጋር ነው። አለመቀደስ የጥበቃን አጥር ያፈርሳል። እግዚአብሔርን አለማክበር፣ በቅድስና አለመመላለስ ጥበቃው እንዲነሣ ልቅ፣ ክፍት፣ የተደፈረ እንዲሆን ያደርጋል። ስለዚህ የጥበቃው አጥር ሁልጊዜ በእያንዳንዱ ሰው ዙሪያ እንዲሆን መቀደስ አስፈላጊ ነው።

በአብና በወልድ መካከል ያለው አንድነት ፍጹም ኅብረት ነው። አንድ ሀሳብ አንድ ዓላማ እንዳላቸው ሁሉ ቅዱሳንም እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለማክበር እንዲህ ዓይነቱ አንድነት ይኖራቸው ዘንድ ***እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ*** በማለት አብን ይጠይቃል። እንዲኖራቸው ይጸልይላቸዋል። ይህ ከማናቸውም የአንድነት ዓይነቶች ሁሉ ጠንካራ የሆነና ፍጹምነት ያለበት አንድነት ነው። የጌታ ጸሎት እንግዲህ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል በሦስትነት ውስጥ ያለው አንድነት በደቀ መዛሙርት መካከልም እንዲኖር ነው።

***17:12 ከእነርሱ ጋር በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበረ፤ ጠበቅኋቸውም።*** እነዚህ ደቀ መዛሙርት ከዓለም ለኢየሱስ የተሰጡ ናቸው (17፥6)። መልካሙ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ

በዓለም ሳለ ሲጠብቃቸው ነበር:: የእርሱ የሆኑትን ከእጁ ማንም አያወጣቸውም (10:29):: አሁን ግን ከምድር ወደ አብ የመሄጃው ጊዜ ስለ ደረሰ ጥበቃውን ለአብ ያስረክባል::

***17፥12 መጽሐፉም እንዲፈጸም ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም::*** ኢየሱስ በስሙ እንዲጠብቃቸው ከተሰጡት መካከል ይሁዳ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥበቃ ሥር መቆየትን ያልወደደ ሰው ነው:: በዚህም በመዝ 41፥9 የተነገረው ቃል ተፈጸመ:: ይሁዳ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንዲሆን መመረጡና ይህን ጥበቃ ትቶ የራሱን መንገድ መምረጡ (ሐዋ 1:24) በእግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣንና በሰው ምርጫ መካከል ያለውን ሚዛን ያሳየናል:: እግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣን አለው፤ ሰው ደግሞ ነፃ ምርጫ ተሰጥቶታል::[75]

***17፥13 አሁንም ወደ አንተ እመጣለሁ፤ በእነርሱም ዘንድ ደስታዬ የተፈጸመ እንዲሆንላቸው ይህን በዓለም እናገራለሁ::*** ከሞትና ትንሣኤ በኋላ ወደ አብ ሲያርግ ደቀ መዛሙርቱ ፍጹም (ሙሉ) ደስታ እንዲኖራቸው ይጸልያል:: የደቀ መዛሙርት ደስታ ፍጹም የሚሆነው ጌታ ከተነሣ በኋላ የተናገረው ሁሉ እንደተፈጸመና የሰጣቸውም የዘላለም ሕይወት ተስፋ እርግጠኛ እንደሆነ ሲመሰክቱ ነው:: ያን ጊዜ ደስታቸው ፍጹም ይሆናል:: ከተነሣ በኋላ ደስታቸው ፍጹም እንዲሆን ይህንን የሚነግራቸው ከመሞቱና ከመነሣቱ በፊት ነው:: በዮሐንስ ወንጌል ስለ ደስታ ቀደም ሲልም በ15፡11፤ 16፡24፤33 ተመልክተናል:: የደስታ ምንጩ ክኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የጠበቀ ኅብረት ማድረግ ነው::

***17፥14 እኔ ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው::*** ቀደም ሲልም ***የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና እነርሱም ተቀበሉት 17፥8*** በማለት ተናግሯል:: አሁንም ***ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ*** ይላል:: ኢየሱስን ያልተቀበለች ዓለም የኢየሱስ የሆኑትን ይህን ቃል የተቀበሉትን ልትወዳቸው አትችልም:: ስለሆነም በምትጠላቸው ዓለም ውስጥ እየኖሩ የተጠበቁ እንዲሆኑ ***ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም 17፥15*** እያለ ይጸልይላቸዋል::

***17፥16 እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም::*** በዓለም ናቸው (17፥11) ማለት የሚኖሩት በምድር ላይ ነው:: ***ከዓለም አይደሉም*** ማለት ከዓለም የተለየ የአኗኗር ባሕርይ አላቸው ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ በዓለም በነበረ ጊዜ በሰይጣን መሪነት በሚካሄደው በዓለም ሥርዓት ውስጥ አልነበረም:: ለእርሱ አልሰገደም:: «ሂድ አንተ ሰይጣን (ማቴ 4፥4-11) በማለት ተቃውሞታል:: እንዲሁም ለሰይጣን እንሰግድም ብለው አንዱን እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመልኩ የሚኖሩት በዓለም ማለት በምድር ላይ ቢሆንም በሰይጣን ገዥነት ውስጥ አይደሉም:: የሰይጣንን ሥርዓት አይቀበሉም በእርሱም ሥርዓት ሥር አይተዳደሩም::

ስለዚህ በምድር ላይ እያሉ ከዓለም ሥርዓት ውጭ የሆነ አኗኗር አላቸው:: አማኞች የልጁ መንግሥት ዜጎች ናቸው (ቆላ 1፥13):: ምክንያቱም ዳግመኛ ተወልደዋልና (ዮሐ 3፥3):: ዳግመኛ የተወለዱ ሁሉ በዚህ ምድር ላይ እየኖሩ የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት አባሎች ወይም ዜጎች ሆነዋል::

***17፥17 በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው፡-*** እንዳለ ይህ የእውነት ቃል ይቀድሳል:: በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያልፋሉ፣ በሚጠላቸው ዓለም ውስጥ ይኖራሉ:: እንዲህ እየኖሩ ኢየሱስ የሰጣቸው ቃል በዓለም እያሉ ከዓለም የተለዩ የሚያደርግ የሚቀድስ ቃል ነው:: ኢየሱስ ከአብ የተቀበለውና ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ቃል (17፥8) ***እውነት ነው***: ይህ ቃል ለእግዚአብሔር እንዲለዩ የሚያደርግ የሚቀድስ ቃል ነው:: ቃሉን በተቀበሉ ጊዜ[76] ቃሉ ለእግዚአብሔር ይቀድሳቸዋል:: እውነት በሆነው በዚህ ቃል እየተቀደሱም ይሄዳሉ[77]:: እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባው ሌላው ነገር ሰው በራሱ የሆነ ቅድስና እንደሌለው ነው:: የሚቀድስ እግዚአብሔር ነው፤ ***ቅዱስ አባት***: የሚቀድስ ቃሉ ነው፤ የእርሱ ቃል:: መጽሐፍ «ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው» (መዝ 119:9) እንደሚል የእግዚአብሔር ቃል ያጥባል፣ ያነጻል፣ ይቀድሳል::

---

[75] The place of Judas among the disciples and his choice to betray Jesus highlight the balance that we find throughout the Bible between the awesome sovereignty of God and the freedom he allows people to exercise. We would tip the balance toward error if we would say that Jesus intentionally withheld his protection of Judas to expose him to the temptation of Satan so that the betrayal could happen. We would also be in error if we would say that the temptation of Satan was stronger than Jesus' ability to protect Judas. Judas was not a puppet or a string. Judas shared the protection offered by the presence of Jesus all during their time together. Judas made his decision to betray Jesus, and by so doing he removed himself from Christ's protection. He passed the point of no return and thereby fulfilled the scriptural prediction. Ibid. p.341.

[76] Positional

[77] Progressive

***17፥18 ወደ ዓለም እንደ ላከኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላኳቸው:-*** ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣው ለሥራ ነው:: ***ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ 17፥4*** እንዳለው የመጣው በተልዕኮ ነው:: ይህ ተልዕኮ እግዚአብሔርን ለዓለም ማስተዋወቅ፤ መግለጥ ነው:: ደቀ መዛሙርት ወደ ዓለም የተላኩ[78] መልእክተኞች ናቸው:: ተልዕኮአቸውም በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ (17:3) እንደሆነ ማሳወቅ ነው::

***17፥19 እነርሱ ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ::*** በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብና መሥዋዕት ለማቅረብ ካህኑ ራሱን ለእግዚአብሔር ይቀድሳል:: አሮን በግንባሩ ላይ «ቅድስና ለእግዚአብሔር» (ዘጸ 28:36-37) የሚል ጽሑፍ ያለበት ጥምጥም ያደርግ ነበር:: ይህም ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መሆኑን፤ መሥዋዕት ለማቅረብ ራሱን ያነጻ መሆኑን ለመግለጥ ይሆናል:: ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በቀደሱ ካህናት በኩል ነውር የሌለበት መሥዋዕት ሲቀርብ እግዚአብሔር ደስ ይለው ነበር::

እንዲሁ ኃጢአት የሌለበት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ቀደሰ ማለት ለይቶ አቀረበ:: አብም በእርሱ መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ ደስ አለው:: ራሱን መሥዋዕት አድርጐ የሚያቀርበው በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የተቀደሱ እንዲሆኑ ነው:: ስለዚህ አማኞች የሚቀደሱት ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ስለሚያምኑት ራሱን ቀድሶ (ፈቅዶና ለይቶ) ስላቀረበ ነው (ዕብ 10፥10):: እንዲሁም እውነት የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ዕለት ዕለት ይቀድሳቸዋል::

***17፥20-21 ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔም ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ::*** ጌታ ለደቀ መዛሙርቱም ከጸለየ በኋላ እንዲሁ ***ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤*** ማለትም በእነርሱ መልእክት በኩል በእርሱ ስለሚያምኑትም ጭምር ጸልዮአል ማለት ነው:: ይህም በዓለም ዙሪያ ያለነውን ክርስቲያኖች ሁሉ ያጠቃልላል:: ኢየሱስ ሲጸልይ በዚህ ዘመን ለምንኖረው ለእያንዳንዳችን ጸልዮአል፤ ሁላችንም ***አንድ*** እንድንሆን አብን ለምኗል:: በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ ስለ ሦስት ነገሮች እንደ ጸለየ እንመለከታለን::

---

[78] የተላኩ ወይም መላክ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከአንድ ቦታ/አገር ወደ ሌላ ቦታ/አገርና ሕዝብ መሄድን ብቻ ሳይሆን በአሉበት አካባቢም ሆኖ ሁልጊዜ ተልዕኮን ተሸክሞ መዞርን ነው:: ተልዕኮውም እግዚአብሔርን ለሰው ሁሉ ማሳወቅ ነው::



አንደኛ:- ***ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ:-***
ለዚህም ለምሳሌ ወይም ሞዴል ያደረገው በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነት ነው:: የሚለምነው ስለ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ቦታና ዘመን ያሉ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ***አንድ ይሆኑ ዘንድ*** ነው:: ይህ አንድነት ፍጹምነት ያለው አንድነት ነው:: ከዚሁ ጋር ***አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥*** በአብና በወልድ መካከል ስላለው አንድነት የምንማረው ኢየሱስ በአብ ውስጥ መኖሩን እንዲሁም ወልድም በአብ መኖሩን ነው:: ከዚህም በመነሣት የሚለምነው አማኞች ሁሉ በአብና በወልድ አንድ እንዲሆኑ ነው::

ሁለተኛ:- ***እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ:-***
ክርስቲያኖች በኅብረት ሊኖሩ የሚችሉት ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ አንድነት ሲኖራቸው ነው:: በወይኑ ግንድ ላይ ያለ ቅርንጫፍ ከግንዱ የተነሣ ከሌሎቹ ቅርንጫፎች ጋር ኅብረት አለው (ዮሐ 15):: እያንዳንዱ ብልት ከሌላው የሰውነት ክፍል ጋር የተያያዘ ስለሆነ አንደኛው ሲጐዳ ሌላው ይሰማዋል፣ አንዱ ደስ ሲለው ሌላው ደስ ይለዋል (1ቆሮ 12፥12-27):: እንዲሁ ከኢየሱስ ጋር የጠበቀ ኅብረት ያላቸው ክርስቲያኖች ለእርስ በርሳቸውም አንድነት አላቸው:: ስለሆነም የጊዜ፤ የቦታ፤ የቋንቋ፤ የዘርና የቀለም ልዩነት ሳይኖር ሕይወትን ከወይን ግንዱ የሚያገኙ እስከሆኑ ድረስ በውስጣቸው ካለው የዘላለም ሕይወት የተነሣ የእርስ በርስ አንድነት አላቸው:: ስለዚህ የአንድነቱ መሠረት በውጭ ያለው «ግንኙነት/ አብሮነት» ሳይሆን በውስጥ የሚኖረው ሕይወት ነው::

ሦስተኛ:- ***አንተ እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ:-***
ይህ አንድነቱ የሚያስገኘው ውጤት ነው:: በኢየሱስ የሚያምኑት መለያየት ሳይሆን አንድነት፤ መነካከስ ሳይሆን መዋደድ ሲኖራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ዓለም ታምናለች::

***17፥22-23 እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ::*** ቀደም ሲል በቁጥር 20-21 እንዳየነው ጌታ «በእኛ» በማለት የሁለቱን አንድነት ገልጾአል:: በዚህም ቁጥር በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነት ሲገልጥ በአንድ ላይ ***እኛም*** በማለት ይናገራል:: ***እኛም*** የሚለው ቃል አብንና ወልድን በአንድነት የሚገልጥ በብዙ ቁጥር የተነገረ ቃል ነው::

ይህም «እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን አብ ይባል የነበረው በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ሆኗል» ብለው ለሚያስተምሩ የስሕተት አስተማሪዎች ሌላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ነው:: *በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ 17:20-21* እንዲሁም *እኛም አንድ እንደሆንን 17:22* ከሚሉት ክፍሎች እኛ የሚለውን ቃል እንመልከት:: ይህ *እኛ* የሚለው ከአንድ በላይ ለሆነ ብዙ ቁጥር የሚያመለክተው አብንና ወልድን ነው:: በእነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ ራሱን *እኔ* ብሎ ይጠራል፣ አብን *አንተ* ይላል፣ ከዚያም ሁለታቸውን በአንድነት *እኛ* ይላል:: ይህም ሁለት መሆናቸውን እንዲሁም አንድነታቸውን ያሳየናል:: አብና ወልድ በአካል ሁለት ናቸው፤ የመለኮት (የባሕርይ) አንድነት አላቸው:: በተጨማሪም በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ እንደምንገነዘበው በምድር ሆኖ አየጸለየ ያለው ወልድ ነው:: ጸሎቱን የሚያቀርበው በሰማይ ላለው ለአብ ነው:: ስለዚህ ሁለቱን እንመለከታለን:: ቢአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው በሦስትነት-አንድነት ዘላለማዊ ነው::

ጌታ *የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ* በማለት የሚናገረው *ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ 17:20* ላላቸው ለክርስቲያኖች ሁሉ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት በመናገር ብቻ የተገለጠ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ክብርም በመግለጥ ነበር:: እግዚአብሔር ለደቀ መዛሙርትና ለሰዎች ሁሉ የታወቀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ክብር ለሚያምኑት ሁሉ ይሰጣል:: ይህም ክብር የሚገኘው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት በማድረግ ነው::

አማኞችን አንድ የሚያደርጋቸው አብ ለወልድ የሰጠው ክብር ነው:: *የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ* ያለው ያ ክብር ወደ አንድነት ፍጹምነት ያደርሳል:: *በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ* ብሎ ጌታ እንደጸለየ አንድነት ወደ ፍጹምነት (ሙሉነት) ያድጋል:: ሰው በጌታ ባመነ ጊዜ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ እንደሚሆንና ዕለት ዕለት በአኗኗሩ በመቀደስም ወደ ፍጹምነት ማደግ እንዳለበት ሁሉ አንድነትም ያድጋል፤ ይጠነክራል::

የእግዚአብሔር ክብር ባለበት ሥታ የአንድነት ፍጹምነት (ሙላት) አለ:: የእግዚአብሔር መገኘት ሁሉን ወደ ራሱ ይሰባል፤ ክብሩ አንድ ያደርጋል:: ስለዚህም ከእርሱ የተነሣ አንድነቱ በሙላት ይሆናል:: ይህ በሆነ ጊዜ ጌታ ሲጸልይ በአማኞች አንድነት *ዓለም አንተ እንደ ላከኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል 17÷22-23* እንዳለ ቢያንስ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ::

- አንደኛ:- አብ ወልድን እንደላከው ዓለም ያውቃል::



- ሁለተኛ:- አብ ወልድን በወደደው መጠን በኢየሱስ ያመኑትንም እንደ ወደዳቸው ያውቃል::

እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አንድነት የጸለየው ከእርሱ ጋር የተገናኙት ሁሉ እርስ በርሳቸው የጠበቀ ኅብረት እንዲኖራቸው ነው:: ቀደም ሲል በ13÷34 ላይ እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ ለደቀ መዛሙርቱ አዲስ ትእዛዝ ሰጥቷቸው ነበረ:: አሁን ደግሞ መዋደድ እንዲችሉ ስለ እነርሱ ይጸልያል:: የዚህ የእርስ በርስ መዋደዳቸውና አንድነት:-

- *መሠረቱ*:- በእርሱ ማመን ነው:: *በእኔም ስለሚያምኑ 17÷20* እንደሚል::
- ዓላማው:- ኢየሱስ በአብ የተላከ እንደሆነ እንዲሁም አብ እነርሱን እንደወደዳቸው ዓለም (ሰው ሁሉ) እንዲያውቅ ነው (17÷23፤ 13÷35)::

ስለሆነም የቅዱሳን አንድነት ለዓለም የሚያስተላልፈው የከበረ መልእክት አለው::

*17÷24 አባት ሆይ÷ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ::* እግዚአብሔርን *አባት ሆይ÷* ብሎ የሚጠይቀው ልጁ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በአብና በወልድ መካከል ያለው የአባትና ልጅነት ፍቅር *ዓለም ሳይፈጠር* ነው:: በመካከላቸው ስላለው ፍቅር *ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ* እንደሚል ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ የሚጠራው ከድንግል ማርያም ከተወለደ ወይም ወደ ምድር ከመጣ በኋላ ካለው ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ከዘላለም ነው:: የአባትና ልጅነት ተዛምዶአቸው ዓለም ሳይፈጠር ከዘላለም ነው::

ጌታ ኢየሱስ *እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ* ብሎ ሲጸልይ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ መፈለጉ እቤት ምን ያህል የከበረ ነገር ነው? እርሱ ተመልሶም ይወስደናል (14÷18):: «ወደ እናንተ እመጣለሁ እንዳለ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፤ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» (14÷3) እንዳለ:: ስለዚህ ከወይኑ ግንድ ጋር የተጣበቁ ቅርንጫፎች (አማኞች) የዘላለምን ሕይወት አግኝተዋል፤ ወደፊትም በዘላለም በክብር ከክርስቶስ ጋር ይሆናሉ::

***17:25 ጻድቅ አባት ሆይ ዓለም አላወቀህም እኔ ግን አወቅሁህ፡-*** ኢየሱስ ቀደም ሲል በ17:11 ደቀ መዛሙርቱን ከዓለም እንዲጠብቃቸው ስለ ጥበቃ ሲለምን ***ቅዱስ አባት ሆይ*** ብሎ ነበር። አሁን ደግሞ ***ጻድቅ አባት ሆይ*** በማለት ዓለም ጻድቁን እንዳላወቀው ይናገራል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል፤ ኃጢአተኛን ይወዳል። ለኃጢአት ዋጋ ለመክፈል ልጁን እንዲልክ ግድ ያለው ጽድቁ ነው። ይህን ግን ዓለም አላወቀም። የላከውን አልተቀበለምና፣ ጠልቶታልና። ***መልእክተኛ*** ው ኢየሱስ ግን የላከውን ያውቃል፤ በእርሱ ያመኑትም እርሱ በአብ የተላከ እንደሆነ አውቀዋል።

***17፥26 እኔንም የወደድህባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም በእነርሱ፥ ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ።*** በ17፥6 ላይ ስምህን ገለጥሁላቸው እንዲሁም 17፥11 በስምህ ጠብቃቸው ብሏል። አሁን ደግሞ፡- ***ስምህን አስታወቅኋቸው*** ይላል። ስሙ ማንነቱን ስለሚገልጥ ስሙን ማስተዋወቅ እግዚአብሔርን ማስተዋወቅ ወይም መግለጥ ነው። ***አስታውቃቸውማለሁ*** ስለሚል እግዚአብሔርን የማስታወቁ ሥራ ወደፊትም እንደሚቀጥል ፍንጭ ይሰጣል። ስሙን የማስተዋወቅ ዓላማ አብ ልጁን የወደደበት ፍቅር በሚያምኑት በደቀ መዛሙርት ላይም እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ደቀ መዛሙርት ሊወድ ኢየሱስ ክርስቶስ በእነርሱ ውስጥ ይሆናል።

በአጠቃላይ በምዕራፍ 17 ጌታ ለደቀ መዛሙርቱና በእነርሱም በኩል እርሱን ለሚያምኑ የጸለየው በዓለም ውስጥ እያሉ የተጠበቁ እንዲሆኑ፣ የተቀደሱ እንዲሆኑና የእርስ በርስ አንድነት እንዲኖራቸው ነው።



# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

በምዕራፍ አሥራ ሰባት የተመለከትነውን ጸሎት ኢየሱስ ወደ አብ ከጸለየ በኋላ በምዕራፍ አሥራ ስምንት ደግሞ ኢየሱስ ከቄድሮን ወንዝ ማዶ ባለው የአትክልት ስፍራ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደ ነበረና በዚያም በአስቆሮቱ ይሁዳ መሪነት ወታደሮችና የካህናት አለቆች ሎሌዎች ሊይዙት እንደ መጡ እንመለከታለን።

በቀደሙት ምዕራፎች (ለምሳሌ፡- 10፥39፣ 11፥54) ፈሪሳውያንና የካህናት አለቆች ኢየሱስን ሊይዙት በፈለጉ ጊዜ <u>ጊዜው አልደረሰም ነበርና</u> በመካከላቸው አልፎ ሲሄድ አይተናል። አሁን ግን ሊይዙት ሲመጡ «ማንን ትፈልጋላችሁ» እንዲሁም «እኔ ነኝ» እያለ ራሱን ለመያዝ አሳልፎ ይሰጣል። ይህም መለኮታዊ የማዳን ዕቅድ ይፈጸም ዘንድ ጊዜው ስለ ደረሰ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በፈቃዱ ያቀረበበት ሁኔታ ነው።

ምዕራፍ አሥራ ስምንት በአጠቃላይ የሚያሳየው ኢየሱስ ከተያዘ በኋላ ስላለፈባቸው የተለያዩ የጥያቄና የፍርድ ሂደቶች ነው።

***18፥1 ኢየሱስም ይህን ብሎ አትክልት ወዳለበት ስፍራ ወደ ቄድሮን ወንዝ ማዶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወጣ፤ እርሱም ደቀ መዛሙርቱም በዚያ ገቡ።*** ይህ የአትክልት ቦታ በሌሎቹ ወንጌሎች ጌቴሴማኒ የተባለው ነው (ማቴ 26፥36-46፤ ማር 14፥32-42፤ ሉቃ 22፥39-46)። ከመሐል ኢየሩሳሌም ወደ ጌቴሴማኒ ለመሄድ የቄድሮንን ወንዝ አቋርጠው ያልፉ ነበር።

***18፥2 ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ጊዜ ወደዚያ ስለ ተሰበሰቡ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ደግሞ ስፍራውን ያውቅ ነበር።*** ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ለመስጠት ከተዘጋጀው እራት እንደወጣ በ13፥26-31 ባለው ተመልክተናል። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የት ይሰበሰቡ እንደነበረ፣ በአትክልት ስፍራውም በየትኛው ቦታ ላይ እንደሚገናኙ የሚያውቅ ውስጥ አዋቂ ሰው ነው። ይህ ቦታ ከዚህ በፊትም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምናልባት ለማረፍ፣ አብሮ ለመሆንና ለማስተማር፣ ለመጸለይም የሚሄድበት ቦታ ይሆናል፤ እንዲሁም ሉቃ 21፥37ን ይመልከቱ።

***18፥3 ስለዚህ ይሁዳ ጭፍሮቹንና ከካህናት አለቆች ከፈሪሳውያንም ሎሌዎችን ተቀብሎ በችቦና በፋና በጋሻ ጦርም ወደዚያ መጣ።*** ችቦና ፋና መያዛቸው ጊዜው ምሽት ወይም ሌሊት እንደ ሆነ ያመለክታል። ይሁዳም በዚያው ሌሊት ከጥቂት ሰዓቶች በፊት ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት እንደሄደ በ13፥30 ተመልክተናል። ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው በግልጽ ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት ሁሉ እያዩት ነው። ከጌታ ጋር የነበሩት ደቀ መዛሙርትም ጥለውት የሸሹበት ጊዜ ነበር (ማቴ 26፥56)። ከሌሎቹም ወንጌሎች እንደምናየው ይሁዳ ጌታን አሳልፎ የሰጠው በመሳም ነበር (ማቴ 26፥49፤ ማር 14፥45፤ ሉቃ 22፥47-48)።

***18፥4 ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና፦ ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው።*** ኢየሱስ በሰው ልብ ያለውን ሁሉ ያውቅ ነበር። «ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር ... ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና» (1:24-25)። አሁንም ሰዓቱ እንደ ደረሰ አውቆአል (17፥1)። ስለዚህ ***የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ*** ሰዓቱ ስለ ደረሰ ራሱን አቀረበ እና የመጡቱንም ሰዎች፦ ***ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው።*** እነርሱም ***የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት 18:5***፡

ቀደም ሲል የካህናት አለቆች ነቢይ ከናዝሬት (ከገሊላ) አንዳይነሣ እታውቅምን? (7:52) ብለው ተናግረው ነበር። አሁን ግን ሲያጠምዱት ሲመጡ ***የናዝሬቱን ኢየሱስን*** ብለው ይጠሩታል። አዎ ኢየሱስ ከናዝሬት ነው፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው። ለጥያቄያቸውም የሚመልስላቸው፦ ***እኔ ነኝ 18:5*** ብሎ ነው። ይህ ***እኔ ነኝ*** የሚለው ቀደም ሲል በ8፥58 የእርሱን መለኮትነት ከሚገልጠው አጠራር ጋር ተመሳሳይ ነው።

ሲይዙት ሲመጡ፦ ***አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር 18፥5***፡ የመጡት የሚፈልጉት የናዝሬቱ ኢየሱስን እንደ ሆነ ሲናገሩና ጌታም፦ ***እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ 17፥6***፡ እስቲ ምን ጣላቸው? ጋሻና ጦር ያለው በእነርሱ እጅ ነው፣ ወታደር የያዙ እነርሱ ናቸው። ይህ በጌታ ኢየሱስ ቃል (ንግግር) ውስጥ የሚያልፈውን ኃይል ያመለክታል። እግዚአብሔር ሲናገር ተራሮች ይንቀጠቀጣሉ ይጨሳሉ (ዘጸ 19:18፤ ዘዳ 4:12፤ መዝ 29:3-9)። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር ቢመጣም በእንዳንድ ሁኔታዎች እና በሚያደርጋቸውም ምልክቶች በመለኮትነት ኃይልና ሥልጣን ሥራዎችን ይሠራ እንደነበረ አይተናል (ማር 2:10፤ ሉቃ 11:20)። እንግዲያውስ እነርሱ እንዲይዙት ኢየሱስ ራሱን ባያቀርብላቸው ኖሮ እነዚህ ወደ ኋላ የወደቁት ሰዎች በወደቁበት



ለሁልጊዜም በቀሩ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ያደርግ ዘንድ ስለ ወደደ ሰዓቱም ስለ ደረሰ፣ ***ደግሞም፦ ማንን ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። 18፥7***፡

***18፥7-8 እነርሱም፦ የናዝሬቱን ኢየሱስን አሉት። ኢየሱስም መለሰ፦ እኔ ነኝ አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው አለ።*** ከአብ ከተቀበላቸው መካከል አንዳቸውንም እንደማያጠፋ ቀደም ሲል በ6፥39 እና በ17፥12 አይተናል። እነዚህ ይሄዱ ዘንድ ያላቸው ከይሁዳ በቀር ሌሎቹን አሥራ አንድ ደቀ መዛሙርቱን ነው። ***ይህም፦ ከእነዚህ ከሰጠኸኝ አንዱን ስንኳ አላጠፋሁም ያለው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው 18፥9***፡ እርሱ መልካም እረኛ ነውና ነፍሱንም ለበጎቹ አሳልፎ ይሰጣልና፤ (10፥41) ***እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው አለ***፡

***18:10 ስምዖን ጴጥሮስም ሰይፍ ስለ ነበረው መዘዘው፣ የሊቀ ካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቆረጠ። የባርያውም ስም ማልኮስ ነበረ።***ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ እንኳ ለመሞት የተዘጋጀ እንደሆነ የገለጸ ሰው ነው (ሉቃ 22:33)። አሁን ሰዓቱ ደርሶ ሲይዙት ሲመጡ ያን ዝግጅቱን የገለጸበት አንዱ መንገድ በያዘው ሰይፍ መጠቀም ነው። ኢየሱስን እንዳይወስዱት ለመከላከል ያለዚያም የሚቻለውን ተጋድሎ በማድረግ የተናገረውን ቃል ለመጠበቅ የሞከረ ሰው ነው።

ምናልባት እኮ ጴጥሮስ መታገሉን (ጆሮ መቁረጡን) ቀጥሎ ቢሆን በመካከላቸውም ሌላ ሰይፍ የያዘ ነበርና (ሉቃ 22፥38) ቢሳካለት ኖሮ ኢየሱስ እንዳይሞት መከልከሉ ነበር። በሌላም ጊዜ ይህ «አይሁንብህ» (ማቴ 16:22) ብሎታል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሞት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ የዓለምን ኃጢአት እንዲያስወግድ ነው።

ጴጥሮስ ስላደረገው ነገር ጌታ አላመሰገነውም። እንዲያውም ***ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው 18፥11።*** መቼም ጴጥሮስ ለጌታ ያሳየው መውደድና ታማኝነት በጣም ትልቅ እንደሆነ ግልጽ ነው። ነገር ግን ዋናውን ዓላማ ይህም ጌታ ጽዋውን መጠጣት እንዲገባው ረስቷል። ስለሆነም ኢየሱስ ለጴጥሮስ አትከላከል፣ አትከራከር የእግዚአብሔር ፈቃድ በእኔ ሕይወት ይፈጸም ሲል ***ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው*** አለው።ያስደንቃል! ኢየሱስ ማንም ስለ እርሱ እንዲሟገትለት አልፈለገም። ኢየሱስ በፊቱ ያለውን ***ጽዋ*** (መከራና ሞት) ይጠጣው ዘንድ ይህ የአባቱ ፈቃድና ጊዜው እንደሆነ ስላወቀ ይህን ለመቀበል ራሱን ፈጽሞ ያቀረበ ሰው ነው።

በዚህ ዘመን ላለን የጌታ ተከታዮች ይህ ***አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን?*** የሚለው ምን መልእክት ይኖረዋል? የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሕይወቱ የተገነዘበ ሰው ከእርሱ መልካም የሆነውን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ለመቀበል ራሱን በፈቃዱ ለእግዚአብሔር ያቀርባል (አይንፈራገጥም):: ጽዋው መራራ ቢሆንም ራሱን ለእግዚአብሔር የሚያቀርብ ሰው ክርክርና ሙግት የሌለበት ሕይወት ሊኖር ይገባዋል:: ለጊዜው እጅግ መራራና ከባድ ቢሆንም ውጤቱ ግን እግዚአብሔርን ለማክበር እና ለብዙዎች ጥቅም ይውላል:: ስለዚህ በክርስቲያኖች ሕይወት የእግዚአብሔር ፈቃድ በሆነ መንገድ ጽዋን መጠጣት በሚያስፈልግበት ጊዜ ያን የቀረበውን ከመከላከል ይልቅ የሚበጀው የሚያስችል ጸጋ ከእርሱ መጠየቅ ነው::

አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳናስተውል ወይም በሌሎች የተቀደምንና የተረታን እየመሰለን ነገሮችን በእኛ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ የምንጥርባቸው ጊዜያት ይኖራሉ:: ጴጥሮስ የወሰደው እርምጃ በኢየሱስ ፊት ሞገስ እንዳላስገኘለት ሁሉ እኛም ልናደርግ ያሰብነው ነገር መልካም ቢመስለንም በዚህ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ አለበት ወይ? ብሎ መጠየቅና እንዲህ ከተረዳን ፈቃዱ በምድር (በእኛ ሕይወት) እንዲፈጸም ከእርሱ ጋር መስማማት ይበጃል:: ስለሆነም የሕይወት ጉዞ «እግዚአብሔርን አመለጥሁት» ዓይነት እንዳይሆን በእጅጉ ማስተዋል ያስፈልጋል::

***18፥12-13 ኢየሱስን ይዘው አሠሩት፤ አስቀድመውም ወደ ሐና ወሰዱት፤ በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ለነበረው ለቀያፋ አማቱ ነበርና::*** በዚህ ዓመት ሐናና ቀያፋ ሁሉቱም ሊቀ ካህናት ነበሩ::[79] አይሁድ ሐናን እንደ ሊቀ ካህን አድርገው ይቆጥሩትና በሊቀ ካህንም ማዕረግ ይጠሩት ስለ ነበረ ኢየሱስን አስቀድመው ወደ እርሱ ወሰዱት:: ምንም እንኳ ጊዜው ሌሊት ቢሆንም ያሰቡትን ለማድረግ እጅግ ተቻኩለው ነበር:: ሐናም በዚያው ሌሊት ሊያደርግ የፈለገውን አደረገ::

***18፥14 ቀያፋም አንድ ሰው ስለ ሕዝብ ይሞት ዘንድ ይሻላል ብሎ ለአይሁድ የነገራቸው ነበረ::*** ይህንን ምክሩን በ11:49-52 ባለው ተመልክተናል:: ቀያፋ ይህን ያለው ደኅንነት ስለሚገኝበት መንገድ ሳይሆን ሮማውያንን ስለ ፈራ የተናገረው ነበረ::

***18፥15 ስምዖን ጴጥሮስም ሌላውም ደቀ መዝሙር ኢየሱስን ተከተሉት። ያም ደቀ መዝሙር በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀ ነበረ፥ ወደ ሊቀ ካህናቱም ግቢ ከኢየሱስ ጋር ገባ::*** ለመጀመሪያ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ

[79] በዚህ ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 49 ይመልከቱ::



መካከል ጌታን ተከትለው የሄዱት እነዚህ ሁለቱ ስምዖን፣ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር ናቸው:: ሌሎቹ ጥለው እንሄዱ በማቴ 26:56 እናያለን:: ይህ በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀው ***ሌላው ደቀ መዝሙር*** ማን እንደሆነ በስም ባይጠቀስም በ20፥2፤ 21፥20፤24 ላይ በተመሳሳይ አጠራር የተጠራው ዮሐንስ በመሆኑ ይኸው ዮሐንስ የዚህ ወንጌል ጸሐፊ ነው ማለት ነው::

***18፥16 ጴጥሮስ ግን በውጭ በበሩ ቆሞ ነበር:: እንግዲህ ከሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀው ሌላው ደቀ መዝሙር ወጣ ለበረኛይቱም ነገር ጴጥሮስን አስገባው::*** ይህ ሌላው ደቀ መዝሙር ከሌሎች የጌታ ደቀ መዛሙርት ይልቅ በሊቀ ካህናቱ ዘንድ እንዴት እንደታወቀ እዚህ የተገለጠ ነገር የለም:: ይኸው ደቀ መዝሙር ግን በሩን ትጠብቀው ለነበረችው ሴት/ አገልጋይ/ገረድ ነግሮ ጴጥሮስ ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ እንዲገባ ፈቃድ እንዳስገኘለት እናያለን::

***18፥17 ይህች በረኛ የነበረችይቱም ገረድ ጴጥሮስን፦ አንተ ደግሞ ከዚህ ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን? አለችው:: እርሱም፦ አይደለሁም አለ::*** ይህ ከኢየሱስ ***ደቀ መዛሙርት አንዱ ... አይደለሁም*** ማለቱ የጴጥሮስ የመጀመሪያው ክህደቱ ነው:: ቀደም ሲል ግን ነፍሱን ስለ ኢየሱስ መስጠት እንኳ ቢሆን እንደሚያደርገው በ13፥37 ገልጾ ነበር::

***18፥18 ብርድ ነበርና ባሮችና ሎሌዎች የፍም እሳት አንድደው ቆመው ይሞቁም ነበር፤ ጴጥሮስም ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ይሞቅ ነበር::*** ኢየሱስን ሊይዙት የሄዱት ሻለቃው፣ የአይሁድም ሎሌዎች እና ባሮች ናቸው:: ጴጥሮስ የጌታ ደቀ መዝሙር ካይደለ በዚያ ሌሊት ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ለምን ሄደ? በዚያ ጨለማና ብርድ እዚያ ቦታ ምን ያደርጋል?

***18፥19 ሊቀ ካህናቱም ኢየሱስን ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው::*** ይህ ኢየሱስ ላለፈበት የፍርድ ሂደት የመጀመሪያው ደረጃ ነበር:: የሐና ጥያቄ ምናልባት ለንት ደቀ መዛሙርት አሉህ? ብሎ ቁጥራቸውን ሲያውቅ አመፅ ለመቀስቀስ የሚችል መሆን አለመሆኑን ለመገመት ይሆናል:: እንዲሁም ትምህርትህ ምንድን ነው? የሚለው እርሱ ንጉሥ እንደሆነ ቢገልጥለት ይህ ቄሳርን ተቃዋሚ መሆኑን በራሱ አንደበት ተናግሯል ብሎ ማስረጃ ለማድረግ ሊሆን ይችላል::

የጌታ መልስ ደግሞ፦ ***እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኩራብና በመቅደስ እኔ ሁልጊዜም አስተማርሁ፥***

*በስውርም ምንም አልተናገርሁም 18፥20* የሚል ነበር። ኢየሱስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ብዛትም ሆነ አነማን እንደሆኑ ያልተናገረው ደቀ መዛሙርቱን ከክፉ ለመጠበቅ ይሆናል። ቀደም ሲል *እነዚህን ተዉአቸው 18፥8* እንዳለ። ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው በምኩራብ በመገኘት፤ ወደ ቤተ መቅደስም በመግባት፣ በበዓል ሁሉ በመገኘት ነበረ። እርሱን የሚከተሉት፤ ያደረገውን ምልክት ያዩ፣ የመሰከሩ ብዙዎች ናቸው። ስለዚህ በድብቅ የሠራው ነገር አልነበረም። ለነገሩ ይህንን ሊቀ ካህናቱም ሆኑ ፈሪሳውያን ያውቁ ነበር። ሎሌዎቻቸውን ልከው ሳይዙት የተመለሱት ትምህርቱን ከሰሙ በኋላ ነበርና (7:45-46)።

ስለዚህም ጌታ፡- *ስለ ምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ፥ እነዚህ እኔ የነገርሁትን ያውቃሉ አለው 18፥21። እነሆ እነዚህ* የሚለው ምናልባት ይዘው ወደ እርሱ ወደ ወሰዱት ሎሌዎችና ባሮች ማመልከቱ ይሆናል። ከእነዚህ ውስጥ እንዲይዙት ታዘው በትምህርቱ ተገርመው ሳይዙት የተመለሱ ነበሩ (7:45-46)።

የጌታ እንዲህ ዓይነት አመላለስ ድፍረት የመሰለው ሎሌ፡- *ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመልሳለህን? ብሎ ኢየሱስን በጥፊ መታው 18፥22።* ኢየሱስ የቆመው የመዳኘት ሥልጣን ባለው በሊቀ ካህናቱ ፊት ስለሆነ ሊቀ ካህናቱ በጥፊ እንዲመታ ሳያዝ ይህ ሎሌ መምታቱ ይገርማል። ሥርዓት ለማስከበር አስቦ ይሆናል እኮ! ሥርዓት ግን ትክክል የሆነውን በማወቅና በማድረግ ነበረ። በዚህ ጊዜ በሐና ፊት ታስሮ የቆመው ኢየሱስ ሎሌውን፡- *ክፉ ተናግሬ እንደ ሆንሁ ስለ ክፉ መስክር፤ መልካም ተናግሬ እንደ ሆንሁ ግን ስለ ምን ትመታኛለህ? 18፥23* በማለት ምንም ክፉ የሆነ ነገር እንዳልተናገረ አስረዳ። ይህ ሁኔታ በጳውሎስ የሆነውን ያስታውሳል (ሐዋ 23፥2-5)።

*18፥24 ስለዚህ ሐና እንደ ታሰረ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ሰደደው።* ወደ ቀያፋ መስደዱ በጊዜው በወንበር ላይ ወደ ነበረው ሊቀ ካህናት (ማለትም የዚያን ዓመት ሊቀ ካህናት ሆኖ በሥልጣን ላይ ወደነበረው) መላኩ ነው። ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ የፍርድ ሂደት ሁለተኛው ደረጃ ነው። በዚህ ጊዜ *ስምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ይሞቅ ነበር። እንግዲህ፡- አንተ ደግሞ ከደቀ መዛሙርቱ አይደለህምን? አሉት። እርሱም፡- አይደለሁም ብሎ ካደ 18፥25።* ሁለተኛው ክህደት ነው።

*18፥26-27 ጴጥሮስ ጆሮውን የቈረጠው ዘመድ የሆነ ከሊቀ ካህናቱ ባሮች አንዱ፡- በአትክልቱ ከእርሱ ጋር እኔ አላየሁህ አልነበርሁምን? አለው። ጴጥሮስም እንደገና ካደ፥ ወዲያውም ዶሮ ጮኸ።* ሦስተኛው የክህደት ቃል የተነገረው ጌታ ኢየሱስ፡- «ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» (13፥38፤ ማር 14፥30) ብሎ እንደተናገረው ነው። ያን ጊዜ ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ሲለው ጴጥሮስ ፈጥኖ ነፍሱን እስከ መስጠት ድረስ ከመወራረድ እንግዲህ «አቤቱ አንተ እርዳኝ፤ አግዘኝ» ቢል ምንኛ በተሻለ ነበር። እንዲህ ማለትን ጴጥሮስ የተማረው በሕይወት ጉዞው ዘግይቶ ነው። በ21፥15-29 ባለው ክፍል ትወደኛለህን? ብሎ ደጋግሞ ሲጠይቀው ለሦስተኛው ጥያቄ የሰጠው መልስ «አንተ ታውቃህ» የሚል ነበር። ይህ አንተ ታውቃለህ ምላሽ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ሁልጊዜም ቢያደርገው ምንኛ መልካም በሆነ ነበረ።

*18፥28 ኢየሱስንም ከቀያፋ ወደ ገዥ ግቢ ወሰዱት፤ ማለዳም ነበረ።* በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበረው ገዢ ጲላጦስ ነው። ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ መውሰዳቸው ሦስተኛው የፍርድ ሂደት ነበር።

*18፥28 እነርሱም የፋሲካን በግ ይበሉ ዘንድ እንጂ እንዳይረከሱ ወደ ገዡ ግቢ አልገቡም።* አይሁድ ስለ መንጻት ሕግ እጅግ ይጨነቃሉ። ውጫዊ በሆነ ነገር ላይ ያተኰሩ የነፍስ መንጻትን የዘነጉ ናቸው። በእነዚህ አይሁድ ሥርዓት መሠረት የፋሲካ በዓል በሚሆንበት ጊዜ ወደ አሕዛብ/ የማያምን ሰው ቤት መግባት ያረክሳል። ይህን ያደረገ ወደ መቅደስ ሲገባ ወይም የፋሲካን በዓል ሥርዓት ሊያደርግ አይፈቀድለትም። ሕግን ለመጠበቅ ይጥራሉ። በውስጣቸው ግን ክፋትና መግደል ተከምሯል (ማቴ 23:30-31)። ውጭውን የሚያጸዱ ውስጣቸው የቆሸሸባቸው ናቸው (ማቴ 23:25)። *አይሁድ ወደ ገዡ ግቢ ስላልገቡም ጲላጦስ ወደ ውጭ ወደ እነርሱ ወጥቶ፡- ይህን ሰው ስለ ምን ትከሱታላችሁ? አላቸው 18፥29።* የሰጡትም መልስ፡- *ይህስ ክፉ አድራጊ ባይሆን ወደ አንተ አሳልፈን ባልሰጠነውም ነበር 18፥30* የሚል ነው። ኢየሱስ እንደ *ክፉ አድራጊ* ተቆጠረ።

*18፥31 እናንተ ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት*። በዚያን ዘመን አይሁድ በሮማውያን ቅኝ ግዛት ሥር ስለ ነበሩ የተወሰነ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ነበራቸው። መጠነኛ ቅጣት ወይም ፍርድ ሊሰጡ ነፃነቱ ተሰጥቷቸው ነበር። በኢየሱስ ላይ ግን ያሰቡት ፍርድ ከዚህ ያለፈ ከባድ ስለ ነበረ ለጲላጦስ የሚመልሱለት፡- *ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም 18፥31* በማለት ነው። ኢየሱስ እንዲሞት ስለሚፈልጉና በተሰጣቸው የውስጥ አስተዳደር ነጻነት ደግሞ በእነርሱ ደረጃ ሰው እንዲገድሉ ስላልፈቀደላቸው ይህን ሲያመለክቱ ነው። በዚህም፡-

***18፥32 ኢየሱስ በምን ዓይነት ሞት ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።*** ጌታ ኢየሱስ እይሁድ እርሱን ከመያዛቸው በፊት የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ይላል ብሎ በምን ዓይነት ሞት እንደሚሞት አስቀድሞ ተናግሮ ነበረ (12:32)። በድንጋይ መወገር ሳይሆን በመስቀል እንደሚሞት ሲያመለክትም ነው። አይሁድ የሚገድሉት በድንጋይ በመውገር ነው። ሮማውያን ደግሞ ወንበዴን ወይም እመፀኛ የሚሉትን የሚገድሉት በስቅላት ነው። እይሁድ ኢየሱስን ለመግደል ብዙ ጊዜ የፈለጉ ቢሆንም ኢየሱስ ግን በተደጋጋሚ የተናገረው አሟሟቱ በስቅላት እንጂ በድንጋይ በመወገር እንደማይሆን ነበር (ማቴ 20፥19)። በኋላ ላይ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው ገደሉት (ሐዋ 7:58)። ቢሆንላቸው ኖሮ ኢየሱስንም እንደ እስጢፋኖስ በድንጋይ በወገሩት ነበር።

የኢየሱስ ክርስቶስ አሟሟት በድንጋይ በመወገር ሳይሆን በመስቀል ላይ በመስቀል መሆን ነበረበት። ይህም ስለ ብዙ ምክንያቶች ነው።

- በመጻሕፍት ከአጥንቱ አንዳች አይሰበርም የሚለው (መዝ 34:20) ይፈጸም ዘንድ ነው። በመወገር አጥንት ይሰበራል (ዘጸ 12፥46) መወጋትም ባልኖረ (ዘካ 12፡10)።
- አይሁድ በድንጋይ ቢወግሩት ስለ እርሱ መሞት ተጠያቂዎቹ አይሁድ ብቻ በሆኑ ነበር። በመስቀል ላይ በመሞቱ ግን ተጠያቂው የሰው ዘር ሁሉ ነው። አይሁድ እንዲሞት ስለጠየቁ፤ ሮማውያን (አሕዛብ) በእጃቸው ስለ ሰቀሉት። ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት አይሁድም አሕዛብም በአጠቃላይ ዓለም ሁሉ ተጠያቂ ነው (ሐዋ 2፡23፤ 4፡27)።
- የመስቀል ሞት ርግማን ያለበት ሰው እንዲሞት የታዘዘበትን ዓይነት አሟሟት ይገልጣል (ዘዳ 21፡23፤ ገላ 3፡13)። የእግዚአብሔርን ቁጣ ማስትም መርገም ያለበት ሰው የሚሞተው በስቅላት ነው። በመስቀል ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን መርገም (ኃጢአት) ተሸከመ።

***18፥33 ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን ጠርቶ:- የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? አለው።*** አይሁድ ኢየሱስን የከሰሱት ራሱን ንጉሥ ነኝ ይላል በማለት ነበር (ሉቃ 23፡1-2)። ጲላጦስ ይህን የጠየቀው ለማረጋገጥ ነው።



***18፥34 ኢየሱስም መልሶ:- አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህን? አለው።*** ለዚህ ለኢየሱስ ጥያቄ ጲላጦስ የሰጠው መልስ እርሱ ከኢየሱስ ወገን እስመሆኑን በመግለጽ:- ***እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ፤ ምን አድርገሃል? 18፥35*** በማለት ነው።

ኢየሱስም:- ***መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው 18፥36፡*** በዚህ ዓለም ያሉ ነገሥታት ሎሌዎች (ወይም ወታደሮች) አሏቸው። ንጉሣቸው ሲያዝ መከላከላቸው የማይቀር ነው። ኢየሱስ ግን «ማንን ትፈልጋላችሁ?»፤ «እኔ ነኝ» ብሎ ራሱን አቀረበ፤ ጴጥሮስንም ሰይፍህን ወደ ስገባው ክተተው ብሎታል። ስለሆነም የእርሱ መንግሥት የዚህ ዓለም ባሕርይ የሌለው የእግዚእብሔር መንግሥት እንደሆነ ያስረዳናል።

***18፥37 እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው።*** ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ንጉሥነት እውነቱን በከፊል ተረድቷል። ያልተረዳው ትልቅ እውነት ግን አለ። ይህም መንግሥቱ የዚህ ዓለም እንዳይደለ ጲላጦስ አሁንም አልተረዳም። ጌታም ለጥያቄው ***እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ትላለህ 18፥37***[80] ብሎ መለሰለት።

***18፥37 እኔ ለእውነት ልመሰክር ለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤*** በማለት ተልእኮውን ይገልጻል። ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ስለ እውነት እንዲመሰክር በአብ የተላከ ነው። የመልእክተኛ ውን ድምጽ የሚሰማ እውነትን የሚወድ ሰው ነው። ከእውነት ወገን የሆነ እውነት የሆነውን ኢየሱስን ይሰማል።

***18፥38 ጲላጦስ:- እውነት ምንድር ነው? አለው።*** አብዛኛውን ጊዜ እንደ ጲላጦስ ላለ ሰው እውነት አብዛኛው ሰው የተቀበለው ሀሳብ ነው።[81] እውነት ጊዜውን መምሰል፣ ወይም እንደ ሁኔታው ተመሳስሎ

---

[80] በአዲስ መደበኛ ትርጉም:- ጲላጦስም፤ «ታዲያ ንጉሥ ነህ ማለት ነዋ!» አለው። ኢየሱስም፤ እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ መናገርህ ትክክል ነው፤ የተወለድሁት፤ ወደዚህም ዓለም የመጣሁት ስለ እውነት ለመመስከር ነው፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ይሰማኛል» አለው።

[81] Pilate was cynical; he thought that all truth was relative - it could be whatever Rome wanted it to be. To many government officials, truth was whatever the majority of people agreed with or whatever helped

መኖር ማለት አይደለም። ሐሰት ጨለማ እንደ ሆነ ሁሉ እውነት ደግሞ ብርሃን ነው። ብርሃን ከጨለማ የተለየ እንደሆነ እውነትም እንዲሁ ከሐሰት የተለየ ነው። ስለሆነም እውነት ጊዜውን መስሎ ማደር ወይም አብዛኛው ሰው የደገፈውን ደግፎ መኖር ማለት አይደለም። እውነት መለኪያ አለው። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት የእውነት መለኪያው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም የመጣው ይህንን እውነት ለመመስከር፣ ለማስተዋወቅ ነው።

***18÷38 ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ:- እኔስ እንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም:-*** አለ። ከዚህ በመቀጠል ጲላጦስ እንዲል የሚጠበቅበት ስለዚህ ፈትቼዋለሁ ነበር። የተቀመጠው በፍርድ ወንበር ላይ ነው። አይሁድ ያመጡት እንዲፈርድበት ነው። መርምሮ በራሱ ቃል ***እንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም*** ብሏልና በደል የሌለበት ሰው ነፃ መስቀቅ አለበት።

***18÷39 እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን?*** አላቸው። ጲላጦስ ፍርድ ወንበር ላይ ሆኖ ምን ማድረግ እንደሚገባው ሕዝቡ እንዲነግረው በመጠየቅ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ያሰበ ፈራጅ ነው። ጲላጦስ ግን ከተጠያቂነት አያመልጥም። በእርሱ ፍርድ ወንበር ፊት የቀረበውንና ምንም በደል ያልተገኘበትን ሰው ነፃ ሊያወጣው ሥልጣን እያለው ሥልጣኑን በአግባቡ አልተጠቀመምና ተጠያቂ ይሆናል።

ሄሮድስ መልሶ ወደ ጲላጦስ ላከው እንጂ ጌታ ከገሊላ ስለሆነ በዚያን ዘመን የገሊላ ገዥ የነበረው ሄሮድስ እንዲዳኝለት ጲላጦስ ወደ እርሱም ልኮት ነበር (ሉቃ 23፡6-7)። ጲላጦስ ኅሊናው የሚነግረውንና የሚያምንበትን ነገር ለማድረግ የማይደፍር ባለ ሥልጣን ነው። ስለሆነም የሚሰጠው ውሳኔ ሕዝቡን ደስ በማሰኘት ራሱን በወንበር ከማቆየት አንጻር የሚያደርገው ነበር። የጲላጦስን ከኃላፊነት የመሸሽ ባሕርዩን ባደረገው ቢያንስ አራት ተግባሮች እንመለከታለን።

- አንደኛ:- ወደ እርሱ ያመጡትን ኢየሱስን ***እናንተ ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት 18÷31*** በማለቱ።
- ሁለተኛ:- ***እንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና በበዓል ለማደርገው ልማድ እርሱን ልፍታላችሁን? 18÷39-40*** ብሎ መጠየቁ።
- ሦስተኛ:- ኢየሱስ እንዲገረፍ በማዘዙ 19÷1-3።ይህም ኢየሱስን በማስገረፍ አይሁድን ደስ ያሰኝ መስሎት ነው።
- አራተኛ:- ***ንጉሣችሁን ልሰቀለውን? 19÷15*** ብሎ ሲጠይቅ ውሳኔውን ሕዝቡ እንዲወስንለት መፈለጉ፤

በአራቱም ሁኔታዎች ጲላጦስ የነበረውን የቦታ ሥልጣን ተጠቅሞ ኢየሱስ ነፃ ነው ብሎ ሊፈርድ ይችል ነበር። ኢየሱስን ***እንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም*** ባለው መሠረት ነፃ ለቅቄዋለሁ ቢል አይሁድ ይቃወሙታል፤ ሁከትም ሊቀሰቀስ ይችላል፤ እንዲያም ሊል ከሥልጣኑ ይወርድ ይሆናል። ከዚያም አልፎ የሮም ገዥዎችም ሊፈርዱበት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ትክክል የሆነውን ቢያደርግ ኖሮ ከእውነት ጋር ቆመ ይባል ነበር። ጲላጦስ ግን እውነትን ያልወደደ፣ ከእውነትም ጋር ለመቆም ያልደፈረ ባለሥልጣን ነው።

በማቴ 27÷19 ላይ እንደምናየው የጲላጦስ ሚስት «በዚህ ጻድቅ ሰው ላይ አንዳች ነገር አታድርግ» ብላ በሕልምዋ የተቀበለችውን መከራ በመግለጽ ወደ እርሱ መልእክትም ልካ ነበር። በወስጡ በደል እንደሌለበት ራሱም መርምሮ ደርሶበታል። ይህም ሁሉ ቢሆን የሚያምንበትን ነገር ለማድረግ አልደፈረም። ብዙ ጊዜ እውነትን እየሸፈነ የኖረ ሰው አንድ ጊዜ በሐሰት መጠመዱ አይቀርም። እውነትን እያወቀ እውነትን የረገጠ ሰው ነው።

ዛሬም ቢሆን በማናቸውም ኃላፊነት ያሉ ሰዎች (ክርስቲያኖችም ሆኑ ሌሎች) የሰውን አፍ ወይም ተቃውሞ በመፍራት እውነት የሆነውን እያወቁ በተቃራኒው የሚወስኑ ሰዎች ከጲላጦስ ስህተት መማር ይገባቸዋል። ወሳኝ ምርጫዎች በመጡ ጊዜ ለጊዜው ቀላሉ ምርጫ የሚሆነው አብዛኛው ሰው የደገፈውን ደግፎ (ወስኖ) ማለፍ ነው። ይሁን እንጂ ቅዱሱ መጽሐፍ «በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው» (ያዕ 4÷17) እንደሚል እውነት የሆነውን እያወቀ የማያደርገው ሰው ኃጢአተኛ ነው።

***18÷40 ሁሉም ደግመው:- በርባንን እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ። በርባን ግን ወንበዴ ነበረ።*** የካህናት አለቆች ጻድቁን ጠልተው

---

advance their own personal power and political goals. When there is no basis for truth, there is no basis for moral right and wrong. Justice becomes whatever works or whatever helps those in power. Ibid. p.367.

የወንበዴና የነፍስ ገዳይ ወዳጅ የሆኑበት ዘመን ነው። በርባን በሮም ላይ ያመፀ፤ ነፍስ የገደለ ነበረ (ማር 15÷7)።

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተደረገው ፍርድ ሂደት የወሰደው ጊዜ ከ24 ሰዓት ያነሰ ሆኖ ስድስት ደረጃዎች ነበሩት። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ በአይሁድ ባለ ሥልጣኖች ፊት፣ ሌሎቹ ሦስቱ ደግሞ በሮም ባለ ሥልጣኖች ፊት ነበሩ።

1. በሐና ፊት (ዮሐ 18÷12-24)። ሐና በአይሁድ ዘንድ ሊቀ ካህናት ተደርጐ ስለሚቆጠር መጀመሪያ ወደ እርሱ አቀረቡት።
2. በቀያፋ ፊት (ዮሐ 18:24-28፤ ማቴ 26÷56-68)።
3. በካህናት አለቆችና አይሁድ ሽማግሌዎች ፊት (ማቴ 27÷1-2)።
4. በጲላጦስ ፊት (ዮሐ 18:28-፤ ሉቃ 23÷1-5)።
5. በሄሮድስ ፊት (ሉቃ 23÷6-12)።
6. በመጨረሻም በጲላጦስ (ጴንጤናዊው) ፊት (ዮሐ 19:13-16፤ ሉቃ 23÷13-25)።



# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

ጲላጦስ «ሙሉ ሥልጣን» እንዳለው ያስባል፤ ምክንያቱም ኢየሱስን *ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? 19÷10* ይለዋልና። የሚደንቀው ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመረመረው በኋላ በአደባባይ በተደጋጋሚ የሚመሰክረው:-

- *እኔስ አንዳች በደል ስንኳ አላገኘሁበትም 18÷38፤*
- *እነሆ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ 19÷4፤*
- *እኔስ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት 19÷6፤* በማለት ነው።

ታዲያ ጲላጦስ አንዳች በደል ካላገኘበት ለምን አይፈታውም? እንዲያውም:-

*19÷1 በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው።* ጲላጦስ ኢየሱስን የገረፈው አይሁድን ደስ ለማሰኘት ፈልጐ ነው። ሊፈታውም ደግሞ ያስብ ነበር (ሉቃ 23÷16)። በዚያን ጊዜ የነበረው መግረፊያ ጅራፍ በወንበዴዎች ላይ ከፍተኛውን የማቁስልና የመጉዳት ደረጃ እንዲያደርስ ተደርጎ ይዘጋጅ ነበር። ይህም ጅራፉ ከቆዳ የሚሠራ ጠፍር ሆኖ በጫፉ ላይ ደግሞ ብረታ ብረት ይቋጠርበት ነበር። ጌታ የተገረፈው እንዲህ በመሰለ ጅራፍ ነው።

*19÷2 ወታደሮቹም ከእሾህ አክሊል ጐንጉነው በራሱ ላይ አኖሩ ቀይ ልብስም አለበሱት።* ከካህናት አለቆች ጀምሮ ጲላጦስና ወታደሮቹ ሁሉ በኢየሱስ ላይ ያላፌዘና ያልተሳለቀ አልነበረም። ኢየሱስ የመጣው ሁሉንም ሰው (ወታደር፣ ካህን፣ ንጉሥ፤ ሌላም) ለማዳን ነው። ሁሉም ተሳለቁበት። ወታደሮቹ የተሳለቁበት ንጉሥ የሚለብሰው ዓይነት ቀይ ልብስ በማልበስ[82] ነበር።

*19÷3 እየቀረቡም:- የአይሁድ ንጉሥ ሆይ÷ ሰላም ለአንተ ይሁን ይሉት ነበር፤ በጥፊም ይመቱት ነበር።* እስቲ እንዲያው ሰላምታና ጥፊ እንዴት አብሮ ይሄዳል? ንጉሥነትና መመታት እንዴት

[82] Purple was the color of royalty.

ይዛመዳል? ይህ ሁሉ የመሳሰቃቸውን መጠን ያሳያል:: በኢሳ 50÷6 ላይ እንደምናየው «ጀርባዬን ስገራፊዎች፤ ጉንጬንም ስጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ÷ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመሰስሁም» እንዳለ ኢየሱስ ክርስቶስ በጥፊ በመቱት ጊዜ ፊቱን አላዞረም:: ወታደሮቹ እንደተፉበትም በማቴ 14÷30፤ ማር 15÷19 ተጽፏል::

*19÷4 ጲላጦስም ደግሞ ወደ ውጭ ወጥቶ:- እነሆ÷ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ አላቸው::* ኢየሱስ ክርስቶስ አንዲት በደል ስንኳ እንደሌሰበት በ18÷38ም ላይ ተናግሯል:: አሁን በድጋሚ ያንኑ ይገልጸል::

*19÷5-6 ኢየሱስም የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ:: ጲላጦስ:- እነሆ ሰውዬው አላቸው::* ጲላጦስ እነሆ ሰውዬው ብሎ ያቀረበው ሰው በጥፊ የተመታ፤ በራሱ ላይ የእሾህ አክሊል ያደረገ፤ የደከመ ነበር:: ይህ ሁሉ ግን በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ (ኢሳ 52÷14-15) ሆነ::

*እነሆ ሰውዬው* የሚሰው አባባል የፌዝ ንግግር ነው:: እንዲህ የደከመን ሰው ምን ያስፈራችኋል፤ እንዲህ የተጎሳቆሰን ሰው ንጉሥ ይሆናል ብሎ ማን ያስባል? እንደማለት ነው:: እንደዚህም ሆኖ:-

*19÷6 የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ባዩትም ጊዜ:- ስቀለው ስቀለው እያሉ ጮኹ:* በእንጨት (በመስቀል) ላይ የሚሰቀል የተረገመ (ወንበዴና አመፀኛ) መሆኑን አይሁድ ያውቃሉ (ዘዳ 21:23፤ ገላ 3:13):: ስለዚህ *ስቀለው ስቀለው* ሲሉ ጥያቄያቸው ኢየሱስ እንዲገደል ብቻ ሳይሆን የተዋረደ ሞት እንዲሞት ማስታቸው ነው:: ጲላጦስ:- *እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት አላቸው 19÷6::* ጲላጦስ ለሦስተኛ ጊዜ በኢየሱስ ላይ ምንም በደል እንዳላገኘበት በአንደበቱ ይመሰክራል::

*19÷7 እኛ ሕግ አለን÷ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል÷ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና አሉት::* በዘሌ 24÷16 መሠረት «ማንም የእግዚአብሔርን ስም የሰደበ ይገደል» የሚሰውን ሕግ መጥቀሳቸው ይሆናል:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መናገሩ አንደ እነርሱ ሀሳብ ስድብ መስሏቸው ነው::

*19÷8-9 ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ፈራ፤ ተመልሶም ወደ ገዥ ግቢ ገባና ኢየሱስን:- አንተ ከወዴት ነህ? አለው:: ኢየሱስ ግን አንዲት ስንኳ አልመለሰለትም::* የጲላጦስ ፍርሃት ምንድን ነው? ጲላጦስን ያስፈራው ምናልባት አይሁድ በአንድ ላይ ሊሞት ይገባዋል የሚል ጥያቄ ስላቀረቡ ሊሆን ይችላል:: ብቻው መቆሙ አስደንግጦት ይሆናል:: ጌታንም *አንተ ወዴት ነህ?* ብሎ ሲጠይቀው ጌታ ምንም አልመለሰለትም፤ በኢሳ 53÷7 አፉን አልከፈተም ያሰው ይፈጸም ዘንድ::



*19÷10 ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው::* ጲላጦስ ሊፈታው ሥልጣን እንዳለው እየተናገረና አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም እያለ አልፈታውም:: ወንበሩ የሚሰጠው ሥልጣን አለ:: ልቡ ደግሞ በፍርሃት ተውጧል:: ስለዚህ ለመፍታት ሥልጣን እያሰው ከልቡ ፍርሃት የተነሣ ሊፈታው አልቻሰም::

ጌታ የሚመልስለት:- *ከላይ ካልተሰጠህ በስተቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም 19÷11* በማለት ነው:: ኢየሱስ በንጉሡ ፊትም ቆሞ የሚናገረው ሥልጣን የሚሰጠው *ከላይ* መሆኑን ነው:: ጲላጦስ በኢየሱስ ላይ ሥልጣን የሰውም:: ጲላጦስ ምድራዊ ነው:: ኢየሱስ ከሰማይ የመጣ ነው:: ከላይ የሚመጣ ከሁሉ በላይ ነው (3:31):: ጲላጦስ አሁን ሊወስን ተዘጋጅቷል፤ ይህ ግን ከላይ ስለ ተፈቀደ ብቻ ነው:: ኢየሱስ በሰዎች እጅ አልፎ እንዲሰጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው::

*19÷11 ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው::* ኢየሱስን ለጲላጦስ አሳልፎ የሰጠው ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ነው:: ጲላጦስ በኢየሱስ ላይ የሚፈርድበት አስቀድሞ ከሳሾች ወደ እርሱ ስላቀረቡትና በደለኛ ነው ስላሉ ነው:: ቀያፋ አይሁዳዊ እንዲሁም የእግዚአብሔር ሕግ የተሰጠው ሕዝብ ሊቀ ካህናት ሆኖ እያለ ወደ ሕዝቡ የመጣውን መሲሕ ሊቀበሰው ሲገባ አሳልፎ መስጠቱ የበሰጠ በደለኛ ያደርገዋል:: ጲላጦስም አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም እያለ በተደጋጋሚ ራሱ እየተናገረ በኢየሱስ ላይ በመፍረዱ በደለኛ ነው:: ፍርድ አለበት:: ለእርሱ አሳልፎ የሰጠው ግን የበለጠ ፍርድ አለበት ማለት ነው::

*19÷12 ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ:-* ጲላጦስ በራሱ የምርመራ መንገድ በደረሰበት ውጤት መሠረት ኢየሱስ በደል ስለ ሌለበት ሊፈታው ፈለገ:: አይሁድ ግን በጲላጦስ ደካማ ጐን ገቡ::

*19÷12 ይህን ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው እያሉ ጮኹ::* አይሁድ ለጲላጦስ እየነገሩት ያሉት እነርሱ ለሮም ንጉሥ ለቄሣር ታማኞች

መሆናቸውንና ኢየሱስ ግን ንጉሥ ነኝ በማለቱ የቄሣር ተቃዋሚ እንደሆነ ነው። የራሳቸውን ንጉሥ፡- ንጉሥ አይደለም ብለው ሲክዱና ለሌላ ንጉሥ ታማኝነታቸውን ሲገልጹ አቤት አለማስተዋል!

***19፥13 ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው፥ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለ ጸፍጸፍ በሚሉት ስፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ።***[83] ጲላጦስ እስካሁን በተደጋጋሚ ኢየሱስን ሲመረምረው ቆይቷል። አሁን ደግሞ ***በፍርድ ወንበር*** ላይ መቀመጡ የሚያመለክተው የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት እንደ ተዘጋጀ ነው። ***በፍርድ ወንበር*** ላይ ተቀምጦ እርሱ በሚወስነው ሁሉ ተጠያቂ ይሆናል።

***19፥14 ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም፡- እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው።*** ለፋሲካ የማዘጋጃ ቀን ሲል ፋሲካ ለአንድ ሳምንት ሙሉ ስለሚከበር የመዘጋጀቱ ቀን አርብ ነበር ማለት ነው። ቀደም ሲል ***እነሆ ሰውዬው 19፥5*** በማለት ኢየሱስን ለሕዝቡ አውጥቶት ነበር። አሁን ደግሞ ***እነሆ ንጉሣችሁ*** ይላል። በሁለቱም ጊዜ የፌዝ ንግግር ይናገራል።

***19፥15 አስወግደው፥ አስወግደው፥ ስቀለው እያሉ ጮኹ።*** ከእውነት ጋር ያልቆመና በጊዜው ነፋስ የሚነዳ ሰው ሁልጊዜ አብዛኛው ሰው የሚያደርገውን ተከትሎ መንጎድ ነው። አይሁድ ከጥቂት ጊዜ በፊት ኢየሱስን በማክበር ጩኸት አሰምተው ነበር። «ሆሳዕና በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው እያሉ ጮኹ» (12፥13)። ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሕዝቡ ሁሉ ሲያየው የፈለገውና የተባረከ ነው እያሉ የጮኹለት ኢየሱስ አሁን ደግሞ ስቀለው የሚሉት ያው ኢየሱስ ነው። <u>የተባረከ ነው ባሉበት አንደበታቸው ወንበዴ ነው ስቀለው አሉ</u>። እግዚአብሔርን ባመሰገኑበት አንደበት የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ሆነው ጮኹ። አይ ሥጋ ለባሽ!!

ጲላጦስም ከጎርፉ ጋር በመጉረፍ፡- ***ንጉሣችሁን ልሰቀለውን? አላቸው 19፥15*****፡** ወሳኔውን ለእነርሱ ተወላቸው። በፍርድ ወንበር የተቀመጠ ግን እርሱ ነበር።

[83] በአዲስ መደበኛ ትርጉም ጲላጦስም ይህን ሲሰማ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው፥ የድንጋይ ንጣፍ በተባለ በአረማይክ ቋንቋ ገበታ ብለው በሚጠሩት ስፍራ በፍርድ ወንበር ላይ ተቀመጠ ይላል። የድንጋይ ንጣፍ የሚለውን እንግሊዝኛው stone pavement ይለዋል።



***19:15 የካህናት አለቆችም ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት።*** ሌላ ንጉሥማ አላቸው። ንጉሣቸው እግዚአብሔር አይደለምን? (መሳ 8፥23፤ 1ሳሙ 8፥7)። እንዲሁስ የሚመጣው መሲሕ ንጉሥ አይደለምን? የእግዚአብሔርስ ሕዝብ ተብለው ሲጠሩ ንጉሥ አላቸው አይደለምን? የንጉሥ ካህናት መባላቸው (ዘጸ 19፥5) ንጉሥ እንዳላቸው አያመለክትምን? ይህን ሁሉ በመቃወም ***ንጉሥ የለንም*** አሉ።

***19፥16 ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።*** ጲላጦስ ለካህናት አለቆች ሀሳብ ተንበረከከ።
***19፥17 ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚለት ወጣ።***[84] ኢየሱስ አሁን በምድር ላይ የሚያደርገውን የመጨረሻ ጉዞ እየተጓዘ ነው። የመጨረሻውም ጉዞው የሚሰቀልበትን መስቀል ተሸክሞ መሄድ ነው። ኢየሱስ መስቀል ላይ እንደሚሞት ያውቅ ነበረ (18፥37)። በመስቀል ከመስቀል ጋር የተያያዘውን ስድብ፤ ንቀትና ውርደት ሁሉ ተቀብሏል።

***19፥18 በዚያም ሰቀሉት፥ ከእርሱም ጋር ሁለት፥ አንዱም በዚህ አንዱም በዚያ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉ።*** ከኢየሱስ መስቀል ***አንዱም በዚህ አንዱም በዚያ*** የተሰቀሉት በራሳቸው በደል ነው። አመፀኞች ነበሩ (ማቴ 28፥37፤ ማር 15፥27፤ ሉቃ 23፥12)። በመካከላቸው ያለው ኢየሱስ የተሰቀለው ግን ስለ ዓለም ኃጢአት ነው። በዚህም «ከአመፀኞች ጋር ተቆጠረ» (ኢሳ 53፥12) የሚለው ትንቢት ተፈጸመ።

ልብ እንበል መስቀል የሆነ ሁሉ የኢየሱስን መስቀል አያመለክትም። በዚያ ቀን ከተሰቀሉት ሦስት ሰዎች የኢየሱስ የሆነው መካከለኛው ብቻ ነው። ኢየሱስ የሰውን ኃጢአት ያስወገደው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ከተሰቀለበት መስቀል ሌላ ትምክህት እንደ ሌለው (ገላ 6:14) እንደሚናገር።

***19፥19 ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም፡- የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበረ።*** ጲላጦስ ቢያውቀውም ባያውቀውም የጻፈው ግን ትክክል ነው። ***ስለዚህ የአይሁድ የካህናት አለቆች ጲላጦስን፡- እርሱ፡- የአይሁድ ንጉሥ ነኝ እንዳለ እንጂ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትጻፍ 19፥21።*** ብለውት ነበረ።

[84] በአዲስ መደበኛ ትርጉም እርሱም የራሱን መስቀል ተሸክሞ በአረማይክ ጎልጎታ ተብሎ ወደሚጠራው የራስ ቅል ወደባለው ቦታ ወጣ ይላል።

***19÷20 በዕብራይስጥና በሮማይስጥ በግሪክም ተጽፎ ነበረ::*** በዚያን ዘመን እነዚህ ሦስቱ ቋንቋዎች በከንዓን ጥቅም ላይ የዋሉ ነበሩ:: ዕብራይስጥ ወይም አረማይስጥ የአይሁድ ቋንቋ ነው፤ ሮማይስጥ ወይም ላቲን የሮማውያን ቋንቋ ነው:: ይህ በዚያን ዘመን ኦፊሴላዊ ቋንቋ ነበረ:: እንዲሁም ግሪክ ያን ዘመን ሁሉም ሰው የሚናገረው ቋንቋ ነበረ::[85]በመስቀል የሚሞት የተነቀፈ ነው፤ ዘዳግ 21÷23::

***19÷22 ጲላጦስም:- የጻፍሁትን ጽፌአለሁ*** ብሎ ሲመልስ ለአይሁድ በፍርድ ሂደቱ ሁሉ የአይሁድን ሃሳብ ሲቀበል ነበር፤ እዚህኛው ላይ ብቻ ከእነርሱ ሃሳብ ሲለይ ይታያል::

***19÷23 ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት! እጀ ጠባቡን ደግሞ ወሰዱ::*** ልብሶቹን ወስደው መከፋፈላቸው በዚያን ዘመን የልብስ እጥረት (ችግር) እንደ ነበረ ያመለክታል:: ታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚሉት ስቅላቱን ለፈጸሙ ወታደሮች የሚሰጣቸው ክፍያ የተሰቀለውን ሰው ልብስ መውሰድ ነበረ[86]::

***19:24 እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ አልነበረም:: ስለዚህ እርስ በርሳቸው:- ለማን እንዲሆን በእርሱ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ::*** ልብሱን መከፋፈላቸው ቀደም ሲል በትንቢት የተነገረው (መዝ 22:18):- ***ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው 19÷24***:

***19÷25 በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ÷ የእናቱም እኅት÷ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም÷ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር::*** እነዚህን አራቱ ሴቶችና አራቱን ጭፍሮች ስንመለከት ሴቶቹ እዚያ የቆሙት በኢየሱስ ሞት ምክንያት በሀዘን ነው:: ጭፍሮቹ ደግሞ ልብሱን ለመከፋፈልና ዕጣ ለመጣጣል ነው:: በመስቀል ላይ ያለው ኢየሱስ ግን ለሁለቱም ወገን እኩል ሞቶላቸዋል:: የሁሉንም ኃጢአት ተሸክሞ በመስቀል ላይ ተሰቅሏል:: እነዚህ አራት ሴቶች እስከ መጨረሻ የተከተሉት ታማኞች ናቸው:: ከደቀ መዛሙርቱ የተለየ ታማኝነትን

[85] *The Lingua franca*

[86] Clothing was not a cheap commodity in those days as it is today. Thus this was part of the <pay> the executioners received for performing their gruesome duties. Ibid. p.378



እናይባቸዋለን:: ደቀ መዛመርቱ ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ ጥለው ሸሽተዋል::

የጌታ እናት ማርያም በዚህን ጊዜ በእንዴት ዓይነት መራር ሀዘን ውስጥ እንደምትሆን መገመት ይቻላል:: ይህንን ከሰላሳ ዓመታት በፊት ስምዖን «አንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» (ሉቃ 2÷35) በማለት ትንቢት ተናግሮ ነበር:: በእርግጥም በዚህ ሰዓት ሰይፍ (ወይም መሪር ሀዘን) በውስጧ እያለፈ ነው::

***19÷26 ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ:-*** ጌታን የተከተሉት ብዙዎች ነበሩ፤ እስከ መስቀል ድረስ ከደቀ መዛሙርቱ የተከተለው ግን አንድ ብቻ ነው:: እርሱም ***ይወደው የነበረው*** ደቀ መዝሙር (ዮሐንስ) ነው::
***19÷26-27 እናቱን:- አንቺ ሴት÷ እነሆ ልጅሽ አላት:: ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን:- እናትህ እነኋት አለው:: ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት::*** ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከተናገራቸው ሰባት ነገሮች አንዱ ይህ ***አንቺ ሴት÷ እነሆ ልጅሽ*** የሚለው ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናቱ ይጠነቀቅ ነበረ:: በመስቀል ላይ በዚያ ጣር ውስጥ ሆኖ ***እናትህ እነኋት*** በማለት ከተናገረው ኃላፊነትና አደራን መወጣትና ማስተላለፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነም እናስተውላለን::[87] ከዚህ እኛም ለወላጆቻችን (በእድሜ ለገፉትም) መጠንቀቅ እንዳለብን ያስተምረናል::

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተናገራቸው ሰባት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው:-

1. የሚፈርዱበትንና የሚሰድቡትን/የሰቀሉትን:- «የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው» (ሉቃ 23÷24)::
2. ከእርሱ ጋር ለተሰቀለው ወንበዴ «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» (ሉቃ 13÷23)::
3. ዮሐንስ እናቱን እናቱን ማርያምን እንዲወስዳት (እንዲጠነቀቅላት) ***አንቺ ሴት÷ እነሆ ልጅሽ አላት ... ደቀ መዝሙሩን:- እናትህ እነኋት አለው ዮሐ 19÷26-27::***
4. «አምላኬ አምላኬ ስለ ምን ተውኸኝ» «ማቴ 27÷46፤ ማር 15÷34)::
5. «ተጠማሁ» (ዮሐ 19÷28)::

[87] ደቀ መዛሙርቱን ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች እንዳያዝኑ ካዘዛቸው በኋላ ተመልሸ እመጣለሁ (14:18) ብሏቸዋል:: እናቱን ደግሞ ለሚወደው ደቀ መዝሙር አደራ ሰጠ::

6. «ተፈጸመ» (ዮሐ 19፥30)
7. «አባት ሆይ ነፍሴን ለአንተ እሰጣለሁ» (ሉቃ 23፥46)።

***19፥28 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደ ተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ፦ ተጠማሁ አለ።*** ዲያብሎስ በምድረ በዳ ሲፈትነው በአቋራጭ ሲያከብረውና ሲያነግሠው ፈልጐ ነበር (ማቴ 4:9)፤ አልሆነለትም። አይሁድም ሲያነግሡት ፈልገው ነበር (ዮሐ 6:15)፤ ያም መንገዱ አልነበረም። አሁን ግን ሁሉ *ተፈጸመ*። ኢየሱስ የመጣበት ዓላማ፤ የመጽሐፉ ቃል (መዝ 69፥21) የሚፈጸመው በመስቀል ላይ ሲሰቀል እንደሆነ ያውቃል።

በመስቀል ላይ የተሰቀለው ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ *ተጠማሁ* በማለቱ እንደማንኛውም ሰው የሚጠማ እንደሆነ ያሳያል።

***19፥29 በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት።***[88] ቀደም ሲል ከመስቀላቸው በፊት ከርቤ የተቀላቀለበት የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጥተውት ነበር (ማር 15፥23)። ያን የሰጡት የመስቀል ላይ ስቃዩንና ሕመሙን እንዲቀንስለት፣ እንዲያደነዝዝለት ብለው ሊሆን ይችላል። ጌታ ግን ሊወስደው አልፈቀደም። ምክንያቱም የኃጢአትን ዋጋ አውቆ ለመክፈል በመስቀል ሞት የሚመጣበትን ሥቃይ ሁሉ በሙሉ ለመቀበል ሲል መሆን አለበት።

***19፥30 ተፈጸመ አለ፥*** በግሪክ ቴትለስታ[89] ሲሆን፤ ይህም ሙሉ ሆነ፣ በሙላት ተከፈለ እንደማለት ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የመዳንን መንገድ ፈጸመው። ዋጋውን በሙሉ ከፈለ። እንዲሁም የብሉይ ኪዳንን ትንቢት ሁሉ ወደ ፍጻሜ አመጣው (4፥34፤ 17፥4)።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ኃጢአት የሚሰረየው ከእንስሳት ወገን በሚቀርብ መሥዋዕት አማካይነት ነበር። ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ይለያልና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅና ኅብረት ለማድረግ መሥዋዕት ይቀርብ ነበር። ይህ በብሉይ ኪዳን ያደረግ የነበረው

---

[88] A jar full of sour wine was standing there. So they put a sponge full of the wine on a branch of hyssop and held it to his mouth. NRSV. በአዲሱ መደበኛ ትርጉም፦ በዚያም የሆመጠጠ ወይን የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሰፍነግ በወይን ጠጅ ነክረው በሂሶፕ ዘንግ ወደ አፉ አቀረቡለት ይላል።

[89] *tetelestai*



መሥዋዕት እግዚአብሔር ያዘጋጀው «በግ» እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ በእምነት የሚቀርብ ነበር። አሁን «የእግዚአብሔር በግ» (1:29) የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቷል። ኢየሱስ የኃጢአት የመጨረሻውንና ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት አቀረበ። እርሱም በሞቱ የዓለምን ኃጢአት ሁሉ በእርሱ ላይ ተሸከመ።

***19፥30 ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።*** ነፍሱን አሳልፎ መስጠቱ እርሱ በፈቃዱ ያደረገው ተግባር ነው። ***አሳልፎ ሰጠ*** የሚለው ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲውል ሞተ ከማለት በላይ ነው። በሉቃ 23፥46 «ነፍሴን ለአንተ እሰጣለሁ» የሚለውንና በመዝ 31፥5 «በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ» ያለውን ያሳስባል። ስለዚህ የኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስ ከእርሱ አልተወሰደችበትም። እርሱ ነፍሱን በፈቃዱ ሰጠ እንጂ (10፥11፤15፤17-18፤ 15፥13 ይመልከቱ)። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ በሁሉም ሰው (ነፍስ) ላይ በራሱም ነፍስ ላይ ያለውን የበላይነት፣ ልዑልነት ያሳያል። ነፍሱን አሳልፎ መስጠት በእርሱ ፈቃድና ቁጥጥር ሥር ነበረ።

አይሁድ ብዙ ጊዜ ኢየሱስን ሊገድሉት ፈልገው ነበር። ጊዜው ደርሶ እርሱ ራሱ «እኔ ነኝ» (18:5) ብሎ ራሱን እስኪሰጥ ድረስ በእርሱ ላይ ማንም ምንም ሊያደርግ አልቻለም። በመጨረሻ ደግሞ «ተፈጸመ» ብሎ ነፍሱን ሰጠ። አስቀድሞም ነፍሱን እንደሚሰጥና እርሱም በትንሣኤ እንደሚያስነሣት በ10፥18 ላይ ተናግሮ ነበር።

***19፥31 ሥጋቸውም በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር፥ ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው፦*** ሰንበት የሚጀምረው በአርብ ዕለት ነው። ይህኛው ሰንበት ደግሞ ልዩ የሆነው ከፋሲካ ጋር አብሮ በመገናኘቱ ነው። አይሁድ በሰንበት እንዳይረከሱ (ዘዳ 21፥22-23) የተሰቀሉት ሰዎች ሥጋ በመስቀል ላይ ሆኖ እንዲቆይ አልፈለጉም። ስለዚህ በመስበር እንዲያወርዷቸው ጲላጦስን ጠየቁ። ***ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላኛውን ጭን ሰበሩ። ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም 19፥32-33።***

***19፥34 ነገር ግን ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ።*** ሰው ጎድኑን በጦር ሲወጋ ካልሞተ በስተቀር ደምና ውኃ ሳይቀላቀል ተለያይቶ አይታይም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ

*ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን* በጦር ሲወጋው ደምና ውኃ ከሰውነቱ መውጣቱ ፈጽሞ መሞቱን ያመለክታል::[90]

ጌታ በጦር ሲወጋ *ደምና ውኃ እንደ ወጣ* እዚያ የነበረው ደቀ መዝሙር ሲመሰክር:- *ያየውም መሰከሮአል! ምስክሩም እውነት ነው! እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል* ***19÷35*** አለ:: ጭፍሮችም ለጲላጦስ ሄደው የነገሩት በእርግጥ ኢየሱስ መሞቱን ነው (ማር 15÷44-45):: ለዚህም ነበር ከተሰቀለበት አውርደው እንዲቀብሩት የፈቀደው (19:38)::

***19÷36-37 ይህ የሆነ:- ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው:: ደግሞም ሌላው መጽሐፍ:- የወጉትን ያዩታል ይላል::*** ጌታ ፈጽሞ በመሞቱና እንደ ሌሎቹ ጭኑ ስላለመሰበሩ በዘጸ 12÷46 እና ዘኍ 9÷12 ላይ የፋሲካው በግ አጥንቱ እንዳይሰበር ከሚለው ጋር ይስማማል:: ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው መሥዋዕት ነውና:: እንዲሁም የወጉትን ያዩታል የሚለው በዘካ 12÷10 የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው (በተጨማሪ መዝ 34:20፤ ራእ 1÷7ን ይመልከቱ)::

***19÷38 አይሁድን ስለ ፈራ በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረ የአርማትያስ ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ሊወስድ ጲላጦስን ለመነ:-*** ጌታን በስውር ይከተሉ የነበሩ ሁለት ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ከሞተ በኋላ ማንነታቸውን እንደገለጡ ከቁ.38-40 ባለው ክፍል እንመለከታለን:: አንደኛው የአርማትያሱ ዮሴፍ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ኒቆዲሞስ ነው:: አይሁድን ስለ ፈሩ ራሳቸውን ሰውረው ነበረ:: በእውነት አማኝ የሆነ ሰው ራሱን ደብቆ መኖር የሚችለው ለአጭር (ለተወሰነ) ጊዜ ብቻ ነው:: እውነተኛ ማንነቱን የሚገልጥበት ጊዜና ሁኔታ መምጣቱ አይቀርም::

የአርማትያው ዮሴፍ ሀብታም ሰው ነበረ (ማቴ 27÷57)፤ የሸንጎ አባል ነበረ (ማር 15÷43)፤ በሸንጎአቸው ክፉ ምክር የማይተባበር ጻድቅ ሰው

---

[90] This piercing would make sure that Jesus was really dead. Medical experts have tried to determine what was punctured to create a flow of blood and water. Some think the pericardial sac was ruptured. John's testimony of this occurrence was important to affirm a major argument in the Gospel against the Docetists who were denying Jesus' humanity. Jesus was indeed a man composed of ***blood and water***. ... The piercing itself would have killed Jesus, but he was already dead as the separation of blood and water reveal. Ibid. p.381



ነበረ (ሉቃ 23÷50-51):: ይህ ሰው *የኢየሱስን ሥጋ ሊወስድ ጲላጦስን ለመነ ጲላጦስም ፈቀደለት:: ስለዚህም መጥቶ የኢየሱስን ሥጋ ወሰደ* ***19÷38::***

***19÷39 ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ::*** ኒቆዲሞስ ከፈሪሳውያን ወገን የሆነና አለቃ የነበረ ወደ ጌታ በሌሊት የመጣ ሰው ነው (3÷1-፤ 7÷50-52):: ኒቆዲሞስ ያመጣው ***የከርቤና የእሬት ቅልቅል*** ከሽቱ ጋር ተደርጎ የኢየሱስን ሥጋ ለመገነዝ እንዲሆን ነበር::

ዮሴፍና ኒቆዲሞስ:- ***የኢየሱስን ሥጋ ወስደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት 19÷40::*** ኢየሱስን በሕይወት እያለ በግልጽ ባይከተሉትም የጌታን ሥጋ ወስደው ለመከፈን እንዲህ ዓይነት የከበረ አገልግሎት ለማድረግ በሞቱ በአንድ ላይ የተገናኙ ደቀ መዛሙርት ናቸው:: አንድ ላይ እንዲህ ዓይነት የከበረን ሥራ ለመሥራት መቻላቸው በድብቅ የጌታ ተከታዮች መሆናቸውን እርስ በርሳቸው ቢተዋወቁ ይሆናል ማለት ይቻላል::

***19÷41 በተሰቀለበትም ስፍራ አትክልት ነበረ፥ በአትክልቱም ገና ማንም ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበረ::*** የአይሁድ የአቀባበር ሥርዓት ሥጋውን በሽቱና በተልባ እግር ልብስ አድርገው መከፈን (በሥርዓት መጠቅለል)ና መቅበር ነው:: ዮሴፍና ኒቆዲሞስም ያደረጉት ይህንኑ ነው:: ኒቆዲሞስ እጅግ በርካታ ከርቤና የእሬት ቅልቅል አመጣ፤ ዮሴፍ ደግሞ እርሱ ያሠራውን መቃብር ኢየሱስ እንዲቀበርበት ሰጠ (ማቴ 27÷60፤ ሉቃ 23÷53)::
***19÷42 ስለዚህ መቃብሩ ቅርብ ነበርና ስለ አይሁድ ማዘጋጀት ቀን ኢየሱስን በዚያ አኖሩት::*** ይህ ከድንጋይ ተጠርቦ የተሠራ መቃብር ዮሴፍ ያሠራው መቃብር ነው:: በዚህም ጌታ በኢሳይያስ በኩል «ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፤ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ፤ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፤ በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ነበር» (ኢሳ 53:9) የተባለው የትንቢት ቃል ተፈጸመ::

# ምዕራፍ ሃያ

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለፈባቸውን የፍርድ ሂደቶች፤ በመስቀል ላይ የደረሰበትን ሁሉ እና እስከ መቃብሩ ያለውን ያስረዳል:: የመጣበትን ዓላማ በመስቀል ላይ «ተፈጸመ» በማለት ጨረሰው:: ምዕራፍ ሃያ ደግሞ የሚጀምረው በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው::

የኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በሦስተኛው ቀን መነሣቱ ከመሞቱ በፊት የተናገረው ሁሉ እውነት እንደ ሆነ ማረጋገጫ ነው:: መነሣቱ በደቀ መዛሙርቱና በሌሎችም ታወቀ::

ሊቀ ካህናቱና አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ እንዳይነሣ በድንጋዩ ላይ ማኅተም አተሙበት (ማቴ 27:66)፤ ጠባቂም ወታደሮች አቆሙ (27:66):: እነዚህ ሁሉ «ኃያላን መጠበቂያዎች» ተጋግዘው እንዳይነሣ እንዲከለክሉት አስበው ነው:: ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ልጅ እንዳይነሣ የሚከለክለው የተፈጥሮ ኃይል፤ ሥልጣን ወይም የሰው ክምችት የለም:: እርሱ ከሁሉ በላይ ነው:: አምን፤ አሜን::

***20፥1 ከሳምንቱ በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች::*** መግደላዊት ማርያም ሰባት ጋኔን የወጣላት (ሉቃ 8፥1-3) እና ጌታን ይከተሉና ያገለግሉት ከነበሩት ሴቶች አንዷ ናት:: ብዙ ይቅር የተባለለት ብዙ ይወዳል (ሉቃ 7:47) እንደሚል በሚሰቀልበትም ቀን ሲሰቀል ከተመለከቱና (19፥25) የት እንደተቀበረም ለማየት ከቆዩት ሴቶች (ማቴ 27፥61) አንዷ መግደላዊት ማርያም ናት:: በማለዳ ወደ መቃብሩ ስትሄድ ሌሎችም ሴቶች አብረዋት ነበሩ (ማቴ 28፥1፤ ማር 16፥1)::

***20፥1 ድንጋዩም ከመቃብሩ ተንከባሎ አየች::*** እነዚህ ሴቶች የሄዱት «ድንጋዩን ማን ያንከባልልናል» (ማር 16፥3) እየተባባሉ ነበር:: ድንጋዩን ለማንከባለል እንደማይችሉ ያውቃሉ:: የድንጋዩ ትልቅነትና የሚያንከባልልላቸው ሰው አብሮአቸው አለመኖሩ ግን ከመሄድ አላገዳቸውም:: ወደ ስፍራው በደረሱ ጊዜ ግን ***ድንጋዩም ከመቃብሩ ተንከባሎ*** አገኙት::

***20፥2 እየሮጠችም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር መጥታ:- ጌታን ከመቃብር ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም አለቻቸው::*** እነ ማርያም ያዩት ሁኔታ አስደንጋጭ ነው:: የድንጋዩ መንከባለል ብቻ ሳይሆን ሥጋው በመቃብር ውስጥ አለመገኘቱ በጣም ስላስደነገጣት ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሄዳ ይህንኑ ገለጸችላቸው:: ወዴት እንዳኖሩትም ***አናውቅም*** ማለቷ ብቻዋን እንዳልነበረች (ሌሎችም አብረዋት) እንደ ነበሩ ያመለክታል:: ***ወስደውታል*** የሚለው አገላለጽ በዚያን ጊዜ የመቃብር (የሬሳ) ሌቦች እንደ ነበሩ አመልካች ነው:: ኢየሱስ እንደሚነሣ የተናገረውን (2:22፤ 20:9) ረስተዋል::

***20፥3 ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር ወጥተው ወደ መቃብር ሄዱ::*** በሰሙት ሪፖርት መሠረት ነገሩን ለማረጋገጥ ወደ መቃብሩ ሲሄዱ:- ***ሌላው ደቀ መዝሙርም ከጴጥሮስ ይልቅ ፈጥኖ ወደ ፊት ሮጠና አስቀድሞ ከመቃብሩ ደረሰ 20፥4::*** ምናልባት ይህ ደቀ መዝሙር ከጴጥሮስ ይልቅ በእድሜ ወጣት ሳይሆን አይቀርም:: ***ፈጥኖ ወደ ፊት*** መሮጡ ደግሞ የሰማውን አይቶ ለማረጋገጥ የነበረውን ታላቅ ጉጉትም ያመለክታል:: ይህ ደቀ መዝሙር ቀድሞ ወደ መቃብሩ ደርሶ ***ዝቅም ብሎ ሲመለከት የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ:: ነገር ግን አልገባም 19:5::*** ቀድሞ ወደ መቃብሩ የገባው ግን ስምዖን ጴጥሮስ ነበረ::

***20፥6-7 ጴጥሮስ ... ወደ መቃብሩም ገባ ... በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው በአንድ ስፍራ ተጠምጥሞ እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ::***[91] ማርያም እንዳሰበችው ጌታን ከመቃብር ወስደውት ቢሆን ኖሮ እንደተከፈነ ይዘውት ሊሄዱ በቻሉ ነበር:: ጥምጥሙና ልብሱ የተገኘው የጌታ ሥጋ በተኛበት (በተቀበረበት) ሁኔታ እንደዚያው ሆኖ ነበር:: ጌታ ሲነሣ ራሱ ላይ የተጠመጠመውን ጨርቅ በማውለቅ፤ ከፈኑንም ፈትቶ በመጠቅለል ሳይሆን ከተጠመጠመበትና ከተከፈነበት እንዳለ ወጥቷል ማለት ነው:: ስለዚህ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ኢየሱስን የከፈኑበት በራሱ ተጠምጥሞ የነበረው ጨርቅና የተልባ እግሩ ልብስ (19፥40) ሁለቱም በአንድ ላይ

[91] አዲሱ መደበኛ ትርጉም:- ስምዖን ጴጥሮስ ደረሰና ወደ መቃብሩ ገባ:: እርሱም ከተልባ እግር የተሠራውን ከፈን አየ:: እንዲሁም በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን ጨርቅ አየ:: ይህም ጨርቅ ከከፈኑ ተለይቶ እንደተጠቀለለ ነበረ ይላል::

ተሰብስቦ (ተጠቅልሎ) አልተቀመጠም። ስለዚህ በእነሳሡ ሁኔታ ላይ ሥርዓት እናያለን።

***20÷8 በዚያን ጊዜ አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣውም ሌላ ደቀ መዝሙር ደግሞ ገባ፤ አየም፥ አመነም።*** ይህ ደቀ መዝሙር ከፈኑና ጥምጥሙ በየቦታቸው መሆናቸውንና ባዶ መሆናቸውን ሲያይ ያን ጊዜ ኢየሱስ ከሙታን እንደ ተነሣ አይቶ አመነ። ደቀ መዛሙርት/ሐዋርያት ያዩትን የሚናገሩ የዓይን ምስክሮች ናቸው። ዮሐንስም ስለ እየውና ስለ ሰማው እንደሚመሰክር በመልእክቶቹም ላይ ጽፏል (1ዮሐ 1:1-2)። ስለዚህ ዮሐንስ ይህን መጽሐፍ የጻፈው ከአየው በመነሣት ሌሎች እንዲያምኑ ነው (20÷31)።

***20÷9 ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁም ነበርና።*** ዮሐንስ ያመነው ከአየው ተነስቶ ነው። መጽሐፍ ግን ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ይናገራል (1ዮሐ 1:1)። እርሱና ሌሎች ደቀ መዛሙርትም ይህን የመጽሐፍ ቃል ገና አላወቁትም፣ አላስተዋሉትም (መዝ 16÷10፤ ኢሳ 53÷11)።

***20÷10 ደቀ መዛሙርቱም ወደ ቤታቸው ደግሞ ሄዱ።*** ጴጥሮስና ዮሐንስ የጌታ ሥጋ በመቃብሩ እንደሌለ ካዩ በኋላ ወደ ቤታቸው ሄዱ። ተስፋ መቁረጥ? ዓሣ ወደ ማጥመድ ለመመለስ?

***20÷11 ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብሩ በውጭ ቆማ ነበር። ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች፡-*** ይህች ሴት ብዙ ጋኔን የወጣላትና ብዙ ምሕረት ያገኘች ስለሆነች (ሉቃ 8:13) ለጌታ ያላት አክብሮት ታላቅ ነው። ስለዚህ ሥጋው ከመቃብሩ ባለመገኘቱና የት እንደሄደ (እንደተወሰደ) ባለማወቋ ታለቅስ ነበር።

***20÷12-13 ሁለት መላእክትም ... አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ? አሉአት።*** እነዚህ መላእክት ሰውን የሚመስሉ ናቸው። ነጭ ልብስ ለብሰዋል። ተቀምጠው አየቻቸው። ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር ወደ መቃብር ውስጥ በገቡ ጊዜ አላዩአቸውምና ምናልባት ያን ጊዜ አልነበሩም? ወይም አልታዩአቸውም? ይሆናል። ለመላእክቱ ጥያቄ የማርያም መልስ፡- ***ጌታዬን ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም 20:13*** የሚል ነበር። ማርያም አሁንም ቢሆን የምትናገረው ***ወስደውታል*** እያለች ነው፤ ተነሥቷል የሚለውን ገና አልተገነዘበችም።

***20÷14 ይህን ብላ ወደ ኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን ቆሞ አየችው፤ ኢየሱስም እንደሆነ አላወቀችም።*** በኤማሁስ መንገድ ይሄዱ የነበሩት



ደቀ መዛሙርት አብሮአቸው የሚሄደው ኢየሱስ እንደ ነበረ አላወቁም ነበር (ሉቃ 24÷15-16)። ማርያምም የሚያነጋግራት ኢየሱስ መሆኑን አላወቀችም። እንዲህ ዓይነቱ አለማወቅ ወይም አለመለየት ከምን የሚመጣ ይሆን? ማርያም ለመለየት ያልቻለችው በዚያን ጊዜ ታለቅስ ስለነበረ ዓይኖቿ ውኃ/እንባ ሞልተው ይሆን? የኤማሁስ መንገደኞችስ? እንዳይለዩት ያደረጋቸው በምንም ሁኔታ እርሱ ሊሆን ይችላል ብለው ስላልጠረጠሩ ወይም ዓይኖቻቸው ተሸፍነው[92] ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ ማርያም የሚጠይቃት ***የአትክልት ጠባቂ መስሎአት፡- ጌታ ሆይ፥ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ 20÷15*** በማለት ትመልስለታለች። የኢየሱስ ሥጋ አልተወሰደም፤ ኢየሱስ ተነሥቶአል፤ ሕያው ነው። ***ኢየሱስም፡- ማርያም አላት። እርስዋ ዘወር ብላ በዕብራይስጥ፡- ረቡኒ አለችው 20:16።***

***20÷17 ኢየሱስም፡- ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፡- እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው አላት።*** ከሞት የተነሣበት አካል ወደ አባቱ የሚያርግበት አካል ነው። ይህ አካል ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት የነበረውን አካል ቅርጽ (ተክለ ሰውነት) ይዞ ነገር ግን የማይሞት፣ የማይበሰብስ፤ የከበረ፤ ሰማያዊ አካል ነው። በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ በትንሣኤ እንደ እርሱ የማይበሰብስ አካል ለብሰው ይነሣሉ (1ቆሮ 15:52-53)። ስለሆነም ወንድሞች ይላቸዋል።

ጌታ ከመሞቱ በፊት ደቀ መዛሙርትን ወዳጆቼ ብሏቸው ነበር (15÷15)። አሁን ደግሞ ከትንሣኤ በኋላ ***ወንድሞቼ*** ይላቸዋል (ማቴ 28÷10)። የመቀራረቡን ዕድገት (የመጠጋጋቱን ቅርበት) ያሳያል። በዕብ 2÷11-14 ባለው ክፍል «ወንድሞች ብሎ ሲጠራቸው አያፍርም» ይላል።

እዚህ ቁጥር ላይ የምናስተውለው ሌላ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ እንደሚሄድ ሲናገር ወደ አባታችን እና ወደ አምላካችን አላለም። ያለው ***ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ*** ነው። የእግዚአብሔር አባትነት ለኢየሱስና ለደቀ መዛሙርቱ ለየቅል ስለሆነ ከእነርሱ ጋር በአንድነት አባታችን አይለውም። የእግዚአብሔር አብ ለኢየሱስ ክርስቶስ አባትነት ከዘላለም ሲሆን የሚያመለክተውም በአባትና በልጅ መካከል ያለ ዘላለማዊ ተዛምዶን[93] ነው። በአንጻሩ በደቀ መዛሙርት እንዲሁም በአማኞችና በእግዚአብሔር አብ መካከል ያለው

[92] «ዓይኖቻቸው ተይዘው ነበር» (ሉቃ 24:16-17)
[93] Relationship

አባትና ልጅነት ደግሞ መነሻ (መጀመሪያ) ያሰውና ዳግመኛ በመወሰድ የሚገኝ ልጅነት ነው።

***ወደ አምላኬ*** ሲልም ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ «ኢየሱስ አምላኬ፥ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?» (መዝ 22:1፤ ማቴ 27:46) እንዳለው ፍጹም ሰው የሆነው ጌታ ኢየሱስ በሰውነቱ[94] እግዚአብሔር አምላኩ መሆኑን ያስገነዝባል። ከመጀመሪያ ከእርሱ ጋር የነበረው ቃል፤ ሥጋ እንዲለብስና ወደ ምድር እንዲመጣ በአብ የተላከ በመሆኑ እግዚአብሔር አምላኩ ነው። በመለኮትነቱ[95] እግዚአብሔር አባቱ ነው።

***20፥19 ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት፥ አይሁድን ስለ ፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፥ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው።*** ኢየሱስ ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ ይከተሉት ለነበሩ ራሱን ይገልጥላቸው ነበር። በተነሣበት ቀን ለሴቶቹ (ማቴ 28፥8-10)፤ ለጴጥሮስ (ሉቃ 24፥34)፤ በኤማሁስ መንገድ ይጓዙ ለነበሩ ለሁለቱ (ማር 16፥12-13፤ ሉቃ 24፥13-35) ተገለጠ። ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተሰበሰቡበት ሄዶ ራሱን ገለጠ።

በዚያ ምሽት ኢየሱስ እንደተነሣ ያረጋገጡ፣ ያመኑ ደቀ መዛሙርት ቢኖሩም ከፍርሃታቸው ግን ገና አልተላቀቁምና በራቸውን ዘግተው ተሰብስበው ነበር። በማቴ 28፥7 እንደምናየው ወደ ገሊላ እንዲቀድሙትና እዚያ እንዲያገኛቸው ለደቀ መዛሙርቱ መልእክት ልኮባቸው ነበር። በዚያ ቀን ግን ወደ ገሊሳ አልሄዱም። አሁንም ያሉት ከአይሁድ አለቆች ተደብቀው በኢየሩሳሌም ነበሩ።

ጌታ በመካከላቸው የተገኘው ***ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ*** ነው። በዚህም የምናየው የጌታን ሁሉን ቻይነት ብቻ ሳይሆን የትንሣኤውን አካል የተዘጉ ደጆች እንደማይከለክሉትም ነው።

***ሰላም ለእናንተ ይሁን*** ሲላቸው በተለይ ለነበሩበት ሁኔታ ታላቅ ትርጉም ነበረው። ቀደም ብሎም በ14፥27፤ 16፥33 ሰላማቸው የተጠበቀ እንዲሆን ነግሮአቸዋል።

ጌታ ራሱን ከገለጠ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የሆነላቸው አምስት ትልልቅ ነገር አለ።

- የኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በመካከላቸው መገኘት። ይመራቸው የነበረው መምህራቸው በአመፀኞች እጅ ስለ ተገደለና እነርሱም ስለ ሸሹ በዚያ ፍርሃት ውስጥ የነበሩ እንደ ገና ማየታቸው።
- ሰላም ለእናንተ ይሁን ማለቱ (20፥19፤ 21)። ለፈራ፣ ለደነገጠ ትክክለኛው መድኃኒት የኢየሱስ ሰላም ነው።
- ተልእኮ ይሰጣቸዋል። እልካችኋለሁ ይላቸዋል።
- ለተልእኮው የሚያስፈልጋቸውን ኃይል ይሰጣቸዋል። መንፈስ ቅዱስን እፍ በማለት።
- መልእክት ይሰጣቸዋል። ይቅር የማለት መልእክትን ይዘው እንዲሄዱ።

***20፥20 ይህንም ብሎ እጆቹንም ጎኑንም አሳያቸው። ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው።*** ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ[96] ያዩ መስሏቸው ፈርተው ነበረ (ሉቃ 24፥37)። እርሱ መንፈስ አለመሆኑን ***እጆቹንም ጎኑንም*** በማሳየት አረጋገጠላቸው። ጌታ ቀደም ሲል «ለጥቂት ጊዜ አታዩኝም ከዚያም ታዩኛላችሁ ታዝናላችሁ ነገር ግን ሃዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል» (16፥16፤20) ብሏቸው ነበር። ያ ለጥቂት ጊዜ ያዘኑበት ሁኔታ ጌታ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የሃዘን ጊዜ ነው። እርሱን ያላዩበት ጊዜ ነው። አሁንም ፍርሃታቸው ደጆች ዘግተው እንዲቀመጡ አድርጓቸዋል፤ ፍርሃት ውጧቸዋል። ከዚያም ደስ ይላችኋል ያላቸው ጊዜ ደረሰና አሁን ደቀ መዛሙርት ጌታን ሲያዩ ደስ እያላቸው ነው። ከዚህ በኋላ ደስታቸውን ማንም አይወስድባቸውም (16፥22)። ጌታ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷልና በክብር ሲያርግም ያዩታልና ደስተኞች ይሆናሉ።

***20፥21 ኢየሱስም ደግመኛ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው።*** ተልእኮ ከመስጠቱ በፊት ሰላማቸው በእርሱ የተጠበቀ እንዲሆን ለሁለተኛ ጊዜ ***ሰላም ለእናንተ ይሁን*** ይላቸዋል። የተረጋጋ መንፈስ እንዲኖራቸውና የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ በመንፈሳቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ነው። አብ ኢየሱስን ልኮት ነበር (17፥18)። ኢየሱስ ይህን ተልእኮ ለደቀ መዛሙርቱ ***እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ*** በማለት ያስተላልፋል። ደቀ መዛሙርት ራሳቸውን የላኩ ሰዎች አይደሉም፤ የተላኩ ናቸው። ለሚሄዱበትም የሚያስፈልጋቸውን ሰላም ጌታ ሰጥቷቸዋል።

[94] In his humanity
[95] In his divinity (deity)
[96] ghost

***20፥22 ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።"*** ደቀ መዛሙርቱ ይህን አገልግሎት ወይም ተልእኮ ለመፈጸም ከመጀመራቸው በፊት ኃይል መቀበል ነበረባቸው። ይህንም ኃይል ኢየሱስ እፍ በማለት ሰጣቸው። እዚህ ላይ እንደምናየው ጌታ እፍ ያለባቸው በደቀ መዛሙርቱ ላይ ብቻ ነበረ። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አንድ እንደምንመለከተው «ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ተቀመጡ» ብሎ አዟቸዋል። ይህ ተስፋ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርትና መቶ ሃያ በሚያህሉት ላይ በወረደበት ጊዜ ተፈጸመ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ከጭቃ ካበጀው በኋላ እፍ ሲልበት «ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ» (ዘፍ 2፥7)። ሰውን ከሌላው ፍጡር ልዩ የሚያደርገው የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር እፍ እስኪልበት ድረስ ሰው ሕይወት አልነበረውም። ሕይወትን የሰጠው የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አሰበት» (ዘፍ 2፥7) እንደሚል እፍ ያለበት ሕይወትን ነው። ከዚህም እስትንፋስ የተነሣ ሰው ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። በመጀመሪያው ነፋስ ለሰው ሕይወትን ሰጠው። ኢየሱስ በደቀ መዛሙርት ላይ እፍ ያሰባቸው ሁለተኛው ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያደርጉ ዘንድ ኃይልን ይሰጣቸዋል።

***20፥23 ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸውም ተይዞባቸዋል አላቸው።*** ይህ የተልእኮአቸው ክፍል ነው። ***አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ 20፡21*** እንዳለ አሁን የኃጢአትን ይቅርታ የማስገኘት አገልግሎትን ሰጥቶ ወደ ዓለም ይልካቸዋል። ለዚህም አገልግሎት መንፈስ ቅዱስን ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ ይህን አገልግሎት የሚፈጽሙት በራሳቸው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት ነው።

ኃጢአትን ይቅር ማለት የኃጢአት ይቅርታ መስጠት መለኮታዊ ሥራ በመሆኑ ማንም ሰው ከራሱ የኃጢአትን ይቅርታ ሊሰጥ አይችልም። በማር 2፥5-12 ባለው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሽባውን «አንተ ልጅ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ» ሲለው «ከጸፎች እንዳንዶቹ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ተባባሉ» (ቁ.7)። ጌታም «ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ» (ቁ.10 አላቸው)። ስለሆነም ኃጢአትን ይቅር ማለት መለኮት የሚያደርገው ሥራ ነው። ስለዚህ

---

[97] ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብዙ ጊዜ ተነግሯል (7፥37-39፤ 14፥16-20፤ 26፤ 15፥11 16፥7-15)።



ይህ በሰው ሥልጣን ውስጥ ያለ አይደለም። በእግዚአብሔር ላይ የተፈጸመ በደልን ይቅር ብሎ መሠረዝ የሚችል ራሱ እግዚአብሔር ነውና።

ኃጢአትን ይቅር ማለት ጽድቅን ከመስጠት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ማጽደቅና መኰነን የሚችለውም እግዚአብሔር ብቻ ነው (ሮሜ 8:33-34)። እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው በተቀበሉት ተልእኮ አማካይነትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚፈጽሙት አገልግሎት መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ወንጌልን ሲሰብኩና ይህንም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲያደርጉት በኢየሱስ የሚያምኑ ኃጢአታቸው ይሠረይላቸዋል። ያላመኑት ደግሞ እንደተያዘባቸው ይቀራል ማለት ነው።

***20፥24-25 ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ... የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው።*** ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ባገኘበት በመጀመሪያው ቀን ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር ቶማስ አብሮ አልነበረም (20፥19-23)። ኢየሱስ እንደሚነሣ ደቀ መዛሙርት የነበራቸው ጥያቄ ወይም ጥርጣሬ በቶማስ እንደበት ተነገረ እንጂ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ (ማቴ 28፥17)። በ14፥5 ላይ «የምትሄድበትን አናውቅም» ብሎ በብዙ ቁጥር ሲናገር ምናልባት የብዙዎቹን ለማሳወቅ በአርሱ እንደበት መግለጹ ሊሆን ይችላል። እንደ ቶማስ ዓይነት ሰዎች አብረዋቸው ያሉትንም ሀሳብ ቀድመው በመግለጽ ይታወቃሉ። ስለዚህ ቶማስ «ተጠራጣሪው» ቢባል እርሱ ቀድሞ ስለተናገረ እንጂ የተጠራጠሩ ሌሎችም ነበሩ።

በሌላ በኩል ግን ኢየሱስ አልዓዛርን ለማስነሣት ወደ ይሁዳ እንሂድ ሲል ቶማስ «እኛ ደግሞ አንድንሞት አብረነው እንሂድ» (11:16) ያለ ኢየሱስን ለመከተል የቆረጠ ሰው ነው።

***20:26 ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ።*** ጌታም ከተነሣ ስምንት ከሆነውም በኋላ ቢሆንም ደቀ መዛሙርት አሁንም በተዘጋ ደጅ ውስጥ ነበሩ። ይህን ያደረጉት ምናልባት የአይሁድ የተነሣሣ ቁጣ ገና ስላልበረደ ሊሆን ይችላል። ***20፥26 በዚህ ጊዜ ጌታ አሁንም በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለእናንተ ይሁን ይላቸዋል።*** አሁን ቶማስ በመካከላቸው ተገኝቶ ስለ ነበረ ጌታ ***ቶማስን፦ ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ የተጠራጠርህ አትሁን አለው 20፥27***። ቶማስ እንደ ተጠራጠረና እጁንም በጎኑ ለማስገባት

ጠይቆ እንደ ነበረ ለጌታ የነገረው ሰው የለም። ጌታ ግን በሰው ልብ ውስጥ ያለውን ሁልጊዜ ያውቃል (2:24-25)። ጌታም ቶማስን እምነቱ የጸናለት እንዲሆን ያደፋፍረዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው የትንሣኤ አካል የከበረ አካል ነው። አልዓዛር ከሞት ሲነሣ የተነሣው የቀደመውን፤ ተመልሶ የሚሞት ደካማ ሥጋውን ይዞ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣው በማይሞት በማይበሰብስ አካል ነው። የተወጋው ጎኑና የተቸነከሩት እጆቹ እነርሱ ከነምልክታቸው አሉ። ስለሆነም ቶማስን ***ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው*** አለው።

መጽሐፍ «የወጉትን ያዩታል» (ዘካ 12:10) እንደሚል የተወጋው ጎኑ ከትንሣኤም በኋላ ከእርሱ ጋር አለ። ይህ በነቢያት እንደተነገረ በወገኖቹ ዘንድ የቆሰለው ነው ((ዘካ 13:6)። ይህ ሁሉ በተጨማሪ የሚያመለክተው ከትንሣኤ በኋላ ኢየሱስ መንፈስ አለመሆኑን ነው። ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ የትንሣኤን አካል ወሰደ። የተቸነከሩት እጆቹና የተወጋውም ጎኑ ይታያል። ይህን ደቀ መዛሙርት አዩት፤ ይህ አካል አለ፤ ወደፊትም እኛ እናየዋለን።

***20፥28 ቶማስም፦ ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት።*** የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትነት በመግለጽና በማክበር ተናገረ።

***20፥29 ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው አለው።*** ጌታ እንዲህ ሲለው ቶማስን ማስተማሩም መገሰጹም ጭምር ነው።

***ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው*** የሚለው ከደቀ መዛሙርት በኋላ በእነርሱ ትምህርት የሚያምኑትን ሁሉ ያጠቃልላል። ባለንበት ዘመን «በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳምን እርሱ ራሱን ይግለጥልኝ ወይም ተአምር ያሳየኝ» እያሉ የሚናገሩ ሰዎች አሉ። ***ሳያዩ የሚያምኑ*** የሚለው ቃል ግን የሚያሳስበን የተባረክን የምንሆነው ሳናይ ብናምን መሆኑን ነው። ማረጋገጫ ለሚፈልግ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ቃሉ ምስክርና ማረጋገጫ ነው። እንዲሁም የቅዱሳን ምስክርነት፣ የተለወጡ ሰዎች የሕይወት ምስክርነት ሁሉ ማረጋገጫ ነው።

***20፥30 ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ።*** በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ያደረጋቸው ምልክቶች ስምንት ያህል እንደ ሆኑ ቀደም ብለን ተመልክተናል። እነዚህን ብቻ እንዳላደረገ ግን ይህ ቁጥር ይነግረናል። ከአራቱ ወንጌሎች ለመቁጠር እንደሚቻለው ጌታ ያደረጋቸው ምልክቶች ሰላሳ



አምስት ያህል ናቸው። ሆኖም ***በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ*** እንዳለ እነዚህ ብቻ ነበሩ ማለት አይደለም።

የምልክቶቹ ዓላማም የዓለም መድኃኒት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መመስከር ነበር። በምልክቶች በመገረም እዚያ ላይ ብቻ ማቆም የምልክቶቹን ዋና መልእክት መዘንጋት ነው። አቅጣጫን እንዲያመለክት በመንገድ ላይ እንደተተከለ ቀስት ምልክቶቹ ሁሉ የሚያመለክቱት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰዎች ምልክቶቹን አይተው ወደ ኢየሱስ በመሄድ በእርሱ እንዲያምኑ መንገድ የሚያሳዩ ናቸው።

***20፥31 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።*** ይህ ቃል የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበትን ዋና ዓላማ የሚያጠቃልል ነው። ይህ ወንጌል የተጻፈው ሰዎች በኢየሱስ በማመን የዘላለም ሕይወትን ያገኙ ዘንድ ነው።

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

በዚህ በዮሐንስ ወንጌል የመጨረሻው ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተነሳ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ እንደተገለጠላቸው እናያለን:: እንዲሁም ጌታ ከሁለት ሳምንት በፊት ክዶት የነበረውን ጴጥሮስን ሲያነጋግረውና ኃላፊነት ሲሰጠው እንመለከታለን::

***21፥1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ገና ተገለጠላቸው::*** የጥብርያዶስ ባሕር ለገሊላ ባሕር ሌላ መጠሪያ ነው:: ጌታ ከመሞቱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር ከትንሣኤ በኋላ በገሊላ እንደሚያገኛቸው ነግሯቸው ነበር (ማቴ 28፥10፤ ማር 14፥28):: ደቀ መዛሙርቱ ግን ባለማመናቸውና በመፍራታቸው ከኢየሩሳሌም ሳይወጡ ቆይተዋል:: አሁን የተገለጠላቸው ***በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ*** በመሆኑ ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሩሳሌም ወደ ገሊላ ሄደዋል ማለት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ በኢየሩሳሌም ተገለጠ፤ ከዚያ ደግሞ በገሊላ:: ወደ ሰማይ ያረገው ከኢየሩሳሌም ከደብረ ዘይት ተራራ ነው (ሐዋ 1፥12)::

ጌታ በኢየሩሳሌም ስድስት ጊዜ ያህል ተገልጧል፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ የተገለጠው በገሊላ ነው:: ከትንሣኤ በኋላ ጌታ የተገለጠላቸው ሰዎች፤ የተገለጠባቸው ሁኔታዎችና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው::

1. ለመግደላዊት ማርያም (ማር 16፥9-11፤ ዮሐ 20፥10-18)::
2. በመቃብሩ ለነበሩ ሴቶች (ማቴ 28፥8-10)::
3. ለጴጥሮስ በኢየሩሳሌም (ሉቃ 24፥34፤ 1ኛ ቆሮ 15፥5)::
4. በኤማሁስ መንገድ ለነበሩ ሁለት ሰዎች (ማር 16፥12-13፤ ሉቃ 24፥13-35)::
5. በተዘጋ ደጅ ውስጥ ለነበሩት ለደቀ መዛሙርቱ (ማር 16፥14፤ ሉቃ 24፥ 36-43፤ ዮሐ 20፥19-25)::
6. ቶማስን ጨምሮ ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት (ዮሐ 20፥26-31፤ 1ቆሮ 15፥5)::



7. በገሊላ ባሕር ዓሣ ያጠምዱ ለነበሩት ለባት ደቀ መዛሙርት (ዮሐ 21፥1-14)::
8. በገሊላ ተራራ ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት (ማቴ 28፥16-20፤ ማር 16፥15-18)::
9. ለአምስት መቶ ሰዎች (1ቆሮ 15፥6)::
10. ለኢየሱስ ወንድም ለያዕቆብ (1ቆሮ 15፥7)::
11. ጌታ ወደ ሰማይ ሲያርግ ይመለከቱ ለነበሩት (ማር 16፥19-20፤ ሉቃ 24፥44-49፤ ሐዋ 1፥3-13)::

***21፥2 ስምዖን ጴጥሮስና ዲዲሞስ የሚባለው ቶማስ ከገሊላ ቃና የሆነ ናትናኤልም የዘብዴዎስም ልጆች ከደቀ መዛሙርቱም ሌሎች ሁለት በአንድነት ነበሩ::*** እነዚህ ደቀ መዛመርት በቁጥር ሰባት መሆናቸው ነው:: የዘብዴዎስ ልጆች ዮሐንስና ያዕቆብ ናቸው:: እነዚህ ሰባቱ ***በአንድነት ነበሩ***:: ሌሎች አራቱስ የት ሄዱ? በአንድነት ያሉትስ ምን እየሠሩ ነው?

***21፥3 ስምዖን ጴጥሮስ፦ ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ አላቸው:: እነርሱም፦ እኛም ከአንተ ጋር እንመጣለን አሉት:: ወጥተውም ወደ ታንኳይቱ ገቡ በዚያችም ሌሊት ምንም አላጠመዱም::*** በሕይወታቸው እጅግ አስደናቂ ነገር ከተፈጸመና ካዩ ገና ሁለት ሳምንት ያህል ጊዜ ነው:: ለሦስት ዓመት ተከትለው የተከተሉት ጌታ እያዩት በካህናት አለቆችና አይሁድ ተይዞ ተሰቀለ:: እነርሱም ተበተኑ፤ ተደበቁም:: በኢየሩሳሌም ደጃ በተዘጋ ቤት ውስጥ በድብቅ ለመሰብሰብ ሞክረዋል:: አሁን ደግሞ ወደ ገሊላ መጥተዋል:: ከመካከላቸው አራቱ የት እንደ ሄዱ አልተገለጠም:: አንድ ላይ የተሰበሰቡት ሰባቱ ግን ገሊላ ከመጡ በኋላ ቀጥሎ ምን እንደሚያደርጉ ሳይቸገሩ አይቀሩም::

ስለዚህ የዚያ ቡድን መሪ ሆኖ የሚታየው ***ጴጥሮስ ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ*** ሲላቸው ሌሎቹም አብረውት ሊሄዱ ተነሡ:: ከመካከላቸው አብዛኞዎቹን ጌታ የጠራቸው ዓሣ ሲያጠምዱ ነበረ:: ሰባቱም ተጋግዘው ለማጥመድ ተሠማሩ፤ ይሁን እንጂ ሌሊቱን ሙሉ ደክመው ***ምንም አላጠመዱም***:: እነዚህ ደቀ መዛሙርት እንደ ገና መሰባሰብ፤ መጽናናት፤ መታደስ የሚያስፈልጋቸው ሆነዋል::

***21፥4 በነጋም ጊዜ ኢየሱስ በባሕር ዳር ቆመ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም::*** ገና እየነጋ ስለሆነና ኢየሱስም የቆመው እነርሱ ከነበሩበት ሁለት መቶ ክንድ ያህል ርቀት (21:8) ላይ ስለሆነ ደቀ መዛሙርቱ ያላወቁት በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ወይም

ኢየሱስ እነርሱ ወዳሉበት ቦታ ወደዚህ ይመጣል ብለው ስለማይጠብቁ ሲሆንም ይችላል:: ያለዚያም እንደ ኤማሁስ መንገደኞችና መግደላዊት ማርያም እነዚህም ለጊዜው ለይቶ ማወቅ ተስኗቸው ይሆናል:: ጌታ ደግሞ *ልጆች ሆይ፥ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው 21፥5::* እነርሱም *የለንም ብለው መለሱለት 21:5::*

*21፥6 እርሱም:- መረቡን በታንኳይቱ በስተቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ አላቸው:: ስለዚህ ጣሉት፤ በዚህም ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ ሊጐትቱት አቃታቸው::* ደቀ መዛሙርቱ ሌሊቱን ሁሉ ዓሣ ለማጥመድ ሞክረው ምንም አልያዙም:: ይህ በባሕር ዳር የቆመው ሰው *በስተቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ* ብሎ ሲያደፋፍራቸው ለእነርሱ ትልቅ ተስፋ ፈንጣቂ ቃል ነው:: *ስለዚህም ጣሉት በዚህም ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ ሊጎትቱት አቃታቸው 21:6::*

ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል በሉቃ 5፥1-11 ጴጥሮስና ሌሎች ደቀ መዛሙርት ዓሣ ሲያጠምዱ ምንም ያላገኙበትን ጊዜ ያሳስበናል:: በዚያ ሰዓት ኢየሱስ ወደ ጥልቁ እንዲሄዱ በነገራቸው መሠረት በመታዘዛቸው እንደ ቃሉ ድንቅ ሆነ:: ያን ጊዜ ጴጥሮስ በኢየሱስ እግር ሥር ወድቆ «እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ ከእኔ ራቅ» ብሎት ነበር (ሉቃ 5፥8):: ብዙ ዓሣ በማጥመዱ ጴጥሮስ ስለ ኃጢአተኝነቱ ይናገራል:: በዚህም ስለ ጌታ ሥልጣንና ቅድስና እንዲሁም ስለ ራሱ ማንነትም ጭምር ይገልጻል::

ኢየሱስ *በስተቀኝ ጣሉት 21:6* ሲል እርሱ ሁሉን እንደሚያውቅ ያሳያል:: እርሱ በባሕር ውስጥ ያለውን ያውቃል:: ምን? የት ቦታ? በምን ያህል መጠን? መቼ? የሚለት ሁሉ በፊቱ የተገለጡ ናቸው:: ዓሣ መኖሩን ብቻ ሳይሆን ዓሣዎች እንደሚጠመዱ ወደፊት የሚሆነውን ያውቃል::

*21፥7 ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን:- ጌታ እኮ ነው አለው::* በሉቃስ 5 ወደ ጥልቁ መረባችሁን ጣሉ ባለበት ጊዜ ዮሐንስ ከጴጥሮስ ጋር ነበረ:: አሁን ደግሞ ተመሳሳይ ተአምር ሲፈጸም ዮሐንስ ኢየሱስን ቶሎ እንደለየውና *ጌታ እኮ ነው* እንዳለ እናያለን:: ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ ያደረገው ደግሞ የሚያስደንቅ ነው::

*21፥7 ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበርና ልብሱን ታጥቆ ወደ ባሕር ራሱን ጣለ::* ጴጥሮስ በንግግርና በድርጊት ሌሎችን የሚቀድም፤ ፈጥኖ የሚጠይቅ፣ ፈጥኖ መልስ የሚሰጥ፤ ችኩልና ፈጣን ሰው ነው:: ያ ባሕርይው አሁንም በጉልህ



ይታያል:: ዓሣ ለማጥመድ ጀልባውን ይዞ የሄደው ጴጥሮስ ነው:: አሁን *ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ* የጴጥሮስ የመጀመሪያ እርምጃ ወደ ኢየሱስ መሮጥ ነው::

*ጴጥሮስ* ከጀልባ ወጥቶ በባሕር ላይ ለመንዝ ቀዳሚ ሰው ነበረ (ማቴ 14፥28-31):: በተራራውም ላይ ማደሪያዎች ለመሥራት ጥያቄ ያቀረበ ሰው እርሱ ነው (ማር 9፥5-6):: እግሩን እንዳያጥብ ኢየሱስን ለመከልከል የሞከረ እርሱ ነው (ዮሐ 13፥8-9):: ኢየሱስን ለማሰር በመጡት ላይ ሰይፍ ያነሣ እርሱ ነው (18፥10)፤ የካደም እርሱ ነው (18፥26-27):: አሁንም ከነበረበት ከታንኳ ወጥቶ በመዋኘት ወደ ኢየሱስ ፈጥኖ የሄደ ሰው ጴጥሮስ ነው:: በዚህ ሁሉ ጴጥሮስ ለኢየሱስ ያለውን ብርቱ ፍቅር ያሳያል::

ይልቁንም አሁን ኢየሱስን ከካደው በኋላ ገና በሁለት ሳምንት ያህል ጊዜ ውስጥ ከሌሎች ይልቅ እርሱ ታንኳው ወደ ምድር እስኪደርስ ሳይጠብቅ ወደ ኢየሱስ ፈጥኖ ለመድረስ መፈለጉ በውስጡ ያለውን ብርቱ ስሜት ይገልጻል:: ቀድሞ የሄደው ምናልባት ኢየሱስን ለብቻው አግኝቶ ይቅርታ ሊጠይቀው፤ የቀደመውን ኅብረት ለማደስ ፈልጐ ይሆን? ሳይሆን አይቀርም ግን አልተጻፈም::

*21፥8 ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ከምድር ሁለት መቶ ክንድ ያህል እንጂ እጅግ አልራቁም ነበርና ዓሣ የሞላውን መረብ እየሳቡ በጀልባ መጡ::* ከተያዘው ዓሣ ይበልጥ አሁን የሚያስቸኩለው ጉዳይ ስላገኘ ጴጥሮስ ጥሏቸው ቀድሞ መጥቷል:: ሌሎቹም በጀልባ መረቡን አመጡ::

*21፥9 ወደ ምድርም በወጡ ጊዜ ፍምና ዓሣ በላዩ ተቀምጦ እንጀራም አዩ::* በሚነድ እሳት ዙሪያ ጴጥሮስ ከጥቂት ቀናት በፊት የሆነውን ያውቃል:: አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ነህን? ብለው ስጠየቁት አይደለሁም ብሎ ደጋግሞ የካደው በእሳት ዙሪያ ቆመው ሲሞቁ ነበር:: አሁን እዚህኛው እሳት (ፍም) አጠገብ ያሉት ኢየሱስና ጴጥሮስ ብቻ ናቸው:: ምን ተባብለው ይሆን? ጴጥሮስስ ይህኛውን እሳት ሲያይ ኢየሱስንም ደግሞ አሁን በአጠገቡ ሲያየው ምን በውስጡ አስቦ ይሆን? ጌታ ያን የቀደመ ድካሙን አላነሣበትም፣ አልቀሰቀሰበትም:: ጴጥሮስ ያን ጊዜ ምርር ብሎ አልቅሶ ነበርና::

*21፥10-11 ኢየሱስም:- አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ አላቸው:: ስምዖን ጴጥሮስም ወደ ጀልባይቱ ገብቶ መቶ አምሳ ሦስት ታላላቅ ዓሦች ሞልቶ የነበረውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ይህንም ያህል*

***ብዙ ሲሆን መረቡ አልተቀደደም::*** ኢየሱስ በቀኝ በኩል ጣሉ ካላቸው በኋላ ከያዛችሁት ዓሣ አምጡ ይላቸዋል:: በጌታ ትእዛዝ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያስገርም ፍሬያማነት ታዬ:: ሌሊቱን ሙሉ ደክመዋል፣ ጌታ ከተናገረ በኋላ ብዙና ***ታላላቅ ዓሦች*** ተያዙ:: ትዕዛዙን ፈጥኖ የሚፈጽመው ጴጥሮስ ነው::

መረቡም ዓሣ ሞልቶ ነበር፤ ***ይህንም ያህል ብዙ ሲሆን መረቡ አልተቀደደም::*** በአንድ ጊዜ ብዙ ተአምር ሆነ:: የዓሦቹ ትልቅነት፣ የቁጥራቸው መብዛት፤ የመረቡ መሙላት፣ ከዓሣው ብዛትና ከትልቅነታቸው አንጻር መረቡ አለመቀደዱ የሚያስገርም ነው::

እነዚህ ደቀ መዛሙርት በጣም ብዙ ዓሣ ይዘው መረቡ ግን ቢቀደድ ምን ማለት ይሆናል? ዓሣስ አግኝተን ነበር፣ ልንጎትተው አልቻልንም ብለው መረቡ ከእጃቸው ቢያመልጥና ቢበተንስ? መጨረሻው ያላማረ ጥሩ ጅማሬ መሆኑ ነው:: እዚህ ላይ ልብ እንበል:: ኢየሱስ አንድ ትዕዛዝ ሲሰጥ በአፈጻጸሙ ላይ ለሚመጣው ችግር ሁሉ የተሟላ መልስና መፍትሔ በእርሱ ዘንድ አለው:: ጌታ የጀመረውን ሥራ በሙላት ወደ ፍጻሜ ያደርሳል:: በቅርብና በሩቅ ጊዜ በአፈጻጸሙ ሊመጡ በሚችሉ ችግሮች ሁሉ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ መፍትሔ አለው:: ስለሆነም የመረቡ አለመቀደድ የሚገልጸው የተአምሩን ዓይነት ብቻ ሳይሆን ተአምር ሠሪው ስለ ሁሉም ሁኔታ (ዙሪያ ገቡን) እንደሚጠነቀቅ ነው:: ጌታ ይህን ሲያደርግ ***ከደቀ መዛሙርቱ አንድ ስንኳ:- አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና 21÷12::***

***21÷13 ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንስቶ ሰጣቸው÷ እንዲሁም ዓሣውን::*** ከጌታ ጋር አራት ክበሉ ከሁለት ሳምንት በላይ ሆኗል:: አሁን ደግሞ ከሞት ከተነሣው ኢየሱስ ጋር ይበላሉ:: ይህ ልዩ ደስታን የሚሰጥ ጊዜ ነው:: ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር አብሮ እንደበላ ጴጥሮስ በሐዋ 10÷41 ላይ መስክሯል::

***21÷14 ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ ሦስተኛው ጊዜ ነበረ::*** ደቀ መዛሙርቱን ጌታ ሲጠራቸው ሰዎችን አጥማጆች እንደሚሆኑ (ሉቃ 5÷10) ነበረ:: አሁን ግን ዓሣ ወደ ማጥመድ ተመልሰዋል:: በዚህ ምዕራፍ ከቁ.15 ጀምሮ እንደምናየው ጌታ ለጴጥሮስ የአገልግሎት አደራ ይሰጠዋል::

***21÷15 ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን:- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ÷ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው::*** ይህ የዮና ልጅ ስምዖን የሚለው አጠራር



የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሲሆን ማለት መጀመሪያ ሲያገኘው የጠራበት ነበረ (ዮሐ 1÷43):: ስሙም ተቀይሮለት ኬፋ (1÷43) ተብሎ ነበር:: ጴጥሮስ በተቀየረለት ስም መሠረት አለት መሆኑ ገና አልታየም:: ***ከእነዚህ ይልቅ*** ለሚለው ቃል/ሐረግ የተለያየ ትርጉም ይሰጠዋል::

- አንደኛው:- ከእነዚህ ሰዎች የበለጠ ትወደኛለህን? ነው::
- ሁለተኛው:- እነዚህን ሰዎች ከምትወድበት ፍቅር በበለጠ እኔን ትወዳለህን? ሲሆን፤
- ሦስተኛው:- ከእነዚህ ነገሮች (ጀልባው፤ መረቡና ዓሣዎች) በላይ እኔን ትወደኛለህን የሚል ነው::

እነዚህ ሰዎች ከሚወዱኝ መጠን የበለጠ አንተ ትወደኛለህን? የሚለው የተሻለ ትርጉም ይሆናል:: ምክንያቱም ሌሎች ደቀ መዛሙርት እንኳ ቢክዱህ እኔ ግን አልክድህም ብሎ ነበርና (ማቴ 26÷33፤ ማር 14÷29፤ ዮሐ 13÷37):: በሁሉም ሁኔታ ጴጥሮስ ይወደው ከነበረው ሰውም ሆነ ነገር የበለጠ ኢየሱስን ይወድ እንደሆነ ነው የተጠየቀው::

ኢየሱስን ሦስት ጊዜ አላውቀውም ብሎ የካደውን ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ***ትወደኛለህን? 21:15፣16፣17*** ብሎ ደጋግሞ ይጠይቀዋል:: ጴጥሮስም እንደሚወደው ሲገልጽለት ***ግልገሎቼን አሰማራ 21:15፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ 21:16*** እና ***በጎቼን አሰማራ 21:17*** በማለት ኃላፊነት ይሰጠዋል:: እዚህ ላይ ጥቂት ነጥቦችን ልብ እንበል::

1. አደራ የሚቀበል ሰው ከበጎቹና ከግልገሎቹ በላይ አደራ የሰጠውን ኢየሱስን ሊወድ ይገባል:: ጌታ ስለ በጎቹ (በእርሱ ስለሚያምኑትና እርሱን ስለሚከተሉት ሰዎች) አደራ ሲሰጠው ሲል የሚጠይቀው በጎችን ይወድ እንደሆነ ሳይሆን ራሱን ኢየሱስን ይወደው እንደሆነ ነው:: በጎች ለመጠበቅ አስቀድሞ ጌታን መውደድ፤

2. ለጴጥሮስ የሚሰጠው ግልገሎችን፤ ጠቦቶችን፤ በጎችን ሳይሆን ***ግልገሎቼን፣ ጠቦቶቼን*** እና ***በጎቼን*** ነው:: አስተዋይ ሰው እገናዛቢ የሆነችውን (ባለቤትነትን የምታመለክተውን) ***ቼን*** ልብ ይላል::

3. ኢየሱስ ለጴጥሮስ ያስተላለፈው አገልግሎቱን እንጂ ባለቤትነትን አይደለም:: ጴጥሮስ ከጌታ የተቀበለው አገልግሎትን (አደራን) ብቻ ነው:: ግልገሎቹ፣ ጠቦቶቹ፣ በጎቹ የጴጥሮስ እንዲሆኑ አልተሰጠውም፤ የኢየሱስ እንደሆኑ ለዘላለም ይቀጥላሉ::

4. ኢየሱስ በመንጋው ውስጥ በተለያየ ደረጃ፣ አቅም፣ እድሜ ላሉ አባሎች ሁሉ ይጠነቀቃል:: እንዲሁ በአገልግሎት ላይ ያለም ሰው የሚጠነቀቀው በተወሰነ ደረጃ ላይ ላሉት ብቻ ሳይሆን ለመንጋው በሙሉ መሆን አለበት::

5. ኢየሱስ ለጴጥሮስ የሚሰጠው የማስማራትና የመጠበቅ ተግባርን ነው:: እነዚህ ሲከናወኑ በአንድ ላይ የመሪ ተግባሮች ይሆናሉ:: መሪነት የሚገለጠው ተግባሮችን በመፈጸምና በማገልገል ነውና::

***21፥17 ሦስተኛ:- ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና:- ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ!*** አለው:: ማዘኑ የቀደመውን ክህደቱን በማስብም ሲሆን ይችላል:: ***አንተ ሁሉን ታውቃለህ*** ማለቱም እንዲሁ ያን ጊዜ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ (ማቴ 26:75) ሲለው ጌታ ያለው እውነት መሆኑን ጴጥሮስ አረጋግጧልና ወደፊትም ስለ እኔ ሲሆን ያለውን ***አንተ ታውቃለህ*** ማለቱ ይሆናል:: ከዚህ ጊዜ በኋላ የጴጥሮስ የሕይወት አቅጣጫ ተለወጠ:: *ሥራውም* ዓሣ ከማጥመድ የኢየሱስ ምስክር ወደ መሆን ተለወጠ::

ኢየሱስ ጴጥሮስን ለመሪነት እየዘጋጀው ነው:: አስቀድሞ ግን በውስጡ ያለውን «ትምክህት» እንዲጥል ያስተምረዋል:: በራሱ የተማመነ ጴጥሮስ ወድቆ ታይቷልና በጌታ በመታመን ***አንተ*** ታውቃለህ ማለትን ይማርና ያስተውል ዘንድ ጌታ እያስተማረው ነው:: በእግዚአብሔር የበለጠ ይቷመን ዘንድ የራሱን ድካም ለይቶ መረዳት አለበት:: ያን ጊዜ በእግዚአብሔር ይመካል፤ ትሕትናን ይማራል::

***21፥18 አንተ ጕልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደ ምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፥ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል:: አለው::*** ከዚህ የጌታ ንግግር በፊቱ ምን እንደሚጠብቀው ጴጥሮስ ገብቶታል:: በሁለተኛ መልእክቱ ስለ ሞቱ ተናግሯል (2ጴጥ 1፥14):: ከታሪክ እንደሚታየው ጴጥሮስ የሞተው በኔሮ ዘመን በሮም ከተማ ተሰቅሎ ነበር:: በምሳሌያዊ አነጋገር ጌታ ***እጆችህን ትዘረጋለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል 21:18*** ያለው ጴጥሮስ የሚሞትበትን የሞት ዓይነት አመልካች ነበር:: ***በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ 21:19::***



ጌታን በሞት (በአሟሟት ዓይነት) ማክበር:: ለክርስቲያን መኖርም ሆነ መሞት ለእግዚአብሔር ክብር ነው::[98]

***21:19 ይህንም ብሎ:- ተከተለኝ አለው::*** ይህ ለጴጥሮስ በአንድ በኩል ጥሪውን ማደስ ነው፤ በሌላ በኩል ለቀሪው ዘመኑ ሊያደርግ የሚገባውን የሚገልጽለት መመሪያ ነው::

ከሦስት ዓመታት በፊት በዚሁ በገሊላ ባሕር አጠገብ ጌታ ጴጥሮስን አግኝቶ የተናገረው «ተከተለኝ» (ማቴ 4:18) የሚል ነበር:: አሁንም ***ተከተለኝ*** ይለዋል:: በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብዙ ሁኔታዎች አልፈዋል:: ጴጥሮስ ጌታን ሲከተለው ነበር፤ የካደበትም ጊዜ ነበረው:: አሁን እንደገና ***ተከተለኝ*** ሲለው የቀደመውን ጥሪ ማደስ በመሆኑ ለጴጥሮስ ትልቅ መጽናናትና ተስፋ የሚሰጥ ነው::

እንዲሁም ከሦስት ዓመት በፊት ጀምሮ «ተከተለኝ» የተባለው ጴጥሮስ አሁን ከሦስት ዓመታት ደቀ መዝሙርነትና ሥልጠና በኋላም ጌታ ጴጥሮስን የሚለው ***ተከተለኝ*** የሚል ነው:: ትናንትም ዛሬም መከተል፤ የማያቋርጥ የደቀ መዝሙርነት ሕይወት:: ይህን ***ተከተለኝ*** የሚለው ጥሪ እስከ ሽምግልናው ሲጠብቀው የሚገባ ጥሪ ነው:: መከተል የአንድ ቀን ወይም ወቅት አርምጃ ሳይሆን የሁልጊዜ ተግባር በመሆኑ በመከተል ቀጥል፤ አትቁም፤ አታመንታ እስከ ፍጻሜ ቀጥል ማለት ነው::

ጴጥሮስ የጌታን ግልገሎች፤ ጠቦቶችና በጎች እንዲጠብቅና እንዲያሰማራ አደራ ተሰጥቶታል:: የመጠበቂያውና የማሰማርያው ዋና መንገድ ኢየሱስን በመከተል ነው:: ጴጥሮስ የተሰጠው የአገልግሎት መመሪያ ጌታን የሚከተል መሪ እንዲሆን ነው:: ኢየሱስን ይከተላል፤ የኢየሱስን በጎች ያሰማራል፤ ይጠብቃል:: ኢየሱስን የሚከተል መሪ የአገልግሎት ትኩረት «የትልቁን መሪ» ፈለግ (ዱካ) ተከትሎ በመሄድ ወደ እርሱ ፈቃድ ማድረስ ነው (1ጴጥ 2:21)::

***ተከተለኝ*** ሲል እኔ የምሰጠህን አደራና ኃላፊነት በምፈልገው መንገድ ልትሠራ የምትችለው እኔን ስትከተል ብቻ ነው ማለትም ነው:: ጌታ ሥራው እንዲሠራለት የሚፈልገው እርሱ በሚፈልገው መንገድ እንጂ ሠራተኛው ወይም አገልጋዩ በሚሻው ሁኔታ አይደለም::

---

[98] Peter was crucified in Rome under Nero around AD 65-67. Ibid. p.408.

***21፥20-21 ጴጥሮስ ዘወር ብሎ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ፤ እርሱም ደግሞ በእራት ጊዜ በደረቱ ተጠግቶ፦ ጌታ ሆይ፥ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው? ያለው ነበረ። ጴጥሮስም ይህን አይቶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት ይሆናል? አለው።*** ጴጥሮስ አንተ በሽምግልናህ ትሞታለህ ስለተባለ ስለ ሌሎቹ በተለይም ***ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር*** (ስለ ዮሐንስ) መጨረሻ ማወቅ ፈልጓል። በተለይም ዮሐንስ ኢየሱስን ***ሲከተለው*** ስላየ «እሺ እኔ የምሞት ከሆነ» አንተ የምትወደው ዮሐንስስ ***እንዴት ይሆናል?*** ማለቱ ነው። ያው ሰው አይደል!

***21፥22 ኢየሱስም፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ አለው።***[99] ምን አግዶህ[100] የሚለው ስለ ዮሐንስ አንተ ምን ቸገረህ? ይህን ልትጠይቅ አይገባህም፤ ስለ እርሱ መንገድና አጨራረስ እኔ አውቃለሁ፤ አንተ ለራስህ የተሰጠህን የመከተል ጥሪና ሩጫ ፈጽም እንደ ማለት ነው።

ዮሐንስና ጴጥሮስ በብዙ መንገድ ተመሳሳይነት አላቸው። ጌታን ለመከተል የተጠሩበት ጊዜ ተመሳሳይ ነው። ብዙ ጊዜ ከጌታ ጋር ከነበሩት ሦስቱ ደቀ መዛሙርት መካከል ሁለቱ ዮሐንስና ጴጥሮስ ናቸው። በመጨረሻዋ ሌሊት ጌታ ወደ ገዥው ግቢ በወሰዱት ጊዜም እንኳ ሁለቱ አብረው ገብተው ነበረ። በትንሣኤ ማለዳ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቃብር የሄዱት አብረው ነበር። ጌታ ካረገም በኋላ በአገልግሎት አብረው የተለለፉ ሰዎች ናቸው። በኋላም መልእክቶችን የጻፉ፤ ምዕመናንን ያበረታቱ፣ ያጽናኑ፤ የደገፉ ታላላቅ የጌታ ሐዋርያት ናቸው። በአጠቃላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለደቀ መዝመርነት ክተጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ክጌታ ያልተለዩ፤ እርስ በርሳቸው ያልተለያዩና ተመሳሳይ አገልግሎት ያከናወኑ ናቸው።

ይህም ቢሆን ሁለት እኩል በአገልግሎት የተጠመዱ ሰዎች መንገዳቸውና ፍጻሜአቸው አንድና ተመሳሳይ ይሆናል ማለት አለመሆኑን እንገነዘባለን። የእያንዳንዱ ሰው ጥሪ ኢየሱስን መከተል ነው። መሪው ኢየሱስ ለእያንዳንዱ ሰው ያቀደለት መንገድ አለው። የመንገዱ ርዝመትና አጨራረሱ የሚወሰነው በጠሪውና በመሪው ነው። ስለሆነም ጴጥሮስ እንደጠየቀው ዓይነት «እኔን ትሞታለህ (ይገድሉሃል) ካልከኝ ለምትወደው ምን አዘጋጅተህለታል?» የሚል ስሜት የእግዚአብሔርን መለኮታዊ አሠራር መጠየቅ ይሆናል።

[99] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም «ኢየሱስም እስክመለስ ድረስ በሕይወት እንዲኖር ብፈልግ እንኳ አንተን ምን ቸገረህ? አንተ ራስህ ተከተለኝ አለው» ይላል።

[100] What is that to you?



እግዚአብሔር ደግሞ አይጠየቅም፤ አይመረመርም። ሁሉንም በሥልጣኑና እንደ ፈቃዱ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅነት አይጠየቅም። የወደደውን ያደርጋልና።

ዛሬም ቢሆን ተከተለኝ የሚለው የጌታ ጥሪ ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል፣ አገልጋይ፣ መሪ ለሁሉም የሚሆን ቃል ነው። ሁሉም ሰው የተጠራው ኢየሱስን እስከ ፍጻሜ እንዲከተል ነው። ስለዚህ በክርስቲያኖች መካከል ማወዳደር ወይም ማነጻጸር ፈጽሞ አያስፈልግም። ለዚህኛው ይኼን ሰጠው፤ ለዚያኛው ደግሞ ይኼን አደረገለት ብሎ በጌታ ላይ መናገር የእግዚአብሔርን አሠራር አለመረዳት ነው። በመሠረቱ እያንዳንዱ ሰው የተሰጠውና ያለው ነገር ሁሉ የሚገባው አይደለም። ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስለሆነና ከራሱ የሆነ ነገር ስለሌለ ያ ለዚያ ሰው እጅግ ብዙ ነው። ከዚህም አልፎ በተሰጠው ባይረካ ከሌላው ጋር ራሱን ማወዳደር ደግሞ ሌላ በደል ይሆናል። ሰጪው እንደወደደ እያከፋፈለ ይሰጣልና።

***21:22 ኢየሱስም፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ?*** ባለ ጊዜ ***ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚለው ይህ ነገር ወደ ወንድሞች ወጣ 20፥23***፡ ጌታ ያለውን በትክክል ሳይረዱ የራስን ፍቺ መስጠት ይህ ሳያጣሩ ማውራት ይባላል። ይህ ያልሆነ ወሬ ነው።[101] እነዚያ ***ወንድሞች*** «በመሰለኝ» ከማውራት እዚያው ላይ ጌታ ሆይ፥ አንተ እስክትመጣ አይሞትም ማለትህ ነውን? ብለው ቢጠይቁት የተሻለ በሆነ ነበር። ምክንያቱም፣ ***ኢየሱስ፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ? አለው እንጂ አይሞትም አላለውም 21፥23***፡[102] በቀደመውም ዘመን በወንድሞች ጌታ የተናገረውን በትክክል ያለመረዳት ችግር ነበረ ማለት ነው። በይመስላል ከመናገር ከምንጩ ንጹሑን መቅዳት ይሻላል።

***21፥24 ስለ እነዚህም የመሰከረ ይህንንም ጽፎ ያለ ይህ ደቀ መዝሙር ነው፥ ምስክሩም እውነት እንደሆነ እናውቃለን።*** ጸሐፊው ዮሐንስ የጌታ ደቀ መዝሙር የሆነ ያየውን የመሰከረና የጻፈ ሰው ነው። ስለዚህ ምስክሩ እውነት ነው (1ዮሐ 1፥1-3)።

[101] ይህ መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያስተምሩ፤ ለሚሰብኩ ሰዎችም ትምህርት ነው። መጽሐፉ (ክፍሉ) የሚለውን በሚገባ ሳያጠኑና በትክክል ሳይረዱ ያለሆነ ትርጉም መስጠት ውሸት እንደ መናገር፤ ያለሆነ ወሬም እንደማውራት ነው።

[102] Early Church History reports that after John spent several years at the exile on the island of Patmos (Rev 1:9), he returned to Ephesus where he died as an old man, near the end of the first century. <u>Ibid</u>. p.412.

***21፥25 ኢየሱስም ያደረገው ሌላ ብዙ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል።*** የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ በመጨረሻው የሚመሰክረው እርሱ የጻፈው እውነት እንደ ሆነ ሆኖም ይህ መጽሐፍ የጌታ የኢየሱስን ሕይወትና አገልግሎት በሙሉ የያዘ አለመሆኑን ነው። ምክንያቱም በወንጌሎች ከተጻፉት ምልክቶች ወይም ተአምራት እንኳ በዮሐንስ ወንጌል የምናገኘው ሰምንት ያህሉን ብቻ ነው። ከዚህ ሌላ ያልተጻፉ ብዙ ነገሮችን እንዳደረገ ዮሐንስ መስክሯል (20:30) እኛም አንባቢዎች ይህንን ማስብ አይከብደንም።

በመጨረሻም እንባቢ ሆይ:-

ይህን ማብራሪያ ለመጻፍ ስነሣ ስለ መጽሐፉ ከነበረኝ እውቀትና መረዳት አሁን ስጨርስ የተሻለ ግንዛቤ ያገኘሁ ይመስለኛል። አሁንም ግን በድጋሚ ለማሳሰብ የምፈልገው መጽሐፉ እጅግ ጥልቅ የሆነ ምስጢርና እውነት የያዘ በመሆኑ ሁሉ ነገር በበቂ ሁኔታ በዚህ ማብራሪያ ተገልጿል ብዬ አላስብም። ስለዚህ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲያበራልዎ እየጸለዩ በተደጋጋሚ መጽሐፉን እንዲያጠኑት ለማሳሰብ እወዳለሁ።

ይህን መጽሐፉ ለመጻፍ መፈለግን በውስጤ ላደረገና እፈጽመው ዘንድ ለረዳኝ ሕያው እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን። አሜን።

- ከድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ «የእግዚአብሔር ልጅ ነው» ማለት ምን ማለት ነው?
- ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛ መንገድ ማን (ምንድን) ነው?
- እውነተኛውስ አምላክ ማን ነው?
- የሥላሴን በሦስትነት-አንድነት እንዴት መረዳት ይቻላል?
- የዘላለም ሕይወት ማግኘት (ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት) የሚቻለው እንዴት ነው?

አንድ ሰው ዓላማና ትርጉም እንዲሁም ዋስትና ያለው ኑሮ ለመኖር ለእነዚህና ተመሳሳይ ለሆኑ ዋና የሰው ልጅ ጥያቄዎች በቂ መልስ ማግኘት አለበት:: መልሱ በጥቂት ገጾች አስደናቂ እውነቶችን በያዘው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይገኛል:: ይህ ማብራሪያም ይህን በግልጽ ሁኔታ ለመረዳት ያግዛል::

ወደ ዓለም የመጣው ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ የዲያብሎስን ሥልጣን በሞቱ በመሻር የጨለማውን «አቅም» ሰብሮአል:: ጨለማ አላሸነፈውም፤ መቃብር አልያዘውም፤ እርሱ ሕያው ነው:: ተመልሶ ላይሞት፤ ከሞት የተነሣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ማንም የለም::

ዋጋው 18:00 ብር

Printed by Andnet Printers